በሃይማኖት ካባ
የሚሠራ ደባ

ከዶ/ር ለይኩን ብርሃኑ

- መስከረም ፳፻ ዓ. ም.

© 2007 by Dr. Leykun Berhanu
® የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው
All Rights Reserved
አንደኛ ኅትመት መጫከረም ፳፻ ዓ. ም.
First Edition September 2007

ISBN NO. 0-9709903-3-2

መጽሐፉን ለማግኘት በሚከተለው
አድራሻ መጠየቅ ይቻላል።

Inquires can be sent to
lberhanu@cox.net

ማሳሰቢያ

አንባቢ ሆይ! በዚች አጭር ማስታወሻ የማቀርበው አቤቱታ በእውኑ ልመናና ምለላ እንጂ እንደ ነቀፋና ዘለፋ ፈጽሞ አይቆጠርብኝ። የአጸጻፌም ዓላማ ሰው ለማሳዘን ሳይሆን ለምሥክርነት የሥራ ድርሻዬን ለማበርከትና ለመወጣት ነው። ወገኑን የሚዘልፍ፥ ራሱ የተወረፈ መሆኑንም በሚገባ እረዳለሁ። ነገር ግን ራሴን ዝቅ አድርጌ በኢትዮጵያዊነት በእውነት ስለ እውነት በድጋሚ የምጠይቀው፥ ስለ እውነት ለመመስከር እንጂ ማንንም ለመጉዳትና ሊማበሳጨት ወይንም ለማሞገስና ለማወደስ የተሠነዘረ ኃሳብ ያለመሆኑንም በቅድሚያ አሁንም በአክብሮት እገልጻለሁ። እኔም ማንንም ወይንም ድርጅትን ወክዬም አይደለም የምመሰክረው። በራሴና በማንነቴ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ ለአገር ፍቅር፥ ለቤተ ክርስቲያን ክብር ብዬ ስሜቴ ተገፋፍቶ እንዳንድ ቃላት በኃይል የተወረወሩና የከረሩም ቢኖሩ የጎደለውን በመምላት፥ የተጣመመውን በማቅናት፥ ከይቅርታና ከሥርየት ጋር እንድትመለከቱልኝ እሁንም ደጋግሜ ደጋግሜ በአክብሮት እጠይቃለሁ።

ዋናው የመጽሐፉ ዓላማ ስለገጠሙን ችግሮች መፍትሔና አቤቱታ ለማቅረብና ለመሻት ያለንንም አመክሮ ለማካፈል ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለማንም ኢትዮጵያዊ ለቋንቋው ለባሕሉ ለትምህርቱ ለእምነቱ በጠቅላላው ለማንነቱ ሁሉ መታወቂያውና መገለጫው ናት። ይህ ግንዛቤ እንዲያገኝ በመጽሐፉ ጥረት ተደርጓል። በሃይማኖት ስምና ሰበብ ቤተ ክርስቲያናችንን በኅጢን መስረቁ እንደ ልምድ ተወሰደና ስለ ቀኖና ቤተ ክርስቲያኗ ጽርፈት ከዚያም እልፎ ተርፎ ዘለፋ ተጀምሯል። ይህም መቆምና መወገድ ያለበት ስለሆነ ይህን በሚያደርጉ የሃይማኖት ድርጅቶች ላይ ጠንከር ያለ መልእክትም ተካቶበታል። እንዲሁም ለብዙዓን አባቶች፥ ካህናት፥ ምዕመናንና ወጣቶችም ኃላፊነት መብትና ግዴታም ከዚሁ ጋር ተጠቃሏል። እንግዲህ «ማዬ በቀጠነ ቆሎዬ ባረረ ማሩኝ» የሥርዓተ ማኅበሩ አባባል እንደተጠበቀ ይሁንልኝ። በእስፈላጊው ሁሉ አውቄ በድፍረት፥ ሳላውቅ በስሕተት ለሠራሁት በደል ይቅርታችሁ ፈጽሞ አይለየኝ።

የሽፋኑ መግለጫ

፩ . የሰንደቅ ዓላማችን ዓርማ

ከሁሉ በፊት ለምን ይህን የጥንቱን የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የመጽሐፉ ሽፋን ለማድረግ እንደፈለግሁ ጥቂት ልበል። ይህ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማና አርማው የእግዚአብሔርንና የኢትዮጵያን ግንኙነትና አንድነት ብቻ ለማስረዳት መሆኑን ስለፈለግሁ ነው። እስካሁን ግንዛቤ አግኝቶ የቆየውና የነበረው ይህ የአንበሳ አርማ የንጉሣውያን ልዩ መለያ ሆኖ ብቻ ነበር የሚታወቀውና የተለመደው። ነገር ግን የምልክቱ ምሥጢር እንዲያ አይደለምም። በአጭር ቋንቋ አንበሳው እስከ ዘውዱና መስቀሉ የራሱ የባለቤቱ የኢየሱስ ክርስቶስ ምልክትና ሥዕል ነው። ከዚህ ሌላ አንዳችም ትርጉም የለውም። የኢትዮጵያንና የእግዚአብሔርን ጠባቂነትና አምላካዊነት አምና የተቀበለች ጥንታዊትና የአዳም መጀኛ ምድረ ኤዶም ኢትዮጵያ ናትና ነው። ይህ ምልክት የኢየሱስ የትንቢት ስሙና መገለጫው ብቻ ነው። ይህ ዓቢይ ጉዳይና ምሥጢር ምንነት በኢትዮጵያውያን ዘንድ በግልጽ እንዲታወቅ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ የመጽሐፉ መጎናጸፊያ ሆኗል። አንዲት ማስረጃ ላቅርብ።

«Ethiopia gave to the world the first idea of right and wrong and thus laid the basis of religion, and of all true culture and civilization. The ripe social and moral development of mankind in the Nile (Ghion) Valley is 3000 years older than of the Hebrews. Here the Jews received almost all of their early culture. Our moral heritage therefore drives from them and it has come to us rather THROUGH the Hebrews than FROM them.... Professor James Henry Breasted (an American "leading Egyptologist"), The Dawn of Conscience, New York, 1933."

ባጭሩ ከላይ የሠፈረው ቃል አባባል እንዲህ ነው። ታዋቂው ፕሮፌሰር ጄምስ ሄንሪ ብርስቴድ የግንዛቤ ንጋት በተሰኘው መጽሐፋቸው ኢትዮጵያ ለዓለም ለመጀመሪያ እውነትንና ሐሰትን ያሳወቀች አገር ናት ይህም ለሃይማኖት መሠረት ነው። ሥልጣኔን

ባሕልን ሥነ ምግባርን አዳብራና ይዛ የተገኘች አገር ናት ይህም የግዮን ሥልጣኔ በመባል ይታወቃል። የሚገርመው ግን ጥንታዊው ባሕል እምነት ሁሉ የፈለቀውና የተገኘው ከኢትዮጵያ ሆኖ ሳለ አይሁዶች ሁሉንም እምነትንና ባሕልን ከኢትዮጵያ ቀድተው ልክ ከእነሱ የተገኘ አድርገውና አስመስለው ለዓለም አቀባይና የመጀመሪያዎቹ እነሱ እንደሆኑ አድርገው ይናገራሉ። ኢትዮጵያውያን መሆናቸው ቀርቶ። አይሁዶች ምንም የራሳቸው የሆነ ነገር ከቶ የላቸውም በሙሉ ከኢትዮጵያ ነው የወሰዱት ሲሉ የኢትዮጵያን የሥልጣኔ የእምነትና የባሕል ሁሉ መጀመሪያ እንደሆነች በመጽሐፋቸው አረጋግጠዋል።

ስለዚህ ይህ ሰንደቅ ዓላማ ከዓርማው ጋር የመጽሐፉ ሽፋን ሆኖ የቀረበበት ዋና ምክንያት ስለምንነቱ ግንዛቤ እንዲኖር ይረዳል በማለት ሲሆን ስለማንነቱም አብዛኛው ወጣት እንደማያውቀው ለስተረዳሁ ለማስገንዘብም ነው። ይህም የሰንደቅ ዓላማ አርማ ታላቅ ምሥጢር ያለው በመሆኑ የኢትዮጵያ መለያና መታወቂያ የማንነታችንም መግለጫ ሆኖ ኖሯል ቆይቷልም። ነገር ግን ከጊዜም ብዛት ከሥርዓቱም ዓይነት ይመስላል የንጉሣውያን መለያና መታወቂያ መስሎ ታውቆበታል። ይሁን እንጂ መነሻ ኃሳቡም ሆነ እሠራሩ የሰሎሞንን ሥርወ መንግሥት መገለጫና መታወቂያ ተደርጎ ግንዛቤ ተወስዶበት ኖሯል። ነገር ግን አይደለም። ያለመሆኑንና ስለማንነቱም ስመግለጽ እነሆ! በድጋሚ ለማስገንዘብ የመጽሐፉ ሽፋን ሆኖ ቀርቧል። ቀደም ሲልም ላሳተምሁት መጽሐፍ ተመሳሳይ ሽፋን ነበረው። ያንንም በሽፋኑ ብቻ ስለ ነገሥታት በተለይም ስለ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሚናገር መስሏቸዋል። ይሁንና ከዚህ ውጭ ነው። እንዲያውም በምንም ዓይነት መልኩ የፖለቲካ ንክኪ ፈጽሞ የለውም። ይህ ግልጽ እንዲሆንና ግንዛቤ እንዲወሰድ በቅድሚያ አሳስባለሁ።

የሰንደቅ ዓላማችን ዓርማ፥ የማንነታችን ግርማ ነው። በሰንደቅ ዓላማችን ላይ የነበረው ዓርማ <u>ባለ ዘውድና ባለ መስቀል</u> አንበሳ ማንኛቸውንም ምድራዊ ነገሥታት ፈጽሞ አይወክልም። የሚወክለው ኢትዮጵያንና መሢህ ኢየሱስን ብቻ ነው። «አንበሳ ወጽአ እምገዳም ውእቱኬ ወልደ አምላክ ውእቱ።» [እነሆ አንበሳው ከዱር ወጣ አሱም ወልደ አምላክ ኢየሱስ ራሱ ነው] ተብሏልና! እሱም አንበሳው ኃይሉን፥ ዘውዱ ምድራዊ ዙፋኑንና መስቀሉ ደግሞ አዳኝነቱንና ማንነቱን «ቃል ሥጋ ኮነ።» [ዮሐ. 1:14] አምላክ ሰው ሆነ። «ተሰብአ ወተሠገወ እመንፈስ ቅዱስ» በመንፈስ ቅዱስ ፈጽሞ ሰው ሆነ የሚለውን ነው። ይህም በትንቢት ለኢትዮጵያውያን የተሠጠ እውነተኛ ልዩ ፀጋ ነው። «ሞፀ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ»

[እነሆ! ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ ድል ነሥቷል።] [ዮሐ.ራእይ.፭፡፭] የሚለውን ቃል ለሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት መለያና መታወቂያ እንደሆነ ብቻ ተደርጎ በስሕተትና በዘልማድ ግንዛቤ ተወስዶበት ኖሯል።

እንደሚታወቀው ወላጆቻችን ትንቢትን የመቀበልና የመተርጎም ስጦታ ያላቸውና የነበራቸው በመሆኑ ሁሉንም በትክክል በመገንዘብ በሥራ ላይ እንዲውል አድርገውት እናገኘዋለን። ይህን በሰንደቅ ዓላማችን ላይ የነበረውን ዓርማ የወሰዱትና ያገኙት ስለ መሢሁ ኢየሱስ መምጣት መውረድና መወለድ የተገነዘቡ በመሆናቸው ከአገራችን ሰንደቅ ዓላማ ላይ እንዲታይና እንዲኖር አደረጉ። ይህን ዓርማ ስንመለከት መገንዘብና መረዳት የሚገባን የእሱ የራሱ የኢየሱስ አምሳል ምልክትና ሥዕል መሆኑን ነው። ይህንኑም በማድረግ ሰንደቅ ዓላማችንን እናከብረዋለን እኛም እንከበርበታለን። ይህም ሌላው ጽላታችን በተለመደው አነጋገር ሌላው ታቦታችን ማለት ነው። ወይንም በሌላ አገላለጽ የእግዚአብሔር መገለጫ ነው። በጠላት ዕጅ እንዳንወድቅም እንጠበቅበታለን። ታላቁ ምሥጢርም ከዚህ ላይ ነው። ከዚህ ውጭ ሌላ ትርጉም ፈጽሞ የለውም። ኢትዮጵያ ከእግዚአብሔር ጋር ያላት ግንኙነት መገለጫውና መታወቂያው እጅግ ብዙ ነው። ነገር ግን በረጋ መንፈስ መመልከትንና ማስተዋልን ይጠይቃል።

እንዲሁ በአጭሩ ስመቃኘት ያህል «ኢትዮጵያ ታበጽሕ ዕደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» [ኢትዮጵያ ዕጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች መዝ. 68:36] ቀጥሎም በሌላም በኩል «ወወህብከሙ ሲሳዮሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ» [አንተ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ ሰዎችም ምግባቸውን ሠጣሃቸው።] መዝ. 73:14፤ ለኢትዮጵያውያን ምግባቸውን ሰጥሃቸው ሲል በዓለም ውስጥ ካሉት አዝርዕትና አትክልት ሁሉ ልዩ የሆነውን እጅግ በጣም ደቃቅና የትም ዓለም የማይገኘውን የጤፍን እህል ምግብ ይሆናቸው ዘንድ ሰጣቸው ብለው ይተረጉሙታል። በሌላ በኩል ደግሞ «ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ፥ ነገሥተ ተርሴስ ወደሰያት አምሃ ያበውኡ» መዝ.71:9-10 [የተርሴስና የዳሕላቅ ደሴቶች ማለት የኢትዮጵያ ነገሥታት ዕጅ መንሻ ያቀርቡለታል። እኒህም ሰብአ ሠገል ናቸው። የሳባና የዐረብ ነገሥታት ዕጅ መንሻ ያመጡለታል። አንድም ለጌታ ባዜን ንጉሠ ኢትዮጵያ ይገብርለታል። «ወአመ፲ወ፮ ዓመተ መንግሥቱ ለባዜን ንጉሠ ኢትዮጵያ ተወልደ እግዚእነ ኢየሱስ» [ባዜን በኢትዮጵያ በነገሠ በአሥራ ስምንት ዓመቱ ጌታ ኢየሱስ ተወለደ እንዲል፤] [መዝሙረ ዳዊት አንድምታው 71:9-10] ይህንኑም ቃል ኢሳይያስ

በትንቢቱ እንዲህ ብሎታል። «በዚያን ዘመን ለሠራዊት ጌታ ለእግዚአብሔር ከረጅምና ከለስላሳ ሕዝብ ከመጀመሪያው አስደንጋጭ ከሆነ ወገን ከሚሰፍርና ከሚረግጥ ወንዞችም ምድራቸውን ከሚከፍሉት ሕዝብ ዘንድ ፥ ዕጅ መንሻ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር ስም ወደሚገኝበት ለፍራ ወደ ጽዮን ተራራ ይቀርባል።» [ኢሳ. 18:7]

«የእሥራኤል ልጆች ሆይ እናንተ ለእኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን?» [አሞጽ 9:7] ከዚህም ባሻገር ኢትዮጵያ የታቦተ ጽዮን መኖሪያ፥ የመስቀሉ ክፍል ግሽን ላይ መቀመጫ፥ ሉቃስ የሣላቸው የቅድስት ድንግል ማርያም ሥዕሎች ከተለያዩ በታዎች ላይ መገኘት እኒህ ሁሉ የሚያመለክቱት ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር ዙፋን መዘርጊያና የንዋየ ቅድሳቱ ግምጃቤት መሆኗን ነው። የምትጠበቀውም በሱ ብቻ ነው። ስለዚህም ሀገረ እግዚአብሔር የሚል መጠሪያ አግኝታበታለች።

ስለዚህም «ኢይጠፍእ ምልክና እምይሁዳ ወምሥፍና እምአባሉ እስከ አመ ይረክብ ዘጽኑሕ ሎቱ ወውእቱ ተስፋሆሙ ለአሕዛብ።» [በትረ መንግሥት ከይሁዳ አይጠፋም። የገዥም ዘንግ ከእግሮቹ መካከል ገዥ የሆነው እስኪመጣ ድረስ የአሕዛብ መታዘዝም ለእርሱ ይሆናል።] [ዘፍ.49:10] ይህን ስለ መሢሁ ስለ ኢየሱስ የተነገረውን ትንቢት በመከተል ኢትዮጵያ በሰንደቅ ዓላማዋ ላይ ዘውድና መስቀል የያዘ አንበሳ እሱም ማለት የኢየሱስን ሥዕል መለያ፥ መታወቂያና ዓርማዋ አድርጋ ስትገለገልበት ኖራለች። ይህም ማለት የሰሎሞናዊው ሥርወ መንግሥት ልዩ መለያና መታወቂያ ነው ብላ አልነበረም። ነገር ግን ወላጆቻችን የምሥጢሩ ባለቤቶች ስለነበሩ ጉዳዩን አያይዘው በሰምና ወርቅ ምሳሌ ሰሙን ለዘውዱ መገለጫ፥ ወርቁን ደግሞ ለራሱ ለኢየሱስ ምሳሌ አድርገው ሲገለገሉበት ኖሩ እንጂ!

ታዲያ ስለሞናዊው ሥርወ መንግሥት በሌላ ሲተካ የአንበሳውንም ዓርማ ባለማለታዋልና ባለመገንዘብ ተልጦ ተነሣ። ይህም ብቻ አይደለም እንዲያውም «ሣሌ ሉያ» እግዚአብሔር የነበረና ያለ ወደፊትም የሚኖር የሚለውን የኢትዮጵያን መሠረታዊ የእምነት ቃልም «የሌለና ያልነበረ ወደፊትም የማይኖር» በሚል በሩሳውያን የመናፍቃን ቋንቋ ተተክቶ ነበር። ይህም የክህደት ትምህርት የሥርዓተ መንግሥቱ ብሔራዊ እምነት ሆኖ እርስ በርስ አፈጻጀን። ምድርም በደም ጠገበች። የሬሳዎች ማከማቻም ነበረች።

ነገር ግን እንዲያ ባዮቹ ኮሚኒስቶቹ የእሱም ሥርዓት ተቀባዮችና አራማጆቹ እንደ ጉም በነው እንደ ጢስ ተነው ሲነሡ፥ እግዚአብሔር ግን በኢትዮጵያ ላይ እነሆ አለ ይኖራልም ይመለካልም።

ነገር ግን ያም አልፎ ሌላው ሲመጣም የአንበሳው ዓርማ ወደ ሰንደቁ አልተመለሰም። ይሁን እንጂ ዳግም ምጽአቱ ተመልሶ መምጣቱ እንደ መጽሐፉ አባባል አይቀሬ ይሆናል። «ዳግመ ይመጽእ በስብሐት። ይኩንን ሕያዋነ ወሙታነ ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ።» [ዳግመኛም በምስጋና ተመልሶ ይመጣል። በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ ለመንግሥቱም ፍፃሜ የለውም።] [ጸሎተ ሃይማኖት የዘወትር ጸሎት ገጽ 5] ስለሆነም ኢትዮጵያንና አምላኳን መለየት ወይንም መነጣጠል ከቶ አይቻልም። የሆኑትም ለተወሰኑ ወራት ብቻ ነበር። ይህንም በተግባር የተመለከትነው ነው። ይሁን እንጂ የመሢሁ የኢየሱስን ዓርማና ምስል የያዘው ሰንደቅ እስካሁን አልተመለሰም። ነገር ግን በዬአብያተ ክርስቲያናቱ፥ በግምጃቤቶችና በአብያተ መዘክሮቻችን ውስጥ ይገኛል። ይሁን እንጂ «ዳግመ ይመጽእ በስብሐት» ማለት ተመልሶም በክብርና በዕልልታ ይመጣል እንደተጠበቀ ነው። በእሱ ፋንታ ግን እንደተወራራሾች ምኞትና አስተሳሰብ ሰንደቅ ዓላማው በተለያዩ ዓርማዎች ተተክቶ ይታያል። እኒህም በኢየሱስ ምስል ፋንታ በየጊዜው በሰንደቅ ዓላማው ላይ የተጣፉት ምልክቶች ከኢትዮጵያ ጋር ምንም ዓይነት የሥጋም ሆነ የመንፈስ የዝምድና ትስስር ጨርሶ የላቸውም። ስለሆነም ይህም ድርጊት ሊቆይ የሚችለው የእውነተኛውና የታሪካዊው ዓርማ ማንነትና ትክክለኛነት ግንዛቤ በኢትዮጵያውያን ዘንድ እስከሚፈረጥም ድረስ ብቻ ነው።

ሌላው ቀርቶ የሚገርመው ነገር ቢኖር የአንበሳ አደን የተያዘ ይመስል በየሀውልቱ ላይ የነበረውንና ያለውን አንበሳው የደፋውን ዘውድ ፈቅፍቆና ሰብሮ በመጣል ጊዜ ባከኗል ገንዘብም ፈሷል። ያውም ድንጋዩ ለተሸከመው ነገር ነው። ይህ አፈፃፀም ታሪክን መዋሸት መሆኑን ያለማሰተዋል ነው። «እውነትና ጢስ መውጫ አያጣም» የሚለውን የአበውን አባባል ያለማገናዘብ ነው። ከዚያም በላይ አፈፃፀሙ ታሪክን ከመዘንጋትም ባሻገር ብቻ ሳይሆን ማን አለብኝነት እንደሆነ ማወቁም የማይጸን ነው። በዚህም ሳቢያ ጠቃሚ ታሪካዊ ማስረጃዎች ያሉባቸውና የነበሩባቸው የሐውልት ቅርጾች፥ የግድግዳ ሥዕሎችና ፊልሞች እንደባከኑም የምንገነዘበው ነው። ይሁን እንጂ የምንመክረው ቅርሰ ይጠበቅ፥ ማንነታችንን እንድናውቅ

ይሆናል። ይህም የሁላችንም ኃላፊነት ነው። ወደ ዓርማው ምንነት እንሂድ።

፪ . የመስቀሉ ዓርማ

«አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል» [መስቀሌን በመስቀሌ ላይ አኑር/ አስቀምጥ] የዚዕን እጅግ በጣም የረቀቀ የአባባል ምሥጢር የምንረዳው በጥሬ ንባብ ብቻ ሳይሆን በትርጓሜና በምርምርም ነው። የመስቀል ዓርማ ምንድን ነው? ከሁሉ በፊት መስቀል ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት የነበረና ያለ ነው። ምሳሌነቱም የሰው ልጅ የምስል መልክ ነው። ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በፊት የኢትዮጵያውያን ነገሥታት መስቀል ዓርማቸው ወይንም በትረ መንግሥታቸው ነበር። ለዚሁም ማስረጃ የንዕዙ ፊደል አንዱ ተ የሰው ልጆች ዓርማ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህን በተመለከተ የአባ ተስፋ ሥላሴ ሞገስን ከተ እስከ ቶ የሠፈሩትን የመስቀል ቅርጾች ይመለከቷል።

ስለሆነም የተን ፊደል እስከ ሳብዑ ወይንም ሰባተኛው ፊደል ድረስ ስንቆጥረው ቶ ን ሳብኡን ወይንም ሰባተኛውን ፊደል እናገኛለን። ይህንን ነው ምዕራባውያን ሳይቀሩ ምንም መነሻና መድረሻ ቃል ሳይጨምሩ እንዳለ ስሙን በግዕዙ አጠራርና ሥያሜ «አንቅህ» [Ankh] ወይንም ሕይወት በመባል የሚያውቁት። ቶ ራስ ያለው ሰው ወይንም ሰብእ ይህ ቃልም ሰብአ ሰባት አደረገ ካለው የግዕዝ ቃል የወጣ ነው። ሰብእ ማለት ሰው ማለት ነው እሱም ከሰባት ነገሮች የተፈጠረ ስለሆነም ነው። እነሱም አራቱ ባሕርያተ ሥጋ ማለት መሬት ውሀ ነፋስና እሳት ሲሆኑ ሦስቱ ደግም ባሕርያተ ነፍስ ለባዊት ነባቢትና ሕያዊት ማለትም አሳቢት ተናጋሪትና ዘለዓለማዊት ሲሆኑ ድምራቸው ሰባት ወይንም ሰብእ ማለት ነው።] ከዚህም ባሻገር ኢየሱስ በመስቀል ላይ ነፍሱን ሲሠጥ «ወአጽነነ ርእሶ ወመጠወ ነፍሶ» [ራሱንም ዘንበል አድርጎ ነፍሱን ሠጠ።] ዮሐ. 19:31] ይህም በቀጥታ የሰባተኛው ወይንም ሳብኡ የቶ ፊደል የእንቅሕ [Ankh] ወይንም ሕይወት ተብሎ የሚታወቀው የሰው ልጅ ዓርማ ምልክት ምሳሌ ነው። ይህም ኢትዮጵያዊ ፊደል ቶ የሰው ልጅ ምሳሌና ኢየሱስም የሰውን ልጅ ያዳነበት የመስቀል ሥያሜና በተግባሩም የነገሥታት ዓርማ ሆኖ የኖረ ነው። በርግጥ በሮማውያን ዘመን ደግሞ የወንጀለኛ መቅጫ ወይንም የሰው መስቀያ ሆኖ ቆይቷል። በምርምር ብንመለከተው ሰውን በሰው መግደል ወይንም ማጥፋት እንደሆነ እንረዳለን።

ከዚህ ላይ ልብ ልንለው የሚገባው የግዕዝ ፊደላችን ቀዳሚ ፊደልና ምሥጢራዊ ቋንቋም መሆኑን በጥሞና ይገነዘቧል። በቀደሙ ዘመናት ደግሞ የኢትዮጵያ ነገሥታት በሄዱበትና በተቀመጡበት ቦታ ሁሉ በዕጃቸው ይይዙት ነበር። ይህም የበትረ መንግሥት ቀዳሚ ምሳሌ መሆኑ ነው። ይህ ሕይወት ወይንም እንቅህ እየተባለ የሚጠራው [ቶ] የመስቀል ምስል ደግሞ የአዳም ወይንም የሰው ልጅ ምሳሌ ነው። እሱም አንደኛውንና ሁለተኛውን አዳም ይወክላል። ዳግማይ አዳም እየተባለ የሚታወቀው ደግሞ መሢሁ ኢየሱስ ነው። በነገራችን ላይ መሢህ የሚወጣው ደግሞ ከኢትዮጵያ ብቻ እንደሆነም ተጽፏል። ታዲያ ኢየሱስ ኢትዮጵያዊ ነው? የሚለውን የምርምር ምልከት ከዚህ ይፈልጓል። [Professor Martin Bernal / ፕሮፌሰር ማርቲን በርናል Black Athena Vol. I 1987 ገጽ 431] ይህ ራሱን የቻለ የምርምርና የጥናት ዘርፍ ነው። ጊዜው ሲፈቅድ ይመጣበታል።

ስለሆነም በመጀመሪያው አዳም ላይ ሁለተኛው አዳምን አኑር ተብሎ በትንቢት የተነገረለት ኢየሱስ ነው። የቃሉም አባባል «አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል» የዚህን ምሥጢር ሰመመርመር የግዕዝ ፊደል ምሥጢሩን ይገልጥልናል። እንደሚታወቀው የግዕዝ ፊደል ከሀ እስከ ፐ ድረስ በመልክና በስም 26 በመለያ ቁጥር ግን 800 ነው። የዚህን ምሥጢር አስረስ የኔሰው ነገደ ካም በተሠኘው መጽሐፋቸው በሚገባ ተንትነው ያስረዳሉ። [ነገደ ካም 1951 ገጽ 10]

እንግዲህ ኢየሱስ ዳግማይ አዳም የተሠኘበትና መልእኩ ገብርኤልም እነሆ! ወንድ ልጅ ትወልዳለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ [ሉቃ.2:31-32] ብሎ ለድንግል ማርያም ሲነግራት ሁለተኛው አዳም መሆኑን ነበር ያረጋገጠላት። እንዴት አወቅነው? ብሎ ለሚጠይቅ ሰው መልሱ በራሱ በስሙ የፊደል ቁጥር እወቅነው ተረዳነው። እንዴት? ለሚል ደግሞ ማስረጃው እነሆ! እንደሚታወቀው ሃያ ስድስቱ ፊደሎች እያንዳንዳቸው የመታወቂያና የመለያ ቁጥር አላቸው ያልነውም ለዚህ ዓቢይ ጉዳይ መተርጎሚያ ስለሆኑም ነው። ያንድ ጦር ሠራዊት አባል የሚታወቀውና የሚጠራው ከስሙ ይልቅ በተሠጠው መታወቂያና መለያ ቁጥር ነው። ይህንም ጥበብ ከፊደሎቻችን ቀድተውታል ብንል የተመቸ ነው። በዚህ ብቻ አላበቃም በምዕራባውያን አገሮች እያንዳንዱ ዜጋ እንደተወለደ በተሠጠው ስም መሠረት የመለያና የመታወቂያ ቁጥር ይሠጠዋል። በሱም ከልደቱ እስከ ሞቱ የሚሠራውና የሚያደርገው ሁሉ ተመዝግቦና ታውቆ ይቀመጥበታል። ይህም የግል ማኅደር መሆኑ ነው። ታዲያ ባጠራሩ ሶሻል ሴኩሪቲ [የጋራ ደኅንነት] ብለን

እንተርጉመው። ይህንም ከግዕዝ ፊደሎቻችን ወስደውታል። በምዕራባውያን ከተሞች መንገዶቻቸው እንደኛ ስም መጠሪያና ቁጥር ተሠጧቸዋል። ይህም ማለት ስሙና አጎዙ ይዘት ትክክል ባይሆንም ማንኛውም ቃል የአጎዝ ንባብና ትርጉም ያለው መሆኑን እንረዳለን ይህንም ከኛ ያገኙት ነው። ኢትዮጵያውያን ለልጆቻቸው ስም ሲያወጡ በምሥጢር ባለ ስሙ የሚጠበቅበትን መልካም ስው የሚሆንበትንና አዋቂና ብልህም እንዲሆን ከጽንሰቱ እስከ ስሙ ስያሜ ድረስ በትርጉምም ከአባቱ ስም ጋር የተጣጣመ ትርጉም እንዲኖረው አደርገው የስሙን/አጎዞች ቁጥረው ተጨንቀው አውጥተው አውርደው ነበር የሚሠይሙት። ይህም የስሙ ትርጓሜ ወደ ማንነቱ ይመራል። በምሥጢሩ ግን የባለ ስሙ ደኅንነት የሚጠበቅበት ይሆናል። ስም እጅግ በጣም አድርጎ የተግባር ውጤት በተሠያሚው ላይ አሰው ያመጣልም። ለዚህም ነው «እስመ ስሙ ይመርሆ ጎበ ግብሩ።» [ስም የሥራ መግለጫ ነው] የሚባለው። ይህ በእንዲህ እንዳለ የፊደሎቻችን አቀማመር ባለ ቁጥር መሆን ብቻ ሳይሆን እጅግ በጣም ቁጥር ስፍር የሌላቸው ምሥጢራት ይቀዱባቸዋል። ከእነዚህም ውስጥ የትንቢት የራዕይና የሕልም መተርጎሚያነታቸው እሙን ነው። ይህን የትንቢት ትርጉም በሥራ ላይ ውሎ የምናገኘው በዓለም መድኃኒት በመሢሁ በኢየሱስ መውረድና መወለድ የተነገረው ትንቢት በፊደሎቻችን አጎዝ በትክክል ተተርጉሞ መገኘቱ ነው።

የፊደሎቻችንን አጎዞች ወደፊት በሚቀርብ ሠንጠረዥ ላይ የምንመለከተው ይሆናል። ይሁን እንጂ እንደ ማስረጃ በማድረግ ለማቅረብ የምሻው የራሱን የኢየሱስን ስምና የስሙን ፊደላት አጎዝ አቆጣጠር ነው። ከዚህ ላይ ኢየሱስ ከግነት የወጣውን የመጀመሪያውን አዳም ወደ ጥንተ ቦታው ለመመለስና ለመታረቅ ነውና አመጣጡ በአጠራር ዳግማዊ አዳም ወይንም ሁለተኛው አዳም በመባል ይታወቃል። ይህም ቃል ለኢየሱስ የትንቢት መገለጫውና መታወቂያው ስሙ ነው። ኢየሱስ ማለት በፊደሎቻችን አጎዞች መሠረት ዳግማዊ አዳም ማለት ነው። በኢየሱስና በአዳም ስሞች መካከል የንባብ ልዩነት እንጂ በትርጉምና በምሥጢር አንድ ናቸው። ይህም ማለት አዳም ማለት ኢየሱስ ማለትም ነው። ለዚህም ነው ትንቢት በሥራ ላይ ዋሰ ተፈፀመ በትክክል ተተረጎመ የምንለው። ይህም አባባል በብሉይ ኪዳን የተነገረው ትንቢት ሁሉ በሐዲስ ኪዳን ተፈጽሟል። አሁንም ልብ እንበል የኛ ፊደሎች እንዴት የምሥጢር መመርመሪያና የትንቢት መተርጎሚያ መሆናቸውን በጥሞና መገንዘብ ነው። አሁንም ኢየሱስ ሌላው መጠሪያ ስሙ ሁለተኛው አዳም ነው። በዚህ ስም ለመጠራቱና ለመታወቁ ደግሞ የመጻሕፍት ማስረጃዎቻችን ከብዙ በጥቂቱ እነሆ! «ወባሕቱ ኩነኖሙ ዳእሙ

ሞት እምአዳም እስከ ሙሴ ለእለሂ አበሱ ወለእለሂ ኢአበሱ በእንተ ይእቲ ኃጢዓቱ ለአዳም እስመ ኩሉ በአምሳለ አዳም ተፈጥረ እስመ አዳም አምሳሉ ውእቱ ለዘሀለዎ ይምጻእ።» [ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢዓትን ባልሠሩት ላይ እንኳ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ አዳም ይመጣ ዘንድ ላሰው ሰእርሱ አምሳሉ ነውና።] [ሮሜ 5:14 ፤ ቀጥሎም «እስመ በአሐዱ ብእሲ ኮነ ሞት ወበካልኡ ብእሲ ኮነ ትንሣዔ እምውታን። ወበከመ በአሐዱ አዳም ኩልነ ንመውት ከማሁ በክርስቶስ ኩልነ ነሐዩ።» [ሞት በሰው በኩል ስለ መጣ ትንሣዔ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና። ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና። ፩ ቆር. 15:22]

እንዲሁም «ተፈሥሒ ኦ ቤተልሔም ሀገሮመ ሰነቢያት እስመ በኀቤኪ ተወልደ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዳግማይ አዳም ከመ ያግብኦ ለአዳም ቀዳሚ ብእሲ እምድር ውስተ ገነት ...» [ቤተልሔም ሆይ ደስ ይበልሽ ሁለተኛው አዳም፡ ኢየሱስ የቀደመውን ሰው አዳምን ወደ ገነት ይመልሰው ዘንድ ካንች ዘንድ ተወልዷልና!] [ውዳሴ ዘሰኑይ] እንዲሁም ተጨማሪ ማስረጃ «ተፈሥሒ ኦገነት ነባቢት ማኅደሩ ለኢየሱስ ክርስቶስ ዘኮነ ዳግማይ አዳም በእንተ አዳም ቀዳሚ ብእሲ፤» [ነውር ጉድፍ የሌለብሽ ፍጽምት ሆይ ደስ ይበልሽ። ስለቀደመ ሰው አዳም ሁለተኛ አዳም የሆነ የኢየሱስ ክርስቶስ ማደሪያው የሆንሽ ሆይ ደስ ይበልሽ።] [ውዳሴ ማርያም ዘረቡዕ] ከዚህ በኋላ የዚህን የቀደመው አዳምንና ሁለተኛውን ወይንም ዳግማዊ አዳምን ወይንም ኢየሱስን የስሙን አሠያየምና የአባባል ምሥጢር ትርጉም ከኢትዮጵያ ፊደሎቻችን ዘንድ እንፈልገው። አዳም የሚለውን ስም የፊደል አጎዝና ኢየሱስ የሚለውን ቁጥረን ስንደምረው የምናገኘው ድምር 144 ነው። የግዕዝ ፊደላት ምን ያህል ምሥጢራዊ መሆናቸውን እንረዳለን። ራሳችሁ ደምራችሁ ድረሱበት። የፊደሎቻችን ስምና አጎዝ ከዚህ በታች በልዩ ሠንጠረዥ ቀርቧል።

እንግዲህ ምን እንላለን? ዕፁብ ድንቅ እንጂ! እኛ ኢትዮጵያውያን እናስብ ወደማንነታችን እንመለስ። ያለንን ታላቅ ሀብት የትም አንበትነው። ከዚህ ላይ አቤቱታውና ልመናው ጥንታዊውና የሰው ልጅ አፍ መፍቻ የሆነው ይህ ምሥጢራዊው የግዕዝ ቋንቋችን ወደ መማሪያነቱ ወደ ት/ቤቱ ክፍል ይግባ። የሰው ያለህ ያገር ያለህ ግዕዝ የመንፈሳዊ ሕይወት ቁልፍ ብቻ አይደለም። የዓለሙ ጥበብ ሁሉ መቅኛ እንጂ! ይህን ከላይ የተጠቀሰውን አጎዝ ማለት የ144 የድምር ውጤትና ምንነት በራዕየ ዮሐንስ እንዲህ ሲል

እናገኘዋለን። «ወእምዝ ቆመ ዝክቱ በግዕ ሳዕለ ደብረ ጽዮን ወምስሌሁ ፲ወ፬፻ወ፸፪ እለ ጽሑፍ ውስተ ፍጽሞሙ ስሙ ወለመ አቡሁ ወለመ ቅዱስ መንፈሱ።» [በጉ በጽዮን ተራራ ቆሞ ነበር ከእርሱም ጋር ስሙና የአባቱ ስም የመንፈስ ቅዱስም በግምባራቸው የተጻፈላቸው መቶ አርባ አራት ነበሩ።] [ራዕይ.14:1] ምሥጢሩንም በሚገባ ልብ ይሏል። ፈደሎቻችንን እዘበራርቆ መጻፉ ምን ያህል ታሳቅ ስሕተት መሆኑን ከዚህ መረዳት እንችላለን። ይህን ትርጉም ከግዕዝ ሌላ ማን ይናገረዋል? ማንነታችንን እየጣልነው ነው። የምንለውም ለዚህ ነው። ጥንቃቄ ሊደረግለት ይገባል።

ያንዲት ሳንቲም መጉደል አንድ ብር እንደማያሰኘው ሁሉ የኛም ማንነት ካንዲት አንጓ ፊደል መጉደልና መዛባት ትልቁን ዓቢይ ጉዳይ ያሳስተዋል። ማስታወስ የሚገባን የውሀ ጠብታ ድንጋይን እንደሚፈረክስ ሁሉ ትንሿም ለሕተት ኢትዮጵያዊነታችንን ታሪካችንንና ማንነታችንን እንደምታጠፋው መገንዘብ ይገባናል። እኛ እኮ ለዓለም ሕዝብ ምሥክሮች ነን። ይህን መሳይ ፊደል ጥለን የአውሮጳ ውራጅ እንለብሳለን። ያውም የሙት ልብስ። እኛ የኤቢሲዲ ምሁራን ልብ እንበል። እንመርምር እውነቱን እንሻ ማንነታችንን እንወርውረው። አከብረን እንያዘው። ለልጆቻችን ቅርስ እናኑርላቸው። ራቁታቸውን አናስቀራቸው። አንድ ቀን ወደ እውነቱ ሲመጡ ይረግሙናል። የማንነታችንን ብኩርና በደረቅ ዳቦ አንሸጠው። አዎ ዘመኑ ወርቅ የረከሰበት መዳብ የነገሠበት ጊዜ ነው። ግን እስከ መቼ??? የማያልፍ ነገር ከቶ የለም። «ዓለሙኒ ኃላፊ ንብረቱኒ ኃላፊ እለመ ኩሉ ኃላፊ ውእቱ።» [ንብረቱም ዓለሙም ሁሉም ያልፋል።]

፫. የዘውዱ ትርጉም

ዘውድ የንግሥና ዓርማ ነው። «ኢይወጽእ ምሥፍና እምአባሉ ለይሁዳ።» [ንግሥና ከይሁዳ ዘር አይወጣም] ይላል። አሁንም ትንቢቱ ወይንም አባባሉ የተነገረው ስለ ኢየሱስ መውረድ መወለድና ዳግም መምጣት ነው። ለዚህም አንበሳው ራሱ ኢየሱስ መስቀልና ዘውድ በራሱ ደፍቶ ታያቷል ይህም የምሥጢሩ ትርጓሜ ነው። እንግዲህ ዘውድ የደፋና መስቀል የያዘ አንበሳ በሰንደቅ ዓላማው ላይ ማረፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ የእግዚአብሔር ልጅነትና የአምላክነቱን መግለጫ መለያና መታወቂያ ማድረግ ነው። ኢትዮጵያ ሀገረ እግዚአብሔር ሕዝቡም ሕዝበ እግዚአብሔር ነው። የሚያሰኘውም አንዱ ምሥጢር ይህ ነው። ይህን የሚያረጋግጡ ብዙ ማስረጃዎች አሉን። ነቢየ እግዚአብሔር ሙሴ እሥራኤልን ከግብጽ ባርነት ነፃ ለማውጣት ከመነሣቱ በፊት ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ ኢትዮጵያዊቷን ሲጻራን አግብቶ ልጆች ወልዶ የኖረው ኢትዮጵያ ነው። [ዘፀ.3:21-22] የአመራር ሥልጠናም ያገኘው ከኢትዮጵያዊው አማቱ ከካህኑ ከዮቶር ነው። ዮቶርንም ካህን የሚለው ቃል የሚያሳየው ምሁርና የእግዚአብሔር አገልጋይነቱን ለመግለጽ ነው።

ታዲያ ኢትዮጵያ ነፃ ለሚያወጡት ሁሉ ማሠልጠኛና መምከሪያ ቦታነቷን ያረጋግጣል። ምዕራባውያን አፍሪቃን ሲቀራመቱ አፍረው የተመለሱት ኢትዮጵያን አንይዛለን ብለው በመነሣታቸው ነው። ከእነሱ ሠይጣናዊ ቅኝ አገዛዝም ኢትዮጵያ ራሷን አድና ሌሎችን የአፍሪቃ አገሮች ነፃ ለማውጣት ኢትዮጵያ ያልተሳተፈችበት አገር ከቶ የለም። የቅርብ ጊዜ ምሳሌ የሚሆኑት አገሮችም ኬንያ፥ ደቡብ አፍሪቃና ዝምባብዌ ዋቢ ተጠቃሽ ምሳሌዎች ናቸው። የግዛቤ ጉድለት እንጂ ኢትዮጵያ ቢጣሉ አስታርቃ ለተጠቁት አጋር ሆና ከራስዋ ድንበር ጥበቃ አልፋ ተርፋ ለሌሎችም ለትታደግ ነበር አሁንም ትታያለች። በየመን የነበሩትን ክርስቲያኖች በዘመነ ካሌብ ሄዳም ሪድታለች ታድጋለች። ይህን ሁሉ አስባስቦ መመልከቱ ኢትዮጵያና እግዚአብሔር የማይለያዩ ያንድ ሳንቲም ገጽታ መሆናቸውን ነው። ይህም ማለት ኢትዮጵያውያን ሲያጠፉ በቀጥታ እንደ ሕፃን ልጅ በእግዚአብሔር አለንጋ ይገረፋሉ። ከጥፋታቸው ታርመው ተፀፅተውና ተመልሰው ወደ እርሱ ይመጣሉ። በዚህ ሠላሳ ዓመት ውስጥ እንኳን የተፈፀሙትን ማስተዋሉ በቂ ነው። ዛሬ እግዚአብሔርን ለማመስገን «እሉ እሎንቱ እእባን ይኬልሑ» [እኒህ ድንጋዮች ይዘምራሉ።] [ሉቃ.19:41] እነሱ ዝም ቢሉ ድንጋዮች አፍ አውጥተው ያመሠግናሉ የተባለው ቃል አስተዋይ አእምሮ አጥቶ ነው እንጂ የዘመኑ ቪዲኦዎችና ቴፖች ወይንም የድምፅ መቅረጫዎች የድምፅ ማጉያዎች ሁሉ ከፍላቸው ከድንጋዮች ነው። ታዲያ እነሱ ዝማሬውን እያቀለጡት አያይደለምን? እኒህ የድምፅ መፍጠሪያ መሣሪያዎች ሁሉ የቃሉ ቀጥተኛ ትርጓሜዎች ናቸው።

ከዚያም ባሻገር ዛሬ በየቤተክርስቲያኑ የሚዘምሩት ወጣቶችም የቃሉ ትርጉም ናቸው። አስቀድሞ የተነገረላቸው መሆናቸው ነው። ቃሉም እነሆ! «እምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሎከ ለብሐተ...» [ምሥጋናን በሕፃናት አፍ አዘጋጀህ] [መዝ.8:2] ኢትዮጵያና እግዚአብሔር ያንድ ሳንቲም ገጽታዎች ናቸው ለማለት ያነሣሳን ለኢትዮጵያውያን አምላካቸው እግዚአብሔር ብቻ ነው። ለእግዚአብሔርም ልጆቹና ሕዝቡ ኢትዮጵያውያን ናቸው። የሁለቱ እንድነት የተሣሠረ ነው። ለዚህም ነው

«ወወሀብኩሙ ሲሣዮሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ» [አንተም ለኢትዮጵያ ሰዎች ምግባቸውን ሠጠሃቸው።] [መዝ.73:15] ተብሎ የተነገረላቸው። የዚህም ቃል ትርጉም ጤፍን ለምግባቸው ሠጣቸው ለማለት ነው ብለው አበው ተርጉመውታል። ቀደም ሲል እንደገለጽነው ምግብን ለልጆቹ የሚሠጥና የሚመግብ ደግሞ ወላጅ እንደሆነ እንረዳለን።

ኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር ዙፋንነት የተመረጠችው ቀደም ብሎ ነው። ለዚህም ነው ፣ታቦተ ጽዮንን በእክሱም ፥ የክርስትና እምነትን በራሷ ሰው ሐዋርያነት በባኮስ ወይንም በተለምዶ በሚታወቅበት የቅጽል ስሙ ጃንደረባው ሥዩመ ሕንደኬ ንግሥተ ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ፈቃድ መልአኩ ፊልጶስን ልኮ ተጠምቆ ማምጣቱ [የሐዋርያት ሥራ 8:26 - 39]፥ ከዚያም በፊት የኢትዮጵያ ነገሥታት በተለምዶ ግን የጥበብ ሰዎች ወይንም ሰብአ ሠገል በኮከብ እየተመሩ ሄደው የኢትዮጵያን ልዩ ምርቶች ማለት ወርቅ ለመንግሥቱ ዕጣን ለክህነቱና ከርቤ ለሞቱ ምሳሌ የሆኑትን ገፀ በረከቶቻቸውን ሠጥተው መጥተዋል። ይህም እንደሚፈፀም አስቀድሞ በኢሳይያስ ትንቢት ተነግሮላቸው ነበር። የትንቢቱም ቃል ቀጥሎ የሠፈረው ነው። «የግመሎች ብዛት የምድያምና የጌፌር ግመሎች ይሸፍኑሻል ሁሉ ከሳባ ይመጣሉ ወርቅንና ዕጣንን ያመጣሉ የእግዚአብሔርንም ምስጋና ያወራሉ።» [ኢሳ. 60:6] ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ኢትዮጵያውያን ትንቢትን በቋንቋቸው በግዕዙ ስለሚተረጉሙ ነው። ይህ ብቻም አይደለም። በየዓመቱ ወደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የሚሄዱት ኢትዮጵያውያን በዕለተ ጰንጠቆስጤ ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተመልተው የአካባቢውን ቋንቋ ሲናገሩ ከተናገሩባቸውና ከሰሟቸው ቋንቋዎች ውስጥ የሰው ልጅ አፍ መፍቻ የሆነው የግዕዝ ቋንቋም ተናግረውበታል። በቋንቋቸው መነገር ተደንቀውም ታምር መሆኑን ተገንዝበው በጴጥሮስ ስብከት በኢየሱስ እምነውና ተጠምቀው የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን መሥራች አባላት ሆነው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰዋል። እነሱም ክርስትናን ወደ ኢትዮጵያ ካመጡት ተቆጥረዋል። ግሩም ድንቅ አይደል?

ዘውዱ የእግዚአብሔርን ግዛት ማመልከቻ ነው። አንዳንድ ሰዎች ይህ ምልክት መስቀል አለበትና ሙስሊሙን አይወክልም የሚሉ አሉ። ጉዳዩ ግን የግንዛቤ እጥረት እንጂ ተቃውሞ አይደለም። ውክልናው ለሃይማኖታዊ ድርጅት ሳይሆን ለመላው ለአዳም ልጆች ሁሉ ነው። ነገር ግን የምሥጢሩ ባለቤቶችና ተርጓሚዎች በመሆናችን ጠብቀን ያዝነው እንጂ! የክርስትና

ሃይማኖት መግለጫ ብቻ አይደለም። ይሁንና አባባሉን ልድገመው የተለየን የሃማኖት ክፍልን የሚወክል ሳይሆን የእግዚአብሔርን ሞገስና ግርማ መግለጫ ምልክት መሆኑን ሠፋ አድርጎ ማየትና ማሰብ ነው። በችካላ የሚደረግ ነገር ሁሉ ገልብጡኝን ያስከትላል። ከማይታወቅ ባሕር ውስጥ እንደመዋኘት ይሆናል። በዚያም ላይ አበው እንደሚሉት «ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል» መሆኑ አይዘነጋ ለማለት ነው። በዕድሜ የሚበልጥን ወንድም ጋሼ እኅትን እትዬ ማለት የመከባበር የትሕትናና ባሕላዊ የመታወቂያ ባሕሪያችን ነው። ማንነትን ለማወቅ ትምህርት ቤት መሠራት የለበትም። ከቤትና ከጎረቤት ከፍ ብሎም ከአካባቢ የሚጠኑና የሚቀሰሙ ሰብአዊና ኢትዮጵያዊ ተውፊቶች ናቸው። እንግዲህ የአንበሳው ሥዕልና አርማ ምንነት የኢየሱስ የእግዚአብሔር ምስል መሆኑን ተገንዝበን ክብርና ሞገስ ብንሠጠው እንከበርበታለን። አገራችንንም ከመከራ እንጠብቅበታለን። ስለሆነም ሳያውቁ ማጥፋት እንደ ስሕተት ባያስቆጥርም ቅሉ አውቆ ማጥፋት ግን ደረቅ ወንጀል ነው። ስለዚህ ባለፈው ተፀፅተን ከሚመጣው ተጠብቀን እንኑር።

መታሰቢያነቱ

ራሳቸውን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር መንግሥት ሸንደረባ ላደረጉ፥ ስለ ሃይማኖታቸው ጽናት፥ አንገታቸውን ለስለት፥ እግራቸውን ለስንለት አካላቸውን ለእሳት፥ በጠቅላላው ለመከራና ለሥቃይ አሳልፈው ለሠጡ፥ ትሩፋት ለፈፀሙና ስተጋደሉ ብዙዓን፥ ቅዱሳን፥ ሐዋርያት ጻድቃን፥ ሰማዕታት፥ ኢትዮጵያውያን በተለይም ራሳቸውን ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ክብር ሐዋርያዊ ተጋድሎ ለፈፀሙት፥ በገዛ ሕዝባቸው መካከል በራሳቸው ለዎች የሰማዕትነት ሞትን ለተቀበሉት ስታላቁ ሐዋርያ አባት ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ስማዕት ዘኢትዮጵያ፣ [1902 – 1971]

በጎርትመት በጸምና በጸሎት በትሩፋት ቤተ ክርስቲያናችንን በዜማ በቅዳሴ በመጻሕፍት ማሄድ በማስተማር በመላ ሕይወታቸው ላገለገሉትና ብዙዎቻችንን አስተምረው ለዚህ ላደረሱን ታላቁ አባት ለብፁዕ አቡነ አብርሃም የሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ [ጎዳር ፲፪ ቀን ፲፱፻፭ – ነሐሴ ፳፰ ቀን ፲፱፻፸፩ ዓ. ም.]

እንዲሁም ካህናትን በማሠልጠን በማስተማር ብዙ በጊዜያችን የሚገኙ ዘመናዊ ለባከያነ ወንጌልንና ሊቃነ ጳጳሳትን ያፈሩትና ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ በመጻፍ ላበረከቱት ታላቁ ምሁር አባት ለብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ [1932 - 1982] ተበርክቷል።

እውቅናና ምስጋና

ጥንታዊቷንና ቀጥተኛዋን በእግዚአብሔር ልዩ ፈቃድ በፊሊጶስና በኢትዮጵያዊው ሐዋርያ በባኮስ ሥዩመ ንግሥት ኢትዮጵያ ጥምቀት ለተመሠረተችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በጽኑ ለተጋደሉ ላገለገሉ ራሳቸውን አስርበው መምህራንን ላፈሩ ቤተ ክርስቲያኗን እንድትገለገል ላደረጉና አሁንም በማድረግ ላይ ላሉ ኢትዮጵያውያን መምህራን አክብሮቴንና አድናቆቴን በታላቅ ትሕትና አቀርባለሁ።

አሁንም በየሀገረ ስብከቱ በየገዳማቱና በየአድባራቱ ጉባዔ ዘርግተው ዜማ ቅኔ የመጻሕፍት ትርጓሜን የሚያስተምሩ መምህራን አብዛኞቹ በነፃ ጥቂቶቹ ያለ በቂ ደሞዝ ተኮርኦተ ርእሱን [የሾህ አክሊሉን] የሚዘከሩበት ማለት ስራሳቸው ጥምጣም እንኳን የሚሆን ሻሽ በማትገዛ ደሞዝ ስም ሳይደናቀፉ በጽናት ለሚያስተምሩ ክብርና ሞገስ ይድረሳቸው።

እኒህን መምህራን የመደገፍ የመንከባከብና የማበረታታት ግዴታ ለክርስቲያኑ ወገን ብቻ ሳይሆን ስመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግሥት ኃላፊነትና ግዴታም ነው። ዛሬ ኢትዮጵያ እንዲህ ነበረች ናት እየተባለ የሚነገረው ሁሉ ቅርስ የእኒህ መምህራን የጉባዔ አባቶችና የአነሱም ያላሠለስ ጥረት ቀጣይነት ነውና እንድንደግፋቸው ብሔራዊና ሃይማኖታዊ ግዴታ አለብን።

ማውጫ

ርእስ ገጽ

የሽፋኑ መግለጫ 5
፩. የሰንደቅ ዓላማው ዓርማ 5
፪. የመስቀሉ ዓርማ 9
፫. የዘውዱ ትርጉም 13
መታሰቢያ 17
እውቅናና ምሊጋና 18
ማውጫ 19

ምዕራፍ አንድ

ፊደል የትምህርት መጀመሪያ የማንነት መታወቂያ..... 22
፩. የቅዱስ ሲኖዶስ ተቃውሞ 36
፪. ፳፮ቱ የግዕዝ ፊደላት ስም መልክና መለያ ቁጥር 43
፫. የ፳፮ቱ ፊደላት ትርጓሜ 45
፬. ዘመኑ የረሳቸው ትውልዱ የናቃቸው ፊደላት .. 46
፭. የግዕዝ አጻጻፍ ዕድገት 47
፮. ከግዕዝ የተወለዱ ቃላት ወአንዛት 53

ምዕራፍ ሁለት

ስምዑ ዘንተ ኩልክሙ አሕዛብ [ጴንጤ መጤ ይሀን ስሙ]..... 63
፩. የመታሰቢያ ድግሦች 83
፪. አጽምኡ ሕዝብየ [ወገኖች አዳምጡ]..... 110

ምዕራፍ ሦስት

፩. አአምሩ ወለብዉ/ አወቁ ተገንዘቡ 122

፪ ሥልጣነ ክህነት 138

ምዕራፍ አራት

፩ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ከሥልጣን እንዴት ወረዱ?..... 148
፪ ቅዱስ ሲኖዶስ የአባቶች አንድነት /ልዩነት..... 173
፫ ከፊተኛዋ የኋለኛዋ ትብሳለች..... 189

ምዕራፍ አምስት

የቤተክርስቲያን ማዕርገ ክህነትና አገልግሎት

፩ ማዕርገ ክህነት..... 199
፪ ካህናት ዘበምድር..... 206
፫ የሰበካ ጉባዔ..... 220
፬ በጉብዝና ለእግዚአብሔር ልዕልና 240

ምዕራፍ ስድስት

መፍትሔና ማጠቃለያ 252
ዋቤ መጻሕፍት 272

ምዕራፍ አንድ

ፊደል የትምህርት መጀመሪያ የማንነት መታወቂያ

ለየዋሃን ወገኖቻችን ኢትዮጵያውያን ከሁሉ በፊት ወንድማዊ አስተያየት አለኝ። እሱም የራስን ጥሎ የባዕዳን ባሕልን አንጠልጥሎ መሄድ ቀና አይደለምና ይብቃ ነው። በቅድሚያ የባዕዳንን ከመናፈቅ፥ ሄዶም ከመዘፈቅ፥ አስቀድሞ የራስን ማወቅ፥ ማንነትን መጠበቅ ያስኛል ብልህ ሊቅ። ሌላው ለኛ የሆነውን እንኳ ካለማወቅና ካለመገንዘብ ብቻ መልሰን የኛኑ ጥበብ አስወስደን አንደገና መልሰን አስሞርደን በላዩ ላይ የነበረውን ጽሕፈት አሠርዘንና አሰደልዘን ወይንም አስጠፍተን አንበለው ወይ በብድር ያሊያም በስጦታ ወይንም በግዢ እናግበሰብሰዋለን ታዲያ ተቸገርን ብለን አንናገራለን። ከዚህ ላይ ነው ምላሊያችን ቦታ የሚያገኘው። «ሳይቸገር ጤፍ ብድር» የሚባለው። ጤፍ ለኛ ብቻ የተሠጠ ነው እያልን እሱኑ እንኳ አሳልፈን ሠጥተን ለመበደር መሰለፋችን ትክክል ያለመሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

ለዓለም ሁሉ ትክክለኛውን እምነት ያስተማርን ኢትዮጵያውያን ነን። ማስረጃችንን ላቅርብ። እንዲህ ይላል ትርጉሙን እጽፋለሁ። «ኢትዮጵያ ለዓለም እውነትንና ሐሰትን ለመጀመሪያ ጊዜ አስተማረች። ይህም የእምነትን መሠረት ጥሏል። ከዚህም ባሕልንና ሥልጣኔን መሠረተች።» [*100 Amezing Facts About the Negro* / ገጽ 10 በ J.A. Rogers, 1934. ስለዚህ ለእምነቱ ምንጭ እኛው ነን። አሕየወ ኖረ ሕይወት ሠጠ ካለው ቃልም ለእግዚአብሔር መጠሪያ ያደረግነው ስመ አምላክ ሕያው አምላክ ብለን ነው።

የኢየሱስን ስም ምንነት ማለት ትርጉም ለማወቅ ሃያ ስድሱቱን የኢትዮጵያን ፊደላት በጥንቃቄ ማጥናት ያስፈልጋል። ይህም ማለት መለኮታዊ ምሥጢር የተገለጸበትና ምድራዊ ህብት የታወቀበት ብሎም የሚጻፍበት ፊደል ነውና ነው። ማስረጃውንም ከላይ ተመልክተናል። ጉዳዩን ሳይረዱ ብቻ ፊደል መለወጥ ከዊቃ ላይ ወድቆ እንደ መፈራገጥ ነው። አወዳደቁም ድንገተኛ ያለጥንቃቄ ከመሄድ የተነሣ የሚፈጠር አደጋ ማለት ነው። አንዲህ ማድረግም ያለማስተዋል ብቻ ሳይሆን ድንገተኛም ነው። በዳጥ የተመሰለውም

ለዚሁ ነው። ቶሎ ብሎ ከወደቁበት ተነሥቶ ያለመበረታታት ግን እንደገና ተመልሶ አዘቅት ውስጥ መውደቅ ነው። አሁን እንኳን ወድቀናል። ነገር ግን መውጣት ከፈለግንና ከጣርን አም መመንጠቅ እንችላለን።

የኛን ብቸኛ የምሥጢር ቋንቋችን የሆነውን ግዕዝን ምዕራባውያን በዩኒቨርሲቲዎቻቸው እያጠኑት ነው። ለኛ ግን በምትኩ የእነሱን አንተና አንቺን የማይለይ ኢሕጋዊ ቋንቋቸውን እንድናጠና ያብጠለጥሉናል ቁም ስቅላችንን ያወጡታል በግድም ሆነ በውድ ያስጠኑናል። ትምህርት ቤቶቻችንንም በእነሱ ቋንቋዎች ጠፍረው አስረውታል። የኛን ግን በራሱ ቤት መዋልና ማደር ከልክለውታል። ከዚያም አልፎ ተርፎ በሃይማኖት ስም ለሃይማኖት አስተማሪነት ያሠለጠኗቸው የዋሃን ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን የሆኑት ያሁኑ ጴንጤዎች ወይንም በጥቅል ስማቸው ፕሮቴስታንቶች የራሳቸው የሆነውን ራስ በቀል ፊደላቸውን እስጠልተዋቸው እንኳን ሊያጠኑት ቀርቶ አውጥተው የትም በትነውት ወደ እነሱው ቋንቋቸውና ፊደላቸው ከግዕዝ መቅዳታቸውን ሳያውቁ ዘው ብለው ገብተዋል። በእውኑ ከዚህ የበለጠ ምን ምርኮ አለ? ከዚህስ ወዲያ ምን ባርነት አለ? ከዚህስ ወዲያ ምን ቅኝ ግዛት አለ? አያላዝንምን? ዋ! ወገኔ ይህ አሰላለፍ እንደ አበው ምሳሌ በሬን ካራጁ ጋር ማዋል ነው። ውጤቱ የሚታወቀው ከቄራው ሲደረስ ነው። በዚያን ቀንና ቦታ የሚሆነው በቀላሉ አባባል መታረድ ነው። አገርንም አስረክቦ ባዶ ዕጅን መቅረት ይሆናል። ማንነትን እንደማጣት የመሰለ አስከፊ ድህነት ርዛትና ጉስቁልና በሕይወት ውስጥ የለም። ይህ ተግባር ደግሞ ልጅን የልጅ ልጅን ወይንም ቀጣይ ትውልድን አሽከርና አገልጋይ አድርጎም ማኖር ይደረሳል። ታዲያ ይህ ተግባር የገዛ ልጅን በቢለዋ አጋድሞ እንደማረድ ያስቆጥራል።

በውጭ ሃይማኖት ለበብ ማንነታቸውን አጥተው የታሪክና የባሕል ለደተኞች የሆኑትን አፍሪቃውያን አገሮችን በጥሞና ይመለከቷል። «ጎረቤትህ ሲታማ ለኔ ብለህ ስማ» ከዚህ ላይ ነው። ነገር ግን አሁን በሚሠፈረው ቀለብ ብቻ ተዝናንቶ መቀመጥና የማንነትን ብኩርና በስንዴ ንፍሮ መሸጥ በታሪክ ላይ ታላቅ ጠባሳ መተው ነው። እንደ ቦይ ውሀ የሚፈሰው ገንዘብ ለአንተ ወይንም ለእናንተ መቀለቢያ ነውን? ለሙክትኩ ጪው ፥ ቂጣው፥ ቆሎውና አሻሮው ካልተሠጠው አይሰባም። ታዲያ ለበጉ ረጅም ዕድሜና ጤንነት ታስቦ ነውን የሚቀለበው ወይንስ ለእነሱ ምግብነት? ይህን የማወቅ ግዴታ አለብን።

ስለዚህ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ለማንነቱ ለታሪኩና ለተውፊቱ ዘብ ይቁም። ሁሉም ስማንነቱ ወታደርና አምባሳደር ነው። ማንነትን መሸጥ መለወጥ የሚያስከፍለው ዋጋ ገንዘብ ሳይሆን ደም ነው። ደም መገበር ማለት መጥፋት መሞትና መቀበር ማለትም ባንድ ላይ ነው። በፈደል ሞለወጥ የጀመረ ጉንፋን ወደ ሳንባ ነቀርሳነት ስመለወጥ ብዙ ጊዜ አይፈጅበትም። አለመያዝ እንጂ ከተያዙ ወዲያ ውጤቱን ለማየት ፈጣን ነው። ኢትዮጵያዊነትና ማንነት በጥንቃቄ ካልተጠናና ካልተያዘ ውጤቱ ተያይዞ ገደል ነው። ይህን ያነሳሁት በተለያየ መንገድ እኛ ባላሰብነውና ባልጠበቅነው ሁኔታና ገጽታ ጠላቶቻችን እየመጡ የሚማርኩን መሆናቸውን ለማመልከት ነው። ይህ መከራቸው ትላንት ወይንም ከትላንት ወዲያ የተጀመረ አይደለም። ቢያንስ ከአምስት መቶ ዓመት በላይ የሚሠሩት የተንኮል ደባ ነው። ከትውልድ ወደ ትውልድ እንደ ዘመኑና እንደ ሁኔታው በሚያመቸው ሁሉ በቀጣይነት የሚሠሩትና የሚፈጽሙት የግፍ ተግባር ነው። ዛሬ የሚያመርቱት ልብስ ብልሃቱ፣ ዛሬ የሚያመርቱት ራዲዮን፣ ኮምፒውተርና በጠቅላላው የመገናኛ አውታር ሁሉ የጥበቡ መጀመሪያ ከየት የተወሰደ ይመስለናል? አበው ለዚህ መሰዩ ጥቃት የሚሉት ምሳሊያዊ አነጋገር «ያላወቁ አስቁ» ነው።

አሁን እንኳ ሰው ሁሉ እኩል ነው በሚባልበት ዘመን የቀለም ልዩነት በፖለቲካው በኢኮኖሚውና በማኅበራዊው ኑሮ ሁሉ የሰማይና የምድርን ያህል የተረራቀ ልዩነት አለው። ይህም በቀስም ያለው ልዩነት የአይጥና የድመት ጉርብትና ነው። የሚዳቀል የሚዋሐድ አይመስልም። እንዲህ በቀላሉ የሚናድም አይደለም። ገና ብዙ ነፍስ ይጠፋበታል። ካፎቱ የወጣ ሠይፍ ነው። በዓለም ላይ በልዩ ልዩ በሽታ ከሚያልቀው ሕዝብ ቁጥር ይልቅ በዘር በሃይማኖትና በቀለም ምክንያት የሚፈሰው ደም እጅግ ብዙ ነው። እሥር ቤቶች ከአፍ እስከ ደገፋቸው ጢን ብለው የሞሉት ከላይ በተወሱት ምክንያቶች መነሻነት እንደሆነ ባለሙያዎች ደጋግመው መሥክረዋል።

ይህን ጉዳይ ከእውነተኛው ዕይታ ጋር ስናወዳድረው በሃይማኖት ቤቶቻችን እንኳ የሚታዩት ሥዕሎች እውነት የሌላቸው የአስተሳሰብ የጥላቻ የዘር የቀለም የበላይነትና የበታችነት ነፀብራቆች ሆነው ይገኛሉ። የኢየሱስና የሐዋርያት የሥዕል ሠሌዳ ላይ እንኳን የይሁዳ ሥዕል ብቻውን ተለይቶ የጥቁር ሰው መልክ ወይንም ቢያንስ ቢያንስ ጥቁር የራስ ፀጉር ተሠጥቶታል። ለምን ብለን ጠይቀናል? ኢየሱስና ሐዋርያት ግን በምርጥ ፈረንጆች መልክ ተውበው እናያለን። ባንጻሩ ደግሞ የሠይጣን ምስል ተመርጦ

የአፍሪቃዊ መልክ ተሠጥቶት እንመለከታለን። ይህ ከእውነት የራቀ ሆን ተብሎ በቤተ ጸሎት እንኳን ሳይቀር የዘርና የቀለም ልዩነት ይንፀባረቃል። ጉዳዩ ተገለባብጦ እንጂ ከመጀመሪያው ሰው ከአዳም ጀምሮ የሰው ልጅ መልኩ ጠይም ነው። ፕሮፌሰር አስተሪሊንግ ሚን ይህንኑ አባባል *Missing Link* ገጽ 16 መጽሐፋቸው እረጋግጠውታል። ይህን ለይቶ የሚመለከት ጥቁር ዓይን የለንም ያሰኛል።

በጃንሆይ ጊዜ የሚቀለድ ነገር ነበር። ጃንሆይን ጋዜጠኞች ከጥቁርና ከነጭ ማን ይበልጣል ብለው ቢጠይቋቸው ከዓይንህ ከፍል የቱ ነው የሚያየው ጥቁሩ ወይንስ ነጩ ብለው ጥያቄውን በጥያቄ መለሱለት ተብሎ ይነገር ነበር። ነገሩ የመከላከል ኃሳብ መጀመሩን በጨዋታም መልክ ቢሆን እናያለን። በዚያውም ላይ የጃንሆይን ብልሀነትም ያስተምራል። ይህ አስተሳሰብ መዳበር አለበት። በሰው ልጅ ዕኩልነት መሚገት ይገባል። ይህን ደግሞ የምንጀምረው ከሕዝብ አካባቢዎች፣ ከአብያተ ክርስቲያናትና ከመሳሰሉት ያሉትን ነገሮች ማረምና ማስተካከል ስንችል ነው። ይህም ማለት የነበሩትን ሥዕሎች እንሳጥ ማለትም ሳይሆን እንዳሉ ያስተሳሰብ ማስተማሪያ ማድረግ ስለሚቻል ነው። የወደፊቶቹን ግን እንዳይደገሙ መጠንቀቅ ያሻል። ይህ አስተሳሰብ ከመነልበቱ የተነሣ በኛውም መካከል እንኳን ጥቁሩ ደማቅ ጥቁሩን «ይህ ሠይጣን» ብለን እንጠራለን። ይህ አባባል ምን ያህል ከፍተኛ ያስተሳሰብ ለውጥ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል።

የጠላቶቻችንን የአድላዊነት ጉዞ ጎረግ ስንጎትተው የቤተ መቅደሱን መጠላዕት [መጋረጃ] ሁሉ አብሮ ይስበዋል። እንግዲህ ይህ የሚያመለክተው ተስበው ተስበው የት እንደ ደረሱ ነው። ኢየሱስንና ቅድስት ድንግል ማርያምን ፈረንጆች ሳይሆኑ እንደሆኑ ተደርጎ የፈረንጅ መልክ ተሠጥቷቸው እኑን መስለውና አክለው ተሥለው ስናይ የምናደርገው ስግደት በዕጅ አዙር ለማን ሆነ? ዞሮ ዞሮ ውጤቱ «የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው» አልሆነምን? የሚፈለገውም ይኸው ነው። ፈረንጅ የበላይ ነው መሆኑ ነው። ነገር ግን ምን ይደረግ? እንዴት ይስተካከል? ያልን እንደሆነ ጽዳት ከራስ ቤት ያውም ከደጅ ነውና የሚጀመረው እኒህን መሳይ ሥዕሎች ወደ አብያተ ክርስቲያናቱ ውስጥ ገብተው እንዳይሰቀሉ መከላከል ይገባል። ሠዓሊዎቻችንንም ይህን ከሚመስለው ተግባር እንዲቆጠቡ መምከር ያስፈልጋል። እነሱም ከሚያዩትና ከሚሰሙት ስለሆነ የሥራ ውጤቶቻቸውን የሚያንፀባርቁት መነገር አለባቸው። የምርቶቻቸው ተቀባይ ቤተ ክርስቲያን እስከሆነች ድረስ አስተካክሉ ቢባሉ ሌላው ቢቀር ገበያው ያስገድዳቸዋል።

አንድ ማስረጃ ልተው። ጉዳዩ ከተነሣ ዘንድ ስለ ካህናት አልባሳት ትንሽ ልናገር። የቀደሙ አባቶቻችን የምንኩስና ልብሶቻቸው በሙሉ ነጮች ነበሩ። ለምን የተባለ እንደሆነ ነጭ ቀለም የኃዘን መግለጫ ልብስ ሲሆን ጥቁር ደግሞ የደስታ መዋቢያ ልብስ ስለነበር ነው። ይህን በተመለከተ ከሌሎቹም መጽሐፎቼ ላይ አውስቼዋለሁ፤ ይሁንና ባሁኑ ለዓት የምናያቸው የካህናት ልብሶች በአብዛኛው ጥቁሮች ናቸው፤ በተለይ አባቶች በጥቁር ልብስ ይታያሉ ይታወቃሉ። እንደ ባሕላችንና እንደ ሃይማኖታችን ተውፌትም መልበስ የነበረባቸው ነጭ ነበር። ነጭ ልብስ አስካሁንም የኃዘን ልብስ መሆኑ የሚታወቀው ለው ሲሞት የሚገነዘው በነጭ ጨርቅ ነው። አስከሬኑ የሚለብሰውም ነጭ ልብስ ነው። ነገር ግን ኃዘንተኞች በአሁኑ ጊዜ ለብሰው የሚታዩት ግን ጥቁር ከል የገባ ማለት ነጩን አጥቁረው በመልበስ ነው። ሳያውቁት ግን ያን ልማደ አበው ለመዘከር ባንገታቸው ላይ ነጭ ክር ያሥራሉ። ይህ ነበር ነጭ የሆነ ልብስ የኃዘን መግለጫ ሆኖ የኖረው።

ታዲያ በቤተ ክርስቲያን አባቶችና በገዳማት መናንያን አለባበስ ዘንድ ይታወቅ የነበረውን ነጩን የኃዘኑን ልብስ መልክ ለውጠው የደስታውን ልብስ ጥቁሩን የኃዘን ልብስ አደረጉት። የኃዘኑን ልብስ ነጩን ደግሞ የደስታ ልብስ፥ የደስታውን ልብስ ጥቁሩን የኀዘን ልብስ ተደርጓል። ይህም አለዋወጥ ከልብሱ ላይ ብቻ ሳይሆን ያረፈው ከአብያተ ክርስቲያናት ሥዕሎችም ቄምር ላይ ነው። ከቤተ ክርስቲያን ገብተን ሥዕሎችን ስንመለከት መላእክትን እንደ ነጮች፥ ሠይጣናትን እንደ ጥቁሮች ተሥለው እንመለከታለን። ይህም ማለት ጥቁርን የኃዘን የመከራ የኃጢዓት የበደል ሥራ መግለጫ ሆኖ ሲቀርብ በአንፃሩ ደግሞ ነጭ የበጎ የመልካም የቅድስና ሥራ መግለጫ ሆኖ አንመለከታለን። ይህ አሠራር በልብሱና በሥዕሉ ላይ ብቻ እልቀረም። ዞሮ ዞሮ በኛ በጥቁሮች ላይ ተንፀባርቆ የሚታይም ነው። ስለዚህም ጥቁር ዝቅተኛ፥ ጥቁር ተገዥ፥ ጥቁር አሽከር፥ ጥቁር አገልጋይ፥ ጥቁር የመጥፎ ሥራዎች መግለጫና የሠይጣናት መለያ ሆኖ ቀርቧል። የሚያሳዝነው ይህን እንኳ አይደለም አይሆንም የሚል መጥፋቱ ነው። ለነገሩ ቢባልም ሰሚም የለም። በዘልማድ ሰው ከሚያየውና ከሚሰማው ብቻ መማሩን መርጦ ጥቁርን ለበጎ ነገር መጠቀሚያ ሆኖ አይታይም።

የምንኩስና ልብስ ከነጭነት ወደ ጥቁርነት ሲለወጥ ሥዕሉም ላይ ጥቁርን የሠይጣን መግለጫነቱ ተቀባይነት ሲያገኝ ያልተለወጠውና ያለው የካህናቱ ጥምጣም የአክሊለ ሦኩ ምሳሌ ሆኖ ያለው ሻሹ ነጭነቱን የመከራ ምሳሌነቱን ነው። በነገራችን ላይ ቆቡና ጥምጣሙ የውክልናው ምሳሌ የእሾሁ አክሊልነት ነው። ነገር

ግን ነጭ ልብስ የኃዘን ልብስ ለመሆኑ ማስረጃው ሃይማኖታዊና ባሕላዊም ነው። እንደምሳሌም ብንመለከተው እነ ማርያም መግደላዊት እሁድ ጥዋት ወደ ኢየሱስ መቃብር አስከሬኑን ሽቱ ለመቀባት ሲሄዱ የሆነው እንዲህ ነበር። «ወደ መቃብሩም ገብተው ነጭ ልብስ የተጎናጸፈ ጎልማሳ በቀኝ በኩል ተቀምጦ አዩ።» [ማር.16:5] ይህ የሚያሳየው ከመቃብር ቦታ ላይ የሚለበስ ነጭ ልብስ እሱም የኃዘን መግለጫ መሆኑን ነው።

በሥዕል በአስባበስ በአሠያየም ፈረንጁን ለመምሰልና ለመሆን ሲባል አድባራቱን ገዳማቱን ቆቡን ቀሚሱን ሁሉ ፈረንጅ ካደረግነው ውሎ እድሯል። ደግሞ ደጋግሞ ቢነገርም ከሁስቴ ፍንክችም ከግንባር ላይ የተነቀሰ የጥቁራት ልምድ ሆነና እምቢ ሆነ። በናቴ ባባቴ መቅደስ ያሻየን ብቀድስ እንዲሉ አሁንም አብያተ ክርስቲያኑን ካቴድራል እያሉ መሠየም አንደቀጠለ ነው። በዚህ ስም የሚታወቁ አዲስ አበባ ሁለት ካቴድራሎች ነበሩ። ታዲያ ለመለየት ሲባል የካቶሊኩ ወይንስ የኦርቶዶክሱ? ካልተባለ የቀጠሮው ቦታ ይጠፋፋና ወትሮም ኃጥዓን ተቀጣጥረው ያለመገናኘቱ የተለመደ ነው ይሆናል። ይህ ሁሉ የሚያሳየው በስም በአለባበስ ሥልጣኔ እንደማይገባ መገንዘቡ ይስተዋል። አስተሳሰብንና ድርጊትን መለወጥ ቅድሚያ ይሠጣቸው እንላለን።

ብዙ የዓለምን ሊቃውንት ያነጋገረው የኢየሱስ ክርስቶስ መልክ ምን ይመስል ነበር? የሚለው ጥያቄ ነው። ለነገሩ ሁሉም እንደ ማስረጃ የሚጠቀመባቸው ሁለት ጉዳዮች አሉ። እነሱም አንዱ ጲላጦስ ጴጤናዊ ለንጉሥ ለጢባርዮስ ስለ ኢየሱስ መሰቀልና መሞት የተሠጠውን ፍርድና ስለ ኢየሱስ ታሪክ የመልክ አቋም ገልጾ የጻፈውን ደብዳቤ አስረጅ አድርገው ኢየሱስ የቀይ ዳማ መልክ እንደነበረው ያረጋግጣሉ። በሁስተኛ ደረጃ ደግሞ በራዕየ ዮሐንስ ምዕራፍ 1:14 -15 የሠፈረውን ቃል አስረጅ ያደርጋሉ። ይህ በእንዲህ እንዳስ የእነ ሚካኤል አንጀሎ ሥዕሎች ከኢየሱስ ክርስቶስ ጀምሮ አብረውት የነበሩትን በሙሉ የኮከሺያን መልክ ማለት ነጮች እንደሆኑ አድርጎ ነው የሣለው። ይህም የፓሊስቲንያን ወይንም ፍልስጥኤማውያን መልክ እንዳልሆኑና እንዳልነበሩ ተደርገው ነው በሥዕሉ የቀረቡት። ከዚያ ወዲህ ግሪኮችና ቫቲካኖች የፈረንጅ ሥዕሎች አያባዙ ዓለምን አዳረሱት። ይህ ትክክል እንዳልሆነም ተደጋግሞ ቢነገር ስሕተቱ አልታረመም። ይባሱኑ በየቦታው የሚታየው ይሸው ብቻ ሆኗል። ሥዕሎቻቸውን የራሳቸውን ውበትና ቅላት ወይንም ላሕይ ሠጥተው የሚሥሉ ኢትዮጵያውያን እንደሆነ ይነገራል። ይሁን እንጂ በአሁኑ ሰዓት አብያተ ክርስቲያናቱን

ያጣበበው የፈረንጅ መልክ ያሏቸው ሥዕሎች ናቸው። ኢትዮጵያውያን ሥዕሎቻቸውን ብቻ ሳይሆን ድርሰቶቻቸውንም በተገቢው መልክና አባባል ጽፈዋቸው ብዙ ቦታ እንመለከታለን። ለማሰረጃም ያህል ከብዙ በጥቂቱ ከመልክአ ሕማማተ መስቀል ውስጥ አባባሉን እንመልከት። «ሰላም ለዝከረ ስምከ በመጽሔተ መለቀል ዘተከልአ። ወለሥዕርትከ ጸሊም ዘደመ ተኮርያ ተቀብዐ። ....» ወለሥዕርትከ ጸሊም የሚለውን ነው መጥቀስ የፈለግሁት። ይህ «ወለሥዕርትከ ጸሊም» [ጥቁሩ የራስ ፀጉርህ] የሚለውን ገላጭ ቃል ነው። ኢየሱስ ጥቁር የራስ ፀጉር የነበረውና ጠይምም መልክ እንደነበረው መረዳቱ ግልጽ ነው። የኢየሱስን መልክና ፀጉር የፈረንጅ ማድረግ ከቅንነት ሳይሆን ሆን ተብሎ በተንኮል መሆኑን ይገነዘባል። ይሁንና አበው በድርሰቶቻቸው እውነተኛውን ቃል አስፍረውት እንደዚህ ይገኛል።

የአብያተ ክርስቲያናትን ሀብትና ንብረት መተዳደሪያ በደርግ መንግሥት በአዋጅ ሲወሰድ የውስጡን ደግሞ በጠመንጃ በበር ሠበራ እየተገባ ባዩኝና ባላዩኝ የስርቆት ፈሊጥ እየተቀነባበረ መጻሕፍትና ንዋየ ቅድሳት ወደ ዘመዶቻቸው አጎጉር ወደ ምዕራባውያን አገር አውንም እየተጋዙ ነው። በቅርቡ የቅዱስ ሳሊበላ መስቀል በመታወቂያ ስሙ «አፍሮ አይገባ» ከአውሮጳ ተይዞ ተመልሶ አልመጣምን? የታቦትንማ ጉዳይ ማውሳትም አያሻም እነሱ ሲሰርቁት ከብር ሊኖረው ሲያጡት ደግሞ ለመዝለፊያ ማድረጉ የግፍ ግፍ ነው። «የሌባ ዓይነ ደረቅ መልሶ ልብ ያደርቅ» ማለቱ የማያስነውር ከሆነ ይቅርታ አየጠየቅሁ አባባሉን ግን እጠቀምበታለሁ። ኃላቤን በሚገባ ይገልጽልኛልና ነው። ታዲያ ቢጮህ የሚወጣ ጎረቤት ታጥቶ ነው እንጂ ችግሩ አጉራ ከዘለለ ውሎ አድሯል። የአፍሪቃ አንት አገሮች ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ሆይ በኛ የደረሰ እንዳይደርስብሽ ራስሽን ጠብቂ ይላሉ። የኬንያው የነፃነት አባት የመጀመሪያው ያገሪቱ ፕሬዝዳንት ከቡር ጆሞ ኬንያታ አንድ ታላቅ ቃለ ምዕዳን አስምተዋል። በዕጃችን መጽሐፍ ቅዱስ ሠጥተው ዓይናችሁን ጨፍኑ እንጸልያለን ብለውን ስንጸልይ ከቆየን በኋላ ዓይናችንን ስንገልጥ አገራችን በነጭ ተወራ አገኘናት። ይህ ተራ መልእክት አይደለም። ቃለ ምዕዳን እንጂ! የማይገባኝ ነገር ቢኖር «ማርን ሽጦ ምን ይገዟል» እንደተባለው ከአርቶዶክስ ተዋሕዶ ሌላ ምን ሃይማኖት ያስፈልጋል? ዶሮን በቆቅ መለወጥ ካልሆነ በስተቀር።

ታቦተ ጽዮንንስ ለመሥረቅ ምን ያልታቀደ ምንስ ያልተዶለተና ያልታሰበ ነገር ነበር? ታቦተ ጽዮንን ፍለጋስ ሲባል የጽላት ስርቆት እንደ ቤተ ክርስቲያን እመት በየቤተ ክርስቲያኑ

የተፈፀመውን የጉድ ጉድ የምናውቀው አይደል። ስንቶቹ ታስረዋል ስንቶችስ እስከ ጽላቱ ተይዘዋል? ፖሊስ ጣቢያዎች ይቁጠሩት። ይህ እንግዲህ ወንጌልን መስበክ ወይንስ ወንጌልን ማጥፋት? ዛሬ በምዕራባውያን አገሮች የሚገኙት የብራና መጻሕፍት ቁጥር ዕልፍ አዕላፍ ናቸው። በዕርዳታ ስም ዝርፊያ በእንላለም/በእንባረክ ስም ስርቆት በእንጎብኝ ስም ስለላ ስምዳራዊውም ሆነ ለስማያዊው መንገድ አይቀናም። ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር አገር እንጂ የሰዎች አገር ብቻ አይደለችም። የጦር ጀኔራሏ እግዚአብሔር ሠራዊቷ መላእክት ናቸው። ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚሆን ነገር ከቶ የለም። በኢትዮጵያ ላይ ድንጋይ የሚወረውሩ የድንጋዩ ማረፊያ የወርዋሪዎች አናት ነው። ስለዚህ ልቦናውን እውነቱን ለኢትዮጵያውያን ይስጥ ያንድ እናት ልጆችን ሆድና ጀርባ አያድርግ አንዱ ሌላውን የሚደግፍ እንጂ ጠልፎ የሚጥል አይሁን። ወንድምህን ጨርቃም ብለህ አትሳደብ። ወንድምህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ እንጂ!

ስለሁሉም ሃይማኖታቸውንና አገራቸውን ሊጠብቁና ሊከላከሉ ይገባል። ድሮውንም የሃማኖት ርዳታ አልፈለግንም ነበር ስንዴው ሃይማኖት ካልተከተለው ወይንም ካልተደባለቀበት ቁርባን አይሆንም ሆነና በተከፈተለት በር ገብቶ ዓይን ልኳል ብሎ የሚያላውር ጥርስ ልፋቅ ብሎ የሚሠብር የጉትቻ ማላደሪያ ጆሮ ልብሳ ብሎ የሚተለትል ያንገት ጌጥ ሳድርግ ብሎ ጉረሮ የሚቆርጥ ፀጉር ላሳጥር ብሎ ናላ መፈጥረቅ ሆነና ተቸገርን። ስለ ሃይማኖታቸው የሞቱ የነበሩንና ያሉንን ያህል ደግሞ ሹመት እንጂ መከራ ስምኤዎችንም አገኘን። እንግዲህ ይህ ሁሉ ሀብትና ፀጋ ከሆነ ሁሉም በየዓይነቱ ሞልተውናል ተርፈውናል ብንልላ! ጠላት እታላጣን ተብሎ የለ? አያድርገውና ድንገት ጠላት አውርድልን ብሰን ይሆን? ቢሆንም ጠላትህን ውደድ የሚለውን ቃል ለመፈፀም ይሆናል ብለን እናልፈዋለን። ስለሆነም ለሚያላድዱችሁ ጸልዩ ታላቅ ትምህርት ነው። ለዚህስ አይደል ከፉን በከፉ አትቃወመው በሥራ ላይ ያለው ምፀት ካልሆነ ይህ ትምህርት ሥር ሰዶ ያለውና የሚኖረው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው ቢባል የሚስማማ ይገኛል? ካለ እሺ በጎ ወሸንያ!

ከዚህ ቀጥሎ እንደማሳስቢያ ላቀርበው የምሻው ጉዳይ ቢኖር እስካሁን ያጣናቸውና የተነጠቅናቸው የኢትዮጵያ ማንነት ቅርሶቻችንና መታወቂያዎቻችን የትኞቹ ናቸው? ባሕሎቻችን እስከነዘርፎቻቸው ማለት ትሕትና ታማኝነት መፈቃቀር ተከባብሮ መኖር ከኔ ይልቅ ላንተ መበባልን አንደ ግል ሀብትና ንብረት መቁጠርን እንዲሁም ለሌሎቹ ደግሞ ምሳሌ የሚሆነው ከትላንት

በስቲያ ወደ አገሩ የተመለሰው የአክሱሙ ሐውልት አንዱ ቋሚ ምሥክር ነው። ይህን ያጣነውን ቅርስ ለማስመለስ የተደረገውን ጥረት እጅግ አድርገን እናደንቃለን። ይቅጥል መልካም ሽጋ ይባል። ከዚሁ ጋር ደግሞ አውቀን በድፍረት ሳናውቅ በስሕተት ከሆነም ግንዛቤ እንድንወስድበት እጅግ በጠና ላስገነዝብ እወዳለሁ። ያሉኝም አቤቱታዎች በሚከተሉት ቅዪሶቻችን ላይ ያተኩራሉ።

አንደኛ፣ ይህ የሰው ልጅ አፍ መፍቻ ቋንቋ የሆነው ግዕዝ በሥርዓተ ትምህርቱ ገብቶ እንዲሠጥ፥

ሁለተኛ፣ የግዮን ወይንም የዓባይ ስም ተሰውሮ «ናይል» እንዳይባል፥

ሦስተኛ፣ አበሻና አቢሲኒያ፥ የሚሏቸው መጠሪያዎች ኢትዮጵያ የሚለውን ስምና መታወቂያ ማደብዘዣያና ማደናገሪያ ስለሆኑ እንዳይባሉ ማድረግ፥

አራተኛ፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ሕዝብ ቋንቋ የስሙ አጠራር ከአማርኛ ወደ ኢትዮጵያውኛ እንዲለወጥ ናቸው።

በእንደኛ ተራ ቁጥር ስላለው ስለ ግዮን ስምና መጠሪያ ጉዳይ የምለው ይህ ነው። ግዮን የታላቁ ወንዛችን መጠሪያ ዋና ስም ነው። ታላቅነቱንና ረጅምነቱን ለመግለጽ ደግሞ ዓባይ ይባላል። በመሠረቱ ግዮን የሚለው ቃልም ከግዕዝ የተገኘና የወጣ ነው። እሱም ሳየ ሸሸ እገር ጥሎ ሄደ እውነተኛ የተግባር ስሙ ነው። አሁን ግን እነ ግፍ - አይፈሬ ደንበኛ ስሙን ከመጽሐፍ ቅዱስ እንኳን ሳይቀር የሚታወቅበትን መጠሪያ ግዮንን ለውጠው «ናይል» አሉት። ዓለሙም ተባብሯቸው «ናይል» በመባል እየተጠራ ነው። እንኳን ባዳዎቹ ቀርቶ የኛዎቹ ኢትዮጵያውያኑም የድርጅቶቻቸው መጠሪያና መታወቂያ አድርገውታል። በዚህ ከቀጠለ ነገ ከነገ ወዲያ ደግሞ የልጆቻቸው መጠሪያ ሊሆን ነው። ይህን የመሳሰለውን እንኳን የሚጠባበቅላት የምሁራን ድርጅት፥ የጥናትና የምርምር ተቅዋም የሌላት አገር ለምን ሆነች? ልጆችዋ በውጭው እንጂ በቤታቸው ቅቤ ስላልተናቀሩ ይሆን? አንድ ከደብረ ዘይት ወደ አዲስ አበባ መምጫ መንገድ ላይ በትልቁ ሠሌዳ ላይ እንዲህ የሚል ተጽፍል። ልብ በሉ። «kani Gari» [ካኒ ጋሪ] ምን ማለት ነው? በቀጥታ የግዕዝ ቃል ነው። የተጻፈው ግን በላቲን ወይንም በሮማን ፊደል ነው። ካኒ ማለት ኮነ ካለው የግዕዝ ቃል የተወሰደ ሆነ ይሁን ማለት ሲሆን ጋሪ ደግሞ ምሕዋር መንገድ መሄጃ ሐረ ሄደ ካለው የግዕዝ ግሥ የወጣ

ነው። በተለምዶ ጋሪ በፈረስ የሚጎተት በጎማ የሚሽከረከ መሄጃ መኪና ወይንም ሠረገላ የሚታወቅበት በጋሪ ነው። ይህን እንድ ላይ ስንገጥመው መልካም ጉዞ ቀና መንገድ ይሁን ለማለት ነው። ተርጓሚም አያሻው በግልጥ ይታወቃል። በላቲን ስለተጻፈ ሌላ ቃል የማይታወቅ ኢትዮጵያዊ ያልሆነ ይመስላል። ግን ግዕዙ በላቲን ተጽፎ ሲነበብ በማየቱ ተገርሜ አድናቆቴን ለማካፈል ነው። ከዚያ ውጭማ ምን ይባላል? «ንነሂ ንነግር ወኢንዘብጥ» [እኛ እንናገራለን ታሳብ እናቀርባለን ያየነውን እንመሠክራለን እንጂ እናሰገድድም] ተብሏል። ግንዛቤዬን ለመግለጽ ነው።

በሦስተኛ ደረጃ ስላለው ስለ አገራችን መታወቂያ ስምና የሕዝብ መጠሪያ እየሆነ ያለው አበሻና አቢሲኒያ የሚሉት ስሞች የኢትዮጵያ ስም ማደናበሪያ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊት ተብሎ ሳለመታወቅ የሚጥሩ ሰዎች አውቀው የሚያደናግሩባቸው ፈሊጦች ናቸው። ኢጣሊያን አዲስ አበባን በወረራች ጊዜ የመጀመሪያ ባንኳን ስም የጠራችው አቢሲኒያ ባንክ ብላ ነው። «ባንክ» እንደ ግዕዙ እሠያየም ከሆነ ቤተ ርዴ ከዓለም አቀፍ የንግድ ድርጅቶች ጋር እጅግ የመታወቅና አብሮ የመሥራት ባሕርይ ስላለው ስሙ ኢትዮጵያ የሚለውን እንዲተካላቸው ባላቸው ውሳጣዊ ተንኮል መሆኑን ብዙዎቻችን እልተገነዘብነውም። ይባስ ብሎ አሁንም ታሪክን ያለመመርመርና ያለመረዳት ሆነና አቢሲኒያ ባንክ ተቋቁሟል። አቢሲኒያ የሚሉን ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ጨርሶ ለማውደም ነው። አሁንም ይታሰብበት። ስምን መለወጥ በታሪክ ያለወቅሳል። ነገር ግን ወደ ትክክለኛውና ወደ ታሪካዊው ስም ለመመለስ ፍርድ ቤት ማመልከት ነው። ታሪክን መጠንቀቅ ለተተኪው ትውልድ ጥሩ ዘርን መዝራት ነው። ጥሩ ዘር ለማግኘት ደግሞ አረሙ መነቀል አለበት። ስለዚህ ለአቢሲኒያ ባንክ ባለቤቶች አቤቱታዬ ይድረስልኝ።

በየዋሕነትና ጉዳዩን ግንዛቤ ውስጥ ባለማስገባት የከተሞቻችን ድርጅቶችም ስማቸው በኢትዮጵያ ቋንቋዎች መዝገበ ቃላት ጨርሶ የማይታወቁ ናቸው። ጣሊያንኛ ፈረንሳይኛ ላቲንኛ በጠቅላላው ፈረንጅኛ ናቸው። የቡናና የጫት መሸጫ ሱቆች ሳይቀር እውሮጳዊ ስም ሲሠጣቸው ምን ይባላል? ቡናና ጫት እንኳን የስም ለውጥ እንዴት ያድርጉ? ያልታሰበበትና ግንዛቤ ያልተወሰደበት ታላቅ ስሕተት ነው። የከተሞች ባለ ሥልጣናት ከእንዲህ ዓይነት ስሞች የከተሞቻችንን ጽዳት ቢያስጠብቁልን መልካም ነው። የንግድ ድርጅቶች ስም በጣም ተዘበራርቋል። እንኳን ለማስታወስና ደግሞ ለመጥራት በትክክል እንኳን ለማንበብ ግራ የሚያጋቡ ናቸው።

ከመሐል ወጣ ካሉት ቦታዎች ለሚመጡ ኢትዮጵያውያን እንዴት ይሰማቸው? አንበው የሚረዱት እኮ ስም ጨርሶ የለም። ስምሳሌም ያህል ራስ አሉላ አባ ነጋ፥ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ፥ ደጃዝማች ባልቻ አባ ነፍሶ፥ ደጃዝማች በላይ ዘለቀ፥ ራስ አበበ አረጋይ፥ ደጃዝማች ዘርዓይ ድረስ ተብሎ ቢሠየም አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ደጋግሞ ባነበበው በነፂር። እሱ ማን ነው? ማን ነበር? ብሎ ታሪኩንም ይማርበት ነበር። አሁን ግን ካሉት ስሞች አንዣር ሲታይ ኢትዮጵያ ነው ያለሁት ወይንሸ ሌላ አገር ከተማ ውለጥ በማሰኘት ላይ ነው።

እንዲያው ዓይን ዘወትር የሚያየውን ለምዶት ካልሆነ በስተቀር ያስደነግጣል። ያውም አዲስ አበባን ያህል ከተማ ወገኖቻችን በፋሽስት ዕጅ በአዲግና በአክፋ የተጨፈጨፉባትን እንዴት ተደርጎ? የፈሰሰውን ደማቸውን በጣማ አንደ መርገጥ ነውና ቢታሰብበት ርቆ ሳይሄድና ተተኪው ትውልድ ጋር አብሮ እንዳያድግ በቶሎው ቢታረም መልካም ይሆናል። ይህም ማሳሰቢያ ነው። ወላጆቻችን ደማቸውን አፍስሰው አጥንታቸውን ከስክሰው ከአውሮጳ ቅኝ ግዛት ነፃ አድርገው ያስረከቡንን አገር ኢትዮጵያን ዛሬ እኛ ይህ ትውልድ ኢትዮጵያውኛ ስማችንን በፈረንጅ ስም አርቶዶክሳዊውን እምነታችንን በመጤ ጳንጤ ሃይማኖት ለውጠናል። ይህ ሥልጣኔ አይደለም። የስም መለወጥ መሠልጠን አይደለም። ስሙን ብንለውጠው ባለንብረቶቹ ተለወጡ ማለት ነውን? ከመንገድ ቁጭ ብላ የምትለምን ደሃ ልጁን ጌታቸው ብትለው ለሰሚው ምፀት ነው። ጌታሁን ብትለው ግን መልካም ምኞት ነው።

ስለዚህ ግንዛቤ እናድርግ? የዚህ የዚህማ በአውሮጳውያን ቅኝ ግዛት ሥር ከነበሩት አገሮች በምኑ ይሆን የምንለየው? መለያና መታወቂያችን ቋንቋችንና የሱም መግለጫ የሆኑት ፊደሎቻችን ናቸው። ዛሬ ስማችንና ሃይማኖታችንን ብቻ ሳይሆን የለወጥነው ፊደሎቻችንንም ለውጠናል። የአውሮጳ ፊደሎች የተቀዱት ከግዕዝ መሆኑን ብናውቅ ኖሮ እንዴት በደነቀን በነበር? R. G. Latham የተባሉ ምሁር Man and His Migration በተሰኘው መጽሐፋቸው ገጽ 156 ላይ «የኢትዮጵያ ቋንቋ ማለት ግዕዝ በዓለም የመጀመሪያው ቋንቋ ነው» ሲሉ ገልጸውታል። መቼም ራስን ያለማወቅ ወይንም ማሳሳት ከበደሎች ሁሉ በደል ነው። እንደሚባለው «ሰው ራሱ ያለማወቁን አለማወቁ ነው» አባባል ትክክል ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያዊ ዶሮችንን በፈረንጅ ቆቅ እንለውጠው። ይህም ዓይነቱ ልውውጥ የሚሆነው ሰዶ ማሳደድ ነው። በውስጡ ግን የሚካሄደው ሜራና ተንኮል መሆኑን ሳይረዱ በወጥመዱ ውስጥ በወደቁ

ወገኖቻችን እናዝናለን ልቦና ፍጠርላቸው ብለንም እንመኛለን እንለምናለን። እኒህን አበሻና አቢሲኒያ የሚሉ የመጠሪያ ስሞች በጠላቶቻችን ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊት እንዳንባል የተፈጠሩ ቄምብሎች መሆናቸውን ተረድተን ግንዛቤ ውስጥ እንድናኖረውም እማፀናለሁ።

አንድ ልናስታውሰው የሚገባ ጉዳይ አለ። እሱም ወደድንም ጠላንም እኛነታችን ከኢትዮጵያ ጋር የተያያዘና የተቆራኘ ነው። ኢትዮጵያዊ ጠይምነቱን ነብር ዝንጉርጉርነቱን አይለውጥም። ተብሎ በነቢዩ ኤርምያስ ተነግሮልናል። [ኤር. 13:23] የትም እንሁን የት ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊት ከመሆን አንወጣም አንዘልም። የተሰጠን የመታወቂያ ደብተር ስምና መልካችንን ለማገናዘብ እንጂ የፈረንጂ መልክ አያላብሰንም ወይንም ፈረንጅ አያደርገንም። እሱም መለወጣችንን ከቶ አያመለክትም። ይሁን እንጂ ዞሮ ዞሮ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊት ከመባል የሚገታን አይሆንም። አንድ ኢትዮጵያዊት ወይንም ኢትዮጵያዊ መልካም ሆነ መጥፎ ነገር ብትሠራ ቢሠራ የሥራቸው መጠሪያና መታወቂያ ኢትዮጵያ ናት። እንደ ምሳሌም የምናየው ኢትዮጵያውያን ራሮች [አትሌቶች] በሩጫ ሲያሸንፉ ውጤቱ የሚሄደው ወደ ኢትዮጵያ ነው። ኢትዮጵያ አሸነፈች ነው የሚባለው ከዚያ ነው ወደ ሯጩ ስም የሚሸጋገረው። ይህ የሚያስገነዝበው ከሰውየው ስም ይልቅ ኢትዮጵያ የሚለው ስም ጎልቶ ይነበባል። ለዚህም ነው የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ወጥቶ የሚውለበለበው። በርግጥም ወክሎ የተሰለፈው ኢትዮጵያን መሆኑንም ባለመዘንጋት ነው። ይህ መልካሙ የተግባር ውጤት ምሳሌ ነው። እንዲሁ ሌላው ኢትዮጵያዊ ኢሰብአዊ ተግባር ቢፈጽም አሁንም እንዲህ የተሰኘ ኢትዮጵያዊ ወይንም አንድ ኢትዮጵያዊ ይህን አደረገ ተብሎ የተግባሩ ውጤት የሚሄደው ወደ አገሩ ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያዊነት የጋራ የክብራችንና የማዕርጋችን መግለጫ ነውና ሁላችንም በጋራ ታላቅ ጥንቃቄ ልናደርግበት የሚገባ ንዑድ ክቡር ስም ነው።

እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱ ወገኖቻችን ቢኖሩ በአሜሪካ ያሉት አፍሪቃን አሜሪካን ናቸው። እኒህን ወገኖቻችንን ከአፍሪቃ አፈናቅለው አሜሪካ ሲያመጧቸው የማንነታቸው ማጥፊያ አድርገው የወሰዱት በመጀመሪያ ስማቸውን መቀየርና መለወጥ ነበር። ከዚያም የመጡበትን ቦታና አድራሻ ሳይነግሯቸው አፍነው አንደ እንስሳ ሲሸጧቸው ሲለውጧቸው መኖሩ ነው። አሁን ትልቁ የአነሱ የእግር እሳት የሆነው ከየትኛው የአፍሪቃ አገር ከየትኛው ቋንቋ ተናጋሪ ክፍል መወሰዳቸውን ያለማወቁ ነው። በትክክል ቢያውቁት ኖሮ ወላጆቻቸው ወደመጡበት የአጎጉር ክፍል በመሄድ ቋንቋውን

አጥነተው እሱም ቢኖር ወደዚያም ሄደው ሰመኖር የሚመኙት ወገኖቻችን ብዛት ቁጥር ሥፍር የለውም። በኛ እንኳን ያላቸው መንፈሳዊ ቅናት በቋንቋ የሚገልጹት አይደለም። የራሳችን ፊደል የራሳችን ቋንቋ የራሳችን ምግብ አሠራር አሰባበስና ወግ ማዕርግ ምን ያህል ታላቅ ፀጋና በረከት መሆኑን የምንረዳውና የምንገነዘበው ከእነሱ ጋር ቁጭ ብለን ስንወያይ ነው። ሳናውቀው በጣታችን ላይ ያለውን የወርቅ ቅለበት ከሚታ ላይ እንደጣልነው ያስቆጥራል። ወደ ጥቁር ወገኖቻችን መሰስ ስንል የነገሯቸውና ያስጠኗቸው ጥቁር የነጭ አገልጋይ መሆኑንና ከነጭ በታች ሆኖ መፈጠሩን ነው። ከዚህም በላይ ታሪክ እንደሌላቸው አስጠንተዋቸዋል። እንኳን ታሪክ የሰው ነፍስ እንኳን እንደሌላቸው እየነገሩ ነው የገዟቸው። አድሜ ሰወላጆቻችን ደማቸውን አፍስሰው አጥንታቸውን ከስክሰው ሁሉን ነገር ጠብቀው በክብር ስኛ አስረክበውናል። እኛስ? እኛማ እኛ እንጂ ሥራቸውንና ድካማቸውን አይጥ የበላው ልቃቂት አላደረግነውምን??? ይሁን እንጂ በወጣቱ ትውልድ ተስፋ እናደርጋለን ወደ ማንነታቸው ይመለሳሉ ማንነታቸውን ያውቃሉ ያከብራሉ ብለን ከፍተኛ ተስፋ እናደርጋለን። በዚሁም እንጽናናለን።

ይህ የግፍ ታሪክ ድግግሞሽ አፍሪቃን በቅኝ ግዛት ዘመን ደግመውታል። እነ ግፍ አይፈሬ አሁንም በኛም ላይ ለመድገም ከበታው ሳንለቅ ማንነታችንን እያጠፉና እየለዋወጡብን ነው። የኢትዮጵያን ስም እንኳን በየጊዜው ከሚያሳትሙት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያውም ከሃይማኖታዊው መጽሐፍ በሐሰት አትመስክር ከተጻፈበት ገበታ ውስጥ ታላቅ ሽፍጥና ሐሰት ይፈፀማል። ለዚህም ነው በሃይማኖት ስም ከሚደረግ ደባ ራሳችንን እንጠብቅ የምንለው። ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ከታላቁ መጽሐፍ ውስጥ እየሠረዙ ሱዳን፣ ደቡብ ግብፅና ኩሽ እያሉት ነው። ይህን በዓይናቸው እያዩና እያነበቡ ዝም ያሉት የኛዎቹ የእነሱ ሃይማኖት ተሸካሚዎችና አስተላላፊዎች ስለኛ ታቦትና የኛን መጻሕፍት እንድናቃጥል ይጮሃሉ። መቃጠልስ ያለበትና የሚገባው በተንኮልና በሐሰት እየታተመ የሚሠራጨውን የኢትዮጵያን ስም አውጥቶ የጣለውን መጽሐፋቸውን ነው። የኢትዮጵያን ስም ያሊያዘውን መጽሐፍ አታንቡት ከቤታችሁም ካስ አውጥታችሁ ጣሉት። የዚህ ዓይነቱ መጽሐፍ አካፋፋዮች ወደ ኢትዮጵያ ከማስገባታችሁ በፊት ኢትዮጵያን አስታውሱ አትርሱ በሏቸው። መጽሐፍ ቅዱስ አቃጥሉ ብሎ ጻፈ እንዳትሉ። አበባሌን ልድገመው የኢትዮጵያን ስም አውጥታችሁ የጣላችሁበትን መጽሐፍ አንኳን ማንበብ በዓይንም አይታይ።

እንደኔ አባባልና ምኞት ቢሆን ኖሮ ወጣቱን ቤት አዘግታችሁ ስታስለቅሉት ማየት አይሆነኝም ነበር። እናንተም የተሳሳተውን ያልተስተካከለውን መጽሐፍ ከማስረግ እንኳን ተባበሩን ተቆጠቡልን። ይህ የኢትዮጵያውያን ሁሉ አቤቱታና አደራ ነው። ታዲያ ወገኖቼ ይህን የመሰለውና እንዲህ ስእናንተ እንዲመች ተደርጎና ተስተካክሎ በየጊዜው የሚሠራጨው የእግዚአብሔርን ቃል መከለስና መበረዝ አይደለምን? ከዚያም በላይ ታላቅ የማታለያ የማስመሰያና የማጭበርበሪያ መሣሪያ አልተደረገምን? የዋሃንን የምታጠምዱበትን መሣሪያችሁን እንኳን ክብር አልሠጣችሁትም። ይህ የሚያመሰክተው የምትፈልጉትን የተነሣችሁበትን የመበታተን ሥራ እንጂ ስለ ቃልነቱ ትክክለኛነት እንኳ ቁብ የላችሁም። ብዙም ሩቅን ሳንሄድ ከአሥር ዓመት በኋላ የሚሆነው ኢትዮጵያ የሚል ቃል ከቅዱሱ መጽሐፍ ውስጥ ጨርሶ የለም ብላችሁ በተሰመደው እንደበታችሁ ትመሠክራላችሁ። ምሥክርነት ማለት እናንተ ዘንድ እኮ ያሰውንና የነበረውን የሰም ማሰኘት ነው። ጥቁርን በነጭ እውነትን በሐሰት ግዕዙን በላቲን የመሰዋወጡ ተግባር እንደዚህ ነውና ነው።

ጥቁር ስነጭ አገልጋይነት የተፈጠረ ነው ብላችሁ አስተምራችኋል። ማስረጃ ላቅርብ። ፕሮፌሰር እስተርሊንግ Ethiopia the Missing Link in African History በተሰኘው መጽሐፋቸው በገጽ 8 ላይ «ጥቁር ከነጭ በተፈጥሮ ዝቅተኛ ነው» የሚሉትን የምዕራባውያን ጸሐፊዎችን ተቃውመው ሲጽፉ አባባሉ አሉ ፕሮፌሰር ስተርሊንግ «ይህ ዓይነቱ አመለካከትና አባባል ሰዎችን ብቻ ሳይሆን የፈጣሪንም ሥራ ማዋረድ መናቅና ዝቅ ማድረግ ነው» ሲሉ ገልጸውታል። ከዚህ ላይ የምንለው የናንተ የስብከታችሁ ፈሊጥ ይህ መሆኑን አደባባይ ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ምሥጢር ነው። የሚገርመው እናንተም ታውቆብናል ብላችሁ ያለመታከታችሁ ሌላውም ይህን ሁሉ በደል እያየ ከስሕተቱ ያለመማሩ በጣም የሚገርምና የሚያስደንቅ ነው። ከዚህ ወዲያ ምን ዓይነት ማስረጃ ማቅረብ ይቻላል? የሚያሳዝነው የሚታሰሉና በወጥመዳችሁ የሚገቡ ሰዎች ማግኘታችሁ ነው።

ከዚህ ላይ የተንኮሉ ከንተሮ የሚያርፈው በኢትዮጵያ ሞንቅላት ነውና ይህን ደባ ያወቅነውና የተገነዘብነው ኢትዮጵያን በየጊዜው ከሚታተመው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማውጣታችሁን ነው። ስለሆነም ይህን ፀሐይ የሞቀውን ደባ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተቃውማ ደብዳቤ ጽፋለች። ይህም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ

ውሳኔ በመስከረም ወር 1990 ዓ. ም. የተላለፈ ነው። የቤተ ክርስቲያኗን ተቃውሞ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ በትክክል ተቀድቶ ከዚህም ጋር አብሮ እንዲነበብ አቅርቤዋለሁ። ሙሉ ቃሉም እንደሚከተለው ነው።

፩. የኢትዮጵያን ስም ከቅዱስ መጽሐፍ በሚሠርዙት ላይ የቀረበ ተቃውሞ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ያቀረበው የተቃውሞ ውሳኔ ይህ ነው። ... የአሜሪካ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር «የዛሬ እንግሊዝኛ ትርጉም ጉድኒውስ ባይብል» በሚል ርእስ አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ እ. ኤ. ዘ. አ. በ፲፱፻፷፯ የማሳተሙ ጉዳይ ነው፤ በዚህም ኅትመት ሁለት አስገራሚ ሁኔታዎች ተከሥተዋል፤ እነዚህም በአንድ በኩል በዕብራይስጥ ኩሽ በግሪክ በላቲን [ሮማይስጥ] በግዕዝና በሌሎችም የጥንት ቋንቋዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም «ኢትዮጵያ፡ ኢትዮጵያዊ፡ ኢትዮጵያውያን የሚሉት ቃላት ሱዳን ሱዳናዊ ሱዳናውያን» በሚል የቃል ትርጉም ተተክቶ ሲለወጥ፤ በሌላ በኩል ደግሞ [አሪት ዘፍጥረት ፪፡፲፫] ዐባይ ከኢትዮጵያ ወይም ከኩሽ ይነሣል የሚለው ዐረፍተ ነገር ማለትም የሁለተኛው ወንዝ ስም ግዮን ነው እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከባል የሚለው ወደ ሱዳንነት ሳይለወጥ በሐዲስ ኪዳን [በግብረ ሐዋርያት ፰፡፳፯] ኢትዮጵያ የሚለው በብሉይ ኪዳን እንደተነገረው ወደ ሱዳንነት ሳይለወጥ መተው ነው።

የአሜሪካ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ኢትዮጵያን ሱዳን ለማለት የተነሣበት ምክንያት ግልጥ ሆኖ ሊታይና የታሪክም ሆነ የምርምር መሠረት ሊገኝለት አልቻለም። ስለዚህ ሁኔታው በእንጥልጥል ላይ የሚገኝ ጥያቄ ሆኖ ነው የሚታየው ቢሆንም አንባብያንን ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ ይመራል የሚል ስሜት ስለሚፈጥር የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበርና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቅዱስ ሲኖዶስ ይህን በመጽሐፍ ቅዱስ ይዘት ትርጓሜና ታሪክ ላይ ያልተመሠረተ አዲስ መጥ ከሥተት በመቃወምና ሁኔታውም ወደ ትክክለኛው ታሪካዊ ቦታው እንዲመለስ ለማድረግ ከዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ጋር በተደጋጋሚ ደብዳቤዎችን መለዋወጥ ግዴታቸው ሆኖ ነበር።

ማኅበሩም ለተጻፉለት የተቃውሞ ደብዳቤዎች በመጀመሪያ የቀደመውን የተዛባ ትርጉም ለመለጠት ከተደረጉት መከራዎች በቀር በዕብራይስጥ ኩሽ የሚለው ቃል የዛሬውን ሱዳንንና የዛሬይቱን ኢትዮጵያ የሚያጠቃልል በመሆኑ ኢትዮጵያ የሚለውን ሱዳን ብሎ መተርጎም የተሳሳተ መሆኑን ስለተገነዘበ ወደፊት በዚህ ዓይነት መልክ እንዳይታተም ለማድረግ ወደ ስምምነት ላይ የተደረሰ ስመሆኑ በሰጠው መልስ አረጋግጧል።

ነገር ግን በዚህ ዓይነት ትርጉም የተዛባው መጽሐፍ ቅዱስ <u>ጉድኒውስ ባይብል</u> በመላው ከፍላተ ዓለም የተሰራጨ እንደመሆኑ መጠን በሚሊዮን በሚቆጠሩ ሰዎች ዕጅ የገባና የተሳሳተ ግንዛቤን ያስጨበጠ መሆኑ አያጠራጥርም። ... ስለዚህም በዚህ ትርጉም የተሳሳተ ግንዛቤን ስጨበጡና ወደፊትም ስሚያሰጋቸው አንባብያን ትክክለኛውን ታሪክ ለማስረዳት ይህን አጭር መልእክት ማስተላለፍ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ይህ ከፍ ብሎ በዝርዝር የቀረበው ቤተ ክርስቲያኗ ያደረገችውን ጥረት ለማመልከትና በዚሁም ውሳኔ መሠረት ይህን ከላይ ተደጋግሞ የተጠቀሰውን መጽሐፍ ቅዱስ እንዳይነበብ ቅዱስ ሲኖዶስ አረጋግጧል። ስለዚህ ኢትዮጵያን በጦርና በመርዝ ጢስ ያለመጥፋቷን ሲያረጋግጡ በሚጎዱበት መንገድ ሁሉ ያለማረፋቸውን ከዚህ ድርጊታቸው በሠፊው መገንዘብ ችለናል። ኢትዮጵያውያን እንደሚሉት ሌባ ተይዞ ዱላ ይጠየቃል ወይ ነውና ይህን በቤተ ክርስቲያናችን የተወገዘና እንዳይነበብ ውሳኔ ያለፈበትን መጽሐፍ በተቻለ መጠን ከኢትዮጵያውያን ዕጅ እንዲወጣ በሆነው መንገድ ሁሉ ጥረት ማደረግ የበኩላችን ሃይማኖታዊ ግዴታችን ነው። ይህ በማይታየው ጦራቸው ኢትዮጵያን መውጋትና መግደል መሆኑን ልብ ከሉ። ይህ አፈጻጸም ደግሞ ኦርቶዶክሳውያንን ብቻ የሚመለከት ጉዳይ አይደለም። ኢትዮጵያን የሚመለከት እንጂ! ስለዚህ ጉዳይ በመላ ኢትዮጵያውያን የጋራ ኃላፊነት መሆኑን ተገንዝበን ድርሻችንን እንድናበረክት ኢትዮጵያዊ አደራ አለብን። በኢትዮጵያና በዓይን አሁንም ቀልድ የለም።

የተሠጣትም መልስ ይቅርታና ወደፊት በሚታተሙት መጻሕፍት ላይ እንደግምም ነው። መጠየቁም ራሱ አወቅንባችሁን ያረጋግጣል። የነገው ትውልድ በተለምዶ ይቀጥልና ነገ ከነገ ወዲያ ኢትዮጵያ የሚል ስም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኖሮም ተጽፎም አያውቅ መባሉ የማይቀር ነው። የዛሬ ትውልድ ግዮንን በ«ናይል» ለውጦ በሌለና ባልተጻፈ ነገር ላይ እነሱ ስሙን በቀየሩት ትውልዱ ተከትሎ ዛሬ ኢትዮጵያውያን ድርጅቶቻቸውን ግዮን ብሎ

በመጥራት ፈንታ «ናይል» ብሰው ሠይመውት የምናየው ነው። ጉዳዩ የጀመረው ቀስ በቀስ ነው። ነጋሪ ዓየሁ ባይ ተዉ ባይ እስከጠፋ ድረስ ከመጽሐፍና ከታሪክ ስማችንን እየፋቁና በሌላ እየሠየሙ ከሁሉም ውጭ ያደርጉናል። የዛሬው ትውልድ ከሳይ እንደጠቀስነው ናይል ማለት ትክክለኛ ስም እንደሆነ እንጂ ስሕተት መሆኑን ቢያውቅ ኖሮ የድርጅቶች መጠሪያ ባልሆነ ነበር። እነሱ በዚህ ተመክሯቸው ነገ ከነገ ወዲያ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ጨርሶ አልነበረችም ማለቱን የተየያዙት ጉዳይ ስለሆነ ስሟን ከገፀ ምድር ሳያጠፉት አርፈው አይተኙም። የጭካኔያቸውን ክብደት የምንመዝነው የእግዚአብሔር ቃል ነው እያሉ ከሚጠቅሱት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢትዮጵያን ሲያወጡ ምን ዓይነት ድፍረትና ይሉኝታ ቢስነት መሆኑን በዚሁ ብቻ መረዳት ነው። አሁን በመሆን ላይ ያለው በሬ ካራጁ ጋር ይውላል ነው። የምሳሌውን ትክክለኛነትና ገላጭነት የምንረዳው ሲፈፀም መሆን የለበትም። በቅድሚያ ጥንቃቄ እንድናደርግበት የቀረበ እውነተኛ ምሳሌ ነው። ከሆነ በኋላም ዘካሪም ነጋሪም አያገኝም። አብዛኛዎች የአፍሪቃ አገሮችን ያጠፋበት ሥውር ድምፅ የለሽ መሣሪያቸው ስለሆነ ብዙ ሕዝብና አገር አውድመውበታል። በተግባር ፈትነው እረጋግጠውበታል።

ቀደም ሲል በኢጣሊያ ወረራ ምክንያት ያን ያህል ጦርነትና ደም መፋሰስ እየተካሄደ እንኳን በነበረው ግንኙነት ኢጣሊያኖች ለለ ሮማ ከተማ ውበት በተናገሩትና በሰበኩት ተማርከውና ተታለው የልጆቻቸውን ስም የሮምነሽ ሮማን ብለው የሠየሙና የተጠሩ ኢትዮጵያውያንን እናውቅ የለምን? እንዲሁ እነሱ ይሉት የነበረውን የገበያ ቦታን ስም መርካቶ የሰንደቅ ዓላማችንን ስም ባንዲራ እያልን እስካሁን ድረስ የምንጠራ አለን አይደለምን? ምንም እንኳ መርካቶ እንዳይባል አዲስ ከተማ ተብሎ የተሠየመውን በተለምዶ በመተው አሁንም ሉቅ ሲከፈት መርካቶ ማለት ግዕዝ ወይንም ጉራጌኛና አማርኛ እንደሆነ ተወስዶ ሲሠይሙት እናያለን። ያውም በጠላት በፋሽስት ከተማ ስም ከየዋህነትና ከግንዛቤ ማነስ ምክንያት መሆኑ ነው። በዚህም ምክንያት በአሁኑ ሰዓት ብዙ የምናውቃቸው በሮም ከተማ ሞግሽነት የሚጠሩና የሚታወቁ ሮም፥ ሮማን፥ የሮም፥ የሚባሉ ሰዎች የሉምን? የንግድ ድርጅቶቻቸውንስ መርካቶ ናይል ያሉና የሚሉስ የሉምን? እኒህ ጥቂት ምሳሌዎች ናቸው። ዞሮ ዞሮ እናስተውል እንመልከት። አሁንም በአገርና በዓይን ቀልድ የሰም ነው።

ብዙ ጊዜ በዘልማድ ነገሮች መሥመር ሳይዙ ይቀሩና የሚያውቁት በማያውቁት ይተካካሉ ሲተላሰፉ በመቆየታቸው

በጊዜውና በወቅቱ ታርመውና ተስተካክለው ያልተቀመጡ ነገሮች ከጊዜው ብዛት ከትውልዱም ሽግግር መተካካት ጋር ባንድ ወቅት ችግር ያልነበረው እንደ ችግር ቀናው በመጥፎ ክፉው በበጎ ቦታ ተለዋውጦ ተወራርሶ ይገኛል። በዚያን ጊዜ ደግሞ የሚያውቀው አንሶ የማያውቀው በዝቶ ሲገኝ ምንም ምን ይሁን የድምፅ ብልጫ ያገኙና ያልሆነው ሲሆን የነበረው እንዳልነበር ሆኖና ቀጥሎ ይገኛል። ነገር ግን ያለመታደል ሆነና ምንም እንኳ አገራችንን ከጠላት አገዛዝ ወላጆቻችን ደማቸውን አፍስሰው አጥንታቸውን ከስክሰው በነፃነት ቢያቆዩንም ቅሉ በደካማ ጎናችን በኩል በተገኘችዋ ትንሽ ቀዳዳ ሁሉ ገብተው በርና መስኮት ከፍተውበት ከመስኮትም ሦስት አራት ከበርም ዋና በር የጓዳ በር ብለው መግቢያውንና መውጫውን አስፍተውት እናገኘዋለን። ለዚህም ምክንያት ሆኖ የነፃነታችንን ግድግዳ ያስነደለው ዘመናዊው ትምህርትና «ሃይማኖት የግል አገር የጋራ ነው» የተሰኘው አዋጅ ባይሆንም ዲስኩር ነበር። እኒህ ሁለት ነገሮች በሠራነው በር ባወቅነው መንገድ ሳይሆን እንደ ጨረር በተገኘው የግድግዳ ቀዳዳ ሁሉ በመግባት ነበር። ዛሬ አንዱና ክቡን ቤት ቅርፁን ሰቀላ ግድግዳውን ነዳድለው በርና መስኮት ብቻ አድርገውት የሚታየው። ይህም እንደ ሥልጣኔ ተወስዶና ተመልካች አግኝቶ ቦታ ይዞ ይገኛል።

በዚህም ምክንያት በሃይማኖት ስም ክፍፍል ይኸውም የሌሰውን እንዲኖር በቃል በመፍጠር የተሠራና የተድቦለቦለ የክፋፍለው ዕቅድ በተግባር ውሎ እያየነው ነው። የልጆች ማሳደጊያ ወተት ቦቅራ ሲሆን የእውቀት መናቀሪያቸው ደግሞ የውጭ አገር ትምህርት ሆነ። ስለሆነም የኛኑ ጥበብ መራራና ጎምዛዛ የማይቀመስ የእነሱን ግን ማርና ጣፋጭ አድርገው በማቅረባቸው የልጅ አእምሮ ነጭ ወረቀት ነውና የሠጡትን ከመቀበልና ከማያዝ አልተለየም። የወጣቶች ስሕተት ነው ባይባልም የወላጆች ግን ጥፋት ለመሆኑ መከላከያም አያስቆጥር። ይህ ከሆነ ዘንድ ከዘመናዊው ትምህርት ቤት የሚመረተው የተዘራውን ነውና ፈረንጅኛ አበባሉ አነጋገሩ አለባበሱ ታሪኩ ባሕሉ ወዘተ ... ሁሉ «እንደ ንጉሥ አጎንብሱ» ሆኖ ቁጭ አለው። ከዚህ የተመረተው ከእንድነት ልዩነት፥ ከማንነት ወደ ፈረንጅኛነት መለወጡ የግድ ሆነ። ከዚህ ጉዞ በኋላ ቋንቋዎቻችን ከመናገሪያና ከመግባቢያነት አልፈው ተርፈው ማደነጋገሪያ ሲሆኑ ወንዞቻችንም የሽንኩራ የበቆሎ የሽንኩርትና የተለያዩ አታክልት ወዘተ... ማብቀያነታቸውን ማለት የተፈጥሮ ባሕሪያቸውን ትተው ለኛ መከፋፈያ አጥር ሆኑን። እስካሁን የሚሠጡን አገልግሎት ይኸው ነው። ወደፊት ግን የወንዞቻችን አገልግሎት በርግጥ ይሰወጣሉ ወደ ጥንተ ተፈጥሯቸው ተመልሰው ለጓሮ አትክልት ማብቀያ ለልብሶቻችን ማጠቢያ ለምግቦቻችን

ማብሰያ በመሆን የሚያገለግሉበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ይመጣል በዚህ እንጽናናለን።

ይህም ሆነና ከምናየውና ከምንገነዘበው ጋልኛ ማለት ወንጀል እሮሞኛ ማለት ትክክለኛ እንዲሁም አማርኛ ማለትም የጨቋኝ የነፍጠኛ መነጋገሪያና ማስገደጃ ቋንቋ ነው ተብሎ በእኒህ በሁለቱ መነጋገሪያዎች ላይ በጥቂት ሩ ኢትዮጵያውያን ዘንድ የተለየ አመለካከት ተወስዷል። እንዲያው ጠብ ያለሽ በዳቦ እንደሚባለው ሆኖ ነው እንጂ ይህ አመለካከት ሸንደ ቁምነገር ተወስዶ ዋና የጥላቻ መግለጫ መሆን አልነበረበትም። ከሁለቱም ወገኖች ወይንም ቋንቋዎች ያልተዛመደና ያልተዋሐደ ኢትዮጵያዊ ፈልጋችሁ አምጡ ቢባል በመብራት እንኳ አይገኝም። ታዲያ አንዱ በሌላው ላይ የመወሰን መብት ማን ሰጠው? በጉልበት አውራው እኔ ነኝ። ወይንስ ለሰማዩ እኔ እቀርበዋለሁ? ጥናት ይደረግበት። ከዚያ ደግሞ ሕዝቡ ይወያይበት ይነጋገርበት ታጥቦ ይድረቅ ከዚያ ትክክለኛ የሚባለው ግንዛቤ ይወሰዳል። ይህ አስካልሆነ ድረስ ለምርምር ያልደረሱትንና እውነቱንም ፈልገው ለማግኘት የማይችሉትን ወጣቶች እጅግ ማደናገር ነው። ነገሩን ሁሉ በጉልበት አይሁን። በማስረዳትና በመግባባት ይሁን። በጉልበት የሆነ ነገር ሁሉ ዘለቄታው እጅግም ነው። ብዙም ሥር አይሰድ። የሚሆነው በብርጭቆ ውስጥ እንዳለ አበባ ነው። አምሮ የሚቆየው ለሳምንት ያህል ነው። ከዚያ ወዲያ የሚሆነውን እናውቀዋለን።

የገብረ ማርያም ጥርስ ተስብሮ የደበላ ጥርስ ይስቃል ማለትም ዘበት ነው። ከሳቁም ሁሉም ይሳቁ እንጂ አንዱ ሲያዝን ሌላው መሳቅ ከማኅበራዊ ኑሮ ሕግ ውጭ ነው። በዘፈን ቤት አይለቀስም። በልቅሶም ቤት አይዘፈንም። ይህ ደግሞ በትምህርት ቤት የሚጠናም አይደለም። አብሮ በመኖር ሁሉም እኩል የሚያውቀውና የሚገነዘበው ነው። በዚህ እገሌ ከእገሌ ይበልጣል አይባልም። የሚባል ቢኖር እገሌ ጨዋ ነው ባሕሉን ወግና ሥርዓቱን ያውቃል ይጠብቃል ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ እገሌ ክፉ ሰው ነው። ቂመኛና ተንኮለኛ ነው በመባል ይታወቃል። ከዚህ ውጭ ምንም ነገር የለም። መቸቻል መተጋገስ መረዳዳት አንተ ትብስ መበባል ታላቅ ኃላፊነት የተመላበት ኢትዮጵያዊነት ነው። የአብሮ መኖሩም ፈሊጥ ይኸው ነው። በዚህ አኗኗር የሺህ ዘመናት አመክሮ አለን ምሥጋና ለወላጆቻችን ይሁን። ከዚህ በተረፈ ደግሞ ጊዜ ይፈተዋል። ጊዜም ያስተካክለዋል። ጥርስ በጥርስ ዓይን በዓይን አይደለም። ግራ ጉንጭህን ሲመታህ ቀኙን ስጠው በሚለው በይቅርታ በመቸቻል በመግባባት ከአውነቱ ይደረሳል። ስለሆነም የተወለደ ሁሉ አያድግም። የታመመም ሁሉ አይሞትም። የኅለመሰ ይሸመግላል።

የሸመገለም ያረጃል ያረጀም ይሞታል። ይህ እውነት ነው። የተፈጥሮ ሕግ ነውና ነው። ለዚሁ አባባል ሁሉም ይሆናል ግን እስከሚያልፍ ያለፋል። ማጽናኛው ግን «ተገሀሥ እም እኩይ ወግበር ሠናየ።» [ክፉውን ትተህ በጎውን አድርግ] ነው።

ስለዚህ የተነግሁበትን ሳጠቃልል የአገራችን የኢትዮጵያ ቋንቋ አማርኛ ተብሎ ከሚታወቅ ይልቅ ኢትዮጵያውኛ ቢባል ትክክለኛና እውነተኛ ይሆናል። ይኸውም ስሙን በተግባሩ ገለፀ ማለት ነው። ቢያንስ ቢያንስ ጉዳት አለው የሚል ቢኖር ኢትዮጵያውያን አይደለንም የሚሉትን ገፍትሮ ያስወጣል። ለእነሱም «በማያድሩበት ቤት አያምሻቸውበት» ይሆንላቸዋል። ስም የሥራ መግለጫነቱን ይያዝ ነው አቤቱታው። እንደሚሆንም ርግጠኛ ነኝ። እንዴት ቢባል አበው እንደሚሉት ቸር ተመኝ ቸር እንድታገኝ ነውና ነው። ቀደም ሲል በመጽሐፌ ላይ ስለ ነፃነት በዓል አከባበር ከመጋቢት 28 ቀን ወደ ሚያዚያ 27 ቀን እንዲሸጋገር ኃሳብ አቅርቤ ነበር ተፈጽሟል ሆኗል። በኔ ኃሳብ አቅራቢነት ተደረገ ሆነ ለማለት ሳይሆን ስለ እውነቱና ስለ ትክክለኛነቱ ሌላውም ተመልክቶት ተፈፀመ ለማለት ነው። እንዲሁም በሌላው መጽሐፌ «ፀፀት» በተሰኘው ላይ እጅግ ቁጥራቸው የበዙ ተማሪዎች ለመምህርነት ሥልጠና የሚመለመሉት ከጎጃም ነበር። እነሱም ለሥልጠና የሚጎጓዙት ወደ ደብረ ብርሃን ሐረርና አሥመራ ነበር። ለምን ት/ቤቱን ማሠልጠኛውን ከዚያው ሠልጣኞቹ ካሉበት አይከፈትም? ብዬ ኃሳብ አቅርቤና ተመኝቼ ነበር። እነሆ አሁን የመምህራን ኮሌጅ ከደብረ ማርቆስ ተሠርቷል። ከዚያም አልፎና ተርፎ ዩኒቨርሲቲም እየተገነባ ነው። ስለዚህም ምኞትና አቤቱታ ተፈፀመ ይሏል እንዲህ ነው። ከዚህ ልምድ በመነሣት ነው አማርኛም የተግባር ስሙን አንድ ቀን ይይዛል የሚለው ተስፋዬ ጽኑ ነው ያልሁት።

ቀደም ሲል ስለ ግዕዝ ፊደላት አጎዝ አውስቻለሁ። የግዕዝ ቋንቋ የትንቢትና የራዕይ መተርጎሚያና ማስሊያም ነው ያልሁትን ለማመሣከር እነሆ ፊደላቱን እስከ አጎዛቸው ድረስ ከዚህ በታች ሠፍረዋል። የግዕዝ ፊደላት በቁጥር ሃያ ስድስት በአጎዝ ስምንት መቶ ናቸው። አያንዳንዱ ፊደል ቃሉ ተደምሮ የሚሠጠው የአጎዝ ውጤት ማንነትን ያረጋግጣል። ስለዚህ ትንቢቱ ደርሷል? አልደረሰም? ብሎ ለማረጋገጥ የግዕዝ ፊደል ፍቱን ነው። የምሥጢር መክፈቻም ቁልፍ ነው። እኒህ የግዕዝ ፊደላት አጎዞች በጥንቃቄ ሊያዙና ሊጠኑ ይገባል። ያለበለዚያ ሐኪሙን ግንበኛ ግንበኛውን ሐኪም ማድረግ ይሆናል። በአግባቡ ብንጠቀምባቸው እጅግ ተዝቆ

የማያልቅ እውቀት ሀብትና ንብረት አለባቸው። ለዚህ ሁሉ መፍትሔው ባሮሩ ግዕዝን ወደ ት/ቤቶች ማስገባት ነው። ሕፃናቱ እብረውት እየተጫወቱ ይደጉ ይመንደጉ። ከዚያ በኋላ ግንኙነታቸውን ወደ የነፍስና የሥጋ ዝምድና ከፍ ያደርጉታል ያዋሕዱታል። ስለዚህ የግዕዝ ፊደሎቻችን እስከነ አጎዛቸው ሕፃናቱን ይተዋወቋቸው ይቆባቧቸው። እነሆ! ፊደላቱም በሚከተለው ሁናቴ ቀርበዋል።

፪. ፳፭ቱ የግዕዝ ፊደላት ስም መልክና መለያ ቁጥር

ክፍል ፩

ፊደላቱ					መለያ ቁጥራቸው		
ሀ	ሁ	ሂ	ሃ	ሄ	ህ	ሆ	፩
ለ	ሉ	ሊ	ላ	ሌ	ል	ሎ	፪
ሐ	ሑ	ሒ	ሓ	ሔ	ሕ	ሖ	፫
መ	ሙ	ሚ	ማ	ሜ	ም	ሞ	፬
ሠ	ሡ	ሢ	ሣ	ሤ	ሥ	ሦ	፭
ረ	ሩ	ሪ	ራ	ሬ	ር	ሮ	፮
ሰ	ሱ	ሲ	ሳ	ሴ	ስ	ሶ	፯
ቀ	ቁ	ቂ	ቃ	ቄ	ቅ	ቆ	፰
በ	ቡ	ቢ	ባ	ቤ	ብ	ቦ	፱
ተ	ቱ	ቲ	ታ	ቴ	ት	ቶ	፲

ክፍል ፪

ጎ	ጐ	ጒ	ጋ	ጔ	ጕ	ጘ	ጙ
ኀ	ኁ	ኂ	ኃ	ኄ	ኅ	ኆ	ኇ
አ	ኡ	ኢ	ኣ	ኤ	እ	ኦ	ኧ
ከ	ኩ	ኪ	ካ	ኬ	ክ	ኮ	ኯ
ወ	ዉ	ዊ	ዋ	ዌ	ው	ዎ	ዏ
ዐ	ዑ	ዒ	ዓ	ዔ	ዕ	ዖ	዗
ዘ	ዙ	ዚ	ዛ	ዜ	ዝ	ዞ	ዟ
የ	ዩ	ዪ	ያ	ዬ	ይ	ዮ	ዯ

ክፍል ፫

ደ	ዱ	ዲ	ዳ	ዴ	ድ	ዶ	ዷ
ገ	ጉ	ጊ	ጋ	ጌ	ግ	ጎ	ጏ፤
ጠ	ጡ	ጢ	ጣ	ጤ	ጥ	ጦ	ጧ፤
ጸ	ጹ	ጺ	ጻ	ጼ	ጽ	ጾ	ጿ፤
ፀ	ፁ	ፂ	ፃ	ፄ	ፅ	ፆ	ፇ፤
ፈ	ፉ	ፊ	ፋ	ፌ	ፍ	ፎ	ፏ፤
ፐ	ፑ	ፒ	ፓ	ፔ	ፕ	ፖ	ፗ፤

፫. የ፳፯ቱ ፊደላት ትርጓሜ

ሀ . ብሂል ህለዎቱ ለአብ እምቅድመ ዓለም።
ለ . ብሂል ሰብሰ ሥጋ እምድንግል።
ሐ . ብሂል ሐመ ወሞተ
መ . ብሂል መንክር ግብሩ ለእግዚአብሔር።
ሠ . ብሂል ሠረቀ በሥጋ።
ረ . ብሂል ረግዓት ምድር በቃሉ።
ሰ . ብሂል ሰብአ ኮነ እግዚእነ።
ቀ . ብሂል ቀዳሚሁ ቃል።
በ . ብሂል በትሕትናሁ ወረደ።
ተ . ብሂል ተሰብአ ወተሰገወ።
ኀ . ብሂል ኃያል እግዚአብሔር።
ነ . ብሂል ነሥአ ደዌነ ወጸረ ሕማመነ።
አ . ብሂል አአሩቶ ወእሴብሖ ለግዚአብሔር።
ከ . ብሂል ከሃሊ እግዚአብሔር።
ወ . ብሂል ወረደ እምሰማይ።
ዐ . ብሂል ዐርገ ሰማያተ።
ዘ . ብሂል ዘኵሎ ይእኀዝ እግዚአብሔር።
የ . ብሂል የማነ እግዚአብሔር ገብረት ኃይለ።
ደ . ብሂል ደመረ ሥጋነ ምስለ መለኮቱ።
ገ . ብሂል ገብረ ሰማያተ በጥበቡ።
ጠ . ብሂል ጠዐሙ ውታእምሩ
ከመ ጌር እግዚአብሔር።
ጰ . ብሂል ጰራቅሊጦስ መንፈስ ጽድቅ።
ጸ . ብሂል ጸጋ ወክብር ተውህበ ለነ።
ፀ . ብሂል ፀወነ ኮንከነ።
ፈ . ብሂል ፈጠረ ሰማየ ወምድረ።
ፐ . ብሂል ፓፓኤል ስሙ ለአምላክ።

ተመሳሳይ ድምፅ አላቸው ተብሎ ባንድ መልክ እንዲቀረጹ ወይንም ባንዱ ፊደል ብቻ እንዲወከሉ የተፈረደባቸው ፊደላት እንደሚከተለው ተለይተው ይጠራሉ ይታወቃሉ ይነገራሉ። ይህም ሲሆን የእያንዳንዳቸው ሕልውና ተጠብቆ መኖር ይገበዋልና አንዱ ከሌላው በአጠራርም በአጎዝም በስምና በመልክም ልዩ ነበሩ ናቸውም። ዛሬ ግን ምንም እንኳ መልካቸው ቢለያይም የጥንት ድምፃቸው ጠፍቶ በተመሳሳይ

ድምፅ ወይንም በአንድ ሰም ለሰምትጠሩ ከመካከላችሁ በአንዱ ብቻ እንድትጠሩ የሚል ፍርደ ገምድል ውሳኔ ይህ ትውልድ ለሰፈረደባቸው በይግባኝ ላይ ናቸው። ጉዳዩን በጥሞና ስንመለከተው አበበ ተብለው የሚጠሩት ሰዎች ያንዱ አበበ ንብረት የሁሉም ነው ብሎ እንደመወሰን ነው። የመብታችን ይጠበቅ ጩኸትም እነሆ እየተሰማ ነው። አቤቱታም እየቀረበ ነው። ባለፈው ወይንም በዚህ ትውልድ መብታቸው ቢጣስ እንድ ቀን ነፃነታቸውን ተጎፍጽፈው ወደ ጥንተ ክብራቸው እንደሚመለሱ ጥርጥር የለውም። የሊቃውንቱ ኃይል ማነስና መቀነስ ብቻ ነው የእኒህ ፊደላት ማንነት እየደበዘዘና እየጠፋ የመጣው። ሆኖም የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት አዘጋጆች ተፀፅተው ሲመለሱ አባቶች እንደሚሉት እውነትና ጢስ መውጫ እያጣም ነውና አንድ ቀን ወደ ጥንተ ክብራቸው መመለሳቸው አይቀሬ እውነት ነው። ይሁን እንጂ ለጊዜው በዚህ ትውልድ አንድና ተመሳሳይ ድምፅ አላችሁ ተብለው ባንድ ፊደል ብቻ እንዲወሰኑ የተፈረደባቸውና ስለተባሉት ፊደላት መልካቸው ስማቸውና አጎዛቸው እንደሚከተለው ተቀምጧል። አንድም ሦስትም ወይንም አንድም ሁለትም አይደሉም። የሥላሴ ርቀትና ምሥጢርም ፈጽሞ የለባቸውም። ልዩነታቸውን ከዚሁ መረዳት ይቻላል።

፬ . ዘመኑ የረሳቸውና ትውልዱ የናቃቸው ፊደላት መልክ ስምና አጎዛ

መልክ	ስም	አጎዛ
ሀ	ሃሌታው ሀ	አንድ
ሐ	ሐመሩ ሐ	ሦስት
ጎ	ብዙኃኑ ጎ	ሠላሳ
ሠ	ንጉሡ ሠ	አምስት
ሰ	እሳቱ ሰ	ሰባት
አ	አልፋው አ	አርባ
ዐ	ዐይኑ ዐ	ሰባ
ጸ	ጸሎቱ ጸ	አምስት መቶ
ፀ	ፀሐዩ ፀ	ስድስት መቶ

ይህን በመሰለ መልክና አጎዛ ተለይተውና ማንነታቸውን ጠብቀው ያሉትን ፊደላት እንዳፈነነ መጻፍ ማለት ጥንተ መዝገብን መሠረዝና መደሰዝ ወይንም እንደ ነፍስ መግደል የሚያስቆጥር ወንጀል መፈፀም ነው። የግዕዝ ፊደሎቻችን በአጎዛ የተቀመሩ ስለሆነ ያሰቦታቸው ማስቀመጥ ማለት በተራ አነጋገር ወንድ ልጅህን ለወንዱ ልጂ ሚስትነት ስጠኝ ብሎ እማላጅ እንደመላክ ነው። ምንም እንኳ ከተፈጥሮ ሕግ ውጭ በሚኖርበቱ ወቅቱ ወንድ ለወንድ ሴት ለሴት የሚጋቡበት ጊዜ ቢሆንም ቅሉ ምላሌው አይሠራም የሚሉ ቢኖሩ ተጠንቀቁም ለማለት ነው። ብዙ ተባዙ እንጂ ምክኑ ስለማይል ቃሉ ይህንኑ ዋቢ በማድረግ ነው። እንድ ጓደኛ ያለውን አስታወስሁ። አንድ ሰው በቅርብ ለሚያውቀው ጓደኛው ዋስ እንዲሆን ይጠየቃል። ተጠያቂ ሰው አይሆንም ይላል። ምነው ጓደኛህ አይደለም እንዴ? በዚያውስ ላይ ጓደኛህን እንደ ራስህ ውደድ ይል የለምን መጽሐፉ ተብሎ ሲነገረው የሠጠው መልስ ታዲያ እንደ ራስህ እንጂ ከራስህ በላይ ይላል ወይ? ሲል መልሷል። የሚገባኝን የፈለግሁትን ለማድረግ ማን አለኝ ከልካይ መሆኑ ነው። እንድ ሰው ማን አለብኝ ካለ ከኅብረተሰብ ትስስር ወጥቷል ማለት ነው። ማስጠንቀቂያው ከዚያ ዓይነት ሰው ይጠብቃችሁ ያድናችሁ ይሠውራችሁ ነው።

፭ . የግዕዝ አጻጻፍ ዕድገት

ስለ ግዕዝ ጥንታዊነት የሰው ልጅ አፍ መፍቻነት ቀደም ሲል ተናግረናል ጽፈናል ማስረጃም ሰበናል። ይሁን እንጂ ግዕዝ በቋንቋነት ብቻ ሳይሆን ቀዳሚነቱ በፊደልም በመቅረጽ ቀዳሚነት አለው። ለዚሁም የእያንዳንዱን የፊደል ትርጓሜ አቅርቧል። ብዙዎች የተሰማሙበትና ያረጋገጡት ጉዳይ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ እንኳ ምሥክር ቁጠር ከማያሰኝበት ደረጃ ላይ ነው ማለቱ ይቀላል። ይሁን እንጂ የፊደል መልኮች የአጻጻፍ ፈሊጦችን ስንመለከት ትልቅ አስረጅ ይሆናል። በቅድሚያ ግዕዝ ሲጻፍ በግዕዙ ፊደል ማለት በመጀመሪያው ብቻ ሆኖ ሲነበብ ግን በዝርዝር በድምፅ ሰዋዎች ታጅቦ ነበር። ይህም ማለት ያለ ሆሄያት ያለ አናባቢዎች ይጻፍና በአናባቢዎች ይነበባል ማለት ነው። ምሳሌ ነገሠ የሚል ቃል በመጀመሪያ ፊደሎች ተጽፎ ሲነበብ ግን ንጉሥ ይባላል። ይህ የሆነበት ምክንያት ጽሕፈት ሲጀመር የመጻፊያ ሠሌዳዎች በድንጋይና በሸክላ ላይ ስለነበር በመሮ በመቆርቆርና በመሰርሰር በመቅረጽ ሲሆን ምን ያህል ጊዜና ጉልበት እንደሚጠይቅ መገመቱ ቀላል አይደለም። ታዲያ ይህን የመሰለውን ችግር ለመወጣት

ይቻል ዘንድ በግዕዝ ፊደል ብቻ የሚጻፍ ሆኗል። ለምሳሌ የአስኳላ ተማሪ እንደሚገነዘበው በእንግሊዝኛ ተጽፈው የማይነበቡ ፊደሎች አሉ። ምሳሌ KNOW ይህ ቃል ሲነበብ ክኖው ተብሎ ሳይሆን ኖው ተብሎ ነው። እንዴት እወቅነው ቢባል በትምህርት ክኖው ብለህ አታንበው በመባል ተጠና ማለት ነው። እንደዚሁም ሁሉ በግዕዝ ማለት በመጀመሪያ ፊደል ተጽፎ ሲነበብ ግን በድምፅ መስማዎቹ ይነበባል ይህም የተገኘው በትምህርት ነው። በኋላ ግን የመጻፊያ ሠሌዳዎች በጻበሩና በተሻሻሉ ጊዜ እንጻሉ ለባቱም ሆሄዎች መጻፍ ቀጥለዋል። ይህን በዕድገቱ እናየዋለን።

ግዕዝ የመጻፊያ መሣሪያውን አሻሽሎ ወደ አንለሳት አዋንት ቅጠልና ወደ ዛፍ ልጥ ሲሸጋገር በእነዚህ ሠሌዳዎች ላይ መጻፍ እንዲያመቸው ከላይ ወደታች መጻፉን ትቶ እንደ ቅጠሉ ቅርጽ አቀማመጥ ዝግዛግ መጻፍ ቀጠለ። ይህ የአጻጻፍ ስልት ለግዕዝ ሁለተኛው የአጻጻፍ እድገቱ ደረጃ ነው። አስካሁን ድረስ በአጻጻፍ እድገቱ እብራይስጡን ግሪኩንና ሮማይስጡን ሁሉ ቀድሞ ይገኛል። ከዚህ በኋላ የመጻፊያ ሠሌዳዎችን ወደ ብራናና ወደ ሣንቃ ሲለውጥና ሲሸጋገር የአጻጻፍ ስልቱንም ለወጠ። በዚህን ጊዜ በእነዚህ የመጻፊያ መሣሪያዎች ሲጠቀም አጻጻፉን ከቀኝ ወደ ግራ አደረገ። በዚህ አጻጻፍ ላይ የቀጠሉት ወይንም በመጻፍ የተነሡት እብራይስጡና ዐረብኛው ይገኛሉ። ግዕዝ በዚህ አጻጻፍ ስልት ላይ እያለ በግዕዙ ፊደል ላይ ሲድስቱን ሆሄያት ማለት የድምፅ መስማዎችን መጻፍም ማንበብም ጀመረ። ሁሉን ማለት ንባብና ጽሕፍት ተባበሩ። በዚህ ላይ አላበቃም። ግዕዝ ከዚያ ከነበረበት የአጻጻፍ ደረጃ ተሻግሮ ከግራ ወደ ቀኝ መጻፉን ቀጠለ። ይህ ለግዕዝ የአጻጻፍ ደረጃው አራተኛ ነው። በዚህን ጊዜ ግሪኩና ሮማይስጡ ከዚህ አጻጻፍ ደረጃ ላይ ግዕዝ እንዳለ መጻፍ ጀምረዋል።

ይህም ግዕዝ በቋንቋ ብቻ ሳይሆን ቀጻሚነቱ በአጻጻፉም የመጀመሪያ ነው ያልነው ለለዚህም ነው። ይህን በበለጠ ደግሞ ለመረጻት የእብራይስጡ የግሪኩና የሮማይስጡ ወይንም የላቲኑ ፊደል ከግዕዝ መቀዳታቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሠንጠረዦች መመልከት ነው። ሦስቱም ገበታዎች የሚያረጋግጡት የግዕዝ ፊደላት ለተጠቀሱት ቋንቋዎች ፊደላት ምንጭ መሆናቸውን ነው። ሠንጠረዦችም እንደሚከተለው ሠፍረዋል። ዐይን ዓይቶ ልብ ይፈርዳል ነውና ራሳችሁ ምሥክሮችና ዳኞች እንድትሆኑ ተጋብዛችኋል። ጥንት ሊቃውንቱ አባትና ልጅ መሆናቸውን የሚያውቁበት ፊሊጥ ነበራቸው። አሁም ልጅ በምንም ታምር የአባቱን ጥፍር አክሎና መስሎ ይወለዳል። ታዲያ አንድም ከዕጹ ያሊያም ከእግሩ ጥፍር ላይ ወላጅ አባቱን ስለሚመስል አዋቂዎቹ በቅድሚያ የአባቱን ጥፍሮች አቀማመጥ በደንብ ከተመለከቱ

በኋላ የልጁን በማስተያየት ልጅህ ነው ወይንም አይደለም ብለው ይወስኑ ነበር። ይህም በዘመኑ የማወቂያ ፊሊጥ ነበር። ይህም ለሴቷ አድልተው ያልወለድሁትን ልጄን እንዳሳድግ አደረጉ የሚሉ ልጆ-ጠል አባቶች ማጉረምረም ሰላበዙ ከዚያም ላይ ሚስት ከቤት ሆና አጉራ ተዘሎ ስለሚወለዱ ምንም ልጃቸው ቢሆንም ቅሉ ከጋብቻ ውጭ ለጥቂቶች እንጂ ለብዙዎቹ ክብረ – ነክ ስለነበር አባት ወዶ የማይቀበለው ካልሆነ አይገደድም የሚል ሕግ ወጥቶ ሰው ሳያውቀው በምሥጢር ማሳደጊያ ይሠጡና ያሳድጉም ነበር። እናቶችም ሆኑ አባቶች በመጨረሻ እድሜያቸው ላይ ሲደርሱና እንደሚሞቱም ሲያረጋግጡ በኑዛዜያቸው ላይ አባቱ ዕገሌ ነው ሲሉ አባቶችም እሱ ልጄ ነው አካፍሉት አለጠጉት ብለው በኑዛዜያቸው ያጻድቁት እንደነበር የትላንትና ትዝታ ነው። በዚህ ላይ እንዳለን ነው ዛሬ ያውም አሁን በቅርቡ በደም ምርመራ [ዲኤንኤ] የአባትና የልጅ ዝምድና በግልጽና በሕግ ተቀባይነት ያገኘውና ማወቅ የተጀመረው።

ስለዚህ በሚከተሉት ሠንጠረዦች የሠፈሩትን የእብራይስጡን የላቲኑንና የግሪኩን ፊደላት ከግዕዙ ፊደላት መልክ ጋር በማነፀፀር እንድትመለከቱና እንድታረጋግጡ ከዚህ በመቀጠል እያንዳንዳቸውን በልዩ ሠንጠረዥ ተዘጋጅተው ቀርበዋል። በዚህን ጊዜ እንደ ወላጆቻችን እናንተም የፊደላቱን መልክ ቅርጽና አቋም ተመልክታችሁ አንተ የግዕዝ ልጅ ነህ ከግዕዝ የተቀዳህ ነህ እንድትሉ በዓይነት እነሆ! እንደሚከተለው ቀርበዋል። በነገራችን ላይ እኒህ የፊደላት ገበታዎች የተቀዱት አባ ተለሩ ሥላሴ ሞገስ ካቀረቡት ሠንጠረዥ ላይ ነው።

ሠንጠረዥ አንድ

ከግዕዝ የተቀጻው የዕብራውያን ፊደል ይህን ይመስላል።

5340 - 4250 B.C.	Eth.	1831 - 1500 B.C.	Heb.
FROM THE ETHIOPIC	ኧ or ት	TO THE HEBREW	א
FROM THE ETHIOPIC	ጋ.	TO THE HEBREW	ב
FROM THE ETHIOPIC	ጌ.	TO THE HEBREW	ג
FROM THE ETHIOPIC	ጎ.	TO THE HEBREW	ד
FROM THE ETHIOPIC	ኀ.	TO THE HEBREW	ה
FROM THE ETHIOPIC	ኘ.	TO THE HEBREW	ו
FROM THE ETHIOPIC	ኔ.	TO THE HEBREW	ז
FROM THE ETHIOPIC	ኸ.	TO THE HEBREW	ח
FROM THE ETHIOPIC	ሁ.	TO THE HEBREW	ט
FROM THE ETHIOPIC	ጋ፦ሊት	TO THE HEBREW	י
FROM THE ETHIOPIC	ካ. or ኃ	TO THE HEBREW	כ
FROM THE ETHIOPIC	ኌ or ኻ	TO THE HEBREW	ל
FROM THE ETHIOPIC	ዉ.	TO THE HEBREW	מ
FROM THE ETHIOPIC	ጎ. or ኀ	TO THE HEBREW	נ
FROM THE ETHIOPIC	ዐ.	TO THE HEBREW	ס
FROM THE ETHIOPIC	ፋ.	TO THE HEBREW	ע
FROM THE ETHIOPIC	ፈ. or ፐ	TO THE HEBREW	פ
FROM THE ETHIOPIC	ፋ.	TO THE HEBREW	צ
FROM THE ETHIOPIC	ቀ.	TO THE HEBREW	ק
FROM THE ETHIOPIC	ገ.	TO THE HEBREW	ר
FROM THE ETHIOPIC	ጠ.	TO THE HEBREW	ש
FROM THE ETHIOPIC	ኸ.	TO THE HEBREW	ת

ሠንጠረዥ ሁለት

ከግዕዝ የተመለደው የግሪኩ ፊደል ቅጅ

THE ETHIOPIA ALPHABET 4250 - B.C.	Eth.	THE GREEK ALPHABET HAVE BEEN TAKEN FROM THE ETHIOPIC 1100 - 900 B.C.	Grk.
FROM THE ETHIOPIC	ሀ ሐ	TO THE GREEK	Α Α
FROM THE ETHIOPIC	ለ	TO THE GREEK	Ϝ Ν
FROM THE ETHIOPIC	በ ዐ	TO THE GREEK	Β β
FROM THE ETHIOPIC	ገ	TO THE GREEK	Γ
FROM THE ETHIOPIC	ዘ	TO THE GREEK	Ζ
FROM THE ETHIOPIC	ሠ	TO THE GREEK	Ε
FROM THE ETHIOPIC	ደ	TO THE GREEK	Δ
FROM THE ETHIOPIC	ጠ	TO THE GREEK	Θ Β
FROM THE ETHIOPIC	ኀ	TO THE GREEK	Ι ι
FROM THE ETHIOPIC	ለ	TO THE GREEK	Λ
FROM THE ETHIOPIC	ሐ	TO THE GREEK	Η
FROM THE ETHIOPIC	መ	TO THE GREEK	Μ
FROM THE ETHIOPIC	ዐ ኀ	TO THE GREEK	Ο
FROM THE ETHIOPIC	ፐ	TO THE GREEK	Π
FROM THE ETHIOPIC	ፀ	TO THE GREEK	Ρ
FROM THE ETHIOPIC	ሠ	TO THE GREEK	Σ
FROM THE ETHIOPIC	ተ	TO THE GREEK	Τ
FROM THE ETHIOPIC	ፈ ፘ	TO THE GREEK	Φ φ
FROM THE ETHIOPIC	ሀ	TO THE GREEK	Υ
FROM THE ETHIOPIC	ኀ	TO THE GREEK	Χ
FROM THE ETHIOPIC	ሐ	TO THE GREEK	Ψ
FROM THE ETHIOPIC	ዐ	TO THE GREEK	Ω Ω

መንጠረዥ ሦስት

ከግዕዝ የተገኘው የላቲን ፊደል

THE ETHIOPIAN, 4200 B.C.		THE LATIN, 507 B.C.	
FROM THE ETHIOPIC ALPHABET	Eth.	TO THE LATIN ALPHABET	Lat.
FROM THE ETHIOPIC	ሀ ለ	TO THE LATIN	A A
FROM THE ETHIOPIC	በ ወ	TO THE LATIN	B
FROM THE ETHIOPIC	ቸ	TO THE LATIN	C
FROM THE ETHIOPIC	ሐ	TO THE LATIN	H
FROM THE ETHIOPIC	ኀ	TO THE LATIN	I
FROM THE ETHIOPIC	ነ	TO THE LATIN	L
FROM THE ETHIOPIC	መ ሜ	TO THE LATIN	M
FROM THE ETHIOPIC	ዐ ፈ	TO THE LATIN	O
FROM THE ETHIOPIC	ፐ	TO THE LATIN	P
FROM THE ETHIOPIC	ተ	TO THE LATIN	T
FROM THE ETHIOPIC	ኡ	TO THE LATIN	U
FROM THE ETHIOPIC	ሰ ቨ	TO THE LATIN	V
FROM THE ETHIOPIC	ሠ	TO THE LATIN	W
FROM THE ETHIOPIC	ኸ	TO THE LATIN	X
FROM THE ETHIOPIC	ኘ	TO THE LATIN	Y
FROM THE ETHIOPIC	ዘ	TO THE LATIN	Z

፮ . ከግዕዝ የተወሰዱ ቃላት ወአጎዛት

ሀ . ከግዕዝ የተቀዱ የአጎዝ ምልክቶች

በተለምዶ የዐረብኛ አጎዞች ተብለው የሚነገሩት አሥሩ የቁጥር መደቦች በቀጥታ ከግዕዝ ስመቀዳታቸው አሁንም መልካቸውንና ቅርፃቸውን ይመስከቷል።

፩ ፪ ፫ ፬ ፭ ፮ ፯ ፰ ፱ ፲

1 2 3 4 5 6 7 8 9 10

ግዕዝ እንደ ስሙ ትርጓሜ የሰው ልጅ አፍ መፍቻ የመጀመሪያ ቋንቋ ነው። ስለሆነም ቀዳሚ ስሞች አወጣጣቸውና አሠያየማቸው በግዕዝ ነው። ይህም በመሆኑ ድጎረ ግዕዝ የመጡ ፊደላት ከቀዳሚው መቅዳት ደንብ ነውና ብዙ ቃላት እንዳሉ ተወሰደው ለሌሎችም አገልግሎት በመስጠት ላይ ናቸው። የሚቀጥሉትን ምሳሌዎች ይመለከቷል።

ለ . ከግዕዝ የተወሰዱ ቃላት

ያሕዌ	ዘለዓለማዊ አምላክ / እግዚአብሔር [የሆባ/ጀሆባ]
ሃሌ ሉያ	ቅድመ ዓለም የነበረ አሁንም ያለ ወደፊትም የሚኖር
አዳም	ትርጉም እድ ወእም ወይንም ወንድና ሴት
አብርሃም	[አብ ዘ ሃም/ካም] ትርጉም የካም/ሃም አባት፣ የብዙዎች አባት ትሆናለህ። ትንግርት እንጂ የጥሬ ቃሉ ትርጉም አይደለም።
አሜን	ይሁን ይደረግ።
መና	ትኩስ ዳቦ አምባሻ ጎብስት ተሰፋ
ያም	ጣፋጭ ዕፅ ሥኳሬ ድንች።
ሦከር	ሥኳር ዕፀ ሦከር የሸንኮራ አገዳ
ዕፀ ቃውህ	ወይንም በዓለም ስሙ ኮፊ/ቡና በክፉ ክፍለ ሀገር በገፍ የበቀለ
ኤከሶን	የምድር ዘይት ወይንም ያሁኑ ቤንዚን።
ሰንበት	[ሳባት] ሰባተኛ ቀን ወይንም በአሁኑ አጠራር ቀዳሚት ሰንበት ወይንም በነጠላው ቀዳሚት/ቅዳሜ

ምሥጢር	ጥልቅ የማይመረመር በዓይን የማይታይ በዕጅ የማይዳሰስ፣
ዋው!	አድናቆት ቃለ አጋኖ!
ዬዬዬ!	ወዮ አያድርስ እግዚኦ ጡኽት ገዓር ሰቆቃ ልቅሶ
ላላላ!	እንጉርጉሮ ዘፈን
ዕልል	የደስታ መግለጫ
ዲያቆን	አገልጋይ ተላላኪ
አብ	አባት
እም	እናት
አንድ	ወይንም ኤንድ
ሰላም	ፍቅር ርጋታ
ዓየር	ሰማየ ሰማያት ሕዋ
መዚቃ	የመሣሪያ ድምፅ መዝፈኛ ማመሥገኛ
ቀኖና	ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ ውግዘት
ቆቅ	ዶርሆ የምትበላ አሞራ [Quail]
አምኒቲ	ርኅሩኅነት ደግነት ተስማሚነት ገር
ዱድ	ጓደኛ ጎረቤት ዘመድ ወዳጅ
ኖኅ	ፀጽታ መረጋጋት

ሐ . ትእምርት ወይንም ምልክት

«ወሀብኩሙ ትእምርተ ለእለ ይፈርሁከ ከመ ያምስጡ እምገፀ ቅስት ወይድኅኑ ፍቁራኒከ።» [ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው።] [መዝ. 59:4–5] እግዚአብሔርን ለሚወዱትና ለሚያመልኩት ሁሉ የመዳን ምልክት የማንነት መታወቂያ ይሠጣቸዋል። ይህም ይታወቅ ዘንድ ምልክት መታወቂያና መግለጫ ይሆን ዘንድ ሠጣቸው አበጀላቸው።

መ . አርባዕቱ ትእምርተ ቀመር [+ - x ÷]

እኒህ ምልክቶች ከኢትዮጵያው መስቀል ወይንም በአጠራሩ አንቅሕ ተወስደዋል። ቀደም ሲል እንደገለጽሁት ሁሉ የግዕዙ ፊደላችን የተ ሳብኡ ቾ አንቅሕ ተብሎ ይጠራል። እሱም የሰው ልጅ ምሳሌ ነው። ይህን የመጀመሪያውን የሰው ልጆች አባትና እናት የተፈጠረው እንጂ ያልተወለደው አዳም [እድ ወ እም] የሱ መግለጫ ነው። ይህን ፊደል ወይንም ምልክት ለስሌት መቀመሪያም ተደርጎ ተወስዷል። ምሥጢሩ እንዲህ ነው። ሁለት የሚሆነው አዳም ባንድነት መገለጹ የመደመር ምልክት ሆኖ ተወስዷል። ከርሱ ጎን

ወይንም አካል ከእድ እምን ቀንሶ ሔዋንን ፈጠረ። ይህም ምልክት – የመቀነስ ምልክት ሆነ። አጠራሩም የመቀነስ ምልክት ተብሎ ተጠራ። ቀጥሎም እኒህ በአካል ሁለት የሆኑትን አንደገና ብዙ ተባዙ ምድርንም ምልዋት በሚል ትዕዛዝ እንዲባዙ ሆኑ። የዚህም ምልክት X የማባዣ ምልክት ተደርጎ ተወሰደ። ከዚያም አዳም መሬት ነህ ወደ መሬት ትመለሳለህ። «አ አዳም መሬት አንተ ወትባቡ ውስተ መሬት» [አዳም ሆይ አንተ መሬት ነህ ወደ መሬትም ትመለሳለህ] [ውዳሴ ዘሠኑይ] ሲለው የሕይወቱ ፍፃሜ ሆነ። ይህም ምልክት + የማካፈል አሱም ቆሞ የነበረው የሰው አካል ወደቀ አጥንቱ ተሰባበረ ሥጋው በሰበሰ ደቀቀ ረገፈ። ምልክቱም የሚያሳየው ይህንኑ ነው። ስለዚህም ነፍስና ሥጋ የሚለያዩበት የሚከፈሉበት ሥጋ ወደ ምድር ነፍስ ወደ ሰማይ የምትወጣበት ምልክት ስለሆነ የማካፈል ምልክት [÷] ተደርጎ ተወስዷል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ይህም ምልክት ተ በሌላ አገላለጽ የማዕዘናተ ዓለም ምልክትም ነው። እሱም ይህን ይመስላል።

ሰሜን

ምዕራብ + ምሥራቅ

ደቡብ

ይህን ምልክትም የማዕዘናተ ዓለምም መግለጫ ነው። ምሥራቅ መወለድ ወደዚህ ዓለም መምጣት ሲሆን በዚሁ አቅጣጫ ያለው ክፍል ደግሞ ምዕራብ መግቢያ ማለት ጎልፈት በሞት የመለየት ምሳሌም ነው። ሰሜኑ የቀኝ ጎን ደቡቡ ደግሞ የግራ ጎን ምሳሌያት ናቸው። ከዚሁ ጋር አብሮ ተደርቦ የሚሄደው ምልክት ደግሞ ይህ X ምልክት ነው።

ሠ . ትእምርተ ፈቲው X

እሱም በአጠራሩ ትእምርተ ፈቲው ይባላል። ብዙ ተባዙ ምድርንም ምልዋት የሚለው ቃል መሰያ ነው። በነገራችን ላይ ፍቅር በሦስት ይመደባል። ፍቅረ እግዚአብሔር ፍቅረ ሰብእና ፍቅረ ቢጽ ይህም ፍቅረ ፈቲው ነው። ቢጽ ሲል የወንድና የሴትን ግንኙነት የሚያረጋግጥ ነው። እኒህም በአሥርቱ ቃላት ተጠቃለዋል። እነሱም በፍፁም ልብህ እግዚአብሔርን አምልክ፣ አናትህንና አባትህን እከብርና አታመንዝር ማለት በአንድ እርጋ ማለት ነው። እኒህ እንደተጠበቁ ሆነው የማዕዘናት ምልክቶችም ሆነው ያገለግላሉ። እንደ ግዕዙ አጠራርና አሠያየም ቀዳሚ ቋንቋ ነውና መሥዕ ዓዜብ

ሊባ ወባሕር ብሎ ሲጠራቸው ሌሎቹ ግን በትርጉም ስለወሰዱቸው መስዕን ምሥራቃዊ ሰሜን አዜብን ደቡባዊ ምዕራብ ሊባን ደቡባዊ ምሥራቅና ባሕርን ደግሞ ስሜናዊ ምዕራብ ተብለው ይታወቃሉ። ይህም ከላይ እንደተገለፀው የብዙ ተባዙ ምሳሌ ነው። ይህን ዓርማ ለቦታም አቅጣጫ ማመልከቻ ብቻም ሳይሆን ምሥጢራዊ ምልክትም እንደሆነ ተደርጎ ተወስዷል። ከፍተኛ የሆነ የአቀማመጡ ምሥጢር አለው። ዋና ከተማቸውን ሲሠሩ ወይንም ድንኳኖቻቸውን ሲተክሉ ወይንም ሀብት ንብረት የጦር መሣሪያ ሲያስቀምጡ በዚህ አቅጣጫ ነው። ምክንያት በቀላሉ ጠላት አይደፍረውም። ለጠላት አይመቸውም ነው። ለምን ቢባል ቀማኛ ሌባ በጠቅላላው ጠላት የማያገኘው ለማድረግ የፈለገውን ላለማግኘት አያስችልም የሚያሰኝ ምክንያት አለውና ነው።

ስለዚህ የእነዚህን ምልክቶች ምሥጢር ያገኙት ሁሉ ተጠቅመውባቸዋል። ይህንኑም የኔቶ የጦር ቃል ኪዳን ዓርማ አድርገውት ይታያል። የአሜሪካ የመከላከያ ጽ/ቤት ወይንም ፔንታጎንም ዓርማው አድርጎታል። እንዲሁም የአሜሪካን ዋና ከተማ ዋሽንግተን ዲሲ በዚሁ የማዕዘን ምልክት አቅጣጫ እንደ ጥንታዊ ኢትዮጵያውያን ከተሞች ተቀይሷል። ይህን ሁሉ በሚገባ ያጤኗል።

በሌላ በኩል ይህ የ ተ ፊደል የመስቀል ምልክታችን ስለሆነም «መስቀል ኃይልነ መስቀል ቤዛነ መስቀል መድኃኒተ ነፍስነ» [መስቀል ኃይላችን ነው። መስቀል መበዣችን ነው። መስቀል የነፍሳችን መዳኛ ነው።] ብለን እንጠረዋለን። አንዲሁም በአካላችን ላይ የመስቀል ምልክት በምናደርግበት ጊዜ ርኩሳን መናፍስት ይሸሻሉ ብላ ቤተ ክርስቲያን ስለምታስተምር ወደ መቅደሱ ለንገባ «አአትብ ገጽየ በኩለምተናየ በትአምርተ መስቀል በስመ ሥላሴ» [በፊቴና በመላ አካላቴ ላይ በመስቀል ምልክት አማትባለሁ በሥላሴም ስም] ይባላል ይደረጋል። የመስቀል ምልክት ከተለያየ በሰውነት የአካል ክፍል ላይ እየተነቀሰ መለያና መታወቂያ ሆኖም ነበር። አሁንም አለ። ከግንባር ላይ ከዕጅ ላይ በአንገት ላይ ከደረት ላይ ወዘተ... እየተደረገ የመስቀሉ መግለጫ ሆኖ ይታያል። ከዚያም አልፎና ተርፎ በአንገት ጌጦች በዕጅ አንባሮች ላይ ከወርቅና ከብር የተሠሩ መስቀሎች የጌጥ ምልክትነታቸው የክርስትና ምልክትነቱን ወረዶታል። የሴቶች ቀሚስ በመስቀሉ ተጠልፎበታል። ከጎራዴው ከካራው ወይንም ከቢለዋው ላይ ሁሉ የመስቀል ምልክት ተዘውትሮ ይታያል። በቤት በሮች በአጥር ላይ ሁሉ በመስቀል ምልክት ተሠርተው ይታያሉ። በተለይማ ከመቃብር ቦታዎች ላይ የማይቀርና

የግድ የሚደረግ ሆኖ ይታያል። ምን ያህል በምልክት ላይ ያለንን ግንዛቤ ያመለክታል።

ይህን ሁሉ በጥቅሉ ለንመለከተው ጥንታዊነታችንን መስቀልን ከክርስትና በፊትም የሰው ልጅ ምልክት አድርገን አንገለገልበት እንደነበር ቀደም ሲል ተወስቷል። ፊደሎቻችንም የልዩ ልዩ ነገሮች መለያ መታወቂያና ምልክት ከዚያም መግለጫዎች ናቸው። ታዲያ ይህ ሁሉ የሚያመለክተው የሰው ልጅ ሥልጣኔ ጀማሪዎችና መሥራቾች መሆናችንን አንረዳለን። ስለ ምልክት ገና ብዙ በሠፊው እንወያያለን። የመስቀልን ምልክት ለሰው ልጅ ሥዕል መልክና ቅርጽ አድርገን መጠቀማችን ያስደንቃል። ከዚህም ለየት ብሎ የምናያቸው ምልክቶች አሉን። ከዚህ ውስጥ አንዱ አምሮት ወይንም ሽታ ወይንም ፈረንጆች የልደት ምልክት (Birth Mark) የሚሉት ነው።

ረ . አምሮት/ሽታ

አምሮት ሽታ ወይንም የልደት ምልክት ተብሎ የሚጠራው ምንድን ነው። በብዛት ሳይሆን አልፎ አልፎ አሁንም በአንዳንድ ሰዎች ዘንድ ይገኛል ይታያል። በተሰይ ይህ ዓይነቱ ምልክት በሩቅ ምሥራቅ ሰዎች ዘንድ የታወቀና የተለመደ ነው። አሁም አንድ ሕፃን ሲወለድ ከወገቡ ዝቅ ብሎ በጀርባው በኩል አረንጓዴ መልክ ያወጣል። ይህ ላንድ ሰው ብቻ ሳይሆን በሁሉም ሕፃናት ላይ ነው። ሆኖም ወደ ሰባት ዓመት ሲጠጉ የነበረው ምልክት ይጠፋል። በኛ አካባቢ ግን በተለይም በካም ነገዶች ላይ ምልክቱ ሲወጣ ማለት አብሮ የሚወለድ ነው። ይህ ምልክት ስላለበት ሰው ማንነት ገላጭ ሆኖ የቀረበ ነው። ይህም ማለት የሚነበብ ፊደል ወይንም ምልክት ይዞ ይወጣል። ለምሳሌም ያህል ጸነአ ማለት ጽኑእ ኃያል፣ ነገሠ ብሎ ንጉሥ ወዘተ... በምልክቱም ሆነ በንባቡ የሚተረጎም ምልክት ይዞ ይወለዳል። ይህን ምልክት የሚያነቡና የሚተረጉሙ አዋቂዎችም ነበሩ።

ስለዚህ ያ ሰው ማንነቱን መመረጡን ከራሱ አካል ላይ ይዞት ይወለዳል ማለት ነው። እንደ ምልክቱም ያ ሰው በሕይወቱ ውስጥ የሚሆነው ዕድል ተወስኖ ይወለዳል ማለት ነው። ይህን ምልክት እውነተኛነት የሚደግፍና የሚያረጋግጥ የማስረጃም አባባል እናገኛለን። ይኸውም «እለ ተጎርዩ እምከርሠ እሞሙ» [ከእናታቸው ማኅፀን ጀምረው የተመረጡ] ማለት ነው። ይህን ቃል ትንቢተ ኤርምያስ ላይ እንዲህ ሲል እናነበዋለን።

«የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ። በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ። ከማኅፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ። ለአሕዛብም ነቢይ አድርጌሃለሁ። እኔም ወዮ ጌታ እግዚአብሔር እነሆ እግዚአብሔር እነሆ ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም አልሁ። እግዚአብሔር ግን እንዲህ አለኝ። ወደምሰድድህ ሁሉ ዘንድ ትሄዳለህና የማዝዝህንም ሁሉ ትናገራለህና ብላቴና ነኝ አትበል። እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና።» [ኤር. 1:4--8]

ይህን አባባል በተለይም ጆን ካልቪን የፕረስፒቴሪያን ቤተ ክርስቲያን መሥራች በሚገባ የእምነቱ ዶክትሪን ማረጋገጫ አድርጎታል። ስለዚህም በመዋዕለ ዘመኑ ሀብታም የሆነ ሰው የመጽደቁ ዋና ምልክት ነው ብሏል። ይህም ትምህርት ለአሜሪካ ዕድገት መሠረት ጥሏል። ካፒታሊዝምም የተወለደው ከዚህ እምነት መግለጫ ሥር ነው። ስለዚህ ገንዘብ ማካበት የመጽደቁ ማረጋገጫ ተደርጎ ስለተወሰደ ለመከበር ሲባል የማይደረግ የማይፈጠር ነገር የለም። ይህም የዕድገትን በር የሥልጣኔን ግሥጋሴ ፈጥሯል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ይህ የአምሮት ምልክት ብዙ ምሥጢርና ጥበብ ያለው በመሆኑ ብዙዎች እንዲኖራቸው መሻት ጀመሩ። እሱን የሚተካ ሌላ ፈሊጥ የተፈጠረው ደግሞ ንቅሳት ከሰውነት ላይ ማድረግ ነው። ግማሹ ኃይለኛ ለመሆን ሲፈልግ የአንበሳ ምስል የዘንዶ ምስል የእባብም ሳይቀር በሰውነታቸው ላይ መንቀስ ቀጠሉ። ከዚያ አልፎ ተርፎ ደግሞ ከፊታቸው ላይ ምልክት ማውጣት ከዕጅ ላይ መነቀስን አስፋፉ። ዛሬ በኑብያ በሱዳን በሰሜን ኢትዮጵያና በደቡብ ኢትዮጵያም እስካሁን ድረስ በፊት ላይ የሚታይ ምልክት ነው። ከማንነት መታወቂያነት አልፎ ተርፎ የዓይንን ብርሃን ያጎለብታል ከተለያዩ በሽታዎች ይከላከላል የሚልም ልማዳዊ ሥራ ተሠጥቶት ሁሉም አድርጎት የሚታይ ነው። አመጣጡና አጀማመሩ ግን ከአምሮት/ከሽታ መነሻነት በእናት ማኅፀን ውስጥ መመረጥ ነው። እሱም የማንነት መግለጫነቱ ስለታመነበት ነው።

እንደገና አካል አበላሽነቱን በመረዳት ንቅሳቱን ከፊትና ከዕጅ ላይ መሆኑን አስትተው በጠልሰም መልክ ማለት በብራና ጽፈውና ሥለው በአንገትና በዕጅ ወደሚታሠር ምልክት ለወጡት። ይህንም በተግባር የምናየው መስጦመ አጋንንት መግረፌ ፀር ግርማ ሞገስ ክታብ ለሁሉም ሰው ይደረግ እንደነበር የትላትም የዛሬም እውነት ነው። በተለይም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ ኗሪዎቻችን ዘንድ ተዘውትሮ የሚደረግ ነው። ቀደም ባሉት ወላጆቻችን ዘንድ ይደረግ ነበር። እንደ ምሳሌም የምንወስደው በቅርቡ የዓፄ ቴዎድሮስን ክታብ የኢትዮጵያ ፓስታና መገናኛ ሚኒስቴር ቴምብር

አሠርቶበታል። ይህም ቴምብር በአሁኑ ሰዓት ገበያ ላይ ይገኛል። ጠልሰሙ እንደ ሁኔታው በተለያየ መልኩ ይዘጋጃል። ለልማነ ሰብእ ለግርማ ሞገስ ከሰው ሠራሽ አደጋ መከላከያ ግለት ከሚወረወር ጦር ከሚተኮስ አሩር ከመሳሰሉት ሁሉ ልዩና ምሥጢራዊ በሆነ መንገዱ መከላከያ ነው።

ይህንኑ ምልክትም በመንፈሳዊ በኩል የአጋንንት ማራቂያ የመንፈስ ቅዱስ ማቅረቢያ ቢሞቱ ማጽደቂያ ተደርጎም በአንገት ይጠለቃል በዕጅ ክንድ ይታሠራል። ቢሞቱ አብሮ ይገነዛል መቃብርም ይወርዳል። ይህ ዓይነቱ ክታብ ደግሞ መንፈሳዊ ነው በአጠራሩም ልፋፊ ጽድቅ ነው። ክፍሉ ብዙ ነው። ከዚህ ውስጥ ግን መንገደ ሰማይ ነፍስ ከለበሰችው ሥጋ ተፈታ ወደ ፈጣሪዋ ፊት የምታደርገውን ጉዞ የሚገልጽ ክፍል ሁሉ ያለው ነው። ይህን በተመለከተ በሌላ ክፍል በስፋት ይወሳል ያንኑ መመልከት ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞም የሚነገር ቢኖር ስለ ስም አወጣጥ ነው። ስም ይወጣ ከቤት ይከተል ጎረቤት ማለት እንደ ወላጆች ፈቃድና ፍላጎት ስም ይወጣል ከዚያም ጎረቤት ይቀበላል። ከዚያም የዚያ የባለ ስሙ መታወቂያና መጠሪያም ይሆናል። ይሁን እንጂ አንድ ሰው እንደ ኢትዮጵያዊ አሠያየም የሁለት ስሞች ባለቤት ይሆናል። አንዱ የዓለም ስም በመባል ሲታወቅ ሁለተኛው ደግሞ የክርስትና ስም ይሆናል። የዓለም ስም ሲወጣ እንደ ፊደሎቻችን አጎዝ መሠረት እንደ ሊቃውንቱ አሠያየም ወይንም እንደ ወላጆቹ ገጠመኝ ይጠራል። ስም ያንድ ሰው መጠሪያው ብቻ ሳይሆን የባሕርይውም መግለጫና መታወቂያም ነው። ለዚህም ነው ሊቃውንቱ «እስመ ስሙ ይመርኖ ጎበ ግብሩ» [ስሙ የሥራው መግለጫ ነው] የሚሉት። ስም የሥራ መግለጫና የማንነቱም መታወቂያ ስለሆነም የስም አወጣጥ ታላቅ ጥንቃቄ ሲያደርጉበት ይታያል። በስሙ ላይ የፊደሎች አጎዝም ወሳኝነት ስላለው የፊደሎችን ማንነትና ልዩነት ጠንቅቆ ማወቅም አስፈላጊ ነው። ለዚህም ነው ዕጅ በሏፈረ ቀለም በተነከረ መጻፍ እንደሌለበት አጠንክረን አያራ የምንለው። ፊደላቱ በቦታቸው ገብተውና አርፈው ካልተጻፉ መድፈሙን ማረሻ ማረሻውን መድፈ ማድረግ ይሆናል። የፊደሎቻችንን አቀማመጥና ማንነት በጥንቃቄ ሊጻፍ ይገበዋል። ባንዳንድ ባሕሎቻችን ደግሞ በተወለደበት የቀን ስም ይጠራል። ለምሳሌ እንደ ጋምቤላ ጎብረተሰብ ለዚህ ማስረጃ ነው።

እንዲሁም በኩናማ ጎብረተሰብ ደግሞ አናት ልጅ ስትወልድ በመጀመሪያ ባየችው እቃ ወይንም እንስሳ ስም የሚጠራ ይሆናል ይባላል። ይሁንና ስም የማንነት መለያ በመሆኑ አንዳንድ አዋቂዎች

የፊደሎቻችንን አጎዞች መሠረት በማድረግ ሕፃኑ የሚወለድበትን ቀን ብቻ ሳይሆን የሚፀነሥበትንም ዕለት አስበው አውጥተውና አውርደው የሚጠብቁ ነበሩ። ወደ ስም ስንመጣ ለሙን በጥንቃቄ የፊደላቱን አጎዞች ጠንቅቀው የሚያወጡ አሉ። እኒህም ወላጆች እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው እንጂ አልፎ አልፎ ይገኛሉ። ይህም የሚረዳው በስም አወጣጡ በንቅላቱና በክትባቱ የሚያደርጉትን ድካም ቀናኝነት ስላለው ነው። በእዲህ ዓይነቱ ጥንቃቄ የሚወለዱና የሚሠየሙ ሰዎች በአስተላለብ በምርምር አዲስ ነገር በመፍጠር በሕይወታቸው ውስጥ ቅድሚያ አላቸው። በጠቅላላው ብልሆች አዋቂዎችና ተመራማሪዎች ይሆናሉ። በሥራም ታይቷል።

አሁን አሁን የጥበቡ ባለቤትነት ከተሠረቀና ከጠፋ በኋላ ሆነና እየተረሳ መጣ አንጂ የሚታወቅ ተግባር ነበር። ከዚህ የተረፈውን ደግሞ በስሙ ሥያሜ ያስተካክሉለታል። እንደ ምሳሌም የሚታወሰው ስም አወጣጥ ላይ በቀጣይነት ወይንም የመንግሥት ሥልጣንን ለመረከቡ ብለው በመጀመሪያ ስማቸው ፊደል መሠረት ቀ ይነግሥ፥ ደ ይነግሥ፥ ኃ ይነግሥ የሚለውን የትንቢት ቃል መሠረት በማድረግ ስም አወጣጥ ላይ ብዙ የሚጨነቁና የሚሠይሙ ወላጆች እንደነበሩ የሚታወስ ነው። ከዚህ ላይ የማንረሳው ቢኖር የእነ ሆሜርንና የሄሮዶቶስን ስለ ኢትዮጵያውያን የጻፉትን ከዚህ ላይ ልብ ይሏል። ባለ ቅኔው ሆሜር እኒህ ኢትዮጵያውያን አማልክት ናቸውን? ወይንስ የአማልክት ወገኖች? ሲል የታሪክ አባት ተብሎ የሚጠራው ሄሮዶቶስ ደግሞ ስለ ኢትዮጵያውያን ደግነት ጠንካራነትና መልክ ቆጆነት እንዲሁም ባለፀጋነትና አድሚ ጠጋብነት የገለፀውን ከዚህ ላይ ግንዛቤ ውስጥ ያካትቷል። ሆሜር በኤልያድና ኦዲሴ ሄሮዶቶስ የፔርሺያ ጦርነት በተሰኙት መጻሕፍትን ጠቅሰው ሀጎስ ዓለማየሁ በሀገረ እግዚአብሔር 1994 ገጽ 43 – 44] ገልፀውታል። ይህን አባባል ከዚህ ያሠፈርሁት ምን ዓይነት ጠንካራ ተደናቂ ሀብታምና ጤናማ ትውልድ መኖሩን ለመግለጽ ነው።

ሰ . የዳዊት ኮከብ

[ሰውና እግዚአብሔር] ሰማይ ወምድር ምድርና ሰማይ አንድነት ግንኙነት ስምምነት ትስስርነትን የሚገልጽ ምልክት ነው። «ኢትዮጵያ ታበጽሕ ዕደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» [መዝ. 67:36] ኢትዮጵያ ዕጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች። ልመና ዋያቄ

ማቅረብ ሲሆን የተሠጠው መልስ ወይንም ኢትዮጵያ ጠይቃ ያገኘቻቸው መልሶች ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉት ናቸው።

አንደኛ፡ ወሀብኩሙ ሲሳዮሙ ለሕዝበ ኢትዮጵያ። የሚለውን እናገኛለን። [መዝ. 73:13]

ሁለተኛ፡ ነገሥታትዎችዋ ለመሢሁ ኢየሱስ ኮከብ እየመራቸው ሄደው ገፀ በረከታቸውን አቀረቡ። [ማቴ.2:2]

ሦስተኛ፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ለፊልጶስ ነገረው። ወደ ጋዛ ሄዶ ባኮስን እንዲያስረዳውና እንዲያጠምቀውም ተላከ። [የሐ ሥራ 8:26 - 39]

በኢትዮጵያና በእግዚአብሔር መካከል እጅግ ብዙ ብዙ ጉዳዮች ተከናውነዋል። ተፈጽመዋል። እኒህን ሁሉ ድርጊቶች እናያለን እናነባለን። ይህ ታላቅ ምሥጢር ነው። በአጠራር ብቻ የዳዊት ኮከብ በሚል ሥያሜ እናውቀዋለን። ስለዚህ በዚህ ኮከብ ምሳሌነት ኢትዮጵያና አምላክ ያላቸው ትስስር ማስረጃና መታወቂያ ነው። አስረጅነቱም ሰማይና ምድር አንድ ሆኑ ነው። «ሰማያት ይነግራ ስብሐተ እግዚአብሔር» [ሰማያት እግዚአብሔርን ያመሠግናሉ። መዝ.18:1] እንደዚሁም «ስብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር ለእጓለ እመሕያው ሥምረቱ።» [ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ። ሉቃ. 2:14]

ሸ . ትምእርተ ሰላም [ሲዋስቲካ]

ትእምርተ ሰላሙን ወይንም የሰላሙን ምልክት የጀርመኑ አምባገነን ሂትለር ሲዋስቲካ ብሎ ጠርቶታል። የሰላሙን ምልክትም ወደ ጥል ምልክትነት ለውጦት እናገኘዋለን። አሰሳሉንም አዛዙሮታል። ይህ ምልክት ሌላ አይደለም የአርባዕቱ አማልል ምልክት ነው። እኒህ ምልክቶች ቦገዕዙ አጎዝ ጌ ሰባቱ ነው። እሱም የተደራረቡ የሰባቱ አጎዝ ማለት ነው። አቀማመጣቸውም አንዱ ባንዱ ላይ ከምልክቱ እንደሚታየው ተደራርበው ነው። የሁለቱ ምልክቶች መገናኛ ላይ የመስቀል ምልክት ይገኛል። ይህም ማለት የሰው ልጅ ሰላም ድኅነት ፍቅርና አድነትን ማመልከቻ ናቸው። ሰውና እግዚአብሔር ሰላምና ፍቅር በአንድ ላይ የተጌጡበት የሰላም ምልክት ነው። ሰባት ቁጥር ሁልጊዜ ፍፁም ምሉዕ ነው። እንደ ሰባት ቁጥር በሥራ ላይ ውሎ የሚገኝ ምንም ነገር የለም። ሰባት የሰው

ልጅ ሥነ ፍጥረትን ዓይነት ያመለክታል። ሰባቱ የሳምንት ቀናት የሰው ልጅ መገልገያና የዕረፍቱ ቀናት ናቸው። ስድስቱ የሥራ ሰባተኛው የዕረፍት ማለት ነው። በትኩረት ስንመለከታቸው የግዕዙ አጎዝ ጌ ነው የዚህ የትእምርተ ሰላሙ ምልክት ሆኖ የቀረበው። ዋና መጠቀሚያና መዋቀሪያ ሆኖ ነው።

ምዕራፍ ሁለት

ስምዑ ዘንተ ኩልክሙ አሕዛብ
[(ጴንጤ መጤ) ይህን ስሙ። መዝ. 48:1]

የተከበራችሁ አንባብያን ሆይ! ጆሮዎቻችሁን አውሱኝ። ዓይኖቻችሁን አበድሩኝ። አቤቱታዬን እዳምጡልኝ እዩልኝ። ጉዳዩ እንዲህ ነው። ለዚች አጭር ጽሑፍ መነሻ ዋና ምክንያት ከሆኑኝ ጉዳዮች መካከል አንዱ እንደ ዋና ክፍል አድርጌ ያቀረብሁት ይህ ነው። በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምረው ከካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ራሳቸውን በመለየት በጀርመን ሉተር፣ በፈረንሳይ ካልቪን፣ በስዊዘርላንድ ዝዊንግሊንና በኋላም በአሜሪካ ራሱን አሻሽሎና አደራጅቶ የሦስተኛውን ክፍለ ዓለም ወጣት ዒላማ ያደረገ መርሀ ግብሩን በወጣቱ ሕይወት ላይ ያነጣጠረና የዘረጋ ሃይማኖታዊ ድርጅት ተቋቁሟል። እሱም በስም አጠራሩ የእንጠቆስጤ ሃይማኖትና በሌሎችም በተለያዩ ስሞች ይጠራል። ይህ ድርጅት አነግቦ የሚሄደውና የሚንቀሳቀሰው አንድ ትልቅ መጽሐፍ ነው። ስሙም ሳይለወጥ እንዳለ ሁሉም እንደሚጠራው «መጽሐፍ ቅዱስ» ይሉታል። ውስጡ ግን እጅግ አድርጎ ተበርዟል። ለእነሱ እንዲያገለግል ሆኖ ተስተካክሎ ታትሟል። ታዲያ ኢትዮጵያ የለችበትም ስሟ ተደምስሷል።

ይህን መጽሐፍ ሲያዩትና ሲመለከቱት ሰላማዊና መንፈሳዊ ይመስላል። ነገር ግን የአፍሪቃን ሕዝብ የሕይወት ታሪክ ባሕል ቋንቋ በጠቅላላው ማንነትን ጨርሶ ያወደመና እመድ ያደረገ የቅኝ ገዥዎች የጦር መሣሪያ ነው። ይህን ይዘው የሚዘዋወሩትም ድምፅ በሌለው መሣሪያ ስውን ሁሉ የሚማርኩና ማንነቱን የሚያጠፉ የተቃዋሚው/የዲያብሎስ ሠራዊት ናቸው። እንዲህ ሲያይዋቸው ዋሩ ዘመድና ወዳጅ ይመስላሉ። ነገር ግን «የዋህ እንስሳ ከአጥፊዎቹ ጋር ውሀ ይጠጣል» እንዲሉ ከወንዙ ምልስ የሚሆነውን እኛ ባንረዳውም ቅሉ እነሱ ግን በሚገባ ያውቁታል። ይሁን እንጂ እኛም ቢሆን ማወቅ ከፈለግን ታሪክ ደጎና አድርጎ ያስተምረናል። በእስያና በአፍሪቃ በተጠናከረ መልኩ የአካባቢውን ተወላጆች በመመልመልና በማሰልጠን በተለይም ወጣቱ ላይ ያነጣጠረ ዓላማ ይዞ ተወላጆችን በጋሻጃግሬነት እሠልጥኖ ያሠማራ ሃይማኖታዊ ውስጠ ምሥጢራዊ አዘል ድርጅት ነው። በአስባበሱ ካህን ስትርንቱ ግን እሳት የላሰ የጦር ሠራዊት ተወርዋሪ ክበብ ነው። በደንብ ካልተመለከቱትና ካላስተዋሉት በስተቀር ሲያዩት ሰው ይመስላል። በባሕርይና በተግባር

ግን ፍፁም የጮጨው ታላቁ ድብ ነው። በምድቡም የቃኤል ቡድን ነው።

መቼም ማንም በግልጽ እንደሚያውቀው ዓላማው ወጣቱን ትውልድ ከተሰያየ ብሔራዊና ሃይማኖታዊ ተውፊቱ በማላቀቅ የምዕራባውያኑን አስተሳሰብና ፍላጎት ለመጫን ነው። ስርጭቱን በዓለም ዙሪያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎችን በመክፈት ወጣቱን በእቡጥጥቱ የሚቀጥ ድርጅት ነው። ከዚያም አልፎ ተርፎ ኢትዮጵያ ውስጥ ሲገባ ክርስትና ባልደረሰባቸው የአገሪቱ ክፍሎች አንዲያስተምር ፈቃድ አገኘ። [የኢትይጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በሉሌ መልእኩ 1997 ገጽ 146 - 150] ትንሽ ቆሎ ይዞ ወደ አሻሮ ይጠጉ እንዲሉ ክርስትና ሳልደረሰበት ክፍል የምትለዋን የእሽታ ፈቃድ ይዞ ከዋና ከተማችን ሽመቀ። ክርስትና ያልደረሰበት የሚለው ምደባ ከቶ አልሠራም። ያማ ቀርቶ ሌላ ዘፈን መጥቶ እንዲሉ ያልደረሰበት የሚለው ኃረግ መሆኑ ቀርቶ ወደ ክርስትና ማዕከል ወደሚለው ተሰውጦ በዋና ከተማው ውስጥ ምሽጉን አደረገ። ከዚያም በከፋ መልኩ ከፍተኛ የመማሪያ ትቅዋሞች በር ላይ ቤት በመከራየት አዲሱንና ትኩሱን ኃይል ወጣቱን መያዝ ጀመረ።

ያን ለጋ አእምሮ ምሕንድስና ሕክምና ምርምርና ጥናት የሚያካሂድ ዊንቅላት ዓለም ከንቱ ናት በሚል ሰብክት የትምህርቱን ወጋገን አጨለመበት። ቤት ዘግቶ የሞተ ሳይኖር ማልቀስ ማስለቀስ፥ ያልታመመውን አሳምሞ ማዳን፥ ያልሞተውን ገድሎ ማዳን አናደርጋለን ትርዕይቱን ቀጠሰ። ትምህርታቸውን ያቋረጡ ከትምህርት ቤቶች የወጡ ወጣቶች በቀይ ቀለም የነደደ መጽሐፍ ተሸክሞ በየመንገዱና በየመንደሩ መንገላወድ የዕሰት ተዕሰት የብዙኃኑ ተግባር ሆኖ መታየት ጀመረ። እናቴ በዕንቁላሉ ጊዜ በገረፍሽኝ ሆኖ መታየትም ሆነ። በኔ ስም መከራ ይደርስባችኋል ትሰደባላችሁ ትገረፋላችሁ ብለው ስላስተማሯቸው የወላጆች ቁጣና ግርፋት ከተግሣፁ በፊት ቦታውን ስለያዘው የባሕርባፍ ለበቅ ግርፋት ለተገራፊው ሳይሆን ድካሙ ለገራፊው ወላጅ ሆነና አረፈ። በዚህ ዓይነት ካላማቸው የተፈናቀሉ የወጣቶች ብዛት ቤት ይቁጠረው።

ወጣቶቹ ከተሳቡባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች ሲኒማ መመልከት ኬክና ኮካ በነፃ መብላትና መጠጣት የመጫወቻ ቦታዎችን እንደልብ ማግኘት የመሳሰሉት ጥቂቶቹ ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ ሳይታመሙ ታመዋል የተባሉት ሲድኑ፥ ያልሞቱት

ሞተው ሲነሡ፥ ባልታወቀ ቋንቋ መናገር ሲሰማ አኔም እንደነሱ በሆንኩ ለልጆች መንፈሳዊ ቅናቶችን ፈጠሩባቸው። ይህን ሁሉ የተጠኑ ብልሃቶችን በለጋ አእምሮ ተቋቁሞ ለማለፍ ምን አቅም ተገኝቶ? ስለዚህም የተንኮል መረቡ በትጣለ ቁጥር ዕልፍ አዕላፍ ወጣቶችን ማጥመድ ትግባራዊ ሆነ። ማን ተቋቁሞ ይቻለው? ወላጆችም ከአቅም በላይ ስለሆነባቸው እሱ ያመጣውን ራሱ ይመልሰው ብሎ ከመጸሰይ በስተቀር ሌላ ምርጫ ጠፋ።

ከዚህ ላይ ግን ወላጆችና አዋቂዎች ሊገነዘቡት የሚገባ ጉዳይ አለ። አሱም ክርስትናን ለመቀበል ከመጀመሪያዎቹ አገሮች ውስጥ አንዷ ኢትዮጵያ ሆና ሳለ የክርስትና ቅራሪና ዓይነት ያለው ይመስል ክርስቲያኑን ክርስቲያን የሚያደርግ ቡድን ያስፈልጋል? ምንም እንኳን «ሃይማኖት የግል አገር የጋራ ናት» ቢባልስ ቅሉ ውሀ ቅዳ ውሀ መልስ ጨዋታ ማድረግ ይገባል? ይህን ለአውነተኛ ክርስቲያኖች ልተወው ልበልና ልቀጥል። ክርስቲያኑን ክርስቲያን የማድረግ ጨዋታ ለንት ገንዘብ እንደሚፈስበትስ ገምተን እናውቃለን? እጅግ ብዙ ብዙ ነው። ይህን መሰል ሥራ ከመሥራት እውነተኛ የክርስትና ሥራ ከሆነ ለንቶቹ ከት/ቤት ተፈናቅለው በየመንገዱ የሚዞሩ አሉ? ክርስቲያኑን ክርስቲያን ከማድረግ ይልቅ አራቱን መደቦች ቢያሰተምሩትስ! ስለ መሠረተ ጤና [ሀይጅን] እንዲያውቅ ቢያደርጉስ! ይህ ሁሉ ቀርቶ የባሰውን ስለ ዓለም ከንቱነት በሽታው ሁሉ በኢየሱስ ማመን የሚለቅ ከሆነ ዳቦ ሁሉ ተጋግሮ የሚቀርብ ከሆነ ሥራስ ምን ያደርጋል?

እነሱ ግን በአገራቸው በቤት ላይ ቤት ይሠራሉ ማለት ከፎቅ ላይ ፎቅ ያውም ሰማይ ጠቀስ ያንፃሉ። በቀን የሥራ ፈረቃቸው ሦስት ነው። ይኸውም ሦስት ጊዜ ስምንት ሃያ አራት ሰዓት እየሠሩ አየጣሩና እየጋሩ አገራቸውን እያለሙ ነው። በኢትዮጵያ ግን የኛን ወጣት ዓይኑን አስፈፍነው ሲያስለቅሱትና በማያውቀው ቋንቋ ሲያስላዝኑት ይውላሉ። በጸሎት በሽተኞችን ያውም በነሱ ጸሎት የሚፈውሱ ከሆነ በየአገሮቻቸው ቁጥር ስፍር የሌለው ሰንት በሽተኛ እያላቸው ምነው አልፈወሷቸው? እንደሚታየው ግን በየሠፈሩ ሆስፒታል እንደሠሩ ነው። እነሱ ዘንድ ያልፈወሰው ጸሎት ከኛ ዘንድ የፈዋሽነት ጥርስ እንዴት አወጣላቸው?

የሕክምና ጥበብ የሕክምና መማሪያዎችን ለራሳቸው በገፍ እያመረቱና እያስተማሩ ሰኛ ወጣት ግን በጸሎትና ዳቦ ቀርቶ ክብሪት በማያስገዛ ቋንቋ በማናገር ወርቃማ ጊዜውን በከንቱ ያሳልፉበታል። ይህንም የሚያስረዳ ቃል እንዲህ ሲል ቀደም ብሎ

ተጽፏል። ትንቢቱም «ወሰምዐ ልሣነ ዘኢየአምር» [ቢቆርጡት ቢፈልጡት የማያውቀውን ቋንቋ ያዳምጣል ይቀባጥራል። መዝ. 80:5] የትርጉም ማብራሪያው የግሌ ነው። እንግዲህ የራሱን የአባትና የእናቱን እምነት ይነቅፉበታል ይሰድቡበታል። ከዚህስ የበለጠ ምን ግፍ ምንስ ኃጢዓት ምንስ በምድር ላይ ወንጀል አለ? በሃይማኖት ስም ደረቅ ወንጀል ሲፈፀምስ ከማየት ወዲያ ምን በደል አለ? ይቅርታ የማይሠጠው የበደል በደል ነው። ለኢትዮጵያ ወጣት በሥራ እንዲያምን ማድረግ እንጂ በኢየሱስ ስም በታምራትና በድንቅ ሥራ ብቻ ሕመማንን መፈወስ የተራቡትን ማጥገብ ዓይነቱ ትምህርትና ሥልጠና ያውም በነሱ እኮ ነው። ድንጋዩን ዳቦ ነው ብላው ብሎ እንደ መስጠት ነው። ከፍተኛ ማታለል ነው። ከእግዚአብሔርም ጋር ማጣላት ነው። የሃይማኖቱስ መጽሐፍ የሚለው የማይሠራ አይብላ ነው።

እንድ ጊዜ ካለፈ የማይመለሰውን የወጣትነት እድሜ በዋዛና በፈዛዛ እንዲያሳልፈው ማድረግ ማለት መጽሐፍ ቅዱሱን እንደ ጠብመንጃ ሰባኪውን እንደ ገዳይ እድርጎ መላክ ነው። በዕጅ የየዛው መጽሐፍና የሰባኪው ቃል ለዘለዓለም ደሃና ለማኝ አድርጎ የሚያስቀር ነው። ያውም ለኢትዮጵያዊ የሃይማኖት ትምህርት እንዴት ተደርጎ? ይህ መቼም ይቅር የማይባል ታላቅ በደል ነው። ይህን ማድረግና መሥራት ያውም በኢትዮጵያዊ ወጣት ላይ የግፍ ግፍ ነው። ከዚህስ ወዲያ ጭካኔ ከዚህስ ወዲያ ኃጢዓት በምድር ላይ ምን አለ? በነፍላቸው ብቻ ሳይሆን ቀልዱ በሥጋቸው በሚራበውና በሚጠማው ላይም ነው። የዕለት ምግብ ለሌለውና ሥራ አጥቶ ለሚያንጓችር ወጣት ስለዚህ ዓለም ከንቱነት መስበክ የሚያየውና የሚያውቀው ያለበት ስለሆነ ይህንኑ መንገር ዓይንን በሾህ እንደ መጨቅጨቅ ነው። ያሊያም በችግሩ እንደ መሳቅና እንደ መቀለድ ነው። እንዲያውም ያልበላውን ማከክ ይሏል እንደዚህ ነው።

ኢትዮጵያዊው ኢትዮጵያዊቷ ወጣት ሆይ! ዕጆቻችሁንና እግሮቻችሁን በማይታይና በማይዳሰስ እግር ብረት አሥረው ዓይኖቻችሁን በነዊ ጨርቅ ጥቅጥቅ አድርገው ጨፍነው ጆሮዎቻችሁ ከነሱ ሌላ ድምፅ እንዳትሰሙ በስም ደፍነው ሰላላችሁበት ዓለም ከንቱነት እያበሠሩ ስለሚመጣው ዓለም ስለማታውቁት አገር ጀግና እንድትሆኑ ሲያዘጋጅዋችሁ ማየትና መስማት ማለት አጥንታችሁ ተለቅሞ ከማይገኝበት ገደል ላይ እንደጣሏችሁ ቁጠሩት። እወቁት ተገንዘቡት። ወርቃማውን ጊዚያችሁን በከንቱ አታስገድሉት። እንቢ አንጃ እሻፈረን በሏቸው ጥበብ ብትማሩና ብትቀስሙ ነው የሚበጃችሁ። የእነሱ ጸሎት ቤት የናንተ እሥር ቤት ነው። የምትጸድቁበት ላይሆን የምትከነኑበት ነው። ሃይማኖት አላችሁ።

ከናንተ ተርፎ ለልጅ ልጅና ለዓለም ሁሉ የሚበቃ ነው። የእነሱ የሃይማኖት ትምህርት ለእናንተ መርዝ እንደመጋት ነው። ከእነሱ ጸሎት ቤት በሄዳችሁ ቁጥር እድሚያችሁንና ሕይወታችሁን ከእላት ላይ እንደ ወደቀ ጅማት አኮማትራችሁት ነው የምትወጡት።

ወጣቶች ሆይ! ተማሩ ተመከሩ ወደ ማንነታችሁ ተመለሱ። የእነሱ ሃይማኖት መላ አፍሪቃን ያደኸየና የገደሰ እንጂ ያዳነ አይደለም። ዛሬ በዘርና በድንበር ጦርነት ላይ ተጠምዶ ያለው የአፍሪቃ ሕዝብ እንጂ አውሮጳውያን ዘንድ አሜሪካውያን ዘንድ ወይንም በጠቅላላው በነሮች እገሮች ዘንድ አይደለም። እነሱማ ሃምሳውን አገር ባንድ አስተዳደር ሥር ጠፍረው ይዘውታል። አሁን አንኳ ራሳቸውን በጋራ ለመከላከል የአውሮጳ አንድነት መሥርተው በጋራ እየመከሩ ነው። የኛኑ ግን እራትና እምስት ላይ እንደ ቡና ማፍያ ፍልጥ ይሠነጣጥቁታል። ይበታትኑታል። የውሻን ጥርስ በአጥንት ይፈሩ ከዚህ ላይ ነው። በአፍሪቃ ላይ የደረሰው በደል ከኛ ዘንድስ አልገባምን? የቱ የአፍሪቃ አገር ነው ጠላትን ተቋቁሞ በነፃ ያለና የኖረ? የራሱን ባሕልና ቋንቋስ ያላጣስ አገር ማን ነው? አፍሪቃውያን እንዲህ ይሉናል። እኛን ያያችሁ ተቀጡ። ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ሆይ! ተመለሱ ተመከሩ ወደ ማንነታችሁ ቅረቡሩ። ከመጥፎ ሥራዎቻቸው ተማሩ። በነፃነት ያለፍርሃትና ያለመንቀጥቀጥ እንድትኖሩ። ቋንቋችሁን ግዕዝን ተማሩ ተመራመሩ። የዓለም ጥበብ ሁሉ የተቀዳበት ቋንቋ ነው። የሰው ልጅ አፍ መፍቻም ነው። ይላሉ አፍሪቃውያን ወገኖቻችን፣ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ሆይ! ባታውቁበት እንጂ እንደኛ ማን የታደለ አለ? ከሞት በኋላ ሳይሆን በሥጋ እያለን በገነት ውስጥ እንድንኖር ኢትዮጵያን የመሰለ አገር በምድር ላይ ከኛ በቀር የተሠጠው ሕዝብ አለን? በዕጅ የያዙት ወርቅ ከመዳብ እኩል ነው ሆኖብን ነው እንጂ!

ለኢትዮጵያውያን ሃይማኖትን ማስተማር ማለት አበው እንደሚሉት «ልጅ ሰናቷ ምጥን አስተማረች» ነው። ወይንም ሌላ ተጨማሪ ምሳሌም «ሥራ ከምፈታ ልጄን ላፋታ።» ነው። የወጣቱን ሕይወት ደቂያማ አንካሳና እውር ማድረግ ነው። ስለ ኢየሱስ ብላችሁ በዚህ ወጣት በዕድሜው አትጫወቱበት። የወጣቶች አእምሮ ነዊ ወረቀት ነው። የሠጡትን ሁሉ የሚቀበል ነውና የማይነበብ የቀለም አተላ አትቸልሱበት። የኑሮውን የዓይን ብረትም አታፍሱበት። የሕይወቱን የጀሮ ታምቡርም አትንደሉበት። ብዙ ቤተሰቦችን የሚረዱ ከያኒዎችን [አርቲስቶችን] እግዚአብሔር የሠጣቸውን ፀጋ እንዳይጠቀሙበትና ዘመድ አዝማድ እንዳይረዱ አላደረጋችኋቸውምን? የናንተን የመረብ ሜራ ቆራርጠውና በጣጥሰው

ለመውጣት አቅም አጥተው እንጂ በእውኑ እግዚአብሔርን እያስደሰቱ ነውን? የተሠጣቸውን መክሊት እንዲቀብሩና እንዲጠየቁበት እያደረጋችኋቸው ነው። ሰውን መውደድ እግዚአብሔርን መውደድ ነው። የተቸገረን መርዳት ለእግዚአብሔር ቃል ተገዥና ታዛዥ መሆን ነው። በሙያቸው በቅድሚያ ዘመዶቻቸውን ከዚያም እናቶ አባት የሌላቸውን ሕፃናት የሚረዱ ሙዚቀኞች የሉምን? እጅጋያሁ ሺባባውን ወይንም «ጂጂን» ተመልከቱ። ለበጎ ሥራዎች ኮከብ ናት። በሙያዋ እግዚአብሔር በሠጣት ፀጋ መልሳ እግዚአብሔርን እያገለገለችበት ነው። የተራቡና የተጠሙ ሕፃናትን እየተንከባከበች ነው። እግዚአብሔር ይባርካት። እናንተማ ባለሙያዎቻችንን የባለፀጋ ለማኝ አድርጋችኋቸው መታየቱ ለኛ ለኛ ኃዘን ለናንተ ለናንተ ደግሞ የምሥራች ነው። ይህ ዓይነቱ አሠራር የምድሩን ሕይወት ያጨለመ የሰማዩንማ መንገድ እንዴት ያፈራርሰው? ያም ሆነ ይህ የምትጸድቅዋንና የምትኮነነዋን ነፍሳችሁን በጎረቤትነታችን እናውቃታለን። ሥራችሁን እንመለከታለንና! በቃ ሃይማኖት ያውም ፕሮቴስታንታዊ እምነት ለኢትዮጵያዊ ተቀበል አመን ማለት ያለውን ልብስ አስወልቃችሁ ራቁቱን በመሀል ገበያ በአደባባይና በአውራ ጎዳና ላይ እንደማበሄድ ነው። ይህም ዕይታ ለዚያ ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት እብደት ነው። ራቁቱን የሚሄድ እንደምናውቀው በራሱ በመንፈሱ የማያዝዝ ሰው እብድ በሽተኛ ነውና! ጤነኞችን በሽተኛ ዓይናማዎችን ዓይነ ሥውር እያደረጋችሁ ነው። ይህን ደግሞ የወር ደሞዝ የሚጠብቀው ሥጋችሁ ብቻ ሳይሆን ነፍሳችሁ በሚገባ ትመሠክርባችኋለች።

ይህ ሁሉ በደል ሲፈፀም ወላጆች ቢያዝኑም ቅሉ ተከባብሮ መኖር ያንዱን ዕምነት ሌላው ማክበር አለበት በሚለው መርኖ መሠረት ዝምታ ቢነግሥም ከትዕግሥት በላይ ሞልቶና ተርፎ እየፈሰሰ መውጫ መግቢያ ታጣ። እጸድቅ ብየ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች ሆነና ክርስቲያኑን ክርስቲያን ማድረግ ሥራ አስፈችነቱ እየታወቀ ዝም ቢባል የሆነው ጥንታዊቷን ቀዳሚቷን የእምነት ቤተ መቅደሷን የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ማጎሳቆልና መዝለፍ ከቤተ ክርስቲያን በማይገቡ ቃላት ያውም ወንጌል በተነበበበት አፍ ውስጥ አያፍ ነገር ማውጣት ምን ያህል ጌቶቻቸውን ቢተማመኑ ነው እንዲህ ላሊንጣቸውን የጣሉት ያሰኛል። ይህን መሳይ ካንድ የወንጌል ቃል ሰባኪ ከሚባሉ ሰዎች የጉድ ጉድ ሰድብ የሚወርደው? ዛሬ ዛሬ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የዕጅ መጥረጊያ ፎጣ አድርጋችኋታል።

ይህን መሳዩን ጉዳይ ነው አበው በምሳሊያቸው ሲናገሩ የመጀመሪያው ስሕተት ሁለተኛው ድፍረት ሦስተኛው ግን ንቀት ነው ያሉት። አሁን እንደምናየው ግን ከንቀት አልፎ ተርፎ አራተኛ ደረጃ ገብቷል። እሱም ማን አለብኝነት ሆኗል። ሁሉም ተከባብረው ክርስቲያኑን ክርስቲያን ማድረጉም እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ማንአለብኝነቱም እንዳለ ሆኖ ከዚህ ሁሉ አልፎ ተርፎም ቀኖነዋን ትምህርቷን ገዳማቷንና የመናንያኑን ኑሮ እጅግ በጣም ባጎሳቆለ ቋንቋ ከምሁራን ያውም መንፈሳውያን አስተማሪዎች ከዚያም በላይ ኢትዮጵያውያን በሆኑ ሰዎች በማይጠበቅ ዘለፋ ቤተ ክርስቲያናችንን ይሳደባሉ። በዚህን ጊዜ ግዴታ ሥልጣነ ክህነቱ ያላቸው በደሞዝ የሚያገለግሉት ብቻ መልስ ይስጡበት እነሱው ይጨነቁበት ብለን ዝም ብንል ክርስቲያናዊ ግዴታችንን አልተወጣንም ማለት ነው። በቁሰገበዝነቱና በቡራኬው ጣልቃ አንግባ እንጂ ይህንማ በሚመስለው ያገባናል። ያውም እንደ ጦር አንገታችንን በመሰበቅ ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በተለይም ለሙስሊሙ ለካቶሊኩና ለፕሮቴስታንቱ ዕንግዳ ተቀባይ ናት። ከዚያም በላይ ቤተ ክርስቲያኗን ማንቋሸሽ ማለት የኢትዮጵያን ዓይን በጋለ ብረት እንደመውጋት ነውና ዕጅ ይሰብስብ ከዚህ ላይ ነው በዓይንና በአገር ቀልድ የለም የምንለው።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በተለምዶ ጳንጠቆስጤ እየተባለ የሚጠራው ይኸው ምዕራባዊው የፕሮቴስታንት ቅርንጫፍ ሃይማኖት ተከታይና አገልጋይ የሆኑት በተለይም ራሳቸውን መጋቢ እረኛ ወይንም ፓስተር ብለው የሚጠሩት ኢትዮጵያውያን ራሳቸው ተሳስተው ሌላውን ለማሳሳት በደሞዝተኛነት የሚሠሩ የምዕራባውያን ተቀጣሪዎች ጥንታዊቷንና ብሔራዊቷን የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት አጉራ ዘለው፥ አምባ ደርምሰው በሚናገሩትና በሚበትኑት ጽሑፍ በአጠራሩ ጽርፈት፥ በተግባሩ ግን ጥፋት ያውም የመርዝ ጢስ ብዙ አማንያንን አፍነውበታል። እጅግ በጣም አድርገው አሠቃይተውበታል። ጎድተውበታልም። ይህ በደል ከደረሰባቸው ኢትዮጵያውያን ውስጥም የዚች ማስታወሻ አቅራቢ እንደ ኢትዮጵያዊነቱና ኦርቶዶክሳዊነቱ አንዱ ነው።

እኒህ የጳንጠቆስጤ ሠራዊት ያሉንንና የተመኙልንን እናስተውል። በየገዳማቱ ያሉትን ድርሳናት ገድላት መዘተ... መጻሕፍትን ይቃጠሉ ብለው ሰበኩ። የሚገርመው ግን ስብከታቸው ትንቢት ሆኖ ተቆጥሮ እንደሁ አይታወቅም ወይንም «ሆድ ያባውን ጌሾ ያወጣዋል» ነገር ይሁን ይህ በሚሰበክበት ጊዜ የቃጠሎውም ተግባር አብሮ በመፈፀም ተጠናቀቀ። የት ቢሉ መልሱ ደብረ ዳሞ

ገዳም ነው። ዕለቱን ለመዘክርም ቃጠሎው የተፈፀመው ነሐሴ ፲፫ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ. ም. ነበር። ይቃጠሉ ተብሎ ትዕዛዝ የተላለፈባቸው ንዋየ ቅድሳትና መጻሕፍትም የትንቢቱ ወይንም የምኞቱ ቃል አርፎባቸዋል። ለመሆኑ ለዚህ ዓይነቱ ቃጠሎ ተጠርጣሪ ቢፈለግ ማን ሊሆን ነው? እበውስ ሲናገሩ «በለፈለፉ ይጠፉ» እንኳ ባይሆን «ሚያ ባልሁ ፍየል ክፈልሁ» ግን አይታለፌ ነው። ስለ ቃጠሎው ጉዳይ ምርመራ ለያዘው ክፍል ማስረጃነቱ ያገለግል ይሆን? መቼም እንደምናውቀው «የአቦን ሰንደ የበላ ሳይጠይቁት ይለፈልፋል» አባባል የማይታለፍ ምሳሌያዊ አነጋገር መሆኑን ግን የተመልካች ልብ ይፈርዳል። [ዘመድኩን በቀለ *ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ* 1992 ገጽ 154 –155]

ለምን የእንጠቆስጤ ሥራዊት በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ አንሳራጎሩ? እርሷንስ ለመጉዳትና ለማጎሳቆል ለምን መከሩ? ዓይኖቻቸውንስ ለምን አከረሩ? ለምንስ ጣቶቻቸውን ቀሠሩ? «ብር ላበደረ ጠጠር፥ እህል ለእበደረ አፈር» እንዲሉ ብሉይ ኪዳንን በአምነት፥ ከርስትናን በተስፋና በትንቢት፥ ከዚያም በጥምቀት አምና ተቀብላና አክብራ ያቆየችና የኖረችን ቤተ ክርስቲያን መተናኩልን ምን አመጣው? በእውኑ ታቦትን አክብራና ጠብቃ በመያዝዋ ያስነቅፋታልን? ያሰድባታልን? «ንባብ ይቀትል ወትርጓሜ የሐዩ» [ንባብ ይገድላል ትርጓሜ ግን ያድናል።] የሚለውን ካለማስተዋልና ካለመገንዘብ እንጂ እንኳን የእግዚአብሔር ስም የተጻፈበትን፥ በደብተራ ኦሪት የእግዚአብሔር መገለጫ የነበረውንና የሆነውን ይህን ታቦተ ሕግ ለመንቀፍ ምን አሳሰባቸው? ምንስ አነሳሳቸው? ኧረ! ዋና ምክንያታቸው ምንድን ነው? ከዚህ ላይ መድራችሁ ያዙ። የመልሱ አመልካች ቀስት ያለ ከዚህ ላይ ነው። እንዲሁ ከመሃል ሜዳ ተነሥተው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ያየሁበትን ዓይኔን አመመኝ እንዲሁ አልመጣም።

በእነሱ ቤት የሙጀሌ ቁንጣ በሳጥን ይዘው ሲመጡ የሰውን እግር እያስበሱ ለማከም ነው። በሽታውን በቀኝ ዕጅ መድኃኒቱን በግራ ዕጅ ይዞ በሰላምና በጤና የሚኖረውን ሕዝብ ታምሃልና ላከምህን ምን አመጣው? በሽታውን ያመጣው እሱ አካሚ እሱ ታማሚው ግን እኛ፥ እየቀደዱ መስፋት አይደለምን? እኛው ታማሚ እኛው ታካሚ አልሆንምን? የመከራውና የጉስቁልናው መርገም ተሸካሚ ለምን ይህን ሕዝብ ያደርጉታል? ታዲያ ይህን የመሰለ ሥራ በሚፈጽሙብን ሰዎች ላይ ምን እናድርግ? የማያዳግም መልስ ቋሚ መልስ ግርግር የሌለበት መልስ መሠጠት አለበት። የኛ ሕዝብ መጫወቻ የኳስ ሜዳቸው አልሆነምን? ከዚህ ላይ እኮ ነው «በሞኝ

ቤት ሌባ ተማታበት» የሆነው። ብሉይ ኪዳንን ከክርስትና አሳምረንና አጥብቀን ከሁሉ በፊት ይዘን የኖርነውን ሕዝብ ትላንት ገና ከተመሠረተና የኢየሱስን ስም እንኳ በጆሯቸው የሰሙት ትላንት ገና መቶ ዓመት እንኳ አልሆናቸውም። ታዲያ ከኛ ቤት መጥተው ኢየሱስን ተቀበሉን ምን አመጣው። በኢየሱስ ስም ስለሚመጡት ገና አስቀድሞ ተጠንቀቁ ብሎን ነበር። ቃሉም «ውቁ ኢያስሕቱክሙ። አስመ ብዙኃን ይመጽኡ በስምየ» [ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ። ብዙዎች በስሜ ይመጣሉና ብዙዎችንም ያስታሉ።ማር. 13:5-6፡]

የኛም ሰዎች ቸልተኛ ሆኑ በጎቻቸውን ከደጅ ሳይሆን ከጉረኗቸው ውስጥ ከፍተው ማስወሰድን ችላ አሉ። በዚሁ እንዲቀጥሉ ፈቀዱላቸው። በጎቻቸውን የመጠበቅ አደራቸውንም ችላ አሉ። አሁን ዊራሹኑ ይባስ ብሰው ቤቱን ልቀቁልን አመጡ። ልጆቻችሁን ገብሩልን ሆነ። በአሁኑ ጊዜ የጸሎት ቤት ጉድጓድ ያልተቆፈረበት ሠፈር ለመሆኑ ይገኛል? ከዳቦ ቤቱ ቁጥር ይልቅ በእጥፍ የእነሱ መገኛ ዋሻ ጨምሯል በዝቷል። ይህ የጸሎት ቤት ጉድጓድ የምን መዋያና ማደሪያ ይመስላችኋል? በጎችን የሚበሉ ተኩላዎች ማደሪያና መከማቻ አይደለምን? ክርስትናን ለኢትዮጵያውያን መሰበክ ማስተማር እኮ! «ከባልሽ ባሌ ይበልጣል ሽሮ አበድሪኝ» ማለት እኮ ነው። በእውነቱ ከፍተኛ ንቀት ነው። ታላቅም ውርደት ነው። ይህን አይደለም የሚል ይኖራልን? ከልብ ካዘኑ እንባ አይገድም ነውና እንደ ክርስቲያኖች ቋንቋ እስቲ እንነጋገር። በእውነት ከልብ ለኛ የሚያስቡ ከሆነ ከጸሎት ቤት ይልቅ ት/ቤት ለምን አይሠሩልንም? መቼም እኛ የእነሱ መጽደቂያ ለመሆን ካበቃን። ሙጀሌ መጣ መድኃኒቱም ጠፋ። ታዲያ ሰው ሁሉ እግረ ሽፋፋ ሆኖ ቀረ። አንድም ቁምነገር አንዳችም ጥቅም አላየንም አልሰማንም እያደር መርዶ ነው። ጎበዝ በርህን ዘግተህ ተኛ። ግቢህን ሠፈርህን ጠብቅ። እኛ ኢትዮጵያውያን ኢየሱስን ከማወቃችንም ባሻገር የሴቶቻችን እንገት በወርቁ በብሩ ላይ የተሳለው መስቀሉ ነው። የቀሚሳቸው ጌጥ ጥልፍ ሁሉ በመስቀሉ የተሸቆጠቆጠበት ነው። ሌላው ቀርቶ ያንገቱ ንቅሳት መስቀል አለበት። ከዚያም አልፎ ተርፎ በግንባራቸው በዕጃቸው የመስቀል ንቅሳቱ በአጎቶቻችንና በአናቶቻችን ላይ የሚነበብ ነው።

ካህናቻችን መስቀል ከዕጃቸውና ከደረታቸው ተለይቶም አያውቅ። ወንዱም ሆነ ሴቱ የእግዚአብሔር ልጅነቱን ማረጋገጫ ማተብ በአንገታቸው አለ አድርገው ይውላሉ ያድራሉ። የጀግኖቻችን ጋሻ ጦርና ጎራዴ በመስቀል ጎረማ የተጌጠ ነው። የምግብ

ማቅረቢያው መሰቡ አምሮና ተውቦ የተጌጠው በመስቀል ኃረግ ነው። አንዲያው ሁለምተናው በጠቅላላው ከሕይወት እስከ ሞት መታገሮቻችን ሁሉ በመስቀል ምልክት የተጌጡ ናቸው። ታዲያ ለዚህ ሕዝብ ክርስትናን ሊያስተምሩት ይመጣሉን? ከእርሱ ይማራሉ አንጂ! ገንዘብ ተመስከ። ገንዘብ ገዛን። ረህባችን ጉድ አደረጎን። ኤሳው በምስር ንፍሮ ብኩርናውን አንደ ሸጠ ሁሉ ዛሬ አኛም ማንነታችንን በገንዘብ ሸጥን። እነሱም ገዙን። የሚሞተው ሥጋችን ማንነታችንን አሸጠን። ኢትዮጵያውያን ወገኖች ሆይ! ጽኑ ቆዩ። ወደማንነታችሁ ተመለሱ። እስቲ አንገቶቻችሁን በእግሮቻችሁ ሥር አድርጉና አስቡበት። ዳር ድንበሩን ታዩታላችሁ። ኢትዮጵያውያንን ክርስትና ለማስነሣት ከኢየሱስ ጋር ሊያስተዋውቁን ሰለ ኢየሱስ ሊነግሩን መጥተናል አሉን። ይህን ለማለት ለመሆኑ የሞራል የሥነ ምግባር ብቃት አላቸውን? እናስተውል እናስብ። አፍሪቃውያን ወንድሞቻችንንና አኅቶቻችንን አንመልከት። ከእነሱ እንማር። ኢየሱስን ካወቅነው ክርስትናን ከተቀበልን ሁለት ሺህ ዓመታችንን እነሆ አከበርን። ለእርሱ ምስጋና እናቀርባለን። እኛ እኮ ሰላምታችን በእግዚአብሔር ስም ይጀምራል እንደዚሁም ይጨርሳል። እንደምን አደርህ? አግዚአብሔር ይመስገን ነው። ቋንቋችን ልብሳችን ሰላምታችን ጌጣችን ከውጭ እስከ ውስጥ ያሉት እቃዎቻችን ሁሉ በእግዚአብሔር ስም ያጌጡና የተዋቡ የተመሉም ናቸው።

ታዲያ አኛን ነው ሰለ እግዚአብሔር የሚነግሩን? ከግንባራችን ያለውን መስቀል እንኳ መመልከትና ማየት አልቻሉም። «ዓይን ቦሙ ወኢይራእዩ እዝን ቦሙ ወኢይሰምዑ ዕድ ቦሙ ወኢይገሡ [ዓይን አያላቸው የማያዩ፥ ጆሮ እያላቸው የማይሰሙ፥ ዕጅ እያላቸው የማይዳስሱ ናቸው መዝ. 113:13-15] የተባሉት እነማን ናቸው? ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን እውቅናና ግንኙነት ግንዛቤ ውስጥ ያላስገቡትን ዛሬ መጥተው መውጫ መግቢያ የሚያሳጡንን የሃማኖት መለዮ ለባሾችን አይደለምን? ሕዝቡ ተውን ቢሳቸው ካባ ደርበው መስቀል አንግተው በድፍረት የናንተ ነን ይሉ ጀመር። የኢትዮጵያ ሕዝብ ስም ማውጣት ችሎታው ድንቅ ነውና «አርቶ ዱንጪ» ወይንም የአርቶዶክስ ጸንጪ ነን ባዮች ሲል ሠይሟቸዋል። እኒህ ሰዎች በኢየሱስ ስም በኃጣዌ መሢኅነት አሠቃዩን እጅግ በጣም ክፉኛ ተሠቃየን። እርስ በርሳችን አጣሉን ለያዩን። ባልና ሚስትን አፋቱ። ልጆቹን በረንዳ አዳሪዎች አደረጉብን። በቃ እንበላቸው። እነሱ ኢትዮጵያ ውስጥ ሊሠሩ ከፈለጉ መንገድ ይሥሩ። የውህ ጉድጓድ ይቆፍሩ። ውህን መገደብ በመስኖ መጠቀምን ዘመናዊ ከብትና ንብ ርባታን በመሳሰሉት ቢረዱን ደስ ባለን። ስለ ኢየሱስ ለመንገር ግን እኛ ቀድመናቸዋል። ፊልጶስን ይጠይቁት። የባኩስን

[የጃንደረባውን] ታሪክ በሚገባ ይመርምሩ ያጥኑ። [የሐሥራ. 8:26-39]

ስለዚህ በቃን በቃ ልንላቸው ይገባል። ከፈለጉ በርበሬ ይትከሉ። ቡና ያልሙ። ኮክ ያፍሩ። ጽጌረዳ ያብቡ። ስለ ክርስትናው ግን ተውት አያምርባችሁም። ሕዝቡንም ሥራ አታስፈቱት። በተለይም ወጣቶችን የነገ አገር ተረካቢዎችን በማንነታቸው በባሕላቸው በወጋቸው በማዕረጋቸው ይደጉ። ኢትዮጵያዊነታቸውን አትሸርሽሩባቸው። እናንተ እኮ አናንተማ አገራችንን ኢትዮጵያን ከምታስተምሩበት መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስሟን እያወጣችሁ እየጣላችሁ እንዴት እኛን ለማስተማር ከጀላችሁ? ታላቅ ድፍረት ነው። ለኛ ደግሞ አጅግ አድርገን መናቅ ነው። እንዲያው ምንስ ብንደኸይ ምንስ ብንቀጥን ጅግታችንን እንድንሰጣችሁ ትጠይቁናላችሁን? የጉድ ጉድ የንቀት ንቀት ነው።

አንተ ወጣት ኢትዮጵያዊነትህ ክዕንቁዎች ሁሉ ዕንቁ ነው። በማንነትህ ኮርተህ ሙት። ጥበብን ተማር እንጂ የሃይማኖትማ የቤትህ ምሰሶ ሁሉ የሃይማኖት ምልክት ያለበት ነው። የአባቶችህንና የአናቶችህን ሃይማኖት የታመመ የሚያድን የሞተ የሚያለማ ነው። ለአንተ ጥበብ መቅሰም እንጂ የውጭ ሃይማኖት አያስፈልግህም። አንተ እኮ ታላቅ የአግዚአብሔር ጀግና ትውልድ ነህ። አንድ ጊዜ በተአምር ክርስትና የተሠጠህ ንዑድ ክቡር ሕዝብ ነህ። ራስህን ጠብቅ ማንነትህን አወቅ። ላንተ ክርስትናን መስበክ ወርቃማውን ጊዜህን በከንቱ ሊያበላሹብህ ነው። ተውኝ በላቸው። የናትና የአባትህን እምነት ተረከብ። የሚያጸድቀው ምግባረ ሠናይ የተሳበሰው ፍፁም እውነተኛ ሃይማኖት አለህ ይበቃሃል። አግዚአብሔርን አመስግን። ወደ ትምህርትና ወደ ጥበብ ለመማርና ስመቅሰም አዘንብል። ካለህ ሃይማኖት ውጭ ጊዜህንና ማንነትህን የሚገድል ስለሆነ ተጠንቀቅ። በማንነትህ ኑር። የእነሱ ትምህርት ውጤቱ አይጥ የድመትን አፍንጫ እንደ ማሽተት ነው። ከዚህ ውጭ የሚጨመርም የሚቀነስም የለም። ለአንተም ከዚህ ወዲያ ምንም ምን የሚነገር የለም። ይሁንና አንድ አንቆቅልሽ ልነገራችሁ «የነበዝ ቤት ከፍቷን ውላ ከፍቷን ታድር።» ምንድን ናት? መልሱን ለየራሳችሁ ንገሩት።

ሌላ አንድ ኢትዮጵያዊ ምሳሊያዊ አባባል ላውጋችሁ። እንደምታውቁት በአገራችን ጅብ በላተኛ ነው። አህያ ደግሞ ተበይ ሆኗ ዘወትር ይነገራሉ። ታዲያ አንድ ቀን ጅቦና አህይት ካንድ ወራጅ ወንዝ ላይ ውሀ ለመጠጣት ይገናኛሉ። አጋጣሚ ሆኖ ጅብ ከላይ አህያ ከታች ሆነው ሲጠጡ ጅብ ገልመጥ ብሎ ያይና ለነገር

መጫሪያነት ስሚ አህይት ውህውን አታደፍርሽብኝ ይላታል። ምነው ጋሼ ጅቦ አንተ ያስህ ከላይ እኔ ያስሁ ከታች እንዴት አድርጌ ነው የማደፈርስብህ ትለዋለች። እሱም ቢሆን ምክንያት ፍለጋ እንጂ ነገሩ ጠፍቶት ስላልሆነ አደፈረስሽብኝ እኮ ነው የምልሽ ብሎ ጠቡን ቀጠለ። ውጤቱን ከጠቡ መነሻ ምክንያት መርምሩት። የሆነውንም ተረዱት። አሁንም ዝሁለት ሺህ ዓመት በፊት ንጉሥች ወይንም በወል ስማቸው ሰብአ ሠገል በኮከብ ተመርተው ኢየሱስ ከተወለደበት ቦታ ድረስ ተጉዘው ገፀ በረከት አበርክተው የተመለሱ ሰዎች ልጆችን ትላንት የተነሡ የሃይማኖት ድርጅቶች ኢየሱስን እናስተዋውቃችሁ ማለት ምን ፍለጋ ይመስላል? አይዟችሁ ወጣቶች ተመራመሩ አባቶቻችሁን ጠይቁ። ሃይማኖትን መለወጥ ማለት ሸንኮራ አገዳ መምጠጥ አይደለም። ማንነትን የሰውነትን አካል በሙሉ እንደ መለዋወጫ አቃ አውጥቶ መሸጥ ማለት ነው። ይህም ማለት ኢትዮጵያዊነትን ማኅበራዊ ኑሮን ባሕልን ቋንቋን ፊደልን መረዳዳትንና መተሳሰብን ሁሉ አውጥቶ መጣል ነው። ስለዚህ ራሳችሁን ጠብቁ በጣምም ተጠንቀቁ።

ከብሉይ ኪዳን ጀምረን ለሙሴ ልጃችንን ድረን ጽላተ ሙሴን ተቀብለን ይዘን አኑረን ያውም አከሱም ዘንድ አስቀምጠን እምነ ጽዮን አያለችን ከዚያ ጀምሮ አከብረን ይዘን የቆየነውን ታቦተ ሕግ አውጥታችሁ ጣሉትን ምን አመጣው? ሰጥሩ ምክንያት ይመስላልን? ውህውን አታደፍርሽብኝ ማለትን አይመስልም? አዎ ይመስላል። ስክርስትና እምነት ከኛ ወዲያ ቀራቢ የለውም። የኛ ካህናት በሕግ ፀንተው የሚኖሩ በከፍተኛ ሥነ ሥርዓት በአንብሮተ ዕድ የሚሾሙ ናቸው። ቤተ ክርስቲያናችን ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ ጀምሮ በመሰቀል ያጌጡ ስብሐተ እግዚአብሔር ሲነገርባቸው የሚውሉ የሚያድሩ ሦስት መቶ ስልሳ አምስት ቀናት ቅዳሴ ምሥጋናና ጸሎት አንደ በረዶ ሲወርድባቸው እንደ ጤዛቴ ሲፈስባቸው የሚኖሩ ናቸው። እንኳን ለሰው የዱር አራዊት እንኳ የሚመለክሩት አገልግሎት የሚሰጥባቸው አብያተ ክርስቲያናት ያሉንን ኢትዮጵያውያንን ከየሠፈሩ ቤት እየተከራዩ ዳንኪራና ልቅሶ ከሚካሄድባቸው ቤቶች ውስጥ ኢትዮጵያውያንን ማስለቀስ ሙሾ ማስወረድ እንኳን ሰውን እግዚአብሔርን እንኳ እንዴት ያስቆጣው? ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ተመለሱ ባላችሁ እምነት ጽኑ ያ በሉቃስ ወንጌል ላይ ታሪኩን ያነበባችሁትን ወጣት ታሪክ ልብ በሉ። ካባቱ የወሰደውን ገንዘብ ካጠፋ በኋላ አሪያ ጥበቃ ገብቶ ከርከሮዎች ከሚበሉት እንኳ በልቶ ለመጥገብ እስኪመኝ ድረስ እንደተሠቃየ ልብ በሉ። በኋላ ግን ወደ ወላጆቹ ቤት እንደመጣና የተደረገለትን አቀባበል ታውቁታላችሁ። [ሉቃ.15:11-32] ታሪኩን ስበስጠ ግንዛቤ

አንብቡት። ይህ ምሳሌ ስዛሬ ኢትዮጵያውያን የቀረበ እውነተኛ ምሳሌ ነው። የተሳሳታችሁ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ወደ እምነታችሁ ተመለሱ።

ታዲያ የዛሬዎቹ ክርስቲያኖች የትላንቱ ጣዖት አምላኪዎች አሕዛብ በየት በኩል አልፈው ሄደው ነው ጥንታዊቷንና ብሔራዊቷን ቤተ ክርስቲያን ስመቃወም የተንገዳገዱት። አአምሯቸው በጥፋትና በተንኮል ሥልጠና ደንገዘ የሚይዘውንና የሚጨብጠውን መለየት አቅቶት በሚያወዛናብረውና በሚያወላክፈው ህኬት የኢትዮጵያን ድኅነትና ማንነት ውስጥ ስውስጥ አንደ ምስጥ በሚነሪምዱት ምዕራባውያን ጌቶች ተልከው እንጂ! መልእክተኛ ወይንም «ሚሺነሪ» በመሆናቸው የመኖሪያ ሥራ ለማከናወን እንጂ! እነሱ እነማን ናቸውና! በአነጋገሩ፥ በአጠቋቆሩ፥ ቅብጥ ቅልጥ ያሉ ልሙጥ ቱባ ኢትዮጵያውያን አይደሉምን? የሚያሳዝነው ዓይንን ለማፍረጥ፥ ጆሮን ለመቁረጥ፥ አሱም የራሳችንን ማንነት እንዳንመለከት፥ ስለ ራሳችንም ሰምተን እንዳናውቅ የተደረገብን ረቂቅ ተንኮል ያውም ጥልቅ ጥልቅ ኢክርስቲያናዊ ባሕርይ ካለው ክፍል አንድነው እንጂ! በኢየሱስ ስም ሌላውን ጨርቃም ብለው እንዴት ይሳደባሉ? ይህ ራሱ የማንነታቸውን ባሕርይ እንደ ስማቸው ሥያሜ ሠይጣናዊነት ወይንም ፕሮቴስታንታዊ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። በነገራችን ላይ «ፕሮቴስታንት» ማለት በግሪኩና በዕብራይስጡ መዝገበ ቃላት ሠይጣን ወይንም ዲያብሎስ ማለት ነው። ስለዚህም ነው ስለማንነታቸውም በሠፊው የሚያረጋግጠው።

ከዚህ ላይ አንድ የአበው ትንቢታዊ ምሳሌያዊ ብሂል አለ። አንድ ኢትዮጵያዊ ገበሬ ያሳደገውን በግ ከመንገዱ ርዝመት ደክሞ ዋጋ አንዳይቀንስበት፥ እንዳይጎትተውም ተሸክሞ፥ ለመሸጥ ወደ ገበያ ይሄዳል። የበጉን ማማር ያዩ ሰባት ቀማኞች ተመካክረው፥ በአንድ ቃል ተስማምተው፥ ይህን ሰው የተሸከመኸው ውሻ ነው ብለን አሳምነን በጉን አናስጥለው ተባብለው ከተለያየ ቦታ በመንገዱ ላይ ሸምቀው፥ ሁሉም ባንድ ቃል ውሻ ተሸክሞ እንደሚሄድ ነገሩት ወተወቱት። ከሰባቱ ሦስቱን ውሻ ተሸክመሃል ሲሉት፥ በያዘው ዱላ ለመምታት ምንም አላመነታም። ነገር ግን ከአራተኛው ሰው ተመሳሳይ ቃል ሲነገረው በራሱ ላይ ጥርጥሬ አሳደረ። አምስተኛውና ስድስተኛው ሲነግሩት የተሸከመውን ከጫንቃው ላይ አውርዶ መጎተት ጀመረ። ከሰባተኛው ቀማኛ ላይ ሲደርስ እውነትም ልክ አይደለሁም ውሻ ነው የተሸከምሁት ብሎ ተታሎ ጥሎላቸው ሄደ ይባላል።

ትርጉም ሰባቱ ቀማኞች ከእነ አባ ማስያስ አበብን ካስገዛው ካቶሊካዊ አሳሳች ጀምሮ የኢትዮጵያ ጠላቶች ናቸው። ኢትዮጵያዊ ትውልድ ላይ መከራና ጉስቁልና እንደ በረዶ የሚያወርዱ ማንነቱን ያስጣሉበትና ያሳደገውን በግ እንኳ ውሻ ነው ባሉት አምኖና ተታሎ ባዶ ዕጹን የሄደበትን ይህን ትውልድ ማንነት ያመለክታል። ታዲያ ዛሬ የኢትዮጵያዊነት ማንነት፥ ፊደል፥ ቋንቋ፥ ታሪክ፥ ባሕል፥ ሃይማኖት መለያቢያ፥ መሳቂያና መሳለቂያ የሆኑበት ዘመን አይደለምን? የኛን ጥለን፥ የባዕዳኑን አንጠልጥለን ያለንበት ያ ትንቢት የተነገረለት ትውልድ ልጆች አይደለንምን? ለመሆናችንስ ከዚህ ወዲያ ምን ምሥክር ያስፈልጋል? ኢትዮጵያን ለማዳከም ሳይሆን እንዳልነበረች ለማድረግ ያልማሉ። ካለሙም ዘመናት አስቆጥረዋል። የሕልም ሰዎች ናቸውና ነው። በተለይም የአሜሪካ ሕልም በቃል የሚነገርለት በአባባልም የታወቀለት ነው። ነገር ግን ኢትዮጵያን ለመጉዳት የሚደረገው ሕልም ትርጉሙ «አትምከር ይምከሩ በቆፈሩት ጉድጓድ ገብተው ይቀበሩ» ነው።

ስለዚህም ለሕልመኞች የታወቀ መሠረታዊ አባባልም አለን። እሱም «ሐለሙ ሕልመ ወኢረከቡ ምንተ።» [ሕልምን አለሙ ያገኙት ግን የለም] ነው። ይሁን እንጂ አልተጎሣቆልንም፥ አልተዳከምንም ብለን እንዋሸም። ሁለት እግሮች እያሉን እናነከሳለን። ማነከሱም ቀርቶ፥ ቆሞም መንገዳገዱ በዝቶ፥ በእንፉቅቅ የኑሮውን ጉዞ ቲያይዘነዋል። እውነቱ ያለንበት ሁኔታ ለኛ ሃይማኖት አስተማሪ ተቀጥሮልን ለናይ ምን ያህል በጉሥቁልናችን እንደሚቀለድ ይታየናልን? ኢትዮጵያውያንን በገነት ከኢየሱስ ጋር አብሮ ለማኖር እየተደከመልን ነውን? ይልቁንስ ከገነቷ አገራችን እያስወጡን ነው። እያባረሩን ነው። ልብ ያለው ልብ ይበል። የእነሱ አገር እኮ ነው የገነትና የሲያል ምሳሌ ሆነው ያሉት። ኢትዮጵያማ መንግሥተ ሰማያት ብቻ ናት። በአገሩ ምጸተኛ፥ ከአገሩ ውጭም ለደተኛ፥ ኑሮ ወይንስ ውርደት? ተሠቃይቶ በንዴትና በኃዘን ተበልቶ፥ ተበጫጭቆ እንዳልሆኑ ሆኖ መሞት። ሳገሩ እንደሠራ ሰው ቁም ነገር ፈጽሞ እንደሚሸኝ ሰው ከሣጥኑ ተከቶ ወደ መቃብር መግባት ሆነ። ነገ ከነገ ወዲያ ተመልሼ የተበላሸውን አቅንቼ፥ ለሕዝቤ ሠርቼ እመለሳለሁ ከማይባልበት ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ በሕይወትም ሆነ በሞት በምሰጥ መበላት ፀፀቱ ጎልቆ መሣፍርት የለውም።

አንድ ኢትዮጵያዊ ሕልም ያይና ለተርጓሚ ይነግረዋል። ሕልሙም እሱ በአልጋ ላይ ሆኖ ብዙ ሕዝብ እየዘፈነና ዕልል እያለ አጅቦት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሄድ ነው። የአላሚ ምኞት ልትነግሥ ነው እንዲባል ነበር። በቃ ሕልሜ ይህ ነው ይለዋል።

ሕልም ፈቺም ይኸው ብቻ ነው ይለዋል። አስፈቺ አዎ ብሎ ሕልሙን ይደመድማል። ታዲያ ፈቺም ይህማ ሞተህ አስከሬንህ በአልጋ ላይ ሆኖ እየተለቀሰ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሄድኸው ለጸሎተ ፍትሐት ነው ሲለው፥ እይ ከአልጋውኮ እንጣጥ ብዬ ወረድሁ ብሎ አላሚ ይመልሳል። ተርጓሚ እሱማ ወደ መቃብር ስትወርድ ነው ሲለው፥ አላሚ እንጃ እምቢ እንዲያውም ሕልም የሚባል ነገር አላየሁም አለው ይባላል። አላሚና ተርጓሚ የተለያዩ ሰዎች ናቸው። አላሚ ሁሉ በአልጋው ተንፈላሶ በሕዝብ ታጅቦ ሰመሄድ ቢመኝም ተርጓሚው የእሱን መንፈላሰስ ሕልሙ አላሳየውም። የባሰውኑ የታየው ወደ አዘቅት ሲሄድ ነው።

የሁሉም ሕልም አልጋው ላይ ልውጣ ባይ ከሆነ ተሸካሚውና አጃቢው ከየት ይመጣል? ሁሉም ቀባሪ ከሆነም ሟች የለም። ሁሉም ሟች ከሆነም ቀባሪ ይጠፋል። ለለዚህ ሕልሙም እንደ አቅም ሲሆን ነው ታሳቅ ችሎታ የሚሆነው፥ ያለበለዚያ ሞቼ፥ ተነሥቼ፥ አገሬን አቅንቼ፥ እልፍኝ ከአዳራሽ ሠርቼ፥ ቆንጆ ባለሙያ ልዩ ምርጥ ሚስት አግብቼ፥ ልጆች አፍርቼ፥ የልጅ ልጆች አይቼ፥ እንደገና እሞታለሁ ማለት፥ ማንነትን ካለማወቅ የሚደረግ ታሳቅ የሰሕተት መዋዠቅ ነው። ከሞት በኋላ ሕይወት ማለት ይህ አይደለም። ያ መጋባትና መፋታት የሌለበት፥ በቤት ሙያ በቀን ሥራ የማይዋትቱበት፥ የደለታ ወይንም የመከራ ሕይወት ነው። የእሱም ቁልፉ በምድር እያሉ የሚፈጽሙት ተግባር ነው። ሰው እያለቀየሙ አገርን፥ ወገንን እየቆለመሙ ግን በምድር የከፋው በለማዩም ቤት ይሆናል የሚጠገንነው።

የዚች መጣጥፍ መሠረተ ጉዳይም የኢትዮጵያውያን ሚሺነሪዎች ወይንም በእነሱም አንጋገር «ፓስተሮች» ጸረፋ በዋናነት ምክንያት አድርጎ ይነሣ እንጂ! እንደ እበው አባባል «በገዳዩ አትፍረዱ ሟችም አናዳጅ ነው» የሚሉት እንደተጠበቀ ነው። ቤተ ክርስቲያናችን በሰላም፥ በአንድነት፥ በፍቅር፥ በጸሎት፥ በትሕትናና በአስተዳድር ብትዋብ ኖሮ እንኳን ባዳው መጥቶ ሊያንገራግራት ይቅርና ወደ በሯ እንኳን ብቅ ለማለት ይብረከረክ ነበር። በየት አልፎ? ማንስ ፈቅዶለት? እንኳን ወደ ውስጥ ሊገባ ይቅርና አጥር ግቢዋን እንኳ ዘወር ብሎ ለማየት አይደፍርም ነበር። የመንደር ሌባው እንኳን አለ የሚባለው በራቸውን ክፍት እየተዉ ሌባ ይራገማሉ ነው። ትክክለኛ አባባል ነው። ወዶም አይደለም። እንዲያው ለሙ በየቦታው ሌባ ሌባ ስለሚባልበት ነው። ለሌብነቱ ምክንያት መሥጠቱ ነው። በሩ የተዘጋና እጥሩ የጠነከረ ቢሆን ኖሮ

ገብቶ ሊሠርቅ ይቅርና ታሳቡም እንደማያድርበት ነው ራሱ ሌባው ማስረጃ የሚያቀርበው። አዎ! በርን ቆልፎ፥ አጥርን አጠናክሮ፥ ያለን የአባ ወራ ቤት ማንም አይደፍረውም። ገብቶ ለመሥረቅ፥ አጥሩንና በሩን ለመሥበር፥ አስቸጋሪነቱንም ለመሥረቅ ከመሄዱ በፊት አስቀድሞ የሚያጠናውና የሚያስብበት ነውና ነው።

ና

ኢትዮጵያን የመሠለች ቅድስት አገር ይዞ፥ በጠላት ሴጣ ወሬ ደንዝዞ፥ ተቅበዝብዞ ለመኖር፥ መፈጠርም፥ መከሠትም ፈጽሞ አያስፈልግም። ሰው በዓለም ላይ የሚኖረው ሕይወት፥ እጅግ በጣም አጭር፥ ትንሽ፥ እንደ ጤዛ ጥኋት ታይታ ከርፋድ ላይ የምትጠፋ መሆኗን መገንዘብና ማወቅ የማንነት ጥበብ ነው። በዚች ሕይወት ውስጥ ከሚያልፍ ይልቅ የማያልፍ ስም መግዛት አውንም ብልህነት ነው። ለልጁ ምን ሀብት አፈራሁ ከማለት ይልቅ ለወገኔ ለአገሬ ምን አስተዋጽኦ አደረግሁ ማለቱ የበለጠ አውንም ታላቅ ብልህነት ነው። እንደ ታላቅ አቤቱታና ምስላ ያቀረብሁት ፕሮቴስታንቶች ኢትዮጵያን የመሠለች ሀገረ እግዚአብሔር ለመንቀፍና ለመዝለፍ ለምን ጣሩ? ለምንስ ጋሩ? እነሱ የኢየሱስ መንግሥት ተቆርቋሪ፥ እኛ ደግሞ የበሩና የመስኩቱ ሠባሪ ሆንን መቅረብ ነበረብን? ያውም በኛዎቹ በራሳችን ሰዎች እንደበት የሚነገር ነው።

ጉዳዩን አተኩረን ስንመለከተው እጅግ ያሳዝናል ያስለቅሳል። በእውኑ የራሳችንን ጩኸት አልተቀማንምን? የሚያስሙት ኡኡታና ጩኸት ትርጉሙን ቢያውቁት ኖሮ በጀርባቸው ድንጋይ አዝለው ከባሕሩ ቢሠጥሙ እንደኛ ምርጫቸው ይሆን ነበር። ደግሜ ደጋግሜ እንዳልሁት በመሠረቱ ስለ ሃይማኖት ከኢትዮጵያ ይማራሉ እንጂ ኢትዮጵያውያንን ሃይማኖት እናስተምር ማለት ሰውን ሳይሆን እግዚአብሔርን ማስቆጣት ነው። ኢትዮጵያኮ አምላኳን አውቃ ዕጆቿን ዘርግታ የጠየቀችውን ሁሉ የተቀበለች ቅድስት አገር ናት። ታዲያ ከእሷ ይመጡና ይቀበላሉ እንጂ እንዴት ሃይማኖት ሊያስተምሯት ይኩራራሉ? ራሱ የእግዚአብሔርን ማደሪያ እንደማርከስ ነው። ይህም ቀደም ሲል በትንቢት ተነግሮባቸዋል እንዲህ ሲል «እግዚኦ ቦኡ አሕዛብ ውስተ ርስትከ ወአርኮሱ ጽርሐ መቅደስከ።» [ጌታ ሆይ! በባሕር በእሳት በተራራ በአራዊት በጨረቃ በከዋክብት በድብና በዘንዶ አምላኪዎች አሕዛብ ወደ ስምህ ማሞገሻና ማወደሻ ወደ ሆንችው ርስትህ ኢትዮጵያ መጡ ገቡ። የሥጋህ መፈቱቻ የደምህ መቅኛ የሆነውን ቤተ መቅደስህን ንጽሕና አረከሱብህ ነቀፉብህ ሰደቡብህ። መዝ. 78:1-2] ይህ ደግሞ በሰውም

ዘንድ ነውር በእግዚአብሔርም ዘንድ መቅሠፍትን መሻት ነው። ይሁንና ይሁን እንጂ! የሚከተለውን አቤቱታ አቀርባለሁ።

በዚህ ማመልከቻ ውስጥ ለቤተ ክርስቲያናችን ጠላቶች ተቃውሞ፥ ለቅዱሳንና ለብዑዓን አባቶች፥ ለካህናት፥ ለወጣቶችና ለምዕመናን አቤቱታ አብሬም አቅርቢያለሁ። ሁላችንም በተለያየ መልኩ የምናየውና የምንሰማው ብሔራዊና ሃይማኖታዊ ጠላት በአሁኑ ሰዓት በመጀመሪያ ከንፍ ከዚያ እንደ አባብ በልቡ እንደሚላብ አሸን ዙሪያችንን ፈልቶብናል። በጸሎት፥ በትሩፋት ለእግዚአብሔር መንግሥት የኖሩትን፥ በኢየሱስ ስም ደረታቸውን ለጦር፥ አግራቸውን ለጠጠር፥ አንገታቸውን ለሠይፍ፥ ራሳቸውን ለወንጭፍ ሠጥተው ያለፉትን የሃይማኖት አርበኞችን፥ ሰውን ከመከራ ለመታደግ የሚለላኩትን መላእክተ እግዚአብሔርን የሚነቅፉና የሚዘልፉ ሰዎች ተነሥተዋል። ልፈፋቸውም ከሩቁ ሳይሆን ከቅርቡ ይሰማል። በየመንደራችንም ይደመጣል። ሌላው ቀርቶ «ናሁ እምይዜሰ ያስተበጽኡኒ ኩሉ ትውልድ» [ከእንግዲህስ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል] [ሉቃስ 1:49] ብላ የተናገረችውን ቅድስት ድንግል ማርያምን እንኳን የሚያቃልሉ ናቸው። በዚህም ተግባራቸው ምዕመናኑ ፀረ ማርያም ይሏቸዋል። ሥራቸው በፀረ ማርያምነት ብቻ አላበቃም። ፀረ ሕዝብ ፀረ ኢትዮጵያ ፀረ አርቶዶክስ ፀረ ጻዳቃን ወሰማዕታት ፀረ መላእክት ፀረ አንተና አንቺ እኔና እኛነትም እንጂ! ለአባባሉማ በወንጌሉ ለእነሱ የዕጅ ኳስ በተናገሩ ቁጥር እያነሱ የሚቀረቅቡት በቡጢና በጥፊ የሚጠፈጥፉት መጽሐፍ ውስጥ ስለ ድንግል ማርያም የተጻፈውን አላዩትም። አላነቡብትም። ማንበብስ አንበውታል ነገር ግን ከተነሡበት ዓላማ ጋር ስለሚቃረንባቸው ትተውት እንጂ! መጽሐፉማ እንዲህ አድርጎ አሳምሮና አስውቦ ያነበዋል። ያውም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እንዲህ ሲል፡

«ቡርክት አንቲ እምአንስት ወብሩክ ፍሬ ከርሥኪ» [ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው።] ቅድስና፥ ከእናትነትና ከእመቤትነት ጋር ብሎ ያረጋገጣላትን ቅድስት ድንግል ማርያምን ዳቦ በሠረጠጠው አፋቸው ያቃልሏታል። የጌታን እናት ለስደቦና ላቃለለ ሰው እንኳን ተግሣፅ ሞት ሲያንሰው እንጂ! አይበዛበትም። «ከመረቁ አውጡልኝ ከሥጋው ጸመኛ ነኝ» ዓይነት አባባል የኢየሱስ ወዳጅ ነኝ። ነገር ግን ከቅድስት እናቱ ጋር ዓይንና አፈር ነኝ ማለት እንዴት ይቻላል? ለጌታ ኢየሱስ ፍፁም ታዛዦችና አገልጋዮች ለሆኑት ለመላእክት፥ ለሰማዕታትና ለጻድቃን ሁሉ በጠላትነት ለተለለፈ አመጸኛና ግድ የለኝም ባይ ሃይማኖታዊ

ድርጅት በእውነቱ እንዴት የኢየሱስ ወዳጅ ሊሆን ይችላል? ይህ ራሱ ማደናቆሪያ ወይንም ማታለያ አሠራር ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው።

አበው ይህን በተመለከተ የተናገሩት ምሳሌ «ጌታውን ካልናቁ ውሻውን አይመቱም» ይላል። ለእንደነሱ ላሉት ዓይነት አሳሳቾች ነው። ስለ ኢየሱስ ሰው መሆን ታላቅ ምሥጢር ተነግሮት መጥቶ ቅድስት ድንግል ማርያምን ጌነሆ! ትጸንሻለሽ። ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ። ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ ብሎ እንዲናገር የተላከውን፥ ስለ ድኅነታችን ያበሠረልንን መልአክ ማቃለል፥ መስደብና መዝለፍ በእውነቱ የክርስቲያንነት ባሕርይ ነውን? ወይንስ ዲያብሎሳዊ ተግባር? ኢትዮጵያዊነትን የሚያጠፋ «ሚሺነሪነት?» ማለት ይህ ነው። ይህን ደግሞ አንባቢ፥ ተመልካችና አድማጭ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይፍረድ።

ለእነዚህ ዓይነት ጠላቶች በኢየሱስ ስም የነበረንን የያዝነውንና ያለንን ከዕጃችን ፈልቅቀውና አውጥተው ለመውሰድ ዕጃችንን ጠምዝዘዋል፥ አንገታችንን ቆልምመዋል። አሁን ያለንበት ሁኔታ ይህን ይመስላል። የእነሱ ማንነት ሲታወቅ ደግሞ የበግ ለምድ ለብሶ መቅረብ የተኩላዎች ባሕርይ ነውና እኛን መስለውና አክለው <u>ስመ ጥምቀቴ ገብረ ኢየሱስ</u> በተባለ በብዕር ስም የተጻፈው *ገድል መይስ ገደል?* መጽሐፍ እውነተኛይቱን ሃይማኖት፥ ውስጠ አዋቂ ሆኖ፥ ቀዩ ተኩላ በግ መስሎ ከመንጋው ተደባልቆ እያሳሳተ ነው። እንዲህ ያለ ቅጥፈትና ሐሰት አዘጋጅቶ ያውም በሃይማኖት ስም የዋህኑን ማሳሳት ታላቅ ኃጢዓት ነው። ታላቅም ርግማን ነው።

የሚገርመው ግን ዓርባ ዘጠኝ ጊዜ በኢየሱስ ስም እየተገዘቱ ከመሰማት በስተቀር በእውኑ ኢየሱስን በግልጥ ያውቁታል? ይቀበሉታል? ታላቁ ተልእኳቸው በስሙ ቅኝ ግዛት ለማፍራትና አገር ለመውረር፥ አገር ለማጥፋት፥ ሕዝብን እርስ በራሱ ለመከፋፈልና ለማጋደል የተነሡ ክፍሎች አይደሉምን? የሚገርመው ቢኖር ይህ ሥጋዬ ነው እንኩ ብሉ። ይህ ደሜ ነው እንኩ ጠጡ። ብሎ የሠጠውንና በመስቀል ላይ ለቆረሰው ሥጋውና ለፈሰሰው ደሙ እንኳ ሳይቀር አክብሮት የላቸውም። ለመታሰቢያ ብለው ብቻ እንዳልሆነ ያደርጉታል። ለመስቀሉ፥ ለቅድስት ድንግል ማርያም እናቱ፥ ለመላእክቱ፥ ለስግዕታቱ፥ ለጻድቃኑና ለሐዋርያቱ ሁሉ ምንም አክብሮት የላቸውም። እኛ ስለምናከብር ግን ይሰድቡናል ይነቅፉናል። «ነጋዴ የሚያዝነው ራሱ በመቀማቱ ሳይሆን ጓደኛው ሳይቀማ በመቅረቱ ነው» እንደሚባለው እኛ ያለን ስለሌላቸው፣ እንደ እነሱ ራቁታችንን ያለመሄዳችን ያስቀጣቸዋል። ያናድዳቸዋል። ሲሆን

ሲሆን ሊያጠፉን፥ ያሊያም እንደ እነሱ ምንም የሌለን እንድንሆን ይሻሉ። ከመጋረጃው ውስጥ ካለው አገርን ከመከፋፈሉና ሕዝቡን እርስ በራሱ ከማጠላላቱና ከማስተራረዱ ባሻገር መሆኑ ነው።

እንግዲህ ሁላችንም በጋራ ስለ እነዚህ ሰዎች የምንጠይቀው አንድ ዓቢይ ጉዳይ አለን። እሱም ከኢየሱስ ጋር ያላቸውን ዝምድና እንዴት ነው የምናውቀው? ከኢየሱስ ጋር አብሮ የሚያስሄድ አንዳችም ባሕርይ፥ አንዳችም ሥነ ምግባር አንዳችም ተውፊት ሃይማኖታዊ ትስስር ጠርሶ የላቸውም። ለመሆኑ ክርስቲያንስ የሚያሰኝ ስመ ምክንያት አላቸውን? የእኒህን ሰዎች ሥራ ተመልከቱ። በሚገባ እጥኑ መርምሩ አስተውሉ ተገንዘቡ።

ፀረ ሥጋውና ደሙ
ፀረ ማርያም
ፀረ መስቀል
ፀረ መላእክት
ፀረ ሰማዕታትና
ፀረ ጻድቃን ናቸው።

እንግዲህ እኒህ ሰዎች ብራቸውን በኮረጁ፥ መጣፋን ደግሞ በሻንጣ ይዘው መጥተው ሁሉንም ባንድ ላይ ከፍተው በተኑት። መጽሐፍ ቅዱስ የመጣበትም ሆነ ብሩ ተመልሶ ብር ተመልቶ ለመመለሱ ግን በርግጠኝነት ነው። ዘርቶ ማጨድ ወይንም ነግዶ ማትረፍ ይሏል እንዲህ ነው። ታዲያ በዚህ ሁኔታ ወደ አገራችን ከገቡ ጀምሮ ምን አመጡልን? ከማለት ይልቅ ምን ምን ፍዳና መከራ አመረዱብን? ብንል በግልጽ ማየት እንችላለን። የዘርና የጎሣ መለያየት፥ እርስ በራሳችን በጠላትነት እንድንተያይ፥ አንዱ አንዱን እንዳያምነው አላደረጉምን? የዛሬው ነፃ አውጭ የሚሉት የለበጣ ስም፥ የዕጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ አምጭና አርቢዎች እነሱ አይደሉምን? ዛሬ በየአቅጣጫው በምሥራቅ፥ በምዕራብ፥ በሰሜንና በደቡብ የሚታዩት ችግሮች በሃይማኖት ጦር መሪነት የተፈጠሩ አይደሉምን?

ወገኖቻችን ሆይ! ራሳችንን ታሪካችንን እንጠብቅ። ከኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ የይማኖት ውጭ ሃይማኖት ፍለጋ መባዘን ታላቅ ሞኝነት ነው። እንዲያውም «ልፋ ያለው በሕልሙ ኩንታል ሲሸከም ያድራል» እንደተባለው መሆን ነው። የሐዋርያት ሥራ 8:26-39 ድረስ ያለውን ካነበባችሁ ራሱ በቂ ነው። በዚያ ሁኔታ ከተቀበልነው የክርስቶና እምነት ውጭ መሄድ አንድም የሂትለርና

የሞሶሎኒ ዓላማ ያለው፥ አገር ወራሪና ሕዝብ አጥፊ መሆን ነው። ሚሽነሪዎች አገራችን ውስጥ በግልጽ ገብተው፥ መንቀሳቀስ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ የምናየውና የምንመለከተው፥ ታላቁ ዒላማቸው የአንድነታችንን እስስር መበርበርና ማዳከም ነው። ከዚያም አልፎና ተርፎ ነፎች በኛዎቹ [ዛሬን በልተን ነገም እንሞታለን] ባዮች ተተክተው ሕዝቡን ያተረማምሱታል።

ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ሆይ! ሃይማኖት አንዲት ናት። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የዓለም ሕዝብ የሚያያንቃትና የሚመለከታት ናት። ታሪካዊት፥ ብሔራዊት ከመሆኗም ባሻገር የእግዚአብሔር መንበር ናት። ከዚህ ወጥቶ የት ለመሄድ ነው? ከሞቀና ከደመቀ ቤታችሁ አስወጥቶ ግድግዳው ባልተመረገ፥ ጣራው ባልተከደነ ቤት ውስጥ መኖር ትርፉ በብርድ መቀሠፍ ነው። ጥንቃቄ እናድርግ። ልጆቻችንን እንጠብቅ። ከየመንደሮቻችን እኒህን ሠይጣናት እናሰወጣ እናስለቅቅ። በሃይማኖት ስም የሚበትኑብን የመከራና የሥቃይ ትቢያ ነው። ወላጆቻችን ለብዙ ሺህ ዓመታት ያቆዩንን ሃይማኖት እንጠብቅ። ማርን ሽጦ ምን ይገዛል ከዚህ ላይ ነው። ሃይማኖት የእግዚአብሔርን ልጅነት ማግኛ መንገድ ናት። ወይንም የእግዚአብሔርን ልጅነት ማረጋገጫ ደረሰኝ ናት። ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ወደ ሌላ መለወጥ ያለ ጉዳዩ ገበያ እንደሚወጣው የቤት እንስሳ መሆን ነው። በግልፁ አባባል «ውሻ ያለ ጉዳዩ ገበያ ይወጣል» እንዲሉ ነው።

ተዝካር ይቅር ሰንበቴ ይጠንቀር ቡና አትጠጣ እሳት አትጨማሩ አትቀባበሩ ቤታችሁን ዘግታችሁ ለየብቻ ኑሩ። ይህ ሁሉ አሽክላ የሚሠሩት ተንኮል ለውይይት ለዕይታ ለትዝብት እንዳይወጣ ፀሐይ መቶት እንዳይገረጣ ነው። እነሱ ግን ገንዘብ በአራጣ እቁብን በእጣ ያበረታታሉ። አዛኝ ቅቤ አንጓች ይላቸዋል። ለኛ አሰበው ሌት ከቀን ተጨንቀው እንቅልፍ አጥተው ለኛ ጥቅም የማይታሰም የማይታሰብ ነው። እኛ የምንለያይበትን አንድነታችን እንደ በጋ ውሀ የሚነጥፍበትን እንደ ምንጭ የሚደርቅበትን እንጂ መቼ በጎ ታስቦልን ያውቃል? ያለንን አጥተንና ነጥተን ከልመናው ሰልፍ እንዲያዩን አይደለምን? የሌት ከቀን ጥረታቸው? የበሬው አካል ይወድቃል ብላ ስትከተል እንደዋለችው ቀበሮ የማንበላውንና የማናገኘውን ሥዕል እያሳዩን እኒሁን በመከተል የወጣትነት እድሚያችንን በዋዛና በፈዛዛ ያሳልፉብናል። ያገሬ ሰው ግን እንዲህ ብሏል። ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል።

፩ . የመታሰቢያ ድግሶች

[እኅውየ አለ የአምኑ ብየ ሊተ ገበርክሙ፣ ማቴ. 25:40]

[ለሌላውም እንደናንተ ላለው ለአንዱ ያደረገ ለእኔ እንዳደረገ ነው።] በጻድቁ ስም የሠጠ የጻድቁን ዋጋ ያገኛል። ወገኖቼ ሆይ! መዝክር፥ መመጽወት ይቅር ሠይጣናዊ ነው የሚሉን ለምን ይመስላችኋል? የኢትዮጵያ ሕዝብ ልጁን ሲድር ተዝካር ሲያደርግ ብቻውን አይደለም። ዘመዱ ተሰባስቦ፥ በጋራ ደግሶ ነው የሚድርለት። ተዝካርም ሲያወጣ እንዲሁ፣ ቤት ሲሠራም፥ አዝመራውን ሲሰበስብና ሲወቃም ተባብሮና ተረዳድቶ ነው። ይህም ያንዱ ችግር የሌላው ሆኖ የኖረና የቆየ በመሆኑ ተሳስቦ ኖሯል። ይህ ደግሞ አንድነት ስላለው አገሩን ለጠላት ሳያስደፍር ኖሯል። በመከራውና በደስታው ተሳስሮ የኖረበትን ማኅበራዊ ኑሮ ከበጣጠሉበት እንደ ፈለጋቸው ለማድረግ ነው። ከሃይማኖቱ ጋር አብሮ የተጠረዘው ጥናታቸው ይህ ነው። ይህን ለማስቀረት ደግሞ በሃይማኖት ስም ገብተው መበታተን ነው። ከዚህ ላይ ረጋ ብለን የምናስብበት ታላቅ ጉዳይ አለ። ሰንበቴና ተዝካር ይቅርን ምን አመጣው? ምሥጢሩ ይግባን። አንዱ ሲሞት ሌላው እንዳይደርስለት ለማድረግ ነው። ይህም አንዱ ሲገደል ቤቱ በቀማኞች ሲሰበር ቢሞት ሌላው ካልደረሰለት ምን ሆነ ማለት ነው። ይህ ደግሞ አንዱ ለሌላው ካልደረሰ ነግ በኔ ነውና ሌላውም አይደርስም። ለየብቻ ይዞ ነጣጥሎ ማጥፋት ማለት ከዚህ ላይ ነው። በየዘመኑ የሚጎዱብን አቅድ ምንጊዜም እንዳወጡ ነው። ያ ደግሞ በሥራ ውሎላቸው እናያለን።

ከዚህ ላይ አንድ የተፈፀመ ድርጊት ልጥቀስ የኢትዮጵያ ጥንታዊው ትምህርት በቃልና በንባብ ነበር። እጅግ ብዙ የተራቀቁ ሲቃውንት ነበሩን። ያልተመረመረ ጥበብ አልነበረም። ያን ጥበብ ወደሚቀጥለው ትውልድ እንዳይተላለፍ በአጭር ለማስቀረትና ለማጥፋት ሲሉ የማይተላለፍበትን መላና ምክንያት መፍጠርና ማውጠንጠን ጀመሩ። የሚጽፍ ካህን ጠንቋይ ነው። ስለዚህ ጠንቋይ ከሆኑ ካህናት ዘንድ አንዱት ሄዳችሁ መስቀል ትሰማላችሁ? የሚል ስብከት በሰፊው ሠበኩ። አንዳንድ ሕዝብ አካባቢ የሚያከብራቸውን አረጋውያን አንድ ላንድ ይዘው በውለታም በሆነው ሁሉ አሳመኑና የሚሉትን የሚያረጋግጡ ትክክል ነው ባዮችን አዘጋጁ። ከሚያምኗቸውና ከሚያውቋቸው አፍ ሲሰሙት እውነት ነው ብለው ተቀበሏቸው። ከዚያ በኋላ ሲጽፍ የታየ ካህን ጠንቋይ መተተኛ ይባል ጀመር። ስሙም ጠፋበት። ያን ያዩና የተመለከቱ ካህናት

ደግሞ እንዲያ ላለመባል ፈሩና የጽሕፈቱን ነገር እርግፍ አድርገው ተዉት። እንዲያውም አንዳንድ ቦታ የሚጽፍ ካህን እንዳይቀድስ ግዝት ተላለፈ። ያ በቃል በንባብ የተካበተና የተጠና ትምህርት ምርምርና ጥናት ለተተኪው ትውልድ የማበተላለፊያውን መንገድ ዘጉበት። ያ የተካበተ እውቀት ሊቃውንቱ በሞት ሲጋረዱ ይዘውት ቀሩ። ይህም የኢትዮጵያውያን ጥናት ተዳከመ መነመነ ከንቱ ሆኖ ቀረ። ውጤቱ ይኸው ዛሬ ዕጃችንን መቅረት ሆነ።

ይህን ያለፈ ታሪካችንን ይዘን ወደ አሁኑ ስንመለስ ደግሞ ዛሬ ማኅበራዊውን ኑሮ ለማፈራረስ ለሕዝቡ በሚመስል ቋንቋ ውስጥ ውስጡን ግን የሠበካ ጉባዔ አባላትን በማግባባትና እውነት በማስመሰል ስለ ተዝካር አቆርቋዥነት እየነገሩ አብሮ የሚኖረውን ሕዝብ ለመለያየት እያስቀሩት ነው። ካህናቱም እንዳይቆጡ ከቤተ ክርስቲያን ብቻ እንዲሠዋ እደረጉ።ጊዚያዊ ማታለያ ነው። የካህናቱን አፍ መዝጊያ ነው። ተዝካር እኮ ይቅር አላልንም ከቤተ ክርስቲያን ይሰጥ ነው ያልነው እንዲሉ ነው። ይህ የጥፋት መጀመሪያ ዘዴው ነው። ከጥቂት ዓመታት በኋላ ደግሞ ከቤተ ክርስቲያንም ምን ይሠራል ማድከሚያ ነው ብለው እንደጀመሩት ጨርሰው ያጠፉታል። አንዳንድ ካህናት ይህን ተቃውመው ቢናገሩም ይኸው ድግሱ እንዳይቀርበት ተብሎ ሦስትና አራት ሆድ ያለው ይመስል በሆዳምነት ይወነጅሉታል። ከዚህ ዓይነቱ ልፈፋ ለመዳን ሲል ዝምታን ይመርጣል። ከዚህ ላይ ስለ ተዝካር ብቻ አተኩረን አንየው። የማኅበራዊው ዓይን እየጠፋ ነው። አንዱ ለሌላው ጥላና ከለላ ካልሆነው ሕይወቱ የሞተ ነው። አንድነት የጎለበተበትን ፈርጣማ ክንድ መቁረጥ ነው። ይህ ታላቅ ግንዛቤ ይወሰድበት። ካህናትም አይሆንም በሉ። ተዝካር ይቀጥል። መረዳዳቱ ላይ አተኩሩ። የገና ገና ድግስ ፈልጎ ለምን ይቀራል ይላል የሚለውን የይሉኝታ አባባል ፈርታችሁ ታላቁንና ማኅበራዊውን ኑሮ ሲፈርስ ዝም ልትሉ አይገባም።

ተዝካርን አስቀረን ብለው እየፎክሩ ያሉት እኮ ፕሮቴስታንቶቹ ናቸው። የሚጽፉትን አታንቡምን? ራሳችሁን ጠብቁ። ሰው እንዲህ ይለናል ብላችሁ አትሸሹ። ለመሆኑ ለምንድን ነው ተዝካር እንዲኖር አበው የደነገጉት? «ሕያዋን ይጸልዩ ለሙታን ወሙታን ይጸልዩ ለሕያዋን።» [ሕያዋን ለሙታን ይጸልያሉ። ሙታንም ለሕያዋን ይጸልያሉ።] ነው። ሙታን በአካለ ነፍስ ሕያዋን ደግሞ በአካለ ሥጋ ሆነው አንዱ ለሌላው ይጸልያሉ። ሙታን ከፍተኛ ጸሎት ያስፈልጋቸዋል። ብዙ ነፍሳት ከሥጋቸው ከተለዩ በኋላ በሕይወት ዘመናቸው በሠሯቸው ተግባራት ነፍሳቸው ወደ ሰማይ መውጣት ሳትችል ቀርታ ከመሬት ላይ ከሥጋቸው መቃብር

ቦታ ወደሚኖሩበት ቦታ በመመላለስና በመደናገጥ እጅግ ብዙ ዘመናትን ያሳልፋሉ። ይህ እንዳይሆንባቸው ግን ጸሎት የሚያደርግላቸው ሰዎች ያስፈልጓቸዋል። ጸሎት ለሙታን ከመሬት ወደ ሰማይ ያሰወጣቸዋል ወይንም ያሳርጋቸዋል። ጸሎት ከፍተኛ መሣሪያ ነው። ታዲያ ይህን የሚያውቁ አባቶቻችን ለአንድ በሥጋ ላንቀላፋ ሰው ነፍስ ከጸአተ ነፍስ ማለት ነፍሱ ከምትወጣበት ሰዓት ጀምሮ የጸሎት ሥርዓት አዘጋጅታለች። ለዚሁም መጽሐፈ ግንዘትን ይመለከቷል። የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የጸሎትን እጅግ አስፈላጊነት በመረዳት ለአንድ በሞት ለተለየ ሰው ነፍስ የዕለቱ ሰት ወደ መቃብር አስኪወርድ ድረስ ልዩ ጸሎት ታደርጋለች። ከዚያም የሣልስት የሰባት የአሥራ ሁለት የሠላሳ የዓርባ የሰማንያ የመንፈቅ የዓመትና የዓመታት ሥርዓት ደንግጋ በትጋት ለነፍሳት ትጸልያለች። ይህን ሁሉ ጸሎት የምታደርገው ነፍሳት ከመሬት ወደ ሰማይ እንዲያርጉ ከዚያም በላይ ተገቢውን የጽድቅ ቦታ እንድታገኝ ለመርዳት ነው። ምን ያህል አባቶቻችን አዋቂዎች ነበሩ? ይህን የጸሎት ሥርዓት አንድ ሰው ብቻውን እንዳይከብደው ደግሞ አንዱ ሌላውን እንዲረዳው የመረዳዳትና የመተጋገዝ ማኅበራዊና ባሕላዊ ሥርዓተ አበው በመደንገግ ነው።

ወገኖቼ ሆይ! ይህን የመሰለ አመክሮ ያለበትን ሙታን የሚረዱበትና የሚታገዙበትን ሥርዓት የዛሬዎቹ አዲስ መጤዎች እነሱ ያዩት ምድራዊውን ዓለም አደላድለው የሚኖሩበትን እንጂ ስለ መንፈሳዊ ሕይወት ብዙም ስለሌሉበት አያውቁትም። በዚህም ምክንያት የጎብረተ ሰቡን አንድነት የሚሠብሩበት ጎዳና ስለሚከተሉ ብቻ በዚሁ ዓይን ተመልከተው ተዝካር ይቅር ብለው ይታገላሉ። አስቀረነውም ብለው ይፎክራሉ። አንድ የምንረዳው ጉዳይ ቢኖር አባቶቻችን ቢያንስ በዓመት ሁለትና ሦስት ጊዜ ሱባዔ ይገባሉ። በዚህን ጊዜ ከሚያውቋቸው ሰዎች ነፍሳት ጋር ይወያያሉ ይነጋገራሉ። ከሱባዔም ሲወጡ ለቤተ ሰቦቻቸው መልእክት ይዘው ይመጣሉ። በዚህን ጊዜም የአትርሱኝ ጸሎት የተደነገገውም አንዱ ምክንያት ለዚህ ነው። ይህን የመሰለው ልምድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተረሳ ስለሆነ ዊራሹት እኒሁ የምድር አጋንንት በተለይም እነሱ ውር ውር በሚሉባቸው የከተማ አብያተ ክርስቲያናት ባሉት የሠበካ ጉባዔ አማካይነት እየተጠጉ ሥርዓት እያሻሩ ነው። አሰካሁን ተጠብቆ ያለው በገጠር ከሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ነው። የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን መሠረት ወደ ቤተ ክርስቲያን ተጠግቶ በድንገት ቢሞት ፍትሐት ፈትታ ከሣልሰት እስከ ዓርባ ሕዝቡን ደልድላ ቅዳሴውና ፍትሐቱ ይደረግለታል። የማዴታ ተዝካር የሚያወጣለት ሰው የለውም ብላ አትተወውም። እንዲያውም የአጥቢያውን ምዕመናን

አደራጅታ ዝክርቱ ሁሉ አንዲፈፀም ታደርጋለች። ምክንያቱም ጸሎቱና ፍትሐቱ ለሙታን እንደሚያስፈልጋቸው ስለምታውቅ አንዲደረግለት የግድ ትሳለች። አንድ ክርስቲያን ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ሲያርፍ የሁሉም ወገን መሆኑን በመረዳት ነው። ይህም የሚያሳየው የግድ ተዝካር የሚያወጣለት ከሌለው ፍትሐትም አንፈታም አትልም። ፍትሐት ለድግስ መብያ አድርጎ መመልከት ፍፁም ስሕተት ነው። ለነፍሳት ጠቀሜታ ያለው መሆኑን በመገንዘብ ነው።

ቀደም ሲልና አሁንም በገጠር አብያተ ክርስቲያናት እንደተጠበቀ ያለው አንድ ሰው ከተቀበረ በሦተኛ ቀኑ ከመቃብሩ ተሂዱ ይለቀስ ነበር። ይህም ሥርዓት ምክንያት ሆኖ የቀረበው እኛ የብሉይ ኪዳን ሰዎች ስለሆን እንደ አሕዛብ ያለ ሥርዓት ስለሌለን እነ ማርያም መግደላዊት በሦስተኛው ቀን የጌታ ኢየሱስን አስከሬን ሽቱ ለመቀባት ገሥግሠው መሄዳቸውን እንደ አርዓያ ተወስዶ የሟች ዘመዶችና መንደርተኞች በሙሉ ሄደው ያለቅሳሉ። ያም ድርጊት ለሟች ቤተ ሰብ ትልቅ መጽናናትን ይፈጥራል። ያለበትንና ያረፈበትንም ቦታ በአአምሯቸው ቀርፀው ስለሚመጡ ምን ሆኖ ይሆን እንዴት ይሆን ከሚለውና የቀብሩንም ቦታ ለመጎብኘት በሚሄዱ ቁጥር በውስጥ ያለውን ኃዘን ይከፍላል። በየሳምንቱም አየሄዱ ይጎበኙታል። ከሚኖርበት ቤት ሄደው ዓይተውትም አንደመጡ ስለሚቆጥሩት በጣም ይጽናኑበታል። ለዚህም ነው ወደ መቃብር ተሂዶ መለቀስና እንደምን ሰነበትህን ሥርዓት አድርገው ይዘውት የቆዩት። አሁን አሁን በከተማ ውስጥ ቀርቷል። ይህ ሁሉ አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ትዝታ የለውም አንደ አሕዛብ ትንሣዔ ሙታንን ለማያምኑ ከሞተ በቃ አለቀ ደቀቀ ስለሆነ የእነሱን ግዕዘ ልማድ ሰው ሁሉ እንዲከተል ያደርጋሉ።

ወገኖቼ ሆይ! ስንት ጊዜ አንታለል? የመጀመሪያው መታለል የዋሕነት፥ የሁለተኛው ድፍረት፥ የሦስተኛው ግን ንቀት አይደለምን? እንግዲህ ተዝካር ይቅር። ስንበቴ አያስፈልግም የሚለው ጩኸት ጸንቶና ተገንብቶ የኖረውን አንድነቱን ለመሸርሸር ብቻ ነው። እንደ ዓይኑ ይመካበት የነበረውን የአባቱን ባድማ ወይንም ቦታ፥ አንዱ በውርስ፥ ሌላው በገደብ ስም ቀማው። አሁን የሚፈታት ሚስቱ ብቻ ናት አጠገቡ ያለች። ልጆችም ከትምህርቱ ትምህርት የላቸውም፥ የሚያርሱት መሬትም የላቸው፥ የሚቀጠሩበት መሥሪያ ቤት ወይንም ድርጅት የላቸውም። የትምህርት ዕድሚያቸውን የት እንደሚያሳልፉት ራሳችሁ ፍረዱ። ታውቁትም አላችሁ። ለቀባሪው ማርዳት ይሆናል። ይህ አገርን የሚያፈራርስ፥

የጎብረተሰቡን አንድነት የሚደረምስ፥ መንፈሳዊ፥ ሃይማኖታዊ ነው ብሎ መውሰድ እንዴት ይገባል? አባካችሁ ሊታሪክ ስንቅ አዘጋጁላት። እድሚያችንን ለአገራችንና ለሃማኖታችን መሳለቂያና ማንኳሰሺያ አናድርገው።

ከሁሉ በፊት ፀንታ የኖረችና ያለችን ሃይማኖታችንን ለመውረር መነሣቱ የበደል በደል ነው። እነሱ የኛዎቹ እረኞች በአማን እረኞች ተቃዋሚዎቹ ማለት ፕሮቴስታንቶቹ ያዩት ከጠላት ዕጅ የሚጣልላቸውን የዕለት ጉርስና የዓመት ልብስ ማግኘታቸውን ነው። ይህንኑም እንደ ፀጋ ቆጥረው የሠይጣን መልዕክተኛ ሆነው መቅረባቸው ወደፊት በታሪክና በትውልድ ዘንድ ለዘለዓለም ሲያስረግማቸው እንደሚኖር አሁንኑ ሊገነዘቡት ይገባል።

እኛ ትተናቸው፥ ችላ ብለናቸው ቢቀመጡ እንኳን አንድ ቀን የሠይጣን ሥራ ነውና የሚያካሂዱት ደረቅ ወንጀል፥ ዕጅ ከፍንጅ አስይዞ ጥርስ ወደሚፋጭበት ደይን እንደሚጣሉ ዳግመኛም ሊገነዘቡት ይገባል። ሠይጣን በመውደቅ ሳይ ነው። ድሮም የተጣለ ነውና! አሁንም ሥጋ ለብሶ እናንተን ገዝቶ ያስግራው ሠይጣን አሽክላው እየተሠበረ ነው። ለዚህ መቼም ዕንግዳም፥ ባዳም የለም። ነገር ግን ሁሉ ነገር በግልጥ ካልተነገራቸው ሰው ያወቀብን ስለማይመሥሳቸው ብቻ ነው። በየቦታው የሚረግሙንና የሚሰድቡን አንሶ አኛን ለማነወር መጽሐፍ አየጻፉ አየዘለፉን ነው። ቀደም ሲልም ይህ ዓይነት መከራ አድርገው የአባቶቻችንን ነፍስ ይማር መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ኮክሐ ሃይማኖት በተሰኘ መጽሐፋቸው እጅግ ዕፁብ ድንቅ በሆነ መልኩ መልስ ሠጥተዋቸዋል። እንዲሁም አቶ አሥረስ የኔሰው መኑ አንተ ትቤ አክሱም በተሰኘው ዝነኛ መጽሐፋቸው ተገቢውን መልስ ሠጥተው ገሥፀዋቸው ነበር። እንደ ገና ጊዜውን ጠብቀው ይህን ትውልድ ግራ ለማጋባትና ለማሳሳት ያውም በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ካባ ለማደናገር ስመ ጥመቀቴ ገብረ ኢየሱስ ብለው መቼም እነሱ ቤት ምክረ ሥላሴ ተክለ ማርያም አይባልምና በግብር ተለይተው በስም ብቻ ኦርቶዶክስ ለመምሰልና ለማደናገር ወስመ ጥምቀቴ ገብረ ኢየሱስ ብለው ቀረቡ። የሚገርመው ግን ሰው ሁሉ የሚታወቅበትን የተለመደውን ያባታቸውን ስም እንኳ ሳይጨምሩ አንድ ነጠላ ስማቸውን ብቻ ጽፈው ያባታቸውን ስም ለመንገር ያፈሩ ሰው እሳቸውም መምህር ጌታቸው በሚል መጠሪያ በስም ጌታ በግብር ደሃ የሆኑ ሰው «ገድል ወይስ ገደል» በሚል ርዕስ መጽሐፍ አዘጋጅተው በትነዋል። ውስጠ ምሥጢሩን የማውቅ ከቤተ ክርስቲያን ያደግሁ በተሰኘ ቅጥፈት ቀጥሎ በመጠኑ ከጽሑፉ ውስጥ ያሉትንና የቀባጠሩትን አቀርባለሁ።

ይሁንና መምህር ጌታቸው ወስመ ጥምቀቱ ገብረ ኢየሱስ ከማለት በስተቀር ከላይ እንደገለጽሁት ስለማንነታቸው እንዲታወቅ ያልፈለጉ ጨለማ ለብሰው የሠይጣን ተግባር የሚፈጽሙ ጎሳዊ ሰው ናቸው። እኒህ ሰው ቤተ ክርስቲያን እደግ መስለው በጥራዝ ነጠቅነት እንዳንድ ነገር ከማንሳትና ከመጣል በስተቀር ስለሚናገሩት ስለሚጠቅሱት የጽሑፍ ማስረጃ ናምንነት ምንም እያውቁም። ብቻ ለማደናገር ሰውን ለማታለል ሆን ብለው የሚቃብዙ ሰው ናቸው። የወይራና የጽድ ዛፍ ለመንቀል ሲታገሉም ይታያሉ። መንቀል የሚችሉ እንዲባሉ እንጂ! እንደማይነቅሉት ርግጠኛ ናቸው። ከቤተ ክርስቲያኑ ትምህርት ይልቅ በዘመናዊው ትምህርት እጅግ በጣም የተራቀቁ ሊቅ ናቸው። ይህን በግልጥ መመሥከር ይቻላል። እስከ ትናንትናው ቀን ድረስ ያለውን ሃይማኖታዊ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ሕይወት ዝርዝር ሁኔታ በሚገባ ያውቁታል።

ከዚያ ባሻገር ደግሞ እርሳቸው የጻፉትን መጽሐፍ እነ ፓስተር ወይንም እረኞቹ ከሰማይ የወረደ አድርገው በእነሱ ቤት መሆኑ ነው ፈንጥዘውበታል። ምክንያቱም ገድል፡ ተአምር፡ ድርሳን፡ የሚተረጉም ሰው ማግኘት ማለት በእነሱ ቤት ለዚች ቤተ እግዚአብሔር መቅሠፍት ወረደባት ብለው ዓላማቸው ተሳክቶላቸው ውስጠ ምሥጢር አዋቂ ሰው እገኙና በምድር ደስታ ሆነ ብለዋል። እኒህ «ገድል ወይስ ገደል» ብለው የጻፉ ሰው የሚጠየቁት ጉዳይ አለ? እሳቸው ማን ናቸው? ማን ነዎት? ማንነታቸውን ደብቀው ቀርበው የቤተ ክርስቲያንን ውስጠ ምሥጢር አውቃለሁ ብትንትኗን አወጣታለሁ ብለው የቀረቡ ሰው ለመሆናቸው ማስረጃው በመጀመሪያ ስማቸውን ደብቀው የክርስትና ስማቸውን ብቻ መናገራቸው ነው። እንዳንዶችማ ፎቶግራፋቸውንም ሳይቀር አይደለም እንዴ ከመጽሐፋቸው ላይ የሚስቀምጡት? እንኳን ሙሉ ስማቸውን መንገር ይቅርና የአያቶቻቸውንም ስም ከዚያም አልፎና ተርፎ የተወለዱበትን መንደር ሳይቀር ነው የሚያስቀምጡት። ያም ማለት ስለኔ ለማወቅ ከፈለጋችሁ ሂዱና ጠይቁ ማለት እኮ ነው። መልካም ነው ሽጋ ነው።

እሳቸው እዋ ጌታቸው ግን ስማቸውን በሙሉ ማሥፈር ራሱ በሥውር የሚሠሩትን የሚያጋልጥባቸው መስሎ ስለታያቸው ማንነታቸውን ደበቁት። ይህ ራሱ ሠይጣናዊ ሥራ ለመሆኑ ተጨባጭ ዋና ማስረጃ ነው። ከእኒህ ሰው ምን እውነት ይጠበቃል? ከዚህ ውጭ ምንም ዓይነት ከእሳቸው መጽሐፍ አይጠበቅም። የሚገርመው ግን ማንነታቸውን የእሳቸው ፓስተር አመጡባቸው። ቢያንስ ቢያንስ «በጨለማ የኖሩ አሁን ግን የወንጌል ብርሃን የወጣላቸው» ብለው

አቀረቧቸው። እሳቸው ግን ስመ ጥምቀቴ ገብረ ኢየሱስ ብለው የቤተ ክርስቲያን ልጅ መስለው ለማሳሳት ነበር የተነሡት ብዙም ሳይሄዱ ራሳቸውን በራሳቸው ኢየሱስ በገሀድ አጋለጣቸው። በሥውር ሊያሳስቱ መጡ በገሀድ ተጋለጡ። ይህ ራሱ እንዱ የተአምረ ኢየሱስ ክፍል የሚሆን ነው። አይመስላችሁም?

ከመምህር ጌታቸው መጽሐፍ «ከገድል ወይስ ገደል» ውስጥ ጥቂት ልጥቀስ። ... ስሕተቱ እንዲታረም ወደ ቀደመው የሐዋርያት ትምህርት እንመለስ ብለው የተነሱት ሰዎች መሪ የነበረው መነኩሴ አባ እስጢፋኖስ «ለማርያምና ለመስቀል [ለእንጨቱ] የሥላሴ ክብር ይገባቸዋል በክብር ከሥላሴ ጋር ተካክለዋልና» ስግደት ይገባቸዋል የሚለውን ወንጀል ሲቃወም «እንስ ኢይሰግድ ለባዕድ ዘእንበለ ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ» ትርጉም «እኔስ ለአብ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ እንጂ ለባዕድ አልሰግድም» ብሎ እንደነበር መዘክሮቹ ያስረዳሉ» [ገድል ወይስ ገደል ገጽ 9 ፡ 1995]

ከዚህ ላይ ቅድስት ድንግል ማርያም ለወልድ ባዕድ ናትን? የድንግል ማርያምን ሥጋ ባይዝ ወይንም ባይለብስ ኖሮ ኢየሱስስ የምንለው ይኖረን ነበር ወይ? ኢየሱስ ብለን ያወቅነው እኮ ከቅድስት ማርያም በመወለዱ ነው። መስቀሉስ ለኢየሱስ ባዕድ ነውን? ሥጋውን የቆረሰበት? ደሙን ያፈሰሰበት ምሕረት ያወጀበት እይደለምን? በዚህ መስቀል ላይ ባይሞት ድኅነት ነበረን? ከመስቀሉ ላይ ሆኖ ነፍሱን ሲሠጥ ፀሐይ አልተጋረደችምን? መሬት አልተንቀጠቀጠችምን? መስቀሉ ለኢየሱስ ባዕድነቱ ከቶ ከምኑ ላይ ይሆን? እናትና ልጅ ባዕድ የምታደርጉ በስምም በግብርም ሠይጣናት የሆናችሁት ብቻ ናችሁ። የእናትና የልጅን ዝምድና ምን እንደሚመስል መዝገበ ቃላት ተመልከቱ። እናትና ልጅን የሚነጣጥል አሁንም ሰይጣን ብቻ ነው።

ስለ እባ እስጢፋኖስ «ደቂቀ እስጢፋኖስ» የተሰኘ መጽሐፍ በቅርቡ ያነበብሁት የገድል ትርጉም ይታወሰኛል። ታዲያ መጽሐፉን ጠላቶቻችን ጠምዝዘው ሊጠቀሙበት ይችላሉ የሚል ስጋት እድሮብኝ ነበር። ሥጋቴ እውን ሆነ። ይኸው አሁን ሠይጣኑ «ገድል ወይስ ገደል» ከተሰኘው የክህደት መጽሐፉ ውስጥ ማስረጃ ሆኖ ቀረበላቸው። ሠይጣኑ እይመረምሩም አያገናዝቡም ያን ለማድረግ ደግሞ መጻሕፍቱን ማሄድ ወይንም መቀጸል ይገባል። ስለዚህ ምክሬ ፀርበሬን ለነፋስ አያሳዩም ነው። ወይንም እያያዙንና አጠቃቀሙን አብሮ ማሳወቅ ይገባል። ያለበለዚያ «ሥጋ ያለ ቤቱ ጥንብ ነው።» መሆኑ ነው።

መምህር ጌታቸው ወስመ ጥምቀቱ ገብረ ኢየሱስ «በገድል ወይስ ገደል» መጽሐፋቸው ለለ ጸሎተ ፍትሐት ሲተቹ ከግንዘቱ ውስጥ ጠቅሰው «እምድኅረ ሞቱ ለሰብእ አልቦቱ ንሥሐ» ይላል ብለው በለሚደረገው ጸሎተ ፍትሐት ነቅፈዋል። ይህን ግንዘቱ ከጻፈ የአሳቸው ስፈፋ ከምኑ ላይ ነው? ግንዘቱ ላሉት ላልሞቱት ማስጠንቀቂያ ማስተማሩኮ ነው። ቀጥለውም በጸሎተ ፍትሐት ጊዜ መዝሙረ ዳዊት የጸሎቱ ክፍል እንደሆነ ተናግረው በፍትሐቱ ላይ አንድ ምዕራፍ ሳይሆን የሚጸለየው እንዳሰ መዝሙረ ዳዊቱ አንድ መቶ ሃምሳው ምዕራፍ ነው። እሳቸው ግን አንዱን ምዕራፍ ሃምሳ አንደኛውን ቆንጽለው ከውስጡ ያለውን ጥሬ ንባብ ያሳያችሁ አውንም ልድገመው ጥሬ ንባብ ጠቅሰው ካህናቱ ፍትሐት ብለው ርግማን ሕዝቡ በማያውቀው በግዕዝ ያነበንቡበታል ብለዋል።

እኔህ መምህር ጌታቸው ይቀልዳሉ። መዝሙረ ዳዊቱንም እንደ ገድሉ አውጥታችሁ ጣላችሁት? ምኑ ሊቀራችሁ ነው? ያ ሃምሳ ነብር አየሁ ያለው ሰውና አሳየህም የሚለው ተመዳዳሪው ንግግር ታወሰኝ። አየሁ ብሎ ካቀረበው ሃምሳ ነብር ውስጥ አንድ እንኳ አሳየህም አስኪለው ድረስ በክርክሩ ቆይተው በመጨረሻም አንዱንም ነብር አሳየህም ተራ አደረለው። እሱንም አሳየህም ሲለው ያየሁት የነብሩን ጅራት ነው አለው። አሁንም ውሸታም ጅራቱን አሳየህም አለው። በመጨረሻ በለው ነብሩን ያለ ጅራት እስቀረው አለ ይባላል። አሁንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የጎዳን መስሏችሁ መዝሙረ ዳዊትንም አውጥታችሁ ጣላችሁት? ምኑ ሊቀራችሁ ነው? ይህ የሚያሳየው ተንኮልና በሕተት ፍለጋ ብቻ እሱም ማደናገሪያ የሚሆን ስትፈልጉ ከጉድጓዱ ውስጥ ገላችሁና ወደቃችሁ።

እኛ ከስሕተታችን የማንማር ዝንጉዎች ሆነን ነው እንጂ! እነ አባ ማለያስ በቆፈሩት ጉድጓድ ላይ ነው እኮ! አሁን ፕሮቴስታንቶቹ የሚሠሩትን ቤት የሚገደግዱት። በአውኑ ስላማችንን ነሥቱው፥ መሣሪያ አድለው፥ ርስ በራሳችን አዋግተው፥ አገራችንን ቀምተው፥ የእነሱን ዓላማ የሚያራምዱትን ወታደሮች ከድንበራችን አሥፍረው፥ የሰላም ጠባቂዎች ይሉናል። የራሳችንን ለዎች መልምለው፥ ነፃ አውጭዎች ብለው እንደሠየሟቸው ማለትኮ ነው።

አሁን በባሕር ምድር [በኤርትራ] የሚታየው የኑሮ ውጣ ውረድ ጤፍ በወርቅ ሚዛን እየተሸጠ አይደለምን? ይህ ነው ነፃነቱ? ወንድምን ከወንድሙ፥ እኅትን ከእኅቷ፥ የልጅ ልጅን ከአያቱ የተለየበቱ? አቤት የሀገር ፍቅር ማኅበር ልጆች፥ ወንድሞቻችን፥

እኅቶቻችን እንዴት አለቻላችሁ? እንዴትስ ታገሣችሁ? ቁጣችሁን ማን በላው? ገጸ ባሕርያችሁን እንዴት እንደ ጨው አሟሙላችሁ? እግዚኦታ አሁንም ለእናንተ እነሆ! ባለቤት ሲመህ ነው ጎረቤት የሚደርስውና ጩሁ እንመጣለን። የሞቀ ቤቶቻችሁን በውሸት ተታላችሁ ጥላችሁ ሄዳችሁ። እንመለስ በትሉ እነሆ በየፋፋው በሣር ዳስ ወድቃችሁ፥ በገዛ አገራችሁና ተወልዳችሁ ባደጋችሁበት መንደር ለደተኞች ተብላችሁ ታሥራችሁና ተገዝችሁ ትገኛላችሁ። አይገርምምን? አያሳዝንምን? በእውኑ ዋይታና ልቅሶ ለወንድሞቻችንና ለእኅቶቻችን፥ ለእናቶቻችንና ለአባቶቻችን ይገባል።

ከዚህ ላይ ነው ውሾችን ደህና አድርጎ መፍራት የሚገባው። የቀደዷቸው በሮች ጅቦችን አለገብተው፥ ማንነታችንንና ያለ የሌለ ጥሪታችንን የርዳታው በቆሎ በመጣበት ጆንያ ወርቁ እየሞላና እየታሠረ በመውጣት ላይ ያለው። እንግዲህ በተቀደደው ግድግዳ የገቡት እነ በም አይጠሬ መምጣታቸውና መግባታቸውም ታሪካዊ ቦታዎቻችንን ለመሳብኘት ሳይሆን ማንነታችንን ለማጥፋት፥ ህብታችንን በዓየሩ ጋኔን እየጫኑ ለመሳተት እንጂ! የውሾችም ጥርስ የሚፈራው በበር ቀዳጅነታቸው ነው። ለዚህም ነው በአባባላችን «የውሻን ጥርስ በአጥንት ይፈሩ» የተሰኘው።

ስለዚህ በሃይማኖት የመጣ ጠላት ራሱን የቻለ ትልቁ ማን ብለን እንጥራው? በሙ ሲጠራ ደግሞ ከያንዳንዳችን ራስ ላይ ወጥቶ ቁጢጥ እንዳይል አያ ስም አይጠሬ ብለን እንለፈው? ይልቁንስ ኢትዮጵያ የገባውንና ያለውን ለም አይጠሬ በቶሎው እስከ ሠንኮፋ ነቃቅለን እንጣለው። ታሪክ ራሷን ትደግማለች እንዲሉ አድዋን እንድገማት። ታዳጊ ሕፃናት ልጆቻችንን በክሎና ማንነታቸውን አለክዶ እንደ ሄሮድስ ከመፍጀቱ በፊት አሁኑኑ በተግባር እንላለን። ልጆቻችንን የመጠበቅና የመንከባከብ የወላጅነት አደራ አለብንና ኃላፊነቱ ለያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ወላጅ ሁሉ ብሔራዊና ሃይማኖታዊ ግዴታው ነው።

የኢትዮጵያን ማንነት ይዛ የምትወዛወዘዋን ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ሃይማኖት ለማጥፋት የተጠነሰሰው ሤራ የሚያደርሰው ጥፋትና ዕልቂት ከኤይድሱ በጥፍ የባሰ ነው። ጥያቄው የመኖርና ያለመኖር ነው። ደርግ የኢትዮጵያን ሕዝብ ህብትና ንብረት ሲወርስ የቤተክርስቲያኗንም መተዳደሪያ ህብት ወርሶባታል። በዚያም ምክንያት ቤተ ክርስቲያኗ ተቸግራ ባለችበት ወቅት ታላቁ አባት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ወዕጨጌ

ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ለደርግ መጋቢት ፩ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. በጻፉት ደብዳቤ እንዲህ ብለው ነበር።

... በዚህ ጊዜ አንድ ሊዘነጋ የማይችል እውነት ሊነገር ይገበዋል። በአሁኑ ጊዜ የሚባለው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም እንደ ሌሎቹና የሃይማኖት ድርጅቶች ሁሉ የቆየ ይዞታዋን አጥታ ድጋፍን ከሌሎች ትጠይቅ የሚል ይመስላል። እስቲ ከማን ትጠይቅ? ከሳውዲ ዓረቢያ ነውን? ከቫቲካን ወይንስ ከዓለም ሉተራን ድርጅቶች? ይህ ሁሉ እንዳይሆንማ ጥንታዊቷና ኢትዮጵያዊቷ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያናችን ... ችግር ቢደርስባት አቤት የምትለው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው።»

[ከመምህር ኪዳነ ማርያም ጌታነህ መጽሐፍ፣ *«የሐሰት ምሥክርነት ለቋሚ ምሥክርነት የተሠጠ መልስ»* አዲስ አበባ 1994 ዓ.ም ገጽ 101]

ቅዱስነታቸው በደብዳቤያቸው አገላለጽ የኢትዮጵያ ሕዝብና የአርቶዶክስ ሃይማኖት እንደ ፀሐይ ብርሃንና ሙቀት የማይለያዩ፣ አንድ ባሕርይ መሆናቸውን እንዳረጋገጡት ሁሉ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ብቸኛ ብሔራዊት ኢትዮጵያዊት ሃይማኖት ናት። ይህ በግልጽና በይፋ የታወቀና የተረጋገጠ ፀሐይ የሞቀው፣ አገር ያወቀው እውነታና ዓቢይ ጉዳይ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ የቱርክን እስላም ወረራና የካቶሊኩን ሼራ ደሙን አፍስሶ አጥንቱን ከስክሶ ያቆየው በዚችው ብቸኛና ብሔራዊት ሃይማኖት መሪነት ነው። ይህንኑ ነው ቅዱስነታቸው ያረጋገጡልን።

ስለሆነም ትላንትም ሆነ ዛሬ ኢትዮጵያውያንን ከሚያጠፋና ከሚያሳቁል ሃይማኖት እኛነታችንን እንጠብቅ። ልጆቻችንን ከነሱ ጉያ እንፈልቅቅ። ከበጎች መካከል ገብቶ የሚጸልይ የቀበሮ ባሕታዊ [ሚሺነሪ] የተልዕኮው [የሚሽኑ] ፈሊጥ ምን ለማድረግ ይሆን? «የጨው ገደል ሲናድ ሞኝ ይለቃል፣ ብልህ ያለቅሳል» ይጠበቅ። በእውኑ ከባዕዳን ሃይማኖት ድኅነት፣ ከጅብ ቤት ቁርበት ለማግኘት ማሰብ በከንቱ መታከት ነው። እንዲያውም «ልፋ ያለው በሕልሙ ኩንታል ሲሸከም ያድራል» መሆን ነው። ይህን ደግሞ በዚሁ ፈሊጥ ያደጉና የተመነደጉ ከናታቸው ማኅፀን ሰውን ለማሳሳት ከተመለመሉ ከጥቂት የጥፋት ልጆች በስተቀር ማንም ያውቀዋል።

ስለዚህ ኢትዮጵያውያን ሆይ! ችግሩ የስንዴና የበቆሎ ጉዳይ አይደለም። ችግሩ የማንነት የኢትዮጵያዊነት ጉዳይ ነው። በተለይ ልጆቻችን በየጴንጤው ጸሎት ቤት ሄደው ሲውሉ ገናና ኳስ ጨዋታ ሊያዩ ወይንም ሆያ ሆዬ ሊጫወቱ አይደለም። የሚጫወቱት ግን በባሕላቸው፣ በታሪካቸው፣ በቋንቋቸውና በጠቅላላው በራሳቸው ማንነት ላይ ነው። ሲመለሱም እንዳይሆኑ ሆነው ማንነታቸውን ተነጥቀው፣ ሃይማኖታቸውን ለውጠው፣ በአባብ መርዝ ተነድፈው፣ በዕፀ በለሱ ደንዝዘው፣ ፈዘውና ደንግዘው ሲያለቅሱ ውለው ነው።

ከዚህ ላይ ነው የወላጅነት አደራ ያለብን። ልጆቻችን እባብ በአንገታቸው እየጠመጠሙ ሲጫወቱ እያየን መላእክት ይጠብቋቸዋል ብለን ችላ ብንል በሚደርሰው አደጋ ፀፀታችን ምንግዜም ከልባችን የሚወጣ አይሆንም። የታሪክም ተወቃሾች ያደርገናል። በማንነታችን ላይ የመጣ እጅግ በጣም አደጋ መሆኑን በሚገባ ተገንዝበን ተተኪውን ትውልድ እንጠብቅ። ያለበለዚያ ሁለት ችግሮች ይገጥሙናል። አንደኛው የወላድ መካን ያደርገናል። ሁለተኛው ሃይማኖት፣ ሀገር፣ ባህል፣ ታሪክና ወግ የሌለው ትውልድ ተክተን ማለፋችን ያስቆረጠናል። በምድር ያስወቅሰናል፣ በሰማይ ቤትም ያስኮንነናል። የኢትዮጵያንም ጥፋት እውን እናስደርጋለን።

ይሁንና እኛም እንደ ቀደሙ አባቶችና እናቶች ይህን ሰው ሠራሽ ችግር ጥርስ እናክም ብለው ከሚሠብሩ፣ ዓይን እንኳል ብለው ከሚያጠፉ፣ የጆሮ ጌጥ ማሳያ ብለው የጆሮ ነጋሪት ከሚቀዱና ከሚያደነቁሩ የእፉኝት ዘሮች ልጆቻችንን ካልጠበቅን ራበን ሲሉን በዳቦ ፋንታ ድንጋይ፣ በዓሣ ፋንታ እባብ የምንሠጣቸው ወላጆች መሆናችን ነው። ያለበለዚያ ግን አሁን በመደረግ ላይ ካለው ትዕይንት ልናድናቸው አንችልም። ይህ የሚያሳየው ከጎላፊነት ርቀን የምንገኝ ለመሆኑ ታላቅ ማስረጃ ነው። ልጆቻችንን በዕንቁላሉ ጊዜ እንምከራቸው። በሬ ሠርቀው በሚገረፉበት ጊዜ ምነው ልጄ ብንል በዕንቁላሉ ጊዜ በመከራችሁን የሚል መልስ እንደምናገኝ ግን አንጠራጠር። በሰኔ ያልተዘራ በጎዳርና በታጎሚስ አይታወድም። በጥርና በየካቲትም ጎተራ አይገባም። ስለሆነም አስቀድመን ካልገታነው ውጤቱ ደግሞ እኛንም ሆነ ልጆቻችንን በጥቅሉ ሁላችንንም የሚጎዳ ለመሆኑ ለዓይን ቅጽበት ያህል እንኳን አንጠራጠር። በገዛ አገራችንና መንደራችን መጻተኞች አንሁን። ዝምታ በዝቷል። የዝምታ ብዛት ደግሞ የጥፋት ሰመመን ነው። ይህንኑ አበው በምሳሊያዊ አነጋገራቸው እንዲህ ብለውታል። «ዝምታ ለበግም አልበጃት አሥራ አምስት ሆኗ አንድ ቀበሮ ፈጃት።» ከዚህ ተግባራዊ አመክሮ፣ መማር መመራመር፣ መገንዘብ የእያንዳንዳችን

ኢትዮጵያውያን ሁሉ ሙሉ ኃላፊነት ነው። ምሳሊያዊ እነጋገሩም የእውነቱ ማረጋገጫ ነውና ትኩረት ልናደርግበት የሚገባ ዓቢይ ጉዳይ ነው። ይህን ባናደርግ ግን የሁለት ዓለም ስደተኞች ለመሆናችን ማረጋገጫ ነው።

ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ሆይ! ከሚመጣው ሳይሆን አሁን ከተጋፈጠን መዓት ራሳችንን እንጠብቅ በከፍተኛ ደረጃም እንጠንቀቅ። ተግተን እንጸልይ። ራሳችንን ከጠላት ፈተና እንለይ። ኢትዮጵያውያን የሃይማኖት ችግር እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ፈጽሞ የለብንም። አይኖረንም። እንዲያውም ተርፎን ከሃሌ ሉያ እስከ አሜን ለዓለም ሕዝብ ሁሉ አድለናል። ይህም ራሱ የግዕዛችንን ቀዳሚነት ያስረዳል። ለዚህ ሁሉ ታላቁ ማለረጃችን ታሪካችን ነውና እሱኑ እናጥና።

እንዲያውም የኛ ሃይማኖት በገንዘብ የተገዛና በደም የተመሠረተ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ተፈቅዶ የተሠጠን እንጂ! የሚያስደንቀው ዓቢይ ነገር የራሱን ሰብዕና ለማብሠር መልአኩን ወደ ቅድስት ድንግል ማርያም እንደላከው ሁሉ በዚሁ አንጻር ለሚወዳቸው ለድንግል ማርያም አደራ ለሠጣቸው ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ መልአኩን ወደ ፊልጶስ ልኮ ኢትዮጵያዊውን ባለሥልጣን፥ የንግሥቲቷን እንደራሴ ባኮስን ወይንም በተለምዶ በሚታወቀው ስሙ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባን እንዲያጠምቀው አድርጓል። ከዚህ ወዲያ ሃይማኖት፥ ከዚህ ወዲያ ታምር ምን አለ? ይህን እያወቁ ከዚህ ውጭ ሃይማኖት ይዘን መጥተናል። የናንተው ግን ያረጀና ያፈጀ ነው ቢሉን በእውኑ እናትህ አርጅታለችና ከዚህ ወዲያ አትጠቅምህም ከቤትህ አውጥተህ ጣላት ሠይጣናዊ ዓይነት ምክር አይደለምን? በዚህስ ምክራቸውና ውትወታቸው ተገፋፍተን እናታችንን አውጥተን እንወረውራለንን?

እነሱማ የማይሉን የለም። ስለ ጌቶቻቸውም ሲናገሩ፥ እኒህ እነ አባባ ቀዩ ቆርቆሮ በሰማይ የሚያበሩ፥ በምድር ብረት የሚያሽከረክሩ፥ ሽክላውን የሚያናግሩ፥ ለትንግርቱ ለታምሩ የተፈጠሩ፥ እንደ በረዶ የነጡ የነጡ ናቸው። የሚሠጡትም ገንዘብ ከኪስ ተርፎ በሳንዱቅ የሚኖር፥ እሱምኮ! እሱም እንጂ! ዶላሬ ዶላር ነው። አይ ቀልድ ይች ናት ለካ እውነቷ አርጅታ ነዋ ውሸት የተባለችው። ለነገሩማ የኛዋን እጾላ ወስደው ለሚን ቀያይረው፥ እ፡ን፡ አጥፍተው ር፡ን፡ ጨምረው ዶላር እንጂ ከየት አመጡት? [እ ፡ ዶላ ፡ር] ያውስ ከአዶላ መች ወጡና! «እንኳን ይችን የዝንብ ጠንጋራ እናውቃለን» የምንለውን ጠበብት ቀን የሠጠው ቅል

ድንጋይ ሠበራውን አወረዱብን። ቅሉ ድንጋዩን ሠቀረው። ጉድ የእነጉድ ጉዳጉድ ሆነና በዘመኑ የማይሆነው ሆነ።

ከታሪካችን እንደምንረዳው ሚሽነሪ ሲባል ነቃቅለው እስከሚጥሉን ድረስ የኛን ቆዳ ለብሰው፥ እኛን ተመስለውና አክለው በምትሐታቸው ወርገው ገብተው በወንፊቱ ቀዳዳ ሾልከው፥ ጎብስተ መና መስለው ያው ከለማይ የመጣን ማለቱ ይቀላቸዋልና ከሞሰበ ወርቁ ውስጥ ሲከፈት ተገኙ። ታዲያ የኛዎች አደንቋሪዎች ደግሞ የሚሉትን እንሰማ፥ የሚሠጡንን እንቀበል ይሉናል። ከፊትም ነበሩ አሁንም ይኸው በገሀድ አሉ። ቁንጣውና ትኋኑ የተዘከረውኮ ለከንቱ አይደለም። እንደ ፓስተሮቹ የአባባል ፈሊጥ፥ ሃይማኖትህን ብትለውጥ፥ በሱፍና በኩፍ ጣማ ትዘንጥ ነው።

ከዚያም ባሻገር የሚሉህ፥ በስፖንጅ ፍራሽ ትተኛለህ። የላመ የጣመ ትበላለህ። የነጣ የተዋበ ነዋ ትለብሳለህ። ባማረና በተዋበ ቤት ውስጥ ትኖራለህ። በቂ ደሞዝ አንኳን ላንተ ለዘመዶችህ የሚበቃ ታገኛለህ። አሜሪካ ሄደህ ትሠለጥናለህ። ከዚያም አውሮጳ ኤሺያ ለስብሰባ ባመት አራት አምስት ጊዜ ትጓዛለህ። ታዲያ ከገዳም በቁንጣና በትኋን ለምን ትበላለህ? ገዳሙን ጥለህ ውጣ የሚለው ምክራቸው ቢነበነብልህ ምን ታደርጋለህ? ከወጥመዳቸው ትገባለህ? ወይንስ ዘለህ ፎክረህ ከወጥመዳቸው ታመልጣለህ? እንተ ማን ነህ? አገርህንና ሃይማኖትህን የምትሸዋ የምትለውጥ? ገንዘቡም ያልቅና ቤቱም ያረጅና ይህም ቀን ያልፍና ያስተዛዝበናል ብትገኝ ጎዳና! ወገን ተጠንቀቅ። ራስህን ጠብቅ። «ዓለሙኒ ኃላፊ ንብረቱኒ ኃላፊ አለመ ኩሉ ኃላፊ ውእቱ።» [ዓለሙም ያልፋል ንብረቱም ያልፋል ሁሉም ኃላፊ ነው።] አገርህን ግን ጠብቀህ ለተረክዚው ትውልድ ማስተላለፍ የግዴታ ግዴታህ ነው።

ፓስተሩ ወደ ገዳሙ የሄዱት መነኮሳትን ለማጥመድና ለመመልመል ነበር። ነገር ግን የሄዱበት እኩይ የምልመላ ተልእኳቸው [ሚሽናቸው] ላይሳካላቸው በመቅረቱ ነው መነኮሳቱን ቡትቷም፥ ትኋናም፥ የቁንጣ ራቶች ብለው የረገሟቸው። ስለሆነም አሁንም እንደገና በድጋሚም ኢትዮጵያውያን የሃይማኖት እርጥባን ጨርሶ አንፈልግም። ከድጎነታችን ብዛት የተነሣ ይመስላል የማይሠጠንና የማንቀበለው ነገር ከቶ አልኖረም። የኤይድስ በሽታም በርዳታ ከመጡልን መቅሠፍቶች አንዱ ሆኖ መቆጠር ያለበት አይደለምን? ያለበለዚያማ በሽታው ኢትዮጵያ ውስጥ የትኛው ክፍለ ሀገር፥ አውራጃና ወረዳ ነው ተፈልፍሎ ያደገው? የሚያሳዝነው እሱም እንደ ርዳታ እህል ከለጋሽ አገር ለሕዝቡ በነፃ መታደሉ

ነው። ኤይድስም ርዳታ ሆኖ በነፃ ለመታደል ኢትዮጵያ ሲገባ ዕጃችንን ዘርግተን ተቀበልነው። ታዲያ ምን እያደረገን ነው? እሱን በልተን ጠግበን ከዚያም በላይ በቁንጣን እየረፈረፈን አይደለምን? እነሱ እንዳሰቡት ከረሀቡ ለአንድ ጊዜ ሳይሆን ለሁልጊዜም አንዳንራብና እንዳንጠማ የሚያደርገን ሆኗል። ከዚህስ ወዲያ ከርዳታ ሠጭዎቻችን ምን እየጠበቅን ነው? በራስ መተማመን ከሁሉ በላይ እውን አሁንም እውን ነው።

የዚህ የኤይድስ በሽታ እንዲህ በዓለም ዙሪያ ፈጥኖ የገሠገሠበት ዋና ምክንያት ምን ይሆን? ለኔ አንድ ነገር ይታየኛል። ቅኝ ግዛቱም አረጀ አፈጀ። ምንምኳን በዕጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ለመታደስ ቢሞክርም ድሪቶ ሆነባቸው። ስለዚህ የፈለጉትን አገር ለመያዝና የራሳቸው ለማድረግ በዲሞክራሲ ስም በእንደራሴዎቻቸው ለመግዛት ቢሞክሩም ሁሉም አገር ላይ እንዳሰቡት ሊሠራላቸው አልቻለም። ጀርባቸውን የሚሠጡ አገሮችና እንደራሴዎች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ። ነፃ አውጭዎችም የተፈለገውን ያህል በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ጀመሩ መዘበራረቅ፥ የተሠጣቸውን ትዕዛዝ አደረጉት ድብልቅልቅ። ሥራቸውም ሆነባቸው ልብ አውልቅ።

ስለዚህ እንደ አማራጭ ሆኖ ከተወሰዱት ርምጃዎች ውስጥ በዋናነት ከሚፈለገው አገር ላይ የሠፈረውን ሕዝብ በዘመናዊ ጥበብ ማጽዳት ነው። እሱም በኤይድስ በሽታ መጠራረግ ነው። ኤይድስ «ብዙ ተባዙ ምድርንም ምሉአት» ተብሎ ከአምላኩ የታዘዘበትንና የተሠጠውን የአካል ክፍል ወደ ማጥፊያነት መሣሪያ መለወጥ ነው። እሱን ለመከላከል ደግሞ የሰው ልጅ ዘሩ እንዳይበቅል በላስቲክ ከረጢት አፍኖ መግደል ነው። ይህም የሰው ልጅ መባዛት እንዲቆም የሰው ዘር ተዘርቶ እንዳይበቅል መካን እንዲሆን ለማድረግ ነው። ለዚሁ ዕቅድ በተጨማሪ ማስፈፀሚያ እንዲሆን የቀረበው ደግሞ ግብረ ሰዶምን ማስፋፋት ነው። እሱም ወንድና ወንድን፥ ሴትና ሴትን ማጋባት ነው። ሁሉ ነገር አሜሪካና አውሮጳ ተደረገና ተሠራ ሲባል የዓለም ሕዝብ በተለይም በመልማት ላይ ያሉት አገሮች መቀበላቸው የውዴታ ግዴታቸው ነው ብለው ስለገመቱት ነው። ይባስ ብለው የሰዶማዊ ካህናት በይፋም እየተሾሙ ነው። እንግዲህ እኒህ ግልጽ የሆኑት የሰው ዘር ማጥፊያዎች እንዳሉ ሆነው የሴቶችን ማኅፀን ከሚያመክኑ ልዩ ልዩ መድኃኒቶችና እያስወረዱ አውጥተው ከሚጥሏቸው ሕፃናት ባሻገር መሆኑ ነው።

መቼም የማይሆነው ሲሆን ድህነታችን ከስንዴ አልፎና ተርፎ ሃይማኖትም ላይቸግረን በርዳታ መልክ የሃይማኖቱንም መግለጫ መጽሐፍ ቅዱሱን እንደ ስንዴው በመርከብ ጭነው አመጡልን።

በዚያውም ላይ የኢትዮጵያን ስም ሠርዘው ደልዘው መኖሩን ጨርሰው አጥፍተው እንኩ ከኢየሱስ ጋር ተዋወቁ አሉን። ከዚሁ ርዳታ ነበር ፓስተሩ ለሄዱበት ገዳም እንዲነበብ የለገሡት። ታዲያ እነ ፓስተር ሮህ ብለው ሃሌ ሉያ! በሉ ይሉናል። የሚያስፈልገንንና የማያስፈልገንን ለይተን እንዳናውቅ ደግሞ እርስ በራሳችን እንዳንመካከር በመካከላችን በስንዴው ኢትዮጵያዊነት እርሻችን ላይ የጥላቻ እንክርዳድ ዘርተውበታል። ስለሆነም ሕይወታችንን ጥርስ ለጥርስ፥ ዓይን ለዓይን እንዲሆን አድርገውታል። የኛን ጥንታዊነት፥ ኦሪታዊነት፥ የሙሴን ሕግ ተቀባይነትና አመንጭነት፥ ከዚህ ላይ ነው ያወቁልን። ለኛ መለያና መነጣጥያ ያገለገላቸው እሱ ሆነና ነው። በሌላ ገጹ የኛ ጥንታዊነት ደግሞ የጠቡ መጫሪያ ክብሪት ሆኖ መቅረቡንም እናያለን። ኢትዮጵያውያን ሆይ! ምንም ብንራብና ብንጠማም የሃይማኖት ችግር ግን ፈጽሞ የለብንምና የርዳታውን አቅጣጫ ከቤታችሁ ለተራቡት ይሁን በቃን እንደነሱ እናመሠግናለን እግዚአብሔር ይባርካችሁ አንበላቸው።

ኢትዮጵያውያን ፓስተሮች ወይንም ራሳቸውን እንደሚጠሩት እረኞች ከእንዲህ ካለው ጦርነት በአዛኝነት ለምን ተመደቡ? የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኢየሱስን አታውቅም ብሎ ለመፋለም ሳይሆን ፓስተሮቹ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክና ማንነት አያውቁም አልልም። ነገር ግን የተጣለባቸውን ፕሮቴስታንታዊ፥ ጴንጤያዊ፥ ጉጎላዊ [የጥፋት] ተልዕኮ ለመፈፀምና ለማከናወን «ከተት ሠራዊት፥ ምታ ነጋሪት» ብለው ስለተነሡ እንጂ!

በእውኑ ኢትዮጵያ ሃይማኖትን ለመጀመሪያ ጊዜ ለዓለም ያሳወቀች መሆኗን ባይማሩት እንኳን እንዳነበቡት ጥርጥር የለኝም። ታዲያ ከዓለም ሕዝብ በፊት አምላክ ፀሐይ ብላ እግዚአብሔርን ስታመልክ የነበረች፥ ከዚያም ብሱይ ኪዳንን ተቀብላ በዕምነት ፀንታ የኖረች ኢትዮጵያ ስለ ኢየሱስ መውረድ፥ መወለድ፥ ትንቢት አመሥጥራ፥ ሱባዔ ቆጥራ፥ በነገሥታቷ አማካኝነት ለተወለደው መሢህ ሕፃን ገፀ በረከት ያቀረበች፥ ከዚያም በላይ ሕፃን ኢየሱስን ተቀብላ ያስተናገደች፥ ኢትዮጵያ አይደለችምን? በጴጥሮስስ ስብከት በሃምሳኛው ቀን የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ስትመሠረት ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ቋንቋ ከሐዋርያት ልሣን ሰምተው በመደነቅ ክርስትናን ተቀብለው አልተመለሱምን? እንዲሁም ፊልጶስ በእግዚአብሔር መልአክ ታዝዞ ባኮስን ወይንም ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ የሚያነበውን ተርጉሞለት አምኖና በዕደ ፊልጶስ ተጠምቆ እምነትን ከጥምቀት ጋር አዋሕዶ ሥርዓት ይዞ አልተመለሰምን? ይህ

ድርጊት ኢትዮጵያዊ ለሆነ ሁሉ ታላቅ ፀጋና ክብር ነው። ከዚህ ወዲያ ሃይማኖት ለመቅሠፍት ነው። በተዉግሪም ማቴዎስና ማርቆስ ኢትዮጵያ መጥተው አስተምረውና አጥምቀው ክርስትናም መሠበኩን አረጋግጠው አልተመለሱምን? ታዲያ ይችን የመሠለች አገርና ሃይማኖት ኢየሱስን አታውቅም እንዴት ይሏታል???

በአሥራ ስድስተኛው ምዕተ ዓመት የተጀመረ ያውም ተቃዋሚ ሃይማኖት ሆኖ የተፈጠረ ይችን ታላቅ አገር ኢትዮጵያን ብሉዩንና ሐዲሱን ኪዳን አንደ ሐፍና ወርቅ አስማምታ ይዛ የነበረችና ያለች ወደፊትም የምትኖር አገርንና ሃይማኖትን ትላንት እመሻሽ የተወለደ ያይደለ የተፈጠረና የተድቦለቦለ ሃይማኖት እንዴት አድርጎ ኢትዮጵያን ኢየሱስን አታውቂም ሲል ይችላል? ምሳሌውን ልድገመው «ልጅ ለእናቷ ምጥ አስተማረች» ይሏል ይህን ነው። እንዲያው ለጠብ መማሪያነት ምን ምክንያት እንፍጠር? ሲባል የተገኘና ያለ ጉዳይ ሆኖ በመገኘቱ እንጂ! ክርስትና ከተሠበከ ከአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመት በኋላ መጥቶ ግለት አራት መቶ ዓመት አንኳን ያልሞላው «ሃይማኖት» የልጅ ልጅ ብኩርናችንን በጥሬና በርግጫ ልውሰድባችሁ ሲለን የታወሰኝ «በሞኝ ቤት ሌባ ተማታበት» የሚለው የአበው ምሳሌያዊ አነጋገር ነው።

በድጋሚም የነቀፋውና የዘለፋው መነሾ ምክንያት ሆኖ የቀረበው እንደ ውግሉው ውል ታቦት ነው። ታቦት ደግሞ በዓድዋው ጦርነት ላይ ታይቶ ክፉኛ ጥርስ ተነክሶበታል። በእውኑ ጽላቱ የእግዚአብሔር ስም የተጻፈበት ከእግዚአብሔር የተሠጠን ከብሉይ ኪዳን ጀምረን አክብረን የያዘነው ብቸኛ መታወቂያችንና መለያችን ሆኖ የኖረውንና ያለውን ክብራችንን እንዴት ሊንቅቱት ተገደዱ? እነሱ የያዙት መጽሐፍ ቅዱስ በእፍሪቃ ሕዝብ ካደረሰው የቅኝ ግዛትና የባርነት ጥፋት፥ ታቦቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ ከተመሳሳይ ወራሪዎች ዕጅ እንዳይወድቅ ተከላክሎለታል ተራድቶለታል። የእነሱ መጽሐፍ ቅዱስ አሁንም በጽኑ እንዲታወቅ የአፍሪቃን ሕዝብ ለቁንጣና ለትኳን ሠጥቶታል ከፋፍሎታል። ማንነቱን አጥቶበታል። ለባርነት ዳርጎታል። የሚናገርበትን ቋንቋ አጥፍቶበታል። የሚጽፍበትን ፊደል ደምስሶበታል። ታሪኩንና ማንነቱን አታጥሎበታል። በጎ፥ በጎ ለያይቶታል። ከልማት ይልቅ እርስ በራሱ እንዲወጋጋ አድርጎታል። እውነቱ ይህ ነው። «ኢትዮጵያዊ ጠይምነቱን ነብር ዝንጉርጉንቱን አይለውጥም» ኤር.13;23። ሲል ኤርምያስ ስለ ኢትዮጵያዊው የተናገረው ስለ መልኩ ብቻ ነውን? ስለማንነቱስ አያጠቃልልምን?

እኒያ ፓስተሮች ወይንም አረኞች የሚሏቸው ኢትዮጵያውያን ክንፈሮቻቸውን ሲያሸሹ ነጭ ነገር ይታይባቸዋል። ያ ነጭ ነገር ደግሞ አንገት ሲቆረጥ ይስታል የሚባለው ነው። በቀላል አገላለጽ ጥርስ-ነጭ ናቸው። አባባሉ ለካስ እውነት ነው። የኢትዮጵያ አንገት ሲቆረጥ የሚስቀውን ክፉኛ ተመለከትንባቸው። ከዚህ ላይ አንድ ምሳሌ ላቅርብ እሱም አንድ መንፈሳዊ አባት ሲያስተምሩን ከሦስት ነጭ ከሆኑ ነገሮች ተጠንቀቁ አሉን። እኛ የምናውቀው አንድ ነጭ ነበር ለካስ ሦስት ደርሰዋልና ብለን ስለማንነታቸው በጉጉት ስንጠባበቅ፥ እነሱም አሉና አንደኛ ቅቤ፥ ሁለተኛ ሥጣና ሦስተኛ ስኳር ናቸው ሲሉን ቀለል አለን። ይህን እንኳን አባባል የፓስተሮቹን አንኳ ነጮች አይመለከትም ይሆናል። ይሁንና ሥጣ እንኳን ሳይቀር በየመኳንንቱ ቤት ጎን ከዳቢት፥ ሽንጥ ከወርች፥ እየተባለ ሲሞናሞን ኖሮ ሳይታወቅ የክብር መግለጫ ሆኖ ሲሞካሹበት ሲፎክሩበት ዕልፍ አዕላፍ የኢትዮጵያን መኳንንት ከዉረስ በኋላ ዛሬ የነጭ ሽረኛ መሆኑ ተጋለጠ። ይሁንና ነጭ ከሚባልና ከሆነ ነገር ሁሉ መጠበቁ ታላቅ ምክር ነው። እነ ነጮ ከራስ እስከ እግር ይነጩ።

ፓስተሮቹ አይደለም ተለወጡብን። በማንነታቸው ላይ ይቀልዳሉ ያስቀልዳሉ። ጦር ያግዝዛሉ። በአሁኗ ሰዓት ይች ጊዜ ሳታልፍ ተመርጣ ይች ሥራ ለምን ተሠጠቻቸው??? የኢትዮጵያን አርቶዶክስ ተዋሕዶን ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ድንጋዮች መፈነቃቀላቸው ታይቶ አይደል? «አካሄዱን ዓይተህ ስንቁን ቀማው» የፈሊጣችሁ ክፍል ሆነና! ለተንኮሉ ጥንሰሳ በውስጥ አርበኞች «ገድል ወይንስ ገደል» ተብሎ ፊታውራሪው፥ መንገድ ጠራጊው፥ ዘበኛም አርቶዶክሳዊ፥ በግብር ፕሮቴስንታዊ የእቃኝነት ስብከቱን አስቀደመ። መምህር ጌታቸው ወስመ ጥምቀቱ ገብረ ኢየሱስ በተባሉ ሰው ተደረሰ የተባለው የፓስተሮቹ ዋቢ መጽሐፍ ገና ሽፋኑን ሲመለከቱት ማንነቱን ይረዱታል። መጽሐፉ ለመሸፈኛ የሚያሳየው የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ነው። ገባ ይልና አንድ ኢትዮጵያዊ አባት እንደ ሥዕሉ አቀራረጽ በሕይወት ያሉ የማውቃቸውን ይመሥላሉ። እሳቸው በዘንዶው ጅራት ወደ ገደሉ አፋፍ ላይ ሲወጡ የደብረ ዳሞ ተራራ ወይንም ገደል መሆኑ ይታወቃል። ከጎናቸው ግን የፈረንጅ መልአክ ቆሞ ይመለከታቸዋል የሚጠብቃቸውም ይመስላል። ከዚያ ወረድ ይልና በመምህር ጌታቸው ወስመ ጥምቀቱ ገብረ ኢየሱስ ይላል። መምህር ጌታቸው የአባታቸውን ስም እንኳን አልተጠሩበትም። የላቸውም ማለት ነው? ያው በስምና በግብሩ የታወቀው የማይባዛው አንድ ጊዜ ተፈጥሮ ፍጥረታትን ሲያስት የሚኖረውን ዲያብሎስን እንደ አባት ወስደውት

ነው ማለት ነው የሰው አባት ስም ያልጨመሩበት። በቅሎ አባትህ ማነው ቢሉት ፈረስ አጎቴ ነው እንዳለው ማለት ነው።

ሌላው የቀልዳቸው ብዛት የአባታቸውን ስም ለመንገር ያፈሩትና የደበቁት መምህር ጌታቸው ስመ ጥምቀታቸውን ሊነግሩን ተነሡ። ገብረ ኢየሱስ ሊሆኑ አይችሉም። በምንም መለኪያ ገብረ ሠይጣን ቢባል የሥራዎ አባት ነውና ይስማማል ባይ ነኝ። መምህር ጌታቸው ማንነትዎን እንኳን ለመግለጽ የፈሩ እርስዎ ማን ነዎት? ግዕዝ እየጠቀሱ የቤተ ክርስቲያን ሰው ለመሠል ያደናግራሉ። እርስዎ እንደ ማስረጃ የሚጠቅሱትን ቋንቋ መልሰው ሕዝብ በማያውቀው ቋንቋ አያነበንቡ ሲሉ በመጽሐፍዎ በገጽ ሃያ ላይ ተናግረዋል። ግዕዝ የኢትዮጵያ ቋንቋ ሆኖ ሳለ ታሪካችን፣ ሃይማኖታችን፣ ዕውቀታችን፣ ጥበባችን፣ ፍልስፍናችን፣ ሕክምናችን፣ ምሕንድስናችንና የሰው ልጅ ሥልጣኔ ሁሉ ሠፍሮ የሚገኝበትን ቋንቋ ማጣጣልና ማዋረድ ራሱ እንደ ይሁዳ ራስዎን በብር የሸጡ፣ የለወጡ መሆንዎን ያሳያል። በዚህ እንጠራጠርም። ስለ ግዕዝ ያለዎት ጥላቻ በጻፍቸው ቃላት ይገልጡታል። ግዕዝ መጠናትና መታወቅ ያለበትን ቋንቋ ማንቋሸሽና ማጣጣል ራሱ የኢትዮጵያን ማንነት መካድ ብቻ ሳይሆን ጦር ወርውሮ መውጋት ነው። የኛን ቋንቋ ጥለን የአውሮጳውያንን ቋንቋዎች እያስጠኑን ባለንበት ወቅት ተቆጭተው እንኳን ግዕዝ ተማሩ የኢትዮጵያን ውስጠ ምሥጢሯን እንድትመረምሩ ምነው ቢሉ ምናለበት? ይህ ራሱ ስለማንነትዎ ቁልጭ አድርጎ ያስረዳል። ይሁን እንጂ ተከናንበው ቢተኙ ገልጦ የሚያይ አምላክ አለና! የሚገርመው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የኛ እያሉ ለማደናገሪያነት መጽሐፍዎ ላይ ሲናገሩ በእርስዎ ቤት ሠይጣናዊው ሥራዎ እንዳይገለጽ ለማድረግና ማንነትዎን ለመደበቅ ነበር። ነገር ግን የራስዎ ለው ፓስተሩ ስለ ማንነትዎ እንዲህ ሲሉ ገለጹብዎት።

> ጌታ ኢየሱስ የከፈለው ዋጋ ያፈሰሰው ደም ለደኅንነቴ አይበቃኝም ብሎ መላእክትን ሰማዕታትን የሚጠራ ድንግል ማርያምን የሚጠራ ሰው የቀወሰ ሰው ብቻ ነው። ታውቃላችሁ ኢየሱስን ትተው ሌላ እማላጅ መፈለግ የሚሄዱ ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስን መናቃቸው እንደሆነ?
> በምድራችን ገድለ ተክለ ሃይማኖት ገድለ መንፈስ ቅዱስ ተአምረ ማርያም ጽላተ ሙሴ ድርሳነ ሚካኤል ወዘተ... የሚባሉ ብዙ ስፍር ቁጥር የሌላቸው አሉ። እነዚህ ምን እንደሆኑ ልንገራችሁ እነዚህ በፀረ ክርስቶስ መንፈስ የተጻፉ በክርስትና ስም ቤተ ክህነት ውስጥ ተቀባይነትን ያገኙ

> ጽሑፎች ናቸው። በቅርብ ጊዜ የገድሎችን አጻያፊና ሴጣናዊ መልእክቶች ያጋለጠ መጽሐፍ በምድራችን ታትሟል። ፀሐፈው በዚያ ሞለማ ውስጥ ለዘመናት የተሰቃዩ ዛሬ ግን ወንጌል ነጻ ያወጣቸው ሰው ናቸው።
> *[ዘኢትዮጵያ ጋዜጣ መስከረም1997 ገጽ 5]*

መምህር ጌታቸው በጨለማ ውስጥ የነበሩ ሲሉዎት እንዴት ተሰማዎት? ከዚህ የበለጠ ስድብ፣ ከዚህ የበለጠ እርግማንስ ምን አለ? በምድር ላይ ሃይማኖትን ከመለወጥ የበለጠስ ምን ውርደት አለ? ያውም እንደርስዎ ያለ ነገሮችን በጥልቅ የሚያውቅ ምሁር ስለ ገድላትና ድርሳናት ለምን እንደተጻፉ የሚያውቅና የሚረዳ አደናጋሪ ምሁር እንዴት አድርገው ነገሮችን አጣመው ስለ ተቀጠሩበትና ስለ ተገዙበት ሰይጣናዊ ድርጅትን ለማገልገል ሲሉ ብቻ በዚህ ዕድሜዎ ያውም በእግዚአብሔር ላይ ውሸት ሲናገሩ ሥጋዎስ ተገዛ እንበል ነፍስዎ እንዴት ተቀበለችው? የሚገርምዎት ነገር ቢኖር በጻፉት የሐሰት ድርሰት ውስጥ ቅድስት ድንግል ማርያምን፣ ሰማዕታትን፣ ጻድቃንንና መላእክትን እንደዚያ አድርገው ሲያዋርዱ የእግዚአብሔርን መንግሥት እየናዱ የሠይጣንን ቤተ መንግሥት እየገነቡ መሆንዎ አይታይዎትምን?

እንድ ታላቅ ተአምር በመጽሐፍዎ ውስጥ አስፍረዋል። እርስዎ አላወቁትም አላስተዋሉትም ይሆናል። የጻፉትን ሐተታ ሁሉ ምንነት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው። ግሩም ድንቅ ነው። እሱም ታላቅ ምሥጢርና ተአምር ነው። ተአምር የሆነውም ከዚያ ላይ ነው። ምን ብለው እንደ ጻፉ ልንገርዎት። በደንብ ያስተውሉ አንባቢዎችም ተገንዘቡልኝ። ስምዎን ነጠላ አባት የሌለው አድርገው ሲያቀርቡ የክርስትና ስምዎን ግን ወስመ ጥምቀቱ ገብረ ኢየሱስ ሲሉ አሠፈሩ። እኒህ ጌታቸው የተባሉ ጴንጤ ገብረ ኢየሱስ ሲሆኑ ቀርቶ መምሰል እንኳን አይችሉም። ገብረ ዲያብሎስ፣ ገብረ ሰይጣን ናቸው ብዬ አቅዋም ወስጄ ከጻፍኩ በኋላ እርስዎ ራስዎ፣ በገዛ ብዕርዎ ያዋረዱትና ዝቅ ዝቅ ያደረጉት መልአክ ፊትዎን ጠፍቶ፣ አፍዎን ከፍቶ፣ ዕጅዎን ዘርግቶ፣ እንዲህ ሲል አጻፍዎት። <u>ገብረ ኢየሱስ ማለት ገብረ ዲያብሎስ</u> ማለት ነው። [ገድል ወይስ ገደል ገጽ 105] አዩት ይህን ተአምር? ከዚህ ወዲያ ለሚያደርጉት ወንጀልና ለተዘፈቁበት ኃጢዓት ከዚህ የበለጠ ምን ማስረጃ ይገኛል?

ከእንግዲህ ወዲያ በአባትዎ ስም ለመጥራት ራስዎ የመሰከሩበት ስም ሰጥተውናልና በእሱ እንጠራዎታለን። እሱም ገብረ ዲያብሎስ እያልን ነው። አንባቢዎች ሆይ! የአኒህን ሰው ዲያብሎሳዊ

ጽሑፍ ያነበባችሁና የሰማችሁ ሁሉ ተጠንቀቁ። ፀሓፊው በራሳቸው መጽሐፍ የክርስትና ስማቸውን ሲተረጉሙ ገብረ ዲያብሎስ ነው ያሉት። ሁልጊዜም እንደምናውቀው ከዲያብሎስ ምን እውነት ተነግሮ ያውቃል? ስለዚህ እኔህ «ገድል ወይስ ገደል» ብለው የጻፉት የዲያብሎስ አሽከር በሙሉ ውሸትና ሐሰት ነው። ለዚሁም ያዋረዷቸው ቅድስት ድንግል ማርያም፥ ቅዱሳን መላእክት ጻድቃንና ሰማዕታት፥ በገሀድ በራሳቸው የፅጅ ጽሑፍና ቃል አጋለጧቸው። አንባቢዎች ሆይ! እባካችሁ በሃይማኖት ዓይን ተመልከቱት። ይህ ራሱ በክፍተኛ ደረጃ የሚታይ ተአምር ነው። እኔ ስሜ ገብረ ዲያብሎስ ነው ከማለት ወዲያ ምን ይምጣ? ይህ ቃል ብቻ ማንነታቸውን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። ሆን ብለው እንደማይሉ ደግሞ እወቁ። ታምሩ ከዚህ ላይ ነው። ለኔ ከንዴትና ከኃዘን አባባሉ አጽናንቶኛል። በራሱ አገልጋዮች ላይ፥ በቅድስት እናቱ ላይ፥ የቀረበው የውርደት ቃል ከማን እንደሆነ ከዚያው ከዲያብሎስ አሽከር መሆኑ ሲነገር፥ ምንኛ እፁብ ድንቅ ተአምር ነው? እግዚአብሔር የተመሠገነ ነው። ሃሌ ሉያ ከዚህ ላይ ነው።

እንኳን የመምህር ጌታቸውን ማንነት በራሳቸው ብዕር አስመስክረልን። ታዲያ ፓስተሩ ይህን ጉድ አላነበቡ ይሆን? ወይንስ ቢያነቡትስ ማን ሆኑና ነው። «በጨለማው ውስጥ የኖሩ አሁን ግን የወንጌል ብርሃን ነግ ያወጣቸው» ሲሉ የመሠከሩላቸው ፀሓፊ ገብረ ዲያብሎስ መሆናቸውን ራሳቸው በማያውቁትና ባልተረዱት መንገድ ኢየሱስ አናገራቸው። በእርሱ ስም ሲቀልዱ ያውም ለኢትዮጵያውያን በግልጽ አናገረልና! ያ ሁሉ ስድብ ከገብረ ዲያብሎስ መሆኑን ወዲያውኑ ጽፈው ሳይዘልቁ አናገራቸው። መጽሐፉን ያነበባችሁ ሁሉ ይህን የእግዚአብሔር ተአምር አብራችሁ ተመልከቱት በጣም የሚያስደንቅ ተአምር ነውና ነው።

ምነው በእግዚአብሔር ስም እንኳን ባትዋሹ? የጠቀሷቸው ማስረጃዎች ደግሞ ዚቅ፥ ገድል ናቸው። እነሱኮ ራሳቸውን የቻሉ ምክንያቶች አሏቸው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ራሳቸውን ስለለቱና ስእሳት አሳልፈው የሠጡትን የኢየሱስ አገልጋዮችንና ጀግኖችን ማሞካሸቷ ነውሩ ከምኑ ላይ ነው? በሰም ተለብደው እንደ ችቦ በእሳት እየነደዱ የአሕዛብ ራት መብያና መፈንጠሪያ የሆኑትን ክርስቲያኖች መዘከር ጉዳቱ ከምኑ ላይ ነው? እንደ ማስረጃ ከጠቀሱት ዚቅ የተጻፈው ለመግሳና ለአድናቆት እንጂ የዕምነት ማስረጃ ተብሎ እይደለም። እርስዎ የቆሙላቸው ፕሮቴስታንታዊ ድርጅቶች ከካቶሊኩ የነበራቸውን ተውፊት የትም በትነውት ባዶ ዕጃቸውን መሆናቸውና ያለ ማስረጃ መቅረታቸው

ሲያናድዳቸው የቁጣ ማብረጃና የአፍ መክፈቻ ያጣ ወራው መሆኑን ይረዱት።

ግዕዝ ስሚጠቅስ ሰው፥ ቅኔ ስሚያውቅ ካህን፥ የዜቁ መጽሐፍ፥ የስንክሳሩ ታሪክና አርኬ ሁሉ ስለ ሰማዕታትና ስለ ጻድቃን ተጋድሎ ውድስና የተደረሰ እንጂ ሌላ ያለመሆኑን እያወቁ በመጽሐፍዎ ሰው ሲያሳስቱበት አቀረቡት። ምን ያህል ጥላቻ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ቢያድርብዎት ነው? ጠለቅ ብለው ንገሮችን የሚከዘቡ ቢሆኑ ናሮ ብዙ ባዩና በተመለከቱ በነበር። ነገር ግን ለስድብና ለዘለፋ ብሎም ለማሳሳት የቀረቡ ሰው ስመሆንዎ ራሱ አደጻፍዎት በሚገባ ያስረዳል።

አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ያህል ኢትዮጵያዊ ዳድቅ አባት በርስዎ ዓይነት ተቃዋሚ ሰው ሲነቀፉ አይቻልም። ገዳሙን ለማጠናከር፥ ገዳማውያኑን ለማበረታታት፥ የተሠጠውን ምክር እንደ እምነት ቃል ወስደው ለስድብዎ ማቀናበሪያ ማድረግዎት እጅግ ያሳዝናል። ምንም በጉዳዩ የሌሉበትና ቢያውቁም ለማሳሳት የተጠበቡ መሆንዎን ብቻ ነው በግልጽ የሚያስረዳው። እንዲያው ለመሆኑ በዚያ ገዳም ስንት አባቶች ተምረውና ሠልጥነው እንደ ወጡበት ያውቃሉን? የኛ አባቶች ጥበብና ማስተዋል የተመሉ በመሆናቸው ገዳማቸውን ለማስተዳደር ሲሉ ብዙ ጥበብ የተመላበትን ዘዴ በምክር መልክ አቅርበዋል። ያልተረዱትና ያልገባዎት እርስዎ ራስዎት ብቻ ነዎት እንዳንል እንደሚያውቁ ይታያል ግን እውነቱን ለማጣመም ሆን ተብሎ የተመለመሉ የዲያብሎስ አገልጋይ ስለሆኑ እንጂ ነው።

መምህር ጌታቸው ወስመ ጥምቀቱ ገብረ ዲያብሎስ ይሆን ማደናገሪያዎን እኛ በሚገባ አውቀንብዎታል። ለማያውቅዎት ለሠይጣናቱ፥ ለእጋንንቱ ይታጠኑ። ደግሞኮ የሚገርመው የናንተው አርቶዶክሳዊው ውስጠ አዋቂ ተብለው እንደ እሥረጂ ተሠይመው መቅረብዎ ነው። ይች ይችማ ኮስማና ምክንያት ናት። ይሁዳ ላይ ታይታስች ታውቃስች። መምህሩን አሳልፎ እንዲሠጣቸው የተቀበለው የሠላሳ ብር ንክኪ ነው። ዛሬስ የዚያች ብር ዘር ከናንተ የምሥጢር ጓዳ ወይንም የአራማ ቤት ወይንም ቤተ ርዴ [ባንክ] የለችም? ዛሬማ ክንዱ ፈርጥሞ፥ በዲሞክራሲ መጎናጸፊያ ተሸፍኖ፥ በኢየሱሴ ስም ተሞናመሩ፥ «ገድል ወይስ ገደልን» የሥራ ዕቅድ አስጠንታ ዛሬም የኢትዮጵያን ማንነት አሳልፋ ለማሰጠት ብሯ ሕያው ናት። በዚህ አንከዳዳም። ሥራዋን እየሠራች ነው። ነገር ግን ግንዛቤ እንዲደረግበት የምንፈልገው «ግበ ክረዩ ወይወድቁ ውስቴቱ» ማስት

በቆፈሩት ጉድጓድ መልሶ መግባቱ አይረሳ። እንዲያው መምህር ጌታቸው በገንዘብ ማንነትዎን ራስዎን ብቻ ቢሆን ሥራ አጥተው መጠጊያ ጠፍቶብቸው እንል ነበር። ነገር ግን አገርዎን ታሪክዎን እምነትዎን ባሕልዎን እንዲያው ሁለምተናዎን እንዴት ነገ ለምትጠፋ ሕይዎትዎ እንዲህ አድርገው ይለውጣሉ? ጤዛ ልሰው ድንጋይ ተንተርሰው ያቆዩንን ቤቷ እምነት ቤተ ክርስቲያን በጥቂት ላንቲሞች ይሸጣሉን? አሁንኑ ይፀፀቱና ይመለሱ። የጻፉትን መልሰው ያንብቡት። ንስሐም ይግቡበት። ሥራዎን እግዚአብሔር አልወደደልዎትም። በራስዎ ብዕር «ገብረ ዲያብሎስ» ብሎ ከማጻፍ ወዲያ ሌላ ተአምር የለም።

ከዚህ ላይ ሊወሳ የሚገባው ኃሳብ ቢኖር ከመምህር ጌታቸው በፊት ግርማ ዘውዴ የተሠኙ ኸው «ኢትዮጲስ» በተሠኘው መጽሐፋቸው መምህር ጌታቸው ወይንም ገብረ ዲያብሎስ ጎልጉለው የዘሩትን በጽሑፋቸው ስለ ጻድቃን፡ ስለ ሰማዕታትና ስለ መላእክት ጎጃጂፈውታል። እንደዚሁም ስለ ድርሳናትና ስለ ጸሎት መጻሕፍትም የሐሰት ምሥክርነታቸውን አቅርበዋል። የቤተ ክርስቲያኗን ሕልውናና ታሪክ ለማጉደፍና የተሳሳተ መረጃ ለመሥጠት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ለዚህም እንደ ታላቅ ማስረጃ የሚጠቀሰው ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደ ገባ የሚመሠክረውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ አንዴት አድርገው እንዳንኳሰሱት ከራሳቸው መጽሐፍ እንደሚከተለው እጠቅሳለሁ። የጽሑፋቸው ንውሥ ርዕስ «ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ምድር የገባው መቼ ነው?» ይላል።

«በመጽሐፍ ቅዱስ ኢትዮጵያ የሚል ስም ከዓርባ ጊዜ በላይ ተጠቅሶ እንደሚገኝ ከዚህ በፊት ተገልጸአል። ይህም በብዛት የሚገኘው በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ነው። በአዲስ ኪዳንም በሐዋርያት ሥራ 8:26-39 ባለው ክፍል እንደምንመለከተው ሐዋርያው ፊልጶስ ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያደርሰው ምድረ በዳ እንዲሄድ የእግዚአብሔር መልአክ ገለጸለት። በዚሁ መሠረት የኢትዮጵያ ንግሥት የነበረችው የንግሥተ ሕንደኬ ጃንደረባ የሆነ ኢትዮጵያዊ በመንገድ ላይ ተገናኘው። ጃንደረባው ከኢትዮጵያ ወደ ኢየሩሳሌም ሊሰግድ ሄዶ ሲመለስ በመንገድ ላይ የኢሳይያስን ትንቢት ያነብ ነበር።

ክፍሉ በኢሳይያስ ምዕ. 53 የሚገኝ ሲሆን የተነገረውም ስለ ጌታ መድኃኒታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ጃንደረባው ያነበው የነበረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል «እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፡

የበግ ጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም እንደሚል እንዲሁ አፉን አልከፈተም። በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ ሕይወቱ ከምድር ተወግዳለችና ትውልዱንስ ማን ይናገራል?» የሚል ነበር። ፊልጶስንም የእግዚአብሔር መልአክ ወደ ጃንደረባው ሠረገላ ቀርበ እንዲያነጋግረው አዘዘው። እርሱም ሮጠ ጃንደረባው ሲያነብ ሰማና በእውኑ የምታነበውን ታስተውላለህን? አለው። እርሱም የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል? አለው። ፊልጶስም ከእርሱ ጋር በሠረገላው ላይ ወጥቶ እንዲያስረዳው ጠየቀው። ፊልጶስም ነቢዩ ስለማን እንደተናገረ በማብራራት ከዚህ መጽሐፍ ጀምሮ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ለበከለት። በመንገድም ሲሄዱ ወደ ውሀ ደረሱ። ጃንደረባውም «እነሆ በውሃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድን ነው?» አለው። ፊልጶስም በፍፁም ልብህ ብታምን ተፈቅዶአል አለው። መልሶም ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እምናለሁ አለ። ሠረገላው ይቆም ዘንድ አዘዘ። ፊልጶስና ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ወደ ውሃ ወረዱ አጠመቀውም። ከውሃውም ከወጡ በኋላ የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ከጋዛ ወደ አዛጦን ነጠቀው። ጃንደረባውም ደስ ብሎት መንገዱን ሄደ፤ ይላል እንጂ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ቤተ ክርስቲያን መመሥረቱ ወይም የክርስትና ሃይማኖት ትምህርት እንዲሠጥ ማድረግ አለማድረጉ አልተጠቀሰም።»

[ኢትዮጲስ 1988 ገጽ 23-24]

ይህን ንባብ እንዳለ የወሰድሁት ግርማ ዘውዴ እንዴት አድርገው ታሪኩን ወደ ሐሰት እንደለወጡት ለማሳየት ነው። ሐሰቱም ጃንደረባው በመጠመቁ ደስ ብሎት ሄደ ብሎ መጽሐፍ ቅዱሱ የመሠከረለትን ሰው ኢትዮጵያ ገብቶ ግን ቤተ ክርስቲያን መሥራቱን አይተርክም ሲሉ ክርስትና በዚህ ጻድቅ ሰው አማካይነት ኢትዮጵያ አልገባም ብለው ካዱት። መጽሐፍ ቅዱሱ የሚገባውን ድርሻ ታምራዊ ሥራ መሆኑን በሚገባ አሥፍሮታል። እንደገና ኢትዮጵያ ውስጥ መጥቶ ይህ ታላቅ ሰው ኢትዮጵያዊ ክርስትናን አስፋፋ አላለፋፋም የሚለውን ታሪክ ተከታትሎ መጻፍ ነበረበትን? ከዚያ በኋላ የተሠረውንማ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ረሐፊዎች ሥራ ነው እነሱም አሳምረው መስክረዋል። የቤተ ክርስቲያን ታሪክ አባት አውሳብዮስ እንዲህ ሲል መስክሮለታል። ብፁዕ ጻድቅ የራሱ ሕዝብ ሐዋርያ የሆነ ሲል አሞካሽቶት እናገኘዋለን። ይህን ክፍል ነው ያልተገነዘቡት ማለት እንኳን ይከብዳል። ነገር ግን አጣመው ለመጻፍ የተነሡ በመሆንዎ የማይባለውን አሉ። ትክክለኛውን ግን ጎሊናዎ ያውቀዋል። የተቀጠሩበትን የድርጅት ሥራ አሳምር ሲሉ ከእግዚአብሔርም ከራስዎ ከአገርዎ ታሪክና እውነታም ጋር ተጣሉ።

ይህ እጅግ በጣም ያሳዝናል። እጅግም ያሰቅቃል። እናንተን የመሰሉ ምሁራን እንዲህ ለደረቅ ዳቦ ታሪካችሁንና ማንነታችሁን በጠራራ ፀሐይ ስትሸጡ መታየቱ እጅግ ያጸይፋል ያሳዝናል ያስቆረጣል።

ከዚህ ላይ ለግርማ ዘውዴ የማቀርበው ጥያቄ የእግዚአብሔር መልአክ ፊልጶስና ኢትዮጵያዊው የፊፀሙት ታላቅ ተአምር እንዲህ በገሀድ እየተነበበ ነገር ግን ጃንደረባው ኢትዮጵያ ገብቶ ማስተማሩ አይታወቅም ሲሉ ከርስትና ወደ ኢትዮጵያ የመጣበትን ታላቅ ምሥጢር ካዱት። ለመሆኑ ግርማ ዘውዴ ኢየሱስ ከአሥራ ሁለት ዓመቱ በኋላ የት ነበር? ወደ ሰማይ ሄዶ ነበር? ወይንስ የት ቆየ? እነ ማቴዎስ የተውልድ ኃረጉን ሲጽፉ ምነው ከአሥራ ሁለት ዓመቱ በኋላ ስላለው ሥራው አልገለጹትም? ይህ ማለት በእርስዎ ዘንድ ኢየሱስ በዓለም ላይ አልነበረም ማለት ነውን? ይህን ጥያቄ ያቀረብሁት ሁሉም ነገር በዝርዝር ያልተጻፈ መሆኑን ለማጠየቅ ነው። ነገሩ ጠፍትዎት ሳይሆን ለማሳሳትና ለማጥላላት የቆሙ በመሆንዎ የማይመስል ነገር አስገብተው ጻፉ።

በእውኑ ዝርዝሩን ለማወቅ ቢፈልጉ ኖሮ የእነ አውሳብዮስን መጽሐፍ ባነበቡ በነበር። አንበውታል ያውቁታል ነገር ግን ለመጥቀስ አልፈለጉም። አውሳብዮስ ስለ ኢትዮጵያዊው ባኮስ ወይንም በቅጽል ስሙ ጃንደረባ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊው ሐዋርያ የራሱን ሕዝብ ያስተማረ የሃይማኖት ፍሬ ብሎ ያሞካሸውን እንደማይታወቅ አድርገው አልክስክሰው አለፉት። በእውነቱ የራሱ ሕዝብ ሐዋርያ የሚለውን የሥራ ስም ባያስተምር ኖሮ እንዴት ያገኘውና ይባልበት ይጠራበትስ ነበር? ሌሎቹ ሲመሠክሩለት ራስዎ በወገንዎት ላይ በሐሰት መሠከሩበት። በራሱ ላይ የጋዛ ውሀ ፈስሰበት እንጂ ምን ሠራ ነውኮ ያሉት። ለመሥራቱም ይኸው መሠከሩለት። ስለርስዎ ግን አወቅን ተረዳን ተገነዘብን። ከዚህ ወዲያ ትዝብት ከዚህ ወዲያ መካድ ከየት ይምጣ? መቼም ተከናንበው ቢተኙ ገልጦ የሚያይ አምላክ አለና በሠፈሩት ቁና ይሠፈርብዎታል አይቀርም። ይህ አባባልዎት በእግዚአብሔርና በታሪክዎ ሐሰት ተናግረዋልና የሐናንያና የሰጲራን ታሪክ እየደገሙት ነው። ታሪኩም በርስዎ ላይ ይደርሳል። ይህ የማይቀር መለኮታዊ ምሥጢር ነው። [የሐ ሥራ. 5:1-11]

እንዲሁም በተጨማሪ ለማብራራት ያህል እንደርስዎ አመለካከትና ግንዛቤ ከርስትና በዚህ ሁኔታ ገባ ካለ ስለ መስፋፋቱ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ፀሐፊዎች ያሠፈሩትን ማንበብ እንጂ ምንም ያደረገው ነገር የለም ይላሉን? ነገር ግን ከዚህ ላይ

እንድናየው የፈለግሁት የመጽሐፍ ቅዱሱን ማስረጃ እንኳን ኢትዮጵያ ላይ ሲደርስ እንዴት እንደምታጣምሙት ለመግለጽ ነው። በእውኑ ከእናንተ ምን ይጠበቃል? እንደ እናንተ አለቆች አባባል ጃንደረባውም ሆነ ንግሥቲቷ ኢትዮጵያውያን አይደሉም ያለማለትዎም ጨርሰው ያልካዱ ያሰኝዎት ይሆን? ከዚህ አቅም እንኳን እንዴት እውነት እንደምትክዱ ታላቅ ማስረጃ ነው። ለመሆኑ የቱ መልአክ ነው የፕሮቴስታንት ሃይማኖት ትክክለኛ ነው ያላችሁ? አዩት ኢትዮጵያውያን ኦርቶዶክሳውያን ተዋሕዶ የሆን ሁሉ መላእክትን ለምን እንደምናከብር? የአገልግሎታቸው ተጠቃሚዎች ነንና ነው። ኢትዮጵያንና ሃይማኖትን በሚመለከት ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ምንም ነገር የተሠራ ያለመኖሩን በሚገባ ይረዱት ይወቁት ይገንዘቡት። እንደርስዎ ዓይነት እንዲሁ በተቀዋሚነት የተመሠረተ በሃይማኖት ስም የፖለቲካ የንግድ የዲፕሎማሲ ሁለ-ገብ ድርጅት አይደለም። ታዲያ ርስዎም ከሳሽና ወቃሽ የለብኝም ብለው እንደ ሌባው አባባል «ባያዩኝ አሰርቅ፥ ቢአዩኝ እስቅ» አያድርጉት። እርስዎ በጽሑፍ ወንድምዎ ባልንጀራዎ ፓስተር ላይ ያሉትን ላስነብብዎት ያዳምጡት።

የፕሮቴስታንቱ ሹም ስማቸውን አልጠራም በሥራቸው ያውቋቸዋል። እሳቸው ደግሞ በቃል በንግግር ከሰጡትና ካስተማሩት ቃለ ወንጌል የሚጠቀሰው እንዲህ ያሉት ነው። ከየትኛው ወንጌል ወይንም መልእክት እንዳገኙት ባይናገሩም ቅሉ ከመጽሐፈ ጽርፈት ወዘለፋ ሳይሆን አይቀርም ብለን እንውሰድላቸው። «አሮሞዎች ዛፉን ቅቤ ይቀባሉ። አማራና ትግሬ ግን ቆርጠውና ጠርበው በልብስ ጠቅልለው ጃንጥላ ይዘው ዕልል ይላሉ» ሲሉ ጽላቱ ስመ እግዚአብሔር እንደተጻፈበት ሳያውቁ ቀርተው አይደለም። ነገር ግን አውቆ የተደበቀን ቢጠሩት አቤት አይልም ነውና! ራሳቸው በጎናቸው አንግበው የያዙት የመጽሐፍ ቅዱስ ጠብመንጃ ከእንጨት ፍቅፋቂ ዱቄት ከተሠራ ወረቀት ላይ የተጻፈ አይደለምን? ታዲያ በራሳቸው አነጋገር በራሳቸው ላይ አልፈረዱምን? ከዚህ ላይ ነው «አንተሥ ፈታሕከ በርእስከ» ንጉሥ ሆይ! በራስህ ፈረድህ የሚያሰኘው። አነጋገር የተፈፀመው። ታዲያ ራሳቸውስ መቼ ከዕንጨቱ ወጡና! ያላገናዘበ የችኮላ የተንኮል አነጋገር ሁልጊዜ አዘቅት ላይ ይጥላል። ለዚህም ነው አበው በምሳሌያቸው «የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሰ» ያሉት። ታዲያ ይህ ሁኔታ በሳቸውስ ላይ አልደረሰምን? እስከዚህ ድረስ እንኳን ቢያንስ ቢያንስ ረጋ ቢሉ አይሳሳቱ ይሆን? ምናልባት እንዳያስቡ ያደረጋቸው የአለቆቻቸው ትዕዛዝ ፋታ ነስቷቸው ካልሆነ በስተቀር ኢትዮጵያዊው ባሕሪያቸው እንዳልሆነ እንገምታለን።

ሰፓስተሩ ተናጋሪ ጥቂት የምለው ታቦት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሃይማኖቱ መገልገያ ብቻ ሳይሆን የማንነቱና የባሕሉ መግለጫም ነው። እንደ ዋና ማስረጃ የሚሆነን የጥምቀት በዓል ነው። በጥምቀት በዓል ምን እንደሚደረግ ለርስዎ ምኑ ይነገራል? የኢየሱስን ባሕረ ዮርዳኖስ መጠመቅን መሠረት ያደረገ በዓል ነው። የሚዘመረውም «ሐረ ኢየሱስ ኀበ ዮሐንስ ተጠምቀ በዮርዳኖስ።» ማለት ኢየሱስ ወደ ዮሐንስ ሄደ በዮርዳኖስም ተጠመቀ ነው። ከዚያ ባሻገር ግን በዓሉ የኦርቶዶክሶች ብቻ ሳይሆን የመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መሆኑን የምንረዳው አባባሉኳን «የጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይቁረጥ ይበጣጠስ» ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ በየዓመቱ ካንድ ላይ ተሰብስቦ ደስታውን የሚገልጽበት ቀኑ ይኸው የጥምቀት በዓል ነው። ይህ እንኳን አያስደንቅዎትምን? ይህን የመሰለ ትውፊት ይች ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ይዛና ጠብቃ መኖሯ?

በድጋሚ ለማጠናከር የዚህ በዓል ተካፋይ ደግሞ ኦርቶዶክሱ ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሁሉ እንጂ! ይህም ማለት በአንድነት ክርስቲያኑም እስላሙም ነው። እንግዲህ ያስቡበት የርስዎ ጦር ወደ ማን እንደሚወረወር፥ ከማን ላይ እንዲያርፍ እንደተፈለገ፥ መልሱ በመላ ኢትዮጵያውያን ላይ ነው። ስለዚህምኮ ነው አበው ሲናገሩ «እፍንጣ ሲመታ ዓይን ያለቅሳል» የሚሉት። እንግዲህ አይርሱ። የርስዎ ዋና ተልዕኮና ሹመት ይችን ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ስማውደም ነው። የሁሉንም ዓይን ማስለቀሱን ግን አይርሱት።

አንድ ነገር ከዚህ ላይ አይርሱ። ከእግዚአብሔር የሆነን እናጠፋለን ማለት ለመጥፋት ነው። ለርስዎም ከፊተኛዋ የኋለኛዋ እንዳትብስብዎት ያስቡበት። አሁን ግን የሚታየው ያ በሩቁ ከባሕር ማዶ ይታይ የነበረው ታቦት ከምዕራባውያን መሀል ከተሞች መጥቶ በዋና ዋና መንገዶች ላይ ተከብሮ በሆታና በዕልልታ ይጓዝበት ጀመር። ይህን እንኳን ሲመለከቱት ምን ይሰማዎታል? ምንስ ይመስልዎታል? የእግዚአብሔር ፈቃድና ተአምር አይደሰምን? እንግዲህ ለእናንተ ተስማሚ የሚሆነው የአበው አባባል «የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል» ነው።

ክቡራን ኢትዮጵያን የፕሮቴስታንት ፓስተሮች ታቦት ላይ ያረፉትን ዓይኖቻችሁን ለተንኮል የሚያውጠነጥነውን አእምሯችሁን ለአንድ አፍታ ያህል ብድግ አድርጉትና እስቲ ሌላ ሌላ ጉዳዩድ ነገር ላሳያችሁ። ይህን ጉዳይ በሚገባ በማስተዋል እንድትመለከቱት ከአደራ ጋር ልጋብዛችሁ። ልብ በሉና ተመልከቱት።

አንደኛ የልደትን በዓል ለማክበር በፕሮቴስታንቱ ዓለም ስንት ዛፍ ይወድማል? ዛፉን በተሰያዩ የመብራት ጌጦች ለማስዋብ ስንት ገንዘብ ይፈሳል? ይህን ኢክርስቲያናዊ አሠራር ተቃውማችሁታል? ከኛ ቤት ብትመጣ መኖሪያ ክፍላችንን አጣቦት ጉድ ታይ ነበር እንደምትሉኝ አልጠራጠርም። ነገሩ እውነት ያለ ነውና! ታዲያ ከሌላው ዓይን ላይ ያለውን ጉድፍ ከማውጣትህ በፊት በራስህ ዓይን ላይ ያለውን ምሰሶ አስቀድመህ አውጣ። [ማቴ. 7:2-3] ታዲያ ይህ ሰናንተ ምኑ ይነግሯል?

ሁለተኛ፡ ዛሬ በየጊዜው በፕሮቴስታንቱ ቤተ ክርስቲያን እየታተመ የሚታደለው መጽሐፍ ቅዱስ የኢትዮጵያን ስም በመሠረዝና በመደለዝ አንድ ጊዜ ኩሽ፥ ሌላ ጊዜ አቢሲኒያ፥ እንዲሁም ደቡብ ግብፅና ሱዳን እያለ እያተመ የሚበትነውን ወንጀል ተቃውማችሁታል ወይ? ኢትዮጵያን ለማጥፋት ከሚያድሙት ቡድኖች ጋር ባትሆኑ ኖሮ ይህን ተመልክታችሁ ዝም አትሉም ነበር። ነገር ግን የእነዚህ ቡድኖች ጦር ሠራዊት አዛዦች [ከማንደርስ ኢንችፍ] ስለሆናቸሁ እሱማ መደበኛ የፓስተርነቱ ሠይፍ ነው ትሉ ይሆናል።

ሦስተኛ፡ የሳቲን ፊደል ከግዕዝ መቀዳቱን እያወቃችሁ፥ የግዕዝን ፊደል በላቲን ተክተው የሚወላከፉትን ወገኖቻችንን ገሥፃችኋቸዋልን? አያችሁት ዕንቁላሉ ሲሰበር ምን እንደወጣ? እባብ የሠይጣን ማደሪያ የኃጢዓት አባት፥ ተግባሩ ማሳሳት ሆነና አረፈው። እንግዲህ ይህን ሁሉ ጉዳጉድ ከጸሎት ቤታችሁ አስቀምጣችሁ ነው የኢትዮጵያን መግለጫና መታወቂያ ለማጥፋት ጎው የምትሮሯጡት። እናንተ አዲሶቹ ክርስቲያኖች የቀድሞዎቹ አሕዛብ ለምን ቤተ መቅደሳችንን ታረክሳላችሁ?

ክቡራን ፓስተሮች ሆይ! የተለመጣችሁ ኢትዮጵያዊያን ባትሆኑ ኖሮ ጠይምነታችሁን ባልተዋችሁ በነበር። እናንተ በጦር መሪነት በማን አለብኝነት ተናገሩ እንጂ የናንተ የሥራ ባልደረቦቻችሁም በሙሉ የሚሮሁት የእናንተን መመሪያ ተከትሰው ነው። ይህ ዘመቻ በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነትም ላይ ዕምቢልታው ይነፋል። እርጋኑ ይመታል። የድምፅ ማጉያው ያናፋል። ራዲዮኑና ቴሌቭዥኑም ያስካካል። የጥሩቱ ውጤት ተሞክሮ የታየው «ያገሩን ሠርዶ ባገሩ በሬ» ማስነቀሉ ነው። ዛሬኮ ያካባቢያችን የኢትዮጵያ አካል የነበሩት አገሮች ብተናና ክፍፍል ከተረጋገጠ በኋላ የወል ስም

ወጥቶላቸው የአፍሪቃ ቀንድ ተብለዋል። ኢትዮጵያ የሚለው ስም ለጠይሙ ዓለም ሕዝብ የመመኪያና የመታወቂያ ስም ሆነና አልተወደደም። እናንተን ምን እንደዋጣችሁ ባላውቅም ቅሉ! ስለዚህም እንዱ የናንተ የሥራ ዘርፍ ሆኖ የተሠጣችሁ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ የምታካሂዱት ዘመቻ አካልና ዘርፍ ነው።

ና

አንድ በመጨረሻ ላይ ላወሳው የምሻው ነገር ቢኖር የዋነውን የበላይ አዛዡን የፓስተሩን ጋሻ አንግበው፥ ጦር ነቅንቀው የሚዋጉት መጸብሃን ሊጠራሩ እረኛ ዕገሌ እየተባባሉ ነው። የቅጽሉን ቃል ስሰማው «ስምን መልአክ ያወጣዋል» አልሁ። እውነትም እረኛ! ከእረኞች የቃላት ውርወራና ዘለፋ ቀርቶ ኢትዮጵያ ከጠላት አንድ ዕጅ ከተረጨው ከመርዙ ጢስ ብተና፥ ከአውሮፕላኑና ከታንኩ ወረራ ሁሉ ድናለች። ዓፄ ምኒልክ በዚያ የአፍሪቃ ቅርጫ በሚካሄድበት ዘመን ለአውሮጳውያን እንዳሉት ኢትዮጵያ ከእግዚአብሔር በቀር ማንም የላትም። ዕጆቿንም ወደሱ ብቻ ትዘረጋለች። አሁንም ነው። ቃሉም ጽድቅ ነው።

ኢትዮጵያዊቷ የሁላችንም እንዲቷ ሕያዊቷና ዘለዓለማዊቷ ኦርቶዶክሳዊቷ ተዋሕዶዋ ቤተ ክርስቲያን ለዘለዓለም ትኖራለች። «አግርር ፀራ ወዕቀብ ሃይማኖታ» [ጠላቶቿን በትን ሃይማኖቷን ጠብቅ] ብላ ትጸልያለችና ነው። ሌሎቹ ተቃዋሚዎቿ የባዕዳን ሃይማኖት ተሸካሚዎች ግን እንደ አባቶቻቸው ፈሪሳውያን፥ ሰዱቃውያን አነሣሣቸውና አበቃቀላቸው ለጥፋት ያው «ስቅሎ! ስቅሎ» ባዮች ናቸውና ትናንት መጥተው፥ ዛሬን ብቻ ታይተው፥ በነጋታው እንደ ጤዛ ይረግፋሉ፥ እንደ ቅንቅን ይበናሉ። አፈጣጠራቸውም ለጊዚያዊ ፍሬቢስ ተግባርና ጉዳይ እንጂ! ዘለዓለማዊነት የለውምና ነው። ስለዚህም «አጽራረ ማርያምን ዓውዱ እንደ ተደፋ ይድፋቸው። መብራቱ እንደ ጠፋ ያጥፋቸው።» የመጨረሻው ምክር፥ በኢትዮጵያ ላይ የምታሰሙት ማንጎራጎር ፍፃሜው ሞት ከዚያም መቃብር ነው።

፪ . አጽምኡ ሕዝብየ [ወገኖቼ አድምጡ]

ኢትዮጵያውያን ኦርቶዶክሳውያን የተዋሕዶዋ ቤተ ክርስቲያን ልጆች በሙሉ ይችን ምክር ስሙኝ። ይችን የኢትዮጵያ

ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛዋንና በአጠራርም ቀጥተኛዋን ርትዕት ወይንም ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ለመጠበቅ ኢትዮጵያዊ ስሆነ ሁሉ የአደራ ቃል ኪዳን አለበት። ስትመሠረትም በልዩ ምሥጢርና ታምር ነው። የእግዚአብሔር መልአክ ለፊልጶስ ሂድና ኢትዮጵያዊውን ባኮስን አነጋግረው የሚያነበውን ተርጉምለትና አጥምቀው ተብሎ ተልኮ አጥምቆት ባኮስም በእግዚአብሔር ፈቃድ የተቀበለውን ክርስትናን ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ በሰበከባት አገር የአውሮፕላን ቲኬት ተቆርጦ ተመጥቶ ክርስትና ላይ ሌላ ክርስትና ሳይሆን እንክርዳድ ለመዝራት የመጡ ናቸው። በምንም መልኩ የእነሱ ክርስትና ለኢትዮጵያውያን ክርስትና ሊሆን አይችልም። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከእግር ጥፍሯ፥ እስከ ራስ ፀጉሯ፥ ድረስ ቀዳማዊት ብሔራዊት፥ ኢትዮጵያዊት ናት። ቤተክርስቲያኗን መቃወም ማለት በማንነቷ ላይ ጦርነት ማወጅ ነው። የተያዘውና የሚደረገውም ይኸው ነው። በመዋዕለ ሕይወት፥ ባለንበት ዘመን፥ ካህናት፥ ምዕመናንና ወጣቶች ይህችን ቤተ ክርስቲያን እንጠብቅ። ለቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎችና ለተወሰኑ ሰዎቻችን ብቻ የሚተው ኃላፊነት አይደለም። እያንዳንዳችንም በየበኩላችን ሃይማኖታዊና ኢትዮጵያዊ አደራና ግዴታ አለብን።

ስለዚህ ቅዱሳንና ብፁዓን አባቶች፥ ካህናት፥ እንዲሁም ወጣቶችና ምዕመናን በተለመደውና ዘወትር በምንጸልየው ጸሎት እንደምናወሳው «ለዘ-ነለፈ ሥርየት ወለዘይመጽእ ዕቅበት» [ላለፈው ይቅርታ ለሚመጣው ደግሞ ጥበቃ] ብለን ተባብለን የቤተክርስቲያናችንን ጎልውና በእንድነት እንጠብቅ። ዛሬ አክብረን በሆታና በዕልልታ አጅበን በምናወድሰው ታቦት ላይ በጆሮ ሲሰሙት በሚቀፍና በሚዘገንን የጽርፈት ቃል የተናገሩ ነገ ከነገ ወዲያ ድንጋይ ለመወርወር አሁን ድንጋይና ጉሊት ለቀማ ላይ መሆናቸውን እንገንዘብ። ነቅተን እንጠብቃቸው። ጊዚያችንን ቆብ ቀዶ ቆብ በመስፋት አናባክነው። የለቀሙትንም ድንጋይ መልሰው አልጣሉትም በታቦቶቻችን ላይ ወረወሩት እንጂ! በታቦት ላይ ማን ድንጋይ ይወረውራል ብለን ሌላውን ያለ አበሳው እንማው? የፎከራችሁት እናንተ የተሳደባችሁት እናንተ ከቶ ሌላ ማን ሊሆን? መቼም የፍየል ባሕሪ አፍን በበግ ማበስ ነውና ሌሎች ናቸው ለማለትና ለመምሰል የተደረገውን ተመልክተናል። አንድ ኢትዮጵያዊ ያውም ኦርቶዶክሳዊ የሆነ ሰው በታቦት ላይ ምንም ይሁን ምን የፈለገውን የፖለቲካ ድርጅት ይደግፍ ከታቦታችን ላይ ድንጋይ አይወረውርም። ማን ከእናንተ ሌላ ይህን የሚያደርግ ከቶ ይኖራል? ወደ እናንተ ያመለከትነውም አሁን አሁን ከመቼውም በላይ ሠይፋችሁን

መዝሣችሁ በቤተ ክርስቲያኗ ላይ እየሠነዘራችሁ ነው። ያለመቁሰሏንና ወደ ሐኪም ቤት ያለመሄዷን አትመልከቱ ሁሉም ሆኗል ተፈጽሟል። ዝምታው ቸልታው ከኛ ዘንድ በለሆነ ብቻ ነው። ለምዕመናን ያለኝ አቤቱታ ይህ ነው። ቀጥሎ በአባትነት በካህንነት በዲያቆንነት በምዕመንነት የዚች ቤተክርስቲያን ወገኖች የሆናችሁ ሁሉ ለቤተ ክርስቲያኗ ደኅና ውሎ ማደር አሰቡ። ጠይቋት ጎብኟት በሃኪ [እንደምን አለሽ] ቅድስት ቤተ ክርስቲያን በሏት።

ይችን አዊር ጊዜ፡ ይችን አዊር ሰዓት እንደ ዓይን ብሌን ታይታ ያሰበለዚያም ብልዊ ብላ እንደምትጠፋዋ ርራ ተቀምጠን አንመልከታት። የቤተ ክርስቲያናችን አዝመራ እጅግ ብዙ ነው። ሰብሳቢ ግን እንደሌለው የምናረጋግጠው እውነታ ነው። የቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቃውንት መለከቱ ይነፋላቸው። የክተቱ ጥሪ ይታወጅላቸው። በሕይወታቸው እንደ ማር የሚጣፍጠውን እውቀታቸውን በአንድነት ሆነው እንዲያዘጋጁልን ይሰብሰቡልን። «አማካሪ የሌለው ንጉሥ ያላንድ ቀን አይነግሥ» ነውና ቤተ ክርስቲያኒቱ ያሰ ሊቃውንቷ ልትኖርና ማንነቷ ሊታወቅና ሊገለጽ አይችልም። አሁንም ከአበው ምሳሌ «ፀሐይ ሳለች ሩጥ እናት ሳለች አጊጥ።» ነውና ያሉንን ምሁራን ከአንድ ክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተቀምጠው የሚወያዩበት አፋጣኝ ሁኔታ ይዘጋጅልቸው። ከአውሮጳውያን ዝርፊያና ከአይጠች ቁርጥማያ የተረፉትን የብራና መጻሕፍት በፕሮቴስታንቶች ተከበው በአሳት ሊያቃጥሏቸው በይፋ አውጀዋልና ትላንት ክትላንት በስቲያ የተነጣጠረብት የደብረ ዳሞ ገዳም የመጻሕፍት ዕቃ ቤት በእሳት እንደጋየ ሁሉ ነገ ከነገ ወዲያ ደግሞ ከዘረፉ የተረፈው የአዲስ ዓለምሰ ቤተ ክርስቲያን ባለ ጽዋ ላለመሆኑ ምን ዋስትናና መከላከያ አለው?

«ገድል ወይስ ገደል?» የተሠኘው መጽሐፍ ለመጽሐፉ ሽፋን አድርጎ የሣለው የደብረ ዳሞን ተራራ ነው። ዋላቻው የነደደበቱ መጽሐፍ በደብረ ዳሞ ገዳም ላይ ሠይጣናዊው ጥፋት አርፎበትስ እንደሆነሳ? ምሥክር ከሌለን ብለን ከመናገር አቅጣጫ ከማሳየት ችላ አንልም። አባካችሁ መላ ዘዴ ብልሃት ይፈጠርለት። ሌላውን ከሠይጣን የመጣውን በመስቀላችሁ አባሩት ይሸሻል። ከዚህ ወዲያ ታላቅ ሥራ የለም። በተረፈ እንዲሁ የጠላት መጠቋቆሚያ የሆናችሁበትን ከንቱ ነገር አርግፍ አድርጋችሁ ተዉት። አባቶቻችን ለእንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመት ሥልጣነ ክህነትን ለግብፆች ብቻ በመተው ከትውልድ ወደ ትውልድ በዝምታ በትዕግሥት ያሳለፉት ፈሪዎች ሞኞች ግድየለሾች ሆነው አይደለም። ነገር ግን ፍፁም መንፈሳውያን በመሆናቸው ነበር። በትግልና በንጥቂያ ለመውሰድ

ቢፈልጉ ኖሮ ብዙ ዕድል ነበራቸው። ለለማንያ አራት ዓመት ኢትዮጵያ ከግብፅ ጳጳስ ሳታስመጣ ቆይታለች። በዚያን ወቅት ራሳቸው ኢትዮጵያውያኑ ዲያቆናትንና ቀሳውስትን በመሾም ያን ጊዜ እንዳሳለፈችው የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ያስተምረናል። ታዲያ እንዲያ ዓይነት ትዕግሥት የነበሩንን ያህል ምነው አሁን?

ስለዚህ በሥልጣነ ክህነት ይገባኛልነት ያውም በገዛ ፈቃድ አስረክቦ መጥቶ ሽመቴን ብሎ መርህ የማይጠቅም ውትወታ መሳቂያነት የራስንም ሆነ የቤተ ክርስቲያንን ክብር እጅግ ዝቅ ማስደረግ ነው። ከእናንተ ደግሞ በአውነት እንጂ ከአውነት ውጭ በሆነ ሥራ ላይ ተጠምዳችሁ መታየት የናንተን ሰዎች ናቸውን የሰው ሥራ እየፈፀሙ ነው እንበል። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያኗን ልብስ በአደባባይ መግፈፍ ነው። እጅግ ሁላችንም የምናፍርበት የምንሸማቀቅበት ሥራ አያደረጋችሁ መሆናችሁን ዘወር ብላችሁ ተመልከቱት። የጡረታን መብት አስጠብቆ መላው የቅዱስ ሲኖዶሱ አባላት በጉባዔ ያፀደቁትን ውሣኔ እንደገና ከኢትዮጵያ ውጭ ሆኖ ያልሆነ ተግባር ሲፈጽሙ መታየት እጅግ ሥጋን ብቻ ሳይሆን ነፍስን የሚያስቆርር ነው። ይህን ማየት እንዴት ተቸገራችሁ? በተተወና በበቃኝ የተውትን ፕትርክና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ስለመድኃኔ ዓለም ብለው ይማለዱን። በገዛ ፈቃድም ከተውት ሥልጣን ላይ የሚደርጉት መረሩረፍ ያለውንና የቆየውን፡ ብርቅና ድንቅ ሃይማኖታዊ ንብረታችንን እያዘረፍን ነው። የሚያልፍ ቀን የማያልፍ ስምም እያሰጠን ነው። እጅግ በጣም አድርገን ልናስብና ልንጠነቀቅ ይገባል። ሃይማኖታችንን በአንድነት እንጠብቅ።

አሁን በእርቅና በሰላም ፋንታ ጥሉና ክርክሩ አንደ ቋያ እሳት በጣም ነደደ። አነሱን ሰጊዜው ገና አይፍኝቸው እንጂ ሕዝበ ክርስቲያኑን ግን ሰብልቦታል። ስለሆነም በአክብሮት የጠየቅነው ምለሳ ችላ ተብሎ በለሜን አሜሪካ ያለውን ሕዝበ ክርስቲያን በሰደተኛው ስም የፖለቲካ ካባ ለብሶ እንደ ፖለቲካ ድርጅቶች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ነፃ የሚያወጣ ሳይሆን ራሱን በራሱ ነፃ አውጥቶ መንበር ሠርቶ ይፈታል ይናዝዛል ሲልም የሾመውንና ያከበረውን ሲኖዶስ ያወግዛል። አርዓያነቱ ለፖለቲካ ድርጅቶች የሚጠቅም ቢሆን እስካሁን ወደ ሰማንያ መንግሥታት በኢትዮጵያ ስም ተመሥርቶ በነበር። ሁሉም ሚኒስቴርና አምባሳደር ሆኖ ተሾሞ አልፎለት ነበር። ይሁን እንጂ ገና ሥራው አልተቀዳም። ሆኖም የተፈፀመው ተግባር በአንዳንዶቹ ዘንድ ተደንቋል። የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሚያፈራርስ ቀርቶ የሚጎንጥ እንኳ ሽልማት አለው። አነሱ ተዝካር ይቅር። ለንበቴ ይቅር ታቦት አያስፈልግም ጳጳስ አንሻም እያሉ

በመሰበክ ላይ ላሉት የስደተኛው ሲኖዶስ እነ ስም አይጠሬን ከበሮ አሳዝሏቸዋል። መዝሙሩም እንደ ተመኘኋት አገኘኋት ሆኗል።

እሥራት ያልደረሰበት ሥጋዊ ሞት ያላጠላበት በአጠራሩ «ሕጋዊው ሲኖዶስ» ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን በመጣስ ስደት ለወሬ ያመቻል ሆነና ማስረጃ የማይቁየቅበትን ድርሰት እያነበቡ ለዚሁ መከረኛ ሕዝብ የሁለት ዓለም ስደተኛነቱን ለማረጋገጥ ከእናት ቤተ ክርስቲያኑም አሳደዱት። ቤተ ክርስቲያኒቱ በቀኖና ቤተ ክርስቲያን መሠረት ሲኖዶሱ ያልፈቀደውንና ያልወሰነውን የሲኖዶስ ግንጠላ አዘጋጅተው አሜሪካ መጥተው እኛ ነን በሚሉ አባቶች የተፈፀመው በደል ታሪክ የማይረሳው ታላቅ የበደል በደል ነው። ለአያንዳንዳቸውም ጎሊና የእግር እሳት እንደሚሆንባቸው ርግጠኞች ነን። ይህን የመሰለ መንፈሳዊውን ህብትና ፀጋ በአመጽ ያውም በስደት አገር እየኖሩ በአገሩና በቤተ ክርስቲያኑ ናፍቆትና ፍቅር ልቡ የነደደውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ላይ አመድ ትቢያ በተኑበት ነስነሱበት። ባያስተውሉ ነው እንጂ እኛ በታሪክም ሆነ በዕድሚያችን ያየነው መንፈሳዊውን ነገር በጉልበትና በኃይል ታግለው ወይንም በጉልበት ቀምተው አባቶች ሥልጣነ ክህነት ሲወስዱ ዓይተንም ሰምተንም አናውቅም። አሁንም ተቀማን ከመንበራቸው ተገለበጡብን የሚሏቸው አባቶችም የፖለቲካ ድርጅቶችም ሌሎችም ወዘተ... ሁሉ የጅራፍ ጩኸት ነው። ራሳቸው ለቀው መጥተው ከዚህ ሲደርሱ ተቀማሁ የማይሆን የማይደፈር የማይገባ እንኳን ከአባቶች አንደበት ሲነገር ይቅርና አብሮ ከሚወጣና ከሚገባ ፊርፋሪው ይቀርብኛል ከሚለው እንኳ አድር ባይና እኖር ባይ የማይጠበቅና የማይነገር ነው። እኛም እናውቃለን የአባቶችም ጎሊና በሚገባ ያውቀዋል። ታዲያ ይህ ለኛም ሆነ ለእነሱ ይገባልን?

ለአንድ ሺህ በድስት መቶ ዓመታት ኢትዮጵያ በአሌክሳንድሪያ ቤተ ክርስቲያን ሥር ስትማቅቅ ስትኖር ለምን በንጥቂያና በዝርፊያ ሥልጣኑን በዕጃቸው አሳደረጉትም? የስደተኛው ሲኖዶስ ተጠሪዎችን ያህል እውቀት ጉብዝና ድፍረትና ብልሀነት ሳይኖራቸው ቀርቶ ነውን? ወይንስ በተቃራኒው እንደነሱ የሥልጣን አሳሾች አልሆን ብለው? ቤተ ክርስቲያናችንን አዋረዱብን። ዝቅ ዝቅ አደረጉብን። በኛ ዕድሜ የምናውቃቸው አባቶች እንኳን ለሥልጣነ ክህነት ሽሚያ ይሰደዱና በአገራቸው በክብር ተሾሙ ሲባሉ እምቢ ብቁ አይደለንም ብለው ሳይሾሙ የቀሩ የሉምን? ምን ያህል ሞኞች ወይንስ በእውነት ብዙኃን ስለሆኑ ነው? በጎንዘብ የማይገዛውን በወገን በአድማ የማይወሰደውን ሥልጣነ ክህነት እንዲሁ ቀባሪ ያጣ ሬሳ

ሆኖ በየመንደሩ ሲጣል ማየት ለኛ ለአባላቱ ምንኛ አሰቃቂ ነገር ነው።

እናንተም አባቶች ይህን በማድረጋችሁ ወገን አላበዛችሁም። ይልቁንም እናንተኑ የሚያጠፋ የአካል ቁስል አወጣችሁ። ይህ ደግሞ ሕክምናም አይኖረውም። ከራስ የሚገኝ የገላ ትል ራስን መልሶ የሚበላና የሚያበላሽ ጠረንን የሚለውጥ ለዓይንም ለአፍንጫም የማይበጅ ቁስለ ሥጋ ነው የፈጠራችሁት። እንዴት አድርገን እንቅረብ? ከዚህ በኋላ ምኞታችንና ጸሎታችን እባክህ ለእድሚያቸው ወሠን ዳር ድንበር አድርግበት። ይበቃቸዋል ነው። ተጸልዮ ተለምኖ የማይታወቅ ቅሠፋቸው አጥፋቸው ያልነው ለአጽራረ ማርያም ነበር እንጂ ለአባት ያውም ለመንፈሳዊ አባት? አይደለም አልነበረም። «አ እግዚኦ ዕቀቦ ለነ ከመ ብንተ ዓይን» [ጌታ ሆይ እንደ ዓይን ብሌን ጠብቀው] እያልን የምንጸልይላችሁን ልጆቻችሁን መልሰን ቅሠፍልን አውዱ እንደተደፋ እንበላችሁ? በአንድ አፍ ሁለት ምላስ አላደረጋችሁንምን? ልጅ ከአባቱ የሚማረው ጥሩ ነው አይደለም ብሎ አይመርጥም አባት አናት የሚያደርጉትን ልጆች ዓይተውና ተመልክተው መቅዳት ብቻ ነው። በኛ አትፍረዱብን የእናንተ ልጆች ስለሆን ነው።

የአሁኑ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላትና መሪው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ አሜሪካ ነበሩ። ጊዚያቸውን ያሳለፉት በዩኒቨርሲቲ ውስጥ በትምህርትና ባላቸው ትርፍ ጊዜም ኢትዮጵያውያኑን ስደተኛ ሕዝበ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያናቸውን ቀኖና ጠብቀው በማስተማር እንጂ አንድ ቀንም ቅዱስ ሲኖዶሱን ሲቃወሙ አልተሰሙም። አላደረጉም ይህንም ሁላችንም በሕይወት ያለንና የነበርን የምንመሰክረው እውነት ነው። ምነው እናንተ ላይ ሲደረስ ይህን የመገንጠል መንፈስ አሳደረባችሁ? ለጽድቅ ወይንስ ለኃጢዓት? መልሱም ተሰጥቶበታል። የጽድቅ ያለመሆኑን ተረድተነዋል ለማለት ነው። ከውግዘት ሌላ መሣሪያ የላቸውም። የሰላም የእርቅ መልእክተኞችንም ልክ ለሰላም ለምሕረት ዕጅ አልሠጣችሁም በአመጻችሁ ቀጠላችሁ። ታዲያ ቅዱስ ሲኖዶሱ ከአካልነት ከአባልነት ከአንድነቱ ማዕድ አነሣችሁ። ይህ ውግዘት ነፍስና ሥጋን አይለይ እንጂ መንፈሳዊ ተግባር የምታከናውኑበትን ሥልጣነ ክህነት መልሶ ወስዶባችኋል። በሥልጣነ ክህነታችሁ ስምም አይጠራችሁም። ከዚህ ወዲያ መሻር ከዚህ ወዲያ በመንፈሳዊ ሕይወት መዋረድ ምን ይምጣ?

በመንፈሳዊ ታሪካችን ውስጥ መንበሩን ትቶ ሄዶ ራሱን እንዳንዱ ስደተኛ አድርጎ የሚኖር አባት በሰው አገር ከተማ ሕጋዊ

ነኝ ብሎ ተነሥቶ ሸ.መት ሲሰጥ በታሪክ የመጀመሪያ ነው። እንደ አንደኛ የመጀመሪያ ተብሎ ለመመዝገብ ካልሆነ በስተቀር ትርፉ ለኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታላቅ ውረደትና ሽንፈት ነው። ለአባላቱ ለምዕመናኑም ታላቅ ኃዘን ነው። እስካሁን ቤተ ክርስቲያኗ ጠንካራ የነበረች ገና ዛሬ ተዋረደች። ይህን ውርደት ባከናነቧት አባቶች ምዕመናንስ ምን እናድርግ? እኛም የመወሰን ግዴታ አለብን። የስደተኛው ሲኖዶስን ማን ነው እውቅና የሚሰጠው? ተቀባይነቱስ የት ላይ ነው? የልጆች ጨዋታ አልሆነም አልመሰለምን? ራስ ቢትወደድ ደጃዝማች እየሆኑ እንጫወት ዓይነት ነገር ሆኗል።

ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ አንዳንድ ስደተኞች አሜሪካ በስደት ተቀምጠው ድሮ አገራቸው ሆነው ይመኙት የነበረውን ፊታውራሪነት ደጃዝማችነትና ራስነት ሹመት ሳያገኙት የቀሩትን በንጉሡ ስም አንዱ ማኅተሙን አስቀርጸ የሸ.መት ደብዳቤ እየጻፈ ገንዘብ የሚቀበል ነበር። እኒያ ተኗሚዎች ደግሞ በዚያ ስም ካልጠራችሁን እያሉ ሲማሉና ሲሳቅባቸው ነበሩ። ታይተዋልም። ክብርም ሆነ ዋቅም የማያመጣ ሸ.መት ለሚመለከተው የቀልድ ቀልድ ነው። ለእነሱ ግን ገንዘብ ስለከፈሉበት ሊጠሩበት ወደዱ። ሸ.መቱም ድሮ ከሚኖሩባት ጎጇቸው ታዛ እንደሆነ እላወጣቸውም። የቤተ ክርስቲያኑም ሸ.መት ተመሳሳይ ነው። ይልቁንም ሸ.መቱ በትትክክል የሚሠጣቸውን አባቶች በከንቱ ዕድላቸውን አበላሽባቸው። አንገታቸውን አንቀው የበለስ ፍሬን አጎረሷቸው። ይህም እግዚአብሔርንና ቤተ ክርስቲያናችንን እናገለግላለን ብለው የመረጡትን የምንኩስና ሕይወት የቀኖና ቤተ ክርስቲያን ማፍረሻ የጽድቅ መደምሰሻ አደረጉባቸው። ሁሉንም የሸመውና የሸለመው ቅዱስ ሲኖዶስ ያልደገፈውንና ያልሰጠውን ሸ.መት እንመገባለን ብለው ተኩነቡት። ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ጣሱበት። እነሱ ተሳስተው ሌሎችንም አሳሳቱበት። እነሱ ተወግዘው እንዳይቀሩ ወደፊት ቤተ ክርስቲያናቸውን ሊያገለግሉ የሚችሉትንም አሰናከሏቸው። ታሪክ ራሷን ትደግማለች እንዲሉ የኤዶም ታሪክ ተደገመ።

የስደተኛውን ሲኖዶስ ማነው እውቅና የሰጠው። የካቶሊክ፣ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጠቅላላ ጉባዔ ወይንስ የኛዎች የተባሉት ምዕመናን ብቻ! እንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት አትወቋቸው ከዋናዋ ቤተክርስቲያን የተለዩ ናቸው ሲሉ ለየአብያተ ክርስቲያኖቻቸው መግለጫ አውጥተዋል። ያገኙት በረከት ይኸው ነው። እኛም የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ከሌሎቹ በበለጠ ለእኒህ ለስደተኛው ሲኖዶስ አባላት እውቅናና

ክርስቲያን አባላት የሆን ምዕመናን በእውነት ስለ እውነት ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ስንል አንድነቷና ክብሯ ተጠብቆ እንዲኖር ያልተቆጠበ ጥረታችንን እንቀጥል። ይህን ሳናደርግ ብንቀር ታሪክም ቤተ ክርስቲያናችንም ትውልድም ይፋረዱናል።

መቼም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያዎች አባቶች በተለይም ከፍተኛውን ሥልጣን ከህነት የተሸከሙት አባት ፓትርያርክ መንበረ ፓትርያርኩን በገዛ ፈቃዱ የተወና ሕዝበ ክርስቲያኑን በትኖና ጥሎ የጠፋ ፈጽሞ ተነግሮም ተነቦም አያውቅ። ቢመኙ እንኳን ወደ ገዳም ለጸሎት እንጂ ወደ አሜሪካ መጥቶ እንደገና ባለቤቱ ሕጋዊው እኔ ነኝ ብሎ ጳጳሳትን መሾም እጅግ በጣም የድፍረት ድፍረት የንቀት ንቀት ፈጽሞ ያለማወቅና የኃጢዓት ኃጢዓት ነው። ገና ሲሾሙም አይገባቸውም ብለው ምዕመናኑ ሲጮሁ ለከንቱ አልነበረም። መራጮቹ ግን በአፈሙዝ ሽታ ስለነበር ከመሞት መሰንበት ብለው በታዘዙት መሠረት መርጠውም ባይሆን በለማቸው መርጠዋል ተብሎ ተነግሮባቸዋል። ያ ሁኔታ ትክክል ያልሆነውን ያህል ፈተና በመጣ ጊዜ በድቡሽት ላይ የተገነባ ቤት በመሆኑ ማዕበሉን ሊቋቋመው አልቻለም ተነቃቅሎ ሄደ። በዚያን ወቅት በዚያን ሰዓት ከሥልጣንም አይውረዱ እስከ ሞትም ድረስ ይጋፈጡ ብለው የመከሯቸው አባቶች ዛሬውኑ በሕይወት አሉ። ነገር ግን ጽናቱ የለምና አይሆንም ብለው ሥልጣናቸውን ለመልቀቅ ወሰኑ። አሰረክበው ተቀመጡ። ቢያዩት ቢጠብቁት ያ የፈሩት ሞት ጨርሶ በሩንም አላንኳኳም። ሁለት ዓመት ተጠብቆ እሥራቱም ሆነ ሞቱ የውሀ ሽታ ሆኑ። ይህማ ከሆነ ወደ ሥልጣኔ ልመለስ ሲሉ ማመልከቻ ለቅዱስ ሲኖዶሱ ሲጽፉ በግልባጭ በዚያን ጊዜ ለሽግግር መንግሥቱ ፕሬዚዳንት ለነበሩት ለአቶ መለስ ዜናዊና በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር ለነበሩት ለአቶ ታምራት ላይኔ በደብዳቤ ጠየቁ። ሲኖዶሱ ጥያቄያቸውን አክብሮ እሱም እንደሳቸው ኃሳቡን ለውጦ አዎንታ መልስ ሳይሰጣቸው ቀርቷል። ይሁንና በወቅቱ ወደ ሥልጣኔ ልመለስ ብለው የጻፉትን ደብዳቤ ወደፊት ከትክክለኛው ቦታ ላይ ይቀርባል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ነው ቅዱስ ሲኖዶሱ ሥራውን ቀጥሎና ምርጫውን አካሂዶ በመንበሩ ላይ እቃቤ መንበር አባት አስቀምጦ ለአቡነ መርቆሬዎስም የጡረታ አበልና መኖሪያ ቤት መኪና እስከነሾፌሩ መድቦ ያኖራቸው። እኒህ አባት የሚወስዱት ውሳኔ ሁሉ ቀና ያልሆነ የባሰውን ደግሞ ሁለተኛ ጥፋት ወደ ኬንያ አቋርጠው አልባሌ ሰው መስለው ገቡ። ያንድ ሰው ነፍስ ይዘው እልነበረም ወደ ኬንያ የሄዱት። እንዲያው አላለውም አንጂ ከጠረፍ ቢያዙ ኖሮ!

ልጅነታችንን መንሳት ብቻ ሳይሆን መልካም አይደለም እንበላቸው። ይህን በማድረግ ሕገ ቤተ ክርስቲያናችንን አጠናክርን ታሪካችንን ጠበቅን የቤተ ክርስቲያኗን አንድነት አጸናን ማለት ነው። ይህን ባናደርግ ግን ቤተ ክርስቲያናችንን ለተወሰኑ ለምናውቃቸውና ለምናፈቅራቸው ብለንም ለምናከብራቸው አባቶች ሰንል ቤተ ክርስቲያናችንን አጎሳቆልን ማለት ነው። እነሱ ነገ ከነገ ወዲያ ኃላፊና ጠፊ ናቸው። ነገና ከነገ ወዲያ ለምትኖረው ቤተ ክርስቲያናችን ህልውና ሰንል ግን ይህን ከሕገ ቤተ ክርስቲያን ውጭ ለተፈፀመ ሥራ እኒህን ፈፃሚ አባቶች ከመደገፍና እውቅና ከመስጠት እንቆጠብ። ይህንም ሰናደርግ ብዙዓን አባቶችን በመጥላት ሳይሆን ከእነሱ ፍቅር የቤተ ክርስቲያናችን አንድነትና ጎልውና ይበልጥብናል በማለት ነው።

ከእነሱም ዘንድ ክርስትና ማስነሳት ተክሊል መፈፀም ጸሎተ ፍትሐት ማሰደረግ ተገቢ አይደለም። ቤተ ክርስቲያናችንን እንወዳለን እንንከባከባለን የምንል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባላት ይህን መፈፀም ሃይማኖታዊ ግዴታችን ነው። ይህንም ሰናደርግ አባ ዕገሌ ዘመዴ ናቸው። አባ ዕገሌን በጣም እወዳቸዋለሁ አባ ዕገሌ የመንደሬ ሰው ናቸው አንበል። በኢትዮጵያዊነት የኛው ወገኖችና አባቶች ናቸው። የጠላነው ሥራቸውን እንጂ እነሱማ የሁላችንም ወገኖች ናቸው። ክጣት ጣት ይበልጣል እንዲሉ ቅድሚያ ለቤተ ክርስቲያናችን በመስጠት እንጂ! ታዲያ ምንጊዜም ምንም ብንወዳቸውና ብናከብራቸው ከቤተ ክርስቲያናችን በላይ ማድረግ ክርስቲያናዊው ግዴታም ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊነቱም ያስገድደናል። እንዲህ ከሕግ ውጭ የሆነ ተግባር ሲፈፀም የቤተ ክርስቲያናችንን በር ካልጠበቅን በዚህ በተሠበረ በር ነገ ከነገ ወዲያ የሚገባውን ብናውቅ ዛሬውኑ ከቤተ ክርስቲያናችን በር ላይ በሞትን እንዳይመጣ አሁንኑ እንበርታ። የማንነታችን መግለጫና ሃይማኖታዊ መገልገያ የሆነችንን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን በሰው አንለውጣት። የታደሱት ራሳቸውን ለሞት አሳልፈው ሠጥተውሳታል። የቀሩት ደግሞ ሞትን ፈርተው መንጋቸውን በትነው ጥለውና የትም በትነው መጥተዋል። እንዲህ ሲባል እውነት ስለሆነ እንኳን ሰጉረሮ ለጆሮም ሲሰሙት ይመራል። ይህን እናውቃለን። በእነሱም ዘንድ እንዲህ ማለት ፍቅርን ሳይሆን ጥላቻን እንደሚያነድ እናውቃለን። ነገር ግን እውነት የግድ መነገር ስላለበት ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው።

ይህን በግልጽ መጻፉና ማቅረቡ ራሱ ሰማዕትነት ነው። መጠላትን መዘለፍን ያስከትላል እሺ በጎ እውነቱን ተናግሮ በመሸበት ማደር ሃይማኖታዊ ግዴታ ነው። ከእነሱ ፍቅር የቤተ

ሁኔታቸው በፎቶ ግራፍ ቢቀረጽ ኖሮ ለእሳቸው ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያኗ ምን ዓይነት ውርደት ነበር? ያ አፈፃፀም ራሱን የቻለ የቤተ ክርስቲያኗን ክብር እጅግ በጣም ዝቅ ማድረግ ነው። እንዴት ሄዱ እንዴትስ ኬንያ ደረሱ? ምን መስለውና አክለው ነበር? ምንስ ገጠማቸው? ብለን ዝርዝሩን መጻፉ መክራውን ማብዛት ስለሆነ አልፈነዋል። ይህ ሁሉ መከራ ቢራሳቸው ላይ ያመጡት እንዲት ነገር ለመፈፀም ሳይችሉ ቀርተው ነው። እሷም ጽናት ናት። «ጽናዕ ጊዮርጊስ» በመባል የምትታወቀዋን ድምፅ የሚነግራቸውና የሚያሰማቸው ጠፍቶ ነው? ቢኖርም አይሰሙ ይሆን? ይህ በእሳቸው ላይ የደረሰው ውርደት እንግልት በቤተ ክርስቲያን አባትነታቸው በሁላችንም ዘንድ እንደደረሰ የሚቆጠር ነው። እጅግ በጣም ያሳዝናል። እጥፍ ድርብ ድርብርብ ሰሕተትና ክብርን ዝቅ ማድረግ በላቸው ላይ ብቻ ሳይሆን በኛ በምዕመናን ሁሉ ላይ ነው።

እንደኛ ጥፋት ወደ ሁለተኛዋ ከዚያም ወደ ሦስተኛዋና ወደ አራተኛዋ ላይ አደረሰቻቸው። ጥፋት አንድ ሥልጣንን በገዛ ዕጅ መልቀቅ፣ ሰሕተት ሁለት በጡረታ ከሁለት ዓመት በላይ ከቆዩ በኋላ በሥውር ወደ ኬንያ ድንበር ጥሶ መሰደድ፣ ስሕተት ሦስት ከኬንያ አሜሪካ ከገቡ በኋላ ሕጋዊው ፓትርያርክ እኔ ነኝ ብለው የሰደት ሲኖዶስ ማቋቋም፣ ስሕተት አራት በሌለና በተዉት ሥልጣነ ክህነት አማካይነት በአንድ ጊዜ አሥራ ሦስት ኤጲስ ቆጳሳትን መሾም። አምስተኛው ሰሕተት ላይሆን በራሳቸው ላይ የደረሰው በውገዘት ሥልጣነ ክህነታቸውን የሠጣቸው ቅዱስ ሲኖዶሱ የሾማቸው መልሶ ቀማቸው። ወደ ኋላ ጥሰውትና አልፈውት ወደ መጡትም ወደ ምንኩስና ለማቸው መለሳቸው።

ይህ ሁሉ የጥፋት ጉዙ ሕማሙ ቁስሉ በላቸው ላይ ብቻ የደረሰ ሳይሆን በሁላችንም በምዕመናኗና በቤተ ክርስቲያኗም ታሪክ ላይ ነው። እጅግ ያሳዝናል። እነሱን የሾመና የሸለመ ቅዱስ ሲኖዶስ ሥልጣናቸውን ሲይዝ እነሱ ደግሞ ዓይን ለዓይን የመሰሰ ውሳኔ ይህ የአሜሪካው ሲኖዶስ የሾማቸውን ሲኖዶስ ሥልጣን ለመያዝ ምን እቅም ምንስ ብቃት አለው? «አባቴ ልጅ አለዎት ወይ? ኧረ የለኝም ልጂ! የልጅ ልጅሳ? በየት አልፎ።» የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ለዚህ ዋና ተጠቃሽ ማስረጃ ነው። የሁላችንም ጥያቄ የሾመና የሸለመን ሲኖዶስ እሱም ጥለውት የመጡት ምን ዓይነት ብቃት አለው እንዲህ ብሰነዋል የሚባለው? አንድ ምሳሌ ላቅርብ። ተክለ ሃይማኖት በረንዳ ላይ ተኝተው ከሚያድሩት ቤተ አልባዎች መካከል አንዱ ለጓደኞቹ ስሙ ጤንነቴ ዝቅ ብሏልና ኑዛዜ ላድርግ ኑ ምሥክር ሁኑኝ ብሎ ይሰበሰባቸውና ኑዛዜውን ይናገራል። እንግዲህ

ክርስቲያን ፍቅር ይበልጣል ነው። አንድ ሎሌ ለሁለት ጌቶች ሊገዛ አይችልም። እኛና የመለስን ሰዎች ከዚህ ላይ ያየነውን የምናውቀውን ከልመሰከርን ሐሰተኞችና ኃጢዓተኞች እንሆንምን? መንፈሳዊ ድፍረት መንፈሳዊ ሕይወት ማለትኮ ስለ እውነት መናገርና መሞትም ነው። ሌላው ቢቀር ስቀጣዩ ትውልድ ምስክርነትን መተው ሃይማኖታዊና ብሔራዊ ግዴታ ነው። ዛሬ ቢኖር ነገን አይደገምም። የሰው ልጅ ሕይወት እንደ ጥላ አላፊ ነው* እንደ አበባም ረጋፊ ነው። እንኳን መንፈሳዊ አባትን ያህል ታላቅ ንውድ ከቡርና ብርቅ ድንቅ በእድሜ የሚበልጥን በመንገድ የሚያገኙትን አረጋዊ እንኳ ፅጅ ነሥተው ስላምታ ስጥተው መንገድ ስቅቀው አክብረው ያሳልፉታል መንፈሳዊ አባትንማ እንደ ታቦት በራስ ላይ የሚያስቀምጡት ታላቅ ክብር የሚሠጡት ነው። አሁንም እነሱን ዝቅ ስማድረግ ፈጽሞ ዓላማ የለኝም። እንዴት አድርጌ እንደማከብራቸው ልብን የሚመረምረው ራሱ እግዚአብሔር ያውቀዋል። ታዲያ የእነሱ የብውዓን አባቶቼ ፍቅር ይብለጥ ብዬ የተፈፀመውን ስሕተት ከመመስከር አልሸሽም። ይህን እንዳላደርግ መንፈሳዊ ሕይወቴ አይፈቅድልኝም ይከለክለኛል። ስነገሩማ ሌሎችስ የሚታመትስ በደል ሲደርስ ዝም አላችሁ እየተባሉ አይደል? እኛስ ዘንድ ይህ እርሮ የገና ገና አሰሚና ጪሂ የለም ተብሎ በደል ሲፈፀም ስሕተት ሲሠራ ዝም እንበልን? አይሆንም አይገባም። ከኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ጥላቻ የእነሱ ፍቅር ይቅር ለምንጊዜም ይጠንቀር። አባቶችም ሊያውቁት የሚገባው ነገር ቢኖር ይህንኑ ማለት ምንም ብንወዳቸውና ብናፈቅራቸውም ከቤተ ክርስቲያናችን በላይ በማድረግ አይደለም። እኛም ምዕመናን ይህን የማናደርግ ከሆነማ እንዲያው አያድርገውና ከእነሱ አንዱ ሌላ ሃይማኖት ቢከተሉ አብረናቸው እንጓዛለንን? አይደለም አይሆንምም አናደርገውም። እንግዲያውስ እኛን መስለውና አክለው ለኛ ወዳጆች ሆነው አባ አባ ብላ ሾማና ሸልማ አባት ብላ ይዛቸው የነበረችዋን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንን ጥለዋት ሲመጡ የስድስት ወር ልጇን ከባዶ ቤት ጥላ የጠፋች እናት የእሷን ደግነትና እናትነት ልጇን መውደዷን ብትነግረን ጎብረተሰባችን እንዴት ያለች እናት ናት? ብሎ አይጠይቅምን? ሥልጣኑ ከህነቱኮ የምዕመናን መጠበቂያ መሣሪያ እንጂ የሰው ማስፈራሪያ የግል ግርማ ሞገስ መታያም የእነሱ በም መስወጫና መከበሪያ ብቻም አይደለም። ሥራውን ከቦታው ላይ ሆነው በተሠጣቸው ሥልጣን ሲያገለግሉበት እንጂ! ያለዚያማ ሲመች ሲመች ሲደላ ብቻ የሚሠሩበት ችግር ሲመጣ ጥለውት የሚሸሹበት ከሆነ ሹመቱ ራሱ እሪ ይላል። ከእነሱ ጋር አልኖርም በቃኝ አስለቅቁኝም ይላል። በመከራ ጊዜ ጥሎ የሚሸሽ ጓደኛ ከጠላት የከፋ ነው። ስለዚህ አሁን የዚች ቤተ

ክርስቲያናችን ዝም ብላ መመልከት አይገባትም። እነሱ ዛሬ ብዙ የመሰበኪያና የመሳቢያ ስልት እንዳላቸው የታወቀ ነው። የእኛም ቤተ ክርስቲያን «እሾህ በእሾህ ይነቀላል» እንደሚባለው በተመሳሳይ ዘዴ ልጆቿን ከያሉበት መስብሰብ ይገባታል። እነሱም ቃሏን ስምተው ነገ ዛሬ ሳይሉ ይመለሱ። የሰው ቤት የራስ አይሆንምና።»

[አባ ጎርጎርዮስ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ በዓለም መድረክ ገጽ 9]

የእነዚህ የመጤ ሃይማኖት ተከታዮች ኢትዮጵያ ሲመጡ በእውኑ ሃይማኖት ሊያስተምሩ ነውን? በእውነት እንነጋገር እስቲ? ሃይማኖት የብሉይ ኪዳን የክርስትና ወይንስ እስልምና? ወይንስ «በስመ አሐዱ ይስሃብ ካልኡ» [አንዱ ሲጠራ ሌላው ይገባል] በክርስትና ስም ገብተን ያሻንን ያፈነገገን እናድርግ ለማለት ነው? መልሱን ብናውቀውም «ነጋዴ ሲያፍር ጨው ይልላል» ዓይነቱ ነገር መሆኑ ነው። የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አሜሪካ ገብታለች ነገር ግን ላሉት ኢትዮጵያን ብቻ ልጅ ሲወልዱ ጸበል መርጨት ማጥመቅ በተክሊል መዳርና ሲሞቱ መፍታት ከዚያም እሁድ እሁድ ብቻ ቀድሶ ማቁረብ ናቸው ያሉት የሚከናወኑት ሥራዎች ከእነዚህ ውጭ ምንም የሚሠራ ነገር የለም። ከዚህ ውጭ ቢኖር ቤተ ክርስቲያኑ በሚታወቅበት የመልአክ የጻድቅ ወይንም የሰማዕት ስም በዓመት በሚከበርበት ቀን ብቻ ተጠራርቶ ሄዶ ማጎሌት ተቁሞ ተዘምሮና ተወድሶ ይበታተናል እንጂ አዲስ አማኝ ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ሲገባ አይታይም። እንዲያ ስማድረግ እኮ ቁሱም ለውጭው አገር የተዘጋጀና የተደራጀ መሆን አለበት። ታዲያ ፈረንጆቹም ሆኑ የእነሱ ተከታዮች ኢትዮጵያውያን መረብ ይዘው የሚሄዱት ወደ ኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞችን ስማጥመድ ነው እንጂ ፈረንጂ ሲይዙ አይታዩም። ራሳቸውን ማስጠመድ ብቻ በበቂነት ተቆጥሮላቸው። ከዚህ ውጭ የሚሸጠውና የሚስወጠው ያው ኢትዮጵያዊው ያውም አርቶዶክሳዊው ብቻ ነው። ትርፍ የሌለው ንግድ ይሏል ይህን ነው። ከዚህ እንውጣ።

ይህ ያስውና የሚሆነው አልቦኃ ብሎ «በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ» እንዲሉ በውጭ እኖራለሁ አለሁ ብሎ የተነሣው የስደተኛው ሲኖዶስ መሪና አባላት ኤጲስ ጳጳሳትን መሾሙን ቀጠለ። የጳጳሳትን ክብርና ማዕርግ ጠርሶ ዝቅ ከማድረግ ሌላ ከብር እንደሁ ፈጽሞ አይጨምርም። ታዲያ ራሱን የሚሰድብ የሚያዋርድ ትሕትና ሊባል ነው? አይደለም አይሆንምም። ይህን የመሰለ ዓላማስ ይዞ መሰደድ ቤተ ክርስቲያኒቱን መበደልና ማጎሳቆል መሆኑን አጥተውት

ሰሞት ፍታቱ ኒው ዮርክ እንዲደረግ። መቃብሬ ደግሞ ቅድስት አገር ኢየሩሳሌም ይሁን ብሎ ኑዛዜውን ካጠቃለለ በኋላ ራሱ ተናዛዡ ይመልስና ኑዛዜዬ በተግባር ይተረጎማል ብዬ አይደለም። ነገር ግን ምን ተናዘ ሞተ ቢባል ይህን ብሎ ነበር እንዲባል ብዬ ነው ሲል ኑዛዜውን ደመደመ እየተባለ ይነገራል። ያ ምሳሌ እነሆ አሁን ተደግሞና በሥራ ተተርጉሞ እየነው።

አይደለም። ለራሳቸው ቂም በቀል መወጫ ቤተ ክርስቲያኗን እንዴት በደረቁ በቀረባ ይላጫታል? በማድረግ ላይ ያሉትን ዘወር ብለው ሲመለከቱት ምን ይሰማቸዋል? እንዴትስ ቆመው ይሄዳሉ? የሥራቸው ውጤት የቤተ ክርስቲያኗን ሽኮና አይነድፈውምን? ወይንስ እኔ ከሞትሁ ሰርዶ አይብቀል ዓይነት ግዝት ማስተላለፍ? ያለውንና የሚኖረውን ሕዝበ ክርስቲያንስ ቁም ስቅሉን መንሳት አይደለምን? ለሀገሩ ለወገኑ ለቤታ ክርስቲያኑ የሚጸልየውን ሕዝበ ክርስቲያን ማደናቀፍ አይደለምን? በእውኑ የጳጳሳት እጥረት ቤተ ክርስቲያኗ አለባትን? እኒህ አባቶች ለዚች በሰሟ ለተሾመና ለከበሩባት ቤተ ክርስቲያን ማሰብ ነውን? ለራሳቸው ከብር ለራሳቸው ምቾት ተከታይ አጋር አጃቢ ፍለጋ ከየቦታው በአገልግሎት ላይ ያሉ መነኮሳትን መሾም ምን ይሆን ትሩፋቱ? ለማቸውን ለውጦ በአባልነት የምናዋጣትን መክሊት የግሪክ መስቀልና የግብፅ ቆብ መግዣ ማዋል በአንፃሩ ግን የአብነት ትምህርት ቤቶች በችግር ምክንያት በመዘጋት ላይ ባሉበት ወቅትና አንዳንድ በገጠሩ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የዕጣን መግዣ አጥተው የፅድ እንጨት ፍቅፋቂ ቤተ ክርስቲያናቸውን እያጠኑ ባሉበት ወቅት ይህ ከውጭ ያለው ክርስቲያን ወገናቸው ርዳታ እንዳያደርግላቸው ተለይቷል ተገንጥሏል ሕጋዊው ሲኖዶስ ከዚህ አሜሪካ ውስጥ ነው ማለቱ አሜሪካ ከመቼ ወዲህ ነው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መቀመጫ የሆነው?

በእውነቱ ሁሉን ንቀን ትተን ያለን ነን ከሚሉ አባቶች ያውም ኢትዮጵያውያን እንዲህ ዓይነት ታላቅ በደል ከቤተ ክርስቲያኗ ላይ ስታደርሱ የደብረ ሊባኖስን ገዳምና መነኮሳት ከፈጀው ከሞሶሎኒ ሠራዊት ተግባር የእናንተን የሚለየው ምንድን ነው? ያውም በገዛ ፈቃዳችሁ ጥላችሁት ስመጣችሁት ሥልጣን የእልክ መወጫ ስትሉ እንዴት ቤተ ክርስቲያናችንን ታጎሳቁላላችሁ? ምዕመናንን ከእናት ቤተክርስቲያናቸው ትለያላችሁ? የእናንተ እረኛነት ጠባቂነት በጎቹን ጠብቁ ሥልጣኑ ከህነታችሁ የምታሠማሩን ወደ ለመለመው መስክ ወደ የምንጠጣው ወደ ጠራው ምንጭ ወይንስ ወደ እናንተ ሥልጣን ማጣት ፀፀትና ጥርስ ማኘጨት ወደ ጥላቻና መከፋፈል ነው? የምትመግቡን ፍሬ ይህ ነውን? ለሕይወታችን ለማኅበራዊ ኑሯችን እንዲያው የነፍሳችንስ ነገር አንድ ጊዜ ሞቶ ቀርቷል። በደርግ ተሸ.መዋል መባልዎስ ሲያንስ ነው። እግዚአብሔር የለም የሚል መንግሥት ጋር አብሮ ከዋለና ካደረ ጋር ምን ይጠበቃል። ስሹመታችሁ ስትሉ ይችን ጥንታዊትና ብቸኛ ቤተ ክርስቲያን እንዴት እንዲህ በአደባባይ ራቁቷን ታስቀሯታላችሁ? ቤተ ክርስቲያንንም የድርጅት መሥሪያ መጋገሪያና ማቡኪያ ወጥ

ምዕራፍ ሦስት

፩ . አእምሩ ወለብዉ [እወቁ ተገንዘቡ]

ና

ከዚህ ላይ ለኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ አቤት የምለው እንዲት መንበር፥ አንዲት ሃይማኖት፥ እንዲት ጥምቀት ሆና ሳለ ዛሬ በየክፍለ ሀገሩ ወጣቱ በፕሮቴስታንት ያውም በጴንጤ ሃይማኖት ራሱን እየተላጨ በጠላት ዕጅ ተማርኮ፥ ከጸሎት ቤቶቻቸው አሥር ቤት እየተጣለ መሆኑን ነው። ፕሮቴስታንቶች ኢትዮጵያ ሲገቡ ክርስትና ባልደረሰበት ቦታ ሄደው ለመሥራት እንጂ ያመነውንና የተጠመቀውን መልሶ ለመከለስና ለመደዝደዝ አልነበረም። የአነዚህ የውጭ ሃይማኖት አጥማቂዎች ጠንቀኛነት ቀደም ላሉት አባቶቻችንም ዊንቀት ሆኖ እንደነበር የምንረዳው ይህን በተመለከተ በአጋጣሚው የተናገሩትንና የገለጹትን በመመልከት ነው። ባንድ ወቅት ታላቁ አባት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ እንዲህ ብለው ነበር።

«ትውልዱ ባላወቀው መንገድ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ሲነቅፍና የባአዳን እምነትን ሲከተል ይታያል። ከቤተ ክርስቲያንም እየራቀ ሄዷል። ልጆቻችሁ በትንሽ ነገር እየተታለሉ የመንደር ሰዎችና ተልከፍካፊዎች ሁነው መቅረት የለባቸውም። ወደ ቤተክርስቲያን ይዛችኋቸው ብትመጡ የለንበት ትምህርት በመማር ሃይማኖታቸውንም ሆነ የአባቶቻቸውን ሕግና ሥርዓት ሊከተሉ ይችላሉ።»

[ትምህርተ ቴዎፍሎስ ኢትዮጵያዊ 1996 ገጽ 9]

ቀጥሎም ይህን ጉዳይ በተመለከተ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ እንዲህ ብለዋል። « ... የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በራሷ ቋንቋ የምትመሰክረው ከራሷ ማንነት ጋር የሚመሳሰል እምነት እያላት እንደሌላት በመቁጠር የገዛ ልጆቿን ከጉያዋ እየነጠቁ እየወሰዱ በሷ እንዲነሱባት የጥላቻን ትምህርት የሚያስተምሩ አያሌ ናቸው። ታዲያ ይህ ተንኮል ያልገባው የኔ አገር ልጅ እውነት የሚናገሩ አየመሰለው እንደ ጠፍ ከብት ወደ ነዱት ይሔዳል። እነሱ ግን ዓላማቸው የእግዚአብሔር መንግሥት አይደለም የላካቸውም እግዚአብሔር አይደለም። ... ይሁንና አምጣ የወለደቻቸው ልጆቿ በመጤ ሃይማኖትና ባሕል ሲበከሉ ቤተ

ምዕመናን አይሮፕላን ማረፊያ ልዩ ሲሞዚን ተከራይተው እቅፍ አበባ ይዘው አባ አባ ባርከን በመስቀልከ ክቡር እያሉ በመዝሙር ሲቀበሏቸው ሥጋ ለብሰዋልና ያን ከኢትዮጵያ ትተውት የመጡትን ሥልጣን ከዚያ ሆነው መላብ ፈለጉ አደረጉም። ስለዚህም ከብሩ ታላቅ ሆኖ በመገኘቱ ሥልጣናችንን እናስከብር ብለው ተነሡ። ድሮ ከነበራቸው በላይ ከብሩ እትዩለሌ ሆኖ ሲያገኙት ስምን በመነኮሳት ብቻ እንታጀባለን በጳጳሳት አንጂ ብለው ልባቸው ከብርን ሻተ። ስለዚህም መነኮሳትን ኤጲስ ቆጶሳት ማድረግ ፈለጉ። ሹመቱ ከዚህ በመለስ እገሌ ከዚያ በመለስ እገሌ ስማለት ዋሪ ሲያደርጉ የመነኮሳት ልብ እንደ ዮሐንስ በማኅፀን እሙ አንደ ዘለለው የጵጵስና ስም ሲጠራ የመነኮሳትም ልብ በደስታ ከላይ ወደታች ተንፈራገጠ። ምኞቱ ፍላጎቱና መፈክሩም ለካስ ምንኩስና ለጵጵስና ሆኖ ናፇል። ደራሲው እንዳለው «ከመ ያነቅሖ ለልበ ዘፋኒ ናብሊስ ፍቅርኪ [ጵጵስና] ያንቅሐኒ በሥጋ ወነፍስ» [የአታሞ ምት የዘፋኝን ልብ እንደሚያነቃቃ ፍቅርሽም በነፍሴና በሥጋዬም ያንቃኝ] ነፍሴና ሥጋዬም በፍቅረ ጵጵስና ያንቃኝ ብለው ዘለው ገቡበት።

ከዚህ ላይ ግን ሳናመሰግናቸው የማናልፋቸው አባቶች መኖራቸውን ነው። ኑ ተሸሙ ኤጲስ ቆጶሳትም ሁኑ ተብለው ሲጠሩ መልሳቸው ለመማርም ሆነ ለማስተማር እንቸገራለንና አይሆንም አይደረግም ይቆየን ብለው መልስ ሰጥተዋል። በእውኑ ምን ያህል ብፁዓን ናቸው? ይህ ሹመት ለቅሥፈት መሆኑን በመረዳትና ሰሚሾሙትም መከራ መሆኑን በመገንዘብ አይሆንም አሉ ባይሾሙም ቀሩ። በአማን አበው መነኮሳት እንዲህ ነው። ምዕመናንም ኮራንባቸው። ባለፈው በሌላው መጽሐፌ ላይ ሰላም ፍጠሩ በእንድነት ሥሩ ብዬ አቤቱታ አቅርቤ ነበር። ከዚያም ላይ እንደገለጽሁት ሰግንያ አሐዱ መጻሕፍት ያልመከሩንን አንድ ኮሳሳ ምዕመን ሊመክረን ነው ወይ አትበሉኝ ብዬም ተማጽኜም ነበር። ተማጽኖዬ አላረገም አልተቀበሉትም። አቤቱታዬ ለቅዱስ ሲኖዶስ አዲስ አበባ፥ አሜሪካ ላሉ ምዕመናንና አበው ሊቃነ ጳጳሳት ነበር። ቅዱስ ሲኖዶሱ የሰላም ልዑካን ሲልክ ከዚህ ያሉት አባቶች ሊቃነ ጳጳሳት ግን አምቢ አሻፈረን ብለው ሳያንጋጯቸው መለሷቸው። መግለጫቸውንም በብፁዕ አቡነ ዘካርያስ ተነቦልናል። ከአይሆንም መልስም በኋላ ኤጲስ ቆጶሳትን ሾሙ። ከዚህ ላይ ሰላምን የማይሹ አባቶችን ስለ ሰላም እንዴትስ ብለው ይጸልያሉ? ያስኝን አከብሮትና ልጅነት በገዛ ፈቃዴ አንስቻለሁ። ለቤተ ክርስቲያን አንድነት እጋደላለሁ። ይህም ድርሻዬና መብቴ እንጂ በስጦታ ወይንም በግዥ የማገኘውም አይደለም። ስመ ጥምቀት ሲሰጠኝ ጀምሮ በወላጆቼ አማካይነት የተቀበልሁት አደራና ሳድግም ሲረጋገጥልኝና ከዚያም ባሻገር

ቤት አደረጋችኋት። እጅግ በጣም በጣም የሚያሳዝን የሚዘገንን ሥራ እየሠራችሁ ነው። በአሜሪካ አገር ሌላ የክህነት ሥርዐ መንግሥት [ዳይናስቲ] ማቋቋማችሁ መሆኑን ዘወር ብላችሁ ዓይታችሁታልን?

አሁን እንዲህ ክልጆቹ አፍና ከራሱ ጉረሮ ሞዊቆ በሚሠጣችሁ ሙዳየ ምጽዋት ተዝናንታችሁ ምግቡን በአገልግል ለሚያቀርብላችሁ ምዕመን ምግብ አይደለምን? ባጎረሰ ዕጁን የሚነክሰው ያለ? ንወሩ ባለ፡ እንግዳ በተቀበለ፡ ከቤቱ ታስወጡታላችሁን? ከቤተ ክርስቲያኑ ማባረራችሁን ካልተገነዘበው እስከሚረዳው ድረስ ብቻ እንጂ በምትሄዱበት አይሄድም። በምትውሉበት አይውልም። በምታድሩበት አያድርም። ነገ ከነገ ወዲያ የእኒያ የደጋግ አባቶች ወግ ማዕርግ የሚደርሳችሁ ምዕመናን ቤታቸውን ሲዘጉባችሁና ዕጃቸውን ሲሰበስቡባችሁ ቤተ ዘግ ባሕታውያን ልትሆኑ ነው። ወዳችሁ ሳይሆን ተገዳችሁ መሆኑ ነው። የበጎ ፈቃደኝነት ተግባራችሁን ተመልክተነዋልና ነው። አሁን ግን በግድ ይሆናል። የግድ የሚሆንበት ቀን ሰዓት አለ አይደል? ጊዜው ሲደርስ በውጤቱ ትረካላችሁ። በምዕመናን ላይ የእናት ቤተ ክርስቲያኑን በር እንደዘጋችሁበት መልሶ የከፈተላችሁን በር ይዘጋል። ያለ ምዕመናን መሾም መሾሟም አይኖርም አይደረግም። ከላይ ሆኖ የሚመለከት እግዚአብሔር ፍርዱን እንደማያርቀው እንማጸናለን።

አቤቱ ጌታ ሆይ በደላችንን ዕይ ተመልከት ከዚህን ጊዜ ጀምሮ ጸሎታችን ነው። እኛ ዴንጤው መጤው ልጆቻችንን ቀማን እያልን በምንሮህበት ሰዓት ይባሱኑ እናንተ በቤተ ክርስቲያናችን ስም አባት መሰላችሁ ቀንታዊቷንና ቀዳሚቷን ቤተ ክርስቲያናችንን ዘጋችሁብን። አዋረዳችሁን አሳፈራችሁን አፋችንን አዘጋችሁ። ኢትዮጵያ እኮ ለሰማንያ አራት ዓመት ያለ ጳጳስ መኖሯን ታውቁ የለምን? ጵጵስና በግብፃውያን ዕጅ በነበረበት ሰዓት ተማፅነን ተሰማምጠን ሰምነን እግዚኦ ብለን እንዳሳገኘነው ያህል ዛሬ በየጎራው በየመንደሩ እንደ ዲቁና ክህነት ጵጵስናን በገፍ ማደላችሁ መንፈሳዊ ምርት ማበርከታችሁ ነውን? ጵጵስና በዚህን ያህል በመቶ አሳደግን ብላችሁ ስምዕመናን ዘገባ ለማቅረብ ነውን? እንደኔ ከሆነ ራሳችሁን በራሳችሁ ዝቅ አደረጋችሁ። የጵጵስናን ክብር በእግሩ ሳይሆን በንብርክኩ አስሄዳችሁት።

የምንጽናናው አናንተ ነገ ከነገ ወዲያ እንደ ጥላ ታልፋላችሁ። «ሰብእሰ ከንቶ ይመስል ወመዋዕሊሁኒ ከመ ጽላሎት

በትምህርት ያገኘሁትና ግዴታ ቃል ኪዳን የገባሁበት አደራ ነው። እስከ ሞት ድረስ ለቤተ ክርስቲያኔ እሚገታሰሁ እከራከራለሁ እውነቱን እመሰክራለሁ። እንዲህ እባላለሁ እኔ አባ እገሌ ይጠሉኛል የሚለው ዊንቀትና ጥበት የለብኝም አይኖረኝም። ሰራሴም አይደል ለማንም አይደል ስለ እውነትና ስለ ቤተክርስቲያናችን ብቻ ነው። ደሞዝተኛም ተጠሪም ተወካይም አይደለሁም። ምንም ዓይነት የጥቅም ንክኪ የለኝም። ስለዚህ ነፃ ኃላብ ነፃ ሥራ ነፃ አገልግሎት ነገር ግን ስለ ቤተ ክርስቲያኔ ፍቅሪ እንጂ!

ወደ ቅዱስ ሲኖዶስ ብፁዓን አባቶች ልመለስ አደራዬንና ተማጽኖዬን ልቀጥል። አባቶች ሆይ! መስቀላችሁን እንሥ። «ግዕ መንፈስ ርኩስ» [መንፈስ ርኩስ ውጣ] ብላችሁ በአራቱም ማዕዘናት የአቡነ ጴጥሮስን ቃሰ ምዕዳን አሰሙ። መሬቷንም ባርኩ። ሕዝቡንም አጽናኑ። የበግ ሰምድ ለብሰው በሕዝቡ መካከል ያሉትን ተኩላዎች ለሕዝበ ክርስቲያኑ አመልክቱ አስጠንቅቁ። እነሱንም ከአካባቢው አርቁ። ይህ አደራ፡ ሐዋርያዊ ሥልጣንና ኃላፊነት ከአደረጋችሁት አክሊለ ሦክና ከያዛችሁት መስቀለ ኢየሱስ ጋር አብሮ ለሰማዕትነት አክሊላችሁ መለያና መታወቂያ የተሠጣችሁ ልዩ ዓርማችሁ ነው። ይህም ሥልጣነ ሐዋርያት ለሕመማን መፈወሻ፡ ለሙታን ማሰነሻ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ነው። ወደ ዓለሙ ሰትላኩ «ሑሩ ወመሐሩ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ዓለም።» [ሂዱ አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ] በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስም ስም አጥምቋቸው [ማቴ. 28:18-20] ስትባሉ ከኃይለ ሥልጣን ጋር እንጂ ባዶ ዕጃችሁን አልነበረም አሁንም አይደለም። መሆንም አይገባውም።

ስለዚህም ሰማዕትነት ለብፁዕ አቡነ ጴጥሮስና ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ልዩ ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ቢሆንም ከናንተም ዘንድ ያለና የሚኖር ነው። በተግባርም እንድታሳዩት የሚጠበቅ ነው። የሊቃነ ጳጳሳቱ ሀገረ ስብከቶች አሁንኑ ከመጤው ሃይማኖት ይጽዱ። በሃይማኖት ስም የተጀመረው ወረራ ተንፍቆ ተንፍቆ የት ላይ ነው ያለው? ይህን ለመመልከት መነጽርም አያሻው። በእውኑ ቤተ መንግሥት ገብቶ እየተንቦራቦረ አይደለምን? እንዴት ከዚያ ደረሰ? የምሥራች ድምፅ ራዲዮ ወንጌል በኢትዮጵያ ተሠበከ ሲሉ የጀመሩት ውሸት እንደሚታወቀው ውሸት ሲያረጅ እውነት ሆነና በቅድሚያ እግዚአብሔር የለም የሚል ሠይጣናዊ ድምፅ ተሰማ። ኢትዮጵያ ያላትና የኖራትን አንደኛና ብቸኛ አምላኳን የለም ሲሉ ተነሡ። እውነቱ ግን አምላኳ አለ እነሱ ግን የሉም። የምሥራቹም ድምፅ መጣና ሄደ። ያለችውና የቀረችው ትንቢት ተነግሮላት ሱባዔ ተቆጥሮላት በራሱ በባለቤቱ ፈቃደ ብቻ የተሠጠችው እውነተኛዋና

የኃልፍ።» [የሰው ልጅ ሕይወቱ ከንቱ ናት እንደ ጥላ ታልፋለችና!] መዝ. 102:7 ሲል ዳዊት በመዝሙሩ ተናግሯል። ቢያንስ ቢያንስ ከሦስት መቶ ሰድሳ አምስት ጊዜ በላይ ደግማችሁታል። ትኩረት ግን አልተሰጠውም እንጂ! ይሁንና የገና ገና ሞት እንኳ ቢመጣ የዝማሬው ቅላጼ «ዓላየንም በሉ አልሰማንም በሉ። ሞቱ ሲፈልገን ሲሻን መጣል አሉ።» የሚደመጥና የሚመረጥ እንደሁ መረዳቱ አይፀናንም። አባቶቼ እናንተም በድምፀ በገናው ተማልላችሁ እንጂ! «ኖሮ ኖሮ ከሞት፥ ዞሮ ዞሮ ከቤት አይቀርም።» የአበው ምሳሌ ነው።

ቤተ ክርስቲያናችን ግን ለዘለዓለም ትኖራለች። የሞቱላትና ያሰገደኋትም አንድ ላይ በሰማይ ቤት ትወያዩበታላችሁ። አንዳንድ ፌዘኞች እንደሚሉት አቡነ ጴጥሮስ በሞኝነትም ድንጋይ ሆነው ቀሩ። እንደ ብልጠቹ ወደ አሜሪካ አልወጡ ሁሉ እንደ ልቡ ወደሚኖርበት አገር ሳይኳቸው ይቀራል? የአባቶቻችንን ክብር እጅግ በጣም ዝቅ አሰደረጋችሁብን። ጵጵሰናን እንደ ሰንበት መክፈለት ለሁሉም ለአያንዳንዱ ስታድሉ መታየታችሁ ለኛ ለኛ መቅሠፍት ለእናንተ ደግሞ ቅዱስነት ከሆነ ጎረቤት ነንና ያጸዳደቁን ፈሊጥ አያየን ነው።

ለአሜሪካ ነፍሰ መቼ እኔ አነስኳት ወይ አያዛልቅም። እንደ ወጡ መቅረትም አብሮ ካልታሰበ በቁመና መሞትን ያስከትላል። ይሁን ይደረግ ጊዜ ይፍታው የማይሉት ጉዳይ ነው። ያልታሰበበት ምክር የተሰየው ታሳብ ነፍስ እንደተለየው ሥጋ ነው። መቼም በሌላ ቢደረግ እንጂ በእናንተማ እንዴት ሆኖ? ሹመቱን ተቀበሉ የተባሉት ጥቂት አባቶች ደግሞ የለም አይሆንም ገና ነን ለማስተማር እንቅፋት ይሆንብናል አሉት። አም ከእንቅፋትም ዛዝላ ይሆንባቸዋል። ጵጵሰና ከመሾም ይልቅ በስደት ጊዜ እንደ ተደረገው እንደ ተፈፀመው «እምከዊነ ካህን ይኄይስ ከዊነ ኖላዊ» [ካህን ከመሆን ጥሻ ጠባቂ መሆን ይሻላል።] እንዳለው ባለ ቅኔ የስደት ሥራ መማር ዝቅ ያለ ሥራ መሥራት ሌሎችን መርዳት እንጂ ተረጂ መሆን የበደል በደል ነው። በሩሲያ እግዚአብሔር የለሹ መንግሥት ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ስትዘጋባቸው ካህናቱ ጳጳሳቱ ሳይቀር የክብር ልብሳቸውን አውልቀው አስቀምጠው በየፋብሪካው ነበር ለሥራ የተሠማሩት። አስከ የኃልፍ መዓቱ ለእግዚአብሔር ነውና ነው።

የኛዎቹ አባቶች ግን ስደት ላይ ሳይሆን ያሉት ድሮ ከሚኖሩበት በላይ ፍትፍቱ በአገልግል ገንዘቡ በአንቦልክ እልልታው ከታቦቱ በላይ አክብሮቱ ልዩ ሆነ። በየደረሱበት ከተማ ሁሉ

ለመጉዳት መነሣታቸውን ስማስገንዘብ ነው። ይህም የስደተኛው ሲኖዶስ በሚል ሥያሜ የሚንቀሳቀሰው ከዋናው ቅዱስ ሲኖዶስ ብቸኛ የቤተ ክርስቲያናችን ተጠሪ ጋር ሳላበሩትና ለተለዩት ክፍሎች በድጋፍ ሰሞነት መታየታቸው የማንነታቸውን ገጽታ በሚገባ ያሳያል። በቤተ ክርስቲያናችን ላይ እነዚህ ተቃዋሚዎች ወይንም ፕሮቴስታንቶች እንደዚህ ዘመን በርትተው የተነሡበት ጊዜ ያለመኖሩን መገንዘብ የግድ ይሆናል። አበው እንደሚሉት «የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው» ብለው መነሣታቸው መሆኑ ነው።

ታዲያ ይህ ሁሉ ግፍና በደል ሲፈፀም ዝምታው ምንድን ነው? ፍርሃትን? ሥቃይን? ሞትን? በመፍራት ነውን? ብፁዓን አባቶች ሆይ! እስከ መቼ በሁለት አግሮቻችን እናነክሳለን? በጎቻችሁን ጠብቁ። ሥጋቸውን በልቶ ሌጦዎቻቸውን ፈቅፍቆ የራሱን ማንነት ለመጻፍ ሥራ ከጀመረ ዘመናት ተቆጥረዋል። በተለይም አሁን በገንዘቡ ኃይል ምርኮውን ካረጋገጠ በኋላ ለቤተ መቅደሱ ምዝበራ ዘመቻው ታውጇል። ጦርነቱ ተጀምሯል። ስለዚህ የኢትዮጵያዊነት ለዛና ላህይ ወርሶ ተጠራርጎ ከመጥፋቱ በፊት አሁንም በድጋሚ በጎቻችሁን ጠብቁ። ከተሞቻችሁን ከርኩሳን መናፍስት አጽዱ። ትምሕርተ ጎቡዓቱም ይጸለይ። ጠላትም «መኑ ውእቱ ዝንቱ ዘአምሥልጣንየ ሰብአ ለቢሶ ሊተ ሞዐኒ።» [ሠይጣንም እሱ ግን ነው ሥጋ ለብሶ ከሥልጣኔ የአሸነፈኝ] ይበል። [ከትምህርተ ጎቡዓት የተወሰደ።]

ብፁዓን አባቶች ሆይ! ቅዱስ ሲኖዶስ ከዓመት ሁለት ጊዜ ጉባዔ ያደርጋል። ያወጣቸውን ውሳኔዎችን ስንመለከት ግን ከታላቁ ችግር ተራራ ዘንድ ደርሶና ተወያይቶ ችግሩን እንኳን አውቆና ተገንዝቦ አንዲጸለይበት ሲያደርግ ዓላየንም አልሰማንም አላነበብንም። ያነበብነው በአራተኛው ክፍለ ዘመን ይከራከሩባቸው ከነበሩት አርዕስተ ጉዳዮች ላይ አንድ ያስተላለፈውን ውሳኔ ነው። ይህም ማለት ደግሞ ሲኖዶሱ ያለ ውሣኔ ይነሣል ማለት ያስመሆኑንም ግንዛቤ ይወሰድልን።

አዲስ አበባ ከተማና የሊቃነ ጳጳሳቱ አኀጉረ ስብከት የመንበር ከተሞች ጤንነት እንዴት ነው? ምን ይመስላል? ወጣቱ ጊዜውን የሚያሳልፈው የት ነው? ምንስ ይሠራል? ይህ ትውልድ የነገይቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተረካቢ መሆኑ የሚዘነጋ ጉዳይ አይደለምና ነው። ሌላው ቀርቶ በየሰንበት ትምህርት ቤቶች ያሉት ወጣቶች መካከል በገንዘብ፥ በኮካ ኮላ አየተማረኩ አይደለምን? ሙዚቃው፥ መዝሙሩ፥ ፊልሙ

ብቸኛዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ናት። የዚች ሃይማኖት ጠባቂና ተንከባካቢ ደግሞ አንድ አምላኳ ብቻ ነው።

ስለሆነም በተቀዳሚ ከታሪካችን እንደምንረዳው በቅድመ ዓድዋና በድኅረ ዓድዋ ያጡትን ድል መልሶ ለማግኘት ኢትዮጵያን ደጋግመው እንደወረሩ ሁሉ የባዕዳንም ሃይማኖት ለብዙ ጊዜ ሞክረው ያልተሰካላቸውን ድል ለመቀዳጀት ቁናት አድርገው ኢትዮጵያውያን የባዕዳንን መልክ ሲያዩ እንደማይወዱና ደማቸውም እንደሚደፈርስ አረጋግጠው እንደ መፍትሔ አድርገው የወሰዱትና በተግባርም ሲያደርጉት የምናየው ራሳቸውን ኢትዮጵያውያንን በነሱ እስተሳሰብና አመለካከት ቀርጸ፡ አስመስሎ፡ አሠልጥኖ፡ ዶላርና መጽሐፍ ቅዱስ አስይዞ መላክ ነው። እነሱም ደሞዝ የሚከፈልበት ሥራ ነውና ያላንኳኩት የኢትዮጵያዊ በር፡ ያልተንቀሳቀሱበት መንደር ጠርሶ የለም። ከዚያም አልፎ ተርፎ ልጁን ያልተቀማ ኢትዮጵያዊም አልተገኘም። በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ልጁን ብቻ ሳይሆንም በጠቅላላው ማንነቱንም አጥቷል። «ውሀ ሲመስድ እያሳሰቀ ነው» እንዲሉ ሆነና!

ሚሲዮንያኑ ኢትዮጵያውያኑን እስቲ ሳታዩን በወሬ ብቻ እትጥሉን ኑና ጸሎት ቤታችንን ጎብኙት ብለው አንድ ኢትዮጵያዊ አረጋዊ ይጋብዛሉ። የተጋበዙትም ሰው ትዕይንት ልዩ ብለው ይሄዳሉ። ተጋባዥ ሰው በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ቤተ ጸሎት ወይንስ ቤተ ምሥያጥ [የመነገሻ ቤት] ሲሄዱ በስኳር የነደደ ኬክ፡ ቡና በወተት፡ ከሚያሸበርቅ ሳሎን፡ ሲቀመጡበት ከምቾቱ ብዛት እንቅልፍ ላይ ከሚጥል ሦፋ ላይ አስቀምጠው፡ የዕለት ችግራቸውን ጠያይቀው ካዳመጡ በኋላ ሲወጡ እንደ ኳስ በብር ያበጠ ኤንቨሎፕ/ፖስታ በመንፈስ ቅዱስ ታዝዘን ነው ለዕለት ችግርዎ ያድርጓት ተብሎ አምስት መቶ ብር ይሠጡና አዛውንቱ ይሸኛሉ። ያን ገንዘብ ወስደው ለዘጠኝ ልጆችና ለሚስት አዲስ ልብስ ገዝተው ደስታ በደስታ ይሆናሉ። ከየት አመጣኸው ይህን ሁሉ ገንዘብ ሲባሉ አባ ወራው በሳቸው አንጋገር «እኔ ጠረ ማርያም የምንላቸው መፈስ ቅዱስ የሚነግራቸው ሰዎች ናቸዋ! እንዲህ ያንበሸበሹኝ» ሲሉ መልሳቸውን ይሠጣሉ። በሚቀጥለው እሁድ እራሳቸው አሥራ አንድ ሆነው ጎረቤቶቻቸውን አስከትለው በጥሩንባ የታወጀ ሠራዊት አስመስለው በሳምንቱ ከጸሎት ቤታቸው ከተፍ አሉላቸው። «ብር ካለ በሰማይ መንገድ አለ።» ሆነና ሃይማኖት በገንዘብ መሸጥ መለወጥ ጀመረች። ገበያዋም ደራች። ከዚያም ማንነቱን እንዲረሳና

ተደግምሮበት ቤተ ክርስቲያኗን የጠብና የክርክር መድረክ አላደረጓትም? ይህ ሁሉ የምን ምልክት ነው? የፀሐይ ጥልቀት የሚታወቀው የእካባቢው ደመና ደም መስረብና መቅላት ሲጀምር ነው። የራስ ጥላም ከቁመት በልጦና ርቆ ሲሄድ አይደለምን?

ዛሬ ለእግዚአብሔር ምሥጋና ይግባው በቁጥር ከዓርባ በላይ የምትሆኑ ሲቃን ጻጻሳት ባላችሁባት ኢትዮጵያ እንዴት በጎች በቀበሮዎች ይበሉ? እንዴት ታቦተ ጽዮን ትንቋሸሽ? እንዴት መላዲተ እምላክ፡ እመ ብርሃን፡ ቤዛዊተ ዓለም፡ የዓለም እማላጅ ትናት? እንዴትስ ስጋና ክብሯ በዳጎን እግር ሥር ይውደቅ? ይህ ሁሉ በደል፡ ይህ ሁሉ ውርደት፡ ይህ ሁሉ ጽርፈት ሲዘንብ እንዴት አስቻላችሁ? እንዴትስ ትዕግሥቱን አደላችሁ? እዎ! «ቁጣውን በትዕግሥት መዓቱን በምሕረት» ብላ ቤተ ክርስቲያኗ ታስተምራለች ትጸልያለች። ይሁን እንጂ ባሕታዊው ስለ ምርኩዛቸው ሲናገሩ ላዩ መስቀል፡ ግርጌው አንካሴ መሆኑን የተመለከተ በዋያቂው ምነው አባቴ ይህን መሳይ መሣሪያ ያዙ ቢላቸው የሠጡት መልስ የመስቀሉንና የሾለውን ክፍል በጣቶቻቸው እያመለከቱ «ለዘመጽእ በሰላም በዝ እባርኮ፡ ወለዘመጽአ በሃኬት በዝ እዘተርኮ» አሉት ይባላል።

ዛሬ የክርስቲያኑ ቤት ሁሉ አፍስሶ፡ ደጁ ሁሉ በሞቃ ተለውሶ፡ ግቢው ተክሉ አጥሩ ሁሉ በፈረንጅ ሠራሽ መብረቅ ፈራርሶ፡ ሕዝበ ክርስቲያኑ የደም ዕንባ አልቅሶ በሚሮህበት ሰዓት እንዴት አልተመለከታችሁትም? እዎን ሥራ እንደሚበዛባችሁ የታወቀ ነው። የካህናቱ ያለመስማማት፡ የዲያቆናቱ እልከኝነት፡ የምዕመናኑ ግራ መጋባት፡ የበላይና የበታች አስተዳደራዊ መዋቅሩ መዛባት፡ ሁሉም በየበኩሉ ሹመት ሹመት ሹመቴን ተነጠቅሁኝ ይመለስልኝ እንደገና ይሠጠኝ፡ ይህ ይደረግልኝ፡ ደሞዝ ይጨመርልኝ የሚሉት የማመልክቻ ደብዳቤዎች ቢጠረዙ ከሰማንያ አሐዱ መዳሕፍት ሰማኒያ አንድ ሺህ ጊዜ ይበልጣሉ። ከብዛታቸውም የተነሣ ከመዝገብ ቤት ሞልተው ተርፈው ወደ መቅደስ ገብተው የሚቀመጡበትን ጊዜና ሰዓት እየተጠባበቁ ነው። እነዚህን በማስተናገድ እንኳን እህል ውሀ የምትቀምሱበት፡ እቡነ ዘበሰማያት እንኳን የምትደግመብት ሰዓት እንደሌላችሁ በሁሉም አቅጣጫ የምናየው፡ የምንሰማውና የምናነበውም ነው።

ይህ መሳዩ ደግሞ ሆን ተብሎ ያላችሁን ጊዜና አስተሳሰብ ጠርሶ ለመሚጠጥና ለማባከን መሆኑን አውቃችሁት ይሆን? ጥናትስ

ኢየሱስን ብቻ እንዲከተል ይሰበክለት ጀመር። እንዲሁም ኢትዮጵያዊነቱን እንዲጠላ እንዲንቅ አደረጉት።

ይህን ጊዜያዊ ጥረታቸውን ቀጥለው በየከተማው እደባባዮች የቀዌን ፈትል ጋቢና ከተልባ እግር የተሠራ ካባ ለብሰው ንፁሕ ዓየር በሁለቱም አፍንጮቻቸውና በመሳብ ላይ ይገኛሉ። አሁን የቀረቻቸው የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ናት። በሷም ላይ ቀደም ሲል ያጡትን ድል እንደገና ለመድገም አሁን የማይፈነቅሉት ድንጋይ የማይናገሩት ቃላባይ የለም። ዘመቻው ቀጥሏል። ዓላማቸውም የጥላቻቸው ግለት ያተኮረበቱን የማንነቱ መታወቂያና መለያ የሆነውን ታቦት ቤተ መቅደስ ገብተው፥ መንበር ገልብጠው ለመስበር ነው። ያ ደግሞ የኢትዮጵያዊነትን ቅስምና ማንነት መሰባበርና መደምሰስ ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው።

ከዚህ ላይ የሆነውን ላስታውስ። በመጀመሪያው እትሜ ከላይ የሠፈረውን ሁከት ያደርጋሉ ብዬ ጽፌ ነበር። የሠይጣን ጆሮ ይደፈን ብዬ ብናገረው ኖሮ አይደርስም ብያለሁ። ይሁንና ባለፈው ጊዜ በ1998 ዓ. ም. የጥምቀት በዓል ሲከበር እነሱ አይደሉም ለማሰኘት በሐኬት የተጠበቡ ናቸውና በወቅቱ ከመንግሥት ጋር ቅራኔ የገጠመውን የፖለቲካ ፓርቲ አርማ ቅስር ጣት እያሳዩ በታቦታቱ ላይ ድንጋይ ወረወሩ። ሰው በዓይኑ የሚያየው ያን የጣት ምልክት በመሆኑ ያውም የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስቲያን በታቦት ላይ ድንጋይ ሊወረውር ይቅርና ዓይኑን አሽንድሮ እንኳ ፈጽሞ አይመለከትም። ሃይማኖቱን ቤተክርስቲያኑን እንኳን ከፖለቲካ ድርጅት ይቅርና ከራሱ አስበልጦ ሃይማኖቱን ይወዳል ያከብራል ነፍሱን አሳልፎ ይሰጣል።

ይህን ለማለት ያስደፈረኝ በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ካህናት መስለውና አክለው «ተሐድሶ» በሚል ስም ተቋቁመው አዋቂና አስተማሪ የሚባሉትን ብዙዓን አባቶችን የእነሱ ተቃዋሚ መስለው ካይዋቸው የራሳቸውን ስም አቡነ ዕገሌ ተሐድሶ ናቸው በማሰኘት በሚጠብቁት ምዕመናን እንዲጠሉና ግርግር እንዲፈጠርባቸው በማድረግ ላይ መሆናቸው ተደርሶበታል። ለዚህ ማረጋገጫ የሚሆነው አሁን በሰሜን አሜሪካ ለተደረገው ሕገ ወጥ ድርጊት ተባባሪ ሆነው በየቦታው ድጋፋቸውን ሲገልጡ መታየታቸውን ስንሰማ ነው ጉዳዩን አጉልቶ ያረጋገጠልን። እጅግ ያሳዝናል። የዕጅ ማስገቢያ ቀዳዳ ባገኙበት ሁሉ እየገቡ ቤተ ክርስቲያኗን ለማጥፋት ካላቸው ፍላጎት የተነሣ በመሥራት ላይ ናቸው። በዚህ አጋጣሚ ተሐድሶ በሚል ስምም ቤተ ክርስቲያኗን

የተጣላውን ታስታርቃላችሁ። እርቅ የሰላም በር እንደሆነችም በሚገባ ታውቃታላችሁ። ሰባት ጊዜ ሰባት ብቻ እንዳልሆነም አስተምራችሁናል። ሰባት ጊዜ ሰባ እንጂ! «ሰላምየ እኁድግ ለክሙ ወሰላመ አቡየ እውሀብክሙ» [ሰላሜን እተውላችኋለሁ የአባቴን ሰላም እሰጣችኋለሁ] [ዮሐ. 14:27] መመሪያችሁ ይህ አይደለምን?

ነገር ግን የዚች የሰላሟ በር ከመጥበቧ የተነሣ ይሆናል ሁለትና ሦስት ሆናችሁ ነን ለነን ለመሄድ እንደተጣበባችሁ እናያለን። ስለዚህ አንዱ ቀድሞ፥ ሌላው ተከትሎ መሄድም ያለና የነበረ አባታዊ ጉዞ ነውና በዚያ ዘዴ ቢቀጠል ሁላችሁም ከሰላሟ አደባባይ በደረሳችሁና ዕረፍተ ሥጋም ሆነ ዕረፍተ ነፍስም በተገኘ በነበር። አሁንኮ ያሏችሁ ሁለት ዕጆች ናቸው። ኃይሉና ጉልበቱ ያለው ከሥልጣነ ክህነቱ ላይ እንጂ! ሁለት እግሮች ኖሯችሁ አንዱን ኢትዮጵያ ሌላውን አፍሪቃና አሜሪካ እንዲሁም አውሮጳና ኤሲያ ብታደርጉት እንዴት ደስ ባለን በነበር። ነገር ግን ያንዱ አባት አካል የሌላውም ነውና በመንፈስ ብቻ ተባበሩልን እንጂ እንኳን ድምፃችሁን እየሰማን መልካችሁንም እያየንና እየተመለከትን ቡራኬአችሁን ከምንቀበልበት ዘመንና እውቀት ላይ ነን።

ይህም ሁሉ እንኳን ሳይደረግ የምዕመናኑ ሃይማኖታዊ ዓይን ከናንተ ርምጃ፥ ከናንተ ጉዞ ተለይቶ አያውቅም። በፀሐይ ብርሃን እጠት ሲጋረድ፥ በዓይነ ኅሊና ይከተላችኋል። በዕለት ጸሎቱም ስማችሁን በማጎሳት ያስታኩታል። ሲኑጋም ሕይወታቸውን ጠብቅ፥ ጸሎታቸውን፥ ምልጃቸውን ከኛ አታርቅ ይላል። የአባቶች ጸሎት፥ የምዕመናኑን ሕይወት ያጣፍጣልና ነው። ታዲያ እባካችሁ አደራ በሰማይ እደራ በምድር ጨውነታችሁ አይለወጥብን። ጣዕሙን አይቀይርብን። እናንተም በጸሎታችሁ የምዕመናኑን ዕገባ አብሰ፥ ልመናቸውንና ጸሎታቸውን ከዳር አድርስ ብላችሁ አሳርጉልን።

እንደሚታወቀውና እንደምንረዳው ሁሉ በመካከላችን ያለው ሃይማኖታዊ የዝምድና ኃረግ አባትና ልጅ ነው። ታዲያ ይህ ከሆነ ልጅ አባቱን ባይመክር እየጠየቀ ይመራመር ያለና የሚኖር ነውና! አንዳንድ ኃሳብ ላቀርብ እወዳለሁ። በዚያውም እንደ አቤቱታም ይቆጠርልኝ። ነገር ግን ከሰማንያ አንዱ ሺህ የማመልከቻ ደብዳቤ ጋር አይጠረዝብኝ።

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እጅግ በጣም ቁጥራቸው የበዙ ምሁራን ያሏት፥ ዕድሚያቸውን በትምህርት፥ በምርምርና በማስተማር ያገባደዱና የፈፀሙ ሊቃውንት

ተደርጎበት ይሆን? አይመስልም አልተደረገም። ከሁኔታው መረዳት ይቻላልና ነው። የቤተ ክርስቲያኗ ተቀዳሚ ተግባር እንዲያው የቱ ነው? አብያተ ክርስቲያናት ማሳነጽ? እሱ እንዳልሆነ ደግሞ አዲስ አበባ ከተቆረቆረች በአንድ መቶ ዓመት ውስጥ አንኳን የታነፁት አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር መቶና ሁለት መቶ ሲሆን ቀርቶ ከሃምሳና ከሰማንያ የሚበልጡ አይመስሉኝም። ነገር ግን በእነዚሁ ባለፉት አሥራ ሦስት ዓመታት ውስጥ በዓይን የሚታዩ ከሁለት መቶ በላይ መሥጊዶች በከተማው ተሠርተዋል። እንደዚሁ ለማነጻጸር ያህል ነው።

ታዲያ የቱ ነው ቅድሚያ ያለው? መምህራንን ማሠልጠንና መላክ? አዎ ሁለት ሦስት ኮሌጆችና እንዲሁም ሌሎች የካህናት ማሠልጠኛዎችና ማዘጋጃዎች በርግጥ አሉ እንዲያውም የተዘጉት ተከፍተዋል አዳዲሶችም ተጨማምረዋል። አድባራትና ገዳማት ወደ ጥንተ ሥራቸው ወደ ትምህርት ቤትነት አያመሩ እንደሆነም እናያለን እንሰማለን። ይሁን እንጂ ከማነሳቸው በስተቀርና እኔንም በሚገባ አዘጋጅቶ ኢትዮጵያውያን ወዳሉበት ዓለም ሁሉ መላኩ ላይ ገና አልተሰፋፋም እንጂ ተጀምሯል። በብዛት ቢሆን ብዙ ዓላማ ያጠምዱ ነበር። ለዚህ ደግሞ የቤተ ክርስቲያኒቱ አስተዳድር ገና ባንድ ገመድ አልታሠረም ይህም የሰበሰቡትን ወይንም የለቀሙትን እንጨት ያለማሠሪያ ማጓጓዙ ብልሃት ያሲያም ፈሊጥ አይደለምና ግዴለሽነት አለበት ቢባል ችግሩን አይገልጸው ይሆን? አዎ አይገልጸውም። ሌላ ለየትና ለወጥ ያለ ምክንያት አለው። ያ መታወቅና መድኃኒት ሊፈለግለት ይገባል። ነገር ግን ለመፍትሔው ከመሄድም በፊት የችግሩን ራስና እግር መለየት የሚያስፈልግ ይመስላል። ይሁን እንጂ ለመፍትሔው ብዙም ትኩረት ሲደረግ አይታይም።

የሲኖዶሱ አባላት ዋና ችግር፥ ታዲያ ምን ይሆን? በአሁኑ ሰዓት ሲኖዶሱ ጳጳሳትን ከመሾምና ከመላክ በላይ የሚላኩበትን ሀገረ ስብከትና ምዕመናንን አቀናጅቶ ሲሠራ አይታይም። አዎ! ከምናውቀው ስንነሣ የአንድነቱ ድልድይ ከተሠበረ ቆል አደር ብሏል። አባትን በጨለማ መስቀል ስመው ያስረከቡም ነበሩ። ታዲያ መምህርን ደቀ መዝሙሩ አሳልፎ የሚሠጥበት ጉባዔ አሁንስ ቢሆን ያን የሚያስቀር ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶሱ ደንግጎ ይሆን? ያ ካልሆነ ትልቁ ሥራ ሕገ ቤተክርስቲያን የምትጠበቅበቱ ዋንኛ ተግባር ተዘንግቷል ማለት ነው። ይህ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ተደንግጎ ካልተጠበቀ የነፍስ መጠፋፋቱ ጉዳይ ከዓይን ቁራኛ ሊድንና ነፃ ሆኖ ሊንቀሳቀስ አይችልም። የቤተ ክርስቲያኗ ታሪክ

አባቶችና ወንድሞች አሏት። ነገር ግን ካሏት መጻሕፍት ብዛትና ሕያውት፥ በሕግና በሥርዓት የተቋቋመ ሕጋዊ የጥናትና የምርምር ጉባዔ የላትም። ይህን ስል ስለ ቤተ ክርስቲያኗ ታሪክና ይዘታ የታተሙትን ላልዘነጋ ነው። አነሰኝ ይጨመርልኝ የልጅ ጥያቄ ነው። ይሁን እንጂ! የሚፈለገውን ያህል በጥራትና በብቃት አዳዲስ ትምህርቶችን አዘጋጅቶ ለማስተማር ጥረት ሲደረግ አናይም። እንዲያውም ያሉንን የብራና መጻሕፍት አይጥ ፈጀብን፥ ርዳታ አድርጉልን የሚሉት እሮሮዎች ላያቸውና ለተመለከታቸው የእግር እሳት ናቸው። በአውሮጳና በአሜሪካ ያሉንን የብራና መጻሕፍት ለመመርመርና ለማሰባሰብ ቀርቶ፥ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን እንኳን በሚገባ መመርመርና መጠበቅ አልተቻለም። እኒህን ምሁራን አሰባስቦ፥ በጀት መድቦ፥ ማስጠናትና ማስመርመር እጅግ በጣም አስቸኳይ የቤተ ክርስቲያኗ አጣዳፊ ጉዳይ ነው። ትልቁና ዋናው የቤተ ክርስቲያኗ ተግባር እንደኔ ይህ መሆን ይገባዋል አላለሁ። እኒያ መጻሕፍት ወደ ተለያዩ ዓለም ዓቀፍ ቋንቋዎች ቢተረጎሙ በዓለም ላይ ያለው በሚሊዮን የሚቆጠረው ጠይም ሕዝብ እንዴት በተማረበት ማንነቱን ባወቀበትና ባረጋገጠበትም በነበር። የቤተ ክርስቲያኒቱም አባል በሆነ በነበር።

ከዚያም ቀጥሎ የማወሳው እንዳጋጣሚ ሆኖ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም ወጣቱ የአገሩንና የቤተ ክርስቲያኑን ታሪክ ፈጽሞ አያውቅ እሱም አይጠይቅ። ቢጠይቅም የት አለ ልሂቅ? ብቻ ሆነና ሁሉም ደቂቅ። ወጣቱም በበኩሉ ከሁሉ ይልቅ፥ አገሩን ሲንቅ፥ የሌላውን ሲያደንቅ ነው የሚታየው። በወጣቱም አይፈረድ ሥርዓተ ትምህርቱም አጋድሞ የሚያርድ፥ ማንነቱን የሚያዋርድ፥ ፍፁም ራቁት የሚያስሄድ፥ ጨርሶ የሚያሳብድ ስለሆነበት ነው። የራሱን የግዕዝን ቋንቋና ፊደል አስወጥተው የአውሮጳውያንን ቋንቋ ሲያስጠኑት ወጣቱ ትውልድስ ምን ያድርግ? ግን ሆን ተብሎ በሥርዓተ ትምህርቱ ታግቶበት እንደ አሮጌ ልብስ አውጥተው ጥለውበት ተቀበዝባዥ ሆኖ ይታያል። የግዕዝ ቋንቋ ቢያውቅ ይሆን ነበር ሊቅ፥ የአገሩን ሀብትና ንብረት የእሱንም ማንነት ለይቶ ያውቅ ነበር። አንድና ሁለት ዓመት ግዕዝ ቢማር በአውሮጳ በአፍሪቃ በአሜሪካና በካረቢያን ደሴቶችና በላቲን አሜሪካ ለሚገኙት ወገኖቻችን መምህር በሆነ በነበር። ግዕዝ ከቤተ መቅደስኳን ወጥቶ መጠጊያ አጥቶ ከደጀሰላም ቀባሪ እንዳጣ አስከሬን ወድቆ ይገኛል።

የቅኔ የዜማ የአቋቋምና የመጻሕፍት በጠቅላላው የአብነት ት/ቤቶች ለመምህራኑ ደሞዝ ለተማሪዎቹ ምግብና ልብስ

ረኽም ነው። የጥንካሬዋን ያህልም ደካማ ጎኖች እንዳሏትም እንረዳለን። ይህ ደግሞ ስማን እንደሚጠቅመው ፈጽሞ ያልታሰበበትና ያልተጸለየበት ጉዳይ መሆኑን መረዳቱ አይከብድም። ፍቅር የሌለበት ሥራ ያውም ማስተማር እንዴት ተዘርቶ ሊበቅል ይችላል? ይህን ችግር የሚፈታ ኃይል የለምን? የችግሩን ዓይነት ስይቶና አውቆ ያበጠውን መብጣት፥ የቆሰለውን መቀባት እንዴት አቃተ?

ብፁዓን አባቶች ሆይ! «በምድር ያሠራችሁት በሰማይ የታሠረ ይሆናል። በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናልን» ያህል ሥልጣነ ክህነት እያላችሁ የሚታሠረውን ማሠር፥ የሚፈታውን መፍታትስ እንዴት አቃታችሁ? እኛኩ የታመመ ትፈውሳላችሁ፥ የሞተ እንኳን ታስነሳላችሁ ብለን ነው በእምነታችን የምንጠብቀው። ታዲያ እንዴት ሰላም መፍጠር፥ በግኅበር መኖር፥ ሁሉን ነገር ባንድ አስተዳድር ሥር ማድረግ ይሆናል ችግር? የዚህን የበደል በር ለመክፈት ቁልፉ ተሠረቀ? መይንስ ተደበቀ? መይንስ ጊዜና ወቅት እየተጠበቀ? አማኙ ሁሉ ዓይኑን ከፍቶ፥ አእምሮውን አንቅቶ መልስ ይጠብቃል። በጸሎቱም ይተጋል። ዉት ግታ ወደ ቤተ እግዚአብሔርም ይገሠግሣል ይሮጣል ይሄዳል። የጸሎቱም ዓይነት ልጅ ስጠኝ፥ ጤንነቴን ጠብቅልኝ ሳይሆን ለዚች ለስምህ ማወደሻና መቀደሻ፥ ለክብርህ መውረሻ የሆነችውን የቤተ ክርስቲያንህን አባቶች ማኅበር ባርክ፥ በዙሪያው ከሸመቁት ጸብአ አጋንንት አድንልን ሠውርልን ነው።

ቅዱሳንና ብፁዓን አባቶች ሆይ!

እኛ የመንፈስ ልጆቻችሁ ስእናንተ ከመጸለይ፥ ከማዘንና ከማልቀስ በስተቀር ምን ኃይል አለን? የዕንባችን መፍሰስና መረጨት ግን በከንቱ እይቀርም። የራኄልን ዕንባ የተመለከተ እምላክ ዕንባችንን በቸልታ እንደ ገል ወተት አያፈሰውም። እምነታችን ጽኑ፥ ኃዘናችን ከልብ፥ ዕንባችን ከምር ነውና! አዎ! አንድ ጊዜ የተሠበረን ዕቃ መልሶ እንደነበር ለማድረግ ፈጽሞ አይቻልም። ግን መጠገንና ማስተካከል ይቻላል። ያውም ስመንፈሳዊ አባቶቻችን ምን የማይቻል ነገር ከቶ አለ? ከፍላጎትና ከማድረግ ከመሸሽ በስተቀር ሌላ ምን ምክንያት ይኖራል? ጥላቻ ነውን? ሕመም ነውን? ሥቃይ ነውን? ሞት ነውን? ኧረ! ምኑ ይሆንን? እናንተኮ የምድር ጨዎች ናችሁ። በናንተ የማይጣፍጥ ምን ነገር አለ? ብትናገሩ ትሰማላችሁ። ብትገዝቱ ከእግር ብረቱ የበለጠ እጥብቃችሁ ታሥራላችሁ። ያዘነውን ታጽናናላችሁ። የታመመውን ትፈውሳላችሁ። እንዲሁም

እንዲያመቸን አስቀድሞ ተነግሮናል። እሱም የት ነበርህ ምን ሠራህ ነው። ታዲያ ስመልሱ በቂ ዝግጅት እድርገናል ወይንስ ነገ ከነገ ወዲያ ይደርሳል ብለን እንደ ቀደሙት የኖኅ ዘመን ሰዎች ውሀው አንገታችን አስኪደርስ እንጠብቃለን? እንደዚያስ አናድርግ።

ብፁዓን ንዑዳን ከቡራን ኢትዮጵያውያን ሆይ! የቤተ ክርስቲያኒቱ ህልውና እጅግ ከከፍተኛ አደጋ ላይ ነው። መቅሠፍቱ ከሳይዋ ላይ እያንዣበበ ነው። ግርማው ያስፈራል በዓይንም ይታያል። የእሳቱ ወላፈን እጅግ ይስግጣል። የድምፁ ነጎድጓድ በጆሮ ይሰማል። የቴግቡ ኃይል እጅግ በጣም ያስፈራራል። ከመጠን በላይ ይገፈትራል። ካስቀስን አሁን እናልቅስ። ከስመን አሁን ተንበርከክን እንግፀን። ነገ ከነገ ወዲያ ጊዜውና ሰዓቱ አሁንም የኛ አይደለም አይሆንምም። ይህ ካልሆነ ከሞት በኋላ ዋይታ ከንቱ ጩኸት፥ ጉንጭ ፍጆታ መሆኑ ነው። ዛሬ ነፍሳችንና ሥጋችን ሳይለያዩ በእንድነት እንደጸኑ አብረው እያሉ የሚሠራ ነው። ከተለያዩ በኋላ ባሕሪያቸውና ጠባያቸው ሲታይ እንዴት እብረው ኖሩ? ያሰኛል። አንዱ የሚሞት የሚበሰብስ ሌላዋ ከፍል በአጠራር ነፍሰ አገር መንግሥት የምትወርስ ናት። የማግኘትዋና የማጣትዋም ዕድል የሚወሰነው ባንድነቱ ላይ ነውና በጥሞና እናስብበት። የነፍስና የሥጋ እጣ ከእጅ ያመለጠ እንቁላል ከመሆኑ በፊት እናስተውል ይችን የምታልፍ ሰዓት ያስሥራ አንሽኖት። አንድ ጊዜ ካለፈች አትመለስም አናገኛትም።

ይህች ታሪካዊት፥ ብሔራዊት፥ አማናዊትና አምላካዊት ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በተራራ ላይ ያለች የመቅረዝ ብርሃን ናት። ፈደል አስቆጥራ፥ ብሔራዊ ክብሯን አስጠብቃ፥ ጠላትን ፈጥርቃ፥ ነፃነትን እስጠብቃ የኖረች ቤተ ክርስቲያን ናት። ይህ ደግሞ ጠላቶቿን እስተባብሮባታል። ወዳጆቿን ነጣጥሎባታል። አንድነቷን አሳጥቷታል። በሌላም በኩል ተመክሮዋ ከፉን በክፉ አትቃወመው በመሆኑ ብዙ ጎድቷታል። ራሰን ዝቅ ማድረግ የትሕትና መለያና ጠባይዋ በመሆኑም ነው። በዚህም ምክንያት ሊቃውንቷ ድርሰት ጽፈው ስማቸውን እንኳ ከማሰፈር ይሸሻሉ። እንደ ከንቱ ውዳሴ እንዳይቆጠርባቸው ከጻፉትም «አነ ኀጥዕ ወአባሲ» [ኃጢዓተኛውና በደለኛው] ዕገሌ የሚል ኃረግ ይጨምሩበታል። በዚህም ምክንያት ለዚህ ዓለም ጣዕመ ሕይወት ብዙም ተጨናቂዎች አልነበሩም። ልብ እንበል ናቸው አይደለም አልነበሩም ነው።

ስለዚህም ነው የግብፅ ጳጳሳት ስአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመታት የሥልጣነ ክህነታቸው ተጠሪዎች ሆነው የኖሩት። ይህም

የሚዘከራቸው አጥተው ይህ ነው ብለው በቋንቋ ሲገልጹትና ሊናገሩት በሚዘገንን ሁኔታ ላይ በችግር ላይ ይገኛሉ። ለአኒህ ሊቃውንትና ለተማሪዎቻቸው እንኳን ገንዘቡን ሥጋውንም ቆርጠ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነው ኢትዮጵያዊ ሥፍር ቁጥር የለውም። ነገር ግን መንገድ የለም። መሸጋገሪያ ድልድይ የለም። ድርጅት የለም። ለጉዳዩ ባለቤት የለውም እንጂ እንኳን ለደሞዝ የሚሆን ገንዘብ ማግኘትና ማሰባሰብ ቀርቶ ለፈረሱ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ማስጠገኛ፥ ለዕቃ ቤቶቻቸውም ማጠናከሪያ፥ የተትረፈረፈ ገንዘብ በተለበለበ በነበር።

የኢትዮጵያ ማንነት መሠረቱ ከግዕዙና ከቅኔው ትምህርት ላይ መሆኑን ማን ይስተዋል? ታዲያ መምህራኑ፥ ሊቃውንቱ ጠም አድረው ሌላው ግን በልቶና ጠጥቶ ያለበት ዘመን መሆን ነበረበትን? ኳስ ተማውተው፥ በቡጢ ሰው ነጥረቀው፥ ሮጠው ተሯሩጠው፥ ተከብረውና አንቱ ተብለው የሚኖሩባት ኢትዮጵያ ለመድኃኒቱ፥ ለጥበቡ፥ ለምርምሩ፥ ለፍልስፍናውና ለምክሩ መሠረት የሆኑት ሙያዎቻችን ግን አረም በልቷቸው፥ ጠለንጅ ወርሷቸው ይገኛሉ ይታያሉ። ይህ በእውኑ እስከ መቼስ ይቀጥላል? እስከ መቼስ ድረስ ነው የማንነታችንን ልዩና ብርቅ ድንቅ መታወቂያዎቻችንን እየሸሸናቸው የምንኖረው? አረ! ለመሆኑ መቼስ ነው የምንታረቃቸው? አቤት የኢትዮጵያዊ ያለህ! አቤት የኢትዮጵያዊት ያለሽ! አቤት የሙራን ያላችሁ! አቤት የለው ያለህ! ከሞትም ሞት እየሞትን፥ ከመቃብርም መቃብር በቁመናችን እየወረድን ነው። የግዕዝ ቋንቋችን የማንነታችን መገለጫችን የጥበባችን ማጎደር ሊኖር የሚችለው ምሁሮቻችንን እንደ ዓይናችን ብሌን ስንጠብቅና ስንከባከብ ነው። ግዕዝ ሲጠፋ እኛም እንዘነጋለን። የማንነታችን አሻራ ተፈልጎም አይገኝምና አሁኑኑ ይታሰብበት። እግዚኦ እንበልበት። እናልቅስበት። እንጸልይበት።

አንድ ሕንፃ ቤተክርስቲያን ለመሥራት አንታገላለን እጅግ መልካም ነው። ግን መምህራኖቻችን፥ የብርሃን ዓምዶቻችን፥ የዐለት መሠረቶቻችን በረሀብና በጥም አያለቁ ቋሚና አስተማማኝ የወር ደሞዝ ሊኖራቸው ሲገባ ያ ቀርቶ እንኳን ጊዜያዊ አርዳታ እንኳን አይደረግላቸውም። ለድርቅ፥ ለረሀብ ተብሎ በካህናቱ አማካይነት የሚለበለበው ገንዘብ እንኳን ዕድሚያቸውን በሙሉ የጣሙ፥ የላመ ለማይቀምሱት መምህራን ሳይሆን የሚሠጠው ወርኃዊ ችግር ለገጠማቸው ብቻ ነው። አሱም እንኳን የሚናኘው ዕርዳታ ግደል፥ ግደላደል፥ ምጽዋት መሥጠት ያውቃሉ ተብሎ ለሚነገርላቸው

ክርስትናን በነሱ ፍላጎትና ምኞት እንዲለፋፋ ባለማድረጋቸው መላው አፍሪቃ የዚችው ቤተ ክርስቲያን አካል ከመሆን አስቀርቶታል። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያኗ ራሷን ችላ መምራት ከጀመረች ወዲህ ከኢትዮጵያ በመውጣት በአፍሪቃ፥ በአውሮጳ፥ በሰሜን አሜሪካ በአውስትራልያ በካረቢያን ደሴቶችና አሁን ደግሞ በፀረብ አገሮች ሞምር ቤተ ክርስቲያን ተክላለች። ይህም እሺ በጎ ወሽነያ የሚያሠኝ ነው። እጅግ, በጣም ደስ ያሰኛል። አጥንትን ያለመልግል። አዎ ሥራ ተሠርቷል ብለን ደስ ይለናል።

ይሁን እንጂ! ይህ ራስን መቻል፥ ጎጆ መውጣት ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ አንድ ኢመንፈሳዊ የሆነ ከፍተኛ ችግር ተከሥቷል። ለሱም እንደ ምክንያት ሆኖ ተከታዮችን አፍርቶ ከግብፅ የመጣውን ሹመት እንደ ቤተ መንግሥቱ ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት መሥመር ተከትሎ እንዲሄድ ፈለጉ። እሱም እንደ ምክንያት የሆናቸው ለቤተ ክህነቱ የሲሃ መንግሥት ባለቤትነት ከተሠጣቸው ከጻድቁ አባታችን ከተከለ ሃይማኖት መንበር መውጣት የለበትም የሚለው አስተሳሰብ ነው። ቤተለይም ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ዕረፍት በኋላ መንበሩን የሚረከበው አባት ከጻድቁ መካን ከገዳመ ተክለ ሃይማኖት ውስጥ ተወልዶ ከውስጧ ያደገ አባት ብቻ ፓትርያርክ መሆን አለበት ሲባል ከፍተኛ ተቃውሞ ተደረገ። ይሁንና በወቅቱ ከነበሩት ሊቃነ ጳጳሳት በዚያውም ላይ በእንደራሴነት ቤተ ክርስቲያኗን በበላይነት ይመሩት የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን የመሠለና ያከለ በወቅቱ ባለመገኘቱና ባለመኖሩ ሹመቱ ለሳቸው ተሠጠ። ይህም በሥራቸው ሁሉ ከፍተኛ ዕንቅፋት እንደ ፈጠረባቸው ብዙዎች ይስማሙበታል። እንዲያውም ለደርግ አሳልፈው ካሠጧቸውና ለሞትም ካበቋቸው አንኳር ምክንያቶች መካከል ውስጥ የዚህ የተከለ ሃይማኖት መንበር ለተከለ ሃይማኖቶች የሚለው የተቃዋሚዎች አድማ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ብዙዎች ይመሠክራሉ።

በዚህም ይሁን በሌላ ምክንያት ደርግ የቤተ ክርስቲያኗን አመራር ሊቆጣጠርበት በሚያስችለው አባት ሥር እንዲውልም ስለፈለገ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን ከመንበራቸው አውርዶ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ጥሶ በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ ሾመ። በዚያን ጊዜ ሕገ ቤተ ክርስቲያን አይፈቅድም ብለው በወቅቱ የነበሩት አባቶች ከጥቂቶቹ በስተቀር ከመቃወም ይልቅ በውድም ሳይሆን በግድና በዛቻ በተደረገባቸው ተጽእኖ በፍራቻ ተሰማምተው ይበል ብለው በቤተ ክርስቲያኗ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ወንጀል ፈፀሙ። በዓላማቸው ጸንተው እስከ ሞት ድረስ መታገሥ ነበረባቸው። ነገር

ረኽም ነው። የጥንካሬዋን ያህልም ደካማ ጎኖች እንዳሏትም እንረዳለን። ይህ ደግሞ ለማን እንደሚጠቅመው ፈጽሞ ያልታሰበበትና ያልተጸለየበት ጉዳይ መሆኑን መረዳቱ አይከብድም። ፍቅር የሌለበት ሥራ ያውም ማስተማር እንዴት ተዘርቶ ሊበቅል ይችላል? ይህን ችግር የሚፈታ ኃይል የለምን? የችግሩን ዓይነት ለይቶና አውቆ ያበጠውን መብጣት፥ የቆሰለውን መቁሰል እንዴት አቃተ?

ብፁዓን አባቶች ሆይ! «በምድር ያሠራችሁት በሰማይ የታሠረ ይሆናል። በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሆናልን» ያህል ሥልጣነ ክህነት እያላችሁ የሚታሠረውን ማሠር፥ የሚፈታውን መፍታትስ እንዴት አቃታችሁ? እኛኮ የታመመ ትፈውሳላችሁ፥ የሞተ እንኳን ታስነሳላችሁ ብለን ነው በእምነታችን የምንጠብቀው። ታዲያ እንዴት ሰላም መፍጠር፥ በግጎበር መኖር፥ ሁሉን ነገር ባንድ አስተዳድር ሥር ማድረግ ይሆናል ችግር? የዚህን የበደል በር ለመክፈት ቁልፉ ተሠረቀ? ወይንስ ተደበቀ? ወይንስ ጊዜና ወቅት እየተጠበቀ? አማኙ ሁሉ ዓይኑን ከፍቶ፥ አእምሮውን አንቅቶ መልስ ይጠብቃል። በጸሎቱም ይተጋል። ዉት ማታ ወደ ቤተ እግዚአብሔርም ይገሠግሣል ይሮጣል ይሄዳል። የጸሎቱም ዓይነት ልጅ ስጠኝ፥ ጤንነቴን ጠብቅልኝ ሳይሆን ለዚች ለስምህ ማወደሻና መቀደሻ፥ ለክብርህ መውረሻ የሆነችውን የቤተ ክርስቲያንህን አባቶች ማጎበር ባርክ፥ በዙሪያው ከሸመቁት ጸብእ አጋንንት አድንልን ሠውርልን ነው።

ቅዱሳንና ብፁዓን አባቶች ሆይ!

እኛ የመንፈስ ልጆቻችሁ ለእናንተ ከመጸለይ፥ ከማዘንና ከማልቀስ በስተቀር ምን ኃይል አለን? የዕንባችን መፍሰስና መረጨት ግን በከንቱ አይቀርም። የራኄልን ዕንባ የተመለከተ አምላክ ዕንባችንን በቸልታ እንደ ገል ወተት እያፈሰሰውም። እምነታችን ጽኑ፥ ኃዘናችን ከልብ፥ ዕንባችን ከምር ነውና! አዎ! አንድ ጊዜ የተሠበረን ዕቃ መልሶ እንደነበር ለማድረግ ፈጽሞ አይቻልም። ግን መጠገንና ማስተካከል ይቻላል። ያውም ለመንፈሳዊ አባቶቻችን ምን የማይቻል ነገር ከቶ አለ? ከፍላጎትና ከማድረግ ከመሸሽ በስተቀር ሌላ ምን ምክንያት ይኖራል? ጥላቻ ነውን? ሕመም ነውን? ሥቃይ ነውን? ሞት ነውን? ኧረ! ምኑ ይሆንን? እናንተኮ የምድር ጨዎች ናችሁ። በናንተ የማይጣፍጥ ምን ነገር አለ? ብትናገሩ ትሰማላችሁ። ብትገዝቱ ከእግር ብረቱ የበለጠ አጥብቃችሁ ታሥራላችሁ። ያዘነውን ታጽናናላችሁ። የታመመውን ትፈውሳላችሁ። እንዲሁም

እንዲያመቸን አስቀድሞ ተነግሮናል። አሱም የት ነበርህ ምን ሠራህ ነው። ታዲያ ለመልሱ በቂ ዝግጅት አድርገናል ወይንስ ነገ ከነገ ወዲያ ይደርሳል ብሰን አንደ ቀደሙት የናኅ ዘመን ሰዎች ውሀው አንገታችን እስኪደርስ እንጠብቃለን? እንደዚያስ አናድርግ።

ብፁዓን ንዑዳን ከቡራን ኢትዮጵያውያን ሆይ! የቤተ ክርስቲያኒቱ ህልውና እጅግ ከከፍተኛ አደጋ ላይ ነው። መቅሠፍቱ ከላይዋ ላይ እያንዣበበ ነው። ግርማው ያስፈራል በዓይንም ይታያል። የእሳቱ ወላፈን እጅግ ይስግጣል። የድምፁ ነጎድጓድ በጆሮ ይሰማል። የቴግቡ ኃይል እጅግ በጣም ያስፈራራል። ከመጠን በላይ ይገፈትራል። ካለቀስን አሁን እናልቅስ። ከለመን አሁን ተንበርክከን እንግፀን። ነገ ከነገ ወዲያ ጊዜውና ሰዓቱ አሁንም የኛ አይደለም አይሆንምም። ይህ ካልሆነ ከሞት በኋላ ዋይታ ከንቱ ጩኸት፥ ጉንጭ ፍጆታ መሆኑ ነው። ዛሬ ነፍሳችንና ሥጋችን ሳይለያዩ በአንድነት እንደጸኑ አብረው እያሉ የሚሠራ ነው። ከተለያዩ በኋላ ባሕሪያቸውና ጠባያቸው ሲታይ እንዴት አብረው ኖሩ? ያሰኛል። አንዱ የሚሞት የሚበሰብስ ሌላዋ ከፍል በአጠራር ነፍስ አገር መንግሥት የምትወርስ ናት። የማግኘትዋና የማጣትዋም ዕድል የሚወሰነው ባንድነቱ ላይ ነውና በጥሞና እናስብበት። የነፍስና የሥጋ እጣ ከእጅ ያመለጠ እንቁላል ከመሆኑ በፊት እናስተውል ይችን የምታልፍ ሰዓት ያለሥራ አንሽኖት። አንድ ጊዜ ካለፈች አትመለስም አናገኛትም።

ይህች ታሪካዊት፥ ብሔራዊት፥ አማናዊትና አምላካዊት ቤተ ክርስቲያን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በተራራ ላይ ያለች የመቅረዝ ብርሃን ናት። ፈደል አስቆጥራ፥ ብሔራዊ ክብሯን አስጠብቃ፥ ጠላትን ፈጥርቃ፥ ነፃነትን አስጠብቃ የኖረች ቤተ ክርስቲያን ናት። ይህ ደግሞ ጠላቶቿን አስተባብሮባታል። ወዳጆቿን ነጣጥሎባታል። እንድነቷን አሳጥቷታል። በሌላም በኩል ተመክሮዋ ከፉን በክፉ አትቃወመው በመሆኑ ብዙ ጉድቷታል። ራስን ዝቅ ማድረግ የትሕትና መለያና ጠባይዋ በመሆኑም ነው። በዚህም ምክንያት ሊቃውንቷ ድርሰት ጽፈው ስማቸውን እንኳ ከማስፈር ይሸሻሉ። እንደ ከንቱ ውዳሴ እንዳይቆጠርባቸው ከጻፉትም «አነ ኀጥዕ ወአባሲ» [ኃጢዓተኛውና በደለኛው] ዕገሌ የሚል ኃረግ ይጨምሩበታል። በዚህም ምክንያት ለዚህ ዓለም ጣዕመ ሕይወት ብዙም ተጨናቂዎች አልነበሩም። ልብ እንበል ናቸው እይደለም አልነበሩም ነው።

ስለዚህም ነው የግብፅ ጳጳሳት ለአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመታት የሥልጣነ ክህነታቸው ተጠሪዎች ሆነው የኖሩት። ይህም

የሚዘከራቸው አጥተው ይህ ነው ብለው በቋንቋ ሊገልጹትና ሊናገሩት በሚዘገንን ሁኔታ ላይ በችግር ላይ ይገኛሉ። ለእነህ ሊቃውንትና ለተማሪዎቻቸው እንኳን ገንዘቡን ሥጋውንም ቆርጦ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነው ኢትዮጵያዊ ሥፍር ቁጥር የለውም። ነገር ግን መንገድ የለም። መሸጋገሪያ ድልድይ የለም። ድርጅት የለም። ለጉዳዩ ባለቤት የለውም እንጂ እንኳን ለደሞዝ የሚሆን ገንዘብ ማግኘትና ማስባሰብ ቀርቶ ለፈረሱ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ማስጠገኛ፥ ለዕቃ ቤቶቻቸውም ማጠናከሪያ፥ የተትረፈረፈ ገንዘብ በተሰበሰበ በነበር።

የኢትዮጵያ ማንነት መሠረቱ ከግዕዙና ከቅኔው ትምህርት ላይ መሆኑን ማን ይስተዋል? ታዲያ መምህራኑ፥ ሊቃውንቱ ጦም አድረው ሌላው ግን በልቶና ጠጥቶ ያለበት ዘመን መሆን ነበረበትን? ኳስ ተጫውተው፥ በቡጢ ሰው ነጥርቀው፥ ሮጠው ተጯሩጠው፥ ተከብረውና እንቱ ተብለው የሚኖሩባት ኢትዮጵያ ለመድኃኒቱ፥ ለጥበቡ፥ ለምርምሩ፥ ለፍልስፍናውና ለምክሩ መሠረት የሆኑት ሙያዎቻችን ግን እረም በልቷቸው፥ ጠለንጅ ወርሷቸው ይገኛሉ ይታያሉ። ይህ በእውኑ እስከ መቼስ ይቀጥላል? እስከ መቼስ ድረስ ነው የማንነታችንን ልዩና ብርቅ ድንቅ መታወቂያዎቻችንን እየሸሸናቸው የምንኖረው? ኧረ! ለመሆኑ መቼስ ነው የምንታረቃቸው? አቤት የኢትዮጵያዊ ያለህ! አቤት የኢትዮጵያዊት ያለሽ! አቤት የምሁራን ያላችሁ! አቤት የሰው ያለህ! ከሞትም ሞት እየሞትን፥ ከመቃብርም መቃብር በቁመናችን እየወረድን ነው። የግዕዝ ቋንቋችን የማንነታችን መገለጫችን የጥበባችን ማኅደር ሊኖር የሚችለው ምሁሮቻችንን እንደ ዓይናችን ብሌን ስንከባከብ ነው። ግዕዝ ሲጠፋ እኛም እንዘነጋለን። የማንነታችን አሻራ ተፈልጎም እይገኝምና አሁንኑ ይታሰብበት። እግዚኦ እንበልበት። እናልቅሰበት። እንጸልይበት።

አንድ ሕንፃ ቤተክርስቲያን ለመሥራት እንታገላለን እጅግ መልካም ነው። ግን መምህራኖቻችን፥ የብርሃን ዓምዶቻችን፥ የዐለት መሠረቶቻችን በረሀብና በጥም እያለቁ ቋሚና አስተማማኝ የወር ደሞዝ ሊኖራቸው ቢገባ ያ ቀርቶ እንኳን ጊዜያዊ እርዳታ እንኳን አይደረግላቸውም። ለድርቅ፥ ለረሀብ ተብሎ በካህናቱ አማካይነት የሚሰበሰበው ገንዘብ እንኳን ዕድሚያቸውን በሙሉ የጣመ፥ የላመ ለማይቀምሱት መምህራን ሳይሆን የሚሠጠው ወርኃዊ ችግር ለገጠማቸው ብቻ ነው። እሱም እንኳን የሚናኘው ዕርዳታ ማደሉ፥ ማደላደል፥ ምጽዋት መሥጠት ያውቃሉ ተብሎ ለሚነገርላቸው

ክርስትናን በነሱ ፍላጎትና ምኞት እንዲስፋፋ ባለማድረጋቸው መላው አፍሪቃ የዚችው ቤተ ክርስቲያን አካል ከመሆን አስቀርቶታል። ይሁን እንጂ ቤተ ክርስቲያኗ ራሷን ችላ መምራት ከጀመረች ወዲህ ከኢትዮጵያ በመውጣት በአፍሪቃ፥ በአውሮፓ፥ በሰሜን አሜሪካ በአውስትራልያ በካረቢያን ደሴቶችና አሁን ደግሞ በዐረብ አገሮች ዊምር ቤተ ክርስቲያን ተክላለች። ይህም እሺ በጎ ወሽነያ የሚያሠኝ ነው። እጅግ ዘጣም ደስ ያሰኛል። አጥንትን ያለመልማል። አዎ ሥራ ተሠርቷል ብለን ደስ ይለናል።

ይሁን እንጂ! ይህ ራስን መቻል፥ ጎጆ መውጣት ከተጀመረበት ጊዜ ጀምሮ አንድ ኢመንፈሳዊ የሆነ ከፍተኛ ችግር ተከሥቷል። ለሱም እንደ ምክንያት ሆኖ ተከታዮችን እፍርቶ ከግብፅ የመጣውን ሹመት እንደ ቤተ መንግሥቱ ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት መሥመር ተከትሎ እንዲሄድ ፈለጉ። አሱም እንደ ምክንያት የሆናቸው ለቤተ ክህነቱ የሲሃ መንግሥት ባለቤትነት ከተሠጣቸው ከጻድቁ አባታችን ከተከለ ሃይማኖት መንበር መውጣት የለበትም የሚለው አስተሳሰብ ነው። በተለይም ክብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ዕረፍት በኋላ መንበሩን የሚረከበው አባት ከጻድቁ መካን ከገዳመ ተክለ ሃይማኖት ውስጥ ተወልዶ ከውስጧ ያደገ አባት ብቻ ፓትርያርክ መሆን አለበት ሲባል ከፍተኛ ተቃውሞ ተደረገ። ይሁንና በወቅቱ ከነበሩት ሊቃነ ጳጳሳት በዚያውም ላይ በእንደራሴነት ቤተ ክርስቲያኗን በበላይነት ይመሩት የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን የመሠለና ያከለ በወቅቱ ባለመገኘቱና ባለመኖሩ ሹመቱ ለሳቸው ተሠጠ። ይህም በሥራቸው ሁሉ ከፍተኛ ዕንቅፋት እንደ ፈጠረባቸው ብዙዎች ይስማሙበታል። እንዲያውም ለደርግ አሳልፈው ካሠጧቸውና ለሞትም ካበቋቸው አንኳር ምክንያቶች መካከል ውስጥ የዚህ የተከለ ሃይማኖት መንበር ለተከለ ሃይማኖቶች የሚለው የተቃዋሚዎች አድማ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ብዙዎች ይመሠክራሉ።

በዚህም ይሁን በሌላ ምክንያት ደርግ የቤተ ክርስቲያኗን አመራር ሊቆጣጠርበት በሚያስችለው አባት ሥር እንዲውልም ስለፈለገ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን ከመንበራቸው አውርዶ ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ጥሶ በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ ሾመ። በዚያን ጊዜ ሕገ ቤተ ክርስቲያን አይፈቅድም ብለው በወቅቱ የነበሩት አባቶች ከጥቂቶቹ በስተቀር ከመቃወም ይልቅ በውድም ሳይሆን በግድና በዛቻ በተደረገባቸው ተጽእኖ በፍራቻ ተስማምተው ይበል ብለው በቤተ ክርስቲያኗ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ወንጀል ፈፀሙ። በዓላማቸው ጸንተው እስከ ሞት ድረስ መታገሥ ነበረባቸው። ነገር

ከታሉ ቆርጠው በአፍ ለሚያኝርሱት ለካቶሊክና ለመሳሠሉት ርዳታ ሠዊ ድርጅቶች ነው።

አባቶች ያለፉበትን የጉዞ ሕይወት፥ እመክሮና ክብር ያገኙበትን፥ ትምህርትና እውቀት የቀሰመብትን እነሱ ካላከበሩት፥ ግን ያስጠጋዋል? ኧረ! ግን ደጋከባከበዋል? ሁኔታውን ሲያስቡት እጅግ በጣም ያሳዝናል። «ለወህቤ ዝናም ከልዕወ ማየ።» [ዝናምን ለሚሠጥ እምላክ ውሀ ከሊከሥት] እንዳለው ባለ ቅኔ ቤተ ክርስቲያንም በእግሯ የቆመችበት መሠረቷ ሲናወጥ ችላ ያለችውን ዓቢይ ጉዳይ ማን ይንከባከበው? ማንስ ይጠብቀው? ማንስ ያስተናግደው? አባቶች በጠቅላላው የአገር ፍቅር እሳት ለሚያነዳችሁና ለሚያቃጥላችሁ የቤተ ክርስቲያን ሰዎች የአገር ምሁራን አቤቱታው ይድረሳችሁ። እኛ አቤት ካላልንበት፥ ካልጸለይንበት ማን ያድርገው? «ለዘንለፈ ሥርየትI ወለዘይመጽእ ዕቅበት» [ላለፈው ይቅር ይበለን ለሚመጣው ይጠብቀን] ነውና እውንኑ ሕጋዊ ድርጅት ተቋቁሞ ለእነ አራት ዓይኖች አንዲትኳን እነሱን የምትመስክት ዓይን አንፈጋቸው። እርዳታ ይጠየቅ። የየሠበካው ጉባዔም ለጉዳዩ ቅድሚያና ትኩረት ሠጥቶት ይርዳ። ይህ ነው የማይባል ውጤት ይገኛል። በውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ ብቻ እንኳን ይህንን ማገዝና መርዳት ቀርቶ ፈለገ ግዮንንም ወይንም ዓባይን ባንድ ቀን መገደብ ይችላል።

፪ . ሥልጣነ ክህነት

ቅዱሳን አባቶች፥ ብዙዓን ሊቃነ ጳጳሳት፥ ቆሞሳት፥ መነኮሳት፥ ቀሳውስት፥ ዲያቆናትና ምዕመናነ ኢትዮጵያ አርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አካላት ሆይ! ሁላችንም እንደ ነነዌ ሰዎች ከእሀልና ከውሀ ተከልክለን፥ በራሳችን ላይ አመድ ነስንለን፥ ማቅ ወይንም በርኖስ ለብሰን፥ ከመሬት ላይ ወድቀን፥ ምሕላ የምንይዝበት ጊዜው ዛሬ ነው። ነገ አይደለም። ነገ ከነገ ወዲያ የመጭው ትውልድ ጊዜና ዘመን ነው። የኛ ዛሬ እንጂ ትላንት አይደለችም ከነበረችም አልፋለች። በምንም ታምር ወደ ትላንት አንመለስም። ያን የትናንቱን እናስተካክላለን ብለን ጊዜ የምናባክን ከሆነ በተሠጠንና ባለን ሰዓትና ወቅት አልኖርንበትም አልሠራንበትም። ይህ ደግሞ ወደፊት በተስፋ ለምንጠብቀው ዓለም የጉዞ ስንቅ የሚሆነን አይደለም። ምን እንደምንጠየቅም ለዝግጅት

ሹመቱን አትፈቅድልንም ብለው አስበው ይሆን? የግብፅስ ቤተ ክርስቲያን በሥጋ ብትለያዩ በመንፈስ አንድ ናችሁ አብራችሁ ኑሩ በማለት ፋንታ ቤተ ክርስቲያኗን ከፍለው ሌላ ፓትርያርክ ለመሾም ለምን ተሽቀዳደሙ? አንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመት ሲኖሩ መለያየት የሚባል እንኳን ሲታሰብ ቃሉም ከመዝገበ ቃላት ውስጥ እንኳ አልሠፈረም ነበር። ይህንም በክርስትና ዓይናችሁ ተመልከቱት። በእነሱ ዘንድ ከኢትዮጵያ ወጥቶ ወደ ጥንተ ታሪካቸው ወደ አሌክሳንድርያዋ ቤተ ክርስቲያን ፊታቸውን መለሱ። መቼም ዘመኑ የግሊንቢጥ ሆነና ከወላጅዋ እናት ከኢትዮጵያ ወደ እንጀራ አባትዋ ወደ አሌክሳንድርያ መንበረ ክህነታቸው ሄደው ተደበቁና ሌላ ችግር ፈጠሩ። እነሱ እንኳ ከኢትዮጵያ ከተለዩበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ሦስተኛ ፓትርያርክ ሾሙ። ኤርትራ እንዲያ ከሆነ አሜሪካስ እንዴት ሊሆን? አሜሪካ የተፈፀመው ድርጊት ሕፃኑን ከታጠበበት ውሀ ጋር ነው ወጥቶ የተደፋው። ቀጥሎ የምናየውና የምናነበው የአሜሪካው ሲኖዶስ ቢያንስ በሁለት ዕጅ ኤርትራውያንን መቅደም አለባቸው ማለት ነው። ይህን በደል በእውነቱ እንዴት ራሳቸው ችሎትና ተሸክሞት እደረ? ለው መንፈሳዊውን ሥልጣን እንዲህ በግድና በጉልበት አብሮኝ አለ ከኔ ፈጽሞ አልተለየም። የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ሳቋርጥም አልተለየኝም። ኬንያም አብሮኝ ነበር። ለው የሚለርቀውና የሚያጠፋው ሥልጣን አይደለም። የማይታይና የማይዳሰስ ነው ብለው ያስረዱናል። ይህንም በማለት ሕዝበ ክርስቲያኑን ያስደነግጣሉ። ለኛ ለኛ ታሳቅ ኃዘን ነው። ራሳችንን ያሳክከናል። እግራችንን ያቃጥሰናል። ዕጃችንን ይለበልበናል።

በእውኑ ለቅዱሳንና ለብዙዓን አባቶች እንደኛ እንደ ምዕመናኑ ችግሩ ባይጠዘጥዛቸው ነው እንጂ ሁሉን ጥለው ጣጥለው እንኳን ገዳም ካደጉበት ተመልሰ መግባት ይቅርና ከእሳት ጉድጓድ ባስገባቸው በነበር። ምነውኮ የኢትዮጵያ ነገሥታት ዙፋናቸውን እየተዉ ወደ ገዳም የገቡ መኖራቸውን እናነብ የለምን? ለዚህ ሥራ እንደ አብነት የሚጠቀሱት ታላቁ ንጉሠ ነገሥት ቅዱስ ካሌብ ናቸው። ለእገራቸው ክብርና ዝና ሲሉስ በጠላት ከመማረክ ራሳቸውን በራሳቸው ለኅልፈት የዳረጉት ዓፄ ቴዎድሮስስ ታላቅ አርዓያ አይደሉምን? የአገራቸውን ዳር ድንበር ሲከላከሉ አንገታቸውን በጠረፋቸው ላይስ ያስረከቡት ዓፄ ዮሐንስስ ምሥክር አይሆኑምን? እንዴት ለዚች ታላቅና ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ሲባልስ ምን የማይሠራ ነገር ነበር። ለሥጋዊው ዓለም ወይንም የመነኮለ ለእግዚአብሔር መንግሥት ራሱን ሕያው ላደረገ አባትማ ይች በጣም እንደ ጨፍ ፍሬ ያነሰች አይደለችምን?

ግን አልሆነም። ለዚህም ድርጊታቸው ታሪክና ትውልድ ለዘለዓለም ሲያብጠለጥላቸው ይኖራል። ይህ ጽናት ያለግንኙነት እንደ ሥራ ልምድ ተቆጥሮ ይሆን አሁንም የተደገመው? ቅዱስነታቸውም በገዛ አገራቸውና ሕዝባቸው ዕጅ በሰማዕትነት አረፉ። ከቅዱስነታቸውም ሞት በኋላ ከታሰበውና ሕጋዊነቱ ከሚነገርለት ከመንበረ ተክለ ሃይማኖት አልሆነም። ያልታሰቡና ያልታለሙ መናኒ አባት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከገዳሙም ባይሆኑ የጻድቁን ስም ተላብሰው ከመንበሩ ላይ ተቀመጡ።

ያ በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ መሾም አይገባም ብለው ያልተቃወሙት አበሳ መልኩን ለውጠ ዳግመኛም በሥጋ ተወለደ። ይህን አፈጻጸም ግን አንት አብያተ ክርስቲያናትና የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ድርጊቱን እውግዘው እዲሉንም ተሿሚ እውቅና ነሥተው ቆዩ። ይህ በእንዲህ እንዳለ ነበር አንድ የቤተ ክርስቲያኒቱ እውቅ ጋዜጠኛ ይህ ትናንት የመጣ ሹመት በየጊዜው ተተኪ በሚለወጥበት ወቅት ሁሉ በተሿሚ አባቶች ላይ ችግር ከሚፈጥርና ከሚያወዛግብ በሕግ ሲናዶሱ ከገዳመ ተክለ ሃይማኖት ብቻ ይሾም ብሎ ቢወሰነው የተሻለ መሆኑን ተናገሩ ይባላል።

ይህ የሥልጣን እወራረስ በቤተ ክርስቲያኒቱ የፈጠረው ችግር የማንነቷን መሠረት እየናጠው ጣራዋንም እየገፈፈው ነው። ከዚህም የተነሣ የትላንቷ ባሕር ምድር ኢትዮጵያ የዛሬዋ «ኤርትራን» ጨምሮ በዚህ ባለንበት የታሪክ ወቅት በተለይም በዚህ ወቅት ይህን ጽሑፍ በማዘጋጅበት ሰዓት ሌላ አዲስ ፓትርያርክ ለኤርትራዋ ቤተ ክርስቲያን ተሾሙ። አሁን ኤርትራ በእነዚህ አሥር ዓመታት ውስጥ ብቻ አሁን ሦስተኛ ፓትርያርክ መሾሟ ነው። ነገር ግን እስካሁን ደግሞ አንድና ብቸኛ ፕሬዚዳንት አሏት። ስለዚህ አራት ቅዱሳን ፓትርያርኮች አሉን። ነገ ከነገ ወዲያ ደግሞ የታሪክ ሂደት ነውና አሜሪካ ውስጥ ቢያንስ ቢያንስ አንድና ሁለት ጉዳዩ አስቸኳይ መፍትሔ ካልተሠጠው ፓትርያርኮች ይሾሙ ይሆናል። አሜሪካ ትልቅ እገር ስለሆነም ወይንም የሁለቱ ፓርቲዎች ዓይነት ሳይሾም ይቀራል? ነገሩ እኮ ዓሊ ሆይ ዓሊሲ ሆይ ሆኗል ጠዋታው። አቡነ አንጦንዮስ እሳቸውም በቁመናቸው በራሳቸው ፈቃድ ይልቀቁ ወይንም መንግሥታቸው አስወግዷቸው አይታወቅም ነገር ግን ከሥልጣናቸው ታግደው በምትካቸው በቅርቡ ብፁዕ አቡነ ዲዮስቆሮስ ተቀብተዋል። እኒህ አባት ለኤርትራ ቤተ ክርስቲያን ሦስተኛ ፓትርያርክ ሲሆኑ የለውጡ ፍጥነት ከቀይ ባሕር ማዕበል እጅግ ፈጥኗል። ይሁን እንጂ የመንግሥቱ ሥልጣን እንደ ወተት የረጋ ያልተነቃነቀ ፈቀቅም ያላለ ካንድ ሰው ራስ ላይ ያልወረደ

አሁንም እስቲ ያለውን እውነታ በረጋ መልኩ እንመርምረው። የቤተ ክርስቲያኗ መልክ ምን ይመስላል? ያልን እንደሆነ ጠውልጎና ተጎሣቁሎ ነው የሚታየው። የዚህ ሁሉ ችግር አሁንም የመለከቱ ድምፅ የሚያሰማው በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ ተሹሞ ሕጋዊው ፓትርያርክ መንበራቸውን ተነጥቁ ነው። በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ጊዜ እንደ ዋዛ ታይቶ ግማሹ በሣቅ፥ ሌላው በመንሰቅሰቅ ያሳለፈው የግፍና የመከራ ወቅት አሁን በዓይን የተበተነ የበርበሬ ዱቄት ሆኖ እያስለቀሰ ነው። መከራውም ከልጅ ወደ የልጅ ልጅ በመተላለፍ ላይ ነው። ያ ቁሞ ብለው የሰቀሉት መከራ ዛሬ እንኳን ቆመው ሊያወርዱት ይቅርና ከንፍ ያለው ሰው እያስፈሰገ ነው።

የሁሉም ዕንቆቅልሽ ሆኖ ወዳለው ችግር ልግባ። በእውነት ስለ እውነት ስለ ቤተክርስቲያናችን ድኅነት እንጂ የአባቶችን የግል ቡራኬና ርግማን ለመሻት እይደለም። እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጅነቴ፥ እንደ ምዕመን አባልነቴ፥ እንደ ኦርቶድክሳዊት ሃይማኖቴ አሁንም ደግሜ ደጋግሜ ልናገረው። «እስመ ቅንአተ ቤትከ በልዐኒ» መዝ. 68:17፤ እንደ አበው አተረጓጎም [በቤተ መቅደስህ ሥዕለ ፀሐይ አቁመውበት መሥዋዕተ እሪያ ሠውተውበት ዓይቼ የቀናሁት ቅናት እንደ እሳት አቃጥሎኛልና።] ለእኔም የቤቷ ቅናት ይበላኛል፡ ይገርፈኛል፡ ያሳምመኛል እጅግ በጣም ይቆጠቁጠኛል፡ ይበዘብዘኛል፡ ያቃጥለኛልም። እንግዲህ ከሁሉ በፊት ይህ ግንዛቤ ነወር ይባልልኝ፡ በታም ይሠጥልኝ።

ጉዳዩ እንዲህ ነው። በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ መሾም ለምን ሆነ? እንዴትስ ተፈፀመ? ቀደም ሲል የዚህ ችግር መንሥዔዎችን በመጠኑም ቢሆን ተመልክተናቸዋል። ይሁን እንጂ ይህ እፈፃፀም ቀኖና ቤተ ክርስቲያንን መጣስ ነው እየተባለ እንደ መፈክር ይነገራል። ጉዳዩ እንዲህ ነው። ይህን ጉዳይ ደግሞ ምዕመናን ማወቅና መገንዘብ አለብን። ከዚያ በፊት ግን የፓትርያርክነት ሥልጣን እንዴት ይወረሳል? ወይንም እንዴት ይተላለፋል? በነገራችን ላይ ሹመቱ የዕድሜ ልክ ሹመት ነው። ለዚህም ነው በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ አይሾምም እየተባለ የሚነገረው። ይህም ማለት አንድ ፓትርያርክ በሕይወት እያለ ሌላ አይሾምም ነው። እንግዲህ ከዚህ ላይ ነው ምዕመናን ለጆሯቸው የሚደርሰው ድምፅና ግርግርታ ከሆነስ ለምን ሌላ ይሾማል? ለዚህ ዕንቆቅልሽ ጥያቄ መልስ የሚያስፈልገው። እንደ ጠቅሚ ታሳብ የሚገለጽ ጉዳይ አለ። የፓትርያርኩ ሹመት በአለው በሚኖረው

ነው። ከእናት ቤተ ክርስቲያኗ ኮብልላ የሄደችዋ ቤተ ክርስቲያን ምንም እንኳ አባት ብትቀያይር የጥንቷ የጥንቷ ሊያደርጋት አልቻለም።

ይህ አመክሮ አሁን በአሜሪካ ተወለድሁ እለሁ እለሁ መጣሁ መጣሁ የሚለው አዲስ ሲኖዶስ ከዚህ ቢግር መልካም ነው። በአሜሪካ አሠራርና ፍጥነት በየአራት ዓመቱ ሳይሆን በየሁለት ዓመቱ የፓትርያርክ ምርጫ ይደረግና ሁላችንም ይድረሰን ተብሎ አመጽ እንደሚጀመር ትንቢት ምነገር የለበትም። ገና ካሁኑ ብዙዎቹ በተረከዛቸው ላይ የቆሙ ናቸው። ሞት ወይንስ ፕትርክና ቀድሞ የሚደርሰውን ባናውቅም ቅሉ በቅርቡ ሌላ ፓትርያርክ ሹመት ዋሽንግተን ዲሲ ላይ እንደሚደረግ ጥርጥር የለውም። ነገር ግን ይህ እንዳይሆን ለማድረግ እንድና ብቸኛው መድኃኒት ሰላም ፈጥሮ አብሮና ተዋሕዶ በአንድ ሲኖዶስ ሥር መተዳደር ብቻ ነው። ያለበለዚያ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስም የሚሆነው ባለፈው ዓመት የፈፀሙት ሹመት ዶሮ ዊራ ዊራ ማረጃዋን እንዳወጣችው እንደሚሆን ልብ ያለው ልብ ይበል። ጆሮ ያለው ይስማ ስለተባለብኝ ነው። እርስ በራሷ የተለያየች መንግሥት አትጸናምን እንዴት አንባችሁ ሳትተረጉሙት እንዳለፋችሁት ለመረዳት ባይጸነንም ቅሉ ምክንያቱም ንባቡ የእናንተን ዓላማ የማይደግፍ ካልሆነ እንደማይተረጎም ስለማውቅም ነው። እሱም ቢሆን ተጠምዞ ዞሮ ተዟዙሮ ወደመገንጠሉ እንዲያመራ ይደረጋል።

እንደኔ ታዝባችሁት ይሆን? በየአቅጣጫው መለየት መገንጠል መለየት ምነው በዛ? እንዲያው የቀረው ቢቀር እንዴት በመንፈሳዊው ዓለም እንኳ መገንጠል ቢበቃ። በእውነቱ ኢሕአዴግን በዚህ ደግሞ እናማረው ለምን አቡነ መርቆሬዎስን አልገደለም ብለን? መታማቱ እንደሆነ አልቀረለትም። ሊገድላቸው ነበር ሲያፍናቸው ነበር እሳቸው ሆነው አመለጡት እንጂ! ባላስበውና ባልጠረጠረው ሰዓት ጠፉበት እየተባለ ነው። ሰው አያሥርም ሰው አይገድልም ተብሎ የሚያማና የሚያማርርም መጣ። ይህም አንዱ መታሚያው ወንጀል ሆኖ ተቆጠረበት። «ሰው ከቆየ ከሚሰቱ ይወልዳል» ማለት እንዲህ ነው? በእውነቱ አሜሪካንንስ በዚህ ደግሞ እናማረው? የሃይማኖት ነፃነት ፈቅዶ ሁሉንም መንግሥት ገንጣዩንም መንግሥት ያዡንም ሁሉንም አንተ ውጣ አንተ ግባ ለማለት እንዲቀናው እንዲህ እንዳንሞት እንዳንድን ከሚያደርገን እገርስ መቼ ይሆን አንድና አንዱ የሚለየው? ሳንሞት እናየው ይሆን?

ባሕረ ነጋሾቹ [ኤርትራዎቹ] ከኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ወጥተው ወደ ግብፅ ተሻገሩ። ኢትዮጵያ እሺ ብላ

አገረሸበት። በዚህን ጊዜ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ምን አደረጉ? ይህ አሁን ለተፈጠረው ችግር ቁልፍ ምክንያት ነው። ምዕመናንም እንዲያውቁት የቀረበ ኃሳብ ነው። ይህን ኃሳብ ሳቀርብ በቀደመው መጽሐፌ ላይ እንደገለጽሁት በቂ መረጃ ባገኘሁ ጊዜ በግልጥ ለማቅረብ ቃል ገብቼ ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ስለጉዳዩ ተከታትዬ እኔ እንደተረዳሁት ያለምንም አዘንብሎ የተፈፀመውን ድርጊት በዝርዝር በሚከተለው ሁኔታ አቀርባለሁ። ፍርዱን ለአንባቢ እተወዋለሁ። ይሁን እንጂ የግሌን አስተያየት በመጨረሻ ላይም አቀርባለሁ።

መንግሥት በጎ ፈቃድ ላይ የተመረኮዘ ነው መባሉ ነው። ራሱን ችሎ ከሱ በሚበልጡ ተወዳዳሪዎች መካከል ያለ አባት በችሎታው ማነስና መቀነስ ምክንያት የምርጫውን ሙሳት በራሱ ኃይል ዋንቶ የማይወጣ ከሆነና መንግሥት ይጠቅመኛል ብሎ ካሰበ ጥላውን ያጥልበታል በግልጽም ባንገቱ ገመድ አስገብቶ ጎትቶ ያወጠዋል። በራሱ ጉልበት ዋንቶ የሚወጣ ከሆነም በፈገግታ ውድድሩን ይመለከተዋል። እንግዲህ ቀደም ሲል ወይንም እስካሁን የተደረጉትን የፓትርያርክ ምርጫዎችን በአጭሩ እንመልከት።

የመጀመሪያው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የደብረ ሊባኖስ ዕጨጌ ነበሩ። ዕጨጌነት ደግሞ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛው ማዕርግ ነው። እንዲያውም ከሳቸው በኋላ ሹመቱን ማለት ዕጨጌነቱን ደርበው የሚይዙት አስካሁን ድረስ ፓትርያርኮቹ ናቸው ስሌላም አልተሠጠም። በዚያውም ላይ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር በጠላት ዘመን አብረው በስደት ላይ ነበሩ። ሲመለሱም አብረው በድል አድራጊነት ገብተዋል። ከዚያም የጳጳሳት ምርጫ ሲደረግ ከተሾሙት መካከል አንደኛውና ሁለተኛው ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አብረው የተሾሙ ናቸው። በመጨረሻም ፓትርያርክነት ለኢትዮጵያውያን አባቶች ሲፈቀድ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሆነው በማገልገል ላይ ነበሩ። በዚያን ጊዜ በውይይትና በንግግር ከግብፅ ሊቀ ጳጳስ መምጣቱ ቀርቶ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ሥልጣኑን ተረክበው ይዘውት ነበር። ያን ጊዜ ነበር ከሊቀ ጳጳስነት ወደ ፓትርያርክነት ያለምንም ተወዳዳሪ የተሸጋገሩት። በርግጥ ቀደም ሲልም ሹመቱን ይዘውት ነበር ማለት ይቻላል። በዚያም ላይ የግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃድም ነበር። በዚያን ጊዜ ስለ ሹመት ጥልና ክርክር ሊኖር ቀርቶ ምኞትና ኃሳቡም አልነበረም። ያን ዘመን ደጉ ዘመን እንበለውና ከብር እንሠጠው። ቢያንስ ቢያንስ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረው ችግር ውስጥ ለውስጥ እንጂ እንዲህ አጥር ጥሶ የሚታይና እንደ ጉም አንዱን ካንዱ የሚጋርድ አልነበረም። ሁሉም በትዕግሥትና በፈሪሃ እግዚአብሔር አክብረው ይዘውት ነበር። ሹመቱም በእውቀት በፈሪሃ እግዚአብሔርና ራስን ዝቅ በማድረግ ይረከቡትና ያገኙት ስለነበርም ነው። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ መንበራቸውን ትተው በኢየሩሳሌም ገዳማት ውስጥ በምነና የቀረቻቸውን መዋዕለ ሕይወት ካሳለፉት ውስጥ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የከፋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ይገኙበታል።

ይሁንና ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ዕረፍት በኋላ ደግሞ ከነበሩት ሊቃነ ጳጳሳት አባቶች መካከል ሦስት ተወዳዳሪዎች

ምዕራፍ አራት

፩. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ከሥልጣን እንዴት ወረዱ?

በቅድሚያ ስለ ስማቸው አጠራርና አጻጻፍ አንድ መንገድ እናስይዘው። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ወይንስ መርቆርዮስ? ከሳቸው የፊርማ ማኅተም ላይ እንደሚነበበው «አባ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ» ሲል ከዚሁ ጋር በእንግሊዝኛ አብሮ ከሠፈረው ስማቸውና ማዕርጋቸው ጋር ደግሞ እንዲህ ተብሎ ተጽፏል። «ABBA MERKORIOS PATRIARCH OF ETHIOPIA» ከዚህ ላይም በአማርኛው መርቆሬዎስ ሲል በእንግሊዘኛው ደግሞ መርቆርዮስ ተብሎ ተጽፏል። እንዲሁም ቅዱስነታቸው የሚመሩት ሲኖዶስ ደግሞ «አባ መርቆርዮስ» ብሎ እንደ እንግሊዘኛው አጻጻፋቸው ወስዶታል። የሳቸው ረዳቶችና የጽ/ቤታቸው ሠራተኞች እንዴት ስማቸውን ማስተካከል ተሳናቸው? ቅዱስነታቸው እንኳ አማርኛውን እንጂ የእንግሊዝኛውን አጻጻፍ ብዙም ላያተኩሩበት ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን በዓለም አቀፍ የሚበተን ስምን እንዴት ጥንቃቄ አልተደረገበትም? የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ስም በአማርኛና በእንግሊዝኛ እንዴት ተስያይቶ ይጻፋል? ይህ በዘልማድ የሚሠራ ሁሉ እንዲህ ነው። ታዲያ አሁን በየትኛው ሆሄ ስማቸውን እንዳፈሙ? መቼም ስም ሲጻፍ በትክክል መሥፈር አለበትና ጥንቃቄ ስለ ስማቸው አጻጻፍ ወይንም ሆሄ ስማድረግ ነው። አንዳንዶች መርቆርዮስ ሲሏቸው ራሳቸው ግን በፈረመብት ደብዳቤና በፊርማ ማኅተማቸው እንደጻፉት መርቆሬዎስ ይላል። ያም ሆነ ይህ አሳቸው እንደፈረመብት ስም መጻፉ የግድ ይሆናል። ይሁንና ሌላ ማስረጃ ለመፈለግ የሰማዕቱን የቅዱስ መርቆሬዎስን ስም ከስንክሳር እንዳገኘሁት አሱም እንዲህ ተብሎ ተጽፏል።

«በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ አምላክ አመ ፳ወ፭ ለሐምሌ በዛቲ ዕለት ኮነ ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያኑ ለቅዱስ መርቆሬዎስ በሀገረ ምስር ዘባቲ አርአየ ተአምራተ ወመንክራተ ዘአልቦ ጎልቍ» [አንድ አምላክ በሆነ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ሐምሌ ሃያ አምስት በዚች ቀን ቁጥር ስፍር የሌላቸው ተአምራትንና ድንቆችን ባሳየባት በምስር አገር የቅዱስ መርቆሬዎስ ቅዳሴ ቤተ ክርስቲያኑ ሆነ።» [መጽሐፈ ስንክሳር ዘወርኀ ሐምሌ አዲስ አበባ

ለምርጫ ይቅረቡ እንጂ በችሎታ ከሁሉም የበለጡና ከዚያም በላይ የፓትርያርኩ እንደራሴ በመሆን ሲያገለግሉ የቆዩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ስለነበሩ እሳቸው ተመረጡና ተሾሙ። እንዲያውም በኢትዮጵያ ምድር ለፓትርያርክነቱ ሹመት ቀዳማዊ ናቸው። እንግዲህ ይህ በእንዲህ እንዳለ ደርግ ወደ ሥልጣን መጣ። የጃንሆይ መንግሥት ወጣ። በዚህ ወቅት በሥልጣን ላይ የነበሩ ሁሉ ከቤተ መንግሥት እስከ ቤተ ዘክህነት የደርግ መንግሥት ጠላት ሆነው ታዩ። የደረሰውንና የተፈፀመውን ሁሉ የምናውቀው ነው። ደርግ በኃይልና በጉልበት ሁሉንም አሠረ የሚገድለውንም ገደለ።

በዚያን ጊዜ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ሁለተኛው ፓትርያርክን አሥሮ በሳቸው ላይ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖትን በማን አለብኝነት ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ ፓትርያርክ እንዲሆኑ አደረገ። በዚያን ጊዜ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተጣሰ። ሊቃነ ጳጳሳቱም ቀኖናውን ማክበርና ማስከበር ሲገባቸው ሁሉም ዝም አሉ። የደርግ ጫናም ነበረበት። ፓትርያርክ በሕይወት እያለ ፓትርያርክ እንዲሾም ሆነ። ታላቅ ስሕተት ነበር። በወቅቱ ከቅርብ ያልመለሱት ችግር ርቆ ሄደ። ይህ በእንዲህ እንዳለ እኒያ አባት ማስት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አረፉ። በዚያን ጊዜ በሳቸው እግር የሚተካ ፓትርያርክ ለመምረጥ አስመራጭ ክፍል ተቋቁሞ ተወዳዳሪ አባቶችን አቀረበ። ይሁን እንጂ በወቅቱ ከምንጊዜውም በላይ እጅግ በጣም ድንቅ የተባሉ ተወዳዳሪ አባቶች ነበሩ። በስም ስመጥቀስ ያህል ጥቂቶቹ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የወለጋ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ፥ ብፁዕ ዶ/ር አቡነ ገብርኤል የኤርትራ ሊቀጳጳስ፥ ብፁዕ ዶ/ር አቡነ ገሪማ በሱዳን የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስና የኢትዮጵያ ክርስቲያናዊ ተራድኦ ድርጅት ሥራ አስኪያጅና ብፁዕ አቡነ ዘካርያስ የጎጃም ሊቀ ጳጳስ እንዲሁም ሌሎች የበቁ የነቁ አባቶች ባሉበት ወቅት ነበር ምርጫ የተፈፀመው።

ሆኖም እነሱ ከምርጫው ውስጥ አልታዩበትም። ቢታዩም አልቀናቸውም። ይሁንና ምርጫ የመንፈስ ቅዱስ ነው ይባል የለ? ስለሆነም ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ሆነው ተሾሙ። በምርጫውም ጊዜ ሆነ ከምርጫው በኋላ በምዕመናን እጅግ መራር ተቃውሞ ነበረባቸው። እንደሚታወቀው ሁሉ ቦታው አንድ ብቻ በመሆኑና ሹመቱም እስከ ዕድሜ ልክ ድረስ ስለሆነ ሰው የወሰነው የዕድሜ ገደብ ያለ ይመስል ሁልጊዜም ቦታውን በሚረከቡ አባቶች ላይ ችግሩ የነበረ ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ በሹመቱም ላይ ብዙም ሳይቆዩ ሦስት ዓመት እንዳገለገሉ የመንግሥት ለውጥ ሆነ። የመንግሥቱን ለውጥ አስከትሎ ከሹመቱ በፊት የነበረው ተቃውሞ

ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት 1993 ገጽ 610] ስለዚህ እንደ ስንክሳሩ ትክክለኛው አጻጻፍ መርቆሬዎስ ነው። ከእንግዲህ ወዲያ ስንጽፍ መርቆሬዎስ ብለን እንጽፋለን እንጂ መርቆርዮስ ብለን አንጽፍም።

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በሹመታቸው ምርጫ ጊዜ የነበረው ተቃውሞ ጊዜውን ጠብቆ የደርግ መንግሥት ሲወድቅ፥ ሥልጣኑን ኢሕአዴግ ሲነጥቅ ያ በየምክንያቱ ታምቆ የነበረው ተቃውሞ አገርሽቶበት በዝቶና ተባዝቶ በዚያውም ላይ የመንግሥትም ዕጅ ታክሎበት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን የሚገፈትር ማዕበል ተነሣ። ማዕበሉን ቅዱስነታቸው ሊቋቋሙት አልቻሉም። በዚያን ጊዜ ከሞት በኋላ የሚተላለፈውን የሥልጣነ ክህነት ወይንም የፕትርክና ማዕርግ በሕይወት እያሉ ይች ጽዋ ከኔ ትለፍ ብለው ጉዳዩን ሕጋዊ በሚያደርገው በሁለተኛው መልቀቂያ ምክንያት መንገድ በራሳቸው ልዩ ፈቃድ በጽኑ ስለታመሙሁ ሳገለግላችሁ አልችልምና ሥራውን ተረከቡኝ ብለው የቅዱስነታቸው እንደራሴና ሌሎችም ሊቃነ ጳጳሳት ባሉበት ለሲኖዶሱ ስንብት አቀረቡ። ከዚህ ላይ ለጥያቄ የሚቀርበው አንድ ፓትርያርክ ሥልጣኑ ወደሌለኛው አባት የሚተላለፈው ወይንም ከሥልጣኑ የሚታገደው በሦስት ምክንያቶች ብቻ መሆኑን በሚገባ ይገነዘቧል።

እነሱም፦

፩. በሥልጣን ላይ ያለው ፓትርያርክ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ፥

፪. ባለው ምክንያት በገዛ ፈቃዱ ሥራውን ሲለቅ ወይንም ሲሰናበት፥

፫. በሃይማኖት ሕፀፅና በሥነ ሥርዓት ወይንም በቀኖና ቤተ ክርስቲያን ግሣት ወይንም ጥሰት በነውር ሲነቀፍና የስሕተቱ ፈፃሚ ሆኖ ሲገኝ በቅዱስ ሲኖዶስ ጉዳዩ ተጣርቶ በሚተላለፍ ውሳኔ ወይንም ውግዘት ከሹመቱ ይሻራል ከአባትነቱም ይለያል።

ከእነዚህ ውጭ ሹመቱ ለማንም አልፋ አትሠጥም። ነገር ግን በእሥር ቤት ወይንም በግዞት ላይ ቢሆን በዓቃቤ መንበር ሥልጣኑ ተይዞ ይቆያል። ይህ ከሆነ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ እንዴት ከሥልጣናቸው ወረዱ? ይህ ጥያቄ ያለምንም መድበለበስ በግልጥ ለምዕመናን መታወቅ አለበት። ወደ ዋና ጉዳዩ ስንገባ ሥልጣናቸውን

ያስረከቡበት ምክንያት አንደኛው እንዳልሆነ ግልጽ ነው። ምክንያቱም በሕይወት አሉና ነው። እንግዲህ ሌላው ምክንያት በፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን ለቀዋል የሚለው ብቻ ሆኖ ይገኛል። ይህስ ትክክል ነወይ? አዎ ትክክል ነው። ዝርዝሩን በሚከተለው ሁኔታ እንመለከተዋለን።

እንግዲህ በተሰያዩ የቤተ ክርስቲያኒቱ መግለጫዎች ጋዜጦችና መጽሔቶች እንዲሁም ያቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔዎች ብሎም በቤተ ክርስቲያኒቱ አባቶች የተሠጡ መግለጫዎችና እንዲሁም ከራሳቸው ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ከጻፉት ደብዳቤ ጭምር በመነሣት ሥልጣናቸውን ያጡት ወይንም የለቀቁት በሁለተኛው ምክንያት በገዛ ፈቃዳቸው ነው የሚለውን እናረጋግጣለን። እሱም በሕመም አመካኝቶ በገዛ ፈቃድ ከፓትርያርክነት ሥልጣን መውረድ መሆኑ ነው። ይሁንና ይህን ውሳኔ ባስተላለፉበት ወቅት ኃላባቸውን እንዲለውጡ የተወሰኑ አባቶች ሄደው አነጋግረዋቸው ነበር። ነገር ግን በቃላቸው ጸንተው አይሆንም ብለው መልሰዋቸዋል። ይህም በሲኖዶሱ ቃለ ጉባዔ ላይ ሠፍሯል። ከዚያም በኋላ ሲኖዶሱ አምስት አምስት ሊቃነ ጳጳሳት እየሆኑ በየሦስት ወሩ እየተመረጡ እንዲሠሩ ውሳኔ አሰተላልፎ ሥራውን ሲቀጥል ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስን ግን ከሥልጣን በገዛ ፈቃዳቸው መልቀቃቸውን አምስቱ ሊቃነ ጳጳሳት ያሉበት በፓትርያርኩ እንደራሴ በብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ የሚመራና የሚከተሉት ሊቃነ ጳጳሳት፣ ብፁዕ አቡነ መቃርዮስ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስና ብፁዕ አቡነ ኒቆዲሞስ ባሉበት የሥራ አመራር ጉባዔ ተመሥርቶ በምልዓተ ጉባዔ ፓትርያርኩ በሕመም ምክንያት ሥልጣናቸውን በገዛ ፈቃዳቸው መልቀቃቸውን አጸደቁ። ይህም ውሳኔ ነሐሴ 28 ቀን 1983 ዓ. ም. በሕዝብ መገናኛ ብዙኃን ማስት በኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን ለሕዝብ ይፋ ተደረገ። ይህም ሲሆን ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የመኖሪያ ቤት፣ መኪና እስከ ሾፌሩና የጡረታ ደሞዝ ወስኖ በጎፋ ቅዱስ ገብርኤል ካለው የጳጳሳት መኖሪያ ቤት ውስጥ በክብር እንዲኖሩ አደረገ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከሦስት ወር በኋላ ደግሞ ሌሎች የሥራ አመራር ሊቃነ ጳጳሳትን ሠይሞ ሥራውን ቀጠለ። በዚያን ጊዜ የተሠየሙት፣

ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ ሰብሳቢ
ብፁዕ አቡነ ገሪማ አባል
ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ አባል [የአሁኑ የአሜሪካኑ ሲኖዶስ

ዋና ጸሐፊ]
ብፁዕ አቡነ በርናባስ አባልና
ብፁዕ አቡነ ኒቆዲሞስ የቅዱስ ሲኖዶሱ ዋና ጸሐፊ ሆነው ሥራውን ቀጠሉ።

እኒህ ሊቃነ ጳጳሳት የሦስት ወር ሥራቸውን ካጠናቀቁ በኋላ የካቲት 9 ቀን 1984 ዓ. ም. ሌሎች ሊቃነ ጳጳሳት ሥራውን ተረከቡ። በዚያን ጊዜ ብፁዕ አቡነ ያዕቆብ የሰሜን ጎንደር ህገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስን የቅዱስ ሲኖዶስ ጊዜያዊ ሰብሳቢ አድርጎ በመምረጥ ስምንት ሊቃነ ጳጳሳት በአባልነት የሚገኙበት ሌሎች የአመራር ሊቃነ ጳጳሳትን ሠየመ። ይህንኑም ሰሕዝብ ገለጸ። ፓትርያርኩ በሕመም ምክንያት በገዛ ፈቃዳቸው ከሥልጣናቸው መውረዳቸው ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን ይፋ ከተደረገ ከለድስት ወር በኋላ መሆኑ ነው። ይህ በብፁዕ አቡነ ያዕቆብ የሚመራው የሊቃነ ጳጳሳት የአስተዳድርና አቃቤ መንበር አባላት ሥራውን ከመረከባቸው በፊት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ከደጋፊዎቻቸውም ሆነ ከአማካሪዎቻቸው እንደ ፈለጉትና እንደተመኙት ወይንም እንዳሰቡት ማለት እሳቸው ሥልጣኑን ቢለቁት ከሌላው ራስ ላይ ያርፋል ብለው ባዘጋጁት ቦታ ላይ ያለመሆኑን ሲያዩና ሲመስከቱ ውሳኔያቸውን እንዲቀይሩ ኃላብ የሠጧቸው ወገኖች ነበሩ የሚሉ ክፍሎች አሉ። በዚህም ምክንያት ወደ ሥልጣኔ ልመለስ ሥራዬን ለማከናወን የሚከለክለኝ የጤናም ሆነ የሌላ ምክንያት የለምና ወደ ሥራዬ መልሱኝ የሚል ደብዳቤ በአድራሻ ለቅዱስ ሲኖዶስ ሲጽፉ በግልባጭ በወቅቱ ወይንም በዚያን ጊዜ ሰነበሩት ባለሥልጣኖች ለአቶ መለስ ዜናዊ የሽግግሩ መንግሥት ፕሬዚዳንትና ለአቶ ታምራት ላይኔ የሽግግሩ መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስቴር እንዲሁም ሰጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ የጻፉት ደብዳቤ በፊርማቸው ያቀረቡት ትክክለኛ ቅጅው ከዚህ ቀጥሎ አብሮ ቀርቧል።

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ደብዳቤ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት
ለቅዱስ ሲኖዶስ የጻፉት ደብዳቤ

ጥር 25 ቀን 1984 ዓ. ም.
ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት
አዲስ አበባ፣

በፓትርያርክነት ሥልጣን ለ3 ዓመት ከሠራሁ በኋላ በ1984 ዓ. ም. መጀመሪያ ላይ ለተወሰነ ጊዜ የነበረውን ወቅታዊ ሁኔታ በመረዳት ገለል ብዬ መቆየቴ የታወቀ ነው።

1ኛ/ ነሐሴ 20 ቀን 1983 ዓ. ም. የተደረገው የቅዱስ ሲኖዶስ ውሣኔ፣

2ኛ/ መስከረም 28 ቀን 1984 ዓ. ም. የተደረገው የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ መንበረ ፓትርያሪኬቱን እንድለቅ ተወስኖ በቁጥር 69/298/84 የተጻፈውን አስታውሳለሁ። በወቅቱ የነበረው የውዥንብር ጊዜ እስኪያልፍ መላው የኢትዮጵያ ምዕመናንና ካህናት ሁኔታውን በእርጋታ እስኪመለከቱትና እስኪያጤኑት ቅዱስ ሲኖዶስም ከታሪክና ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን አንፃር ትክክለኛውን ፍትሕ ተመልክቶ ለመስጠት የሚያስችል ግንዛቤ እስኪያስገኝ ድረስ ዕድል ለመስጠት ዘወር ብዬ መቆየት አማራጭ የሌለው ውሳኔ ነበር። ቅዱስ ሲኖዶስም ጉዳዩን የተመለከተው ከዚህ አንፃር እንደሆነ የውሳኔው ይዘት ያመለክታል።

ስለዚህ ያን ጊዜም ሆነ አሁን ከቅዱስ ሲኖዶስ አባላት ጋርም ሆነ በግል ያለብኝን መንፈሣዊ ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችሉ መንፈሣውያን ተግባራትን ከማከናወን የሚያግድ የጤናም ሆነ የሌላ ችግር የሌለብኝ መሆኑን በግልጽ የቅዱስ ሲኖዶስም አባላት በሙሉ የሚያውቁት ነው። ከዚህም ጋር ላስገንዝብ የምወዳው ቤተ ክርስቲያናችን ካሁን በፊት በአሳለፈችው የረጅም ጊዜ ታሪክ እንደምንረዳው በየወቅቱ ያጋጠማት ችግር በታሪክ ሂደት ብዙ

እንደሆነ የታወቀ ነው፤ በሁላችሁም ልቦና የተቀረጸ ነው። ወደፊትም ምን ዓይነት የታሪክ ይዘት በሀገር ውስጥም ሆነ በዓለም ዙሪያ ሊያስከትል የሚችል እንደሚኖር ዐይነ ልቡና ያለው አይሰወረውም። ይህን ከተመለከትን ዘንድ በእኔም በእናንተም ሊደርስ የሚችለውን በመካከል ከቀኖና ቤተክርስቲያን ጋር አገናዝቦ ማየትና እውነተኛ ፍትሕ መስጠት ለቅዱስ ሲኖዶስ የሚገባ መሆኑን ሁላችንም መገንዘብ ይኖርብናል።

በአጭሩ እንደገለጽኩት እኔ ያለብኝን መንፈሳዊ ኃላፊነት ለመወጣት መንፈሳዊ ተግባሬንም ለማከናወን የሚያግድ የጤናም ሆነ የሌላ ችግር የሌለብኝ መሆኑን ቅዱስ ሲኖዶስ ተረድቶ ቅዱስ ሲኖዶስ ስለዚህ ጉዳይ ያለውን አቋም በአስቸኳይ ይገልጽልኛል በማለት እጠባበቃለሁ። ወደመንበሬም እንድመለስ ውሳኔውን እንዲያስተላልፍልኝ በመጠባበቅ ይሽን ማስታወሻ አቀርባለሁ።....

«እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ።»

ፊርማ

አባ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ
ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ABBA MERKORIOS
PATRIARCH OF ETHIOPIA

ግልባጭ

ለክቡር አቶ መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ፕሬዚዳንት

ለክቡር አቶ ታምራት ላይኔ
የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስቴር

ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ

አዲስ አበባ፣

ቀጥሎም በየዓመቱ በሚደረገው የርክበ ካህናት የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባ በግንቦት ወር 1984 ዓ. ም. ቅዱስ ሲኖዶሱ ባደረገው ምልዓተ ጉባዔ በድጋሚ ብፁዕ አቡነ ያዕቆብን አቃቤ መንበርና የሲኖዶሱ ሰብሳቢ አድርጎ ሠየማቸው። በዚህ ወቅትም መንበረ ፓትርያርኩ ከነሐሴ ወር 1983 ዓ. ም. ጀምሮ ያለአባት በመሆኑ ተተኪ አባት መመረጥ ያለበት መሆኑን ሲኖዶሱ ወሰነ። ቀጥሎም በግንቦት ወር ውስጥ ጠቅላላ የኢትዮጵያ ሊቃነ ጳጳሳት የሆኑ በሙሉ በሀገረ ስብከት ሳይወሰኑና በደርግ ጊዜም በውጭ ያሉትን ሁሉ ጨምሮ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሊቃነ ጳጳሳት በአጠቃላይ እንዲገኙ ጥሪ አስተላለፈ። ሁሉም በጥሪው መሠረት ተገኙ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስና ሌሎችም ከኢትዮጵያ ውጭ ይኖሩ የነበሩት ሁሉ በዚያ ጥሪ መሠረት ወደ ኢትዮጵያ ሄዱ። በዚያን ጉባዔ ላይ ትልቁና ዋናው የመነጋገሪያ ርእስ ስለተተኪው ፓትርያርክ ምርጫ ነበር። ይህን በተመለከተ የአስመራጭ አባላት ቅዱስ ሲኖዶሱ ሠይሞ አሥር ሊቃነ ጳጳሳትን ለተወዳዳሪነት አቅርቦ አስመራጭ አባላት ደግሞ ከአሥሩ አምስት በሙያ በአመክሮ በእድሜም ዊምር አጣርተውና መርጠው እንዲያቀርቡ ቅዱስ ሲኖዶሱ መመሪያ ሠጠ። ከዚያም ሊቃነ ጳጳሳቱ ከመካከላቸው አሥር ሊቃነ ጳጳሳትን ለምርጫው ተወዳዳሪነት መርጠው አስመራጭ ጉባዔ ሠየሙ። በውሳኔውም መሠረት ለምርጫ የሚቀርቡትን ከአሥሩ አምስቱን የሊቃነ ጳጳሳት ችሎታ ዕድሜና አገልግሎት ባካተተ መልኩ ቅዱስ ሲኖዶሱ መለኪያ አውጥቶ ለአስመራጭ አባላት ሥራውን አስረከበ። ይህ የአስመራጭ ጉባዔ ከተጠቆሙት አሥር ሊቃነ ጳጳሳት መካከል አምስት መርጠ ለፓትርያርክነት አቀረበ። በዚሁም መሠረት የተወዳዳሪዎችን የሕይወት ታሪክ በመመርመር እድሜ ችሎታና የሥራ ፍሬ ሁሉ ግንዛቤ ውስጥ አካቶ አምስት ሊቃነ ጳጳሳትን ለምርጫ አቀረበ። እነሱም፡

አንደኛ ብፁዕ አቡነ ጳውሎስ
ሁለተኛ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ
ሦስተኛ ብፁዕ አቡነ ኤልሣ
አራተኛ ብፁዕ አቡነ ሰላማና
አምስተኛ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ነበሩ።

ምርጫውም ሰኔ 8 ቀን 1984 ዓ. ም. እንዲደረግ ተወሠነ። በዚሁ ምርጫም ሊቃነ ጳጳሳቱ፡ የአዲስ አበባ አድባራት፡ የሰበካ

ጉባዔ፡ የአጎራባች ስብከቱ ሥራ አስኪያጆችና የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበራት ተወካዮች በተካፈሉበት ምርጫው ተካሄደ። ለምርጫ ከቀረቡት ሊቃነ ጳጳሳትም መካከል በድምፅ ብልጫ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ አንደኛ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ሁለተኛና ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል ሦስተኛ በመሆን ተመረጡ። ይህ የሆነውና የተፈፀመው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በሕመም ምክንያት ሥልጣናቸውን ነሐሴ 28 ቀን 1983 ዓ. ም. ካስረከቡ ከአሥራ አንድ ወር በኋላ ነበር። ከዚያም የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አፅም ከተቀበረበት ቦታ ተፈልጎ ተገኝቶ የመጨረሻውን ዕረፍት ሐምሌ አራት ቀን አሥራ ዘጠኝ መቶ ሰማንያ አራት ዓ. ም. ከተፈፀመ በኋላ በበነገታው ሐምሌ 5 ቀን 1984 ዓ. ም. የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ሢመተ ፕትርክና የአሪየንታልና የሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት በተገኙበት በኢትዮጵያውያን ሊቃነ ጳጳሳት ተከናወነ።

ይህ ጉዳይ አሁን ከአሜሪካ ውስጥ ከሚገኙት የቀድሞው ሲኖዶስ አባላት ሊቃነ ጳጳሳት አሜሪካ እስከገቡ ድረስ ምንም ዓይነት ተቃውሞ አልነበረም። እንዲያውም አንድ ከቦታው ያልተገኙ ሊቀ ጳጳስ አሁን ከውጭ ካለውና በውግዘት የተለየው ሲኖዶስ አባል የሆኑ «የእንኳን ደስ ያለዎት ቴሌግራም» ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ማስተላለፋቸውን በብፁዕ አቡነ ይስሐቅ *የመፍትሔ ጥሪ* በተሠኘው መጽሔት ገጽ 4 ላይ 1993 ተጠቅሷል። ይህ በእንዲህ እንዳለ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው አስረክበው ከዚሁ ቦታም ለሁለት ዓመት ጊዜ ከቆዩ በኋላ አሁንም በራሳቸው ፈቃድ በሥውር እንደማንኛውም ሰው ወደ ኬንያ ገብተው የፖለቲካ ጥገኝነት ጠይቀው ለተወሰኑ ዓመታት ያህል ናይሮቢ ኬንያ በስደት ቆዩ። ከዚያም አሜሪካ ባሉ ኢትዮጵያውያንና ቀደም ሲል አሜሪካ በገቡትና በነበሩት በብፁዕ አቡነ ይስሐቅ፡ በብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅና በብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ አማካይነት ወደ አሜሪካ ገቡ።

በወቅቱም የምዕራብ አገሮች ሊቀ ጳጳስ በነበሩት ከአቡነ ይስሐቅ ጋር ሆነው ተቀራርበውና በአንድነት ለመሥራት ማንሃተን ኒው ዮርክ ባደረጉት ስብሰባ ተስማምተው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ አስተዳድር ሥር ሆነው ለመሥራት ፈቃደኛ ያለመሆናቸውን በሠጡት ጋዜጣዊ መግለጫ አረጋገጡ። ኒው ዮርክ ታይምስ ጋዜጣም መስከረም 21 ቀን 1991 ዓ. ም. እንደ አውሮጳ አቆጣጠር መለየታቸውን ገለጸ። ከዚህ በኋላ ቅዱስ ሲኖዶሱም በአራቱ ሊቃነ ጳጳሳት ላይ ውግዘት ጣለ። ይህንኑም ጳጉሜን 2 ቀን

1985 ዓ. ም. የውግዘቱን ቃል ለሚመለከታቸው ሁሉ በሲኖዶሱ ጸሓፊ በብፁዕ ዶ/ር አቡነ ገሪማ ፊርማ አስታወቀ። ይሁን እንጂ የውግዘት ደብዳቤው ንስሐ ገብተው ቢፀፀቱና ቢመለሱ በሩ ፈጽሞ ያልተዘጋባቸው መሆኑን ያመለክታል።

ይሁን እንጂ ከጊዜ በኋላ የስደት ሲኖዶስ እናቋቁም ብለው ሲነሱ ብፁዕ አቡነ ይስሐቅ ሲኖዶስ አንድ ነው በዚህ አልስማማም ማለታቸውን «በህገረ ስብከቱ ሲተፈጠረው ችግር የመፍትሔ ጥሪ» ኒው ዮርክ ሚያዚያ 1993 ዓ. ም. ከገጽ 5 – 7 እንዳሠፈሩት ከእነሱ ጋር በኅሳብ አንደማይስማሙና ሁለተኛ ሲኖዶስ ብሎ ማቋቋም ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ በመሆኑ ያለመስማማታቸውን ገልፀው ተለይተዋቸዋል። ይህንኑም በመጽሔቱ ላይ በሠፈው ታትቷል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ሥልጣናቸውን ከለቀቁና በፈቃዳቸው ካስረከቡ በኋላ ሁለት ዓመት ከዚያው ከአዲስ አበባ ከተሠጣቸው ቤት ውስጥ ቆዩ። ከዚያም በድንገት ከነበሩበት ቦታ በሥውር በመለከረም ወር 1985 ዓ. ም. ሁሉንም ጣጥለው ወደ ኬንያ ገቡ። እንዲያው ቢያዙ ኖሮ ያ የፈሩት ሞቱ ባይሆን እሥር ቤቱ ይቀርላቸው ነበርን? ወደ ጎጃምና ጎንደር መሥመር እንኳ አልነበረም ጉዞው። ከዚህ ገዳም ልሳለም ወይንም ልባርክ ወደማይባልበት አቅጣጫ መዝመት በራሱ ጠንካራ አድርጎ ያሳያል። ምክንያቱም ግማሹ ግምለጥ ቢኖርበትም በግማሹ ደግሞ መያዝና መታሠርን ያስከትላል የሚለውን ወዴት አስቀምጠውት ነበር? ያም ሆነ ይህ የተፈፀመው ድርጊት አርዓያነቱ እጅግ አሰቃቂ ነው። ለቤተ ክርስቲያኒቱም እጅግ ዘግናኝ ዜና ነው። የእነ ቅዱስ ጊዮርጊስን ገድል ጠንቅቆ የሚያውቅ የራሱ የለማዕቱን የቅዱስ መርቆሬዎስን ተጋድሎ ያነበበና በስሙም የሚጠራ አባት የወሰዱት ርምጃ ሲሆንና ሲደረግ የማያገባው ፍፁም ልዩና አስደንጋጭ ተግባር ነው።

ይህም ሆኖ እያለ በመፈንቅለ መንግሥት ያውም «በኩዴታ» ወረዱ እየተባለ ሌሎች ሲናገሩ ለንለማ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ሳይሆን እግዚኦ ማራቸው ይቅር በላቸው ዓርባ ዘጠኝ ጊዜ የሚያሰኝ ነው። ምንኩስናው ቃል ኪዳኑ መሀላው ሁሉ እንዴት ከቤተ ክርስቲያን ጓሮ ተጠቅሎ እንዳለ ይቀበራል? መቼም የቤተ ክርስቲያኑን አቀማመጥ ሰንመለከት የቤተ ክርስቲያኗ ቅጽር የሙት መጣያ መሆኗ ነው። እንዲያው ይባስ አታምጣ ነው እንጂ ከገዳማቸው ከምንኩስና ሕይወታቸው የወጡና አካኪ ዘራፍ ያሉስ ዛሬስ በስማቸው ድርጅት ያውም የሃይማኖት መሥርተው በስማቸውስ የሚጠሩስ አሉ አይደል። ለዚህም ተጠቃሽ ሆኖ የሚታወቀው የመጀመሪያው አባ ወይንም ፋዘር ማርቲን ሉተር

በኋላም አቶ ማርቲን ሉተርስ አለ አይደል? እንዲያው እንኳን እንዲያ አላደረገው ብሎ ተመስገን ያሰኛል ያሁኑን ከዚያ ጋር ሲያወዳድሩት የሚሉ አሉ። ሌሎቹ ደግሞ በኃላቡ ተለይተው እንዲያውም በአፈጻጸሙ ተበሳጫተው በቁርጡ የሉተር አቋም የተሻለ ነው። የእሱ ተቃውሞ በቀጥታ እምነቱ ተጎሳቆለ ነበር። የኛዎቹ ግን ሥልጣናችንን ብንጥለውም መልሰን የመውለድ መብት ተከለክልን ብለው ነው። ለግል ክብር ለግል ልዕልና እንጂ ለቤተ ክርስቲያኗ አንድነት ለሕዝበ ክርስቲያኑ ድኅነት ብለው አይደለም። እንዲያውም ይባሱኑ የፈፀሙት ድርጊት በራሳቸው ላይ ትዝብት፥ ለቤተ ክርስቲያኗም ውርደት፥ ለምዕመናኑም ንቀት ነው።

ገና ደርግ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ያረዳትና የገደላት አሁን ነው። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን ባያሾም ኖሮ መቼ ይህች ብሔራዊትና ጥንታዊት የእምነት መሠረት ኢትዮጵያ እንዲህ በጥልና በከርከር ትታወክና መዘባበቻ ትሆን ነበር። ምዕመናን ተደናግጠናል። እጅግ አዝነናል። አልቅሰናል። ዙሪያችንን በጸንጠ መጤ ሃይማኖት ምስቅልቅላችን እየወጣ ለጊዜው ሌሎችን ትተን ነው። በዚሁ በጸንጠ ልጆቻችንን እያስነጠቅን ባለንበት ዘመን እንዴት እንዲህ ከመሃል ሜዳ ጥለውን ጣጥለውን ይጠፋሉ? ይሠወራሉ? አሜሪካ ለፖለቲከኞች ስደተኞች መሥፈሪያ እንጂ የአባቶች ገዳም መቼ ሆኖስ ያውቃል። መቼም እጅግ ዝቅ የሚያደርግና አንገት የሚያስደፋ ሥራ ነው። ለዚህ ሥራ ተባባሪ የሆናችሁ ሁሉ የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ባይከሳችሁና ባያወቅላችሁ የኢትዮጵያ ታሪክ ይፋረዳችኋል። እነ ደጃዝማች ዘርዓይ ድረስ ከሮማ ከተማ ምን ሠሩ? ምን ፈፀሙ? ጣሊያኖች የኢትዮጵያን ለንደቅ ዓላማ ሲረግጡና መሳለቂያ ሲያደርጉ እኒህ ጀግና ተመልከተው አያደለምን ሠይፋቸውን የመዘዙባቸው? *[ዘይዓይ ድረስ፣ በአንተነህ መሠረት ንግድ ማተማያ ቤት አዲስ አበባ* 1957 ገጽ 37] ዛሬ እናንተና እርስዎ ባሉበት ከተማ ከፊት ለፊትዎ ላይ ታቦትን ዳጎን ነው ብለው ሲሰድቡብዎት ምን መልስ ሠጡ? ምንስ አሉ? በገዛ አገራቸው እንደፈለጋቸው ቢሆኑስ ነውን? ሌላውን ደግሞ ሌላው ያጨነቅበት። ይህ ከሆነ ሥራው ሲኖዶሱ ተዋረድንበት አፈርንበት ተሸማቀቅንበት እጅግ ምርር ያለ ልቅሶ አሰማንበት እንልዎታለን። ምዕመናን እግዚኦ እንበል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ኢትዮጵያን ትተው ከወጡ በኋላም በመጀመሪያ ኬንያ ከዚያም አሁን አሜሪካ ውስጥ ይገኛሉ። ከዚህ ላይ ከቅዱስ ሲኖዶሱ ጋር ችግር የተፈጠረበቱ ጉዳይ አሜሪካ አገር ሲኖዶስ ከተቋቋመ በኋላ የመጣ እንጂ መጀመሪያ በፈቃዳቸው

ሥልጣኑን የለቀቁት በመሆኑ ያልተከሠተ ችግር ነበር። አሜሪካ አገር ሲኖዶስ ከተቋቋመ በኋላ «ሕጋዊው ፓትርያርክ እኔ ነኝ» ሲሉ ሌሎችም አብረው ካቋቋሙት ሊቃነ ጳጳሳትም አዎ እላቸው ናቸው በማለት ሁሉም አደመቁት። በዚህ መልኩ አሥራ ሦስት ዓመት ካለፈ በኋላና በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ አይሾምም የተፈፀመው የክህነት መፈንቅለ ሥልጣን ወይንም ግልበጣ ነው ማለቱ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ ሲነገር ከቆየ በኋላ በቅርቡ አሥራ ሦስት ኤጲስ ቆጳሳትን አሜሪካ በተፈጠረው የስደተኛው ሲኖዶስ መሪ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ተሾሙ።

የምዕመናን ጥያቄ በከፍተኛ ደረጃ አየነላ መጣ። አውነቱን የሚመሠክር ሰው ተፈለገ። ምስክርነቱ እንደሰሚውና እንደተቀባዩ ማንነት ቢለዋወጥም ቅሉ ምዕመናኑ የሚሰሙት የተዘበራረቀ ሆነባቸው። እውነቱና ትክክለኛው ሁኔታ አልተገለፀላቸውምና ነው። ጉዳዩ በጣም አሳዛኝና አሰቃቂም ቢሆንም ቅሉ የሆነው ከላይ እንደተገለፀው ነው። ነገር ግን ከኢትዮጵያ ከወጡ በኋላ እኔ ነኝ ሕጋዊው ማለቱ መጀመሪያ ላይ ቀረ። ያችን ቀን ያለምንም ፍርሃት በቆራጥነት ከሚሙቴ ወይ ፍቅቅ ወይ ንቅንቅ ቢሉ ኖሮ ውጤቱ እንደሚሉት ወይ እሥራት ወይንም ግፋ ቢል ሞት ቢሆን አንኳ ለመቀበል ዝግጁ መሆን ነበረባቸው። ያም ላይሆን ይችል ነበር። ከሆነም በፀጋ መቀበል ነበር። ነገር ግን ያች ሰዓት ያች ጊዜ ያች ቀን አልተደፈረችምና አባባላችን ሁሉ መላ ምት ሊሆን ነው። አባታችን ግን ሥልጣናቸውን ያላንዳች ሁከት ያለሞት ወይንም ያለ እሥራት በሰላም ከተሰናበቷትና ከተሰይዋት በኋላ ናፈቀችኝን ምን አመጣው? አበው እንደሚሉት «የፈሰሰ አይታፈስ፥ የተተፋ አይላስ» መሆኑን ዘንግተው መልሰው ሚመቷን ፍለጋ መግባት ውጤቱ በምዕመናኑ ላይ መብራት ማጥፋት ነው። የቤተ ክርስቲያኗንም ታሪክ ማጉደፍ ነው። አንድ የቤተ ክርስቲያኒቷ ታላቅ ምሁር በተፈጠረው ሁኔታ ተጠይቀው የሠጡት መልስ «ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ አንዲህ ዓይነት አቋምና ፍላጎት ከነበራቸው ሰዓቷን አባክነዋታል። ሞትም ቢሆን መቀበል ነበረባቸው። ቢሞቱ አብረናቸው የምንሞት ነበርን» በገዛ ፈቃዳቸው አሳልፈው የሠጧትን ሥልጣን አለኝ ነበረኝ ማለቱ በአሁኑ ጊዜ ለቤተ ክርስቲያኗ መልካም አይደለም። ምዕመናንንም ግራ ማጋባት ነው ብለዋል።

የቀደሙ አባቶች መከራና ፈተና በገጠማቸው ጊዜ ምን አደረጉ? እንዴትስ ተወጡት? የሚለውን ታሪክ ስንመረምር የሚከተሉትን መልሶች እናገኛለን። በቅድሚያ የኢጣሊያን ፋሽስት

ኢትዮጵያን በወረረ ጊዜ በብርታትና በጽናት የሚታወቁት ሰማዕቱ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስን ገድል እናነባለን። ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ ፋሽስት ኢጣሊያንን ኮንነው የኢትዮጵያ ሕዝብና መሬቷም እንዳትገዛለት ብለው አውግዘው ለመድፍ ጥይት ራሳቸውን መሥዋዕት አቀረቡ። ዛሬ ለቤተ ክርስቲያናችን ክብርና ኩራት ሆነው መታሰቢያ ቆሞላቸው የምናያቸውና የምንመሰክታቸው አባት ናቸው። አንዲያም አሁን በቅርቡ ከተወለዱበት ከተማ ፍቼ በስማቸው ቤተ ክርስቲያን አየታነፀላቸው ነው። ከዚያም አልፎና ተርፎ ስዊድን ውስጥ ሳይቀር በስማቸው ጸሎት ቤት ተቋቁሞላቸው መገኘቱን «ይግባኝ ለክርስቶስ በብፁዕ አቡነ ቀውስጦስ 1999 መጽሐፍ እያነበብን ነው። ለቆራጥና ጽኑ አባት መታሰቢያው እንዲህ ቋሚ ነው። ሰማዕቱ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ በደማቸው የኢትዮጵያን ክብር አስጠብቀዋል። የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሞታቸው ስክብር ነውና በደማቸው የአገር አንድነት ተጠበቀች የነፃነት ፍሬም ተለቀመች። ቤተ ክርስቲያንም ከበረች። በታሪካችን መኩሪያና መመኪያ በማግኘታችን የዚች ታላቅና ቀጥተኛ ቤተ ክርስቲያን ልጆችም መኩሪያ አገኘን ሆኑንም።

ይህ በእንዲህ እንዳለም ታሪክ ራሷን ትደግማለች ነውና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስም የለማዕትነት ጽዋን በክብር ተቀብለዋል። የቅዱስነታቸው አርዓያነት ለሃይማኖታችን ጽናት በመከራና በፈተና ጊዜም ብርታት ሆኗል። ቅዱስነታቸው ላይ ፈተናዎች ባንዣበቡባቸው ጊዜ በቅርብ የሚያውቋቸው ሁኔታው ጥሩ አይደለምና ይህ የመጣው መቅሠፍት አስከሚያልፍ ድረስ ዘወር ብለው እንዲቆዩ በማለት ወደ ውጭ አገር እንዲሄዱ ምክር አቅርበውላቸው ነበር። ይሁን እንጂ ቅዱስነታቸው የሠጡት መልስ እንዲህ ነበር።

«እኔ ከዚህ ደረጃ የደረስኩት ከትቢያ ተነስቼ ነው። በሰላሙ ጊዜ ስሾም ስሸለም አባታችን አባታችን እየተባልኩ ስከበር ኖሪያለሁ። ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ከንጉሠ ነገሥቱ ጀምሮ ያሉት ታላላቅ ሰዎች አየታሠሩ ያለፍትሕ እየተገደሉ ነው። አኔም እንደእነሱ በዚሁ በሀገሬና በቤተ ክርስቲያኔ ስም የሚደርስብኝን ማናቸውንም መከራ መቀበል እንጂ መሸሽ ተግባሬ አይደለም። አባቶቼ ሐዋርያትና ሰማዕታት ስለ አውነትና ስለ ቀናች ሃይማኖታቸው ሲሉ በሰይፍ ተቆርጠው በገመድ ታንቀው በእሳት ተቃጥለው በሰማዕትነት ተሠውተዋል። እኔም እንደነሱ ስለ ኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ክብር ስል አስክሞትም ድረስ ቢሆን መከራና ሥቃዩን ከመቀበል በቀር ወደኋላ የምልበት

ምክንያት የለም። ቀደም ሲል በእነ አቡነ ጴጥሮስ ላይ የደረሰው የሰማዕትነት ሞት እኔም ቆርጨ የእነሱን ጽዋ እንድቀበል እንጂ እንድሸሽ አይገፋፋኝም። ለእኔ ሕይወት ስል በብዙ ድካም የተገኘውን የቤተ ክርስቲያንን ክብር አሳዋርድም በአንገቴ ላይ ለለት አያንጣበበ እንደሆነ ይታወቀኛል። ቢሆንም እዚህ ሆኜ የሚመጣብኝን መከራ ለመቀበል ዝግጁ ስለሆንኩ በምንም ተአምር አልሸሽም።» *[ሰማዕቱ ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ መጽሔት ገጽ 37 ሐምሌ 4 ቀን 1984 ዓ. ም. አዲሰ አበባ]*

ይህን የመሰለ አርዓያ ተቀምጧል። ታዲያ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የወሰዱትን ምርጫ በግለሰብ ደረጃ አናከብርላቸዋለን። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ታሪክ አንግር ግን አናወግዘዋለን። ለመሐበቅ ለመንክባከብ በመሐላ የተቀበሏትን ቤተ ክርስቲያን ከሞት በስተቀር የሚለየኝ የለም ብለው የገቡት ቃል ኪዳን እንዴት ይጣሳል? እንዴትስ የትም ይወረወራል። ይህማ «ከሥጋው ጸመኛ ነኝ ከመረቁ አውጡልኝ» ማለት ነው። አሁን ችግር የፈጠረውና ግራ ያጋባው አስካሁንም ድረስ በጸሎት ላይ ነበሩ ችግርም አልተፈጠረም ማለት ባንችልም ቅሉ በአሜሪካ አገር «ስደተኛው ሲኖዶስ» በሚል ስም መንበር ፈጥረው ቢንቀሳቀሱም ቅሉ እናት ቤተ ክርስቲያንን ብዙም አልተደፋፈሩም ነበር። ይሁንና ቆየት ብሎ በስደተኛ ሲኖዶስ ስም «ሕጋዊው ፓትርያርክ» የሚል ቅጽል ተሠጥቷቸው አሱንም ተቀብለው መንቀሳቀስ ጀመሩ።

ምንም እንኳ «ሕጋዊ» የሚለው የስም ቅጽል ለመአስባን ማለት ሚስት ባላቸው ቀሳውስት የሚሠጥ እንጂ ለደናግላን አይደለም። የቋንቋ ዳሕፀ ልሣን ነው። ሆኖም የቃሉ አጠቃቀም ትክክለኛ ያለመሆኑን ለመግለጽ ነው። ተደጋግሞ ስለሚነገር ስሕተቱ ወደ ትክክለኛነት እንዳይለወጥ በመስጋት ነው። ቅዱስነታቸውም በየበዓላቱ ቀናት በሚሠጡት ቃለ ምዕዳን «አባ መርቆሬዎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ» ብለው ማንነታቸውን ገልፀውና አረጋግጠው ይሰናበታሉ። ለብዙዎቻችን የተረዳን ምንም እንኳ ሥልጣን ላይ ባይሆኑም በሕይወት እስካሉ ድረስ በሙ አንድ ጊዜ ከተሠጠ በጥፋት አስካልተሻረ ድረስ መጠሪያነቱ ቀጣይነት ያለው በመሆኑ ነው ብለን አስበን ነበር። ለካስ ቅዱስነታቸው ከልብና አምርረው ተነሥተው ኖሯል። ይህ ለብዙዎቻችን ግልጽ አልነበረም። እንደምናውቀው አንድ ወታደር ጄኔራል ሆኖ በጡረታ ቢለናበት የማዕርግ ስሙን እስክ ሞት ድረስ ከዚያም በኋላ ሲጠራበትና ሲታወቅበት እንደሚኖር ስለምናውቅ ነው። በዚህ ኃሳብ ላይ ራሷም ቤተ ክርስቲያኗ ስማቸውን ሳታነሣ ማለት ሳትሽር እስክ

ጥር 27 ቀን 1999 ዓ. ም. ድረስ በአክብሮት ይዛቸው እንደነበር የትናንት ትዝታ ነው።

አሁን ግን ቅዱስነታቸውም አምርረው አቋማቸውን ግልጽ አድርገው ሌሎችን ኤጲስ ቆጳሳት ሾሙ። በዚህን ጊዜ ቤተ ክርስቲያኗም የማዕርግ ስማቸውን ቀማቻቸው። እንዴትም ሥልጣናቸውን እንደለቀቁ ጉዳዩ ይፋ ተደረገ። ከዚህ በኋላ ቤተ ክርስቲያኗም ብቻ ሳትሆን ምዕመናንም ታላቅ ድርሻ ይኖራቸዋል። አሁን በተፈጠረው ሁኔታ በአሜሪካ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ራሱን የቻለ ከእናት ቤተ ክርስቲያን ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌለው ልዩ በታሪካችን ያልታዩ በእነዚህ አባቶች የተፈጠረ ሀገረ ሲኖዶስ ተቋቋመ ማለት ነው። ይህ ድርጊት የአሜሪካው ሲኖዶስ ከተቋቋመና ሹመት ከቀጠለ ሌሎችስ? የፈለገ ማለት አይደለምን? ዞሮ ዞሮ የሚንደውና የሚያፈርሰው ይችኑ ጥንታዊቷንና ብቸኛይቷን ቤተ ክርስቲያን ነው።

ከእንግዲህ በኃውን ማሰብ እንተውና ነገ ደግሞ በየፈርጁ ሊሾምና ሊያውጅ አይደለምን? «ጎደኛህ ሲታማ ለእኔ ብለህ ስማ» እንደተጠበቀ ይሁንና። የንንደር ሕዝብ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ፣ የሸዋና የመላ ኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ፣ የአሮሞ ሕዝብ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ፣ የአማራው ሕዝብ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ፣ የአፋርና የሶማሊያ ሕዝብ ፓትርያርክ፣ የጋንቤላና የቤንሻንጉል ሕዝብ ፓትርያርክ ከዚያም በከፋና በሌሎችም እንዲሁም መልኩን ለውጦ የአርቶዴንጤ ፓትርያርክ ወዘተርፈ .... ሊሾሙ ነው። «ወፈነወሙ በበነገዶሙ» በየነገዳቸው ላካቸው። ሊሆን ነው። በዚያን ጊዜ ነው ይህች ጠንካራና ብርቱ የአገር ምሰሶ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን እንዳልነበረች የምትሆነው። «የዘፈን መጀመሪያው እስክስታ ነው።» ከበሮው ይመታል አቀንቃኙ ግጥም ያወጣል ይህ አይደል እንግዲህ ዘፈን የሚባለው? ወይንስ «ውህ ሲወስድ እያሳሳቀ» መሆኑ ነው።

አሁን በሰሜን አሜሪካ «የስደተኛው ሲኖዶስ» እየተባለ በመጠራት ላይ ያለው የቤተ ክርስቲያኗን ግድግዳ አልቀደደውም? በሚገባ ነድሎታል። ማን ማን ይሆን የሚገባበት? ይህን ዘወር ብለው ተመልከተውታልን? እኔስ ሰጋሁ ፈራሁ ተንቀጠቀጥሁ አለቀስሁም። ለመሆኑ በአሜሪካ በካናዳ በካሪቢያን በአውስትራልያ በአውሮጳና

በአፍሪቃ ያሉት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት አመሠራረት እንዴት እንደሆነ ግንዛቤ ወስደን እናውቃለን? ብዙዎቻችን እንኳን ይህን የመለለውን ጥቅንጥቅ ልናውቅ ቀርቶ በለሞኑ ግርግር በተነሣው አሜሪካ ውስጥ ስለተደረገው የኤጲስ ቆጳሳት ሹመት ብዙ ምዕመናንን ድርጊቱ አልገባቸውም። የሚያስረዳቸውም ትምህርትም የሚሠጣቸውም አልተገኘም። ትክክለኛው ይህ ነው የሚል የለም። ይህን ለማለት ያስገደደኝ የኢትዮጵያው ሲኖዶስ ውግዘት አስተላልፏል። ወደየትኛው ቤተ ክርስቲያን መሄድ አለብን ተብሎ ለቀረበ ጥያቄ በአካባቢው ወንጌልን የሚሰብኩ ሰባኪ የሠሩት መልስ ጉዳዩ በውይይት ላይ ነው ወደፊት እስከሚገለጽ ባላችሁበት ቆዩ ነበር። ውይይቱ አልቆ ጳጳሳት ተሹመው በዚህም ምክንያት ውግዘት ተላልፎ ቆዩን ምን አመጣው? ለምን የተፈፀመውን ሁኔታ መግለጹ ምኑ ላይ ነው ክብደቱ። ታመሃል ግን በሽታው እስኪሠራዊና እስከሚገድልህ ታገሰ ማለት አይመስልምን? የሚሠጠው መልስ? አዎ አዎ ወይንም አይደለም አይደለም መሆን ሲገባው በይሉኝታ ውንጥውንዝ መጫወት ታላቅ በደል ነው። ራስንም ሥራውንም ያለጠባቂ ጥሎ መሄድ ነው። ይህ ደግሞ ለሥራ እንቅፋት መሆን ነው።

ይህ ጥያቄ ብዙ ነገር አሳየኝ። ምን ያህል የኛ ክርስቲያኑ ወገን ምንም ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን ወይንም ቀኖና ቤተ ክርስቲያን እንደማያውቅ ነው። ሊያውቅ ቀርቶ ለነገሩማ ከቤተ ክርስቲያንም የሚሄደው የፋሲካ የልደት ወይንም የገና የጥምቀት ያመት በዓል ለማክበር፤ ልጅን ክርስትና ለማስነሳት ወይንም በተክሊል የሚያገቡትን ለማጀብና ለው ሲሞት ደግሞ ለቀብር ወይንም ለፍትሐት ከቤተ ክርስቲያን መገኘት እንጂ ከዚያ ውጭ አብዛኛው ወደ ቤተ ክርስቲያን አይሄድም። የሚሄደውም ብዙም አያውቅም። ይህን እንዳለ ይዘን በአሁኑ ለዓት በተለይም በካናዳና በአሜሪካ ያሉትና ተቋቁመው የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት አመሠራረት ግንዛቤ አለን? የምናውቀውስ ይኖራልን? እስቲ ገባ ብለን እንመልከታቸው።

በአሜሪካ ማለት በዩናትድ ስቴትስ አፍ አሜሪካ በሃያ አምስቱ ክፍላተ አኅጉር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስም ተቋቁመው የሚገኙ ሰባ ሁለት አብያተ ክርስቲያናት መኖራቸው ታውቋል። [ዶ/ር ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ *የምዕራባውያን ሥልጣኔና ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ ማኅበራዊና ሥነ ልቡናዊ ትንተና* 1999 ከገጽ 286 - 289።] እነዚህ ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ጠብቀው ከጥቂቶች በስተቀር

የተቋቋሙ አይደሉም። ሰባክያኑም በቤተ ክርስቲያኗ የተላኩም አይደሉም። ቢኖሩም እጅግ ጥቂቶች ናቸው። ከዚሁ ከተቋቋሙት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በሚመሩት በስበካ ጉባዔ አባላት ግብዣ ቪዛ አግኝተው የመጡ ካህናት ናቸው። እነሱም ከሚመሪጡበት መመዘኛዎች ውስጥ በሰበካው ጉባዔ አባላት የሚታወቁ ወይንም መቀደስና ማስተማር የሚችሉ መሆናቸው ተጠይቆ ነው። ከዚያ ውጪ ስለ ሥልጣነ ክህነታቸው ስለሙያቸውና ስለ ችሎታቸው የተመዘከረላቸው ለመሆኑ የቤተ ክርስቲያኒቱ ባለሥልጣናች አውቀው ፈቅደውና መርጠው የላኳቸው አይደሉም። እኒህም ካህናት ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለሰበካ ጉባዔው ብቻ ነው። የሰበካ ጉባዔውም ካልፈለጋቸው የሚያባርራቸው ባለደሞዝና ምንደኛ እንጂ በካህንነታቸው ይህ ይደረግ ይህ ይሠራ የሚሉት ጉዳይ ፈጽሞ የለም። ለለዚህ በቀጥታ ጥገኛ የሆኑ ናቸው ማለቴ ጉዳዩን አሟር ያደርገዋል። በዚህ ሁኔታ የመጡ ካህናት መግባባት ሲያቅታቸውና ምርጫ ሲያጡ ለብሰውት የመጡትን ቀሚስና ቆብ አውልቀው ጥለው እንደማንኛውም ስደተኛ ወይንም ኗሪ ባገኙት የሥራ ፈቃድ ተጠቅመው ኑሯቸውን ይቀጥላሉ። ይህን ያደረጉና የሚያደርጉ ጥቂቶች አይደሉም። ይህ ሁሉ ዝብርቅርቅ የተፈጠረው በምን ምክንያት ነው? ያልን እንደሆነ ከላይ በሠፈው በገለጽናቸው ራሳቸውን ለዚች ቤተ ክርስቲያን ባላስገዙ ራስ ወዳዶችና ጽናት በተለያቸው በቤተ ክርስቲያኒቱ ስም የሚጠቀሙ በተለያየ ደረጃ ባሉ የለበካ ጉባዔ አባላትና ካህናት ነው። «የገበያ ግርግር ለቀጣፊ ያመቻል» እንዲሉ የተለያዩ ድርጅቶች ወገንተኞች [ዜጌዎች] በግልጽ ቋንቋ ግን ዘረኞች የፖለቲካ ድርጅቶች ዕጅ ቤተ ክርስቲያኗ በመውደቋ ነው።

እንግዲህ ለእኒህ ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት አሰገኝ እነማን ናቸው? ብለን ስንጠይቅ ከላይ የተገለጹትን ገፀ ባሕርያት በግልጽ ቁልጭ ብለው እናያቸዋለን። አሁንም በድጋሚ እነሱ እነማን ናቸው? ከተመደቡበት የሥራ ገበታ በጥላቻና በፍርሃት ጥለው በመጡ አባቶች የተቆረቆሩ፤ ቤተ ክርስቲያኗን ተጠግተው ለጠላቶቻቸው ጉድጓድ በሚቆፍሩ የፖለቲካ ድርጅቶች፤ በዘር በነገድ በወንዝ በተመረዙ የአእምሮ እውራን የተቀፈቀፉ ቡድኖች ሆነው እናገኛቸዋለን። በዚህም ምክንያት ቅኝቶቻቸው በሙሉ ወደ ተነሡበት ዓላማና ተግባር ሆኖ ይደመጣል። ባንዲት ቤተ ክርስቲያን ቀኖና አልተመሠረቱም አይሠሩምም። በዚህም ምክንያት የቅዳሴውና የጸሎቱ ሥርዓት ተፋልሷል። የበላይና የበታች የቤተ ክርስቲያኒቷ የክህነት ባለቤቶች ተዋረዳቸው ጠፍቷል። ሁሉም ፓትርያርክ ባይሆኑም ወደፊት ግን የቤቱ ግድግዳ ተነድሷል። የቤተ ክርስቲያኗ

ልማት ይሆን ይመስል መነኮሳት እየታደኑ በግድ ጳጳስ እንዲሆኑ እየተገደዱ ነው። በሌላ አነጋገር ምንኩስና ለጵጵስና ግብ ሆኗል። የክህነት ርባታ ብዙ ተባዙ ምድርን ምልዋት ወይንስ «ሑሩ ወመሐሩ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ዓለም?» ወደ ዓለም ሂዱና አስተምሩ ወይንስ ወደ አሜሪካ ሂዱና ጳጳሳት ሁኑ? ጵጵስና በገፍ ለመነኮሳት እየታደለ ነው። ባንድ ወር ውስጥ አሥራ ሦስት ጳጳሳት መሾም ማለት መነኮሳት ሲያልቁ ወደ ሕጋውያኑ ካህናት መውረዱ ቢያስደስተንም ቅሉ ለደናግል ከተባለም ያላገቡ ዲያቆናት እጩ ተወዳዳሪነታቸው የማይታበል የነገና ከነገ ወዲያ የሚደርስ ጉዳይ ነው። ይህን ታላቅ ንዑድ ክቡር ሥልጣን እንዲህ የመሬት መጥረጊያ አደረጉት። ለተሿሚዎችም ቀና ብለው ሕዝብን እንዳይመለከቱ አንገት የሚያስደፋ ሥራ እንደተፈፀመባቸው ማዘናቸው አይቀርም። በትክክልና በሥነ ሥርዓት ተሹመው ማገልገል የሚችሉትን አባቶችም ዕድል ማበላሸት ማጨናገፍም ነው። ይህንና ነገ ከነገ ወዲያ በተግባር ተተርጉሞ የምናየው ድንቅ የእግዚአብሔር ሥራ እንደሚኖር ግን በእምነታችን እንበረታለን።

ይሁንና በዚህ በአሜሪካ የተፈፀመውን ቤተ ክርስቲያኗን ለሁለት የሚቆርጥና የሚገድል ሥራ ማየት ቀርቶ መስማቱ እንኳ እጅግ የሚያሰቅቅና የሚዘገንን ነው። ይህን ስንል በቦታው ላይ ላሉት አባቶች ነቀፌታና ጥላቻ ይመስላቸው ይሆናል። በእውነት ስለ እውነት አይደለም። ከጸሓፊው ይልቅ ራሳችሁን ለቤተ ክርስቲያኗ አገልግሎት ለሠጣችሁት አባቶች ጳጳሳት መነኮሳት ካህናትና ዲያቆናት እንዲሁም ምዕመናንና ምዕመናት ነው። ዛሬ ስሕተት ሲሠራ በተለያዩ ምክንያቶች ታፍነንና ተከናንበን ብንተኛ ገልጦ የሚያይ የእውነት አምላክ የእያንዳንዳችንን ሥራ ይመለከታል። እንዲህ ያለ ሁኔታስ ሲፈጠር ያልመሠከርንና ያልተናገርን መቼ ልንመሠክር ነው? ነገ የሚዘጋ እንደበት፥ ነገ የሚፈርጥ ዓይን፥ ነገ ከነገ ወዲያ ሊፈርስና ሊበሰብስ የሚችል ግዘፈ አካል ካልሠራንበት የሚገባውን ካላደረግንበት መቼ? ያውም ለዚች እውነተኛና ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያናችን ያልሆን ለማን ልሆን ነው?

ዛሬ በቅጠል ልናጠፋው የምንችለውን ችግር ጣራና ግድግዳውን ማንደድ በተየያዘበት ጊዜ ለመከላከል መነሣቱ ይሻላልን? ወገኖቼ ምንም እንኳ ለሰማዩ ቿሚና ተቿሚ አባቶች ቢቀርቡትም ማለት በቤተ ክርስቲያን ስም ያሉና የሚኖሩ መታወቂያቸውና መለያቸውም መኖሪያቸውና መተዳደሪያቸው ቤተ ክርስቲያኗ የሆነቻቸው እሷኑ የሚከፋፍልና በነደደ እሳት ላይ ወርውረው ሲጥሏት ራሳቸው የመጀመሪያ ተጠቂዎች እነሱ

አይሆኑምን? የጳጳሳት አክብሮት ግርማ ሞገስ ፍርሃተ እግዚአብሔር ፀጋና ክብሩ ሁሉ ተቆርጦ የዋለና ያደረ ቅጠል አልመስለምን? ነገ ከነገ ወዲያ ደግሞ እንኳን ተሹመው ሊያገለግሉበት ቀርቶ ከእነርሱ ጋር እንኳን ውሎ ያደረ ሰው ሁሉ የሚናቅበትና የሚዋረድበትን ቀን እየቀፈቀፉና እያረቡ ለመሆኑ አእምሮ ያለው ሰው ሁሉ የሚያስበው ነው። ይህ መሳዩ ችግር በነሱ ጊዜ በዓይነቱ ባይገለጥም ቅሉ ለነገ ለተነገ ወዲያ ለሚተኩት ልጆቻቸው ወይንም አባቶች ዘንድ ግን ፍዳና መከራ መሆኑ አይቀሬ ነው። ከማን ጋር እንደሚውሉና እንደሚያድሩ ቢያውቁ ኖሮ ጊዜያቸውን በከንቱ ባላሳለፉም በነበር። «እንስሳት ከአጥፊዎቻቸው ወይንም ከሚበሏቸው አራዊት ጋር ውሀ ሊጠጡ ከወንዝ ይወርዳሉ» የሚለው ምሳሌያዊ አነጋገር ለዚህ አሁን ለተፈጠረውና ለተከሠተው ችግር ጥሩ አስረጅ ነው።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከእውነተኛው ከአምልኮተ እግዚአብሔር ወደ ጥምቀተ ክርስትናው የተሸጋገረች ብሔራዊት የእውቀት የጥበብ የነፃነት ዓርማ የሆነችው ቤተ ክርስቲያናችን ሳናውቅ በስሕተት አውቀን በድፍረት ሥርዓቷን የምናፈራርስ በስም በግብር በአካል ክርስቲያን ያውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሆን ሰዎች ሁሉ ዕዳው ከያንዳንዳችን ይፈለጋል። ወደ ልጅ ልጆቻችንም ይተላለፋል። የመጭውንም ትውልድ የማንነቱን ዛፍ መቁረጥ ጉቶውንም መነቃቀል [ማንገል] ነው። ይህም እያንዳንዳችንን የወላድ መካን ያደርገናል። ታሪክ ይወቅሰናል ትውልድም ይረግመናል። ዛሬ በኛ ዘንድ ቀላል መስሎ የሚታየው ጉዳይ ነገ በመጭው ትውልድ ዘንድ በዕጅ የማይጠብጡት የጋለ ብረት፥ ከመሬት የማያነሡት ያልተወቀረ የድንጋይ ክብደት ይሆናል። ለልጆቻችን ለልጅልጆቻችን ለእግራቸው እንቅፋት፥ ለዕጃቸው ስንለት፥ ለአንገታቸው ለት፥ አስቀምጠንላቸው አንለፍ። ይልቁንም በዕምነታቸው እንዲጸኑ፥ የአገራቸውን ታሪክ እንዲያጠኑ፥ በኀብረት በወንድማማችነት በፍቅር አንድ እንዲሆኑ እንጣር። አርያም እንሁናቸው።

ከዚህ ላይ ለተለያዩ ሃይማኖታዊ ድርጅታዊ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ድርጅቶች አደራ ልለው የምሻው በአክብሮት በትሕትናና በአፍቅሮት ስለ አገር ስለ እግዚአብሔር ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ስም የቆቅ ማጥመጃነት እንጂ የእምነት ምስሀብነቱን ብዙም ባይደረግበትም መናገሩ ለእኔም በግሌ ድርሻ የምጨክው እባካችሁ ይችን ቤተ ክርስቲያን በዋቃ ጊዜ የምትደረግ ቦቴ ጣማ አታድርጓት። ክረምት ሲወጣ እንደማትፈለግ ምንም ብናውቅ

የተፈጥሮ ሕግ ነውና ክረምቱ ተመልሶ መምጣቱንም ለማሰብ ነው። ለአኩራፊ ምሳው ራቱ ይሆናል ይባል የለምን?

ሌላ ምሳሌም ልጨምር። የአይጢና የአንበሳውን ምሳሌ እናስታውስ። አይጥ በአንበሳ ብትበላ ካንዲ ነጠላ ጥርስ ተርፋ ለሁለተኛዋ እንኳ አታልፍም ኢንበሳ አይጥን በላትም አልበላትም ለውጥ አታመጣም ሪሀቡንም አትከላለትም። ይሁንና አንበሳ መክራ ላይ ወድቆ ማለት በድር ወጥመድ ተይዞ መንቀሳቀሻ ባጣበት ጊዜ ግን አይጥ ያደረገችለት ውለታ እጅግ ካሳሰበውና ካልጠበቀው በላይ እድናቆት ላይ ጥሎዋለች። ይችን ምሳሌ ይዤ ወደ እናንተ ስብሰብ ልምጣ በዝናብ ጊዜ ጃንጥላ ወይንም ገላ፥ በጨለማ ጊዜ መብራት ተፈላጊ ናቸው። አንድ ቀን ባለባችሁበት ጠባብ መንገድ ስትሄዱ ዝናም ቢመጣ እንዳትመቱ፥ ጥቅጥቅ ካለ ጨለማ በሆነበት ጊዜ ደግሞ ብርሃን ወይንም ባትሪ እንደሚያስፈልግ ይታወቃል። እኒህም ሲኖሩ ነው ከሌሉና ከጠፉ ግን ዝናሙም ይጎርፋል ጨለማውም ሰውን ከሚያድኑ አውሬዎች ጋር ያጣጥማል። በዚያ የዋንቅ ቀን ትታደጋለችና እንዘንላት ጥንቃቄም እናድርግላት። ስለዚህ የዚችን የጥንታዊት ብሔራዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ምንነት ከባሕር የተጣለ እሞሌ አታድርጓት። «ጎበ ህሎ ገደላ ህዬ ይታግብኡ አንስርት።» [እሞሮች የሚበላ ባለበት ቦታ ይሰበሰባሉ]። መከማቻታቸው ስዕለት ጉርስ ለዓመት ልብስ መሆኑን ለመግለጽ ነው።

ስለዚህ እንደ መጽሐፉ ቃል የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር የቁጣርን ስቁጣር እናድርገው። ከላይ የተገለጹት ልመናዎችና ተማጽኖዎች እንዳሉ ሆነው አንድ ምሳሌ ላቅርብ ወጥና ጠጅ የሚዘጋጁት ለየብቻ ሆኖ የሚገናኙት ግን ሁለቱንም አጣጥሞ ባንድ ላይ በሚያስቀምጠው የሰዎች ማዕድ ዘንድ ብቻ ነው። ከዚያ ውጭ ግን ጠጅ ከሚያድርበት ወጥ ድርስ አይልም። የመዘጋጃ ሥፍራቸው የሁለቱም የተለያየ ነው። እንዱ ወዳንዱ አይሄድም ድርሽም አይልም። ይህም የሚሆነው አንዱ በሌላው ስለሚጠፋፉ ነው።

በተለይ አንዳንድ የፖለቲካ ድርጅት ራዲዮ ጣቢያዎችም በዚህ በተፈጠረው ግርግር ትርፍ እናገኝበታለን በሚል ሳቢያ በዚሁ በቤተ ክርስቲያኒቱ በሚጨለው የርጥብ እንጨት ጉዳይ ላይ ቤንዚን ሲጨምሩ ይታያሉ። የአቀጣጣይነቱን ሥራ እንኳ ሙሉ በሙሉ ባንሠጣቸውም የሉበትም ግን አንልም። በአባቶች ላይም ኢትዮጵያዊ ሥነ ምግባር በተለየው እንጋገርና አገላለጽ የሚተላለፈው ጽርፈት እጅግ ዘግናኝና አሰቃቂ ነው። ሌላው ቀርቶ የቋንቋውንም ዕጅና

እግር በስለት እንደ መጉመድ የሚያስቆጥር ነው። ምን ዓይነት ጭካኔ ነው። ለእናንተም ዕድገት መልካም እይደለም። በዕንቁላሉ እንዲህ የሆኑ ከበሬው ላይ ሲደርሱማ እንዴት ሊሆኑ ነው ያሰኛል። አትርሱ የውሻ ጥርስ የሚፈራው በእጥንት ነው። እንጋገራችሁ በአድማጮቻችሁ ዘንድ የትዝብት ውሀ ቋጥሯል። እማርኛ ቋንቋ እኮ አንቱታን ያስተምራል ሰውን ያከብራል። አባትህንና እናትህን አክብርን ሕግ ይጠብቃል። ስለዚህ እየተስተዋለ በችኮላ ባይሆን መልካም ይሆናል። በዚያውም ላይ በቁጣሩ መንግሥት ሥልጣን ላይ የምታውሉትን የትግል ጉልበታችሁን ይቀንስባችኋል። የተወደደውን ማገዶም እንዲሁ አታባክኑት። ቅቤ የሚገኘው ከረጋ ወተት መሆኑን አትዘንጉት። ይህ የኢትዮጵያዊነት አስተያየቴ ነው።

ይህ አሁን በቤተ ክርስቲያናችን ዘንድ የተፈጠረው ችግር በባለቤትነት ጉዳዩን መስዶ ለማስተናገድ ሁሉም ባለው ምን አገባኝ? ምንስ ዶለኝ? ደሞዝ የሚያገኙት በስሙ የሚሞካሹት ተቀምጠው እያዩት እኛ ምን እንሁን? የኔ ከዚህ ውስጥ መግኘት በጥርስ መካከል ጣትን መላክ አይሆንምን? እያልን እምነት እያለን እንደሌለን በግዴለሽነት ብናልፈው ታሪክ ከመቀላ ነፃ አያደርገንም። ራሳችንም በበደሉ መዶሻ እንከሠከሥበታለን። ዞሮ ዞሮ እውነት መመስከር ሃይማኖታዊም ማኅበራዊም ግዴታም ነውና እውነቱን ከመናገር ዝም አንበል። ይህን ባለማድረጋችን ውጤቱ ክእውነቱ ተገፍተረን፥ ከመውጣታችን የተነሣ የተቃጠለውን በቅጠል ማጥፋት የምንችልበትን ጊዜ በከንቱ አሳልፈን አሁን ካለንበት የመታያ ኮረብታ ላይ ሆነን የጠላቶቻችን የጣቶቻቸው መቀሠሪያ፥ የዓይናቻቸው መጠቋቆሚያ፥ የከንፈሮቻቸው መንከሻ ሆንን። «ወረሰይከነ ነገረ ለኅርን። ውተግለቁ ላዕሌነ ጸላእትነ።» [የኅረቤቶቻችን መተረቻ አደረግሽን። ጠላቶቻችንም ዘበቱብን። መዝ.79:6] እንግዲህ ለጠላቶቻችን ተመቻችንላቸው። ስለዚህ ከተመሣሣዩ ፀፀት ለመውጣትና ለመዳን ዛሬውኑ እሁንኑ እውነቱን መመስከር ክርስቲያናዊና ብሔራዊም ግዴታ አለብን። ስለዚህ እውነቱን ለመመስከር እውነቱን ለመናገር ለመዋውም ትውልድ እውነትን ማስጨበጥ የግዴታ ግዴታችን ነው።

ይህን መነሻ በማድረግ ይችን ጥንታዊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንኳን ሁሉን ነገር ትተው ዓለምን ንቀው በራሳቸው አስኬማ ወይንም ቆብ ደፍተው፥ በወገባቸው ቅንአተ አዲም ወይንም የመግነዝ ምልክት አሥረው ባንገታቸው መስቀል ዠርግደው በዕጃቸው መስቀል ይዘው የሌላውን ኃጢዓት ለማስተስረይ ወይንም ለማስወገድ «ይፍታሕ ያንጽሕ

ወይቄድስ» [ይንጻ ይፍታ ይቀደስ] ለማለት የቆሙ አባቶች በስመ ሥልጣነ ክህነት ምክንያት ቤተ ክርስቲያኗን ማወክ ምን ዓይነት አመክሮ ነው? ምንስ ዓይነት አባትነት ነው? ይህስ ምን ዓይነት መንፈሳዊ ሥራ ነው? ምዕመናንስ የአባቶችን ውሳኔ በጭብጨባ የምናጸድቀው ነውን? ወይንስ በምን አገባኝነት በተመልካችነት በአድርባይነት ችላ ብለን የምንተወው ነውን? በዚህ መንገድ ይህን ችግር ብንተወው ማንን ይረዳል? ማንንስ ይጠቅማል? ማንንስ ይጎዳል? ብለን ስንጠይቅ ስለዚህ ከመገረም አልፈን መናገርና ትክክለኛ ያለመሆኑን ማስረዳት የግዴታ ግዴታ ያውም ብሔራዊና ሃይማኖታዊም ነው።

በአሜሪካ የተፈፀመው የሲኖዶስ መፈጠርና መነሳሳትን ኤጲስ ቆጶሳት አድርጎ መሾም ትክክል አይደለም። ቤተ ክርስቲያኗን አትበድሉብን። ሕዝቡንም መከፋፈል ይቁም ይብቃ። በምንም ታምር ጠቃሚ አይደለም። እናንተም ታውቁታላችሁ እኛም እንረዳዋለን። ያገሪቱን አንድነትና ባሕል ሥነ ጽሑፍ ይዛ የምትገኘዋን ይችን ጥንታዊት ቤተ እግዚአብሔር መጉዳት በሥጋም መከራ በነፍስም ደይን ነው። በትንሣዔ ሙታን አምኖ የሚያስተምር አባት እንዴት እንዲህ ያለ ተግባር ይፈጽማል? የተደረገውና የተፈፀመውን እናብቃ ይቁም። ወደ ንስሐ ወደ ይቅር መበባሉ እናቅና። ቂም በቀል ይዘን ከወጣን ወደማንመለስበት አገር ጎዳና ከመውጣታችን በፊት አሁንኑ እንፋቀር እንስማማ። ጥልና ክርክር ከመስቀሉ ከአካላችሁ ከመልካችሁና ከሁለመናችሁ ጋር ጨርሶ አይሄድም። ማንን ለመጉዳት ነው ቤተ ክርስቲያኗን እንዲህ ጆረፌ በጆረፌ የምናደርጋት። እናንተ የተዋችኋትንና ችላ ያላችኋትን ማን ነው ተጠሪ የሚሆናት? ስለ መድኃኔ ዓለም ስለተሰቀለው ኢየሱስ የቂም በቀል ሐውልት ተክላችሁ አትሂዱ አትለፉ።

አንድ የሚገርመኝ ነገር አለ። በ1966 ዓ. ም. በተደረገው የመንግሥት ግልበጣ ወይንም መፈንቅለ መንግሥት በአመፅ የተደረገ ነገር ሁሉ መለያና መታወቂያው ግልበጣ መፈንቅለ መንግሥት ወዘተ ... እየተባለ ነውና ይህ ሁኔታ ሲፈፀም ወታደሩ ሥልጣኑን በዕጁ ያስገባው በመሣሪያ ነበር። የተነጠቀውም በመሣሪያ ነው። ወዶ ፈቅዶ ሳይሆን ተገፍትሮና ተገዶ ነው። ይህ እውነት ነው። የጸሐፊው ፍሬ ነገር ከዚህ ላይ አይደለም። ነገር ግን ይህ የመንግሥት ልውውጥ ሲደረግ ንጉሠ ነገሥቱ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከአገራቸው አልወጡም። የታሠሩት የሞቱትና የተቀበሩትም በአገራቸው ምድር ያውም ከቤተ መንግሥታቸው ሲሆን አስከሬናቸው ካልሆነ ቦታ ቢቀበርም በመጨረሻ በክብር ካሠሩት

ቤተ ክርስቲያንና መካነ መቃብር ውስጥ በክብር አርፏል። ይህን እንደ ቀላል ነገር አንመልከተው አንየው። የሰው ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርም ዕጅ ታምርና ድንቅ ሥራም አለበት። በንጉሠ ነገሥቱና በፓትርያርኩ ላይ የተፈፀመውን ግፍ እናቆየውና እነሱን የተኩት የአገሪቱና የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ምን ሆኑ? ምንስ ደረሰባቸው? የትስ ናቸው? ብለን ስንጠይቅ ተመሳሳይ ሁኔታና አፈፃፀም እንመለከታለን። ጽርፈት አይሁንብኝና እግዚአብሔር በባዕድ አገር አሸሞንሙኖ አስቀምጧቸዋል ብለን እንናገር ወይንስ ቁጣውን አሳይቶባቸዋል? ክቡር ሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት በኬንያ አድርገው ዝምባብዌ ሲሄዱ፥ እንደ ንጉሡ አጎንብሱ ነውና ፓትርያርክ መርቆሬዎስም በኬንያ አድርገው አሜሪካ ገቡ። ከዚህ ላይ ብንጠቅሰው ተስማሚ ይሆን? «ኩሉ ዐረየ ወጎቡረ ዐለወ» ሁሉም አንድ ሆነ ለክፉ ነገር ተባበረ። [መዝ. 13:3]

ከዚያስ ምን ሆነ ምንስ ተደረገ ብለን የጠየቅን እንደሆነ ታሪክ ነውና መነገር አለበት። ታሪክ አይዋሽም። ክቡር ሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በሌሉበት የሞት ፍርድ ሲወሰንባቸው በአንግሩም ብዙዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ከሚለው ማዕርጋቸው የሸማቸውና ያከበራቸው ቅዱስ ሲኖዶሱ በውሳኔው ከዚያ ከረጅሙና ከሚያስፈራው ግርማ ካለው ስማቸው አወረዳቸው። እጅግ በጣም አነስተኛ ወደ ሆነችው ወደ ቀድሞዋ የምንኩስና ወይንም የዓለም ስማቸው «አባ ዘሊባኖስ ፋንታ» አላቸው። ይህ ውሳኔ በሳቸው ላይ ይረፍ እንጂ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ለኛም ለምዕመናኑ ታላቅ ውረደት ነው። የቁም ሞትም ነው። የሥጋስ ሞት የተለመደ የማይቆይና የማይቀር ነው። ይህ ዓይነቱ ግን የመንፈሳዊ ሕይወት ሞት ነው። ድምፀ አራዊት ፀብአ አጋንንትን ታግሠው በጫካው በዱር በገደሉ ወድቀው የሚጸልዩ አባቶች ያሏት ቤተ ክርስቲያን የበላይ አባት የነበሩ ሰው እንዲህ ከዓርባ ዘጠንኛ ፎቅ ላይ አምልጠ እንደወደቀ የአበባ ማስቀመጫ ወርቀ ዘቦ ገንቦ የተሰባበረና የተንከታከተ መሆን ስሁላችንም ታላቅ ኃፍረት ነው። ጽናትና ብቃት በሚትሩ ሳይለኩ የሚፈፀም ሽመት ሁሉ ውጤቱ እንደዚህ ነው። ደርግ የቤተ ክርስቲያንን ሀብትና ንብረት ሲወርስ ማዕርጓንም መዉመሩ የድህነቱና የጉሥቁልናው ደዌ በአባቶች ላይ አድሮና ውሎ ብሎም ከርሞ እነሆ ከዚህ ላይ አደረሳቸው። ይህን የመሰለ ውርደት በቤተ ክርስቲያኗ አባቶች ላይ ማረፉ ታላቅ አበሳ ነው። የፀጋ እግዚአብሔር ገፈፋም ነው። ስጠላቶቻችንም መዘባበቻ መሆን ነው። «የኀብረተ ሰብአዊነት

ይለምልም» መፈክር ብቻ ሳይሆን ትንቢት ናሮ እነሆ እስካሁን የቤተ ክርስቲያኗን ልብ እየጎጎጣት ነው።

እንድ የሞት ፍርድ የተፈረደበት ሰው ስለ ተፈረደብህ የሞት ፍርድ እንዴት እየኸው ተብሎ ሲጠየቅ የሠጠው መልስ «በዳኞችና በኔ መካከል ልዩነቱ እኔ የምሞትበትን ጊዜ ማወቄ ሲሆን እነሱ ደግሞ ያለማወቃቸው ብቻ ነው» ብሏል። እውነትም የሞት ፍርድ የሞትን ቀን ከማወቁ በስተቀር ምንጊዜም ሞት በሰው ላይ ያለና የሚኖር የተፈጥሮ ፍርድ ነው። ሁሉም ቀኑን እየጠበቀ ያልፋል ይሞታልና ነው። ታላቅ ግንዛቤ ነው። ሞት አይፈራም። የማይቀር እዳ ነውና! ምንጊዜም መከፈሉ የማይቀር የግድ የሚሆን ነው። ታዲያ ሞትን በጽናት መቀበልና መጋፈጥ እንጂ ሸሽተው የማያመልጡት የራስ የአካል ጥላ ነው። የሥጋ ሕይወት ፍጻሜው ማሠሪያና መጠቅለያው ሞት ነው። የመቀበሉን ጊዜ መምረጡ እንጂ የማይቀርን እዳ በወቅቱና በክብር መክፈልና ተከሶ ተንገላቶ ወጥቶ ወርዶ እስከ ወለዱ መክፈሉ ጥሩ ደንበኛ ተበዳሪና እዳ ከፋይ አያሰኝም። ከዚህ ተግባር ለአባቶችም ሆነ ለምዕመናን ታላቅ ትምህርት እንደሆነ መረዳቱ እጅግ ይጠቅማል። የዘወትር ጸሎታችንም የሚያስተምረን «ኢታብእነ አግዚኦ ውስተ መንሱት» [ጌታ ሆይ ወደፈተናም አታግባን] ነው። ማቴ 6:13፤ ከገባን ግን እንድንወጣው ኃይሉንና ጽናቱን ስጠን የግድ ይሆናል። ለዚች «ጎድግዋ ወመንንዋ ለዛቲ ዓለም» [ይኽን ዓለም ናቋት ተዋት] በሚለው መርሕ ውስጥ ራሳችንን ያስቀመጥን ስዎች ዓለምን ስንወዳትና ስንንከባከባት መታየት መመረያውን መጣሉ አይደለምን? ያስ እግብ ሙቱ ተሰቀሉ አይደለም ቅስቀላው ታሳቡ በሚፎከርበት ጊዜ ወዬ! ወዬ! አይባልም ነው። መስቀልን ያህል ጦርና ጋሻ ይዞ እንዴት ወደኋላ ይሸሻል? እንዴትስ ፍርሃት ፍርሃት ያሰኛል ነው።

ባንድ ወቅት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ እንደ ተሾሙ መስቀል አወጣሁ ብለው ሽጉጥ መዘዙ እያሉ ያጥላቿቸው ነበር። ይህን አባባል ምክንያት አድርጎ አንድ በአትላንታ ጆርጂያ የሚታተም ሳንድ ኦፍታ የተሰኘ መጽሔት በ1991 ዓ. ም. እትሙ ላይ እንደገለጸው ራሳቸውን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስን አግኝቶ ስለዚሁ ጉዳይ ከላይ የተገለጸውን ጥያቄ አቅርቦላቸው ነበር። ቅዱስነታቸውም ፈቃደኛ ሆነው ስጥያቄው መልስ ሰጥተዋል።

ዝርዝር ጥያቄው እንዲህ ይላል። «አቡነ መርቆሬዎስ ከሻለቃ ተፈራ [መላኩ] ጋር አብረው ሰርተዋል። ሰው ለማሳለም ሲሉ መስቀል አወጣሁ ብለው ሽጉጥ መዘዙ፥ ለደርግ መንግሥት መሣሪያ

መግዣ የገንዘብ አርዳታ ሰጥተዋል፥ የተሾሙት በደርግ እንጂ በቤተ ክርስቲያኒቱ አይደለም ይባላል። ቅዱስነትዎ የሚሰጡት መልስ ካለ፣

መልስ «መስቀሉ ይህ ነው። ዐይን አይቶ ልብ ይፈርዳል። ለመሆኑ ይህን መስቀል በኪስ ለመያዝ ይቻላል? አንተ ራስህ መፍረድ ትችላለህ።» ከዚያም ከሻለቃ መልአኩ ተፈራ ጋር በሠራውበት ጊዜ ምንም ዓይነት ችግር አልነበረም። ለደርግ የመሣሪያ መግዣ አልሰጠውም። ለችግረኛ ወገኖቻችን ግን ሠጥቻለሁ። ብለው የሚወነጅሏቸውን በኃጢዓት አረቂ የለከሩ ሀሰትን እንጂ እውነትን የማይናገሩ ዓይነ ልቦናቸው የታወረ እዝነ ልቦናቸው የደነቆረ መላ ሰውነታቸው በመጥፎ ነገር የደነዘዘ በተንኮልና በሀሰት ልሳን ልስቅ ብሎ ሰውነታቸው ተመርጎ የመንፈስ ቅዱስ ሮራ መግቢያ አጥቶ የሚቃትቱ የዲያብሎስ ዜግነት ያላቸው ናቸው ሲሉ መልሳቸውን አጠቃለውታል። ዝርዝሩን ከመጽሔቱ ማንበብ ይቻላል። ነገር ግን ሌሎችን የተጠየቁትን ሲመልሱ በደርግ መሾማቸውን አላስተባበሉም። ስለሁሉም ሰበስጠ መረጃ መጽሔቱን ማንበብ ነው። *[ሳንድ ኦፍታ መጽሔት ጎሳር 1991 7ኛ ዓመት ቁጥር 2 ገጽ 23 – 24 አትላንታ ጆርጂያ]*

ይህን ያለፈ ነገር ማውሳቱ ምን ያደርጋል? የሚል ቢኖር ትክክለኛውን ለማግኘት ይሆናል መልሱ። ታሪክ ራሷን ትደግማለች ይባላል። እንዲህ ዓይነቱ ነገር እንዳይደገም ለቤተ ክርስቲያኗ አባቶችም ሆነ ለምዕመናን አመከሮ ለማቅረብ ነው። ስሕተት የሚደጋገመው ትክክለኛ ይሆን ይሆናል ብሎ በማሰብ ነው። ትክክል አይደለም ተብሎ ግንዛቤ ከተወሰደበት ግን የመደጋገሙ ውፍረት ይቀጥናልና ነው። ሁልጊዜ እንድ ነገር ከመሆኑ በፊት ሳይሆን ልቅሶችን ከሞተ በኋላ እየሆነ ነው። የማይጠቅም የማይረባ ጩኸትና ልቅሶ ይሉታል።

ይሁንና ሞት ሁለት ዓይነት እንደሆነ ቤተ ክርስቲያን ታስተምራለች እሱም የሥጋና የነፍስ ሞት ነው። እኔ ግን ባሕላዊ አባባላችንን አስረጅ በማድረግ ሦስት ሞት እንዳለ እቅጥራለሁ። ሦስተኛው ሞት እሱም የቁም ሞት ነው። የአገሬ ሰው የሚያውቀው የቁም ሞት ከሁሉ የከፋ መሆኑን ነው። ለምን ቢባል አያዩና እየሰሙ የሚሞት ስለሆነ ነው። ስለዚህ ከሦስተኛውና ከነፍስ ሞት ያድነን። ሁለቱ ሞቶች በተፈጥሮና በሥራ የሚወረሱና የሚፈፀሙ ሞቶች ስለሆኑ ነው። የሥጋ ሞት ሽግግር ያሊያም በሥጋ ማንቀላፋት ተፈጥሮአዊ ፀጋ ነው። ሞት ተብሎም መጠራትና መታወቅም

አልነበረበትም። አበው እንደሚሉት ዕረፍት ተብሎ መታወቅ ይገባዋል። ሳልመኝው የማላልፈው ጉዳይ ቢኖር ከቁም ሞት ያድነን ይሠውረን ማለቱን ነው። የሕዝብ አውራ የሆኑት ሰዎቻችን በቁም ሞት እየተገደሉብን ነው። «ያድኅነነ እመዓቱ ይሠውረነ በምሕረቱ በእንተ ማርያም ወላዲቱ።» [ከመዓቱ ያድነን ስለ እናቱ ቅድስት ማርያም ብሎ በምሕረቱ ይሠውርን] የምሕላ ጸሎታችን ነው። አሜን ይሠውረን።

፪ . ቅዱስ ሲኖዶስ

የአባቶች አንድነት ወይንስ ልዩነት?

በእውነቱ ከሁሉ በፊት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ማን ናቸው? ቅዱስነታቸውን የማያውቅ አለ ብዬ አይደለም። ነገር ግን ይህ ጽሑፍ በቆየ ቁጥር የማያውቃቸው ትውልድ ይመጣልና ማሳወቁ ተገቢ ይሆናል። አሁንም ያለው ሕዝበ ክርስቲያን በተለይም ከውጭ ያለው ከሰም በስተቀር የማያውቃቸው ይበዛል የሚል ግምት አለኝ። ቢኖርም በትክክል የማያውቃቸው ይበዛል። እኒህ አባት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ገዳማት የሚሠጠውን ብሔራዊና መንፈሳዊ ትምህርት አጠናቀው ከዚያም መንኩሰው ከነበሩበት ት/ቤት ወደ ዘመናዊው ት/ቤት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ወደ ሐረር መንፈሳዊ ት/ቤት ተልከው ያንደኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸው ወደ ቅድስት ሥላሴ መጥተው ፈጽመዋል።

ከዚያም ከሌሎች አባቶች ጋር ወደ አሜሪካ ተልከው በቪላድሚር ሴሚናሪ የመጀመሪያ ድግሪያቸውን አግኝተው ለከፍተኛ ጥናት ወደ ፕሪስተን ዩኑቨርሲቲ ገብተው የማስተርስ ዲግሪያቸውን አግኝተው ወደ አገራቸው ተመልሰው ቤተ ክርስቲያናቸውን ማገልገል ቀጠሉ። በአገልግሎታቸውም በተለያየ ማዕርግና በመምሪያ ኃላፊነት አገልግለዋል። በዚያን ጊዜ በቅርብ ሥራቸውን ይከታተሉት የነበሩት ቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ሦስት ጳጳሳትን ሲሾሙ አንዱ ቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ነበሩ። በቅርብ የሚያውቋቸው እንደሚመሰክሩላቸው ቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በልዩ ሁኔታ ይንከባከቧቸው ነበር። ሚመተ ጵጵስናቸውንም ጳውሎስ ብለው ሲሠይሟቸው ባላቸው ዘመናዊ ትምህርት በዓለም ዙሪያ ሄደው ለቀረው ዓለም በዓለሙ ቋንቋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ያስተዋውቃሉ ብለው በማሰብ ነው። እንዲሁ ባጋጠመኝ በድንገት ሳይታሰብበት የተሠጣቸው ስም አይደለም። ቅዱስነታቸውም ጳጳስ እንደሆኑ የተዘረጋላቸውን ሐዋርያዊ ተልእኮ ሳይጀምሩት ከክህነት አባታቸውና ከሌሎች ጳጳሳት ጋር ለሰማንት ዓመት በጽኑ እሥራት ቆይተው ሲፈቱ አባታቸው ቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ግን ከዚያው ከሥር ቤት ተወስደው ተገደሉ የሰማዕትነትን ጽዋ ተቀበሉ። ቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ከእሥር ቤት እንደ ወጡ ወደ ቤተ ክርስቲያናቸው

አገልግሎት ተመለሱ። ከዚያም ያለውን ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ወደ ፕሪንስተን ዩኑቨርሲቲ በመመለስ የዶክትሬት ድግሪያቸውን ጥናት ለመቀጠል ተመለሱ። ት/ቤት በነበሩበት ጊዜ በኒው ዮርክና በአካባቢው የነበሩት ኢትዮጵያውያን ቤተ ክርስቲያን እንዲከፍቱላቸው በጠየቋቸው መሠረት ከፕሪንስተን ዩኒቨርሲቲ ከኒው ጀርሲ ቅዳሜና እሁድ እየተመላለሱ ኢትዮጵያንን አሰባስበው ያገለግሉ ነበር። ይህም ሊሆን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንን ቀኖና ጠብቀው አንዲትም ቀን በማንም ለይ ማለት በአባቶች ላይ ክፉ ነገር ሳይሠነዝሩ አገልግሎታቸውን በመስጠት የጀመሩትን ትምህርት ፈጽመው የዶክትሬት ዲግሪያቸውን አገኙ። የኒው ዮርክ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በምረቃቸው ጊዜ በልዩ መልኩ የዩኒቨርሲቲውን ግቢ አድምቀውት ነበር። ከዚያም መኖሪያቸውን ወደ ኒው ዮርክ ቤተ ክርስቲያኑ ወዳለበት መጥተው በቅርብ ቤተ ክርስቲያኑን አባላት በልዩ ልዩ ማኅበር በማደራጀትና አገልግሎቱን በማስፋት የቅዳሴ ተሠጥዎ በማስጠናት በሚያገለግሉበት ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ የመንግሥት ለውጥ ተደረገ።

ከዚያም ከላይ እንደተገለጸው ቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በነሐሴ ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፫ ዓ. ም. በገዛ ፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን ለቀቁ። ከዚያም እንደማንኛውም አባት እሳቸውም ጉዳዩን ኒው ዮርክ እያሉ ሰሙት። ከላይ እንደተገለጸው ቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በነሐሴ 28 ቀን 1983 ዓ. ም. ሥልጣናቸውን የለቀቁ በግንቦት ወር 1984 ዓ. ም. ቅዱስ ሲኖዶሱ በወሰነው መሠረት በሙሉ የኢትዮጵያ ሊቃነ ጳጳሳት ከያሉበት ስርክበ ካህናቱ ዓመታዊ ጉባዔ ሁሉም እንዲገኙ ባደረገው ጥሪ መሠረት ቅዱስ አቡነ ጳውሎስም ወደ ኢትዮጵያ ሄዱ። በዚያም ስብሰባ የፓትርያርክ ምርጫ እንዲደረግ ቅዱስ ሲኖዶሱ ወስኖ አስመራጭ አባላትንና አሥር እጩ ሊቃነ ጳጳሳትን መርጦ ከአሥሩ አስመራጭ አባላት አምስቱን አጥንተው ለምርጫ እንዲያቀርቡ ሥልጣን ሠጣቸው። የአስመራጭ አባላትም ከአሥሩ አምስት ሊቃነ ጳጳሳትን በተሠጠው መሥፈርት የሚያሟሉትን መርጦ አቀረበ። ምርጫውም ለሕዝበ ክርስቲያኑ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ተነገረ። አምስቱም ሊቃነ ጳጳሳት ማንነታቸው ይፋ ሆነ። መራጮችም የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የአዲስ አበባ ገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች የሠበካ ጉባዔ አባላት የአኀጉረ ስብከት ተወካዮችና የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበራት ተወካዮች በተካፈሉበት ሰኔ 8 ቀን 1984 ዓ. ም. ምርጫ ተደርጎ በምርጫውም ከላይ እንደ ተገለፀው

አንደኛ/ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ
ሁለተኛ/ ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ
ሦስተኛ ብፁዕ አቡነ ሳሙኤል
አራተኛ ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕና
አምስተኛ ብፁዕ አቡነ ሰላማ ሆነው ተመረጡ።

[ዝክረ አበው ልዩ መጽሔት ትንሣዔ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት 1997 አዲስ አበባ ገጽ16]

ይህ የሆነው ቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ሥልጣን በለቀቁ በአሥራደኛው ወር ላይ ነው። እስከዚያ ድረስ ግን ቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ከላይ እንደተገለጸው የጡረታ መብት ተጠብቆላቸው መኪና እስከነ ሾፌሩ ተመድቦላቸውና ቤት ተሠጥቷቸው በመኖር ላይ ነበሩ። ይህ በእንዲህ እንዳለ የቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ሥርዓተ ቀብር ሐምሌ 4 ቀን 1984 ዓ. ም. ብዙ የኢትዮጵያ ሕዝብ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች የአሪየንታል አርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ፓትርያርኮችና ሊቃነ ጳጳሳት የውጭ አገር አምባሳደሮች በተገኙበት ተፈጽሞ በበነጋታው ደግሞ የቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ሚመት ሐምሌ 5 ቀን 1984 ዓ. ም. በታላቅ ሥነ ሥርዓት በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተደረገ። አሁን በአሜሪካ የሚገኙት ሊቃነ ጳጳሳት ሁሉም ከብፁዕ አቡነ ኤልያስ በስተቀር ከሚመቱ ላይ ተገኝተው ቅዱስ አቡነ ጳውሎስን ቀብተዋቸዋል። እውነቱ ይህ ነው። ከዚህ እንደምንሰማውና እንድናጠነው የተደረገው ግን ከዚህ የተዘጋጀውን ልዩ ቃለ ምዕዳን ነው።

ይሁንና ከዚህ ላይ ሌላው የሚያስደንቀው ግን እጅግ በከፍተኛ ደረጃ በዘመናዊው ትምህርት ከተማሩት ኢትዮጵያውያን ምሁራን አባቶች መካከል ቤተ ክርስቲያኒቱ ያገኘችው ዕድል እጅግ በጣም የሚያኮራ መሆኑን ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ከመንበሩ ላይ ከተቀመጡ በኋላ፥ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስና ሌሎችም ሊቃነ ጳጳሳት ከጥቂት ቆይታ በኋላ ከኢትዮጵያ ወጡ። አብዛኛዎቹም ወደ አሜሪካ መጡ። ቁጥራቸውም በዛ አለ። እነሱ አሜሪካ መሆናቸውን ሲያረጋግጡ የግላቸውን ሲኖዶስ ለመፍጠር ተዘጋጁ። በዚህ በሚመለድ ሲኖዶስ ስም በሚታረስ እርሻ የፖለቲካ ስንዴ ለማምረት ያሰቡ የፖለቲካ እንጂ የወንጌል ገበሬዎች ያልሆኑ ባናርስ እናጣምድ ነበር ልምዳቸውን ይዘው አባቶቻቸው እንኳ ባይሆኑ አያቶቻቸውና አጎቶቻቸው ቁሰ ገበዙች ርእሰ ደብሮችና ግራጌታዎች እንደነበሩ የሹመት ኃረግ በመምዘዝ አሁንም ግብዝና ለመሾም ባንዲት ሚስት መጽናት ወይንም መኖር እንደማይከለክል ካረጋገጡ በኋላ ለማቋቋምና ቁሰ

ገበዝ በመሆን አብረው ተሰለፉ። የዲቁና አገልግሎት የነበራቸውማ በተሐድሶ ስም ያልሆኑት ነገር የለም። ይህን ያህል በነፃ አገር ነፃ ሽመት ከወዴት ይገኛል?

ያ በድን ትምህርቱ ተመርቆ ወደቤቱ የሚመለስ ምሁር ፊደል የምትቆጥር ልጅ ዓይቶ አይ! አንቺ ልጅ የገባሽው ዕዳ እንዳለው ደብተራው ቄስ ዲያቆኑ ደብተራ መሆን የሚቻልበት አገር አሜሪካ የክህነት ዲሞክራሲ ይለ ገደብ ተሠጠ ታደሰ። በቴፕ ቢቀደስስ ምንአለበት? በሥራ ላይ ውሏልም ተጠይቋልም። ከዚህ ላይ እኮ ነው እኔ ለአሜሪካ ነፍስ አነስኳት? የተባለው። ከመጠላዕቱ [ከመጋረጃው] ውስጥ ድምፅ ከመንግናው ካህን በጆሮ የሚሰሙት እንጂ በዓይን የማያዩት ቁሰገበዝ አልታዩ እንበለው ቅዳሴውን ይቀምሩታል። ነገር ግን እንደ አገር ቤቱ ካህን ከመቅደስ ወጥቶ መስቀል አያሳልምም። በዓይን የማይታይ ካህን የሚታይበት አገር ተደረሰ። ወይ አሜሪካ የሰው ነፍስ መሥራት የቀራቸው ተብለው አሜሪካኖቹም በድርጊቱ ተወደሱ።

የኛ ካህን በዓይን መታየት ስላልቻሉ። በኋላ ግን ማን ሆኖ ተገኘ መሰላችሁ ከመንግነው መቅረፀ ድምፅ [ቴፕሪኮርደር።] ቴፑም ቄስ ሆነላችሁ። ይህች ናት አሜሪካ። ቤተ ክርስቲያን ታጥቶ ሳይሆን ሙዳዬ ምጽዋት ለካህን ደሞዝ ላለመክፈል የተደረገ ፈሊጥ ነው። ወይንም ካህንም ማግኘት አስቸጋሪ ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ካህናትን አሠልጥናና መመሪያ ቄምር ሰጥታ ገና በሚገባ መላክ አልጀመረችም። ቢኖሩም በጣም ጥቂቶች ናቸው። ይህ ሁሉ የሚያሳየው የቤተ ክርስቲያኗን አንድነት ከምን ቦታ ላይ እንዳለ የሚያመለክት ነው። ቤተ ክርስቲያን በግል ማቋቋምና ማስቀደስ እንደ ገቢ ምንጭ ወይንም እንደ ልዩ ሥራ ተደርጎ መወሰዱን ነው። ዛሬ አባቶች እያሉ ገና ፈሪሃ እግዚአብሔሩ ታጥቦ ሳይደርቅ በአልቸኳይ ካልታረመና ካልተስተካከለ ካደረና ከዋለ ሆድና ጀርባ እየሆነ መሄዱ የማይቀር ነው። ለቤተ ክርስቲያናችን ክብርና ልዕልና ስንል የራሳችንን ፍላጎት መጸም አስፈላጊ ነው። ይህ ደግሞ ሃይማኖታዊ ግዴታችን ብቻም ሳይሆን የማንነታችንንም ልዑላዊነት መንከባከብም ነው።

«ንስሐሰ ትሬስዮ ለዘአበሰ ወለዘኢአበሰ ወለዘማኒ ከመ ድንግል።» [ንስሐስ የበደለውን እንዳልበደለ ዘማዊውን እንደ ድንግል ታደርጋለች] ነውና ነው። ምንም እንኳ የተቆረጠ እንደነበረ ባይሆንም ቅሉ በማይታይና በማይመረመር ጥበቡ ያድሰዋልና «ዛው ንውሰ ክርስቲያን» የተባሉትን «ንው ቡሩክኑ ለአቡየ» ማለቱ

የወንጌል ቃል ነውና! የአስተዳደራዊ ልዩነት የፈጠሩትን እንዳልፈጠሩ አድርጎ ለመቀበል ይቻሳል ይላል ቅዱሱ ሲኖዶሱ። ምንም እኳን የዋናው ሲኖዶስ ተወካይና የአሜሪካ ሀገረ ስብከት መንበርም በአሜሪካ ቢኖርም ቅሉ ከሌሎች በአካባቢው ካሉት «የስደተኛው ሲኖዶስ» ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ተስማምቶና ተቀናጅቶ በተፈጠረው ልዩነት ምክንያት ሊሠራ አልቻስም። ከውጭ ያለው ጎብረተሰብ ደግሞ በአብዛኛው ስደተኛ በመሆኑ ኢትዮጵያ ካለው መንግሥት ጋር ባለው ቅራኔ መሠረት ከዚያ መንግሥት አብራና መስላ የምትሠራ ቤተ ክርስቲያን አትወከሰንም በማለት የጥላቻውን አድማስ አዲሶቹ ቄስ ገበዞች አሰፉት። ይህ ችግር ደግሞ ሲሻኝ ጢስ ወጋኝ ለሚሉት ክፍሎች አመች ሆነላቸው።

ዛሬ ሁለት ሲኖዶስ አንድ በኢትዮጵያ አንድ በአሜሪካ ይገኛሉ ብሎ እውቅና መሥጠቱ ይቅርና መናገሩ እንኳ ያሰቅቃል ይከመድዳል እንዲያውም ያስቀሥፋል። ሲኖዶስ አንድ ነው። አንዲት ቤተ ክርስቲያን አንዲት ሃይማኖት እርሷም ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ኢትዮጵያዊት ብቻ ናት። ለኛ ለኢትዮጵያውያን ከዚህ ውጭ አለ ይኖራል ብሎ መቀበሉ ራሱ ለቤተ ክርስቲያናችን ልናደርገው የሚገባንን እንዳላደረግን ያስቆጥራል። የዚህም ውጤት «ሐሩ እምኔየ ርጉማን ውስተ እሳት ዘለዓለም» [እናንተ ርጉማን ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደተዘጋጀ ወደ ዘለዓለም እሳት ከኔ ሂዱ።] [ማቴ. 25:41] ያስኘናል። ስትታረዝ ስትጎሳቆል በተሰይም በእንግድነት አሜሪካ አገር ውስጥ እያለች እናት ቤተ ክርስቲያናችንን አልጠየቅናትም። አይዞሽም አሳልናትም። በግል ጥቅምና ዝና የእሷን ክብርና ሞገስ ዝቅ ሲያደርጉና ሲያዋርዱ ዝም ብለናታል። በጠላቶቿ ዘንድ መሳቂያና መሳስቂያ አስደርገናታል። በእርሷ ስም ስብሰውና ከብረው እያሉ ክብረ ንጽሕናዋን አጉድፈውባታል።

እመቤት ክብርት ልዕልት ያልተባለችውን ያህል ዛሬ ጣያት አምላኪ ተባለች። አምላኳን የማታውቅ ፍጡር አምላኩ አሰኟት። በአሕዛብ ፊት መሳቂያና መሳለቂያ ሆነች። ለአነሱ ሹመት ሲባል ክብሯን አጣች። ቀሚሷን ለሁለት ቀደደች አስባሏት። የትዕግር ምሳሌ ሆነች። [2ሳሙ.13:11-20] እንዴት ቤተ ክርስቲያናችን ክብራቸውን በማይጠብቁ በእንጀራ ብቻ ለሚኖሩ የአፍ ማማሞጭሞጫ ትሁን? ለክብሯና ለሰሟ የምትጨነቁ ተነሡ። ጊዜው አሁን ነው። እሷን በየምክንያቱ ለሁለት ሊከፍሏት የተነሡትን ራስ ለሁለት እንክፈለው። በዋሉበት አንዋል። ባደሩበት አንደር። የአባታችን ቡሩካን አይደሳችሁምና አናውቃችሁም እንበላቸው። እኛ በግ እንሰሳ ማርባት እንጂ የእባብ ርባታ አልተማርንም አልሠለጠንም። የእባብ

እንቁላል የሚያስታቅፍት ዶሮ ያላት አድሜ ዕንቁላሉን እስከትቀፈቅፈው ድረስ ብቻ ነው። ከዚያማ ባጎረስሁ ዕጁን ተነከስሁ ይሆናል። አሷንም የተቀፈቀፉት ያጠፍታል። በዚህን ጊዜ ዝም ያልን በዚህ ጊዜ ዓይተን እንዳላየን የሆን ጥፋተኞች ነንና «ሐሩ እምኔየ ርጉማን» መባላችን የማይቀር ነው። በሰማይ ቤት ባንባል ታሪክና ትውልድ ፊት እንባልበታለን። ፀሚያልፍ ዝና በሚያረጅ እድሜ በሚያልቅ ልብስ ክብሯ ዝቅ ሲደረግ ዝም ብለናልና እንጠየቅበታለን።

እንግዲህ ይህን በዚህ ማሳሰቢያ ልወጣውና እስቲ በሌላ መልኩ ደግሞ እንመልከተው። እንዲያው ከሆነስ እንበልና ሁለት ሲኖዶስ አገኘን እንደ ህብት፥ እንደ በረከት የሚቆጠርልን ቢሆን ኖሮ ታድለን ባልን በነበር። ነገር ግን አይደለም አልሆነም። የሆነው «ያልወለድሁት ልጅ አባባ ቢለኝ አፌን ዳባ ዳባ አለኝ።» ነው። ከዳባም ዳባ አጽፍ አይሆን አጎዛ እንዲያው ውሀ የነካው ቆዳ እንጂ! እንዲያውም አሜሪካ የተወለደ አሜሪካ ያደገ በሕገ መንግሥቱ መሠረት ዜግነቱ አሜሪካዊ እንጂ ኢትዮጵያዊ የሚያደርገው ምንም ዓይነት ባሕርይም ጠባይም ምክንያትም የለውም አይኖረውም። ታዲያ አሜሪካ የተወለደ ሲኖዶስ ያውም ሕጋዊ ኢትዮጵያዊ እንዴት ሊሆን ይችላል? አሜሪካ የወለዳችሁትን ልጃችሁን ሲኖዶስን ዜግነቱን አትቀይሩበት። ወንድሞቹና አኀቶቹ እነ ጴንጤ መጤ በኢትዮጵያ ደግሞ የግብር ዘመዶቹ እነ ተሐድሶ አይደሉምን? ይህን ካወቅን ውለን አድረናል። የአሜሪካው ሲኖዶስ አፍንጫ ሲመታ የተሐድሶ ዓይን ሲያለቅስ ታይቷል። ፀሐይ ያየችውን ሰው ሳያየው አይቀርም ተብሏልኮ! እንዲያው ብላችሁ ብላችሁ አሁንም ያችን ዶሮ የእባብ ዕንቁላል አስታቀፋችኋት። አሁን ደግሞ እሷኑ ለመጣል እግሯን በመጫኛው አሠራችኋት። ሥራው እስከዚህ ድረስ ነው።

ኧረ ይብቃ! ይህ ዓይነቱ ተግባር አብረዋችሁ የሚውሉትን ሰዎች ወይንም ድርጅቶች እንድንናገር አታስገድዱን። የኛ እኮ አመክሮ «ጓደኛህን ንገረኝና ያንተን ማንነት እነግርሃለሁ» ነው። ባትነግሩንም ነጭ ሽንኩርት የበላ አፍን በሽታው እናውቀዋለን። የኢትዮጵያዊ እኮ ምሳሌያዊ አነጋገሩ «እንኳን ይችን የዝንብ ጠንጋራ እናውቃለን» ነው። ያልሆነውን ይሁን እንዴት ይባላል። ሕጋዊው ሲኖዶስ በአሜሪካ ከኢትዮጵያ ጋር ምንም ምን አይነካካ። ይህ ራሱ አፈፃፀሙ እጅግ በጣም ነፍስ የሚያስቀርር ነው። ለእውነተኛ ኢትዮጵያዊ ተዋሕዶ አርቶዶክሳዊ ጸሎቱ ምነው በዚህ ዘመን ባልተፈጠርሁ ባልነበርሁ ይህን ባላየሁ እየሆነ ነው። ይህ አሜሪካ ተወለደ ተብሎ የተነገረለት ሲኖዶስ እነሆ ታዬ። በተለይ

ለኢትዮጵያውያን «በከመ ሰማዕነ ከማሁ ርኢነ።» [እንደ ሰማነው ዓየነው] ሆነ።

ከዚህ ላይ እንደ ቤተ ክርስቲያን ልጅነት የምወቅሰው በአንጻሩ ሁለቱንም ነው። አሜሪካ የማይሠራ ነገርም ሆነ እቃ የለም። ሁሉም ነገር ከትርፍ ጋር የተየያዘ ነው። ንግዱ ከእቃ ላይ ብቻ ያተኮረ አይደለም። የሃይማኖት የፖለቲካ የዲሞክራሲ የነፃነት የሰው ልጅ መብት ጥበቃ ሁሉም የንግድ ሸቀጦች ናቸው። ስለዚህ ትርፍ ከተገኘበት የማይሸጥ ምን ነገር አለ? ገበያ የሠጠውን መቀበሉ ግዴታ ነው። በኛ አነጋገር ገበያ የሚሠጠውን የእናት ልጅ አያሠጥም አይደል የምንለው? ከዚህ ላይ ነው ቅዱስ ሲኖዶሱ ምንም እንኳ ለማውገዝ ቢፈልግም ወንጀለኛውን ለመያዝ ሲባል ቀይ መብራት ጥሶ በመሄድ አይደለም። እንዲያ ዓይነቱ አሠራር ከወንጀለኛው ይልቅ ሰላማዊውን ሰው መጉዳት ይሆናል። ያ ድርጊትና አፈፃፀም ደግሞ ጥላቻን ያተርፋሉ። «እንዲያውም አልቅስ አልቅስ ይለኛል እንኳን እናቴ ሞታ» ይሆናል። በሌላ በኩልም ሆድ ለባሰው ማዊድ አታውሰውንም ማሰብ ያስፈልጋል።

ቢያንስ ቢያንስ እንደ አበው ነገሮችን በፍጥነት ከማድረግ ይልቅ ሱባዔ ሊገባበት ይገባል። ከአፍ ከወጣ አፋፍ ነውና የራዲዮና የቴሌቪዥን ዘመን አይደል ያውም እንተርኔቱ ተጨምሮበት፤ ጥንቃቄ ማስተዋል ይገባል። አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ለልጃቸው ስም ሲያወጡ ማስተዋል ይሉታል። አንዳንዶቹ ደግሞ ደምሳቸው ይላሉ። ሁሉም ምክንያቶች አሏቸው። ይሁንና ሲሮጡ የታጠቁት ሲሮጡ ይፈታል ብለው አበው የሚነግሩን ከፍተኛ ርጋታና ማስተዋል እንደሚገባ ለማጠየቅ ነው። ስለዚህ ቅዱስ ሲኖዶሱ ጉዳዩን እያወቀ ረጋ ብሎ ከሲኖዶሱ ውግዘት የምዕመናኑን ውግዘት ማስቀደም ነበር። ከዚያም ምክሩና መከራው ሁሉ የማይሳካ ከሆነ የቅዱስ ሲኖዶሱ ውግዘት ለተግባሩ እንደ አቡነ ዘበሰማያት ማሳረጊያ ይሆን ነበር። ከተዋኑ ለማሸነፍ እንጂ ለማባረር መሆን አልነበረበትም። ምክያንቱም ተመልሶ ይመጣላ! ያውም በንት ራሱን ለተዋጊነት ካሰለፈ ኃይል ጦርነት ማድረግ ጥሩ የጦር መሪና አማካሪዎችን ይሻል። መረሳት የሌለበት ገንዘብ ካለ የሚሰለፍና የሚዋጋ አለና ነው።

አሜሪካ ገንዘብ ከሁሉም ቀዳሚነት አለው። የገንዘብን መግቢያ በር የሚዘጋ ሃይማኖትም ሆነ ፖለቲካ ማለፊያ የለውም። ባትቸኩሉ ኖሮ የአሜሪካውን ሲኖዶስ ወደ ባዕቱ ይመለስ ነበር። አስቀድሞ በጦር የተወረወረበት አውሬን በሰላም መያዝ ፈጽሞ አይቻልም ሳይሆን መተማመኑን ያርቀዋል የሚል ስጋት አድሮብኝ

ነው። ይሁንና ለመንፈሳውያን አባቶች ሠይጣንን ድል መንሳት ለነገሩ ጦርም አያስመዝዝም። ባጭሩ ፃዕ መንፈስ ርኩስ ማለት ነው። በጥቅሱ ውግዘቱ መቅደሙ ትክክል አልነበረም ለማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ አባት ተሁኖ የአባትነት ሥራ መሥራት እንጂ ደግሞ ተብሎ ተብሎ የሲኖዶስ ነጻ አውጭ ድርጅት እናቆቁምን? አባቶች የሰላም ሰዎች ናቸው። ጦር መሣሪያቸውም መስቀላቸው ነው። አሜሪካ ሲገባ ወደ ጦር ተለወጠን? ሰላማዊነቱን ለማን ሰጠው? ወይንስ እንደ ሮማውያን መስቀሉን ወደ መቅጫነት ተለወጠ ወደ ጥንተ ተግባሩ ተመለሰን? አብሮ መዋልና ማደር እኮ የማያስተምረው ነገር የለም። የአፍሪቃ ሕዝብ ሰቅድሚያ ልቡ የደነዘዘው በመጽሐፍ ቅዱሱና በመስቀሉ ነገር ነው። ከዚያ በኋላ ነው ወታደሩ የመጣውና ወደ ባሪያነት የተለወጠው አገሩን የተዘረፈው። ይህም እንደሙያ ተቆጥሮ ተገልብጦ ይሆን ነው ሥጋቴ።

መቼም ሁላችንም እንደምናውቀው በሕግ ካለችው ባለቤት ውጭ የተወለደ ልጅ ስሙም ዲቃላ ነው። ምንም እንኳ ስደት ለወሬ ያመቻል ቢባልም ቅሉ ዲቃላ ወለድሁ ብሎ መናገሩ ራሱ ያስነውራል። ለሰሚውም ግራ ነው። በምንም መልኩ ሕጋዊ ልጅ ሊሆን አይችልም። እንደ ኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ሕግ መሠረት አባት ልጄ ነው ብሎ ካልተቀበለው እንደ ልጅ ወራሽ ሊሆን አይችልም። ይልቁንስ ወደ ንስሐው ተመለሱ። ተፀፀቱ አልቅሱ ጡሁ ምርር ያለ ልቅሶ አልቅሱ ያላችሁ በር ይህች ብቻ ናት። አኛም አብረናችሁ አንሆናለን ወደ ንስሐዋ ፈታችሁን ካቀናችሁልን። ለነገሩማ የአክብሮትና የወንድማማችነት ጥሪም ተደርጓል። የማያጠፋ የለም። የአዳም የዚያ የየዋሁ ልጆች አይደለንምን? የጥፋቱ ሁሉ ቁንሮ የሚሆነው ግን ወደ ንስሐ ያለመመለሱ ነው። ወደ ሌላ አገር ሂዶ መኖር እኮ የማደርገውና የምሠራው አይታወቅብኝም ብሎ ያልሆነ ተግባር መፈፀም ለሕተት ነው። ይህም ማለት እንደ ምላሊያችንና እንደ አበው ተመክሮ «ጅብ ከማይታወቅበት አገር ሂዶ ቆዳ አንጥፉልኝ አለ» እንዳይሆን ነው።

ታዲያ ይህን ላደረጉና ለፈፀሙ አባቶች ይቅርታ በንስሐ ከመስጠት ወዲያ ምን ይደረጋል? ቤተ ክርስቲያናችን ደግ ናት። መንፈሳዊት ናት ርኅርኅት ናት የሚያሰኛት ይህን መሳይ በደል ለፈፀሙ ሁሉ ይቅርታ መስጠቷ ነው። ተገዝቶ መሞት እንኳን ለመንፈሳዊው ሕይወት ቀርቶ ለዓለማዊውም ሕይወት ታላቅ እንቅፋት ነው። እስካሁን ለተፈፀመው በደል ሁሉ ማጠቢያው ንስሐ ነው። ይቅር ማለትና መበባል ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ ሥርዓት ነው። ይህን ለእናንተ ምኑ ይነገራል። ይዋል ይደር ላይባል ወደ ንስሐ ተመለሱ። ታረቁ ይቅር ተባባሉ። የቅዱስ ጴጥሮስ ልጆች

እይደላችሁምን? ግዝቱስ በሥልጣነ ጴጥሮስ ወጳውሎስ አይደለምን? ታዲያ ከዚህ ነፃ የምታወጣዋን ጸሎተ ንስሐዋን በተለመደው ጸሎት መድገም ነው። ለጴጥሮስስ ከመምህሩና ከጌታው የተሠጠው መልስ «ወይቤሎ እግዚእ ኢየሱስ ኢይብለከ እስከ ሰብዕ አላ እስከ ሰብዓ በበሰብዕ» [ወንድሜ ቢበድለኝ ሰባት ጊዜ ይቅር ልበለው? አይደለም ሰባት ጊዜ ሰባ እንጂ። ማቴ. 18:22]

ታዲያ ይህን ተራራ የሚያህል ትዕዛዝ ከፈታችን እያለ እንዴት ይቅር ላንበባል ውለን እናድራለን? እንኳን ዓመታት ልናሳልፍ ይቅርና! ይህን ስናይ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ያሰኘናል። ምንም እንኳ በሉ ባንባል ሁኔታው ያሰኘናል። ይህን የመሰለውን ነገር ስናይ ታላቅ ስሕተት አይደለምን? እኔስ ነገሩ ተለወጠብኝ። መጽሐፉ የሚለው እንደዚህ ካህናቱ አባቶች የሚያደርጉት ሌለኛኮ ሆነብን። መልካም አርዓያነታችሁን ብቻ ላይሆን ግዴታችሁን ተወጡልን። ለኛ እኮ ይህን የመሰለውን ጉዳይ እንዳልሆነ ሆኖ ስናየው ለብዙዎቻችን ከኖርንበት ቤት ለመልቀቅ ያስገድደናል። ብዙዓን አባቶች ሆይ ለኛም ለዚች ለብቸኛዋ ቤተ ክርስቲያናችን ልጅነታችንን እንድንወጣው ተባበሩን። ከውጭ ለተወለደና ላደገ ሰው ያውም አሜሪካዊ ለሆነው ሲኖዶላችሁ አታስረክቡን። ከዚህ የተወለዱት ሌሎች ሃይማኖታዊ ድርጅቶች ኢትዮጵያ ገብተው ቁም ስቅላችንን እያወጡት ባለበት ሰዓት ከኢትዮጵያውያን አባቶች የተወለደ አሜሪካዊ ሲኖዶስ እነሆ ማለቱ ለሌሎች መከላከያ መፈጠሩ ነው? ወይንስ ወንድም ጨመርንላችሁ ሊሆን? ይህስ ራስን በራስ እንደ መግደል ነው። ምዕመናኑንም እጥፍ ድርብ ጊዜ መበደል ነው። ይህስ ሊሆን ቀርቶ ሊታሰብም የማይገባው ነበር። ነገር ግን አደረጋችሁት ፈፀማችሁት። አይዟችሁ በርቱ ባዮችም ኢመንፈሳውያን ናቸው። አገራረሱንም ሆነ ገርፎ መጮሁን የተካኑበት ናቸውና አይደንቁንም። ነገር ግን ጥያቂያችን ጨለማን ከብርሃን ጋር መቀላቀልን ምን አመጣው ነው። «መኑ ዘደመሮ ለጽልመት ውስተ ብርሃን» አይደል አበባሉ?

አባቶች ሆይ! ጣት ገማ ብለው ቆርጠው አይጥሉት ነውና ወደ ማንነታችሁ ተመለሱልን። የቤተ ክርስቲያናችንን ክብር አታስደፍሩብን። እናንተ በነደላችሁት ቀዳዳ ሌላ መከራ መድኃኒት የሌለው በሽታ አታስገቡብን። ያለው ደዌ ይበቃናል። ይህን የእምነት ተላላፊ ደዌ አታሠራጩብን። ምክንያትም አትሁኑብን። እነሱ ያመጡብን ደዌ ተብላችሁም በትውልድ ዘንድ ስማችሁ አይብጠልጠል። ኢጣሊያኖች በሞሶሎኒ፥ ጀርመኖች በሂትለር የሚኮሩባቸው ይመስሏችኋልን? አይደለም ያፍሩባቸዋል። እነሱም

የክፉ ሁሉ ነገር ምሳሌዎች ሆነው ቀርተዋል። የታሪክ ወንጀለኞች ሆነው አሉ ይኖራሉ። የእነሱም የሕይወት ፍፃሜ እንዳላማረ ታውቃላችሁ።

ብፁዓን አባቶቻችን ሆይ! እናንተም አሜሪካ መጥታችሁ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ክፈላችሁ ተብሎ ስማችሁ እንዲነሣ እንዲወደስ ትፈልጋላችሁን? አይደለም አይሆንምም። በምንግዴለሽነት በማን አለብኝነት አንጠየቅም አንወቀስም ርምጃም አይወሰድብንም ብላችሁ አስባችሁ ምድራዊ ቅጣት አሥራትና ሞት ፈርታችሁ አያላችሁ አንዲህ ዓይነቱን ተግባር ስትፈጽሙ የአናንተን ጠንካራነት ማሳየት ወይንስ ደካማ ጎናችሁን ገልጠ በአደባባይ ማስተዋወቅ? የሰሎሞንን ፍርድ አስታውሱ። ሕፃኑ ለሁለት ተቆርጠ እንዲሠጣት የተስማማችው አናት ያልወለደችው ልጅ መሆኑን ስለምታውቅ ነው። ይህ ፍርድ ዛሬም ከአናንተ ዘንድ ቀርቧል። የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስን ለሁለት ቆርጣችሁ ስትወስዱ ማንን የመሰላችሁና የሆናችሁ ይመስላችኋል?

መልሱን ለአንባብያንና ለቤተ ክርስቲያኒቱ ምዕመናን ልተወው። አንደኔስ ከሆነ ይልቁንም በነፍሰ ገዳይነት የሚያስጠይቅ መስሎ በግልጽ ይታየኛል። መናገርና መመስከርም አችላለሁ። ማን ይንገር የነበር ማን ያርዳ የቀበር ነውና በጉዳዩ ጣልቃ ገብቼ አባቶቼን ይህ ነገር ይቅር ቤተ ክርስቲያናችንን ይጎዳል ይከፍላል ብለው ከተማፀኑትና ልመና ካቀረቡት ሰዎች መካከል ራሴን ስለምቆጥር ነው። ይሁንና በየትኛው አንቀጽ እንደምትከስሱ አንቀጹንና ንዑስ አንቀጹን ጠቅሼ ባልነግራችሁም ቅሉ ወንጀሉ ወንጀል ነው። በጥቅሉ ግን ነፍስ የገደለ ሰው ወንጀለኛ ለመሆኑ አያጠራጥርም። ምንም እንኳ ነፍስ ያጠፋና የጠፋበት የመከሰሺያ አንቀጽ ልዩነት ያለው መሆኑንም ባልዘነጋውም።

እናንተም ይችን ጥንታዊትና ለዓለም ሕዝብ ብርቅ ድንቅ የሆነችዋን ቤተ ክርስቲያን ለግል ክብራችሁና መኖሪያችሁ ብላችሁ ለሁለት ስትሠነጥቁ እንዴት ወንጀል መሆኑ አልታያችሁም? ካለማወቅ ወይንስ ጭካኔ? ያለማወቅ ያለመጠንቀቅ ብዬ ብል ትረዱበት ይሆናል። የፓትርያርክነት ሹመት ቤተ ክርስቲያንን ለመደገፍ አንጂ ለማዳን አንጂ ጨክን አድርጌ ብናገረው ለመግደል ነውን? አንድነቷን ማንነቷን ለማጥፋት ይሆናልን? ለቤተ ክርስቲያናችን ክብርና ዝና እየፈፀማችሁ ያላችሁ መስሏችሁ ይሆንን? ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስን የጎዳን መስሏችሁ ይሆንን?

ለኔ የሚታየኝ ግን አይደለም። እሳቸውም አሜሪካ ነበሩ። ከዚህም ቆይተዋል ኖረዋል። ነገር ግን አንዲት ቀን እንኳ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን እንዲህ አሏት እንዲህ አደረጓት አልተባሉም። አሁን ነው ይህን አላደረጉም ይህን አልሠሩም ለመፈንቅለ መንግሥቱ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን እንደናንተ አልተባበሩም የእነሱን ጡሽት ይዘው አልቀረቡም ከሆነ መቼም ሁላችንም እንደምናውቀው በደርግ ጊዜ የተሾማችሁና የተሸለማችሁ ነበራችሁና እናንተስ ምን ሠራችሁ? ምን አደረጋችሁ? ተብላችሁ ብትጠየቁ መልሳችሁ ምንድን ነው? «ያንቱ ያንቱ ይመክቱ፡ የኔ የኔ ይፈነክቱ» አይሆንባችሁምን? ይህንም ሰል ዝም ማለት አለባቸው አይናገሩ ለማለት አይደለም። ወቀሳው ግን በናንተ ባይሆን ያምራል ለማለት ነው።

የሰው ልጅ መብት እንደ ዋቃ የተረገጠበት ጊዜ ቢኖር የደርግ አስተዳድር ነበር ከአሁኑ ቢበልጥ እንጂ አያንስም አይደለምን? በዚያን ጊዜ የእናንተ ድርሻ ምን ነበር? ያደረጋችሁት አስተዋጽኦ ምንድን ነው? ጥፋተኛው እሱ ነው ብላችሁ በጣት ስታመለክቱ አራቱ ጣቶች ግን ወደ እናንተ ያላያሉ እንደሚባለው ሁሉ አንዷን ጣት እንኳን ስታመለክቱ ታያችሁ ተብሎ ስትታሙ አልሰማንም አላየንም። በዚህን ጊዜ የበለጠ በደለኞች መሆናችሁን ማመልከታችሁን እናያለን። ትላንትም ነበርን ዛሬም አለን። «በዘነአምር ንኅግር ወበዘርኢነ ሰማዕተ ንክውን።» [ያየነውን እንመሰክራለን። የምናውቀውን እንናገራለን። ዮሐ 3:11] ይህ እንግዲህ እናንተም እኛም አኩል አይተናል ተመልክተናል። ፍርድ ሰየግል ሰየቅሉ መሆኑ ነው። መቼም አኩል ካልፈረደን ከሆነው ዘንድ ፍርድ ተገምድኋል። ታዛቢ ይፍረድ ብሎ ማለቱ ግን የግድ ይሆናል።

ይሁንና አንድ ነገር ልጨምር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ያሉበት መንግሥት ስንት በደል ሲፈጽም አላወገዙም አልኮነኑም አልፈው ተርፈውም ውግዘት አላሰሙም ተብለው በተቃዋሚ ክፍሎች ዘወትር ይኮነናሉ በፖለቲካ መንዶ ይቀጠቀጣሉ። እሳቸው ደግሞ የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ብለው ከሚሠራው ከሚፈፀመው ሁሉ በአርምሞ ተቀምጠዋል ተብለው ይወቀሳሉ። እሳቸው ለመናገርና ለማውገዝ ክተነሡ ደግሞ ያሉበትን መንግሥት ብቻ ሳይሆን የመንግሥት ተቃዋሚዎችንም ያካትታል እንበል። ታዲያ በዚያን ጊዜ ሰባት ጊዜ ሰባ ሰላም ሳይሆን ጥላቻውን የበለጠ አያከረውምን? ስሕተት ከመንግሥት ብቻ ሳይሆን ከተቃዋሚዎችም መቼም ሰዎች ናቸውና አይጠፉም እንበል በእርግጥ ይኖራል

በእርግጥም ሰዎችም ናቸው እንደ ሰው ይሰላታሉ ብሎ ለመናገር ምንም እንኳ በአሁኑ ሰዓት በዝናም ጊዜ ምላስን እያወጡ በሠይጣን መቀስድ በመብረቅ ለመመታት ያመቻቻል አይደል የሚባለው? እንደዚያ እንዳይሆን ብዬ ነው። የሆነው ሆኖ ስሕተት ሲሠራ ሲመለከቱ የድምፅ ማጉያውን ይዘው ሕዝቤን አትበድል አርፈህ ተቀመጥ የምታደርገውን ሁሉ እኮንናለሁ ብለው ቢናገሩ ለመሆኑ እንዲህ አሉ ተብሎስ ይነገርላቸዋል ወይ? እንዲያው እግር ጥሏቸው ቢያደርጉት ለማለት ነው። ማንም አይናገርላቸውም። እሳቸውስ ቢያንስ ቢያንስ የምትሠሩት ገጽታችሁን በዓለም ሕዝብም ሆነ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ያስከፋባችኋል ሳይሉ ይቀራሉን? በሬዲዮና በቴሌቪዥን አይሁን እንጂ! የዓለምን ትኩሳት የመለካትና የመመልከት ብልሃቱ እውቀቱ አላቸው። ለፖለቲካውም እንግዳ አይደሉም። የሚያነቡ የሚመራመሩ ናቸው። ኃይሉ ችሎታው በሚገባ አላቸው። በዚህ ሁሉም የሚስማማበት ነው።

ነገር ግን አሉም አላሉም እንኳን እሳቸው ልዕለ ኃያላን አሜሪካ የሚሉት ሁሉ ለጋዜጦች ማኅበረሰባዊያ እንጂ በእውነት ስለ እውነት ነውን? አይደለም። አሁን ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ችግር ለማውሳት ስለሆነ አነሳሴ መንገዴን አታስቀይሩኝ። ያለማውገዛቸው ያለመኮነናቸው በራዲዮና በቴሌቪዥን ቀርበው ይህን ባለማድረጋቸው እኔም ልጋራው ልበል? አባትነታቸውን የሚጓጉጥ ነው ብለው ቢያዩት ከማድረግ ለምን እንደተቆጠቡ ቢናገሩም ለሚም የላቸው። ይሁን እንጂ በአባትነታቸው የሚሠራውን ስሕተት ከሚሠራው መልካም ነገር ጋር አንዱን በቀኝ ሌላውን በግራ ይዘው ማሳየት መንገር እንዳለባቸው እኔም እስማማለሁ። ሌላው ቢቀር በፋሲካውና በዘመን መለወጫው ጊዜ ከእንኳን አደረሳችሁ ጋር ቢናገሩት መልካም ይሆናል። ይህም ይህን አሉ ተብሎ ቢነገር ምን ያህል የተራበ እንደሚያጠግብም ባላውቅ የአባት ሙያው ጠባዩ ባሕርዩ ስሕተት ሲሠራ ዝም ያለማለት መቆጣት የዕለት ከዕለት ተግባሩ ነውና ቢደረግ ቢፈጽሙት እነሆ! አቤት እላለሁ።

ከዚህ ላይ ወደ «ጸልዩ በእንተ ሰላመ ቤተ ክርስቲያን» [ስለ ቤተ ክርስቲያን ሰላም ጸልዩ] ወደሚለው አቤቱታ ልሸጋገር። ይህች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የሰላም አደባባይ ናት። ከራሷስ ተርፎ ለሌሎች የምታድለዋ እንዴት የሰላም መራብ፥ የሰላም መጠማትና የሰላም መታረዝ ይገጥማታል? ስለ እውነት፥ ስለ ሰላም እንዴት አይጸለያም? ያንዲት ቤተ ክርስቲያን አባቶች፥ ያንዲት መንበር ተወካዮች እንዴት ልዩነትን ከመካከላችሁ ማባረር አቃታችሁ? ይህ መቼም በጣም የሚያበሳጭ፥ የሚያሳዝንና የሚያስለቅስ ነው። በስደት

ያላችሁ አባቶች በደረሰባችሁ መከራ በገጠማችሁ ችግር ላገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ በመሆናችሁ እናዝናለን። ይሁንና ያንን ያቻቻላችሁና ሚዛኑን የጠበቃችሁ መስሏችሁ ይሆን ሌላ ሲኖዶስ ያስፈለጋችሁ? ይህን መፈፀማችሁን ሰኅሊናችሁ ደስ ብሎት የምትቀበሉት ቢሆን ኖሮ እንዴት ባማረ በነበር። ነገር ግን አይደለም መከራና ደይን እንጂ! ጥርስ በሚፋጭበት ዋይታ በሚሰማበት ቦታ መታሠር እንጂ! በእርግጥ በስደቱ ትክክለኛነት አምናችሁ የተቀበላችሁት ቢሆን ኖሮ፥ «ወአንሰ እብለክሙ አፍቅሩ ጸላእተክሙ ባርክዎሙ ለእለ ይሰድዱክሙ። ሠናየ ግበሩ ለእለ ይጸልኡክሙ» [ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁንም መርቁ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ። ስለሚያሳድድዱአችሁም ጸልዩ። ማቴ.5:43-44] ይህ ታላቅ ሥራ እንዴትና ለምን ታስፈ? መከራ ሲያደርሱባችሁ ደስ ይበላችሁን ምን ሠረዘው? በዚህ ፋንታ የሆነው ጥርስን በጥርስ መስበር ነው። ጥርሰ ወላቃ ሆኖ እኮ የምትታየው ቤተ ክርስቲያናችን እንጂ እናንተማ መቼ ትሰባበራላችሁ። ተጎጅዎቹ ማንኛችሁም አይደላችሁም። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ናት። ይህ አፈፃፀም ደግሞ የሚረዳውና የሚያገለግለው ምርጡ በተሠነጠቀ ግድግዳ ለሚደበቁት ለሚውሉትና ለሚያድሩት ለእነ እባብ እስስትና እንሽላሊት ለመሳለሉት በልባቸው ለሚሳቡት በእግር እንኳ ለማይሄዱት መርዘኞች ለምድር አራዊት ነው። በዚህ በተፈጠረ ክስተት ማን ተጠቀመ? ጠላት ማንስ ተጎዳ? ቤተ ክርስቲያናችን ነው። ከዚያም በላይ ደግሞ ቤተ ክርስቲያኗንና ምዕመናኑን ነው። በእውነቱ በዚህ ድርጊት ምዕመናን እጅግ በጣም አድርገው ግራ ተጋብተውበታል። የዘወትር ቁጭትና ፀፀትም ሆኗል።

ነገር ግን ክርስቲያኖች ያውም የጥንታዊቷና የኦርቶዶክሳዊቷ ተዋሕዶ ልጆች ነንና ተስፋ አንቆርጥም። ተስፋም የጽናታችን ዋልታ ነው። የምንጠብቀውና ማየትም የምንሻው የእንዲት ቤተ ክርስቲያን አባቶችን በአንድነት ጉባዔ ነው። መቼም እንዲህ ሁኑ ይህን አድርጉ ብሎ ኃላፊ ማቅረብ ኦርቶዶክሳዊ መብታችንና ግዴታችን መሆኑን ማንም አይነግረንም አያስረዳንም አይመክረንም። የማመልከትና የመወትወት ግዴታችን ሃይማኖታዊና ብሔራዊም ነው። ዕድሜያችንና አመክሯችን የግድ ይሉናል። ጥያቂያችንም መንፈሳዊ ነውና አቀራረባችንም በትሕትና ነው።

የአባቶች በምዕራፍና በቁጥር መለያየት ምዕመናንን እጅግ በጣም የሚያስጨንቅ፥ ሰሚዎችን ደግሞ የሚያስደንቅ፥ ለጠላቶቻችን ደግሞ ዘገር የሚያስነቀንቅ፥ መሬት የሚያስገርፍ ሆኗል። በእውኑ ይህን የመሰለውን ጉዳይ ይዞ፥ ውሎና ማደሩን

እንዴት ቻላችሁት? እንዴትስ ኖራችሁትና አላችሁት? ሲያስቡት እንኳን ራሱ መንፈስ የሚያስጨንቅ ኃዘኑ ራስ የሚፈጠርቅ ነው። ይህንስ ያህል ሩቅና አድካሚ ረዥም የአገር ጉዞ፥ የመንፈቅ ጎዳና አይደለምን? እንዴትስ ቻላችሁት? እንዴትስ ያለ እርቅና ያለ ንስሐ ታገሣችሁት?

እንግዲህ አቤቱታችን ይህ ነው። ወደ ንስሐ ተመለሱ በእርቅ ታጠቡ የፍቅርን ቀሚስ ልበሱ የሰላምን አስኬማ አጥልቁ ነው። የሰላሙ እጦት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ ችግር ነው። የሰላሟ ዛፍ ፍሬ ካልሠጠች ምን ትሆናለች? ዛፏም ትቆረጣለች፣ የሰላምም ፍሬ ትጠፋለች። በምዕመናን ዘንድም ታላቅ ረሀብ ይሆናል። የሰላም መራብ ደግሞ የነፍስና የሥጋም አብሮ መራብና መጠማትም ነው። ይህን ደግሞ ከአባቶች የበለጠ ማን ያውቀዋል? ማንስ ይረደዋል? ታዲያ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ተርበን አጽማችን ፈጥጦ በጠላት ዘንድ መሣቂያ፥ ስወገን ማስለቀሺያ ስንሆን ምን ይመስላችሁ ይሆን?

ቅዱሳንና ብፁዓን አባቶች ሆይ! በዛሬዋ ሕይወታችሁ ነፍሳትን አድኑበት። በጎቻችሁን ጠብቁበት። ዛሬ በመሆን ላይ ያለውን እንዴት እንደምትመለከቱት ባላውቅም ቅሉ «ዳርዋ እሳት መህልዋ ገነት» የነበረችዋ ቤተ ክርስቲያናችን መህልዋም ዳርዋም ገሃነመ እሳት ሆኗል። በጎቻችሁ የት ውለው የት እንደሚያድሩ ብትገነዘቡትስ እንኳን ወቅቷን ጠብቃ የምታልፈውን ሕይወታችሁን ቀርቶ ምንም ምን የማታደርጉት ጉዳይ ባልነበር? ይሁንና በሚያልፈው ሕይወታችሁ የማያልፍ ቋሚና የቀሪ ሥራ ሐውልት አንጹበት። ይህ ሲሆን የግድ መሆኑን ልንገልጽ ልናመለክት መንፈሳዊ ሕይወታችን እጅግ ያስገድደናል።

አንድ ጉዳይ ላመልክት። የዚች ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በተኩላዎች በየቀኑ እየተበሉ መሆኑን ስንት ጊዜ ተመልክታችሁታል? መቼም ሰማንያ አሐዱ መዳሕፍት መክረው ያልመለሱንን አንድ ቆርማዳ ምዕመን ሊመልሰን እንደማትሉ ርግጠኛ ነኝ። ጸሓፊው መልእክተኛና መሥካሪ እንጂ! የቤተ ክርስቲያኗን አስተዳደርም ሆነ ሌላ ድርጅት የምወክል አይደለሁም። የምወክለው እኔኑ ራሴንና የማንነቴን መታወቂያነት የሆንሁባትን ኢትዮጵያዊት ተዋሕዶ አርቶዶክሳዊነቴን ብቻ ነው። ሌሎችን ለማውገዝና ለመኮነንም ዓላማና ተልዕኮም የለኝም። ነገር ግን እንዲህ ዕጅ እግሩን ያጣ ችግር ሲመጣ ግን ስመነግት ሃይማኖታዊና ኢትዮጵያዊ ግዴታ አለብኝ። ከዚህ ውጭ የሚነግም ሆነ የሚጣል አንዳችም ምክንያት የለኝም። ሰው ለመዝለፍ፥ አካኪ ዘራፍ ለማለትም

አይደለም። አንዲያውም ራሴን የምመለከተው «አነ ኃጥዕ ወአባሲ» [እኔ ኃጢዓተኛውና በደለኛው] ብዬ ነው። እኔ በእውቀትና በአስተሳሰብ ንዑስ የሆንሁት ምዕመን ልቅርና ንጉሡ ዳዊት እንኳን «አንሰ ዕዴ ወአኮ ሰብእ» [እኔ ከሰው ያነስሁ ትል ነኝ [መዝ. 21:6] ብሏል። ቤተ ክርስቲያናችን የአትሕቶ ርዕስ መፍለቂያ ነበረች። አሁን ግን ናት ለማለት እጅግ ይከብደኛል። እንደዚያ ብል ደግሞ ምጸትና ውዳሴ ከንቱም ይሆንብኛል ብዬ አስጋለሁ።

በአሁኑ ጊዜ ምዕመናን ሰላምን ተጠምተናል። ሰላምን ናፍቀናል ለዚህ ለጥማታችን ማስታገሻ ደግሞ ውሀ ስንጠይቅ ህሞት እየተጋትን ነው። እንዲህ መሆናችንን አሁንም መናገሩ የግዴታ ግዴታችን ነው። ይሁን እንጂ በአባባሌ ንስሐ ሳልገባ ይቅርታ ሳልጠይቅ ግን እንዳሳልፍ ኢትዮጵያዊ አርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ ክርስቲያናዊ ሕይወቴ የግድ ይሰኛል። ዝሆንና ዝሆን ሲጣሉ የሚጎዳው ሣሩና በአካባቢው ያሉት ዕፀዋት ናቸው። እኒህ ጥቃቅን ዕፀዋት ደግሞ ምዕመናን ናቸው። አሁን ችግሩ የደረሰው በመሳው ምዕመናኑ ላይና በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያኗም ጭምር ላይ ነው። እኛ ግን አሁን እየተጨፈላለቅን፥ እየተረጋገጥንና እየቆሰልን ነው። ሁኔታችንን የሚያዩና የሚመለከቱ የምሕረት ዓይኖቻችሁን አሁንኑ እንሻለን። አቤት የግድ ግድ እንላለን። ቁጣውን በትዕግሥት፥ መዓቱን በምሕረት ብላችሁ መልሱልን። ታረቁና በአሐቲ መቅደስ ሥጋውን ብሉ ደሙንም ጠጡ። ከዚያም ለምዕመናን አቀብሉም ስጡ።

ቅዱሳንና ብፁዓን አባቶች ሆይ! በአሁኑ ሰዓት አባቱን የማያውቅ ልጅ እየተወለደ ነው። «አባቱን አያውቅ አያቱን ናፈቅ» ሆኗል። ያም አባትህ እኔ ነኝ። ያም እኔ ነኝ እያለው በከፍተኛ ውሸንብር ላይ ነው። ምንም እንኳን ለአንድ ብቸኛ ክርስቲያናዊ፥ ያውም አርቶዶክሳዊ፥ ኢትዮጵያዊ ምዕመን አዎ! ብዙ አባቶች አሉት። እነሱም ወላጅ አባት፥ የክርስትና አባት፥ የነፍስ ወይንም የንሥሐ አባት፥ የቀለም አባት «አሕደ ቀለም ዘነገረከ ይኩን ከመ አቡከ» [አንድ ቀለም ያስተማረህን እንደ አባትህ ይሁን] ከዚያም አልፎና ተርፎ የጡት አባት፥ የእንጀራ አባትና የነገር አባት ናቸው። ይህም የሚያሳየው አባት ምን ያህል በሃይማኖታችንና በባሕላችን ከፍተኛ ቦታ እንዳለው ነው። በእናቶችም ዘርፍ እንዲሁ አለ። ያልኖረው ቢኖር የሴት የንስሐ እናት ነው። ነገር ግን አንድ ትንቢት አለ። አሱም ሁለተኛ የወንድ ንስሐ አባት እንዲኖረኝ አሳደርግም አለ የሚባለው ነው። ስለዚህ ሴቶችም የክህነት አገልግሎት የሚሠጡበት ዘመን ይመጣ ይሆናል ለማለት ነው።

ብፁዓን አባቶች ሆይ! የቤተ ክርስቲያኗ የአስተዳደር ሰንሰለት አሁን ቢበጠስም በንስሐ ይቀጠል ይታደስ። እንደ ነበረ፡ እንደቆየው ይመለስ። ይህን ብታደርጉ የሰላም አባቶች ናችሁ። ይህን ባትፈጽሙ ግን የምትጠብቁትኝ መንጋ ለተኩላዎች በትናችሁ ቤታችሁን ዘግታችሁ እንደ ተኛችሁ፡ ችላ እንዳላችሁና እንደ ሸሻችሁም ያስቆጥረባችኋል። ይህ ደግሞ የታሪክም ተወቃሽ ያደርጋችኋል። አማካሪዎች በእውኑ ይኑሯችሁ። ውሳኒያችሁ የተጠናና የተጸለየበት ይሁን እንጂ! እንዲያው ጣለው ግረፈው አይሁን። «ጎድግው ወመንገወ ለዝ ዓለም» [ይህን ዓለም ናቁት ተዉት] በሚለው መርህ ተነሥታችሁ የዚህን ዓለም ጣጣ አስቀድማችሁ ንቃችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማገልገል የመረጣችሁትን ጎዳና አሁንም አቅኑት። ወደዚህ አስቸጋሪው ዓለም ፃማና ድካም ገብታችሁ መንፈላዊ አመራራችሁን አታጠውልጉብን። እኛን በጎቻችሁን ጠብቁን። በተኩላዎችና በቀበሮዎች ተከበን በየቀኑ እየተነጠቅን ነው። በዚህም ምክንያት አሁንስ እጅግ በጣም ፈራን። ከመጠን በላይም ይበልጡኑ እጅግ ሠጋን ተርበደበደን ተንቀጠቀጥን። እናቱ ወንዝ የሄደችበት ልጅ ሳይሆን ልቅሷችን የሞተችበት ሆኗል።

እያንዳንዳችንም አሁንም እጅግ ፈራን። መሄጃ መሸሻ መጫሪያና መውጫ አጣን። አቤት ለአባቶቻችን! ከዚህ ቀውስ አውጡን። አድኑን ጠብቁን። ችላ አትበሉን ባይታወሮች አታድርጉን። አቤቱታችን፡ ልቅሷችንና ልመናችን ይህ ነው። አሁንኑ ተቀበሉን። ቤተ ክርስቲያናችን የእናንተን ሰላም ከሁሉ በፊት ትሻለች። ምነው ማንም ሲገባበት የማናየውን ሕንፃ ደጀ ሰላም ብለን መሠየሙ ብቻ የሰላም በር ከቤተ ክርስቲያን አለ ማለት በቂ ያደርገዋልን? ሰላምስ በምኞት ብቻ ልትገባበትና ልትወጣበት ትችላለችን? እንግዲህ ያለንበትን ሁናቴ በጥንቃቄ መርምሩት። በእውነተኛይቱ ስለ ኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ህልውና ስትሉ መፍትሔ ፈልጉልን። ይህንንም አቤቱታ ከስሞች ሁሉ ስም የበላይ በሆነው በእግዚአብሔር ስም እንጠይቃለን።

፫. ከፊተኛዋ የኋለኛዋ ትብሳለች፡

«ወትከውን ደኃሪት ጌጋዩ እንተ ተአኪ እምቀዳሚት» [ማቴ. 27:64]

ይህ ቃል ከራሱ ከወንጌሉ የተወሰደ ነው። የተባለበትን ምክንያት ስንመለከተው ከፍርሃትና ከስጋት የመነጨ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ይህን ቃል የተናገሩት የፈሪሳውያን ሊቃነ ካህናት ቤተ ምኩራባቸው ላይ አደጋ ያንዣበበ መሆኑን ተገንዝበው ነበር። ዳግማይ አዳም ኢየሱስ ዘወትር እንደሚነገረው ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ እንደ ሕፃን አድጎ የሰውን ልጅ በመስቀሉ እንደሚያድን በነቢያት አናግሮና አስመስክሮ መምጣቱን ዘንግተው ችላ ብለው ላሉበት ዘመን ለሹመታቸውና ለሥልጣናቸው እንቅፋት ይሆንብናል ሕዝብ ያቀለናል ቀቅሙ ይቀርብናል ብለው ማሰቀላቸውን ብቻ የተመለከቱና ያተኮሩ ስለነበር የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ሲል ተናገረላቸው። መጻሕፍትን የሚመረምሩና አዋቂዎች ሆነው ላለ የማንዛቤ እጥረት ነበረባቸውና ነው።

እኒህ የምኩራብ ሊቃነ ካህናት በሐናና በቀያፋ የሚመራው ሥርዓተ ምኩራብ ተንከባካቢዎች ነበሩና የሚያደርጉትን አላወቁም አላቸው። ባለማወቃቸው ይቅርታን አደረገላቸው። አውቆ ማጥፋትና ሳያውቁ ማጥፋት ከፍተኛ ልዩነት አለውና ነው። የሚሠሩትን ቢያውቁ ኖሮ የሚያደርጉትን ከመፈፀም ይታቀቡ ነበርና ነው። ነገር ግን ሳያውቁ ይቅርታ ሳይጠይቁ ምሕረት ተሠጣቸው። የሰውን ልጅ በሞቱ እንደሚያድን የመጣለትን ተልእኮ ቃል ሰው የሆነበትን በተዘዋዋሪ ፈጽመዋልና ነው። ታዲያ እኒህ ካህናት መቃብሩ እንዲጠበቅ ጠባቂዎች እንዲመደቡላቸው የጠየቁበት ምክንያት ከሞተ በኋላ ተነሣ ከተባለ የኛ ነገር ሁሉ ውሀ ይበለዋል ብለው ስግተው ነበር። ያለመገንዘባቸውን ያለማወቃቸውን ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ ነው የሚሠሩትን አያውቁምና ይቅር ያለላቸው። አሁንም ሳያውቁ አውቀው ከፊተኛዋ ኋለኛዋ ትብሳለች አሉ።

ይህን አባባል አቤቱታ ላስማበት ከፍ አድርጌ ልጮህበት ፈለግሁ። በእርግጥ ከፊተኛዋ የኋለኛዋ መባሏን ስላወቅሁ ስለፈራሁና ስለ ሠጋሁ ነው። መቶ በመቶ ግን ርግጠኛ አይደለሁም። ሥጋቴ

ብውዓን አባቶች ሆይ! የቤተ ክርስቲያኗ የአስተዳደር ስንሰለት አሁን ቢበጠስም በንሰሐ ይቀጠል ይታደስ። እንደ ነበረ፥ እንደቆየው ይመለስ። ይህን ብታደርጉ የሰላም አባቶች ናችሁ። ይህን ባትፈጽሙ ግን የምትጠብቁትኽ መንጋ ለተኩላዎች በትናችሁ ቤታችሁን ዘግታችሁ እንደ ተኛችሁ፥ ችላ እንዳላችሁና እንደ ሸሻችሁም ያስቆጥርባችኋል። ይህ ደግሞ የታሪክም ተወቃሽ ያደርጋችኋል። አማካሪዎች በእውኑ ይኑሯችሁ። ውሳኒያችሁ የተጠናና የተጸለየበት ይሁን እንጂ! እንዲያው ባለው ግረፈው እይሁን። «ጎድግው ወመንጎው ለዝ ዓለም» [ይህን ዓለም ናቁት ተዉት] በሚለው መርህ ተንሥታችሁ የዚህን ዓለም ባሳ እሰቀድማችሁ ንቃችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማገልገል የመረጣችሁትን ጎዳና አሁንም አቅኑት። ወደዚህ አስቸጋሪው ዓለም ፃማና ድካም ገብታችሁ መንፈሳዊ አመራራችሁን እታጠውልጉብኝ። እኛን በጎቻችሁን ጠብቁን። በተኩላዎችና በቀበሮዎች ተከበን በየቀኑ እየተነጠቅን ነው። በዚህም ምክንያት አሁንስ እጅግ በጣም ፈራን። ከመጠን በላይም ይበልጡኑ እጅግ ሠጋን ተርበደበድን ተንቀጠቀጥን። እናቱ ወንዝ የሄደችበት ልጅ ሳይሆን ልቅሷችን የሞተችበት ሆኗል።

እያንዳንዳችንም አሁንም እጅግ ፈራን። መሄጃ መሸሻ መግቢያና መውጫ አጣን። አቤት ለአባቶቻችን! ከዚህ ቀውስ አውጡን። አድኑን ጠብቁን። ችላ አትበሉን ባይታወሮች አታድርጉን። አቤቱታችን፥ ልቅሷችንና ልመናችን ይህ ነው። አሁንኑ ተቀበሉን። ቤተ ክርስቲያናችን የእናንተን ሰላም ከሁሉ በፊት ትሻለች። ምነው ማንም ሲገባበት የማናየውን ሕንፃ ደጀ ሰላም ብለን መሠየሙ ብቻ የሰላም በር ከቤተ ክርስቲያን አለ ማለት በቂ ያደርገዋልን? ሰላምስ በምኞት ብቻ ልትገባበትና ልትወጣበት ትችላለችን? እንግዲህ ያለንበትን ሁናቴ በጥንቃቄ መርምሩት። በእውነተኛይቱ ሰለ ኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ህልውና ሰትሉ መፍትሔ ፈልጉልን። ይህንንም አቤቱታ ከስሞች ሁሉ ሰም የበላይ በሆነው በእግዚአብሔር ስም እንጠይቃለን።

፫. ከፊተኛዋ የኋለኛዋ ትብሳለች፡

«ወትከውን ደኃሪት ጌጋዩ እንተ ተአኪ እምቀዳሚት»
[ማቴ. 27:64]

ይህ ቃል ከራሱ ከወንጌሉ የተወሰደ ነው። የተባለበትን ምክንያት ሰንመለከተው ከፍርሃትና ከስጋት የመነጨ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ይህን ቃል የተናገሩት የፈሪሳውያን ሊቃነ ካህናት ቤተ ምኩራባቸው ላይ አደጋ ያንዣበበ መሆኑን ተገንዝበው ነበር። ዳግማይ አዳም ኢየሱስ ዘወትር እንደሚነገረው ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ እንደ ሕፃን እድጎ የሰውን ልጅ በመስቀሉ እንደሚያድን በነቢያት አናግሮና እሰመስክሮ መምጣቱን ዘንግተው ችላ ብለው ላሉበት ዘመን ለሹመታቸውና ለሥልጣናቸው እንቅፋት ይሆንብናል ሕዝብ ያቀለናል ጥቅሙ ይቀርብናል ብለው ማሰቀላቸውን ብቻ የተመለከቱና ያተኩሩ ሰለነበር የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ሲል ተናገረላቸው። መጻሕፍትን የሚመረምሩና አዋቂዎች ሆነው ሳለ የግንዛቤ እጥረት ነበረባቸውና ነው።

እኒህ የምኩራብ ሊቃነ ካህናት በሐናና በቀያፋ የሚመራው ሥርዓተ ምኩራብ ተንከባካቢዎች ነበሩና የሚያደርጉትን አላወቁም እላቸው። ባለማወቃቸው ይቅርታን አደረገላቸው። እውቅ ማጥፋትና ሳያውቁ ማጥፋት ከፍተኛ ልዩነት አለውና ነው። የሚሠሩትን ቢያውቁ ኖሮ የሚያደርጉትን ከመፈፀም ይታቀቡ ነበርና ነው። ነገር ግን ሳያውቁ ይቅርታ ሳይጠይቁ ምሕረት ተሠጣቸው። የሰውን ልጅ በሞቱ እንደሚያድን የመጣለትን ተልእኮ ቃል ሰው የሆነበትን በተዘዋዋሪ ፈጽመዋልና ነው። ታዲያ እኒህ ካህናት መቃብሩ እንዲጠበቅ ጠባቂዎች እንዲመደቡላቸው የጠየቁበት ምክንያት ከሞተ በኋላ ተነሣ ከተባለ የኛ ነገር ሁሉ ውሀ ይበለዋል ብለው ሰግተው ነበር። ያለመገንዘባቸውን ያለማወቃቸውን ግንዛቤ ውስጥ አሰገብቶ ነው የሚሠሩትን እያውቁምና ይቅር ያለላቸው። አሁንም ሳያውቁ አውቀው ከፊተኛዋ ኋለኛዋ ትብሳለች አሉ።

ይህን እባባል አቤቱታ ላሰማበት ከፍ እድርጌ ልመህበት ፈለግሁ። በእርግጥ ከፊተኛዋ የኋለኛዋ መባሷን ስላወቅሁ ስለፈራሁና ሰለ ሠጋሁ ነው። መቶ በመቶ ግን ርግጠኛ አይደለሁም። ሥጋቴ

ግን ይችን ጌታዋን መሪዋን የቤተ ክርስቲያኗን ራስ ኢየሱስን አንድ ባሕርይ ብላ የምታምንን ቤተ ክርስቲያን ሁለት እየሆነች ነው። ከአንድነት ወደ ሁለትነት መበርከት አይደለም። መብዛትም አይደለም። ፀጋና ህብትም አይደለም። አንድን አካል ለሁለት መግመስ የቀዶ ጥገናም ጥበብ አይደለም። ካንገት በላይ ያለን የአካል ከፍል ከአንገት በታች ካለው አካል ጋር መለያየት ማጥፋት ማረድ መግደል ነው። በአዋሩ የማይከፈለውን አካል ከፍሎ በአጉል መግደል ማጥፋት ነው። ይህ ዓይነቱ ተግባር ሲፈፀም እያዩ ዝም ማለት አይቻልም። ሟቹን ማትረፍ እንኳ ባይቻል ገዳይን ማስያዝ አንድ ሰብአዊ ተግባር ነው። ሁለት ወንጀለኛን መቃወም ነው። አሁን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አንገቷን ታረደች ባንልም እግሯን ግን ተቆርጣለች እንኳ ባንል ቆሰላለች። የቆሰለውን እግር ማዳን ይቻላል። እንኳን ቁስልና የተቆረጡትም መተኪያ ዛቢያ እየገባላቸው እንደ ልብ መራመድ ይችላሉ።

አሁንም ተመሳሳይ አደጋ እንዳይደርስ እንዳይደገም መጠንቀቅ ብቻ ሳይሆን ወንጀለኛውን ለፍርድ ማቅረብ ማስቀጣት ማሳሠር የግድ ነው። ዛሬ ምንም ሳይደርስበት ከቀረ የሚቀጥለው ወንጀል እጅግ የከፋ ይሆናል። ሥጋቴ ፍራቻዬ ከዚያ ላይ ነው። ችግሬንና ሥጋቴን ልተርጉመው። አንዱ ሲኖዶስ ሌላ ቅርንጫፍ ሲኖዶስ በቅሎበታል። በሰው አካል ሲሆን ትርፍ ገላ ይባላል። በዕፀዋት ዘንድ ከሆነ ተቀጽላ ወይንም ተገድራ ሲባል፥ ካንድ አባት ካንድ እናት ውጭ የሚወለድ የሚቃረም ልጅ ደግሞ በአጠራር ዲቃላ ይባላል። ግልጥ ፍርጥ ያለው ቋንቋና አነጋገር ይህ ነው።

በእውኑ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የሚታሰብ ቢሆን የሚታዘን ቢሆን በሲኖዶስ ላይ ሌላ ሲኖዶስ ብሎ መጥራት ይገባልን? ያውም እኩ አባቶች መቅረዛችሁ ከኮረብታ ላይ የምትታይ ናት። ተከናንባችሁ ዕረፍት እስከምታደርጉ ድረስ እኩ እንመለከታችኋለን። ከዚያ በኋላ ደግሞ ተከናንባችሁ ሰታርፉ እግዚአብሔር ያያችኋል። መላጆቻችን በምላሌያቸው «ተከናንቦ ቢተኙ ገልጦ የሚያይ አምላክ አለ» ይላሉ። በእውነት ስለ እውነት ቤተ ክርስቲያናችንን እንዲህ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ ላይ ባለችበት ሰዓት እንዴት ምዕመናኑን ሆድና ጀርባ እንዲሆኑ ይደረጋል? እንዲያው የሚንጎደጎደው የትምህርት ጥቅስ ሁሉ ምን በላው? እንዲያው ተዉ አይሆንም የለበትምን? አንዱን ቢወስድብህ ሌላውን ጨምርለት ማለት ምን ማለት ነው? ሹመቱንስ አይመለከትምን? ለዕጁጠባብ ለካባ ብቻ ነውን? ምነው እስከዚህ ድረስ ስለ ሹመቱ ስለ ሥልጣኑ እንዲህ ሆናችሁ? ይህን ሥልጣን ለማግኘት ምን ያህል

ወጥታችሁ ወርዳችሁበታል? የተገኘው በመንፈስ ቅዱስ አይደል የምትሉን? ታዲያ ቢሄድስ? «እግዚአብሔር ወጎበ ወእግዚአብሔር ነሥዐ» [እግዚአብሔር ሠጠ እግዚአብሔርም ነሣ] ኢዮ.1:21] አይደለምን? ለምንስ ከዚህ ሳይ ከሚሠጠውና ከሚነሳው ውስጥ ሥልጣኑን አልጨምር አለ? እኛ እኩ «ጎድግዎ ወመንገወ ለዝ ዓለም» ይህን ዓለም ንቃችሁ ተውት ጥላችሁትም ሂዱ] በሚለው መርጎ ሥር ያላችሁና የሕይወት ጉዟችሁን ያደረጋችሁ መሰሎን ነበር። አሁንስ ተጠራጠርን። ምነው እንደ ባሮክ «ኢታርየኒ ሙስናሃ ለኢየሩሳሌም» በኢየሩሳሌም ፋንታ የኢትዮጵያን ጥፋት አታሳየኝ አላላችሁ። በእውኑ «ሰብእሰ ከመ ሣዕር መዋዕሊሁ ወከመ ጽጌ ገዳም ከማሁ ይፈሪ።» [ሰውስ ዘመኑ እንደ ሣር ነው። ያ ፈጥኖ ደርቆ እንዲጠፋ ፈጥኖ ይጠፋል። እንደ በረሃ አበባም ይረግፋል። መዝ.102:15] በእነዚህ አመክሮዎች ሁሉ ታጥቃችሁ ተነሥታችሁ እግዚአብሔርን ለማገልገል የቆረጣችሁ አባቶች ምነው «ትጻእ ነፍሰየ ምስለ ኢሎፍላውያን» ነፍሴ ከኢሎፍላውያን ጋር ትውጣ ፋንታ ትጻእ ነፍስን ምስለ ሥልጣንነ ጉዳዩን ሁሉ አደረጋችሁት። እንግዲህ ይህን ዓይነቱንማ እንዴት አድርገን ለእናንተ ለብዙዓን አባቶች መናገር ይቻላል። አሁንም እናንተ ብዙዓን አባቶች ትታችሁት ለመጣችሁት ሹመት/ሥልጣን እንዲህ ስትሆኑ በሥልጣኑ ላይ ያሉትንማ እንዴት አድርጎ መውቀስና ማሳሰብስ እንዴት ይቻላል? የሕይወት ተመክሮ መውደቅና መነሣት ያለና የነበረ ነው። እንደ መላእክት ሳይሆን እንደ ሰዎችም ሁናችሁ ተመልከቱት። ሰዎች ናችሁና! በአሁኑ ሰዓት እናንተን ለማውገዝ ሌላ የኒቅያ ወይንስ የዋሽንግተን ዲሲ ጉባዔ እንጥራ?

አንድ ዘወትር የሚገርመኝ ነገር ቢኖር ሲኖዶስ መሥርታችሁ ኤጲስ ቆጳሳትን ሾማችሁ። ለመሆኑ በየትኛው በጀት ልታስተዳድሯቸው ነው? ወይንስ እውር አሞራ ቀላቢ ጌታ ያውቃል ብላችሁ ነው። ያገራችን ሰው ስለ ዓባይ ወንዝ የሚለው አለ። እሱም «ዓባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል።» እንዴት ቢመለከት ነው? ወይንስ አይዟችሁ ሂዱ ቀጥሉ የሚሉት የድርጅቶች ግፊት በዝቶባችሁ? የኔስ ሥጋት «በቅሎ ግዙ ግዙ አንድ አሞሌ ላያግዙ» እንዳይሆን ነው። እንዲያው ነገሩን ስመለከተው መንፈሳዊ ጉዳይ እኩ በትዕግሥት በለኛሳስ ነው። ያውም ከስድሳ ዓመት በላይ ያለ ሰው እኩ «ልጡ የተራሰ መቃብሩ የተማሰ» ነው። እኛን አይመለከተንም ካልሆነ በሰተቀር በአለቀ ሰዓት እንዲህ ቤተ ክርስቲያኗን አውሬዎች በሚሮሯጡበት ቦታ ያውም ሌሊት የደከመችዋን ላሕም ጥሎ መሄድ ማለት ምን ማለት ነው? ትበላ ትጥፋ ግድ የለንም ማለትኩ ነው።

ኡ! ኡ! ኡ! ብለን የአቡነ ጴጥሮስ ያሰሀ! አያልን ያችን የጴጥሮስን ሰዓት አውንኑ አንጥራ።

ብውዓን አባቶች ሆይ! እናንተን ለማጥላላት ብቻ ሳይሆን የእናንተን ቀረም ለመልቀም ሳልመከተል መፈለጋችንን ለመንገር ነው። እኛስ እኛማ ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ስለ ሃይማኖታችን እንደ ሳማ ይፈጀናል። እንደ እሳት ያቃጥሰናል። አባቶቻችን እኮ ናችሁ። የማይመስል የማይረባና የማይጠቅም ሥራ ሲፈፀም ስናይ ዝም ማለት ለኛም ለምዕመናን ተግባር አይሆንልንም። ምንም እንኳ ከአባት ምክር መቀበል እንጂ መምከር ያለመሆኑንም ብናውቅ ልጅም ለአባቱ ካራውን እንጨቱንና እሳቱን ይዘናል በጉ የት አለ? ሲል ይስሐቅስ ጠይቆ የለ? [ኦሪ. ዘፍ. 22:7] መሥዋዕቱ ከኛውና እኛው ስለሆነ መጠየቁ ይፈቀዳል። ተገዢም ነው። ይሁንና ዓይቶ ዝም ሰምቶ ዝም አንልም። ምንም እንኳ አበው ዝም ባለ አፍ ዝንብ አይገባበትም ቢሉንም ቅሉ! ጅቡ የእኔን አግር ነው የሚቆረጥመው ዝም በሉ ያሰውን ሰው ለመሆን ፈጽሞ አንሻም። እንዲህስ አናደርግም። ያው በአቅማችን የተሠጡንን መክሊቶች በተግባር ማዋል አሰብን። ምክንያቱም ውጤቱን እናውቀዋለን። በምዕመናንና በቤተ ክርስቲያን በአባቶችም ዘንድ ባንሸሰምበትና ባንወደስበትም ግዴታችንን ተወጣንበት ማሰቡ ሃይማኖታዊ ነው።

ወደ ትልቁ ፍርሃቴና ሥጋቴ ልውሰዳችሁ። በመጀመሪያ የአበውን ምሳሌ መጥቀስ እጅግ ደስ ይለኛል። አቡም የአመክሮ ውሳኔ ነውና ነው። እንዲህ ይሳል። «ዶሮ ሟራ ሟራ ማረጃዋን ታወጣለች።» እንግዲህ ይህ ምሳሌ ወደተገሠሠለት በአጠራሩ «ሕጋዊው ሲኖዶስ» በአሜሪካ ኤጲስ ቆጳሳትን ሾሞ ሾሞ እንዳሰፈው እንደ እነሱ አበባል ከሥልጣናችን ተወገድን መፈንቅለ ክህነት ተፈፀመብንን አውንስ ቢደገም? አይሆንምምን ትቶ ይሆናልንም ማሰቡ አይከፋም። ከአሜሪካስ የተሾሙት ለመፈንቅለ ሥልጣኑ ቢነሱማ! መቼም አያድርገው አይባልም። እንዲያው ይህን ስንል የድርጅት ሥራ ማከናወናችን አይደለም። ሆኖም አንድ ምሳሌ ልጥቀስ። አቶ ጳውሎስ ኞኞ በአንድ ጥያቄ አለኝ ዓምዳቸው አንዱ እንዲህ ሲል ጠየቃቸው። «በአስፖንጅ ፍራሽ መተኛት የደም ግፊት ያመጣል ይባላል። እውነት ነወይ? መልስ አቶ ጳውሎስ ኞኞ ይህ የጥጥ ፍራሽ ሠራተኞች ወሬ ነው።» የኛም አቀራረብ ያን እንዳይመስል ለማለት ነው። ምክንያቱም እኛ የጥጥ ፍራሽ ሠራተኞች ደጋፊዎች አይደለንምና ነው። ነገር ግን እኛስ የዚች የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች ነን።

ምንም እንኳ የእናት ሆድ ዝንጉርጉርነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው።

ሌላም ምሳሌ አለኝ። ዲማ ውስጥ የምትኖር አንዲት አብድ ወይንም የአእምሮ በሽተኛ ሴት ነበረች። ይች ሴት አንድ ሳይ ተጠጋግተው/ችብዝ ካሉ መንደሮች ትሄድና ይህ መንደር ነገ ይቃጠላል እያለች እየዞረች ስትናገር ታመሻለች። በበነጋታው ምሽት ሳይ ካንዱ ቤት ሳይ እሳት ታያያዝበታለች። ታዲያ አውንም ቤቶቹ በእሳት በሚጋዩበት ወቅት በየሠፈሩ እየዞረች ስነግር ነው አለች እየተባለ እስካውን በስሟ ተረቱ ይነገርሳታል። ስለዚህ አውንም ስነግር ነው ይያዝልኝ። ለአጣጣማት ጥሩ አባባል ናት ። ታዲያ ስነግር ነውን ብንመነዝራት ያ ተጭሮ ተጭሮ ተፈልሶ የወጣው ካራ መልሶ የፈላሽ አራጅ ቢሆንሳ! እንዲያው አያድርገው አደራውን ብለን አንማፀን ወይንስ ስነግር ነውን እንድገማት። ከዚህ ሳይ ነው የምሳሌ ስንቅነቱ በችገረ ጊዜ መበሳቱ።

መቼም አሜሪካ የማይደረግ ነገር የለም። ይሁንና አሜሪካን ውስጥ ያሉት አባቶች አዲስ አማኝ ወደ ቤተክርስቲያኗ ሲያስረክቡ ወይንም ሲነትቱ አሳየንም። አይታይም። ያው መክረኞውን ኢትዮጵያዊ ነው ዘወትር የሚደዘደዘው። የአሜሪካ ሰዎች ደግሞ ኢትዮጵያ ሄደው ፈረንጁ ሳይቀር ኢትዮጵያዊውን ያውም አርቶዶክሱን ራሱን ሳጭተው ከየጸሎት ቤታቸው ሲያሥሩት ይታያሉ። ምነው እኛስ የሚል መንፈሳዊ ቅናት የለም። ምነው ቅናቱ በቅናት ሳይ ሲደራረብ ወደዚህ አሳተኮረም? ለመሆኑ ባንድ ወር አሥራ ሦስት ኤጲስ ቆጳሳት በሕማማተ መስቀሉ ምሳሌ ሲሾሙ ምን ሠርተው? ምን ፈጽመው? ምንስ ሊሠሩ? ብቻ በዚች ቤተ ክርስቲያን ተጠግተን አውድ አውድ እንኳ ሄደን እንዳንጸልይ በሩ ተዘጋብን። አበው እንደሚሉት «ሳል ይዞ ስርቆት ቂም ይዞ ጸሎት አይሆንም» ነው። እርስ በርሳችሁ ይቅር ከማትባባሉ ጋር እንዴት እንጋፋ?

ብውዓን አባቶች ካህናትና ምዕመናን ሆይ! «በየኔታ ጉረሮ ጠጅ ይንቆርቆር በኔ ጉረሮ አጥንት ይሰንቀር።» አውንም እንዲህ እያልንኮ እንዘምራለን። ነገር ግን ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ ውጭ ነው። እንዲህ እያልን ራሳችንን ዝቅ አድርገን ለእናንተ ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ክብርና ልዕልና አየሠራን ምነው ምነው እኮ! እንዲህ አደረጋችሁን? ለዚህ የሆነ ማስረጃ አለን። አቡም እንዲህ የሚል ቃል ነው። «ዘይሴሠይ እክልየ አንሥአ ሰኮናሁ ላዕሌየ።» [እንጀራዬን የበላ በእኔ ላይ ሊረግጠኝ ተረከዙን [እግሩን] አነሣ። መዝ. 40:9]

ተመሳሳይ ምሳሌም ልጨምር አመክሯችን ጥልቅ ነውና! «ባጎረስሁኝ ዕጁን ተነከስሁኝ።» እንዲሁም ልድገም። «እጸያድቅ ብዙ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች።» ይህ ሁሉ የምዕመናን እሮሮ የአቤቱታ መዝሙር ነው። ፍርድ ከማን እንጠብቅ? በማን ነው የምትዳኙት? ይህ ሃይማኖቱን ቤተ ክርስቲያኑን የደገፍሁ መስሎት ከልጆቹ አፍ ሞቂቆ ካለበት ወጪ ሁሉ ቀናንሲ በሚሠጣት በሚያቀርባት ሙዳየ ምጽዋት መልሶ የቤተ ክርስቲያኑን አንድነት የሚደረምስ ቅጽሯን ከሚያፈርስ ጠላት ጋር መርመስመስ ከዚያም አሳልፎ ለመስጠት ተባባሪ ሲሆንበት እጅግ ያሳዝናል። ስቤተ ክርስቲያኗ ካልሆናችሁ ሰላምና ፍቅር በመካከላችሁ ካላኖራችሁ ከናንተ ምኑ ላይ ነው አባትነታችሁ? የእንጀራ አባቶች እንበላችሁ? ለነገሩ የእንጀራ እናት እንጂ ክፋቷ የሚነገረው የእንጀራ አባት እንኳን አይደለም። በዚች በቀረች ሰዓታችን ዕጃችንን ይዛችሁ ወደ ንስሐው አዳራሽ ግቡ። እኛን ብቻ አስገብታችሁ አትዝጉብን። እሜሪካ ነው ያላችሁት። እንደተፈለገው የሚሆንበት ሁሉም አኩል የሆነበት አይደል የሚባለው? የክህነት መንግሥት አቋቁሞ የሚሠራበት ነፃ አገር ነው። ይህች ናት በእውነት አሜሪካ! እንዲያውም የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት እንቀጽ ሠላሳ ዘጠኝ የሠራው በእውነቱ ለእናንተ ነው ብንል ጽርፍት ይመሰል ይሆን? ባይሆን ምፀት እንጂ!

ሁላችንም እንደምንገነዘበውና እንደምናውቀው አንድ ማኅበራዊ ሕዝባዊ መንግሥታዊና ግላዊ ድርጅት ሥራ ሲጀምር በነጋሪት ጋዜጣ ሥራውና ዓላማው ይገለጣል። የሚሠራቸውና የሚያከናውናቸውም የአጭርና የረጅም ዕቅዶችን ያወጣል። ይህን የመዋቅር አሠራር ተሽከመን አምጥተን ከናንተ ዘንድ እናቅርበውና ለመሆኑ አሜሪካ ውስጥ «ሕጋዊ ሲኖዶስ፡ ሕጋዊ ፓትርያርክ» ብላችሁ ሥራ ስትጀምሩ ወዴት ለመጓዝ ነው? ዕቅዳችሁስ ምንድን ነው? አሁን በዋናነትና በግልጥ የሚታየው እናት ቤተ ክርስቲያንን ይህ የአሜሪካው «ሲኖዶስ» ሲጋፋ ነው። የባሰውኑ ብቸኛዋንና ጥንታዊቷን እናት ቤተ ክርስቲያን ህልውና ፈተና ላይ መጣል ነው። ኤጲስ ቆጶሳትን መሾም ከሆነ እነሆ! ከ1985 ዓ. ም. ጀምሮ እስካሁን በመሾም ላይ ናቸው። መሾሙ ደከመኝ ያገዙኝ ሳይባል ያለ ጥናትና ያለ ዕቅድ አንዲትን ቤተ ክርስቲያን አንድን ሕዝበ ክርስቲያን ግራ ማጋባት አይደለምን? መህል አናቱንስ በትልቅ ድንጋይ መግመስስ አይሆንምን? እንዴት ተደርጎ አቤት ይባል። ሁሉን የምታውቁ ከምድሩ ሕይወት አልፋችሁ ከሞት በኋላ ላለው ሕይወት ዋስትና የምትሠጡ ብፁዓን አባቶች እንዴት ታዛቢ በሌሰበት ሰዓትና ዘመን የቤተ ክርስቲያኗን በር ዘው አድርጋችሁ ከፍታችሁ ለዘራፊ ታስረክባላችሁ? እንዴት ማየት ደከማችሁ? ያለ ሲኖዶስ

የመንግሥተ ሰማያት በር አትከፈትምን? ቁልፉ እሱ ብቻ ሆኖ ተገኝቶ ይሆን? ብፁዓን አባቶቻችን ከጸሎታችሁ ብዛት ከዓለሙም መሳሳት ሁሉም ራሱን ወዳድነት ባወናዝረበት አይታ ውስጥ በመሆናችሁ ይሆንን? ወይስ «ለእመ ሐርከ ብሔረ ባእድ ኩን ከማሆሙ» ወደ ባዕድ አገር በሄድህ ጊዜ እነሱን ምሰል የሚሰው ብሂል እንደ መመሪያ ተወስዶ ይሆንን? እረ! አባቶቻችን ምሥጢራችን ቀኖናችን አይለወጥብን። ምንም እንኳ ስቤተ ክርስቲያኑና ለእግዚአብሔር እናንተ አትቀርቡትም አታሰኙን።

መቹም ወደ መጨረሻው ጊዜ የማይመጣና የማይታይ ጉድ የለም። በአሜሪካ የተቋቋመው «ሲኖዶስ» ከማን ነፃ ሊያወጣ ነው? ሹመት መዝራት የጀመረው? እስካሁን እንኳን በአባቶች ላይ በራሳቸው ላይ የሚወርደው የጽርፈትና የውግዘት ማዕበል እንኳን እነሱን ያሉበትንም ቦታ ሥጋት ላይ ጥሎታል። መንፈሳዊውን ሥራ መንፈሳዊውን ሕይወት እንዲህ የጦርነት ሜዳ ማድረግ ተገቢ ነውን? ገና ዛሬ ገና አሁን የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተጎዳች። ራሷን ደፋች። እጅግ ክል ስበሰች። ይሁንና በጸሎታቸው እሳት አውርደው ተቃወሚዎቻቸውን የሚያስበሉ ጠንካራና ብርቱ አባቶች ጤዛ ልሰው ድንጋይ ተንተርሰው ቅጠል ጎርሰው የሚጠብቋት የአምነት ጀግኖች ስላሏት እንኳን በራሷ ስም ተሹመውና አባ አባ ተብለው ከነበሩት ይቅርና መርዝ ከሚበትን ጠላት እንኳ ተቋቁመው ከዚህ ደርሰናል። አባቶች በጸሎታቸው ጀግኖቻችን በጉልበታቸው ጠብቀውናል አስጠብቀውናል ስለሆነም ከዚህ ደርሰናል።

ዓይናቸውን ገስጥ ቢያደርጉት እኮ ዙሪያቸውን ያሉትን የሚራወጡትን ሌት ከቀን ከላይ ታች የሚሉትን መቃብራችንን የሚቆፍሩትን ቢያዩና ቢያውቁ እንዲህ ጣዕምና ስዛ የተሰየውን «ቆብ ቀዶ ቆብ የመስፋትን» ተግባር ርግፍ አድርገው ትተው ወደማጠናከሩና ወደ ሰላሙ ሃይማኖታዊ ወደ ሆነው ተግባር በገቡ በነበር። «እስመ እምቃልከ ትጸድቅ ወእምቃልከ ትትኴነን» [በተናገርኸው ይፈረድልሃል ወይንም ይፈረድብሃል። ማቴ. 12:36] መሆኑን ልቦናቸው እያወቀውና እየተገነዘበው በቃላቸው አልፈልግም ብለው በአደባባይ ያስረከቡትን ሥልጣን ቃላቸውን አጥፈው አላልሁም አልተናገርሁም ሲሉን በዚህ ቃል ብቻ ነበር ሕዝበ ክርስቲያኑን የመጨረሻ በደል ያደረሱበት። ከባዕታቸው ከገዳማቸው ወጥተው ሰሰው ባዳ ለአገሩ እንግዳ በሆኑበት አገር ያስመዘከር ያስመቀበል ኢትዮጵያዊው ያውም አርቶዶክሳዊ ክርስቲያናዊው ባሕል ተብትቦ ይዞት ቤት ሠጥቶ ከሚበላው አካፍሎ ንወሩ አባቶቻችን ብሎ መቀበሉ እንደ በደል ሆኖ ዛሬ ቤተ እምነቱን

ታሪካዊቷንና ብርቅ ድንቋን የቤተ ክርስቲያኗን በርና መስኮት ሰበሩባት። ዛሬ ምዕመናኑ ለሁለት አልተከፈሉምን? ያውም በሚያስቅና በሚያሰቅቅ መልኩ እንጂ! የኛ ሰው ናቸው መደገፍ አለብህ በሚለው መልኩ እንጂ! ይህ አባባል ሁለት ፊት አለው። አንዱ የፖለቲካ የድርጅታችን ለዎች፣ ሁለተኛው የኛ አካባቢ የሚል ነው። ይህ አባባል ከአቡኑ ደጅ ይከትማልን? እንዴት ተደርጎ? ይህ አባባልና አስተሳሰብ ደግሞ አብሮ – አደግ እንደሆነ ብዙዎች ይስማሙበታል። በአደባባይም ይናገሩታል። ሲጀመር ጀምሮ «ሲወለድ ያጠለቀው ሲሞት አወለቀው።» ነው የሚሉ ብዙ ናቸው። ሁሉም አይደሉም። ግን ጥቂቶቹ አዎ ናቸው።

እኔ በግል የማውቃቸው አባት ወደ ምንኩስና ዓለም ከገቡበት ቀን ጀምሮ ከሥጋ ወላጆቻቸውና ከእኅት ከወንድሞቻቸው በአጠቃላይ ዘመዶቻቸው ተለያይተው እንደቀሩ ምስክር ነኝ። እንኳን የመንደሬ ሰው ነው ብለው ሊናገሩ ይቅርና የመነኩሰ አገሩ በዓቱ የዋለበቱና ያደረበቱ የሚሉ ናቸው። አጋጣሚ ሆነና ስኔና ለኛ እንደሚሉት ክሌላው ጋር ገጠማቸው ስደቱ አገናኛቸው። ሌላው አባት ግን አቡነ ዘበሰማያት ከመድገም ይልቅ የት ተወለደህን? ከየት መጣህንን? አሥራ ሁለት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ዓርባ ዘጠኝ ጊዜ ሲሉና ሲታክቱ የሚያድሩ ከመሃላቸው እንዳሉ ሁሉም ይመስክርላቸዋል። እንደ መልካም ተግባር ተቆጥሮ የሚያሸልም ቢሆን ምንም ዓይነት ተወዳዳሪ የላቸውም። የሚያሳዝነው ግን እንደኔ አመለካከት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ አሜሪካ ገብቼ ሥልጣኔን አድሼ ይህችን ጥንታዊት ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ከፍዬ ኤጲስ ቆጳሳትን ሾሜ ትርምሱን አወጣዋለሁ ብለው የሚመኙና የሚያስቡ አባት አልነበሩም። ነገር ግን ነበ ወሰደዎ በመሆናቸው ከመጀመሪያዋ ቀን እስከ መጨረሻዋ ቀን ድረስ እንኩ ያድርጉት ተብሎ በተሠጣቸው በትረ ክህነት ፈቃደ ሰብእ ፈፃሚ ሆነው የነበሩ ያሉና የሚኖሩ በመሆናቸው እንጂ ቢያንስ ቢያንስ ይህን እንመስክርላቸዋለን።

አሁን ጉዳዩን መለስ ብለው ሲያዩትና ሲመለከቱት የሚያዝኑበት ይመስለኛል። አዎ የሚታዘንበት ነው። ኃሳባቸው ትክክለኛ ነው እውነት ነው ብለው የሚቀርቧቸው ለዎች የሚያሳይዋቸው መንገድ የማይዘልቅ ዳር የማያስወጣ ነው። በዚህ ዓይነቱ ጎዳና ጉዞ መጀመሩ ደግሞ አንደኛ የአካባቢው እንግዳ መሆንን ያመለክታል። ሁለተኛ ጊዜንና ያለ የሌለውን ኃይል ካልሆነ መንገድ ላይ በከንቱ መጨረስ ነው። አሁን ሲያደርጉ የሚታየው ካንዳንድ ከተሞች ከአውሮፕላን ወርደው ወደ ሠፈር ሲሄዱ ምዕመናን የሚከራዩላቸው ሊመዚን በመዝሙርና በሞተር ሳይክል

ሲያጅቧቸው በዚያ ሁኔታ ኢትዮጵያ የሚሄዱ ይመስላል። ነገር ግን ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ የሚያስሄድ መኪና መንገድ እኮ የለም። ያለው ብቸኛ መጓጓዣ አውሮፕላን ነው። በአውሮፕላን ግን ኢትዮጵያ ሄደው መኖር ይችላሉ። ተቀባይም ወንድሞቻቸው አሉ። ጥሪውም ውትወታውም እሱው ነው። እንዲህ የሁሉም ልብ በኃዘን ከሚናወጥና ከሚታወክ ቢሄዱ ለእነሱም ፍቅር ለቤተ ክርስቲያናችንም ክብር ነው።

ዛሬ አሜሪካ ያለው ኑሮ ጣዕሙን እያጣ እየገረጣና እንደ ኗሪዎቹ እየነጣ ነው። ሲሆን ወደ አገራችሁ ተመለሱ። የግብርና ሙያ ያላቸውን ሂዱና መሬት ቆፍሩ እረሱ ምሁራኑን የአገራችሁን ማዕድን አስሱ ሁላችሁም በፍቅር ተመላለሱ። ካህናቱም አገራችሁን አወድሱ ብላችሁ ብትመክሩ የሁሉንም ጆሮ በመስቀላችሁ ትዳስሱ። በስደት ከሠላሳ ዓመት በላይ መቆየት ያገር ጉዳት ለየራሱም ታላቅ ናፍቆት ነው። ከዚህ መሆን ትርፉ እጅግ መዋተት ነው። መማር መመራመር መልካም ነገር ለመፍጠር ነው። ስለዚህ እናንተም ግቡ ሌላውንም አስገቡ። ኢትዮጵያን የፍቅር የሰላም አውድማ ትሁን። ይህን ማድረጉ የአባትነት ግዴታችሁ ይሆናል። ያለበለዚያ ግን ከጠላት ጥፋት የምትጠብቋትን ቤተ ክርስቲያናችሁን ጥላችሁ ወጥታችሁ ምዕመናን የራሳቸውን ቤት በውጭ ዘግተው እንዲያቃጥሉ እሳት ማቀበል ነው።

ይሁንና ይሁን እንጂ! ዞሮ ዞሮ ተጎጅዎች በቅድሚያ እናንተው ከዚያም የቤተ ክርስቲያናችን ታሪክ ማንነቷና በጠላቶቿ ዘንድ መሳለቂያ መሆኗ ነው። ከዚህ ዓይነቱ ፃማ ወድካም እንድንወጣ እርዱን። ይህን የመሰለውን በጎ ነገር ለመሥራት ምከሩን። እርዓያም ሁኑን። «ለዘጎለፈ ሥርየት ወለዘይመጽእ ዕቅበት» [ላለፈው ይቅርታ ክሚመጣው ጥበቃ] የሚሆነው ከዚህ ላይ ነው። አሁን ወደ ጣራው የምትወጡበት መሰላል በቅርቡ ይሠበራል። ከዚያ በኋላ ከወረዱ መውጣት ከወጡ መውረድ መመላለስ ያበቃል። ያም ፍፃሜ ዘመን ይሆናል። ምላሌው የዓይነ ሥውሩ መሸፈት ይሆናል። አንድ ዓይነ ሥውር የሕዝቡን ልብ ለመሰቀል ሽፈት ተብሎ እንዲነገርለት ክጓሮው ከሚገኝ ነመንዘር ውስጥ ይደበቃል። ሁለት ቀን ያለምንም ኮሽታ ይውላል ያድራል። በሦስተኛው ቀን ባጠገቡ የሚያልፍ የሰው ዳና ይሰማና አንተ ስለኔ ምን ይወራል? ሕዝቡስ ምን ይላል? ሲል ይጠይቃል። ተጠያቂም ያው ጥጋበኛ እውር ጉድጓድ ውስጥ ገብቶ ወድቆ ይሆናል ይባላል ይለዋል። እውነቱ እንደዚያ ነውና ነው። እሱ ግን የጠበቀው ሽፍቷል አገር ተጠንቋል ታውኳል እንዲባልለት ነበር። ይህንን ምሳሌ አባቶች

ሲናገሩ እንዲሁ አልነበረም። «የሠዊ ሆድ ሳያስብ የበይ ሆድ ያስባልም» ብለውታል።

ከዚህ ላይ ዓቢይ ትምህርት ማግኘት ይቻላል። ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ሰብስቦ በቂሣርያ ሊወያይ ሰዎች ማን ይሉኛል? የዚህን መልስ ካዳመጠ በኋላ እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ? ሲል ጠይቋቸዋል። ቅዱስ ጴጥሮስ በሠጠው መልስ ተወድሰዋታል። ለዚሁም ሽልማት ይሆነው ዘንድ የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ ቁልፍ አግኝቶበታል። [ማቴ. 16:13-20] አናንተም ሕዝበ ክርስቲያኑ ምን ይሰናል? ብላችሁ ብትጠይቁ መልሱን ብትሰሙ ከዋላችሁበት አታድሩም። ካደራችሁበትም አትውሉም። ስለ አባቶች ያለን ውይይት ከዚህ ይቆየንና ወደ ቤተ ክርስቲያኒቱ የሥልጣነ ክህነቱ ማዕርግ አገልግሎትና አስተዳድር እንሸጋገር።

ምዕራፍ አምስት

የቤተ ክርስቲያን ማዕርገ ክህነትና አገልግሎት

፩ ማዕርገ ክህነት

በዚህ ርእስ ሥር ለማቅረብ የፈለግሁት የማዕርገ ክህነቱ ተዋረድ ምን እንደሚመስል ለማሳየት ነው። ይህም ማዕርገ ክህነት አሉ ከሚባሉት ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ምሥጢረ ክህነት ተብሎ የሚታወቀው ነው። ብዙ ምዕመናን ቅደም ተከተሉና ተዋረዱን በብዛት አያውቁትም። ይህን ስማስት የቻልሁትም ብዙ ጊዜ የተደጋገሙ ጥያቄዎች ሲቀርቡ ስላየሁና ስለገጠመኝም ነው። የክህነት ማዕርጋት የሚጀምሩት ከአናጉንስጢስነት ማዕርግ እስከ ፓትርያርክ ድረስ ነው።

አናጉንስጢስ

የአናጉንስጢስነት ክህነት አገልግሎቱ የቤተ መቅደስ ምንጣፍ ማዘጋጀት መሥዋዕት መሥራት የማእጠንት ፍሕም ማዘጋጀት የቤተ ክርስቲያን በሮችን መክፈትና መዝጋትን ስለዚህም ጎፃዌ ኖኅት ተብሎም ይጠራል። በተመግሪም የሚነበቡ መጻሕፍትን ያቀራርባል ይመልሳል። ይህን የመሳሰሉ አገልግሎቶችንም ይሠጣል። ነገር ግን ከመቅደስ ገብቶ መቀደስ ግን አይችልም። ከቅኔ ማኅሌት እስከ ቤተ መቅደስ ድረስ የመለላክ አገልግሎቶችን ለማከናወን የሚያስችል ሥልጣን ነው። ይህም ሥልጣነ ክህነት የሚሠጠው በኤጲስ ቆጶስ ብቻ ነው። ይህም ሥልጣነ ክህነት የሚሠጥባቸው ቦታዎች በተለይም በታላላቅ አድባራት ነው። ከሁሉ በበለጠ የአናጉንስጢስነት አገልግሎት በታላላቅ አድባራት ስለሚዘወተሩ ነው።

ዲቁና

ዲቁና ሙሉ የክህነት ሥልጣን መጀመሪያ ነው። ይህም ሥልጣነ ክህነት መሥዋዕት ከማዘጋጀት ጀምሮ እስከ ቤተ መቅደሱ አገልግሎት ብቁ የሚያደርግ ነው። ይህም አገልግሎት ለዲያቆናት ተቀዳሚ ተግባራት ናቸው። የዲቁና አገልግሎት የተጀመረው በዘመነ ሐዋርያት ነው። የመጀመሪያዎቹ ዲያቆናት በምርጫ የቀረቡት በአጠራርም ሰባቱ ዲያቆናት ናቸው። የእነዚሁም ሊቀ ዲያቆናት

ቅዱስ እስጢፋኖስ ነው። ዝርዝር ታሪኩን ለመከታተል የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ሦስት ከቁጥር ሦስት እስከ ስድስት ድረስ ያለውን ያነቧል።

የዲቁና ክህነት ቀደም ባሉት ዘመናት በተለይም ክህነት መሠጠት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ጊዜ ድረስ ክህነቱን የሚቀበሉት ዲያቆናት በሕግ የተወሠኑ ማለት ሚስቶች ያሏቸውና ተገዢውን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መስጫ ትምህርት በበቂ ተምረው ያጠናቀቁ ምዑራን ነበሩ። ከዲቁናም በቀጥታ ወደ ቅስና ይሸጋገሩ ነበር። ነገር ግን ከግራኝ አህመድ ወረራ በኋላ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጠሉ። አገልግሎታቸውም ተቋረጠ። ስደትም ሆነ። ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወርና መሸሸግም ሆነ። በዚህ ሁናቴ አሥራ አምስት ዓመታት ብዙ መጉላላት በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ሆነ። ብዙ ካህናትም በጦርነቱ አለቁ። ከግራኝ አህመድ ወረራ በኋላ የተቃጠሉት አብያተ ክርስቲያናት መቃኞ እየሠሩ መቀደስ ሲጀምሩ አገልግሎት የሚሠጡት በሕግ የተወሠኑ ዲያቆናት ቁጥር ቀነሰ። ስለዚህም አገልግሎቱ መታጎል ጀመረ። ለዚሁም መፍትሔ ሆኖ የቀረበው ገና በትምህርት ላይ ያሉ ወጣት ልጆችን የዲቁና ክህነት እየሰጡ ማስገልገል ተጀመረ። በዚህም ምክንያት እንደ ልማድ ተቆጥሮ ገና ሕግ ስመሥራት ያልደረሱትን ልጆች ክህነት መስጠት ቀጥሎ እስካሁን ድረስ አሉ። ይሁንና ለአቅመ አዳም ሲደርሱና ትምህርታቸውን ሲያጠናቅቁ ሕግ ሠርተው በሥጋ ወደሙ ተወስነው ከዲቁና ወደ ቅስና እንዲሸጋገሩ ሆኗል። ስለዚህ ከዲቁና ወደ ቅስና በሕግ ተወስኖ ማለት ሚስት አግብቶ ወይንም በምንኩስና ተወስኖ ወደ ቅስና መሸጋገር ናቸው። ስለዚህ የቅስና ሥልጣን ክህነት የሚገኘው በሁለቱ መንገዶች በኩል ብቻ ነው።

ቅስና

ቅስና ከፍተኛ የሥልጣነ ክህነት ማዕርግ ነው። ሥልጣኑም የሚገኘው ወይንም የሚሸሙት በኤጲስ ቆጶስ ብቻ ነው። ይህ ሥልጣነ ክህነት ሥጋ ወደሙን ወደ ኢየሱስ ሥጋ ደሙን ወደ ኢየሱስ ደም ይለውጣል። ያጠምቃል መንፈስ ቅዱስን ያሰጣል ይቀድሳል ያቆርባል ይባርካል ይናዝዛል ኃጢዓት ያስተሠርያል። ይገዝታል ይፈታል ያነጻል ይቀድሳል። ይጸልያል ኃጢዓት ያስተሠርያል። አሁንም የዚህ ሥልጣነ ክህነት ምንጩ ወይንም መገኛው ከኤጲስ ቆጶሱ ነው። ከቅስና ያለው ሥልጣነ ክህነት የውስጥ አገልግሎት መስጫ እንጂ የሹመት ስም አይደለም። ቅስና ግን

ሹመትም መጠሪያም ነው። ስለዚህም ቀሲስ ወይንም ቄስ እገሌ እየተባለም ይጠራል።

ቁምስና

ይህ ሚሥጥ የሚሠጠው ለመነኮሳት ብቻ ነው። ይህም ማለት ምንኩስና በሁለት መንገዶች የሚያዝ ማዕርግ ነው። አንደኛው በድንግልና የመነኮሰና ቅስና ያገኘ ሆኖ ለሁለተኛ ማዕርግ ቆሞስ ይሆናል። ሁለተኛው ደግሞ ሕጋዊው ካህን የሕግ ሚስቱ በሞት ስትለይ ወይንም ከካህኑ ጋር በሆነ ምክንያት አብራ ለመኖር ሳትችል ስትቀርና እሷን ትቶ በምንኩስና ለመኖር ሲፈልግ መመንኮስ ይችላል። በዚህን ጊዜ የቆሞስነት ሥልጣን ይሰጠዋል። ስለዚህ ሕጋዊው ካህንና ድንግላዊው መነኮስ ከቅስና በኋላ ሁለቱም ይቀበሉታል። ይሁንና ይህ ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ካህናት ቆሞሳት ተብለው ይታወቃሉ። የሚሠጡትም አገልግሎት ሁለቱም በእኩልነት ቆብ ይባርካሉ ያመነኩሳሉ። አዲስ ቤተ ክርስቲያን ባርከው ታቦት ያስገባሉ። ይሁን እንጂ እንደ ምንኩስና ስም አባ ወይንም እንደ ቅስና ስም ቀሲስ ተብሎ እንደሚጠራ ቆሞስ አባ እገሌ ተብለው እንደ ሹመት ስም አይጠሩበትም። የተግባር ሹመት እንጂ የመጠሪያ ስም አይደለም። ይሁንና በከተማ ያሉ መነኮሳት የመጠሪያ ማዕርጋቸውን ከፍ ለማድረግ ሲሉ ቆሞስ አባ እገሌ ተብለው ሲጠሩ እንሰማለን። ትክክል አይደለም። ሹመት አሳሽ መሆን ነው እንጂ በብዛት ሥል ጣኑ ያላቸው እንኳን የሹመት ስም ሊያደርጉት ቀርቶ ቁምስና አላቸው ተብለው እንኳ እንዲነገር አይሹም።

ስለሆነም ሕጋዊው ካህን መንኩሶ ቁምስና ሲቀበል ለዚያ ካህን ይህ የሥልጣነ ክህነቱ ጣራ መሆኑ ነው። ይህም ማለት የመጨረሻው ማዕርግ ነው። ከዚህ በኋላ የሚቀጥለውን ሹመት የሚያገኙት ደናግላን እንጂ መለስባን አይደሉም። ይህንም የቤተ ክርስቲያኒቱ ቀኖና ደንግጎታል። ከዚህ ላይ ግን የደብር አለቅነትና የገዳም መምህርነት ሁለቱም ይሾማሉ ያገለግላሉ። ደናግላን መነኮሳት ከቁምስና ማዕርግ በኋላ የሚቀጥለው ማዕርግ ኤጲስ ቆጶስነት ነው።

ኤጲስ ቆጶስነት

ከኤጲስ ቆጶስነት ማዕርግ ስመድረስና ይህን ከፍተኛውን ሚሥት ለማግኘት በሙያ ማለት በትምህርት የበለፀገና ያወቀ በሥነ ምግባሩም የተመሠገነ ቀጥሎም በሚሠጠው አገልግሎት የተዋጣለትና ንቁ ለቤተ ክርስቲያኑ አገልጋይ የሆነ በምዕመናን ዘንድም እጅግ

የተሞገሠ አባት መሆኑ ሲረጋገጥና ሲታወቅ ለኤጲስ ቆጶስነት ምርጫ ይታጫል። ስሚመቱም ይወዳደራል። በምርጫ ካሸነፈ የመጨረሻውን የሥልጣነ ክህነት ማዕርግ ያገኛል። ከዚያም ስሙም ይለወጥና የኤጲስ ቆጶስነት ስም ይሠጠዋል በዚያም ይታወቃል። ይጠራልም። በሚሾምበት ሀገረ ስብከትም ስሙ ይጠራል ይጸለይለታል። ይህን ሹመት የሚሠጠው ቅዱስ ፓትርያርኩ ነው። ከዚህ በኋላ ያሉት ሹመቶች የማዕርግ እንጂ የሥልጣነ ክህነት ማዕርግ አይደሉም። በኤጲስ ቆጶሱና በፓትርያርኩ መካከል በሥልጣነ ክህነት አኩል ናቸው። በማዕርግ ግን ይለያያሉ። ከኤጲስ ቆጶስነት ማዕርግ በኋላ ጳጳስ ሲቀ ጳጳስና ፓትርያርክ የማዕርግ ሹመቶች ናቸው። ኤጲስ ቆጶሳት በአንድነት ፓትርያርኩን ይሾማሉ። ፓትርያርኩ ደግሞ ኤጲስ ቆጶሳትን ይሾማል። አንድ ኤጲስ ቆጶስ ሲሾም ከሀገረ ስብከት ጋር ነው። ከተሾመበት ሀገረ ስብከትም እስከ ፍፃሜ ዘመኑ ድረስ ከዚያ ቦታ አይነሣም። በዕድገት በሲቀ ጳጳስነት ወይንም በፓትርያርክነት ከሆነ ግን ለከፍተኛው ማዕርግ ሥራ ይዛወራል እንጂ የተሠጠውን ሀገረ ስብከት ትቶ ወደሌላው አይሄድም በሌላው ሀገረ ስብከትም ሄዶ አይሾምም። ይህ ሥርዓት ግን ቅዱስ ሲኖዶሱ ያሻሻለው ይመስላል። ሲቃነ ጳጳሳቱን ካንዱ ሀገረ ስብከት ወደሌላው ሲያዘዋውራቸው ይታያል።

ፓትርያርክነት

የጳጳሳቱ የሥልጣን ደረጃ እንዲህ ነው። ኤጲስ ቆጶስ የመጀመሪያው ሹመት ነው። ቀጥሎ ጳጳስ ይሆንና ሠፋ ያለ ሀገረ ስብከት ይሰጠዋል። ከዚያም ሊቀ ጳጳስ ሲሆን ደግሞ በሥሩ ኤጲስ ቆጶሳትን ሲመራና ሲያስተዳድር ነው። አሁን ግን ይህ ተሠርዞ ሁሉም ተጠሪነታቸው ለቅዱስ ሲኖዶስና ለቅዱስ ፓትርያርኩ ሆኗል። ከዚህ በኋላ ፓትርያርክ ለመሾም ሲፈለግ ከመካከላቸው ከአምስት ያላነሱ ከአሥር ያልበለጡ ተወዳዳሪዎች ቀርበው ከመካከላቸው አንዱ የድምፅ ብልጫ ያገኘው ብቻ ፓትርያርክ ሆኖ ይሾማል። ፓትርያርኩም የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር ሆኖ ያገለግላል። ሲቃነ ጳጳሳቱን በቅርብ ይቆጣጠራል ሀገረ ስብከታቸውንም እየተዘዋወረ ይጎበኛል። የሥራም መመሪያም ይሠጣል። ሹመቱም የእድሜ ልክ ነው። ነገር ግን በሦስት ምክያቶች ብቻ ይተካል ወይንም ከሥልጣኑ ይለቃል። እኒህም ምክንያቶች ምንም እንኳ ቀደም ሲል የተገለጹ ቢሆንም ቅሉ ለአጽንኦተ ነገር ማለት ግንዛቤውን ለማጠናከር ይረዳ ዘንድ ልድገማቸው። እነሱም አንደኛ በሞት ሲለይ፣ ሁለተኛ በገዛ ፈቃዱ ወዶና ተስማምቶ በገጠመው ችግር ሥልጣኑን ሲለቅና ሦስተኛ በአምነቱ ሕፀፅ ነውር

ተግባር ሲፈጽም ሲገኝ በቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ሥልጣኑን ይነጠቃል ይወገዛል። ካለ ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ግን ምንም አይደረግም አይሆንምም። ስለሆነም የቅዱስ ሲኖዶሱ ውሳኔ ሁልጊዜም የበላይ ሥልጣን ያለው የጋራ ጉባዔ ነው። ከዚህ ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ውጭ የሚፈፀም ተግባር ሁሉ ቀኖና አፍራሽና የተወገዘ ነው። ስለዚህ ቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ከአፎቱ የወጣ ሠይፍ ነው። ጳጳሳቱ በአንድነት የሚመክሩበት ጉባዔያቸውም ነው። አሱም በአጠራሩም ቅዱስ ሲኖዶስ ይባላል። ቀጥሎ እንመለከተዋለን።

ቅዱስ ሲኖዶስ

ቅዱስ ሲኖዶስ ምንድን ነው? ቅዱስ ሲኖዶስ ከፍተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዋና የቀኖና የውሳኔ ጉባዔ ነው። ቅዱስ ሲኖዶሱ በፓትርያርኩ ሊቀመንበርነት ይመራል። ይህ የሊቃነ ጳጳሳት ጉባዔ ታላቅ ሥልጣን አለው። ይሾማል ይሽራል ያወግዛል ይፈታል የቤተ ክርስቲያንን ሕግና ሥርዓት ይተክላል ይነቅላል ማለት ያሻሽላል አዲስ ሕግም ያወጣል። ቀኖና ቤተ ክርስቲያን እየተባለ የሚጠራው የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግ የሚወሠነው በቅዱስ ሲኖዶስ ነው። የሚያሻሽለውም የሚሽረውም ይኸው ቅዱስ ሲኖዶስ ነው። የቅዱስ ሲኖዶስ ቃል ሠይፍ ነው ይቆር ጣልቃሉ ይሠራል። ቅዱስ ሲኖዶስም አንድ ብቻ ነው። በየሀገረ ስብከቱ ወይንም ጳጳሳቱ በሚሄዱበትና በሚቀመጡበት ይዘውት የሚንቀሳቀሱት የአገልግል ስንቅ አይደለም። የሚኖረውም ያለውም ከመንበረ ፓትርያርኩ ርእሰ ከተማ ብቻ ነው።

ቅዱስ ሲኖዶስ የሚሾምና የሚሽርም ነው። ከቅዱስ ሲኖዶስ ውጭ የሚሾምም የሚሽርም የለም። ቅዱስ ሲኖዶስ መክሮና መርጦ በሾመው ኤጲስ ቆጶስ ጳጳስ ወይንም ሊቀ ጳጳስ ላይ ጥፋት ከተገኘበት በቀጥታ የመሻር ሥልጣን አለው። ከቅዱስ ሲኖዶስ ውጭ የሚካሄደው ተግባር ሁሉ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ ነው። አንድ ጳጳስ ሥልጣነ ክህነቱ በቅዱስ ሲኖዶስ ከተያዘና ከተወገዘ ከሥልጣኑ ተለየ ነው። ክህነት አይሠጥም ቀድሶ አይባርክም የሥልጣን ዕጅ እግሩን አጣ ማለት ነው። በግዝት ላይ ያለ ጳጳስ መቀደስና ክህነት መሥጠት አይችልም። ነገር ግን ይህን ሲያደርግ ቢገኝ ማለት በታገደና ባልታደሰ የመንጃ ፈቃድ መንዳት ማለት ነው።

ቅዱስ ሲኖዶስ አንድና ብቸኛ ነው። አይቀዳም አይገለበጥም አይሰረቅም ከቦታ ቦታ አይዘዋወርም። ቅርንጫፍ መ/ቤትም የለውም። ለዚህም በዓመት ሁለት ጊዜ በመላ አባላቱ ያለበት የጋራ ጉባዔ ያደርጋል። በእነዚህ በዓመት በሚያደርጋቸው ሁለት ጉባዔዎች ሕግ ያወጣል ይወስናል የአስተዳድር መሸኻል ያደርጋል። በሲኖዶሱ ጸሓፊ አማካይነት የተለያዩ የመነጋገሪያ አርእስተ ጉዳዮች ይቀርባሉ። በእነዚያ ጉዳዮች ላይ በጋራ መክሮና ተወያይቶ ውሣኔ ያሳልፋል። ያ ውሣኔ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተብሎ ይሠየማል በተግባር ላይም ይውላል። ለምሳሌ ያህል ቅዱስ ሲኖዶሱ ሲወሥንበት የሚገባው ጉዳይ እጅግም አጠያያቂ የሆነው ጉዳይ እስካሁንም ያልተፈታው ጥያቄ ሴቶች እናቶቻችንና እኅቶቻችን ካንዳንድ ገዳማት እንዳይገቡ ግዝት አለ። ይህን ግዝት አንሥቶ ሴቶችን በማንኛውም ጊዜና ሰዓትና ቦታ ሁሉ ገብተው እንዲጸልዩ መፍቀድ ይችላል። ይህን ውሳኔ የቀደሙ አባቶች ሲወስኑ የተለየና ከጊዜው ጋር የሚሄድ ችግር ኖሮ ይሆናል ከእነዚህ ገዳማት ሴቶች እንዳይገቡ ብለው የወሰኑት። በአሁኑ ጊዜ ግን በዓለም ላይ እንዲህ እንደኛው ብቻውን የቀረ ገደብ ጨርሶ የለም። ለምሳሌ ኢየሩሳሌም ጎልጎታ ላይ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር ውስጥ ሴቶችም ወንዶችም ገብተው ይጸልያሉ። ይህን እንደምሳሌ ብንወስድ ይህን ችግር ቅዱስ ሲኖዶስ ተወያይቶ ግዝቱን አንሥቶ ውሳኔ ማድረግ ይችላል። ይህን የመሰለውን ጉዳይ ማንሣት የሚችለው ቅዱስ ሲኖዶሱ ነው። በዚህ አጋጣሚም ለቅዱስ ሲኖዶሱ ማመልከቻዬን አቀርባለሁ። ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረውን የዖታ አድልዎ ጨርሰው አጥፍተውት ይታያሉ። በኛ ዘንድ ግን እንዲያውም እንደ ችግርም ቀርቦም እያውቅ። መነኩሳያቱም ለምን እንከለክላለን? ይፈቀድልን ብለውም አያውቁ። የተማሩትም እኅቶቻችን ይህ ግዝት ይነሣ ብለውም አያውቁም። እንደተከለከሉና እንደተባረሩ ቀርተዋል። ይህ ግዝት ወይንም ገደብ ቢነሣ እጅግ መልካም ይሆናል።

እናቶቻችንና እኅቶቻችን በየገዳማቱ ይኖራሉ አገልግሎትም ይሠጣሉ። የሴት ገዳምና የወንድ ገዳም ያሏቸው ገዳማት በብዛት አሉ። ታዲያ ካንዱ ገዳም ሁለቱንም ሲያስተናግድ ሌሎቹ ደግሞ የሴቶች እግር ገዳማችንን አይረግጠውም ለምን ይባላል? ጉዳዩ ወደ ቅዱስ ሲኖዶሱ የሚያቀርበውና እንዲወያዩበት ቢደረግ ይህን ገደብ ለማንሣት ችግር ያለበት አይመስልም። ጣና ደሴት ውስጥ ከሚገኘው ከብራን ገብርኤል ገዳም ሁላችንም ሴቶችም ወንዶችም ከጀልባ ስንወርድ ሴቶች በሙሉ ከአጥሩ ውጭ ከዚህ ቆዩ ተብለው ሲያዝኑና ይህ ነገር ትክክል ነው? ብለን ከእነሱ ጋር ስንወያይ ቆይተን ተለያይተናቸው እኛ ወንዶቹ ልንገበኝና ልንሳለም ወደ ቤተ

ክርስቲያኑ አመራን። እነሱ ቀሩ። ይህን ጥያቄ ከዚያ ለሚያስገበኙን አባት ጥያቄውን አነሰሁባቸው። እንዲያውም እኛ በዘመኑ ለነበሩት ሲቀ ጳጳስ ለምን ውግዘቱን አታነሡትም ብንላቸው የአበው ድንጋጌ ስለሆነ እንዲያውም መጠናከር ይገበዋል ነው ያሉን ሲሉ አሰረዱን። ገዳማቱ እንኳ ግዝቱ ቢነሣ ተቃውሞ የላቸውም። ሆኖም ውሳኔውን እነሱም እንደሚያስፈልግ ያምኑበታል። ታዲያ ቅዱስ ሲኖዶስ ወደፊት ሴቶች የክህነት አገልግሎት እንድንሠጥ ሹመቱ ይሠጠን ተብለው ሲጠየቁ መልሱ ምን ሊሆን ነው? ቢታሰብበት መልካም ነው። ስለሆነም ይህን የመሳሰሉትን ጉዳዮች ሊያሻሽል የሚችለው ቅዱስ ሲኖዶስ መሆኑን ለማመልከት ነው። ታዲያ እሁን የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔን በምንጠብቅበት ሁናቴ ላይ እያለን ራሱ ቅዱስ ሲኖዶሱ ችግር ላይ ነው ያለው። በማዕበል እንደሚንገላታ መርከብ ከወዲያ ወዲህ ይላል። የራሱ አባላት ሁለትም ሦስትም ሆናችሁ ብትሰበሰቡ ከመካከላችሁ እገኛለሁ የሚለው ቃል ለሲኖዶስ ተሠጥቶ ጳጳሳት በዋሉበት የሚውል ባደሩበት የሚያድር ጎቡዕ መንፈስ ሆኖ ይታያል። ነገር ግን ቅዱስ ሲኖዶስ የሁሉም የሊቃነ ጳጳሳቱ ሁሉ የጋራ ጉባዔ እንጂ እንደ ዳቦ እየተሸረፈ በኪስ ወይንም ባገልግል ተይዞ የሚዞር የመንገድ ስንቅ አይደለም። ይህ በዘመናችን እየተደረገ በማየታችን ያውም በበቁ በነቁ ዓለምን በናቁ አባቶች ዘንድ ይህ ትክክል ያለመሆኑን ጎሊናቸው እየተረዳው በዚህ ዓይነት ውጥንቅጥ ውስጥ መገኘቱ እጅግ የሚሰቀጥጥ ነው። ስለሆነም ቅዱስ ሲኖዶስ ሥልጣንና ተግባር ይህን ይመስላል።

፪ . ካህናት ዘበምድር

ና

ካህን የሚለው ቃል ቦጥሬ ትርጉሙ አገልጋይ ማለት ነው። የክህነት አገልግሎት ለማን? ለእግዚአብሔር ቤትና ለክርስቲያኖች ሃይማኖታዊ አገልግሎት ሠዊነትና አቅራቢነት በአንብሮተ ዕድ [ዕጅን በመጫን] የተሠየመ ልዩ ምርጥ ሰው ማለት ነው። ለዚህም የአገልግሎቱ መስጫ ተቋምም ቤተ ክህነት ናት። ፪ሚዎችም ሊቃነ ጳጳሳት ናቸው። የሥልጣነ ክህነት ባለቤቶች ጳጳሳት ብቻ ናቸው። አንድ ሕዝባዊ አባባል አለ ይህንኑ የሚያረጋግጥ አንዲህ ይላል። «ጳጳሱ ቂስ ናቸው ወይ? ቢለው ተርፍቸው ያበድራሉ» አለው ይባላል። ጥሩ ማስረጃ ነው። ስለዚህ ካህናት በቀጥታ የጳጳሳት ተበዳሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ተ፪ሚዎችም ናቸው። ዲቁና፥ ቅስና፥ ቁምስና የሚገኙት ወይንም የሚሠጡት አሁንም በጳጳሳት ብቻ ነው። ጳጳሳትን ደግሞ የሚሾማቸው ፓትርያርኩ ወይንም ሊቃነ ጳጳሳቱ በአንድነት ሆነው ነው። ይህ የፕትርክና ሥልጣን ደግሞ ለአንድ አባት ብቻ የሚሠጥ ሹመት ነው። መንበሩም አንድ ነው። ባንድ ወቅት ሁለት ፓትርያርኮች ሊኖሩ አይችሉም። መንበሩም ኢትዮጵያ ፓትርያርኩም አንድ የሚኖረውም መንበሩ ካለበት ቦታ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ብቻ ነው። ከዚያ ውጭ የለም። አይኖርም አይሆንምም። ቀኖና ቤተ ክርስቲያን የሚፈቅደውና የሚያዘዘው ይኸው ነው። ከዚህ ውጭ ግን ሕጋዊ አይደለም። ይህን የሚቃወሙ የማይቀበሉ ግን የክህነት ሰዎች አይደሉም። ሥልጣናቸውም አይፈቅድላቸውም። አንድ መንበር ላንድ አባት እንጂ ለሁለት አይሆንም። ይህን ወደ ቀላል ምሳሌ ብንገልጸው አንዲት ሴት ሁለት ባሎች ልታገባ አትችልም። ይህንንም ክርስቲያናዊው ቀኖና ቤተ ክርስቲያን አይፈቅድም። ለዚህም ይመስላል ከውጭ ሲኖዶስ ከፍተናል የሚሉት አባቶች ሕጋዊ የሚል ቃል የጨመሩበት። የቃሉ መደመር ሕጋዊ አያደርገውም። ሁለት ጊዜ ዜሮ መልሱ ዜሮ ነው።

ስለዚህ ካህናት የሥልጣነ ክህነታቸው ምንጭ የሆነችዋን ቤተ ክርስቲያናቸውን ቀኖና መጠበቅ ማስጠበቅ የግድ ይሆንባቸዋል። ቤተ ክርስቲያን በፖለቲካ በቡድን በምቀኝነት በማን አለብኝነት ስትከፋፈል ዝም ማለት አይሆንምም አይገባቸውም። ከራሳቸው ሕይወት ይልቅ ለቤተ ክርስቲያኗ ሕይወት የበለጠ ማሰብና መኖር

መቆጨት ከዚያም አልፎ ተርፎ መሞት ይጠበቅባቸዋል። የቤተክርስቲያኗ ሕይወት ካልኖረና አንድነቷ ካልተጠበቀ የእነሱ ሕይወት ዘለቄታ አይኖረውም። ከአካሉ የተለየ ራስ ብቻውን አይኖርም። እንደ ዮሐንስ ራስ በታምር ካልሆነ በስተቀር። ካህናቱ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ አገልጋዮች የሚሆኑበት የሚያስመሰክሩበት ጊዜና ወቅት አሁን ነው። ታሪክ የምትሠሩበት አሁን ነው። ያለበለዚያ ከቅርብ የምትመልሱትን ጉዳይ ርቆ ከሄደ ከሰው አዝመራ ከገባና ከተያዘ በኋላ ለመመለስ ሳይሆን የአፈላማ ከፍሎና አቤት ብሎ ማግኘት ነው። ከዚያ ይልቅ ዛሬውኑ መሮጥ መሽቀዳደም መጠበቅና መንከባከብ መሆንና መደረግ አለበት። ይህች ጊዜ ካለፈች በኋላ የሚሆነው ሙሽራው ከገባና በሩ ከተዘጋ እንደ ደረሱት አምስቱ ሰነፎች ቆነጃጅት መምሰል ነው።

በእርግጥ እውነተኞች ያልሆኑ በበሩ የማይገቡና ያልገቡ ምንደኞች ካህናት የሉም ማለት አይደለም አሉ። እንዲያውም ጊዜውንና ውሸንብሩን በትንፋሻቸው የሚያሟሙቁት እነሱ ናቸው። ከላይ እንደገለጽነው በካባው በቀሚሱና በመስቀሉ ለባሽነትና ተሸካሚነት እንጂ ጨርሶ ከሙያውም ሆነ ከሥልጣነ ክህነቱ የሌሉበቱ መች ለአሜሪካ ነፍስ እኔ አነስኳት ባዮች አሉ። ሁላችሁም እንደምታውቁት ባለቤቱ የሠነፈበቱ እንስሳ ያገኘው ሁሉ የሚቄነውና የሚገለገልበት አይደለምን? እንኳን ሃይማኖትን ከማንነት ጋር አጣምራ የያዘች ቤተ ክርስቲያን አስኬማ በለበሱ ዓለምን በናቁ ለነፍሳቸው ባደሩ እነ አባ ዓለም ለምኔ ከተሆነ በኋላ እንዴት ተመልሶ እርፍ ይዞ ወደ ኋላ ለማረስ ይሞክራል? የማይሆነውን የማያደረገውን ሲሠሩ ማየት ለተመልካቹም አስገራሚ ነው። ይህን የመሰለው ሲፈፀም አይዟችሁ በርቱ የሚሉ የሉም ማለት አይደለም። ወደ ተሳሳተ ጎዳና የሚመሩ መኖራቸውን እናውቅ የለምን? ለዚህማ መጽሐፈ መነኮሳት በከፍተኛ ደረጃ ምክሩን ይሠጣል። ጦሩን ታገሡ ሲል ምን ማለቱ ይሆን? የሰባት ሻለቃ ጦር ማለቱ እንዳልሆነ እንረደዋለን። ታዲያ ሚመት ሥጋዊ ጦር አይደለም የሚል ማን አለ? አሁን እኮ ሲሠራ የሚታየው ሊሆን የማይገባው ነው። ይህን አትሥሩ ይህን አታድርጉ ብሎ የሚመክር አባት ራሱ አታድርጉ የሚለውን ቃል ራሱ የሚሽር ከሆነ እንኳን ለሥራው ለጤንነቱስ ምን ማረጋገጫ ይኖረዋል? መልእክት ተቀባዩ ምዕመንስ ምን ዓይነት አመለካከትና ትርጉም ይሠጠዋል? አሁንም በካህን ስም ያልሆነውን የሥራ ጦር ታገሡ። በካህናት ስም የሚፈፀመው ደባ ይቁም። አበው እንደሚሉት «ነገር ሲያመልጥና ፀጉር ሲመለጥ አይታወቅም» ሆኖባቸው ነው እንጂ የካህናት ጉዳይ ከፍተኛ የአምባ መነጋገሪያ ጉዳይ ሆኗል።

አንድ ለጊዜው ስማቸውን ከመጥቀስ የቆጠብሁት ሰው ሥልጣነ ክህነት ሳይኖራቸው በድፍረት ካህን ሆነው ለማገልገል ሲጀምሩ ተገልጋይ ምዕመናን ከሚያዩትና ከሚሰሙት በመነሳት የክህነት ማስረጃቸውን እንዲያቀርቡ ሲጠይቋቸው የሠጡት መልስ ማስረጃዬ በግዕዝ ስለሆነ የቶጻፈው ግዕዙም ስለማይገባችሁ ተተርጉሞ እስኪመጣ ጠብቁ ነበር መልሳቸው። እነሱ ደግሞ የቤተ ክርስቲያኑ መጻሕፍት ከቅዳሴ ጀምሮ በግዕዝ አይደል የሚነበበው ግዕዙንም ቢሆን ያቅርቡት ሲሏቸው የማይገባችሁን? ብለው ወደ ቁጣውና ወደ ዘለፋው ሲሻገሩ ማኅበረ ምዕመኑኑ በጽሑፍ አሰናበቷቸው።
ይህ በዋሽንግተን ዲሲ ከተማ የተፈፀመ ድርጊት ነው። ለእንዲህ ላሉ ካህናት እንኳን ለበላይ አባቶች ተጠያቂነት ሊኖራቸው ቀርቶ የቤት ኪራይ ለሚከፍሉት ምዕመናን እንኳ ተጠሪነታቸው በቂ ሆኖ አልተገኘም። ይህም ብቻ አይደለም። መቼም አሜሪካ ለገበያው ግርግር ሰዎች ምቹ ነውና የሌለ አንድ ትልቅ ካቴድራል በራሳቸው ፈጠራ ሠይመው የዚያ ታላቅ ካቴድራል ደግሞ የበላይ ኃላፊ ራሳቸውን አድርገው ለበታች ደብተሮች እንኳ ላልሆኑ ሹመት ይናኛሉ። ርእሰ ደብር ቀኝጌታ እያሉ በጎብረ ቀለም ያጌጠ ክርታስ አሳትመው ሹመቱን ይናኙታል። መቼም ይህ ሲደረግ የሹመት ያዳብርና ለመሰለው አገልግሎት በነፃ እንደማይሆን እንገምታለን። እንዲህ ዓይነት በስም የከበሩ በሥራ የከሠሩ ሰዎች ጥቁር ካባቸውን ደርበው ጥቁር ኩፍያ አጥልቀው ሲመሽ የሚወልቅ እሁድ እሁድና ሰው ባለበት አካባቢ ብቻ የሚጠለቅ በከተማው ሲጎማለሉ ይታያሉ። እኒህን የመሰሉ ብዙ ናቸው።

እንግዲህ የቤተ ክርስቲያኗ አስተዳድር መዘበራረቅ ያመጣው ግኝት ትክክለኛ ያልሆነ ምሥክርነት እየሰጡና እያስተማሩ ለችግሩ መፍትሔ ከመናገርና ከማቅረብ ይልቅ ማደናገሩን ሙያቸውና ተልዕኳቸው በማድረግ የችግሩ አባባሾችና አፅራረ ቤተ ክርስቲያን ሆነው አሉ ይኖራሉ። ለእንደነዚህ ላሉት የካህናት ካባ ተጎናጻፊዎች የበላይ የክህነቱ ባለቤቶች ግርግር የፈጠረውና ያስገኘው ምርት ይህን ይመስላል። እጅግ በጣም አስደንጋጭ ድርጊት ነው። ቤተ ክርስቲያኗ የማታዝዘውና ያላከችውን ካህን መቀበሉና ለመገልገልም ሲባል ማስተናገዱ ለጊዜያዊ እንጀራ ተብሎ ዘለቄታውን ክርስቲያናዊ ሕይወት ማበላሸት ነው። ይህን ጊዜ ማን ይከላከል። ከማን ማስረጃ ይጠየቅ? ምዕመናን የመቆጣጠር የመከታተል ሙሉ በሙሉ የቤተ ክርስቲያናችው አደራ አለባቸው። ነገር ግን ምዕመናኑም ባንዳንድ ቦታ ቤተ ክርስቲያን የሚመሠርቱት ለአምልኮተ እግዚአብሔር ሳይሆን ለአምልኮተ መንግሥት ማለት ለድርጅታቸው ማጠናከሪያ

በገንዘቡም በለውም ኃይል ምንጭነቱ ፍቱን ሆኖ በመገኘቱ ነው። ይህ መቼም ፀሐይ የሞቀው ሰው ሁሉ የሚያውቀው በገሀድ እውነት ነው።

የሚያሳዝነው ሁሉም ካህኑም የአሜሪካኑም ሲኖዶስና መሥራች ምዕመናንም ካንዳንድ ቦታዎች ተባባሪዎች በመሆናቸው ነው። በቀላሉ አነጋገር «ዚአከ ለዚአየ» [እኔ ላንተ አንተም ለኔ] ዓይነት ትብብር። ታዲያ ለዚህ ሁሉ ሽፋን ሆኗ መገልገያ የሆነችው ይችው ቅድስቲቷ እናት ቤተ ክርስቲያናችን ናት። አሜሪካ ደግሞ እንኳን እግዚአብሔርን ማምለክ ቀርቶ ስሠይጣን አምልኮም ከልካይ የለበትም። እሜሪካ የገባች ቤተ ክርስቲያን ምን እንበላት? እንደ ኢየሩሳሌሟ ምኩራብ የሚገርፍና ጠረጴዛዋን የሚገለብጥ ያውርድባት ብለን እንጸልይ? ከደረሰስ ያድርገው። እንግዲህ እንዴት አድርገን ጸድቃንን ከኃጥዓን እንለይ? ከዚህ ላይ ነው «ኩሎ ዐረየ ወኅቡረ ዐስዉ።» [ሁሉም አንድ ሆነ ተባበረ ወነጀሰ መዝ. 13:3] የሚለው ቃል ትርጉም የሚያገኘው። በዚሁ ዓይነትና መልክ የተቋቋመ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ ነው።

ካህናት ሆይ እግዚኦ በሉ። እንክርዳድም ንፁሕ ስንዴም ያለው ከናንተው ዘንድ ነው። የአሜሪካው ሲኖዶስ ካህናትን ማቅሰስ መነኮሳትን ማቆመስ ሥራው አልፎና ተርፎ ራስን በራስ መተካቱ ላይ ሆኗል ማለትም ኤጲስ ቆጶሳትን መሾሙን የድል መቀዳጃ አድርጎታል። ጳጳሳትን ማብዛት ማበርከት ለቤተ ክርስቲያኗ ብልጽግና ነውን? በሆነማ ምንኛ ደስ ባለን በነበር? ነገር ግን አይደለም። ባለመሆኑም ኃዘናችን ብዙ ድካማችን ጣር ጋር ሆኗል። ይልቁንም የሚያዝኑላትና የሚያስቅሱላት ለዓይናቸው እንቅልፍ ነሥተው ሌት ከቀን ቀሪ ሕይወታቸውን ነገ ከነገ ወዲያ በነዌ ከፈን ስምትጠቀለል ሥጋቸው ክብርና ልዕልና ከመሠጠት ይልቅ ለቤተ ክርስቲያናቸው ቢያውሉት እንዴት ባማረ? እንዴት በተዋበ? በነበር። ይህ ሲደረግ ባለማያታችን ደግሞ እጅግ በጣም አዝነናል።

የአሁኑን ፈጽሞ አያደርገውና ኢትዮጵያን በአንድነቷ ጠብቃ የኖረችው ቤተ ክርስቲያን ከማንነቷ ሥልጣን በጉልበት ተሠርዞ፡ ዘካሪዋ ተዘካሪ፡ መጽዋችዋ ተመጽዋች፡ ይቅርታ አድራጊዋ፡ ምሕረት ጠያቂ ሆናለች። ገፀ ላሕይዋም ሆነ ግብሯም ከስሞና ገርጥቶ እንዲሁም ተስውጦ ይታያል። ይህን ለማለት የፈለግሁት የካህናት መልካምና ቅን ሥራ ወዴት መሄዱንና በምን መልኩ መተካቱን ለማሳየት ነው። ካህናት ጠባ ለኪዳን መሸ ስቁርባን እየተባሉ የአገልግሎታቸውን ዘርፈ ብዙ መሆኑን ይህን በመሰለው

አገላለጽ ሲነገር ይታያል። ከዚያም በላይ ካህን በተወደደበትና ባልኖረበት ዘመን ደግሞ «ታቦት በራሱ ቃሚል በጥርሱ» ተብለውም ተወድሰውበታል። ተደንቀውበታል።

ስለዚህ በዚህ በሰሜን አሜሪካ ካህናቱ በተለያዩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ለክህነት አገልግሎት ከኢትዮጵያ ተጋብዘው ይመጣሉ። አንዳንዶችም እንደ ምዕመኑ በልዩ ልዩ ምክንያት መጥተው ከሕዝቡ ጋር ይኖራሉ። ሁኔታውን ተመልክተው የምዕመናኑን ችግር ተረድተው ቢያውቁትም፥ ባያውቁትም የክህነት አገልግሎት ሥራውን ይጀምራሉ። ምክንያቱም ቅጽ [ፎርም] ሙላ፥ የትምህርት ማስረጃ አቅርብ፥ የበላይ ባለሥልጣኖች ቃለ መጠይቅ ያድርጉልህ የሥልጣነ ክህነት ማስረጃ አቅርብ የለበትም። የሚታየው የካባው አለባበስና መክበስበሱ፥ ከዚያም አልፎ ተርፎ መቀደሱ ነው። ከዚያ ውጭ «አይቴ ነበርከ ምንተ ገበርከ» [የት ነበርህ? ምን ሠራህ?] የለበትም። የሥልጣነ ክህነት ማንነቱ፥ ከሁሉም ማስፈራቱ፥ አንቱ ማሰኘቱ ነውና! ስለዚህም በቀላሉ የሥራው ባለቤቶች ይሆናሉ።

ቀደም ሲልም ካህናትን መስለውና አክለው የሀገርን ደኅንነት ስማስጠበቅ ይሁን ወይንም ሆን ተብሎ ካህናቱን ለማስጠላት የነሱን ልብስ አስለብሰው በየመጠጥ ቤቱ ሲዘዋወሩ፥ አልፎ ተርፎም ከሚወስዱት መርዝ የተነሣ ልብሳቸው እንጂ እነሱ ካህናት ባለመሆናቸው ኃላፊነት የጎደለው ተግባር ሲፈጽሙ ሲታዩ ያስ አበሳቸው እውነተኞቹ ካህናቱ ሲተቹና ሲረገሙ፥ ሲናቁና ሲሰደቡ ነበር። በዚህ ብዙዎቹ ያዝኑና ይተክዙም ነበር። ጊዜውን ጠብቆ ያ ሁኔታ ሲቀየር ደግሞ በልብስ መምሰል ብቻ ሳይሆን በገሀድ ካህን ሳይሆኑ ካህን ሆነውና መስለው የቤተ ክርስቲያኗን ስምና ማንነት እያጎደፉ ያሉ ብዙዎች ናቸው።

ታዲያ «በእንቅርት ላይ ጆሮ ገድፍ» እንዲሉ ያን መሣዩ ሁኔታ በሚከሠትበት ወቅት የበላይ አባቶች አንድነት መጥፋትና የአስተዳደሩም ቀጥተኛ መሥመር ያለመያዝና ያለመጠበቅ ደግሞ የበለጠ የጥፋቱ መሥመር ተመቻችላቸው። በተመሳሳይ መልኩ ካህን ሳይሆኑ ካህን የመሠሉ አሁንም እየተከሠቱ ነው። እንዲያውም በአርቶዶክስ ካባ ፕሮቴስታንቶችም «ተሐድሶ» የሚል ስም ስራሳቸው አውጥተው የአርቶዶክስን ትምህርት የሚያጎሳቁሉ በኢትዮጵያ በዝተዋል ይባላል። ከየትኛው ዕንቁላል እንደሚፈለፈሉ ግን ተለይቶ አልታወቀም ይላሉ። እንግዲህ ከዕንቁላል የሚገኙትን ስንመለከት እባብም አስችበት። ሁኔታው የእባብ ዕንቁላል ሳይሆን አይቀርም። መልካም ነገር ከእባብ አይጠበቅምና ነው።

ይህ ሁሉ እንዳለ ሆኖ የአውነተኞች ካህናት ችግር ደግሞ አመራር የሚቀበሉበት፥ ምክር የሚጠይቁበት፥ የበላይ አባት የላቸውም። አካባቢውን ተመልክተው ወደ አንዱ ከፍል ይጠጋሉ ወይንም ይሸሻሉ። በብቸኝነት ሁሉንም አክለውና መስለው አገልግሎት ይቀጥላሉ። እኒህ የተሻሉት ናቸው ለማለት የምንገደድበት ምክንያት ደግሞ አለን። ጥሩ ድምፅ ያለው መዘምር ቤት ተከራይቶ፥ ምዕመናንን በማስታወቂያ አሰባስቦ ክርስትና ያነሳል፥ ፍትሐት ይፈታል። ቀድሶ ያቆርባል፥ ትምህርት ይሠጣል፥ ደሞዙን ከሙዳየ ምጽዋቱ ላይ ዕጹ እንደ ቸረፈሰ ያገኛል። ስለ ሥርዐ ሥልጣኑ ግን ተጠሪነት አይጠየቅም አያሳይም እሱም አይናገርም። እንደ ምሳሊያዊ አባባሉ «መጽሐፉም ዝም ቄሱም ዝም» ሆኗል። ቀዳሹም በገዛ በተከራየው ቤተ መቅደስ እንደ ፈለገኝ ብቀድስ ይላል። ይህ አሠራር በዚህ ከቀጠለ ነገ ከነገ ወዲያ ይቆረጠማል ወይ? እሱስ ቆርጣሚ ቢገኝ አይደል። ይህ አፈጻጸም የቤተ ክርስቲያኗን የሕይወት ጉዞ እጅግ አድርጎ እያጎቆለው ነው። ማን ነው ለመሆኑ ይህን ውጣ ውረድ ተጉዞ ተጓጉዞ የሚያስተካክለው? ማነው ይህን የተፈጠረ ኮረብታ ዝቅ አድርጎ የሚደለድለው? መልሱ ምን ይሆን? ሌላ ነቢይ እንጠብቅን?

በእውነቱ ከዚህ ላይ ሳይወላ የማይታሰፍ አንድ ዓቢይ ክስተት አለ። እሱም በአሜሪካ በየጊዜው የሚቋቋሙት አብያተ ክርስቲያናት ቁጥር ብዛት ሲታይ የሚደነቅ ነው። ምነው እኒህ ሁሉ ባንድ አስተዳድር ሥር ቢሆኑ ታላላቆቹን የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገዳማትን፥ መምህራንና ደቀ መዛሙርታቸውን ተራራ የሚያህለውን ችግር በፈነቃቀሉት፥ አውርደው በከሰከሱት ብሎ ያስመኛል። የአብነት ትምህርት ቤቶች አንጋጠው የርዳታ ያለህ በማለት ላይ ናቸው።

አዎ! አሁንም በተናጠል የሚረዱ መኖራቸውን ብንሰማም እንደ ፍላጎታቸውና እንደ ምኞታቸው እንጂ በተጠና መልኩና ማዕከላዊነትን በጠበቀ መንገድ አይደለም። ይህም በመሆኑ የሚደረገው ርዳታ አረም የበላው አዝመራ ሆኖ ይታያል። ይሁን እንጂ ዕድሚያቸውን በሙሉ ታርዘው፥ ተርበውና ተጠምተው ቅኔ፥ ዜማ፥ መጻሕፍት ስሚያስተምሩት መምህራንና ተማሪዎቻቸው እርዳታ ይፈልጋሉ ግን አላገኙም። ካህናቱ ለካህናቱ ጥላ ከለላ ካልሆኑ በእውኑ ማነው የሚሆናቸው? በአገር በደረሱት ችግሮች መርጃ የሚውል በየአብያተ ክርስቲያናቱ ተጠይቆ ተበብሰቦም ነበር። ነገር ግን በእውነት ራሳቸው ተርበውና ተጠምተው ትምህርትን ለሚዘሩት መምህራን ሳይሆን ርዳታው የተላከውና

የተሠጠው ለሚወክሏቸው ድርጅቶች ነው። እሱም ከቤተ ክርስቲያን የሚሰበሰብን በቤተ ክርስቲያን በኩል እንዲያልፍ ብልሃት ሆኖ ይመስላል የተሠጠውም ለካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ነው።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከውጭ ላሉት አብያተ ክርስቲያናት ዝምድናው ርቆ ከመዝገብ ተፍቆ ይሆን? «ተድረው ቢመለሱ የወንዝ መንገድ ይረሱ።» ሆነና ድሮ ድሮ ሳይሆን ትላንት ጥለውት የመጡትን ያደጉበትንና የኖሩበትን ገዳምና ደብር ረስተው ወይንስ ችላ ብለው? የሚሠጠውን ርዳታ አሳልፎ ለሌላ የተሠጠው? መቼም የመጽደቂያው መንገድ እንደምትነግሩን ከሆነ አልፋችሁት ሄዳችኋል። እንዲህ ተብሎ ደግሞ ለእናንተ አይነገር። ቢነገር ደግሞ በአቋራጭ ቅሠፈት አለ ትሉናላችሁ። ምነው ጥበባችሁ ፈሲጡ ሁሉ እኔ ለእኔ ከመሆን እኛ ለኛ አልሆን አለ? እግዚአብሔር ያጠብቦሙ ለእውራን እንጂ ለካህናት ምን ነበር ቢል ብለን እናማር? ለኢትዮጵያ ሕዝብ ርዳታ ለማድረግ በካቶሊክ በኩል መላክ ማለት ከዓይን ጆሮን ማመን ሆኖ ነው። የኛ ቤተክርስቲያን ለኛዎቹ ዝምድናው ርቆ እጅግ ተፎልቅቆ ለካቶሊክ ድርጅት ታማኝነት አግኝቶ ተሠጠው። ይህ ነው የቤተ ክርስቲያኗ አንድነት መሳዳት በግልጽ ከሚታዩት ችግሮች መካከል አንዱ ሆኖ ያለው። የሚለመነውን ቁራሽ እንጀራ እንኳን በእንተ ማርያም ላለው መዘክር ሲገባ አትቁም ብሎ ድርና ማተብ ለሚሸጠው ነጋዴ መዘክር እንደ አግባቡ ቢሆን ይሻላል። ያስተዛዝበናል ይህ ቀን ያልፍና መባሉን ልብ እንበል። ተቀባይን ሠጪ ሠጪን ደግሞ ተቀባይ ያደረገ ጊዜ መለወጡ አይቀርም ያም ባይሆን ዝውውር ያለና የነበር ስለሆነ የመቀያየሪያው ሰዓት ሲደርስ የሚሆን ነው።

ካህናቱ፡ ካህናቱ የበላይ አለቃና ተመልካች የሌለበቱ እዛኛና ናዛኛ የማይታይበቱ ይህ ነው የሥልጣን ከህነቱ የበላይነቱ ምሥጢራዊነቱ በሰው ዓይን ያለመታየቱ ያለመመርመሩ ከላይ እንደሁ የሉበት ጳጳሳቱ እንዲሁ እግር ከገበታ የሌለበቱ አንቱታ። በውጭ አገር ያለው የካህናት አኗኗሩ እሁድ እሁድ ከርፋድ ሄዶ መቆም ከመንበሩ። የፈለገውን ያለመኖሩ ተጠያቂነትን በፈፀሙት ተልዕኮአዊ ሥራ መመሥገንን፡ መበረታታትንና መነቀፍን ቢያስወግዳላቸውም ቅሉ ወደፊት የቤተ ክርስቲያኗን ህልውና እጅግ ከፍተኛ አደጋ ላይ እየጣለው ነው። የሚገርመው እኒህ ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት ካህናት ማኅበር መሥርተው ባንድነት ሲያገለግሉ የሥልጣነ ከህነታቸው ሠጭ የሆኑትን አባቶች በእንግድነት መጋበዝና ማስባረክ እንጂ በቅዳሴ ጊዜ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያኗ ሕግ

መሠረት የብፁዓን አባቶች ስም ተወስቶ አይጸለይላቸውም። እነሱም ራሳቸውን ነፃ አውጥተው የራሳቸው ድርጅት አቋቁመው ይገኛሉ። ካህናቱን መካሪ ዘካሪዎችን በምን ቋንቋ ለምን እንዲህ ታደርጋላችሁ ተብሎ ሊነገራቸው ይቻላል? የሚናገር ቢኖርም በትንሹ ለንስሐ ሞት አያብቃህ ትንሿ ርግማን ትደርሰዋለች። ካህናቱም እርስ በእርስ ከመሞጋገስ በለተቀር ከዚያ ውጭ ቢነገር ውግዘት ማስጠንቀቂያው፡ ቅሠፈት የሹመት መሻሪያው ሆኖ ይቀርብለታል። ስለዚህ «ወድሰኒ እዌድሰከ» [አሞካሽኝ ላሞካሽህ] ካልሆነ በስተቀር ከዚያ መሥመር ወጣ ማለት ቀርቶ አመልቆ ማየቱ እንኳ የገህነም ቀለብ ያስደርጋል። በእውኑ እጅግ በጣም አያሳዝንምን? የካህናት መልክ ሰው ይምሰል እንጂ ህብተ መንፈስ ቅዱስ ያላቸው መናዘዝና መቀደስ፡ መባረክና መፈወስ የሚችሉ ናቸው። ለዚህምኮ ነው የአገራችን ሰው «ካህንን ሲያዩት ሰው ጸበልንም ሲመለከቱት ውሀ ይመስላል» ብሎ ምሥክርነቱን የሠጠው።

ስለዚህ ካህናት በዘዲያቸው፡ በማስተዋላቸው፡ በአዋቂነታቸው፡ ተከብረውና ተፈርተው ይኖሩ ነበር። ዛሬ ግን መፈራት በከንፈር ሆኗል። ሁሉም ነገር። አዎ! በካህናቱም አንፍረድ ያው ችግሩ መከራው ዞሮ ዞሮ መሥፈሪያውና ማደሪያው ከአቡን ደጅ መሆኑ ነው። ካህናቱም በአንድነት ከፍተኛ ታላፊነት የተመላበት ሥራ አላችሁ። የመድፈ በሳንላ አንድነት ካልሆነ በስተቀር የተጠማዘዘውን መንገድ የመደልደል ችሎታችሁ የተደነቀ ነው። አባቶቻችሁን እናንተ በአንድነት ብትናገሩ፡ እንወጣ ነበር ከችግሩ። ካህናቱ በጉዳዩ እንኳን ብታስቡበት ኖሮ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያኗ እንዳይፋለስ ይሆን ነበር። አሁንም ሊቃነ ጳጳሳትን ቤተ ክርስቲያናችን ልካለች። መታወቂያና መለያም አድርጋለች። ነገር ግን አገሩ አሜሪካ ሆነና ሁሉም በየጉዣው የያዘው የፖለቲካ የዘር የመንደር እሳት እያቃጠለው ነው። ገና ከዚያ ለመውጣት ያንን ጥሎ እፎይ ለማለት ዓዩኝ ዓላዩኝ አለበት። አወቁኝ አላወቁኝ ከንፈራቸውን በጥርሳቸው የሚነክሱት በኔና ባሌኝ ባፈረኋቸው ምዕመናን ላይ ይሆን? በሚለው የመቃበዝ የመባባት ጥያቄ ላይ ናቸው። ከዚህ ዓይነቱ ጥያቄም ውስጥ ባልተገባም በነበር። ይህ ሁሉ ትርምስ እንዲፈጠር ሌት ከቀን የሚጥሩ ለዓይናቸው ዕንቅልፍ የማይሰጡ መኖራቸውን እናስበው? ለምን ይህን እንደሚሠሩ ግልጥ ባይሆንም ቅሉ ትርፍ ካላገኙበት አንዲህ አይባክኑበትም በነበር።

አንድ ታሪክ ልናገር። አንድ የተፈፀመ ጉዳይ ሲያልፍ ምደባው ወደ ታሪክ ነውና ነው። በቅድሚያ ጳጳሳቱ ወደ አሜሪካ

መጣት ሲጀምሩ በሚገጥር ተደራጁ የጉባረት ሥራ ማኅበር ይመስል የሙያ ማኅበር በቅድሚያ የጳጳሱቱ ማኅበር ቀጥሎ የካህናት ማኅበር ከዚያም የምዕመናን ማኅበር ሁሉም በየፈርጁ ተቋቋመ። ልብ በሉ። ይህ በየፈርጁ የተቋቋመ ማኅበር በአንደኛ ደረጃ ዕቅዱና ዓላማው የሁሉም እናት ቤተ ክርስቲያንን አናውቅም በሉ ነው። ያልፈለጉትም ወፍ እንዳገሩ ትምግስችና ሲፈሩ ሲቸሩ በተአቅቦ ተስማሙ። በዜተ ክርስቲያኑም አመክሮ «ለእመ ሐርከ ብሔረ ባዕድ ኩን ከማሆሙ።» [ከባዕድ አገር በሄድህ ጊዜ እንሱን ምሰል ወይንም እንደ እነሱ ሁን] ነውና የደፈረሰው አስከሚጠራ መስሎና ተመሳስሎ መቆየቱን የመረጡ ብዙዎች ነበሩ።

ይህ ሁሉ በየፈርጁ ድርጅቱ ቀጥሎ ምንም እንኳ የቤተ ክርስቲያኗን ቀኖና የሚያውቁት ጥቂቶች ናቸውና ምዕመናኑም በማኅበር መደራጀቱን ለተንኮል ብለው አልወሰዱትም። ነገሩ ውሎ ሲያድር የየማኅበሩ ስብከት ልዩነት ራስን መቻል የሰበካ ጉባዔ ውሳኔ መተዳደሪያ ደንብ የውስጥ ደንብ አንቀጽ በአንቀጽ ሲደረደር የባለውን ከእናት ቤተ ክርስቲያን ጋር የሚደረገውን ግንኙነት ወደ ውዝዘት ከፍ አደረጉት። ከእናት ቤተ ክርስቲያን ጋር በአስተዳደር ተለይተናል ማለት ተጀመረ። ቀጥሎም በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ ተሹሞብናል። ቀኖና ቤተ ክርስቲያንም ተጥሶብናል የሚለው መፈክር መነበብና መነገር ጀመረ። አብዛኛው ምዕመን ቅዳሴው በግዕዝ ስለሆነ አይገባንም ብሎ ከመሸሽ ይልቅ መማር ሳለ ይህንም የቀኖና ውጥንቅጥ ለኛ አይገባንም በሚለውና በተለመደው ቋንቋ ጣለውና ለተወለኑ ሰዎች ብቻ ተግባር ሆነ። አሁን እንደ ተመኘኋት አገኘኋት ሆነላቸው። ከዚህ በኋላ የጳጳሳቱን ማኅበር ከእናት ቤተ ክርስቲያን ጥርግ አድርገው በውግዘት መለየታቸውን ሲያረጋግጡ መለስ አሉና ጳጳሳቱን እንደገና እርስ በራሳቸው አጣልተው ለያይዋቸው። አንዱ ሌላውን ያወግዝ ጀመር። ተሰደው መጥተው ይኸው እርስ በራሳቸው ይፋጃሉ ከውጭ ያሳመዋቸዋል ያሰኙዋቸዋል። ቀጠል አድርገው ማኅበረ ካህናቱም በተለመደው መንገድ እርስ በርስ መለያየቱን ተያያዘው።

በየቦታው እንደ ንግድ ድርጅት ያለማንም ፈቃድ ከቀኖና ቤተ ክርስቲያን ውጭ ቤተ ክርስቲያን ይከፈታል። ከጥቂት ዓመታት በኋላ አምባገሮ ይፈጠራል። የጥሉ መነሻ ብዙ ነው። ፖለቲካ የመንደር ልጅነት የበላይነትና የበታችነት ሌሎችም ተጨማምረው እርስ በርስ መለያየት ይደረጋል። በዚህም ምክንያት ያንዲት ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በፍርድ ቤት ተካሰው ይንተታሉ። ከዚያም ለሁለት ይከፈላሉ። መግቱ በጠበቃ ይያዝና ክርክሩ ይቀጥላል።

ለጠበቆች ቢያንስ ቢያንስ ከሃምሳ አስከ ሰማንያ ዶላር የተከፈላቸው አንዱን ቤተ ርስቲያን በአደባባይ ራቁቷን ሲያሰድዷት ከብዙ በታ ታይቷል። እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱ በዋሽንግተን ዲሲ ሁለት ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ሁለት መድኃኔ ዓለም ተመሥርተዋል። በቦስተን ሁለት የሚካኤል ቤተ ክርስቲያን በዴንቨር ሁለት የማርያም በሎስ አንጀለስ ሁለት የማርያም ቤተ ክርስቲያን በዳላስና በሌሎችም እንደዚሁ ተከፋፍለዋል። ይህ ሁሉ የሚያሳየው ቤተ ክርስቲያኗ በአስተዳድር ተለይታለች ተብሎ በመለፈፉ እንጂ ያለ ቤተ ክርስቲያኗ ፈቃድ ማቋቋም የማይቻል መሆኑ ቢነገርና ቢደነገግ ኖሮ ይህ ሁሉ ዝብርቅርቅ ባልተፈጠረም በነበር። ትርፉ እኒህ ኢትዮጵያውያን እንዲህ ናቸው መባሉና ትዝብት ላይ መውደቁ ነው። ከዚያም በላይ ከሦስት ዓመት መግት በኋላ ነገሩ በፍርድ ቤት እልቆ ለየብቻቸው ያሉና የሚኖሩ ቤተ ክርስቲያኖች መኖራቸውን በሚገባ ይገነዘቧል። ይህ ሁሉ የቤተ ክርስቲያኗን ታሪክና ጥንታዊነት እጅግ አድርጎ የሚያጎሳቁል ድርጊት ነው።

እኒህ የተከፋፈሉ ያንድ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናንና አብያተ ክርስቲያናት የዓመት በዓል ሲያከብሩም ሁሉም እኛ ዘንድ ኑ ጥሩ ሰባኪ አለን ጥሩ የወንጌል ትምህርት እንሠጣለን የንግድ ማስታወቂያ ሆኖ ቀጠለ አሁንም ይደረጋል። አንዲያውም እኛ ዘንድ ብትመጡ ተከሊል በነፃ እናደርጋለን እየተባለ ማስታወቂያ ሁሉ የሚነገርባቸው ቤተ ክርስቲያኖች ብዙ ናቸው። ይህ ዓይነቱ ችግር በየአህቱ እየተፈፀመ ነው። በዚህም ምክንያት ከላይ እንደገለጽነው ሁለት ገብርኤሎች ሁለት ማርያሞች ሁለት መድኃኔ ዓለሞች ሁለት ሚካኤሎች በየከተማው ይገኛሉ። ይህ እንዴት ሆነ የተባለ እንደሆነ በጥላቻ በገንዘብ እየተጣሉ ነው አዋሩ መልስ። ከዚያ ባሻገር ደግሞ የጠ/ግዛትም ሽቱ አለበት። ይህ ችግር የደረሰባቸው ከተሞች ዋሽንግተን ዲሲ ቦስተን ዳላስ ቴክሳስ ሎስ አንጀለስ ካሊፎርኒያ አትላንታ ጆርጂያ ሚኑሴታ ዴንቨር ኮለራዶ ወዘተ... እኒህ ከብዙ ጥቂቶቹ ናቸው። መሳቂያና መሳለቂያ አልሆንምን? አናት ቤተ ክርስቲያን የማታዝዝባቸው በማንም የማይገዙ የማይናዘዙ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው። እኒህ ሁሉ በክርስትና ስም የሚፈፀሙ ደባዎች ናቸው። ቤተ ክርስቲያን እጅግ ተጎሳቁላለች። እኒህ ሁሉ አባቶች ካህናት ዲያቆናት በቤተ ክርስቲያን ሥር ያለፉ ራሳቸውን ለቤተ ክርስቲያናቸው አገልግሎት አሳልፈው የሠጡ በካህናት አልባሳት የሚታዩና የሚያጌጡ ናቸው። ማንም ጣልቃ እንዲገባባቸው አይፈልጉም። በዚህ ዓይነት አገልግሎት የሚሠጡ ክርስቲያናዊና

ፖለቲካዊ ኩባንያዎች ናቸው። በሃይማኖት ለም የግል ንግድ የሚያካሂዱ የፖለቲካ ሥራ የሚፈጽሙ ናቸው። ዛሬ የውጭ ሲኖዶስ ሲኖር ማኅበረ ካህናቱ ሥራውን ጨርሶ ተበትኗል። ሠርሆተ ማኅበራት ተደርጓል። ስንብት አድርገዋል ማለት ነው። አሁን በስሜን አሜሪካ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት ማለት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባሉ።

አንደኛው ከእናት ቤተ ክርስቲያን ተመርጠው የተላኩ ካህናትና ጳጳሳት ሥር የሚገለገሉ፥ ሁለተኞች አሜሪካ ባለው ሲኖዶስ ሥር ያሉና ካህናት ከአዲስ አበባ በእነሱ በኩል የመጡ ወይንም ከዚህ ሙያው ያላቸውን መቀደስ ማወደስ የሚችሉ፥ ሦስተኞዎቹ ከእናት ቤተ ክርስቲያንም ሆነ አሜሪካ ካለው ሲኖዶስ ሥር ያልሆኑ ገለልተኞች የሆኑ በራሳቸው በጎ ፈቃድ የሚመሩ ናቸው። እንዲህ ያለ ዝብርቅርቅ ብሎ የሚገኝ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና ምስረታ ላይ ናት ቤተ ክርስቲያናችን። እኒህ ሁሉ አብያተ ክርስቲያናት የሚያገለግሉት ኢትዮጵያውያንን ብቻ ነው። ምናልባት አንድ ወይንም ሁለት ቤተክርስቲያኖች ብቻ በእንግሊዝኛ ለካረቢያንና ለመሳሰሉት ክርስቲያኖች አገልግሎት የሚሠጡ አሉ። እንግዲህ ይህ ፀጋና ሀብት ከሆነልን እሺ በጎ ግን አይደለም እጅግ በጣም የሚያሳዝን የሚያስለቅስ በእውነት ኢትዮጵያውያን እንዲህ ነን የሚያሰኝ ነው። ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ቤተ ክርስቲያናችን ይህን በመሰለ መልኳ ትገኖለች። ሥዕለት ለሚሰሙ ታቦታት አንድ እንዲሆኑ ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው ጋር እንዲደባለቁ ተሳሉ ጸልዩ ከልብ እንባ አፍሳችሁ ለምኑ። ሰው የሚፈታው ጉዳይ አልሆነም። ሁሉም ለራሱ አንጂ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የሚያስብ ጨርሶ ፈጽሞ የለም። እንዴት እጅግ በጣም የሚዘገንን ነው። እንዴትስ የሚመር ነው። ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በሠጡ አባቶችና ካህናት በዚህ ዓይነት ቂም በቀል ለብሰው እንዴት ወደ ሥጋ ወደሙ ፍተታ ይቀርባሉ? አግዚአብሔር ሆይ ፍርድህን ስጥ። ዳታንና አቤሮንን ያስጠምህ፥ ለዶምና ገሞራን ያቀጠልህ፥ ምነው ምሕረትህ በዛ? ስምህን መቀደሻና መወደሻ የሆነችውን ይችን ቤተ ክርስቲያን ከሚያጎሳቁሏት ዕጅ አታወጣትምን? ይህ የደጋጎች የምዕመናን ኃዘንና የዘወትር ጸሎትና ጥያቄ ነው።

አበው ካህናት እናንተም ተመስማናችሁ፥ ሕዝበ ክርስቲያኑንም አስደስታችሁ፣ በኖራችሁ በነበር። እስከ መቼስ ድረስ ነው በዚህ ሁኔታ የምትቀጥሉት? ወይ ከዚህ አልሆናችሁ፥ ወይ ከዚያ አልሄዳችሁ። እንዲሁ ከቅርንጫፍ ቅርንጫፍ፥ ከወዲያ ወዲህ

እየተወዛወዛችሁ በተፈጥሮአችሁ የሌለውን ተግባር ታከናውናላችሁ። ለዕለት ጉርስ ለዓመት ልብስ ብላችሁ የዚችን ጥንታዊት ልዩና ብርቅ ድንቅ ቤተ ክርስቲያን የፀጋ የበረከት ቦታ ራቁት ታስቀራላችሁን? አለቡበት ራሳችሁን መርምሩ። ይህ የምትፈጽሙት ሥራ የካህናት ባሕርይ አይደለምኮ! «ኩኑ ጠቢባነ ከመ አርዌ ምድር ወኩኑ የዋሀነ ከመ ርግብ» [እንደ እባብ ብልሆች እንደ ርግብ የዋሆች ሁኑ] ለምኑ ይሆን? የዚህ ቃል ትርጉም ምንድን ነው? ጥበባችሁስ ወዴት አለ? የዋሕነታችሁሳ ወዴት ነው?

ይሁንና እንደሚታወቀው ቀራንዮ ቀራንዩ መድኃኔ ዓለም መድኃኔ ዓለም ካህናቱ ካህናቱ ብለን እንሻገር። የበደላችሁት ራሷን በእንተ ስማ ለማርያም ብላችሁ ያሰተማረቻችሁን እንዲት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ነው። አባቶችስ ሥልጣናችንን ተነጥቀናል ብለው እሱም ቢሆን ነፍስንና ሥጋን አንድ ያደረገ አምላክ ያውቀዋል። ያያቸዋል። ለመሆኑ በትውልድ በሥርዎ ከህነት የወረሱት ርስተ ክህነት ነውን? አነሱን አርዓያ አድርጋችሁ ቤተ ክርስቲያናችሁን መበደሉ ይብቃ በሉት። ሁሉም ያልፋሉ እናንተም ታልፋላችሁ ባላችሁ ጥቂት ጊዜ ሥራ ሥሩባት። ትላንት የነበሩ ዛሬ የሉም። ለእናንተ ምኑስ ይነገራል? ነገር ግን እወቁበት።

አሁን ያለወቅቱና ያለመከሩ በዘነበው ዝናም የቤተ ክርስቲያኗ የአንድነት አዝመራ አልተበላሸምን? ያለ ጥቅም አልቀረምን? የሰዎች ምስክርነት ግን አንዳልሆነ ሆኗል። ነገር ግን የኔ ጥያቄ ቤተ ክርስቲያኗ ጠላቶቿ ከበዋት፥ ጥሏት ማታ ናዳ አየፈነቀሉባት ባለበት ወቅት የሚጠበቀው ምንድን ነው? ይኸውና የፕሮቴስታንቱ ራዲዮኑ፥ ቴሌቭዥኑ ጣላት ግረሩት እያሏት አይደለምን? በለሚ መባረክና መቀደስኮ ሊታጣ እንደሚችልም ከሩቁ መመልከት ይገባል። ያ ካልሆነ የካህንነቱ ንጽሕ ባሕርይ የቱ ላይ ነው? ዓይናችንን ከፍተን እንመልከት። ይህን በማያደርጉት ላይ የተሠጠ ምሳሌም አለ። ለግንዛቤ ያህል እንዲህ ይላል። «አንድ ንብ ከምትሞት ሃምሳ ካህን ቢሞት ይሻላል።» ካህናት አዕይንተ አግዚአብሔር አየተባላችሁ መጠራታችሁን አትርሱ። አሁን ግን የእግዚአብሔር ዓይኖች መሆናችሁ በነበር ካልተያዘ በሥራ አታሳዩትም። ስለዚህ ካህናት ዘበምድር ብለናችኋል ብለን እንውጣ። የምሕረት፥ የይቅርታ፥ የሰላም ዓይኖቻችሁ ይብሩ ይገለጡና ችግሩን ይመልከቱ። ማኅበራችሁ የአድማ መበተኛ፥ ከሠይጣናት ቁራኛ ፈጽሞ መዳኛ ይሁን። ለሁሉም ጊዜ አለው። የምስክርነታችሁ ጊዜው ዛሬ ነው። ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ እንዳሉት «በጊዜ ሥሩበት እንጂ ጊዜ አይሥራባችሁ።»

እንዲሁም ደግሞ ከዚህ ቀጥሎ እንደ ችግር የማቀርበው ከዚህ ለየት ያለውን ሃይማኖታዊ አባትን ማጣቱን ነው። ይህ ደግሞ እንዴት ያለ ከፍተኛ ችግር ፱ምዕመናኑ ዘንድ እየፈጠረ ነው። በአብዛኛው በውጭ ባሉ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ እዳ የሚከፍሉበት ይመስል ሥርዓቱን እያወቁ በቤተ ክርስቲያኑ የሠበካ ጉባዔ አባላት ማንነትና ፍራቻ ካህናቱ በይሉኝታ ተውጠው ሥልጣነ ክህነታቸውን በሚያገኟት ላንቲም ወይንም ምንደኛነታቸውን አረጋግጠው በዝምታ ሥጋ ወደሙ ለመለወጥ በሚደረገው በጸሎተ ቅዳሴ ላይ እንኳን የሲቃን ጻጻላቱ ስም አይነሳም አይወሳም አይጸለይላቸውም። አልፎ ሃጅ አባት ከተገኘ ላንድ ጊዜ ቅዳሴ ብቻ ተወስቶ ይታለፋል። በዚሁ በአሜሪካ ለምሳሌ የጳውሎስም የአጵሎስም አይደለሁም የሚሉት የካህናት ቁጥር ጥቂት አይደለም። አባ ዕገሌ ተወሉ አልተወሉ ምን ያጎድላል? ምንስ ይጨምራል? የሚለው ሳይሆን ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያኗን ያፋልሳል የአበውን ድንጋጌ ይቃረናል ነው።

ቂም በቀል ተይዞ ሥጋ ወደሙ ፈት ይቀረባልን? ካህናቱስ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን የመጠበቅ ግዴታስ የለባችሁምን? የገና ገና ደሞዝ ከፋዮችን ዓይንና ፊት እያያችሁ ሥርዓተ ቅዳሴን ያህል ዐቢይ ጸሎት በፍራቻ ተሸማቃችሁ የሚባለውን ሳለማለት ትስማማላችሁን? የያዛችሁት ሥልጣነ ክህነት አሳት ሆኖ አያቃጥላችሁምን? ይህን እንኳ ለመፈፀምና ለማድረግ ችላ ያላችሁ ለሌላማ እንዴት ተደርጎ ትታመናላችሁ? ይህን ባለማድረጋችሁ ቤተ ክርስቲያን ትወቅሳችኋለች ታፍርባችሁማለች። በቂምና በበቀል ተመልታችሁ የሥልጣናችሁ ባለቤቶችን ስም በጸሎተ መዘክርን ታልፉታላችሁ። እናንተ የማትወዷቸውና የምታፈቅሯቸው አባቶች ጸሎተ ቅዳሴው ማድያ መጉጃና መጥቀሚያ ነውን? እኛስ እንዴት አድርገን በእናንተ ዕጅ መስቀል እንሳለም? ምንም እንኳ እናንተ ለመበቀሉ እንደ ጉጠት እንጂ መስቀሉን ስላይደላችሁ እንሳለመዋለን። እናንተ ግን ግዴታችሁን ለመወጣት ከምዕመናን በታች መሆናችሁን ተረዳችሁትን? ይህን ሁሉ ሲመለከቱትና ሲያዩት በጸሎተ ቅዳሴ ላይ ጥለህ ውጣ ይህን ከምታይና ከምትሰማ ያለኛል። ለእናንተስ ማን ይንገራችሁ? እያወቃችሁ የምታጠፉ አልሆናችሁምን? ሌላው ቢቀር የምትፈትቱት ሥጋ እሳት ሆኖ ይፈጅናል ብላችሁ አስቡ። «ዘቦ ቂም ውስተ ልቡ ወዘቦ ውስቴቱ ሕሊና ነኪር ወዝሙት ኢይቅረብ።» [ንጹሕ ያልሆነ ግን ከቁርባኑ

አይተባል ለለይጣንና ለመላኩተኞቹ በተዘጋጀ በመለኮት እሳት እንዲይቃጠል። በልቡናው ቂምን የያዘ ... እይቅረብ።] መጽሐፈ ቅዳሴ ጉልሕ 1994 ገጽ 82] የሚለው ንባብ እንዲሁ ስጠ ተጻፈ ብቻ ታነቡታላችሁን? ወይንስ የምታነቡትን እትረዱትም? ወይንስ ወቃሽ ከሳሽ የለብንም ብላችሁ ይሆንን? ወይንስ የቀጣሪዎቻተሁን ልብ ለማግለል የማይፈልጉትን ሳለማለት ይሆን? በካህንነታችሁ የሚባለውን ማለት እንዳለባችሁ አስረዱ። ግዴታችሁን ለገንዘቡ ብቻ ላይሆን ለሥርዓተ ቤተ ክርስቲያኗም ተገዥነታችሁን አረጋግጡ። ቅዳሴውን እንደገና ጽፈው ሊሰጧችሁ አይችሉም። እንኳን እነሱ እናንተ እንኳን መለወጥ አትችሉም። ይልቁንስ ይህን ግዴታ ባለመወጣታችሁ እዳ አለባችሁ። ይህ ዓይነቱ አፈፃፀም ደግሞ ወደ ምናለበት አምባ ይደባለቅና መለየቱና ማንጠርጠሩ ይከብዳል። ለሁሉም ጉዳይ መፍትሔውና መድኃኒቱ ለእናንተ እንደ ሥርዓቱ አገልግሉ ነው። ይህን ማድረጉ ተክክል ነው። ከዚያ ውጭ ግን ጥፋት ነው። ለቤተ ክርስቲያኗ ደግሞ ከናንተ ወዲያ የሚቀርባት የለም። እንዲያው «ባልና ሚስት ሊተዋወቁ የሠርገኛ ልቡ አበጠ» ሆኖብኝ ይሆን? ይህን በማለቴ ማሩኝ ይቅርታም አድርጉልኝ።

፫ . የሠበካ ጉባዔ

ከሁሉ በፊት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባል በመሆናችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ። ቀደም ሲል የነበራችሁ አሁን ግን በልዩ ልዩ ችግር የተሰደዳችሁ ኑ ተመልሳችሁ። ቤተ ክርስቲያኗም ዕጇን ዘርግታ ትቀበላችኋለች። ምዕመናን ሆይ! ሃይማኖት በአንድ በእግዚአብሔር ማመንና የመንግሥቱ ወራሽ፥ የለሙ ቀዳሽ መሆን ነው። ሃይማኖት ከሰብአዊ አስተሳሰብና አመለካከት እጅግ በጣም ልዩ ነው። ሲሞቀን የምናወልቀው፥ ሲበርደን የምናጠልቀው አይደለም። እንዲሁም ስናዝን በልቅሶና በእንጉርጉሮ፥ ስንደሰት ደግሞ በከበሮ የምንፈነጥዝበትም አይደለም። ሃይማኖት የማንነት መለኪያ የእግዚአብሔር መገለጫያ ማወቂያና መገዣ የራሱ የባለቤቱ ሰም ነው። አዎ! ሰው በተፈጥሮው ነፃ ነው። የፈለገውን ይይዛል የማይመስለውን ያለወግዳል። ሲጠይቅ ያገኛል። በር ሲያንኳኳ ይከፈትለታል እንጂ ሲርበው አምላኩ የሚያጎርሰው፥ ሲጠማው ውሀ በብርዌቆ ቀድቶ የሚያጠጣውም አይደለም። ስጠኝ ሲል ግን ይሠጠዋል። ይህ ደግሞ እንግዲህ የሚያመለክተው ሰው በራሱ በጎ ፈቃድ የሚመራ መሆኑን እንረዳለን።

ከዚያም በላይ እግዚአብሔርን ዘወትር የሚያመሠግኑ፥ የእሱን ምሕረት ለሚሹት፥ የሥራውን ቅደም ተከተል ይገልጽላቸዋል። ከእነዚህ ሕዝብ መካከልም ኢትዮጵያውያን ይገኙሉ። ሃይማኖት ለመጀመሪያ ጊዜ የታወቀውና የተጀመረው በኢትዮጵያውያን እንደሆነ ታሪክ ያስረዳናል። ከዚያም አልፎ ተርፎ ክርስትናም ሲገባ በራሱ ፈቃድና ተአምራታዊው ሥራው ነው። ዘወትር ሊታወስን የሚገባው ዓቢይ ምሥጢር ቢኖር ይህ ክርስትናን በከፍተኛው ኢትዮጵያዊው ሹም በባኮስ ወይንም በጃንደረባውና በራሱ ደቀ መዛሙርት አማካይነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲሠበክ ማድረጉ ነው። ክርስትና በኢትዮጵያ የተሠበከው በእግዚአብሔር በራሱ ጥበብና ፈቃድ ነው። ከዚያች ቀንና ሰዓት ጀምሮ ያለችውና የኖረችው ይችው የኦርቶዶክሷ ሃይማኖታችን ናት። እነሆ ከቁልኬዶኑ ጉባዔ ጀምራ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተብላ ጸንታ ትኖራለች ትታወቃለችም።

ይችን ሃይማኖት፥ ይችን ቤተ ክርስቲያን በሰይጣናዊ ቅናት ለመገልበጥና ለማፍረስ በየዘመናቱ ከሰብከቱና ከውትወታው ከፖለቲካውና ከዲፕሎማሲው ሁሉ ባሻገር የጦር መሣሪያ ታጥቀው፥ ሠራዊት አሠልፈው ወረዋት ነበር። ግን እንኳን ሊያጠፉት ይቅርና ከመሠረቷም አልነቀነቋትም። ምክንያቱም በራሱ በኢየሱስ መሠረትነት፥ በራሱ በጎ ፈቃድ ላይ የተመሠረተች ናትና ነው። ይችን ቤተ ክርስቲያንም በመንከባከብና በመጠበቅ ያላቸውን በመሥጠት አብያተ ክርስቲያናትን በማነጽ ዋናው የመሠረቷ ደጋፊዎች ሆነው የኖሩት አሁንም ያሉት ምዕመናን ናቸው። ቤተ ክርስቲያን ያለ ምዕመናን ምዕመናን ያለ ቤተ ክርስቲያን ሕይወት የሌለው አካል ነው። እንዲያውም ራሳቸው ምዕመናን ናቸው ቤተ ክርስቲያን የሚባሉት። ያለ ቤተ ክርስቲያን ካህን ብቻውን ምንም የሚሠራው ነገር የለም። አገልግሎቱም ለምዕመናን ነውና ነው። ይህም ምዕመናን ምን ያህል ከፍተኛ ቦታ እንዳላቸው ያረጋግጣል።

ይህን የካህናትና የምዕመናን ጉባዔ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ዕድና እግር ራስና አንደበት ዓይንና ጆሮም ነው። ይህ የሠበካ ጉባዔ ባይኖር ባይቋቋም ኖሮ ቤተ ክርስቲያናችን ምን ትሆን ነበር? ምንስ ይውጣት ነበር? የትስ ትገባ ነበር? ምዕመናን ነገሩን በሃይማኖት ዓይን ተመልከቱት ዕዩት። ይህ የሠበካ ጉባዔ የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ነው። የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት በፀሐይ ግባት ሲከለል የሚመጣውና የሚተካው ጨለማ ሌሊት ነበርና ይህን አስቀድሞ በማሰብ በቀን ገና ሳይጨልም በመቅረዞች ሁሉ ዘይት መሙላት አስፈለገ። ይህም ቤተ ክርስቲያኗ በጨለማው እንዳትሰነካከል ያለ ብርሃንም በጨለማው እንዳታድር ከተኛችበትም እንዳትቀር አድራ እንድትነሣና እንድትውል ተዘጋጀላት። ይህም የመቅረዝ ዘይት ተብሎ ለቤተ ክርስቲያኗ የተዘጋጀው የሠበካ ጉባዔው ነው። በዚህም የሠበካ ጉባዔ ምዕመናን ሕጋዊ በሆነ መንገድ በነጋሪት ጋዜጣ አንድ ድርጅት አሉም የሠበካ ጉባዔ ተቋቋመ። ይህን ጉባዔ ሕጋዊ የሚያደርገው ቃለ ዓዋዲ በአዋጅ በመንግሥት ፈቃድ ተቋቋመ።

ይህ የሠበካ ጉባዔ መመሥረት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን በሮች በጨለማው ተዘግተው እንዳይቀሩ ከመዘጋት አዳነ ጠበቀ። ይህን የሠበካ ጉባዔ እንዲቋቋም የአወጀና ያጸደቀ መንግሥት ሲፈፀም የሚቀጥለው መንግሥት ከግለ ሰብ እስከ ቤተ ክርስቲያን ሀብት ንብረት በሙሉ ወረሰ። ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት የምታገኘው የዓመት በጀት በከፍተኛ ደረጃ ቀነሰ ተቋረጠ። ገዳማቱና አድባራቱ መተዳደሪያ አጡ ነጡ። በዚያን ጊዜ

ዝዘህ የሠቸካ ጉባዔ መሥራችና ኃላፊ አመንዊ በሥራ ተርጓሚ የነበሩት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ለዚያ ሀብትና ንብረቷን ለወረሰና ለቀማ ብሔራዊ ሃይማኖትነትዋን ለሻረ መንግሥት የጻፉት ደብዳቤ ይህን ይመስል ነበር። ቀጥሎ በዝርዝር ቀርቧል። የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ወዕጨጌ ዘመንበሮ ተክለ ሃይማኖት ልዩ ደብዳቤ፤ የተጻፈው መጋቢት ፭ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም. ነበር።

... በዚህ ጊዜ አንድ ሊዘነጋ የማይችል እውነት ሊነገር ይገባዋል። በአሁኑ ጊዜ የሚባለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም እንደ ሌሎቹ የሃይማኖት ድርጅቶች ሁሉ የቆየ ይዘታዋን አጥታ ድጋፍን ከሌሎች ትጠይቅ የሚል ይመስላል። እስቲ ከማን ትጠይቅ? ከሳውዲ ዓረብያ ነውን? ከቫቲካን ወይንስ ከዓለም ሱተራን ድርጅቶች? ይህ ሁሉ እንዳይሆንማ ጥንታዊቷና ኢትዮጵያዊቷ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ... ችግር ቢደርስባት አቤት የምትለው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ነው። [መምህር ኪዳነ ማርያም ጌታህ የሐሰት ምሥክርነት ለቋሚ ምሥክርነት የተሠጠ መልስ አዲስ አበባ 1994 ገጽ 101]

ቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው የሠበካ ጉባዔን አቋቋሙ። በደብዳቤያቸው እንደገለጹለት ለዚያም መንግሥት የጻፉት ደብዳቤ ማስጠንቀቂያም ትንቢትም ነበር። ይች ቤተ ክርስቲያን ለርዳታ ወደ ማን ዕጇን ትዘረጋለች? ወደ ቫቲካን ወደ መካ? ወደ አሜሪካ ወዴት? ወደ ሕዝቧ ወደ ልጆቿ ብቻ ነው። ይህ ደግሞ ለዚያ መንግሥት ጥሩ እንደማይሆንለት ተንብየውለታል። ያም መንግሥት እንደ ዓላውያን መንግሥታት እግዚአብሔር የሰም ባይ ስለነበር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን አሠረ አንገላታ በመጨረሻም ገደላቸው። መንግሥቴን ያናውጣሉ ያስገለብጣሉ ሕዝብ ያነሣሣሉ ብሎ በመፍራት እንጂ ምንስ ወንጀል ሠሩና!

እኒህ አባት ዕጅ እግራቸው በእግር ብረት ታሥሮ ከዓርባ አምስት ቀን ዋሻይ ምግብ ወደ አፋቸው ሳይቀርብ ያሳሰሩና የቆዩ ቅዱስ አባት ነበሩ። አብረዋቸው ቁእሥር ቤቱ ውስጥ ከነበሩትና ከሞት ተርፈው ከተፈቱ ሰዎች መካከል ሁለቱ አበው ካህናትና አንድ ምዕመን ስለ እሥር ቤቱ ሕይወት መጽሐፍ ጽፈዋል። አንደኛው ጸሓፊ አቶ አበራ ጀንበሬ የአሥር ቤቱ አበባ በሚል ርእስ ሲጽፉ ሁለተኛው ጸሓፊ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ የቋሚ ምሥክርነት በሚል ርእስና ሦስተኛው ጸሓፊ ደግሞ ከቡር ንቡረዕድ ኤርምያስ ክበደ ኢትዮጵያ የወለሙ መፋረጃ በሚል ርእስ ጽፈዋል።

እኒህ ሦስቱ ጸሓፍያን ስለ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በጽሑፋቸው ሲዘክሩ ከቡር እቶ አበራ ጀንበሬ የቅዱሰነታቸውን ተጋድሎ እጅግ በግሩም ድንቅ ሁኔታ ታምራዊነቱንና በእምነት ዓይን ያዩትንና የተመለከቱትን ተገርመውና ተደንቀው ጽፈዋል።

ነገር ግን ሌሎቹ ካህናቱ ግን እንደ አቶ አበራ ጀንበሬ አምልተውና እጉልተው አልጻፉላቸውም። እንዲያውም ደካማና ፈዛዛ አድርገው በቅዱስነታቸው ላይ ጥላቻ ያለበት ቃል አሥፍረዋል። ምሳሌ ልጥቀስ። ኢትዮጵያ የዓለሙ መፋረጃ ከገጽ 246-258 የሠፈረውን ማንበብ ነው። ከዚህ ውስጥ ምግብ ለዓርባ አምስት ቀን ሳይመገቡ መቆየታቸው ለእኔ የሚታየኝና የሚሰማኝ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አባት ገድል ለቤተ ክርስቲያኗ ክብር እንደሆነ እንጂ ስእሳቸው የሰማዕትነት መግለጫ ብቻ አድርጌ አልወሰድሁትም። ይህን ድንቅ ታምር ሥራን አሳሠፈሩትም። እንዲያውም ቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ንቡረዕድ አድርገው አሾሟቸው ከዚያ ደግሞ የቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጅ አድርገው ካጠገባቸው አስቀመጧቸው እየተባለ የሚነገረውን በሁለቱ መካከል ያለውን የፍቅር ትስስር አባትና ልጅነት ስሰማ ኖሬ መጽሐፋቸውን ሳነብ ግን ወዳጅ ሳይሆኑ የሚጣሉ ከዚያም አልፎ ተርፎ ከእሥር ቤት እንኳ ያስ እነሱ ፈቃድ ቦታ መታሠሪያ አጥተው ተቸግረው እንደነበር ከቡር ንቡረዕድን ያስደነቃቸው እኔንም የበለጠ አስገርሞኛል። ካህናቱ ካህናቱ እንዲህ ነው ምስክርነቱ! እንድል አድርጎኛል። ለካስ የካህናቱ ምክር በጌታ ኢየሱስ መዋዕለ ዘመን አላከተመችም አሁንም ሕያው ናት። አልሁ።

ሦስተኛው ጸሓፊ ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ደግሞ የቋሚ ምሥክርነት የሚለውን መጽሐፍ ያዘጋጁት የቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን የሕይወት ታሪክ ለመካድና ለማዋረድ ሆን ተብሎ እንደተጻፈ በግልጽ ያሳያል። ድርሰቱ የግላቸው ነፃ አስተሳሰባቸው ነው። ነገር ግን እሳቸው ሊቀጳጳስ ከዚያም ፓትርያርክ ሆነው ሳለ እሳቸው በሥራቸው የደብር አለቃ እንጂ በሥልጣን እንኳ የማይገናኙ አለቃና ምንዝር እንዴት አድርገው ቢጠሏቸውና ቂም ያዥ ቢሆኑ ነው? ሞተው የወቀሷቸው ያሰኛል። በቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ሞትም ቀልደዋል። ይህ ስኔ ለምዕመኑ የሚሠጠኝ ግንዛቤ ሌላውን በሆዳችሁ ቂም በቀል አይደር እያሉ የሚያስተምሩ አባት እንዴት ይህን ሁሉ ጥላቻ ለመግለጽ መጽሐፍ ለመድረስ ታቅቱ? የሚለው ያለደንቀኛል። ለካስ ልብለ ተክህኖውና አስኬማው እንጂ እሳቸውም እንደሌላው ሰው ናቸው አሰኝቶኛል። ለምን እንዲህ ዓይነት ልበ ደንዳና የሆኑ ሰዎች በቆብ ሜና ሥር ይጠለላሉ?

ይሁንና መጽሐፉን በመድረሳቸው ስለ እሳቸው የማናውቀውንና ያልሰማነውን ገድል በራሳቸው ላይ አጻፉ አስነበቡ። ስዘህም ዋና ማስረጃ ሆኖ የቀረበው ስዚሁ ለጻፉት *የቋሚ ምሥክርንት መቃወሚያ* መምህር ኪዳነ ማርያም ጌታነህ የጻፉት *መጽሐፍ የሐሰት ምሥክርንት ለቋሚ ምሥክርንት የተሠጠ መልስን* ማንበብ ነው። ብፁዕ አቡነ መልከ ጼዴቅ ወደ ቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ መቃብር የወረወሯት ድንጋይ ጉና ጉና መሃል ራሳቸው ላይ አረፈች። ይህን ለማለት ያነሳሳኝ ብፁዕ አቡነ መልከጼዴቅ በመዋዕለ ሕይወታቸው እያሉ ከተቀበሉት ሥልጣነ ክህነት ያውም ጵጵስና በውግዘት መሻራቸውን ሳነብ ነው። በቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ላይ ስጻፉት ድርሰት ወይንም ገድል ሽልማት ይሆን? ብዬ አሰብሁ። በዚህ ጉዳይ የእግዚአብሔር ዕጅ ሳይኖርበት ይቀራልን? እሺ በጎ ታዲያ በሳቸው ላይ የደረሰውስ እሺ ይሁን በሥራቸው ነው እንበል ስምን እንደሳቸው በሌሎችስ ላይ? ለዚህ መልስ እንዲሆን የተገኘው «ለኃጥዓን የወረደ ስጻድቃን ይተርፋል» የሚባለው በሥራ ተተርጉሞ ነው ሆነ። ይህስ የሰው ሥራ ወይንስ የሚጠሉት የዚያ የአዲስ እበባው ቅዱስ ሲኖዶስ ከእግዚአብሔር ጋር ተመሳጥሮ የፈፀመው የደባ ውስጠ ምሥጢር? እንደዚያ የመሰለ ትርጉም ስስሚሰጠው ያንኑ ልበል ብዬ ነው። ይህን ሳስበው በክርስትና ሕይወቴ በጣም ይገርመኛል ያስደንቀኛል።

ከዚህ በኋላ በግሌ የተሰማኝን ኃሳብ ልግለጽ። በካህናቱ በኩል የቀረበው ጽሑፍ አመስጋኝ ሳይሆን አማሳኝ ነው። የፈለጉትን የመሰላቸውንና የሚያውቁትን መጻሕፍቱ እንዲናገሩላቸው የፈለጉትን መልእክት አስይዘው በትነዋቸዋል። እኛም ዘንድ ደርሰው እነሆ መልእክቱን እነበብነው። ተረዳነው። ግንዛቤ ደግሞ የጸሓፊው ብቻ ሳይሆን የአንባቢም ድርሻ ነው። ሰላምን ፍቅርን ይቅርታን ከሚዘሩ የወንጌል ገበሬዎች ምርት ምርቱን ስናይ ገለባውና እብቁ በዓይናችን ውስጥ ተሞጀረ። ለዚህ ደግሞ ብቻዬን አይደለሁም። ብዙ ከኔ ጋር የሚስማሙ አሉ። ካነበብሁት እንኳ ዋል አደር ብሏል። የጸሓፊነት መብታቸውን ለመጠበቅ ብዬ ለመሳነጥ ስላልፈስግሁ ነው። ያስ ባይሆን የአበው አባባልም ያስጠነቅቀኛል። እሱም «ወልደው ሳያበቁ፡ በሰው ልጅ አይስቁ።» አለና ነው። ሆኖም እንዲህ አጋጣሚው ሲገኝ «ትኩስ ሬሣ የቆየውን ይዞ ይነሣ» ይባል የስ? አጋጣሚ ሆነና የምጽፍበት ርእስ መርቶ መርቶ ከዚህ ስላደረሰኝ እንደምን እደራችሁና ዋላችሁ ብዬ ስግለፍ ነው እንጂ አስቤበትና ተዘጋጅቼ ብመጣ ኖሮ ያደፈውን ካባ አጥቤና ጨምቄ አስጥቼው አልፍ ነበር። ይሁን እንጂ እኔም ራሴን «ከነገረኛ ጋር ስንቅ አይደባልቁም» ላሰኘውና ላስብለው አልሻም።

ይሁንና እንደ ቤተ ክርስቲያኗ ልጅነቴና አባልነቴ ስመለከተው እኒህ ቅዱስና ሰማዕት አባት የኖሩትም ስቤተ ክርስቲያኗ ነው። የሞቱትም ለቤተ ክርስቲያኗ ነው። ለእኒህ ታላቅ አባት ያዩትንና የሚያውቁትን ግሩም ድንቅ ሥራ እንዴት ሳይጽፉት ቀሩ? የሚል ጥያቄ በአእምሮዬ ይጉላላ ነበር። ምክንያቱም አቶ አበራ ጀንበሬ ከጻፉት በላይ የሚጽፉ መስሎኝ ስለነበር ነው። ስካስ እነሱ የሚያውቁት ሌላው የማያውቀው የተስየ ውስጠ ምሥጢረ ካህናት ከዲቁና እስከ ቅስና ከዚያም ከቁምስና እስከ ጵጵስና የቆየ እብሮ የኖረ ቂም በቀል ኖሯል። ወይንም እነሱ የሚያዩትን የማናይ ኖረናል። አሁን ግን በግንዛቤ ብንለያይም ቅሉ የሚያውቁትን አወቅንላቸው ወይንም አወቅንባቸው። እኔ ደግሞ የእኒህ ታላቅ አባት መከራን በገዛ ምድራቸው የተቀበሉ ሰማዕት ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስን በማይበት ዓይን ነው የማያቸው። ተጋድሏቸው ለኢትዮጵያ እርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታምርና ክብር አድርገን የምንቆጥረው ብዙ ነንና ነው። እንግዲያውስ እኔም ስእኒህ ታላቅ ቅዱስ ሰማዕት አባት ያየሁትንና ያነበብሁትን የማውቅላቸውን ድንቅ ሥራ ከዚህ ላይ ላስፍር።

1. ስአንድ ሺህ ስድስት መቶ ዓመት በግብፃውያን ተነጥቆ የኖረውና የቆየው የክህነት ማዕርግ በቤተ ክርስቲያኗ ታሪክ ውስጥ ስመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ምድር በብፁዓን አባቶች ኢትዮጵያውያን ፓትርያርክነት ማዕርግ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ተሠጠ።

2 እኒህ ቅዱስ አባት ሚመተ ፕትርክናው ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ምድር ሲሠጥ በተቀቡበት ዕለት በቅድሚያ በደብር እስቅነትና ሙሉ ኃላፊነት ያገለገሉበት የመንበረ ፀባያት ቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓቱ በሚከናወንበት ጊዜ ቤተ ክርስቲያኑ በቀስተ ደመና ተከቦ ነበር። ይህን ዓይቻስሁ የዓይንም ምሥክር ነኝ። ድንቅ ነገር ነው።

3 በኢጵቤልዩ ቤተ መንግሥት በደርግ ታሥረው በነበረበት ጊዜ ካሉበት ክፍል በስምም ሆነ በመልክ የማያውቁት ሰው ጠርቶ ከታሠሩበት ክፍል ያን ሁሉ

4 ወታደር አልፈው እንዲሄዱ ሆነዋል። ከዚያም ካሠሩት ጎፋ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ደርሰው ተገኝተዋል። ይህንም ራሳቸው የተናገሩትና በልዩ ልዩ መጽሔቶችም ተገልጧል። ይህንንም ክቡር ንቡረ ዕድ ኤርምያስ ከበደ በመጽሐፋቸው አስፍረውታል። ሆኖም የሠጡት ትርጉም ወደ ከፋ ቦታ እንዲዛወሩ እግዚአብሔር ያደረገው ምክንያት ነው ብለውታል። ይሁን እንጂ ታምር መሠራቱን ግን ገልፀውታል።

5 ከታላቁ ቤተ መንግሥት ክብዙ ታላላቅ ኢትዮጵውያን ጋር በታሠሩበት ወቅት ለዓርባ አምስት ቀን እህል ሳይቀምሱ መቆየት ግሩም ዕፁብ ድንቅ ታምር ነው። ይህንን አቶ አበራ ጀንበሬ በዓይን ምሥክርነት የአሥር ቤቱ አበባ በተሰኘው መጽሐፋቸው በሚገባ ገልፀውታል።

6 የቤተ ክርስቲያኗ ሀብትና ንብረት ከመዘረፉና ከመመዝበሩ በፊት አስቀድመው በምዕመናን እንድትረዳ የሠበካ ጉባዔን በአዋጅ ማቋቋም ለቤተ ክርስቲያኗ ምዕመናን በሃይማኖት ዓይን የሚያዩት ግሩም ዕፁብ ድንቅ ታምር ሥራ ነው።

7. እኒህ ታላቅ ሰማዕት አባት ከአሥፍ ቤት ተወስደው ካንድ አልባሌ ቦታ በገመድ ታንቀው ተገድለው በመዝሙሮ ክበባቸው አጥር ጥግ ተጥለው ነበር። ነገር ግን ከዚያ ከወደቁበት አልባሌ ቦታ እጽማቸው ተነሥቶ እጅግ ቁጥሩ የበዛ ሕዝብና የሌሎም አብያተ ክርስቲያናት ፓትርያርክና ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት በታላቅ ድምቀቱና ክብር ከአሠሩት ዜቱ ክርስቲያን ውስጥ በክብር አርፏል። በዚሁ ቀንም ቅዱስ ሲኖዶሱ የሰማዕትነትን ስምና ክብር ሠጥቷቸዋል።

በእሁኑ ሰዓት ደግሞ በስማቸው ቤተ መዘክር ተሠርቶ ሐውልት ቆሞላቸው ይገኛል። ነገ ከነገ ወዲያ

ደግሞ በስማቸው ቤተ ክርስቲያንይታነጽላቸዋል። ቅ/ቤት ብስማቸው ይሠየምላቸዋል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛና ታላቅ ስማዕት ናቸው። ለቤተ ክርስቲያኗም ታላቅ ክብር ናቸው። የሚገርመው ግን ትናንት ፎቶግራፋቸው ሳይቀር ከግድግዳና ከመጽሐፍ ላይ እየተላጠ የተነሣውን ያህል ዛሬ እነሆ በአደባባይ ላይ ሐውልታቸው ቆሞ ይታያል።

8. ሌላው አስገራሚው ነገር ደግሞ የአሁኑን ፓትርያርክ የጵጵስና ማዕርግ ሲሠጧቸው ጳውሎስ ብለው ሠየሟቸው። እኒህ የመንፈስ ቅዱስ ልጃቸው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስም እውነተኛ የመንበራቸው ወራሽ መሆናቸው እንደ እንድ ታምር የሚቆጠር ዕፁብ ድንቅ ነው። ይህም በመሆኑ በመዋዕለ ዘመናቸው ሊያሠሩት ይመኙት የነበረውን ጅምር ሥራና ዕቅድ ሁሉ እነሆ እየፈፀሙ ናቸው። ጳውሎስም ሲሏቸው የታያቸው በመንፈስ የተገለፀላቸው ኖሮ እነሆ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ፕሬዚዳንት ሆኑ። ይህንም ሥራ በእምነትና በመንፈስ የሚመለከቱት ነው። በፖለቲካው ዓይን ብቻ የማይታይ ነው። ፖለቲካው የእምነቱን ኃይል ይጋርዳል።

9. እነሆ የእኒህ ቅዱስ አባትና ሰማዕት ሥራ ሁሉ በዓይነ እምነት ስንመለከተው አሁን የመንፈስ ቅዱስ መሆኑን የምንረዳው በአሁኑ ሰዓት ያሉት ሊቃነ ጳጳሳት ቀላውስትና ዲያቆናት ሥርወ ሥልጣን ከእነዚሁ ቅዱስ አባት የመነጨና የተሠራጨ መሆኑ ራሱ እጅግ ያስደንቃል። ይህን ሁሉ በእምነት ዓይን ሲመለከቱት እምነት ያጠናክራል። ቤተ ክርስቲያናችንንም ያስደንቃል። ክብሯንም ይጨምራል።

10. እንዲሁም ዛሬ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቀላውስትና ዲያቆናት ደሞዝ ከፍተኛ ሆኗል። የምዕመናንም ተሳትፎ እጅግ ጎልብቷል።

ይሁንና በገጠር ያሉ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ኑሮ ግን ገና እንደቀጨጨ ነው። በተለይም የአብነት ትምህርት ቤቶች እጅግ ተዳክመዋል። ይህ በውጭ የሚገኘው ሕዝበ ክርስቲያን ከእናት ቤተ ክርስቲያኑ ጋር አንድ ሆኖ ቢሠራ ኖሮ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መላ አፍሪቃንም አዳርሳ በነበር። የሰው ልጅ አፍ መፍቻ የሆነውን የግዕዝ ቋንቋም በተሰይ ለአፍሪቃውያን የስማቸው መጠሪያና መጻፊያ እንዲሆን ባደረግችና ባዳረሰች በነበር። ነገር ግን ለመልካም ነገር ሁሉ መሰናክሉ ብዙ ነውና ቤተ ክርስቲያኗን በፖለቲካው ካባ አሸፋፍነው ማስፈራሪያ አደረጓት።

እንደ ቀደሙ አባቶች ቢሆን ነገሥታትን ቀብተው ቃለ መሐላ አስፈጽመው ያነገሥዋቸው ስለነበር ይህን አትሥራ ይህን ተው የማለቱ ሥልጣኑም ኃይሉም ነበራቸው። ዛሬ ከደርግ ጀምሮ ቤተ ክርስቲያን ቀብታ ማንገሥዋን ተቀምታ ተቀምጣለች። ታዲያ በሌላት መሣሪያ እንዴት ትዋጋ? እንዴትስ ታድርግ? ካህናቱም ምዕመናኑም የቤተ ክርስቲያኗ ክብር ይመለስ ብለው አልተጉም። ነገሥታት ቀብተው እንዲያነግሡ ጳሳብ እንኳን አልሠጡም። ያማ እንዳይሆን ደግሞ የመንገሡን ድርሻ ሁሉም በተራ ለማግኘት ተሠልፎ የሚጠባበቀውን ፖለቲከኛ ማስቀየም ሊመጣ ነው። የፖለቲከኛውንና የድርጅቱን ብዛት ስንመለከት እንኳን ባሉት ሰዎች እድሜ ሊደርስ ቀርቶ ሰባት ትውልድ ላይ እንኳ አይደርስም። ስሁሉም ሥልጣን ይዳረስ ቢባል እንኳን ወርና ዓመት ሰዓትና ቀን እንኳ አይበቃም።

ታዲያ ምን የዕጅ ማስገቢያ ቤተ ክርስቲያኗ አላት? የሥልጣን ርክክብና ሽግግር ከነበረው ሕግና ሥርዓት ወጥቶ ባለበትና ሥልጣን በጉልበት ተወስዶ ታውጆ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ተፋተዋል ተብሎ በአዋጅ የጸደቀውን ጉዳይ ቤተ ክርስቲያን በሌላት ቀትር ርግማን ውግዘት እላደረገችም ብሎ ማብጠልጠል ለመሆኑ ትክክል ነውን? አድርጊስ ብሎ መምከር ራስ ወዳድነት አይደለምን? አሜሪካ ሆኖ ስለ ኢትዮጵያ መናገርና መተቸት ዱባና ቅል አበቃቀላቸው እየቅል መሆኑን ያለመረዳት ነው ያሰኛል። ወይንም በሞኝ ዕጅ የእባብ ጉድጓድ ይለኩበት ሲሆን ነው። ይህን የመሰለውን ሥጋዊ አስተዳደርማ እናንተ የነበረውንና ለብዙ ዕልፍ ዓመታት ጸንቶ የኖረውን የመንግሥት ሥርዓት በኀብረት ንደን ያመጣነውና ያፈራነው ስለሆነ ራሳችን እንመገበው እንጂ ሥልጣኗን ማዕርግ ሠጭነቷን ከቀማን በኋላ በሌላት ሥልጣን መንግሥት አደላድይ ብሎ መውቀሱ ሃይማኖታዊም ሰብአዊም

አስተሳሰብ አይደለም። ለቤተ ክርስቲያኗ ቃል ግቡላትና ወደ ቅድመ ሥልጣንሽ እንመልስሻለን በሉ ካህናቱም በጉዳዩ ይተባበሯችሁ። ያለበለዚያ ግን ነፃ አገልግሎት ከማይሰጥበት አገር ተቀምጦ ነፃ እገልግሎት አልተሠጠም ማለት ትክክለኛ አባባል ነው ማለት ይከብዳል።

እንግዲህ እንዲያው ለፖለቲከኞች የማይሆነውን ይሆናል ብሎ መናገር ይቀል ይሆን እንደሁ እንጂ ለቤተ ክርስቲያን ግን አዎ አዎ አይደለም አይደለም ነው አመክሮዋና አስቡላት። ከመንገድ የተገኘውን ድንጋይ ብቻ እያነሡ መወርወር የሚወድቅበትን ያለመመልከት በሰው ራስ ላይ ያርፍና ሰው ይጎዳልንን ከውርወራው ጋር አብሮ ማሰብ ነው። እስካሁን የፈለጓትን አሞራ ዥግራ ናት ብሎ መብላት ስለሆነ የፖለቲካው ጥበብ በዚያ አልተባበርሺም ብሎ ቤተ ክርስቲያኗን መውቀሱና ማዋረዱ ራሱ በቅድሚያ የሚሠሩትን ያለማወቅ ነው። በሃይማኖት ዘንድ በቤተ ክርስቲያን ዘንድ ኃጢዓት የሚባለው እኮ በፖለቲከኞች ዘንድ ጽድቅ ነው። የፖለቲካ ሥራ ከሐሰት የጸዳ አይደለም። ታዲያ በሐሰት አትመስከር ብላ ከምታስተምር ቤተ ክርስቲያን ጋር እንዴት የመዝገበ ቃላቱ ትርጉም አንድ ሊሆን ይችላል። ቤተ ክርስቲያን ስትጸልይ ከጻድቃን ይልቅ ስኃጥዓን ስለሆነ የጸሎቱ ተጠቃሚዎች እነማን እንደሚሆኑና መሆናችሁን ግን ልትገነዘቡት ይገባል እላለሁ።

ይልቁንስ ከዚህ ላይ በአሜሪካ ያሉት አባቶች ለብቻቸው ጎጆ መውጣቱን ርግፍ አድርገው ትተው ወደ አንድነቱ ወደ ሰላመና ፍቅሩ ቢመጡ ስንት ታምር በተሠራ በነበር። ነገር ግን በገዳመ ቆሮንቶሱ የፖለቲካ አሳሳቾች ሰንሰለት ታሥረው ከተራራው ላይ ራሳቸውን ወርውረው መንግሥትና ግዛት የሚያሰጥ ሥራ እየፈፀሙ ነው። በገዳም የነበረ ሰው ከገዳም ወጥቶ ምን የሚያሠራ ነገር ነበር? ብፁዓን አባቶች ለዚህ ሕዝበ ክርስቲያንና አገር ስትሉ አሁንም ልዩነት የመናፍቃን ሥራ ነውና እባካችሁ ርግፍ አድርጋችሁ ተዉት። ቤተ ክርስቲያናችንን እንገንባ የአብነት ት/ቤቶችን እናድስ። ይህን ብታደርጉ ሕዝብም የቤተ ክርስቲያኗም ታሪክ ሲያወድሳችሁ ይኖራል። ይህን ባታደርጉ ግን ትውልድና ዘመን ሲያዝንባችሁና ሲወቅሳችሁ ይኖራል። የእግዚአብሔርን ቤት በሁከትና በነውጥ ትመሩታላችሁን? እግዚአብሔር አይወደውም። ወደ ማኅበራዊ ኑሮውና ጸሎቱ ተመለሱ። እኛንም ደስ ይበለን። በቂም በቀልና በጥላቻ የእግዚአብሔር ቤት አይገነባም። እኛንም ያለንበትን ዘመንና ጊዜ እንደ ኢዮብ አታስረግሙን።

ስለዚህ ምዕመናን ሆይ! አሁን ምን እየሠራን ነው? ቤተ ክርስቲያናችንም በምን ሁኔታ ላይ ትገኛለች? ቤተ ክርስቲያኒቱ እጅግ በጣም ከፍተኛ የሆነ የውስጥ ችግር አልባት። ከዚያ ውጭ ደግሞ ያለውን ሁኔታ እንደምናየውና እንደምንሰማው ያፕሮቴስታንቱ ዓለም በጥንታዊነታችን፥ በቀዳሚነታችን፥ በጠንካራነታችንና በትውፊታችን ላይ ሁሉ ከፍተኛ ዘመቻ በተከፈተም በኛዎቹ፥ በአዲሶች አማንያን እያንገላቱን ነው። እነሱም ያለውን ሁኔታ ግምት ውስጥ በማስገባት ከፍተኛ መፍጨርጨር እያደረጉ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላት ቤተ ክርስቲያን ትኖር ይሆን?

በጣም አድርጎ ከሁሉም በላይ የሚያስገርመውና የሚያስደንቀው፥ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በጻድቃኑ፥ በሰማዕታቱ፥ በመላእክቱ፥ በነቢያቱና በሐዋርያቱ አክብሮቷ ይነቅፍታል። ሰኢየሱስ ጀግኖችና አርበኞች ከብር መሥጠት ያስወቅሳልን? ፕሮቴስታንቱ ትናት የተፈለፈሉ ከመሆናቸውም በላይ እንደ ስማቸው ከነበረችውና አሁንም ካለችው አውሮጳዊቷ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ኮብልለው፥ አዲስ ሕገ ቤተ ክርስቲያን አውጥተው የኢየሱስ አርበኞች ነን ብለው ከወዳጆቹ ለይተውት እሱንም ብቻ ማምለክ ላይሆን በሱሙ የሰውን ልጅ ይሸጡበታል። ይነግዱበታል። ያታልሉበታል። ነፍስ ያጠፉበታል፥ ሰውን የበታችና የበላይ ያደርጉበታል። መጣቱን ያታልሉበታል።

በተለይም በአፍሪቃውያን ላይ የፈፀሙት በደል እነሆ ዛሬ በዓይናችን የምናየው፥ በጆሯችን የምንሰማው፥ ዓቢይ በደል ነው። ይህን ሁሉ ግፍ ላይቀብሩ፥ ዛሬ የራሳችንን ልጆች መልምለውና አሠልጥነው የኛኑ ቤት በኛው ሰዎች ዕጅ ያስፈርሱታል። ከዚህ ወዲያ የግፍ ግፍ ፈጽሞ የለም። ምንስ እስከምንሆን ነው ቁሟ ብለን የምንመስከተው? የቤተ ክርስቲያናችንን ማንቃ ሠብረው ስርቆቱን ትተው፥ በዕጅ አዙር ማዘረፉን እንደ ኋላ ቀርነት ሥራ ተመልከተውት፥ በገሀድ ከቤተ መቅደስ ገብተው መጠላዕታችንን እስከሚገፉት ድረስ ነውን የምንጠብቀው? ቢያንስ ቢያንስ በራችንን በርግደው ገብተው፥ ያሉትን ንዋየ ቅድሳታችንን እንዳይሠብሩት ቢያንስ ቢያንስ ከዚህ ምን ታደርጋላችሁ? ማለት እንኳን የለብንምን? «ሃይማኖት የግል አገር የጋራ ነው።» ማለት እኮ መከባበር ማለት እንጂ እንዲህ መሥመሩን የሳተ ዘለፋና ፉከራ ይደረግባችሁ ማለት አይደለም። አሁንኮ ከየቤተ ክርስቲያኑ ያሉትን መጻሕፍት አቃጥሉ ብለውኮ ነው ያወጁት። የተቃጠሉና የተዘረፉ አብያተ ክርስቲያናትና እቃ ቤቶች መኖራቸውን አታውቁ ይሆን? ከብዙ

የጥቂቶችን የስም ዝርዝር እነሆ! የጥንቷ የአንሻ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን፥ የደብረ ፍሥሐ ሽንኩርት ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን፥ የደብረ ጽዮን ስምና ማርያም ቤተ ክርስቲያን፥የደውስና አማኑኤል ገዳም፥ የቅድስት መልተ ጴጥሮስ ገዳም፥ የመረኢሉ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን፥ እንኮበር የደረፎ ቅድስት ማርያም እቃ ቤት መዝቱ ... [ይግዛኝ ለክርስቶስ በእሱነ ቱውስመስ 1999 ገጽ 91] ፱ይህ ሁሉ በደል በቤተ ክርስቲያን ላይ እየተፈፀመ ቤተ ክርስቲያኗን በላም መንግት ከታመሰውና ክስርቆቱ እጅግ የከፋ ተግባር ነው። ይሁንና በቤተ ክርስቲያኗ ላይ በደል በሚፈጽሙት ክፍሎች ላይ አበው በምሳሊያቸው እንደሚመክሩን እንዲህ ብለዋል። «ጅብ ከሚበላው በልቶ ከሸው ተቀደስ።»

ምዕመናን ሆይ! ዛሬ በራሳችን ፈቃድ ቤተ ክርስቲያናችንን ከሚመጣው መክራ ሁሉ ልመታደግ በሰዉክ ጉጣጌ ተጠናክረን አንድ ድምፅ ሆንናል። ይህም ሕገ ቤተ ክርስቲያንን እፀሠራን ሃይማኖታችንን እያስፋፉን እንኖሬን። ከሥራ ብዛት ይሁን ከይሲኝታ እኛ ኢትዮጵያውያን ምክንያተ ብዙዎች ነንና እጅግ ከፍተኛ አደራና ኃላፊነት ያለበትን ሥራ ችላ ብለነው እንታያለን። ከሁሉም በፊት ቤታችንን የሚያፈሰውን ጣራ በመከደን፥ ያዘመመውን ግድግዳ በማቅናት፥ የፈራረሰውን አጥር በማጥበቅ እንክብካቤ እናድርግ። ይህም ማለት ሁላችንም እንደምንገነዘበው የቤተ ክርስቲያናችን ውሳጣዊ አስተዳደር በአንድ መሥመር፥ በአንድ አስተሳሰብ አንዲሄድ ምንም ጥረት አላደረግንም አላለሁ። የልዩነቱን መንገድ ዘግተን እንድ መውጪያ አንድ መግቢያ ማድረግ የምንችለው እኛው ምዕመናንና የሠበካ ጉባዔ መሪዎች ነን። ይህም ሲባል ልዩነት ከተፈጠረበት ቦታ የሰላም ዘብ በመቆም ነው። ልባቶቻን በአንድነት ብንጠይቃቸውና ብንለምናቸው እምቢ የሚሉን አይመስለም። በሚገባ ያዳምጡናል። ይሰሙናል። አባቶችኮ ያሁኑን አያድርገው እንጂ መናንይንና ሕይወታቸውን እንዳሰ ስእግዚአብሔር መንግሥት ጸንደረባ ያደረጉ ነበሩ። ታይቶ የሚጠፋውን ዓለም ሰዘሰዓለም በሚኖረው በእግዚአብሔር መንግሥት ሲሉም የለወጡ ነበሩ። ስለዚህ ይህን አስተሳሰብ ይዘው አበቶችን አደራ ብለን እናሰቸግር። ልመናችንንና ምለላችንን ከቱ አይንቁም። ችላም አይሉም። ያሰጋን ኃይል ያለንን ጥንካሬ ያውቁታል። ያለኛ እኮ አነሱ ከባሕር የወጡ ዓሣዎች ናቸው። ማዕቀብ ማድረግ እንደምንችልም በሚገባ ይገነዘባሉ።

ይሁንና እስካሁን የተሞከረው በተናጠል እንጂ በአንድነት ጉዳዩን መሥመር አላስያዝነውምና የአንድነቱ ጊዜው አሁን ነው።

ይህን ሳንሠራ ብንቀር እንደ ኃጢዓት ይቆጠርብናል። ታሪክም ይወቅሰናል። ከጽድቅ ይልቅ ኩነኔ ይጠብቀናል። ይህን አሁንኑ እናስተካክል። ከሁላችን የሚጠበቅ ዓቢይ ተግባር ነው። ይህን ባለማድረጋችን የታሪክ ጠላቶቻችን የራሳችንን ልጆች አሠልጥነውና አስታጥቀው፥ በየመደራና በየሠፈሩ እየገቡ፥ በዝግ ቤት ውስጥ ከሚፈጽሙት ደረቅ ወንጀል ሳልፈው ተርፈው፥ ቀን በቀን፥ በራዲዮ፥ በቴሌቪዥን ሁሉ ታላቅ ዘመቻ እያደረጉብን ነው። ይህን የጦር ሠራዊት ትጥቁን እናስፈታው። ለኛ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን፥ ሃይማኖታችን አገራችን፥ አገራችን ሃይማኖታችን የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው።

ይህ በእንዲህ እንዳለም ወጣቶቻችንን ከቤተ ክርስቲያናቸው ጋር እንዲውሉና እንዲያድሩ እናድርግ። በየቦታው አዲስ በመጣው ሃይማኖት ሁሉ እየገቡ እየተሰነካከሉ ነው። ወጣቶቻችንን ማጣት ማለት የአትክልት አርሻዎቻችን ያለ ፍሬ ቀሩ ማለት ነውና እጅግ ከፍተኛ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባናል። አሁን ብዙዎቹ በየቦታው ሲባዝኑ ይታያሉ። እንኳን ወላጅ ያላቸው ናቸው ብሎ ለመናገር ይቅርና ከጎብረተሰቡ ጋር ይኖራሉን ያሰኛል። ልጠነቀቅላቸውና ፈጽሞ ልንከባከባቸው ይገባል። እኛ ወላጆች ልንመክራቸውና ልንቆጣጠራቸውም እስፈላጊ ነው። ደግሞም ፈጽሞ ማድረግ ይገባናል። ያለበሰዚያ ልጆቻችንን ከአገራቸው ታሪክና ሃይማኖት ነቅለን ጣልናቸው ማለት ነው። ምንም የምናወርሳቸው፥ ጊዚያዊ ሀብት ንብረት፥ ርስት፥ ባድማ፥ ባይኖረንና ብንቀማም ቢቻል እኛው ካልቻልን ራሳቸው ከዘንዶው አፍ ፎልቅቀው የመውሰድ ኃይል ስላላቸው እነሱን ማዘጋጀት የግዴታ ግዴታችን ነው። ከዚያም ባሻገር የወላጅና የሃይማኖታዊ አደራ አለብን። ዓይተን እንዳላየን ሰምተን እንዳልሰማን መሆን ፈጽሞ አይገባንም። በዚህ ከቀጠልን የወላጅ መካን ሆን ማለት ነው።

ሌላው በስፋት የሚታየው በተሰይም በውጭ ያለነው ምዕመናን ከርስትና ለማስነሳት፥ በተክሊል ጋብቻ ሰመፈፀምና ለጸሎተ ፍትሐት ሰንል ብቻ ከቤተ ክርስቲያን ከመሄድ በስተቀር የቤተ ክርስቲያኗ ችግር ምንድን ነው? ይህ ቤተ ክርስቲያን በማን ይመራል? ሕገ ቤተ ክርስቲያንን ጠብቆ በሊቃነ ጳጳሳት ተባርኮና ተመርቆ የተቋቋመ ነውን ወይንስ እንዲሁ አገልግሎት ብቻ ስሰሚሠጥበት ዘው ብሎ ገብቶ፥ ዘው ብሎ መውጣት ነው? እንግዲህ ምዕመናን ልጆቻችንን ከርስትና እንዲነሡልን ማድረጋችን የተቀደሰ ሥራ ነው። ነገር ግን አገልግሎቷን የመፈሰጋችንን ያህል አብረንም የቤተ ክርስቲያኗ ችግር ተካፋይ የመሆን ግዴታም አለብን። እኛ

ከተባበርን፥ እኛ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ፥ እንደ አንድ ልብ መካሪ ከሆን፥ የጎደገደው ይመላል። የጎበጠው ይቀናል። በድግዋን ጥላ የተሰደደችውም ሰላም ወደ ቦታዋ ትመለሳለች። ቤተ ክርስቲያናችንም በጽኑው ትጠነክራለች። ወጣቶቻችንም ከቤተ ክርስቲያናቸውና ከወላጆቻቸው ጋር አብረው ያድጋሉ። የማንነታቸው ወራሾችና ተተኪዎችም ይሆናሉ።

ሁላችንም እንደምናውቀውና የበይ ተመልካች ሆነን ያሰንበት ብሔራዊው አንድነታችንና ማንነታችን ድሮ ጥንት በውጭ ወራሪዎች ነበር የሚፈተነውና የመናድ ሥራው የሚከናወነው፥ አሁን ግን ተለውጦ፥ መልኩንም ቀይሮ፥ በኛዎቹ በመልከም፥ በጃንቋም፥ የሥጋችን ቁራሮችና የአጥንታችን ፍላሾች በሆኑት ነው። «ኑሮ ካሉት መቃብርም ይሞቃል» እንደሚባሰው የሃይማኖት ደላላዎች ከበዙበት ዘመን ላይ ነን። አዎ! እኛ ሃይማኖትን ገዝተንም ሸጠንም አናውቅም። ያለ ውጣ ውረድ በራሱ በእግዚአብሔር ፈቃድና ቸርነት የሰው ልጅ በምድር መንቀሳቀስ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እሱን ፈልገን እንድናገኘው አድርጓል። አውቀነውም ስናመልከው ኖረናል። አሁንም አለን። ግን አሁን እርሱን ትተን ማንን እንድናመልክ ነው ገንዘብ የሚሠጠው? የሃይማኖት መለወጫ ገንዘብ ይከፈል ጀምሯል። በገንዘብ ሃይማኖቱን የለወጠ ሰውስ ምኑ ታማኝ ይሆናል? እንዲሁ በዚህን ያህል ገንዘብ ይህን ያህል ሰው ገብቷል ብሎ ከመናገር በስተቀር እንዴት አማኝ ሊሆን ይችላል? ኢትዮጵያዊ እኮ ሃይማኖቱን በገንዘብ አይሰውጥም። ራሱን የማያውቅ ካልሆነ በስተቀር እንኳን በገንዘብ በሠይፍና በካራም አይሰውጥም። አንገቱን አስቀርጠ ዓይኑን አስፈርጠ ሰሃይማኖቱ ተፋጥጠ ኖሯል። ማንነቱንም አስመስክሯል። ይሁን እንጂ አሁን ገንዘብ ይዘው አማኝ ለማደን ለተሰለፉት ሰዎች አዝናለሁ። በገንዘብ ሲገዛና ሲሰወጥ የምናውቀው የሚታረድ በግ ፍየልና በሬ እንጂ ሰውስ ሰምተንም አናውቅ። አይመጣ ጉድስ አለ? ተራው ሰብከት ባዶ እየሆነ ሚዛን አልደፋ ሲል በጥሬ ገንዘብ ገቡበት። ያን ገንዘብ የሠጠ ጌታ የሚነሣበት ረጅምም ዕጅ እንዳሰው ያሰመገንዘብ ነው። አማኝ ከሚገዙበት ትምህርት የሚቀስሙበት ት/ቤት አይሠሩለትምን? ቢሆን እንኳ እነሱ እኮ የሚገዙት ሥጋውን እንጂ ነፍሱን እይሆንም።

የሚገርመው ደግሞ በክርስትና ስም ጸንጌው ነው ያስቸገረው። ለምን የኛን ትተን የእነሱን እንድንይዝ ይወተውቱናል? እኛን መንግሥተ ሰማያት ሰማስገባት አዝነውልን ነውን? ይመስላችኋል? አይደለም። ያስ ቢሆን እንዲህ በዕጅ በእግራችን እየገቡ ባላስቸገሩንም በነበር። ደግነት መሥራት ቢፈልጉ ኖሮ

ወድቆ ለሚሰምነው ሰው መጠለያ ሠርተው፥ ባላቸው ገንዘብ የዕለት ምጽዋት መሥጠት ሳይሆን ሠርቶ የሚኖርበትን ድርጅት በፈጠሩለት በነበር። በእንቅርት ላይ ጆሮ ገድፍ እንዲሉ የባሰውን ከአሥር አንድ ያገኛሃትን አምጣት ትፋት ይሉታል። ምነው ታቦት አያስፈልግም ብለው ከሚለፉ ለምን ከአሥር አንዱ መዋጮዋ ትቅር ብለው አልሠበኩ? ይህምኮ የአፅት ሕግ ነው። ከአሥር አንድም ታቦቱም ከአሪት የወረስናቸው በእምነቱ የነበርንበቱ በመሆኑ ያገኘነው ነው። ትላንት ከትናንትና ወዲያ እንደናንተ ያወቅነውና የተረዳነው አይደለም። እናንተ በድብ፥ በዘንዶ፥ በጨረቃና በከዋከብት በተራራና በዛፍ ያመልኩ ከነበሩት ሰዎች ቅጥረኞች በመሆናችሁ አንጂ ማንነታችሁንማ ብትረዱ ኖሮ ይህን ባላደረጋችሁ በነበር።

እንግዲህ ከተዘረጋው መጋረጃ ውስጥ ያለውን ኢትዮጵያን ለማረድ ከተጋደመው ሃይማኖታዊ ፖለቲካዊ ካራ ውጭም ይበላው ያጣ፥ ሰውነቱ የገረጣ፥ ይህን ደህ ሕዝብ ጌቶቻችሁ በኢየሱስ ስም ይበዘብዙታል። እኛን ግን ዝክርት፥ ተዝካርና ስንበቴ ያስደግሱታል ይሉናል። ያውም የደረሰውና የተራበው መንገደኛ ሁሉ የሚበላውን ምግብ እንደ ኃጢዓትም ቆጥረውብን። የእነሱ መዋጮ ግን የሚሄደው ወደ አንድ ጎተራ ብቻ ነው። ይህን ጉድ ተመልከቱት።

አንድ ጊዜ የአክሱም ጽዮን በዓል ሲከበር በ1966 ዓ. ም. እንደ አጋጣሚ ከቦታው ተገኝቼ ነበር። በዚያን ጊዜ የትግሬ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ትምህርት ሲሠጡ ያሉትን ማውሳት ፈለግሁ። «የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከምሁራን ያልተራቆተችው በሕዝቡ ደግነትና ቤተ ክርስቲያኗም ተማሪ ቁራሽ ፍለጋ ሲመጣ ምዕመናኑ የመዘከር ግዴታ እንዳለባቸው በማስተማሯ ነው። ይህን ትምህርትም ሕዝቡ በተግባር የሚያውቀውና የለመደው በመሆኑ እንደ ብሔራዊ ግዴታው ቆጥሮት አነሆ እስካሁን የሃይማኖቱ ዓምድ የሆኑትን ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ሲያፈራበት ኖሯል። ለዚህ ዓቢይ ሥራ እንደ ምሳሌ የምጠቅሰው የጎጃምን ቤገምድርና የሰሜንን የሸዋን የወሎንና የትግሬን ሕዝብ ነው። እኔ ራሴ በዓይን ምሥክርነት ነው የምናገረው። በጎጃም ተማሪ ከበር ሲቆም ሥራ ውላ ገና ምጣድ ሳትጥድና ሳትጋግር የደረሰባት እንደሆነ ተሚ ተመልሰህ ና ገና ምጣድ እየጣድሁ ነው ትለዋለች። ተመልሶም ሲሄድ ያልተቆረሰ ትኩስ እንጀራ ትዘከረዋለች። ይህ አሠራር እነሆ ብዙ የቤተ ክርስቲያን ምሁራንና አባቶችን አስገኝቷል።» ብለዋል።

ዛሬ ይህን ብዙ ምሁራንን ያፈራውን ማኅበራዊና ሃይማኖታዊ ሥርዓት ነው የኛዎቹ ቹልችላዎች በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ያለውን ዝክርት ለመቃወም የተነሡት። የተቃውሞ ማስነሻ እንጂ ከላይ እንደ ገለጽሁት ቤተ ክርስቲያኗን ለመሸርሸር ምክንያት ማብጁያ ነው። የእውነት አስተማሪዎች ቢሆኑማ ኖሮ መጽሐፍ ቅዱስ የሚታደለው ሕዝብ፥ ለጧት ቁርስ፥ ለቀን ምሳና ለማታ ራት የሌለው መሆኑን ከማንም የበለጠ ያውቁታል። ይህን ዐተመለከተ ምን ያደረጉለት ጉዳይ አለ? ኢየሱስ እኮ የተራቡትን መግቦ፥ የታመሙትን ፈውሶ ነው ያስተማረው። በፈላ ጎጆ አዳራሽ ደሃውን ሕዝብ ሰብስቦ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አዉሳት የሞናችሁ ጨለማ ውስጥ ነው ያላችሁ። ዛሬ ለመዳን ትሻላችሁ? በኢየሱስ እመኑ ይላሉ። ኢየሱስን የማያውቁት ይመስል? ዘመኑ ዑድንና ድርጅት መፍጠር በቀላሉ በድምጽ ብልጫ ተብሎ ትላንት በአገራችን ላይ የደረሰውን እንደተገነዘብን ነገ ከነገ ወዲያ ሳይሆን ከአሁኗ ሰዓት ጀምሮ ደግሞ ቤተ ክርስቲያናችንን ለመናድ ነው። ቤተ ክርስቲያኗ ከተዳከመች የእነሱ ሚሺን ግብ መታ ማለት ነው።

ስለዚህ ኢትዮጵያውያን ሆይ! ሰው በሕይወቱ ውስጥ ለአገሩ ደኅንነት፥ ለሕዝቡ ዕድገት የማያደርግ ከሆነ ሰው በእውኑ ለምን ተፈጠረ? «ቦኑ ለክንቱ ፈጠርኮ ለሰብእ» እግዚአብሔርስ በእውኑ ሰውን ለክንቱ ፈጠረውን? ከቅድመ ልደተ ኢየሱስ ክርስቶስ ጀምራ በእግዚአብሔር እምነት ጸንታ የኖረችውን አገር ዛሬ በጦርነት ያጡትን ወረራ በሃይማኖት ስም ለማግኘት ስለሆነ ይህን ተንኮል በጋራ ልንቋቋመው ይገባል። ይህ ደግሞ የሁላችንም ብሔራዊና ሃይማኖታዊ ግዴታችን ነው። በእውኑ ለምን ዛሬ ሃይማኖት እንደ ድርጅት ተከታዮቹን በገንዘብ መግዛት አስፈለገው? ዛሬ ተበልቶ ነገ ለማይደገም ዳቦ ብለን ለዘለዓለም በልጆቻችንና በአገራችን ላይ መከራ ጥለን አንለፍ። የዛሬ ቀልድ፥ የነገ ፀፀትና የእግር እሳት መሆኑን ለአንዲት ኬክሮስ [ሴኮንድ] እንኳን ችላ ማለት የለብንም። ይህንን ግንዛቤ ውስጥ አስቀምጠን አገራችንንና ሃይማኖታችንን እንጠብቅ።

ፕሮቴስታንት ኢትዮጵያ የመጣው በመርከብና በአውሮፕላን ተጭኖ በአውሮጳውያን ነው። አውሮጳ ደግሞ የሞሶሊኒና የሂትለር ዓለም መሆኑን ፈጽሞ አንርሳ። ከኩርንችት የበለስ ፍሬ ፈጽሞ አይጠበቅም። እንዲሁም ከባሕርዛፍ ላይ የኮክ ፍሬ እንደማይለቀም ሁሉ ነው። ማስተዋሉንና አእምሮውን ይሳልብን። አገራችንን ከወረራ፥ ሃይማኖታችንን ከመከራ፥ ለማዳን ሁላችንም በአንድ ላይ

ዘብ እንቁም። ይህ የሁላችንም ሃይማኖታዊና ብሔራዊ የውዴታ ግዴታችን ነው። ይህን ባናደርግ ታሪክ ራሷን የመድገም ግዴታዋ ነውና በኤይድሱ በወላውና በሌሎችም ወረርሽኞች የምንጠፋው ጠፍተን የተረፍነውን የሰማይ ቅዳጅ በሚያህል መርከብ አሳፍረው ከፈለጉን ለስኳር ተክላ ያለቧለዚያም ለአትላንቲኩ ውቅያኖስ አሣንበሬ የተራበ መጋቢ ናቸውና ወስደው ይሠጡናል። ከዚያ በኋላ ገነት በምድርን ኢትዮጵያን ለእነሱ መኖሪያ ብቻ ያደርጓታል። እንዲያውም አንድ ማስረጃ ላቅርብ። እንዲህ ይላል። «Ethiopia is a paradise for white people» [ኢትዮጵያ ለነጮች መኖሪያ ምድረ ገነት ናት] Baron Roman Prochazka የተሰኘ ጸሓፊ *Abyssinia the Powder Barrel*, ገጽ 16 በተሰኘው መጽሐፉ ላይ ኢትዮጵያ ቀደም ተብላ የነጮች መኖሪያነት የተመደበችና የመወሰድ ተራዋን የምትጠብቅ መሆኗን ልብ ይሏል። እኛም ወይንም ዘሮቻችን ነበሩ ይባላል ወደሚለው የታሪክ ተረት ይሸጋገራሉ። ይህን እውነታ በአፍሪቃውያን አሜሪካውያን ወገኖቻችን ሕይወት የምንማረውና እየተማርን ያለነው እውነታ ነው። ለዚህ ሁሉ የግፍ አገዛዝና ቄካኔን የጀመሩት በኢየሱስ ስምና ባነገቱት መጽሐፍ ቅዱስ አማካይነት ነው።

አባቶቻችን ጠንካሮች አዋቂዎችና አስተዋዮች በመሆናቸው ሕይወታቸውን ለአገራቸውና ለሃይማኖታቸው ሠውተው እስከዚህ አድርሰዋል። ይህ ትውልድ ደግሞ ምንም ያለውን ነገር ሁሉ ቢነጠቅም ቅሉ ለመኖር ያህል አለ። ይሁን እንጂ የማንነቱ መታወቂያ፥ የዜግነቱ መለያ የሆነው መሬቱን ሳይቀር ተነጥቋል። የቀረችው ይችው ሃይማኖቱ ነበረች እርሷንም ዙሪያዋን ከበው እየበጣጠቋት ነው።

ዛሬ በኢትዮጵያ የሃይማኖት ነፃነት አለ በሚል ሽፋን ኢትዮጵያ ያልገባ የሃይማኖት ድርጅት የለም። ሥጋቴ ግን ነገ ከነገ ወዲያ የሰው መሥዋዕት የሚያቀርብ ሃይማኖት ገብቶ ልጆቻችንን እያረደ እንዳይጨርስብን ነው። በኢትዮጵያ የማይሠራና የማይፈፀም ግፍ እንደሌለ ደግሞ የምናውቀው ነው። እሱ ያመጣውን መከራ ራሱ እስከሚመልሰው ድረስ በትዕግሥት ማየትና መጠበቅ ነው የሚለው የማደናገሪያ አስተሳሰብ ከአእምሯችን ታጥቦ መውጣት አለበት። ሃይማኖት እንዲት ናት። የያዝናት የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት በሚገባ የምታጸድቅ ናት። ሃይማኖታችሁን አትለውጡ። ብትለውጡ ትገባላችሁና ወደ ድጡ ወደ ማጡ ከማንነታችሁ በምንም ዓይነት አትገላበጡ።

ይልቁንስ አሁን የመንግሥት አስተዳደር፥ የትምህርቱ ሥርዓት፥ ወደ ኢትዮጵያዊነት ይለወጥ ቢባል የተመቸ ይሆናል። ያለበለዚያ ግን ከአርቶዶክስ ተዋሕዶ ወደ ጴንጤነት መለወጥ ማለት ዕጅንና እግርን በስለት መቆራረጥ ነው። ኧረ! ለመሆኑ የሃይማኖት እጦት ነው ችግራችን? ይህማ ይህ ራሱ በደዌ ላይ ደዌ፥ በበደል ላይ በደል የቆሰለውን ገላችንን በገል መፈቅፈቅ ነው። ታዲያ ሕመሙን የሚያውቀውና የሚሰማው ባለ ቁስሉ እንጂ ለፈግፋጊውማ ጨዋታና ፌዝ ነው። እንግዲህ የደበሎው ወይንም የዳባው ማራገፍ ምንን ለማደናገር እንደሆነ እናውቀዋለን። ጀርባችንን በስለት ለመውጋት ሲፈልጉ ኋላ ኋላችንን ይሄዳሉ። ለምን ሲባል ቀዳሚ ናችሁ ለትሕትና ነው ይሉናል። ለሚያደርጉት ሁሉ ምክንያት አላቸው።

ነገር ግን ዓላማቸው የያዙትን ጨቤ ከጀርባችን ለመጨመር ነው። አሁንም ችግራችን ሃይማኖት አይደለም። ችግራችን እናንተን መልምሎ ከመካከላችን መሠንቀሩ ላይ ነው። የናንተ መኖር መንገዳችንን፥ በራችንን የተሰበረ ጠርሙስ መጣያ ማድረጉ ላይ ነው። ከዚያ በተረፈ እንኳን የናንተ ሃይማኖት ኢየሱስን ሊያስተዋውቀን ይቅርና የሚያጣላንና የሚያራርቀን ነው። ይሁንና ባጭሩ የምንለው፥ እንደ ፀሐይ የሚሞቅ፥ እንደ ሻሽ የሚያደምቅ ሃይማኖት አለን። ለለዚህ ማርን ሽጦ ምን ይገዟል ነውና ስለ ኢየሱስ ብላችሁ ተዉን። የሰላማችንን ምንጭ አታደፍርሱብን። እኛን ክውስጥ የፈጥኝ አሥራችሁ ቤታችንን በላያችን ላይ ዘግታችሁ በእላት እያቃጠላችሁብን ነው። ኢትዮጵያዊነታችን እስከ ማንነታችን ድረስ ያለምንም ቅሪት እንዲነድ እያደረጋችሁ ነው።

የምዕመናን ድርሻ ምንጊዜም የነበረና ያለም ነው። አሁን ግን ያለው የሠበካ ጉባዔ ቤተ ክርስቲያንን ለማስተዳደር በቃለ ዓዋዲ አዋጅ ቁጥር ሕጋዊ ሥልጣን ያለው ሆኖ የመክሰስና የመክሰስም መብቶች አሉት። በእኒህ ግዴታዎችም መሠረት እንደ ውስጠ ደንቡ መሠረት ከተወሰነ ዓመት አገልግሎት በኋላ በምዕመናን ምርጫ ሹመትና ሽረት ሳይሆን ያላገለገለው ያገለገለውን በመተካት ሽክም ማቃለል ነው። የሠበካ ጉባዔ አባልነት ነፃ ሃይማኖታዊ አገልግሎት እንጂ ደሞዝ የሚከፈልበትና የሚሠራበት አይደለም። ይሁን እንጂ የሠበካ ጉባዔው ቀጥሮ የሚያሠራቸው ባለሙያዎች አሉት። በኢትዮጵያ ውስጥ የሠበካ ጉባዔውን በበላይነት የሚመራው የደብሩ አስተዳዳሪ/አለቃው ሲሆን የቀረውን በምዕመናን ይያዛል። ነገር ግን በውጭ አገር ግን የሠበካ ጉባዔ አመሠራረት በቃለ ዓዋዲው መንፈስ ይሁን እንጂ የሥልጣኑን ዳር ድንበር ራሳቸው ተመራጮች ምዕመናን ብቻ ሆነው ይገኛሉ። ካህኑ ግን ደሞዝተኛ ማለት ተቀጣሪ እንጂ

ምንም ዓይነት ሥልጣን ፈጽሞ የለውም። ለሠበካው ጉባዔ ምቹ ካልሆነም የማሰናበቻ ደብዳቤ ይጻፍለታል። በቀላል ቋንቋ ይባረራል። ይህንንም እንደሚከተለው በአጭሩ እንመለከታለን።

በውጭ አገር ያሉ አብያተ ክርስቲያናት የሠበካ ጉባዔዎችና ምዕመናን ይዘትን በንመለከተው እብዛኛው ከአገሩ ውጭ የሚኖረው ሕዝብ በሦስት ምክንያቶች ከአገሩ የወጣ ነው። የመጀመሪያዎቹ አወጣጥና አመጣጥ ለከፍተኛ ትምህርት መጥተው ከዚሁ የቀሩ ናቸው። በሁለተኛና በብዛት ያለው/ከፍል ግን ከዘመነ ደርግ ጀምሮ በስደት የመጣው ነው። አሁን ደግሞ ከአምስትና ከሰባት ዓመት በፊት ደግሞ በሎተሪ የመጣውና የሚመጣው ነው። ታዲያ በእነዚህ በሦስቱ ምክንያቶች የሚመጣው ሕዝብ ቁጥሩ እየጨመረ መጥቷል። በዚያውም ላይ መባዛትም ቀጥሏል። ይሁን እንጂ ይህን በየቦታው የሚገኝ ኢትዮጵያዊ በአንድ አቅጣጫ ለመምራት የማይቻሉባቸው ምክንያቶች አሉት። ያም ሆኖ ልዩነቱን አቻችሎ ሁሉም ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል አስተዋጽኦም ያደርጋል። ክርስትና ያስነሣል። ለወላጆቹ ፍትሐት ያስፈታል ተዝካርም ያወጣል። ዓመታዊ የአባልነት ክፍያም ያደርጋል። ይህ ሁሉ ሲሆን ቤተ ክርስቲያኗ ቀድማ ደርሳ ቡራኬ የምሠጥህ እኔው ነኝ ብላ የበላይነቱን አልወሰደችም። ይህም በመሆኑ በልዩ ልዩ ምክንያት የሚገናኙና የሚተዋወቁ ግለሰቦች በመሰብሰብ ቤተ ተከራይተው ካህን ቀጥረው አገልግሎት መስጠት ይጀምራሉ።

እኒህ ሰዎች የጋራ የሆነ የፖለቲካ አመለካከት ያላቸው ወይንም ካንድ አካባቢ የመጡትን አሰባስበው የመንደር ልጆች ቤተ ክርስቲያን ያቋቁማሉ። ይህም ኢትዮጵያዊነቱንና ሃይማኖታዊውን አፈፃፀም ያስለውጠዋል። ይህም ሁኔታ አሁን ለተፈጠረው ችግር መጋቢ ነው። በዚህም ምክንያት የሠበካ ጉባዔ አባላት በሚፈጥሩት ያለመግባባት ለሁለትና ለሦስት የተከፈሉ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። በገንዘቡም ላይ ክስና ክርክር በየፍርድ ቤቱ ሲዋቀሱ ይታያሉ። ቤተ ክርስቲያኗ ከእንዲህ ዓይነቱ ዕይታ ውስጥ ሆና ትገኛለች። ይህ በእንዲህ እንዳለም አሁን በአሜሪካ የተከሠተው ሁኔታ ለካህናት ብቻ ሳይሆን ጳጳሳትም የፖለቲካ ጥገኝነት በመጠየቅ መምጣት ጀመሩ። አሁን ነገር ተበላሸ። ጳጳሳቱም ምዕመናኑም ሁሉም ስደተኛ ሲሆኑ የስደት መንግሥት ማቋቋም ተሞከረ በቤተ ክርስቲያን በኩል ተቻለ። ቤተ ክርስቲያኗ የአባብ ጉዳንድ መለኪያ ዕጅ ሆነች። በዚህም ምክንያት የአሜሪካው ሲኖዶስ ያውም «ሕጋዊው ሲኖዶስ» ተብሎ ተሠየመ። ታቦቱ ጃንጥላው ቃሚሉ ከበሮውና ጸናጽሉ ሁሉም መጡ። ጳጳሱም ባርክ ምሥራቅ ወምዕራብ

ሰሜን ወደቡብ መሥዕ ወዓዜብ ሊባ ወባሕር ብለው ባረኩ። ታቦት ወጣ መዘምራን በከበሮ አደመቁት።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ነን ግን ኢትዮጵያ ካለው ሲኖዶስ አስተዳድር ጋር ግን አይደለንም እየተባለ ከስብከተ ወንጌሉ ጋር በማሰረጊያነት መነገሩ ቀጠለ። ምዕመናኑ ታቦት ከወጣላቸው ከበሮ ከተመታላቸው ቅዳሴው ከተቀደሰላቸው ከዚያ ውጭ ያለውን ጣጣ መስማትም ማወቅም አልፈለጉ። ቢጠይቁም መልስ የሚሰጣቸው የለም። ሁሉም በተአቅቦ ውስጡን ሳያሳዩ አብያተ ክርስቲያናት በዙ ተባዙ። የደረሰ ሁሉ የሚቀድሰባቸው መስቀል ያለው ሁሉ የሚባርክባቸው ሆኑ። እናት ቤተ ክርስቲያንን በመጎናጸፊያ ጠቅለው አስቀመጧት። የጳጳሳቱም ቁጥር እያደር በረከተ። በጋራ አንድ ላይ ሆነን የሲኖዶስ መንግሥት እንመሥርት ብለው ተነሡ። ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ተሰያዩ። ከእናት ቤተ ክርስቲያንና እንደገና በአሜሪካ ልዩነት ተፈጠረ። ይህ መከር ለፀረ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጠሰ በረከት ዝናመ ምሕረት ሆነላቸው። በዚህን ጊዜ ነው የቃሚል የካህንና የከበሮ ጉዞ ወደ አሜሪካ መጉረፍ የጀመረው። በሠበካ ጉባዔ ስም የፖለቲካ ድርጅቶች መቆጣጠሩን ያዙት። ጳጳሳት ሳይቀሩ የጸሎታቸውን ቅላጼ ቀየሩ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶስ አሜሪካ መጥቷል። ይህ ነው ሕጋዊው ብለው የቀድሞውን ፓትርያርክ ከኬንያ አስመጡ። አሁን ከደረሰበት ደረጃ ደርሷል። ኤጲስ ቆጳሳት ተሹመዋል። አባል አብያተ ክርስቲያናት አይዟችሁ እየተባሉ ነው። በዚህም ምክንያት በተለይ በአሜሪካና በካናዳ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ለሦስት ተከፍላለች። የማይሠራ ነገር የለም። ቢኖር ከጸሎቱ መልስ እርስ በርስ መወነጃጀል ነው። መቼም እድሜ የማይለመንበት ዘመን ነው። ይሁንና አንደኛ የእናት አብያተ ክርስቲያናት ሁለተኛ የአሜሪካው ሲኖዶስ ሥር የሚገኙትና ሦስተኛ ከሁሉም ያልሆኑ ገለልተኞች ናቸው። በዚህ ሁኔታ ቤተ ክርስቲያኗ አንድነትና ሦስትነት አግኝታለች።

፬ . በጉብዝና ለእግዚአብሔር ልዕልና

«ኢትከልዎሙ ለሕፃናት ይምጽኡ ኀቤየ እስመ ለዘከመ እሉ ይእቲ መንግሥተ ሰማያት።» [ሕፃናትን ወደኔ ይመጡ ዘንድ ተዋቸው አትከልክሏቸው! መንግሥተ ሰማያት ለእንደነሱ ላሉት ናትና!] ማቴ. 19:14 ተብሎ የተነገረላችሁ ወጣቶች ሆይ! በየአብያተ ክርስቲያናቱ የምታበረክቱት አገልግሎት ሲታይ እውነትም ወደ እርሱ ትመጡ ዘንድ ሕፃናትን አትከልክሏቸውን ያረጋግጣል። በትንቢትም የታወቀው «አምአፈ ደቂቅ ወሕፃናት አስተዳሎከ ስብሐተ» [ከትናንሽ ልጆች አፍ ምሥጋናን አዘጋጀህ።] [መዝ. 8:2] ስለሆነም ሕፃናት ወይንም ወጣቶች አስቀድማችሁ የተመረጣችሁና ለአገልግሎቱ የተጠራችሁ መሆኑን ትንቢት ተነግሮላችኋል። ከዚህ ወዲያ ምንም ዓይነት ማረጋገጫ የለም። በእውነቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ምርጥ ዕቃ ሆኖ መገኘት እጅግ ያስደስታል። እንኳን ደስ ያላችሁ።

ወጣቶች ሆይ! ከዘወትር አገልግሎታችሁ ባሻገር ያገራችሁንም ሆነ የቤተ ክርስቲያናችሁን ኃላፊነት የወደፊት ተረካቢዎች በመሆናችሁ ከናንተ ጫንቃ ላይ ያለውና የተቀመጠው አደራ እጅግ ከፍተኛ ነው። ስለዚህም ሁላችንም እንደ ዓይናችን ብሌን እንመለከታችኋለን። የወጣት አእምሮ አዲስ ነጭ ወረቀት ነው። የጻፉበትን ሁሉ ይቀበላል ይይዛል ተብሏል። ታዲያ በልጅነት ያወቁት የተማሩት የተነገሩት ሁሉ በሽምግልና እድሜ ጊዜ አንኳን አይረሳም። ለዚህም ነው ልጆችን በወጣትነት እድሜያቸው በቁም ነገርና በሥነ ሥርዓት ማሳደግ ይገባል የሚባለው። በልጅነት ቀጥተኛውን መንገድ ከያዙ ይዘልቁበታልና ነው። በልጅነቱ የተጫመመ ዛፍ እንኳ ካደገ በኋላ ላቃናህ ቢሉት ወደ መሰበር ያዘነብላል። ስለዚህ ላንድ ወጣት የልጅነት አመክሮው መልካም ከሆነ መልካም ሰው እንደሆነና በወንዝ አጠገብ እንደተተከለች ዛፍ ፍሪያማ ይሆናል። ይህንም ምሳሌ ዳዊት በመዝሙሩ እንዲህ ብሎታል። «ወይከውን ከመ ዕፅ እንተ ትከልት ኀበ መኃዝ ማይ እንተ ትሁብ ፍሬሃ በበጊዜሃ ወቆጽላኒ ኢይትነገፍ።» [በውሀ ፈሳሾች ዳር እንደ ተተከለች ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል።] መዝ. 1:3

ዛሬ ወጣቶች ለአገራቸውና ለቤተ ክርስቲያናቸው ቀናተኞችና ተቆርቋሪዎች ናቸው። ይህ ከዳር እስከ ዳር ሁሉንም የሚያስደስት ታላቅ የምሥራች ነው። አዎ ወጣቶች የዛሬ ልጆች የነገ መሪዎች ቤተ ክርስቲያንንና አገርን ተረካቢዎች ናቸው። ዕልልታ ለወጣቶቻችን ይገባል። ይህን ካልሁ በኋላ በዕይታ የታዘብሁትን ከዚያም አልፎ ተርፎ የተፀፀትሁበትን ጉዳይ በምክር መልክ ለማቅረብ እገደዳለሁ። መቼም በምትሠሩት በምታደርጉት ሥራ ሁሉንም ያስደስታል። በተለይም የምታስሙት ጣዕመ ዜማ መዝሙር እንኳን ለሰው ቀርቶ ለእትክልቶችም ዕድገት ተፈላጊነት እንዳለው ተረጋግጧል። በነካ ዕጃችሁ ባማረውና በተዋበው አንደበታችሁ ቀጥሉ እያልሁ አበረታታለሁ። እንዲህ እንደምታሳምሩትና እንደምታስውቡት መዝሙርም የምትከሩበት የምትደምቁበትና የምትታወቁበት አንድ ታላቅ ጉዳይ አለ። እሱም የማንነታችን መለያና መታወቂያ የዓለም ጥበባት ሁሉ የተቀዱበትና የተመዘገቡበት የሰው ልጅ አፍ መፍቻነቱ የተረጋገጠለት፥ ሰውና እግዚአብሔር የተነጋገሩበት «እይቴ ሀሎከ አዳም።» [አዳም ወዴት ነህ? ዘፍ. 3:9] ተብሎ የጠየቀበት የሰው ልጆች ሁሉ አባት አዳም መመሪያ የተቀበለበትን የግዕዝን ቋንቋ አጥኑ። መዝሙራችሁም በአማርኛ ብቻ ሳይሆን ከመቋሚያውና ከጸናጽሉም ጋር ተውቦ የኖረው በግዕዙ ስለሆነ እስከ ጥንተ ይዘታው ጠብቃችሁ ዘምሩበት ተምነሽነሹበት። የኔ ምክር መዝሙራችሁን በግዕዙም ይዳብር ብቻ ሳይሆን በትንቢት የምሥጋና ማቅረቢያነቱ የተነገረለቱንም ቅኔ እንድትማሩበት ነው። «ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲስ።» [እግዚአብሔርን ዘወትር በአዲስ ምሥጋና አመሥግኑት። መዝ. 149:1] እንዲህ ተብሎ የተነገረለትና የተባለው የግዕዝ ጌጥ የሆነው ቅኔ ነው።

ግዕዝን መማርና ማወቅ ሃይማኖታዊና ብሔራዊ ግዴታም ነው። ግዕዝ ለመንፈሳዊ አገልግሎታችሁ ብቻ የሚሆን አይደለም። በአንደኛ ደረጃ የማንነታችሁ መግለጫና መታወቂያ ነው። በሁለተኛ ደግሞ ግዕዝ በከርሠ ምድር ያሉ ማዕድናትን በመሬት ላይ የበቀሉ ዕፀዋትን በውስጧ የሚተራመሱትን አራዊትንና እንስሳትን በዓየር የሚበሩ በባሕር ውስጥ የሚርመሰመሱ ፍጥረታትን በጠፈር ላይ ያሉ ከዋክብትን የጠፈር አካላትን ሰማያትን ወይንም ፕላኔቶችን በምድር ላይ የሚነፍሱ ነፋሳትንና ልዩ ልዩ ጥበባትን ምርምርን ፍልስፍናን ታሪክን ሕግን እምነትን ሁሉንም በሥርዓት አጥንቶ የያዘ ቋንቋ ነው። የአብራይስጡ የላቲኑ ወይንም የሮማይስጡ የግሪኩ ወዘተ... ቋንቋ ሁሉ የፊደል እናት ግዕዝ ነውና ማጥናትና ማወቅ አለባችሁ። በሌሎች አኅጉር የሌሉ ዕፀዋትና እንስሳት በኢትዮጵያ አሉ።

ማዕድናቱም እንደዚሁ ነው። የኢትዮጵያ ዓልማዝ ልዩና ታዋቂ እንደነበር የምንረዳው በጥንቱ ዘመን በአንደኛነት ታዋቂ የነበረው የኢትዮጵያ እንቁ በተለየ ስሙም እንቁጻዝዮን ነበር። ከጥናናነቱ የተነሣ ይህንኑ ምርጥ የከብር ድንጋይ በመጽሐፈ ኢዮብ ላይ ተወስቶ እናገኘዋለን። እሱም የጥበብ ማነፃፀሪያና ማወዳደሪያ ሆኖ ነው። እንዲህ ይላል። «የኢትዮጵያ ቆጸዝዮን አይተካከላትም» [ኢዮብ፣ 28:19] ስለዚህ ግዕዝ ያልሞዘገበው ጥበብ ፍልስፍና ታሪክ መድኃኒት ቅመራ ምሕንድስና የለም። የዓለም ጥበብ ምንጭ ነው።

ነገር ግን በዚህ መታወቅ ቀርቶ በተረት እንኳ የሚናገርልን ጎደም። ግዕዝ ከትምህርት ቤት እንዳይሠጥ ቀደም ብሎ ዘመናዊው ተ/ቤት ሲጀመር ግዕቀብ ተደረገበትና ነው። ለአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ግዕዝ ሲባል ለቅዳሴ ለማኅሌትና ለፍትሐት ብቻ አገልግሎት መስማ አድርገው ይመስከቱታል። እንዲያውም ከሕዝቡም አመክሮ እንደምንረዳው በኔ ሞት አፈር ስሆን ሃሌ ሲሉብኝ ከመባል ደርሷል። ቤተ ክርስቲያን ከቤተ መቅደሱ ጀምራ የትምህርት ሚኒስቴር ሆና በመኖሯ ብቻ ስትገለገልበት ትታያለች እንጂ ግዕዝ የሁሉም ነው። የጥበብ የምርምር የሕክምና የምሕድስናና የቅመራ ማለት የለሌት ሁሉ ቋንቋ ነው። ወጣቶች አጥኑት። ትምህርት ቤት በሩ ተከፍቶለት እስከሚጠና ድረስ ያላችሁን ወርቃማ የወጣትነት እድሜ ግዕዝ ላታጠኑበት እንዳያልፍ እማፀናችኋለሁ። የሚፈለገውን ሁሉ ታገኙበታላችሁ። የዓለም ጥበብ ምንጩ ከዚሁ ቋንቋና መዳሕፍት እንደሚገኝ ላስገነዝባችሁ እወዳለሁ አደራም እላለሁ። ግዕዝ ማጥናት ለእናንተ ከባድ አይደለም ቆሎ እንደመቆርጠም ነው። ቀላል ነው። ካንድ ዓመት በላይ አይወስድባችሁም። ጥቅሙ ግን እጅግ በጣም ታላቅና ብዙም ነው።

ዛሬ አፍሪቃ በምዕራባውያን አድማና ሴራ ተበጣጥሳ ባሕሏንና ቋንቋዋን አጥታ የነጣችበትና የገረጣችበት ጊዜ እንደሆነ ታውቃላችሁ። በየትም የአፍሪቃ አገር የሚናገሩበት ቋንቋ የቅኝ ገዥዎቻቸው ቋንቋዎች ናቸው። ይህን ጉዳይ ወደራሳችን መለስ ብለን ስናየው በወላጆቻችን እንዴት እንኮራለን። እንዴትስ እንከብራለን። በእነሱ ደም በእነሱ አጥንት እኛ በማንነታችን ላይ እንገኛለን። በራሳችን ፊደል እንጽፋለን በራሳችን ቋንቋ እንናገራለን። ይህን ጠብቀው ያቆዩን ወላጆቻችንን እናከብራለን እናመሠግናለን። እኛም ይህን አደራ ጠብቀን ለልጆቻችንና ለልጅ ልጆቻችን ማስተላለፍ ታሪካዊ አደራ አለብን። የማንረሳው ግን ቋንቋችንና ፊደላችንን ወደ እነሱ ለመለወጥ የሚያደርጉትን ሤራ አተኩረን እንመልከተው። ከኛ ተበድረው መልሰው ሊያበድሩን አይገባም።

ቢጽኑ ልንዋጋው የሚገባ ጉዳይ ነው። ሌሎች የአፍሪቃ አገሮች ምን ያህል እንደሚኮሩብንና እንደሚመኩብን አንዘንጋ። ዛሬ የአፍሪቃ አገሮች የሚናገሩበት ቋንቋ ልዩ ነው። የባዳ ነው። ከዚህ ለመውጣት በትግል ላይ ናቸው። የስዋሂኛ ቋንቋ መጠናት ራሱ አንዱና ትልቁ ምሳሌ ነው። ስዋሂሊኛን በግዕዝ ፊደል ሲጽፉ ነው ምሉእ የአፍሪቃ ቋንቋ የሚሆነው። ይህን ደግሞ ነገና ከነገ ወዲያ ይሆናል። ከዚያ ደግሞ ግዕዝ የአፍሪቃ ልሣንነቱን ያረጋግጣል። የግንዛቤ ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ ለአፍሪቃ ነፃነት ተዋግታለች ረድታለች አበረታታለች። የአፍሪቃ አንድነት እንዲመሠረትም እጅግ ታላቅ መሥዋዕት ከፍላለች። ለዚህም ነው የአፍሪቃ አንድነት ዋና ከተማ እንድትሆን የተመረጠችው። ይህ ቀላል ምርጫ እንዳይመስለን በከብር ልንቀበለውና ልናከብረው ይገባል። በዚህ ዕድል በዋና ከተማነታችን ብዙ የምንመግባቸው ብዙ የምንሠጣቸው አሉን። ከክትፎውና ከጠጁ ባሻገር ማለቴ ነው። የአፍሪቃ ቋንቋ ግዕዝ ነው አጥኑት ብለን ለመቀለቀለ በመጀመሪያ ራሳችን ከት/ቤት እንዲገባ ስንፈቅድ ነው። ይህን ብናደርግ ታሪክ ሲያወድሰን ይኖራል። ላለውና ለመጣው ትውልድም ብሔራዊ ቅርስ እንተውላቸዋለን።

የሚገርመው ግን አፍሪቃውያን ምንም እንኳ በላያቸው ላይ ያለውን የምዕራባውያን ተጽእኖ ሁሉ ተጋቁመው ወደ ማንነታቸው ለመምጣት የማያደርጉት ነገር የለም። ሆኖም ገና ናቸው። የወደፊቱ ትውልድ ግን ይችላል። በርግጥ ይችላል። ጠርሶ ነፃ ይወጣል። የዛሬው የአፍሪቃ ነፃነት ሰንደቅ ዓላማ ከማውለበለብና የራስን ሰው መሪ አድርጎ ከመመልከት በስተቀር ገና ፍፁም ነፃነት አልተጨበጠም። ገና በዓየር ላይ ነው። በእያንዳንዳቸው በአፍሪቃ መሪዎች ላይ ያለው ተጽእኖ በቋንቋ የሚገልጹት አይደለም። እንዲያው ለመኖር ሲባል የሚደረግ መፍጠርጠር ነው። ይሁንና ይህን የአፍሪቃን ችግር የመዘዝሁበት ምክንያት አለኝ። እሱም በአፍሪቃ ውስጥ ሁሉም ዓይኑን ከፍቶ የሚመለከታት አገር የአፍሪቃ አንድነት ዋና ከተማ የሆነችው ኢትዮጵያ ለአፍሪቃ አንድነት የምታገለግለው በብዙ ዘርፍ ነው። ከዋና ከተማነት አልፋ ተርፋ ፊደሏን ቋንቋዋን አፍሪቃውያን ይፈልጉታል ሊማሩት ይሻሉ። ሊናገሩበት ይወዳሉ። ታዲያ ለዛሬው ወጣት ግዕዝን ማጥናት ለነገው የአፍሪቃ ትውልድ ቋንቋ አስተማሪ ለመሆን ዕጩነት ነው። ለዚህ ዓቢይ ሥራ እናንተው አይደላችሁምን? በእርግጥም ናችሁ። ከያላችሁበት ጀምሩት። በተለይም የግል ት/ቤቶች ከፍታችሁ ወገኖቻችሁን በዕውቀት የምትመግቡ ኢትዮጵያውያን ግዕዝ በየት/ቤቶቻችሁ እንዲሠጥ እስቲ በር ክፈቱ። ታሪክም ያወድሳችሁ። ኢትዮጵያዊነት አደራችሁንም ተወጡበት።

ዛሬ የኢትዮጵያን በተለይም ይህን ጥንታዊ ቋንቋ የዓለም ጥበብ ምንጭ የሆነውን ግዕዝን እጅግ ቁጥሩ ብዙ የሆነ በአሜሪካ በካረቢያን ደሴቶች የሚኖሩ የአፍሪቃ ተወላጆች ለመማር እጅግ በጣም አድርገው ይሻሉ ይመኛሉ። ይህን ፍላጎታቸውን የሚያሟላላቸው ማን የሚሆን ይመስላችኋል። እናንተው የቋንቋው ባለቤቶች ናችሁ። ባንድ ዓመት ትምህርት የዕድሜ ልክ ፀጋና ሀብት ማግኘት መሆኑን ልብ በሉት። አፍሪቃውያን በራሳቸው ፊደል መማርና መጻፍ የማይቆጨ ይማበላችኋል? እጅግ በጣም ነው የሚቆጨት የሚንገበገቡት። ኦሳ አፍሪቃ ኢትዮጵያ ተብሎ መጠራትን እንደሚመርጡ ግንዛቤ አድርጋችሁ ታውቃላችሁን? ካላደረጋችሁ አስቡ። ዛሬ ጅቡቲ ሶማሊያና ኤርትሪያ ሱዳን ተብሎ መጠራራቱን ራሳቸው ምዕራባውያኑ የኢትዮጵያን ስም ሰመጋረድ ምሥራቅ አፍሪቃ በማለት እየጠሩን ነው። የሚፈጽሙት ያለው ትንቢት ነው። እኒህ አገሮች ድሮም ምሥራቅ አፍሪቃም ኢትዮጵያም ነበሩ አሁንም በውስጣቸው በመልካቸው በቋንቋቸው በባሕላቸው አንድ ናቸው። ልዩነት የተፈጠረባቸው ነፃ መንግሥት ነፃ ሰንደቅ ዓላማ ማውለብለቡ ላይ ነው። ይህም ሲደረግ በውጭ ተጽእኖ እንጂ በሕዝቡ ፍላጎትና ምኞት እንዳልሆነ የምታውቁት አይደለምን?

ወደ አደራዬ ወደ ተማጽኖዬ ልመለስ ግዕዝ አጥኑ። ቅኔ ቤት ሄዶ ቁራሽ ለምኖ መብላት ሳያስፈልጋችሁ መዝሙር እንደምታጠኑት ሁሉ ግዕዝንም አጥኑት። በነፍስም በሥጋም ይጠቅማችኋል። አንድ ምሥጢር ላጫውታችሁ ልብ ብላችሁ አዳምጡኝ። ምዕራባውያን ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ ሞከሩ አልቻሉም ተሸነፉ አፍረውም ተመለሱ። ይህ ያንድ ኢጣሊያን ጎፍረት ብቻ አይደለም ለመላው ቅኝ ገዢዎች በሙሉ እንጂ! ኢትዮጵያ ደግሞ ቅኝገዥዎችን በሙሉ ተዋግታ ያሸነፈች አገር ማለት ድሉ ለመላው አፍሪቃ ሕዝብ ነው። ይህን ኩራት ይህን ድል አድራጊነት ያበገኘች አገር በዓለም ላይ ብርቅ ድንቅ ሆና ታየች ተነገረች በተለይም የአፍሪቃ ዝርያ ተወላጅነት ባላቸው ሁሉ ዘንድ ነበር። ነውም። በአሜሪካ በኢትዮጵያ ስም የጥቁሮች አብያተ ክርስቲያናት መሠየም ጀመሩ የዳግማዊ ምኒሊክና የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ስሞች እንደ ኮከብ ለሁሉም የሚታዩና የሚያበሩ ሆኑ። ይህን አፍሪቃ አፍሪቃ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የሚለውን ስም ለማጥፋት ምን አድማ ተጀመረ። የኢትዮጵያን ስም ያለመጥራት በምትኩ ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይቀር ደቡብ ግብፅ ሱዳን ኩሽ አቢሲኒያ የሚሉትን ስሞች ማደናገሪያ አደረጓቸው። አሁን ደግሞ ምሥራቅ አፍሪቃ ወዘተ... እየተባልን ነው።

ወጣቶች ሆይ! ይህ ብቻ አይደለም ጉዱ የቤቶቻችንን ዶሮዎች በቆቅ እየለወጡብንም ነው። ዛሬ የግዕዝ ፊደል ቀዳሚ ፊደላት መሆኑ እየታወቀ ግዕዝን ወደ ላቲን መልሰው በጦርነት ያላገኙትን ምርኮ በዕጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ እያጠፉብን ነው። ኢትዮጵያውያንን መበታተን ማጠላላት በረሀብና በጉስቁልና መተብተብ ፍቅር አንድነት እንዲጠፋ ማድረግ ሰዎችን መከፋፈል። መፈንቅለ መንግሥት ማዘጋጀት ይህን በመሳለለው የምትጎሳቆለው ማን ናት? አሁንም ቢያንስ ቢያንስ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሰባት በላይ ነፃ አውጭ ድርጅቶች አሉን። እርሻ እንዳይታረስ ትምህርት እንዳይቀጥል ዕድገት እንዳያመጣ ሕዝቡ ወደ ልማትና ወደ ሥልጣኔ እንዳይጓዝ የሚደረገውን ትንቅንቅ የምታዩትና የምትሰሙት አይደል? ኢትዮጵያን በበለጠ ብዙ አገር ለማድረግ ቢያንስ ቢያንስ አምስት አገሮችን ሠንጥቆ ሰማውጣት የሚደረገውን ጥረት ታዩት የለምን? ይህ ሁሉ ለኛ ካንድ ኢትዮጵያ ይልቅ ብዙ ኢትዮጵያ የተከፋፈለች ኢትዮጵያ ለማድረግ ለጽድቅ ይመስላችኋልን? ኢትዮጵያ በፊደሏ በባሕሏ በቋንቋዋ የመላው አፍሪቃ ነፍስ መሆኗን ስለሚያውቁ ማሰናከያ መፍጠር ታላቅ ሥራ ከፍተኛ ቦጀት የተመደበለት ሥራ ነው። ይህን ወጣቶች ማወቅና መገንዘብ አለባችሁ። ይህም ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተረሣና አየተዘነጋ ሲሄድ እነሱ በዕቅዳቸው እያንዳንዱ ጠቅላይ ግዛት ወይንም ክፍለ ሀገር ሌላ መንግሥት ነፃ አገር ሆኖ የእነሱ የዕረፍት ጊዜ ማሳለፊያ ለጊዜው ለዘለቄታው ደግሞ በሽቦ አጥረው በዘበኛ አስጠብቀው ሰመኖር ነው። ታዲያ ወጣቱ ሆይ! በገዛ አገርህ የፈረንጅ በር ጠባቂ ሆነህ ሰመኖር መቼም ቢሆን አትመኝም። ነገር ግን መንገድ ከጠፋ ውርደት ከመጣ ደግሞ ምርጫ የለህም። ዛሬ ግን ምርጫ አለህ። በቅድሚያ የራስህን ማንነት አጠናክረህ ያዝ። እንደ ጥሩ ምሳሌም የሚሆነው ዛሬ መዝሙርህ በየመኖሪያ ቤቱ በየአውቶቡሱ በየቡና ቤቱ በየጠጅ ቤቱ በየመንገዱ ከቤተ ክርስቲያን እንኳ ሞልቶ ተርፎ ስታዩት ሕዝቡ ከእናንተ ጋር መሆኑን መረዳት አይቸግራችሁም። ነገ ከነገ ወዲያ ደግሞ ግዕዙ ሲጠና ግዕዙ ሲታወቅ መጻሕፍቱን ስትመረምሩ ምሥጢሩን ስታውቁት እጅግ ትደሰታላችሁ። ተፈላጊነታችሁም በሠፊው ይጨምራል ይወደዳል ይፈለጋል። ታዲያ ጊዜ አይባክን ነገ ዛሬ አይባል አሁኑኑ ትምህርቱ ይጀመር።

ይህን ስታደርጉ በግዕዝ ፊደላት መጻፉን አስትተው በሮማን ያውም ዘሮቻችንን በመርዝ ጪስ በጨረሱት በጠላቶቻችን ፊደል የሚጽፉትን ወገኖቻችንን ዕጅ ወደ ኋላ እንዲሰበሰብ እናደርጋለን። ይህን ሲያደርጉ በቅንነት በጥናት በእውነት ከግዕዝ ፊደል ይልቅ የሮማን ፊደል ምቹ ሆኖ ይመስላችኋል? አይደለም አይሆንምም። ግን

ለዚሁ ሆን ተብሎ የሠለጠኑ እነሱ ደግሞ ያራቡት ከጥላቻ ጋር ጥላቻው ደግሞ ከግዕዝ ፊደል ጋር ነው። የቅኝ ገዥዎች ቋንቋ ተብሎኮ ተሠይሟል። እጅግ የሚያሳዝን ነው። የሮማን ፊደል ከግዕዝ መቀዳቱን ቢያውቁ ኖሮ ቢያጠኑት ኖሮ እንዴት በደነቃቸው በነበር? እንዴትስ በገረማቸው? በአገራችን ሙጀሌ የምትባል ቁንጫ አለች። በእግር ገብታ አግርን የምትበላ። ይች ትንሽ ቁንጫ በጊዜው ተከታትለው ካልነቀሏት እግርዎ በመጥረቢያ ቆርጠው የጣሉትን ያህል ሙልዋ አድርጋ ትቆራርጣለች። በሙጀሌ የተበሉ ሰዎችን እግር ስታዩ ትገረማላችሁ. /አካሄዳቸውንም ጎታታና ጠማማ አድርጋባቸዋለች። በቶሎው በጊዜው እርማት ካልተደረገበት ካንዱ ትውልድ እንደምንም ብሎ ወደ ሌላው ከተሸጋገረ መልሶ ለማስተካከል በጣም አስቸጋሪና አደገኛ ይሆናል። በሽታው ከዋለ ካደረ መድኃኒት ካላገኘ የማይገድለው ይገድላል። ስለዚህ አሰፈላጊው ርምጃ አሁንኑ ቢወሰድ መልካም ይሆናል።

ከዚህ ላይ አብሬ አደራ የምለው በያላችሁባቸው አብያተ ክርስቲያናት ያሉ የሰበካ ጉባዔዎች የግዕዝ መምህራንን ሊያገኙላችሁ ይገባልና ማሳሰቢያው ይድረሳቸው። በተለይማ የየሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤቶች ከዚህ የበለጠ ምንስ ታላቅ ቁምነገር አላቸው? ይህንስ ከማድረግ ምንስ የሚገታቸው አለ? ለነገሩማ ሥልጣነ ክህነት ከመቀበል በፊት ግዕዝ መማርና ማወቅ የግዴታ ግዴታ ማዕቀብ መጣል አለበት። ተጽእኖ መደረግም ይኖርበታል። ይህን የመሰለውን ውሳኔ ደግሞ የሚወሰደው ቅዱስ ሲኖዶስ እንዲገነዘበው በእናንተ በወጣቶች በታዳጊዎች ስም በታላቅ ጩኸት እጠይቃለሁ። ሥራው ግን የእነሱ ነበር። ሆኖም ምሳ ደርሷል ማዕድ ቀርቧል ተብሎ እንደሚነገረው እናስታውሳቸው። ይሁን እንጂ እያንዳንዱ የሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ሊያደርገው የሚችለው ዓቢይና ቀዳሚ ጉዳይ ነው። ይህ ደግሞ በግዝትም እንኳ መደረግ ያለበት ሥራ ነው። ግዝቱም ከዚህ ላይ ቢያርፍ ይሠራል። የቀደሙ አባቶች የደነገጉት ሕግም አለ። እሱም ልጁን የማያስተምር ወላጅ የገንዘብ ቅጣት እንዲደረግበትና እንዲገዘት ይወሰናል። ይህም በዓፄ ምኒልክ፡ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱና በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥታት ሁሉ ተፈጽሟል። በደርግም ጊዜ መሠረተ ትምህርት «ያልተማረ ይማር የተማረ ያስተምር» ተብሎ ዘመቻ ተደርጎበታል።

ይህ ሁሉ የሚያሳየው ትምህርት ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን ያስረዳል። የወጣቶች የግዕዝ መማርና ማወቅማ ታሪካዊ ብሔራዊና ሃይማኖታዊም ነው። አንዲሁ ከሩቅ ሲመለከቱት ነገሩ ቀላል ይመስላል እንጂ አይደለም። ይህን ማድረግ እጅግ በጣም ጠቃሚ

ነው። ከመሬት ውስጥ ወርቅን፡ ዓልማዝንና ዕንቁን ቆፍሮ የሚያስወጣ ቋንቋ ነው። ግዕዝን አውቆ መገኘት ማለት ኑዳጅን ቆፍሮ የማውጣት ያህል ያስቆጥራል። በምኞት ብቻ ሳይሆን በተግባር ተተርጉሞ ሲገኝ ብቻ ነው እውነተኛ ሀብትና ፀጋ መሆኑን መረዳት የሚቻለው። ወጣቶች ብረት ለብረት ሲጋጭ ስለት እንደሚወጣው ሁሉ እርስ በርሳችሁ ተማማሩ። መጻሕፍት አሉላችሁ። ባይሆን የሰበካ ጉባዔያችሁ መጻሕፍትን ይግዙ ወይንም ትያትር አዘጋጅታችሁ ገንዘብ አግኝታችሁ የግዕዝ መማሪያ መጻሕፍትን ግዙ። ከጀመራችሁት በጎ ሥራ ማድረግ ደስ የሚላቸው ግለሰቦችና ድርጅቶችም ይተባበሯችኋል። ጊዜ አይሠጠው በቶሎው ጀምሩት። እስካሁን በከንቱ የጠፋውና የባከነው ጊዜ ይበቃል።

ወጣቶች ሆይ! የግዕዝ ትምህርት እንዲሁ በሩቁ የሚያዩት ጉዳይ አይደለም። ክፍ ብዬ አንደ ጠቀስኩት ሁሉ ብርቅ ድንቅ ነው። ግዕዝ አንደ ሰሙ ትርጓሜ መጀመሪያ የሰው ልጅ አፍ መፍቻ ቋንቋ ነው። ምዕራባውያን ታሪክ ፀሓፊዎች እንደሚያወሩት በየመን በኩል የመጡት ሰዎች የሚናገሩት የነበረ የዐረብኛና የዕብራይስጥ ወገን ነው እንደሚሉት አይደለም። የእኒህ ቋንቋዎች አባትና እናት እንጂ! ለዚህ ሁሉ ማስረጃው ግዕዝ የመጀመሪያ ቋንቋ ለመሆኑ እንዲህ ሲል ተጽፋል። «ወአሐዱ ነገሩ ለኩሉ ዓለም ወአሐዱ ቃሉ። [ምድርም ሁሉ በአንድ ቋንቋና በአንድ ንግግር ነበረች።] ዘፍ. 11:1 ሲል ይገኛል። ይህን ቃል በጥሞና መመልከት ነው። ግዕዝ ይህን ያህል የመጀመሪያ ቋንቋ ነበር ስንል እንዲያው ኢትዮጵያን ከፍ ከፍ ለማድረግ ነውን? አይደለም እውነት ስለሆነ ነው እንጂ! ብዙ ማስረጃዎች አሉን።

ሌላ ምሳሌ ላቅርብ። የሰው ልጅ አባትም እናትም ሆኖ የተፈጠረው የመጀመሪያው የሰው ልጆች ሁሉ አባት አዳም የስሙ ትክክለኛ ትርጉም ያለው በግዕዝ ብቻ ነው። አዳም ማለት በግዕዝ አጠራሩ እድ ወእም የሁለቱ ቃላት ጥምሬ ነው። እድ ማለት ወንድ እም ማለት ደግሞ አናት ወይንም ሴት ማለት ነው። ሲነበብ ወን አጣማሪውን ቃል ትቶ አዳም ይለዋል። ይህም ቃል ወንድና ሴት ማለት ነው ብለናል። የትርጉሙን ማስረጃ አንመልከት። እንዲህ የሚል ቃል እናነባለን። «ወነደቃ እግዚአብሔር ለይእቲ ፀፅመ ገቦ እንተ ነሥአ እምአዳም ወረሰያ ብእሲተ ወአምጽአ ኀበ አዳም። ወይቤ አዳም ሶቤሃ ዛቲ ፀፅም እምፀፅምየ ወሥጋ እምሥጋየ ለትኩነኒ ብእሲትየ እስመ እምታ ወጽአት ይእቲ» [እግዚአብሔርም ይህችን ከአዳም ጎን የነሣትን ዓጥንት ቀረፀላት ሴት አደረጋት ወደ አዳምም አመጣት። ያን ጊዜም አዳም ይህች ከዓጥንቴ ዓጥንት

ከሥጋዬ ሥጋ ናት ሚስቴ ትሁነኝ አለ እርሷ ከባሏ ተገኝታለችና።] ከዚህ ላይ እኛን በሚገባን ቋንቋ ብንገልጸው አዳምን ወደ ሁለት ሰውነት ወንድና ሴትነት ተመነዘረ ተለወጠ ከአንድነት ሁለትነት ተገኘ ሲል መጽሐፉ የጻፈውን ግዕዙ እንዳለ ቃሉን ሳይለውጥ እስካሁን ድረስ መጠሪያነቱን አዳም ብሎና ይዞ እናገኘዋለን። እዳም ማለት እንግዲህ እድ ወእም ወይንም ወንድና ሴት ብሎ የሠየመውም ለለዚህ ነው። ይህም ቃል እስካሁን ድረስ በዓለም ሁሉ እናትን እማማ እማዬ እማሆይ ማሚ እያሉ እናታቸውን የሚጠሩ ሆነዋል።

ሌላም ምሳሌ ልጨምር ግዕዝ የመጀመሪያ ቋንቋ ያልነውን ኃረግ የሚያጠናክረው አብርሃም የሚለውን ስም እንመልከተው። ይህም ስሙ የተግባሩ ትርጉም ሆኖ እናገኘዋለን። አብርሃም ማለት ቃሉ ግዕዝ ነው። ሁለት ቃል በዘ የተየያዘ ወይንም የተዛረፈ ስም ነው። በዝርዝር ስንመለከተው እንዲህ ነው። አብ ዘ ሃም[ካም] አብ ዘ ሃም ማለት የካም አባት ነህ ወይንም ትሆናለህ ማለት ነው። «ወኢይሠመይ እንከ ስምከ አብራም አላ አብርሃም ይሠመይ።» [ከእንግዲህስ ስምህ አብራም አይባልም አብርሃም እንጂ] [ዘፍ. 17:5 ከዚያም የካም ልጆች ወደሚኖሩበት ወደ ምድረ ከነዓን [ቅኑዓን] ሂድ አለው ሄደ። ይህን ቃል እብራይስጡ አበ ብዙኃን ማለት የብዙዎች አባት አደርግሃለሁ ብሎው ይተረጉሙታል። ዋናው የቃሉ ትርጓሜና አጸጸፉ ግን የግዕዙ ቃል ነው። በዚህም ቃል መሠረት ኢየሱስ የመጣውና የተገኘው ከካም ዘር ከሆነችው ከቅድስት ድንግል ማርያም ነው። አብርሃም የሚለው ስምም አሠጣጥ አምላክ ሰው የሚሆንበትን ምሥጢር ለማጠየቅ ነው። ይህን የመሰለውን ምሥጢረ መለኮት የምንመረምረው በግዕዝ ቋንቋ መሆኑን በሚገባ ያጤኗል።

በዚሁ አንፃር እድ ወይንም ወንድ የክሮሞዞሙ ዓይነት ዋይ ኤክስ [YX] ሲሆን የሴቷ ደግሞ ኤክስ ኤክስ [XX] ነው። ስለዚህም ያንድ ልጅ ጾታው የሚወሰነው በአባት ክሮሞዞም ነው። ዋይ [Y] ከተወሰደ ከሴቷ ክሮሞዞም ጋር ሲዋሀድ ዋይ ኤክስ ማለት [YX] አሱም ወንድ ልክ አዳምን የመሰለ ሰው ተገኘ ማለት ነው። ሴት ስትሆን ደግሞ ከአባት የሚወሰደው ኤክስ [X] ከናትም ኤክስ [X] ሲሆን የምትወለደው ሴት ትሆናለች። ይህም ኤክስ ኤክስ በመሆኑ ነው። ታዲያ ግዕዝ የመጀመሪያ አፍ መፍቻ ቋንቋ መሆኑን ራሱ የአዳም ስም ትርጉም ቁልጭ አድርጎ ያስረዳል። ከሳይንስ ወዲያ ምስክር በአሁኑ ጊዜ ሳሳር ነው። ምሥጢሩ ይህ ነው። አሁንማ ኢትዮጵያም የሰው ልጆች መፈጠሪያነቷ በድንቅነሽ ተረጋግጧል።

እንዲያው በቋንቋው በኩል ያለውን ለማረጋገጥ እንጂ! ዛሬ ዳቦ ያጣች አገር በመሆኗ ለደህ ደግሞ ወዳጅም ክብርም ስለማይሰጠው ታላቋን የሰው ልጅ መፈጠሪያና ማደጊያን አገር ያለታዛቢ እንዳትቀር ታሪኳን ቋንቋዋን ጥበቧን ሁሉ ውረሱ። «ያባት እዳ ለልጅ የአፍንጫ እድፍ ለዕጅ» ነውና! ግዕዝን አጥኑ አጥኑ አጥኑ። ተማሩ ተማሩ ተማሩ። በአገራችሁና በማንነታችሁም ኩሩ።

ግዕዝ የመጀመሪያ ቋንቋነቱን ለማረጋገጥ ሌላ ምሳሌም ላምጣ። አንድ ሕፃን ሲወለድ አብረውት የሚመጡ እውቀቶች አሉት። እኒህም ለሕይወቱ አስፈላጊ ጉዳዮች ናቸው። አንደኛው በሕይወት እንዲቆይ የአናቱን ጡት መጥባትን በጥቅሉ መመገብንና ሁለተኛ ፍሳሳቱንና ስሜቱን የሚገልጽበት ቋንቋ ነው። አሱም ሲቸገር ሲያመው ርዳታ ሲፈልግ ማልቀስ ደስ ሲለው ደግሞ መሳቅ ናቸው። እኒህ ሰሜቶች ዳብረው ቋንቋ ለመፍጠር የሚያስችሉት ሕዋሳት ማለት ጥርስ ማውጣት የከንፈር የመሳስና የላንቃ መጠጠርና የጉረሮ መስፋት ናቸው። እኒህ አካሳት ሲዳብሩ በመጀመሪያ የሚያሰሙት ድምፅ አባባና እማማ ነው። ይህም የሚያስረዳው አባባ ማለት አብ እንዲሁም እማማ ማለት እም ከሚለው የግዕዝ ቃላት የተገኙ ናቸው። ይህ እንግዲህ የሚያስረዳን ግዕዝ በተፈጥሮ የመጀመሪያና የአፍ መፍቻ ቋንቋ መሆኑን ነው።

ስለ ግዕዝ አጻጻፍም አመጣጥና እድገት ትንሽ ማውሳት እፈልጋለሁ። ግዕዝ የሰው ልጅ አፍ መፍቻ ቋንቋ እንደሆነ ተገንዝባችኋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። ይህ ቋንቋ ሌላው ጥንታዊነቱን የሚገልጽበት ሌላው ማስረጃ የአጻጻፍ ስልቱ ነው። የጽሕፈት መሣሪያዎች በሌሉበት ዘመን በድንጋይ በሸክላና በአጥንት በሚጻፍበት ወቅት መጀመሪያ በግዕዝ ፊደላት ማለት በመጀመሪያዎቹ ሆሄያት ብቻ ከላይ ወደታች ይጻፍ ነበር። ለምሳሌ ያህል ነ ገ ሠ ፡ ቀ ደ ሰ፡ ቀ ተ ስ የሚሉትን ፊደላት ሲጽፍ አቀማመጡም እንዲህ ከላይ ወደታች ነበር ፦

ነ
ገ
ሠ

ቀ
ደ
ሰ

ቀ
ተ
ለ

ሲነበብ ግን ንጉሥ ቅዱስ ቅቱል ተብሎ ነው። ይህም በንባብ ጥናት ሕግ መሠረት ይፈፀማል። ስትጂፉ እንደዚህ ስታነቡ ደግሞ እንዲህ በሉት ተብሎ ማለት ነው። ለምሳሌ በእንግሊዝኛ ቋንቋ «KNOW» ተብሎ የተጻፈውን ሲነበብ «ክኖው» ሳይሆን «ኖው» ተብሎ ነው። ለምን ሲባል «ኬ K» አትነበብም ተብሎ ስለተነገረ ብቻ አትነበብም። በትምህርት መገንዘብ ማለት ነው። በኋላ ግን በግዕዙ ፊደል ላይ ስድስቱ አናባቢ ሆሄዎች ተጨምረውበት በመጻፍም በማንበብም እኩል ሆኗል። ይህም በአድገት የመጣ መሆኑን መረዳቱ አይጸንም።

ሁለተኛ የግዕዝ አጻጻፍ ደረጃ ደግሞ ከድንጋይና ከሸክላ አልፎ በቅጠልና በልጥ በመሰሰሉት መጻፊያዎች ላይ መጻፍ ሲጀምር እንደ መጻፊያው ዓይነትና ምንነት ለምሳሌም በቅጠል በግንድና በቅርፊት ሲጻፍ ዝግዛግ መጻፍ ቀጥሏል። ይህም የመጻፊያው ማለት የቅጠሉ ቅርጽ ከላይ ይጠባል ከመሃል ይሰፋል። ያንን ለማዳረስ እንዲቀና የዝግዛግ አጻጻፍ ስልት አስፈላጊነት ይታያል። ይህ እንግዲህ ለግዕዝ የአጻጻፍ ደረጃው ሁለተኛ መሆኑ ነው። ቀጥሎም የእንጨት ሳንቃዎችና የእንስሳት ቆዳዎች ማለት የብራና ጥቅም ከሥራ ላይ በዋለበት ዘመን ግዕዝ ከቀኝ ወደ ግራ መጻፍ ቀጠለ። በዚህን ጊዜ ቋንቋ ፈጥረው መጻፍ የጀመሩትን አንዳንድ ቋንቋዎችን ያጻጻፍ ስልት እናያለን። ከእነዚህም ውስጥ ዕብራይስጥንና ዐረብኛን ለምሳሌ ያህል እንጠቅሳለን። የእኒህ ቋንቋዎችን አነሣስ ስንመለከት እነሱ ወደ ፊደል ቀረፃ ሲጀምሩ ግዕዝ ከሦስተኛ የአጻጻፍ ደረጃው ላይ ነበር። ይህን ልብ በሉ የዕድገት ሂደት ነውና ነው።

ግዕዝ በዚህ አላበቃም። የአጻጻፉን ሂደት ቀጥሎ አሁን ካለበት አራተኛ ደረጃ የአጻጻፍ ስልት ላይ ይገኛል። እንግዲህ በአሁኑ የአጻጻፍ ስልቱ ከግራ ወደ ቀኝ ነው። በዚህ አጻጻፍ ስልት እጅግ በጣም ብዙ የሆኑ የዓለም ቋንቋዎችን እናገኛለን። እንግዲህ በዕድገት ደረጃ ሲለኩ ግዕዝ አሁን ካለበት የአጻጻፍ ስልት አራተኛው የዕድገት ደረጃ ላይ የጀመሩ ናቸው ማለት ነው። ከእነዚህም ውስጥ በቀዳሚነት የምዕራባውያን ቋንቋዎች ይገኙበታል። ለምሳሌም ያህል ላቲን ግሪክ ወዘተ... እኒህ ቋንቋዎችን ከግዕዝ ጋር ስናወዳድር የግዕዝ የልጅ ልጆች ናቸው። ለነገሩማ ከድንቅነሽ ማግስት ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መገኛ መሆኗን ዓለም

አረጋግጠላታል። እውነትና ጢስ መውጣ አያጣም የሚባለውም ስለዚህ ነው። እኛ ብለን ብቻ ቢያበቃ ኖሮ የሚወረወረው ድንጋይ እንደ ባሕር አሸዋ በበዛ በነበር። ነገር ግን ራሳቸው ባሉትና በፈጠሩት የማረጋገጫ ማስረጃ ወይንም ወርቅን በአሳት አቅልጦ ዋጋውን ሳይለውጥ እንደሚያልፍ ሁሉ የአርኪዎሎጂ ወይንም በከርሠ ምድር ጥናት የተረጋገጠ ስለሆነ ምስክርነቱን ወደጉም ጠሉም ይቀበሉታል። ከዚህ ሳይ በአክብሮት የማላስበው ከግዕዝ ወደ ሮማን ፊደል ተከርቸም የገባችሁ ወንድሞችና እኅቶች እንድታስቡበት ነው።

ስለዚህ ግዕዝን መማር ያስከብራል። ግዕዝን መማር ያስከብራል። አገርን ያኮራል። አገርን ያኮራል። እያላችሁም በጣዕመ ዜማችሁ ወጣቶች አወድሱት አሳምሩት አስውቡት ተንከባከቡት ዘምሩለት ዘምሩለት ዘምሩለት። ይህ ምክር ለወጣቶች የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች ይሁን ይደረግ። አነስን በዛን አትበሉ መማሩን ቀጥሉ። በውጤቱ ትደሰታላችሁ የሥጋ ብቻም ሳይሆን የመንፈስ ርካታም ታገኙበታላችሁ። ግዕዝ ለመማር ት/ቤት መሥራት ወንበር መዘርጋት አያሻችሁም። ድሮም ከመሬት ቁሞ ብለው ከዛፍ ሥር ጋደም ብለው የሚማሩትና የሚያጠኑት ነው። ዛሬማ ማለፊያ አዳራሾች አሏችሁ ቢጠፉ ቢጠፉ ደጀ ሰላሙም አለላችሁ። ስንቅ መሰነቅ አያሻችሁም። የመንፈስ ዝግጅትና ውሳኔ ብቻ ነው የሚያሻችሁና ለመማር ተነሡ። እናንተ ጀምሩት ሌሎች ይከተሏችኋል። አርዓያነታችሁን አሣዩ።

ስለዚህ በሌላም በኩል «ኮሎ አመክሩ ወዘሠናየ አጽንኡ።» [ሁሉን መርምሩ የተሻለውን ግን ያዙ።] የወጣትነት ዕድሜ ብዙ የሚጠናበት፥ ብዙ የሚፈተኑበት ጊዜ ነውና ወጣቶች ቢያጠፉም አጠፉ አይባሉም። ተሳሳቱ ነው የሚባለው። ስሕተት የመታረም ዕድሉ ከፍተኛ ነውና ነው። ነገር ግን ታሳቅ ኃዘንና ፀፀት የሚሆነው ስትሰሳቱ የሚመክር ያጣችሁ እንደሆነ ነው። የሚመክርና የሚገሥፅ ማግኘት ራሱ ታሳቅ ቡራኬ መሆኑን በአእምሯችሁ አኑሩት ጠብቁት። ተግሣፅና ምክር ለወጣቶች እንደ ማርና እንደ ወተት ማሳደጊያ ነው። ይጣፍጣል ያፋፋል ጤንነትን ይጠብቃል። አስተሳሰብን ያዳብራል። ማንነትን ያጠናክራል።

ምዕራፍ ስድስት

መፍትሔና ማጠቃለያ

ና

አንባቢዎች ሆይ! የዚች አጭር ትንሽና ጉንጽል መጣጥፍ ማሳሰቢያና ዋና ዓላማ ከመግቢያው ላይ እንደገለጽሁት ሁሉ ይህ ዘመን ትንቢት የተነገረለት አስቀድሞ የታወቀለት ነው ብንል የተመቸ ይሆናል። እንደ ትንቢቱም መንግሥት በመንግሥት ላይ የሚነሣበት፥ ሕዝብ በሕዝብ ላይ ጦርነት የሚያካሂድበት፥ ሐሳውያን መምህራን የሚበዙበት፥ የመሬት መንቀጥቀጥ፥ የባሕር መናወጥ የሚሆንበት መሆኑ ተረጋግጧል። ሁሉም በአንድ ላይ ደርሶ የምናየውና የምንሰማው ትንግርት አሁን እየሆነ ነው። በጣም የሚገርመው ግን ይህ ሁሉ ማዕበል ተነሥቶ ሰው ሲገድል፥ ንብረት ሲያወድም፥ ይህን መሳዩ የተፈጥሮ መቅሠፍት አፍረቃ ውስጥ እንደሌላው ዓለም በብዛት አልደረሰም። በአፍሪቃ ያለው በአብዛኛው ሰው ሠራሽ ችግር አይሎ የሚገኝ ነው። ሰውን የሚያንገላታው፥ ሰው ሠርቶ የበተነው በሽታ ነው። ድርቁ የስንት መቶ አፍላጋት አገር ዓባይ ብቻ የሚበቃት ኢትዮጵያ በውሀ ጥምና በረሀብ ሕዝቧን ትጨርሳለች። ለዚህ ምሳሌም ተስማሚ ናት። በአንጻሩ ደግሞ በተለይም የግብፅ ሕዝብ ዝናም የሚባል ነገር አያውቅም። ሕይወቱ ቆሞ የሚሄደው በዓባይ ወንዝ ብቻ ነው። ነገር ግን እኛን የዓባይን ልጆችን ውሀ ጥማቱ እየገደለን ነው።

ቀደም ሲል እንደምናውቀው በተለያዩ ምክንያቶች በተለይም የአፍሪቃን ማንነት ሙቀትና ቅዝቃዜ የጠላቶቻችን መለኪያዎች መጽሐፍ ቅዱስ ያነገቱ፥ በጢማቸው ርዝማኔና ማማር፥ በአፋቸው ሐሰት ጨርሶ የማይነገር የሚመስሉ አውሮጳውያን አረጋውያን ነበር። ዋናውና ትልቁም ለኛ ምሳሌያችን አባ ማስያስ ናቸው። የእነሱ ማንነትና የዓላማ ጠረን በተለይም ለኢትዮጵያውያን አፍንጫ ገና ሲሸተው እንጢሶውን ይለቃል። ብቻውን ሳይሆን ዓይንንም ያስለቅሳል። ይህ የካቶሊኩ መነኩሴ፥ የእነ አባ ማስያስ ኢትዮጵያን የመውረር ሙከራ፥ አሰብን በመውሰድ ቢጸናም ኢትዮጵያን ግን ዕቅዳቸው ውስጥ ለማስገባት ዕቅዳቸው እንዳልሠራ ከዳር ድንበር ሲታወቅ የተንኮሉ ብልሃት መለወጥ ነበረበት። ያም ሀኬት ዛሬ ከመካከላችን እኛን መስለውና አክለው ራሳቸው ክርስቲያን የሆኑበት

የውሀ ጠፈጠፍ ከጆሯቸው ሥር ያውም ሁለት ሦስት ጊዜ በፍጣ መዥቅ ተደርጎ ገና ሳይደርቅ ስለ ኢየሱስ አዳኝነት ሲነግሩን ተነሡ። ወደኛም ገሠገሡ። መጡ መጽሐፉን ይዘው ሮሁ። ምራቃቸው ከሠርነቃቸው ገብቶ እስከሚተናነቃቸው ድረስ ደነፉ።

የእነሱ ዓላማ ወይንም ሚሽናቸው እኛን ሃይማኖት ለማስተማር አይደለም። እነሱም ያውቁታል። ነገር ግን በሃይማኖት አሳበው የሃይማኖት ካባ ደርበው ህብታችንን፥ ማንነታችንን ገብተው ለመዝረፍና ለማውደም ነው። እንደ ይሁዳ አገራቸውንና ሕዝባቸውን ሃሰት ቀባጥረው ሊያስረክቡ ፋና ወጊ ሆነው ቀረቡ። ይብላኝ ለእናንተ አገራችሁንና ታሪካችሁን በገንዘብ ለመሸጥ ቆርጣችሁ ለተነሣችሁ ሚሲዮናውያን እንጂ! መቼም ትውልድ ሲረግማችሁ፥ ታሪክ ሲያወግዛችሁ አንደሚኖር ግን ተገንዘቡ። በንስሐ ለመመለስ እንዳትሞክሩ ደግሞ ሊቀርባችሁ ነው ዶላሩ። «ዘክልኤ ልቡ እሁክ ውእቱ» [ሁለት ልብ ያለው የታወከ ነው] እንዳለው መጽሐፉ ሆናችሁ መኖራችሁ ግን ያሳዝናል ዋይ ለልስ ያሰኛል።

እናንተ ገና ኢየሱስን ላታውቁት እሱን ብቻ ሳይሆን አርበኞቹንና ጀግኖቹን በስሙ የተጋደሉትንና የሞቱትን፥ ለማዕታትን፥ ሐዋርያትንና ጻድቃንን ላይቀር ለይተን የምናውቅ፥ ሥራቸውን የምናደንቅ፥ ተዋሕዶ ኦርቶዶክሳውያን ነን። ስለ እነሱ ተጋድሎ የተጻፉትን መጻሕፍት የኢየሱስን ክብርና ሞገስ የሚሻሙ አድርጋችሁና አስመስላችሁ ቆጥራችሁና ወስዳችሁ ኡኡ! ትላላችሁ። እናንተ ማን ናችሁ? ፍቁም ኃሳባችሁ፥ ተንኮላችሁ በመላ አፍሪቃ የታወቀ፥ ፀሐይ የሞቀ አይደለምን? እንዲያው ለመሆኑ እናንተ የማን ናችሁ? «ጅብ ከማይታወቅበት አገር ሄዶ ቆርበት አንጥፉልኝ» አለ እንደሚባለው እየመሰላችሁ እንጂ! ይህ ምሳሌኩ የተነገረው በመሠረቱ ስለናንተ ነው። አባቱን አያውቅ አያቱን ናፈቅ እናንተኮ ናችሁ። ይልቁንስ «ልበ ንጹሐ ፍጠር ሊተ እግዚኦ» [አቤቱ ንጹሕ ልብ ፍጠርልኝ] እያሳችሁ በተለይ ኢትዮጵያውያን እንድትጸልዩ አደራ አሳለሁ።

አገርን ሃይማኖትን ለማጥፋት መሣሪያዎች ግን አትሁኑ። ያገራችሁን ክብር በዕለት መቅኑን አትለውጡት። በሚያልፈው ሕይወታችሁ ርግማንና ባርነትን ወደ ሕዝባችሁ አታምጡ። ሃይማኖታችን እንደናንተ በሚዋሹና የበግ ለምድ ለብሰው ሊያጠፉን በተሠለፉትና ባሰፈሰፉት በበግ ለምድ ለባሾች የተመሠረተ አይደለም። በእውነቱ ልታፍሩ ልትነወሩ ይገባል። ሃይማኖታችን እንዴት ከየት እንደመጣ በሚገባ እናውቃለን ራሱ መጽሐፍ ቅዱስ በሚገባ ይተርክልናል። የሐዋርያት ሥራ 8:26-39 ይህን ታምራዊ

ድርጊት ማንበቡ ራሱ ማንነታችንን ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። ለክርስትና እምነታችን ምክንያት ይህ ብቻ ይበቃናል ለማለት እንጂ! እናንት ኢትዮጵያን ሃይማኖት እናስተምራለን የምትሉ የበግ ለምድ ለባሾች አርፋችሁ ተቀመጡ። እግዚአብሔር ከምታደርጉት ማደናገሪያና አሳሳች ሥራ ያውጣችሁ። ያድናችሁ። ልብም ይፍጠርላችሁ። ይህ ስለ እናንተና ያለንና የምናደርገው ጸሎታችን ነው። አሁን ስለምታደርጉት ሚሲዮናዊ ሥራችሁ ትንቢትም ተነግሮባችኋል። ትንቢቱም እንዲሆ ይላል። «እግዚኦ ቦኡ አሕዛብ ውስተ ርስትከ ወአርኮሱ ጽርሐ መቅደስከ።» [ጌታ ሆይ የቀድሞዎቹ አሕዛብ ያሁኖቹ ጴንጤ መጨዎች የክብርህ መግለጫ የስምህ ማወደሻ የክብርህ ማሞገሻ ወደ ሆነችው ወደ ልዩ ርስትህ ኢትዮጵያ ገቡ። ሦስት መቶ ሰድሳ አምስት ቀን ስምህ የሚቀደስበትንና የሚሠለስበትን ሥጋህ የሚፈተትበትን ደምህ የሚቀዳበትን መቅደስህንም አረከሱ። መዝ. 78:1] (የትርጉሙ ማብራሪያ የራሴ ነው።)

ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ሆይ! መቼም በአገርና በዓይን ቀልድ የለምና እውነቱን ተናግሮ በመሸበት ማደር የለበው አመክሮ ነው። ይህን እንድናደርግ ደግሞ የዕድሜውም የአመክሮውም የእምነቱም ሁሉ ተደማምረው ያስገድዳሉ። ዝም ብሎ ማለፍ ሳይመስክሩ መሄድ የተሰጠንን መክሊት እንደ መቅበር ነው። ይህ ደግሞ በመጭው ትውልድ ዘንድ ያስወቅሳል ያስከስሳል። ሃይማኖታዊው ትምህርትም የሚያረጋግጠው የት ነበርህ? ምን ሠራህ? የሚሉት ጥያቄዎች ከዓፀደ ሥጋ ይልቅ በዓፀደ ነፍስ የማይቀሩ መጠይቃን እንደሆኑ ተምረናል። የዚህን ዓለም ሕይወት ከአሜሪካ ኢትዮጵያ በማለት ብናሳልፈው እንኳ በኋላ ወደማይሽከለኮሱበት ቦታ ሲሄድ መልሱ ምን ይሆናል? ጥንቃቄ መደረግ ያለበት ከዚህ ላይ መሆኑን አጠንክሮ ያረጋግጣል። ስለሆነም እውነት የሚናገሩበት ቦታ ከዚህ ነው። ሳይናገሩ ከቀሩ ዋጋው ሽልማት ሳይሆን ውርደት ይሆናል። ስለዚህ እውነት መመስከሩ የውዴታ ግዴታ ሳይሆን የግዴታ ግዴታ ነው።

ምን ይደረግ?

ሁላችንም እንደምንረዳውና እንደምናውቀው የጥበብ የቋንቋ የሰው ልጅም መጀመሪያና መኖሪያ ቦታ አድርጎ የፈጠራት ኢትዮጵያ ከአምላኳ ጋር በሩቅ ሳይሆን በቅርብ የምትተዋወቅና የምትነጋገር አገር ነበረች። ኢትዮጵያውያን አባቶች የጥበብ ሰዎች ነበሩ። ታላቁ መጽሐፍ ሳይቀር የሚጠራቸው የጥበብ ሰዎች ብሎ ነው። የእነ ሆሜርንና የሄሮዶቶስን ምስክርነት ሳይጨመር ለማለት

ነው። ያሁኑ ጥበብ የተቀዳው ከእኒያ የጥበብ ሰዎች አገር ኢትዮጵያ እንደሆነ ልብ እንበል። ኢትዮጵያውያን በደመና ተሞነው ከቦታ ቦታ ይመላለሱ ነበር። በባሕር ላይም መርከቦችን ያንሳፍፉም ነበር። ይህንም ጥበብ የዛሬው በሰማይ ላይ ጉዞን፥ በባሕር ላይ መርከብንም ተክቷል። ይህ በተግባር ይታወቅ እንደነበርና ይሠራበትም እንደነበር ምስክር አለን። ለዚህም ማሰረጃው ይህ ነው። «ወረበብኩ ለሰማይ ከመ ሠቅ። ዘይጠፍር በማይ ጽርሖ። ወረሰየ ደመና መከየዶ። ዘየሐውር በክነፈ ነፋስ።» በቀላል አተረጓጎም [ሰማይንም እንደ መጋረጃ የሚዘረጋ እልፍኙን በውኃ ላይ የሚሠራ ሠረገላውን ደመና የሚያደርግ በነፋስ ክንፍም የሚሄድ ይላል። መዝ. 103:2-3] ይህ አባባልና አነጋገር በአሁኑ በዓት በግልጽ የምናየውና የምናውቀው ነው። እሱም በባሕር ላይ እልፍኙን የሚሠራ ያለው መርከቡን ነው። በደመና የሚሄድና የነፋስም ክንፍ ያለው በቀጥታ አውሮፕላኑንና መንኮራኩሩን ነው። ይህን አስቀድመው የተናገሩትም የጥበብ ሰዎች ኢትዮጵያውያን ነበሩ። ይህን የመሰለውን በምርምር የሚገላልጡ ኢትዮጵያውያን አሁን ከየት ይምጡ? አሁን ያለው ጥበብ ሁሉ በፊት የነበረ ተግባሩም የተወደሰ ነበር።

አሁን ያለፈውን ተመልከተን ያለንበትን ሁኔታ ስናወዳድር የት ላይ ነን? ወዴትስ እያመራን ነው? ይህን የኃሳባችን መንደርደሪያ አድርገን ወደ መፍትሔ ኃሳባችን እናቅና። መፍትሔ የሌለው ነገር፥ መድኃኒት ያልተገኘለት ምች አደር የለም ብለን እናስብ። መቼም አንድ ሰው ወይንም ድርጅት ለበጎ ነገር ይነሣል መልካም ተግባራትንም ይፈፅማል። እንዲሁም በአንፃሩ ለክፉ ነገር ይነሣል የተሠራውን ያፈርሳል የነበረውን ይረሳል። ዛሬ በቤተ እምነቱ ያለውን ትርምስ ስንመለከት በእውኑ መንፈሳዊ ሥራ ነውን? በጎስ ተግባር ነው ያሰኛልን? የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአብዛኛው የምትታወቀው በትምህርቷ በብሔራዊነቷ በመልካም አርዓያነቷ ነው። የቤተ ክርስቲያኒቷ አባቶችም ሥጋቸውን በድለው ለመንፈሳዊው ሥራ ያደሱ ያጋደሉ ነበሩ። ዛሬ ግን ናቸው የሚለውን ማሠሪያ አንቀጽ ደፍሮ ለመናገር ራሱ ወንጀለኛ ያሰኛል። በመንፈሳዊው ሕይወት የሥልጣን ጉጉት እንደ ስበብ ተቆጥሮ የነበረውንና ተከብሮ የኖረውን ስሟን ማንሳቀያ አደረጉባት። ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለው ትውልድ ተነሣባት። መንፈሳዊው ሥልጣን ለመንፈሳውያን እንጂ ለዓላውያን አይደለም አይሆንምም። ቤተ ክርስቲያኗን ለማዳከም ደካማ ሰው መሾም ነው። ሠርቶ የማያሠራ ሰው ምንም ዓይነት የሥራ ፍሬ የማያሳይ ዘፍ እንኳ መቆረጥ እንዳለበት መጻሕፍት ይወተውታሉ። መንፈሳዊውን

ሕይወት ለሥጋዊው ዓለም ጋሻና መከታ ያደርጋሉ። ከውጭ ተሸንፎ ቢመጣ ሚስቱን በቁምጣ ለምን ቢባል የሚያሸንፋት እሷኑ ነውና ነው። እሁን የምናየው በተሰይ የፖለቲካ ድርጅቶች ቤተ ክርስቲያንን የእባብ መግደያ ብትር እድርገው ሲጠቀሙባት ይታያሉ። ውጤቱም እባብ የገደልህበትን ብትር ወደ ገደል ወርውር ነው።

ከዚህ ላይ የግብፅን ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በጥቂቱ ብንመለከት ትምህርት ይሆነናል ብዬ እገምታለሁ። ግብፅ በቅዱስ ማርቆስ የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን ናት። ከመጀመሪያ ምእተ ዓመት እስከ ስምንተኛው ምእተ ዓመት ድረስ ክርስትና ከዳር እስከ ዳር ተሠብኮባት የክርስቲያን አገር ነበረች። በስምንት መቶኛው ዓመተ ምሕረት ላይ ግን በአራት መቶ ሃምሳ አንድ የኬልቄዶን ጉባዔ በኋላ በክርስቶስ ባሕርይ አንድና ሁለት ምክንያት በአንድነቱ ባሕርይ ፀንታ ከካቶሊክ ከተለየች በኋላ ከእምነቱ ልዩነት ይልቅ የፖስቲካው ድጋፍና ተቃውሞ ምክንያት እርስ በርስ መጠላላት መነቃቀፍና መወጋገዝ ቀጥሎ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን ሳትሆን ሌሎችም በመካከለኛው ምሥራቅ አገሮች መካከል ይህ ነው የማይባል ከፍተኛ ጭቅጭቅና ክርክር ቀጥሎ በእምነትና በሥልጣን ውዝግቡ እንኳን ለእብያተ ክርስቲያናቱ ለፖለቲካው ዓለምም መበታተንን እስከተለበት።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የእስላምና ሃይማኖት ተመሥርቶ በክርስቲያኖች መካከል የነበረው ክፍፍል ለእስልምና እድገትና ሥርጭት ከፍተኛ እስተዋጽኦ አድርጓል። በተለይ ግብፅ የሆነው በጠላትነት የፈረጇቸውን ባለ ሁለት ባሕርይ ባዮችን ከርስቲያኖች ሙስሊሞች እንዲያጠቁላቸው በመፈለግ እስልምና ግብፅ ሲደረስ በከበሮና በዕልልታ ተቀበሉት። ከዚያ በኋላ ያልሰለመ የመንግሥት ሥራ እይዝም ወደሚለው ጠባብ ሕግ ሲመጣ ምርጫው መስለምና ሥራ ማግኘት ያሊያም በረሀብ ማለቅ ብቻ ነበር። የጸኑት የግል ሥራ ጀመሩ። በእምነታቸው ጠነከሩ። የቀሩት ሰለሙ። ዛሬ ክርስቲያኖች በግብፅ እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው። ቁጥራቸውን ያሳነሠው የክርስቲያኖች እርስ በርስ መከፋፈሉ መሆኑን ልብ ይሏል።

እግዚአብሔርን ለማገልገል እስኬማ አጥልቀው ቆብ ጭነው ቅናት ታጥቀው ዓለምን ንቀው ያሉና የነበሩ አባቶች ወደ ምንኩስና ዓለም ሲገቡ ጳጳሳት እንሆናለን ቤተ ክርስቲያናችንን እንመራለን ብለው ዕቅድ አውጥተው ምንኩስናውን እንዳልጀመሩት እነሱም

ያውቁታል እኛም እንረደዋለን። ይሁንና በመንፈሳዊውም ሆነ በዘመናዊው ትምህርት እባቶች እንዲማሩና እንዲሠለጥኑ ሲደረግ እዎ በዚያን ጊዜ ለዚህ እሁን ለደረሱበት ከፍተኛ ማዕርግ ሊበቁ እንደሚችሉ ይገምታሉ እንጂ እርግጠኞች እንኳ አይደሉም። አልነበሩም። አብዛኞቹ ደግሞ በአጋጣሚ ከነበሩባቸው ገዳማት በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ዋናው ከተማ ሲገቡና ደጅ ጥናት ሲጀምሩ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይነት ከዚያም የደብር አለቅነት ከዚያም እንደሁኔታውና አጋጣሚው ሁሉ ተደማምሮ ያልጠበቁትና ያልተመኙት ከፍተኛው ሥልጣን ከህነት በራሳቸው ላይ ጠለቀላቸው። ከእግራቸው ሥር ወደቀላቸው። ቢከብዳቸውም ባይችሉትም ቅሉ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተሾመን ማክበር ልማዱ ነውና ያልጠበቁትና ያላሰቡት ሕይወት ውስጥ ዘው ብለው ገቡ። ይህም ሚመት ያስ ድካም ያለ እንግልት ያስ ፈተና ያለ ውጣ ውረድ እንዲሁ በስጦታ በመገኘቱ የአያያዙም ሁኔታ ያን ያህል ጥንቃቄ አልተደረገስትም። የገቡትም ቃል ኪዳን እንደ ዘወትር ጸሎት እንዲሁ በቃል የሚነበነብ መስሎና ሆኖ ተቆጠረ።

በለዚህም ሲመች የሚይዙት ሳይመች ደግሞ የሚተውት መስሎ ታያቸው። እንዲያም አደረጉ። እስካሁን በታሪክ እንዳየነውና እንዳጠናነው አንሾምም ብቁ አይደለንም ብለው ከሚመተ ጵጵስናው ሸሽተው የቀሩ አባቶች ብዙ ናቸው። ከዚያም ከተሾሙም ወዲያ ሁኔታው እስቸጋሪ ሆኖ ሲያገኙት ወደ ገዳሞቻቸው ትተውት የሄዱና የገቡ አባቶችም ነበሩ አሉም። ከዚያ ውጭ ግን እንዲህ እንዳሁኑ እንደ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ በማያሻማ ቋንቋ በግልጽ በገዛ ፈቃዳቸው ሥልጣናቸውን እስረክበው የጡረታ መብታቸው ተከብሮላቸው መኪና እስከ ሾፌሩ ተመድቦላቸው ተቀምጠው መልቀቃቸውን በራዲዮና በቴሌቪዥን ተንግሮ እሳቸው ሥልጣኑን ካስረከቡ ካንድ ዓመት በኋላ ተተኪ የሚሆን አባት በምርጫ ከተሾሙ በኋላ ከዚያም እንድ ዓመት በድምሩ ሁለት ዓመት ቆይታ በኋላ ከነበሩበት በዓት ጥለው ጣጥለው ወደ ኬንያ ስደት ሄዱ። በኬንያ ከተወሰኑ ዓመታት ቆይታ በኋላ ወደ አሜሪካ መጡ። ከሌሎች አባቶች ጋር በመሆን ከተበረታቱ በኋላ ወደ ሥልጣናቸው ለመመለስ እንኳ ሳይሆን ከዚሁ ካሉበት ሆነው እኔ ነኝ ማለት እንደሚችሉ እበረታቷቸው። ሲኖዶስ አሜሪካ መጣ ገባ ሲሉ ያላንዳች ፍርሃት በድፍረት አወጁ። ኢትዮጵያ የለም የሚል ዜና ተፈጠረ። እነሱን ያጸደሰ ቅዱስ ሲኖዶስ ጎልውናው መኖሩ ተከዳ። ተፀሚ ሲከዳ ፀሚ እንዴት አይካድም። የተፈጥሮ ሞት የሌለበት የመንፈስ ቅዱስ የአንድነት ጉባዔ ጎልውና ተደመሰሰ። መንበሩን ለቆ አሜሪካ ገባ ብለው ሠበኩ። እንዴት ተብሎ አይጠየቅ መልሱ ብዙ ነው። ቢጠፋ

ቢጠፋ በታምር የሚል መልስ ማንም የማያንከባልለውና የማይገፈትረው ተራራ አለና ነው። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክነታቸውን ቃለ ምዕዳን በሚያሰጠብቸው በአካባቢው ራዲዮ ጣቢያዎች ማዕርጋቸውን ያነቡ ጀመር። ለካስ ለሌላው ዝግጅት ለማለማመድ ኖሯል። ለብዙኃኑ ግን የተረዳው ከሥልጣንም ቢለቁ ስሙን የሚጠሩበት እንጂ የሚሠሩበት አልመሰለንም ነበር። ቀስ በቀስ ሕጋዊው ፓትርያርክ የሚለው ቅጽል ተጨመረ። በአሜሪካ ሕግ ወይንስ በኢትዮጵያው ሕግ? አልተለየም። ሁሉም ነገር በምሥጢር ተያዘ። ነገር ግን ውስጥ ውስጡን እንዲያሰሙና ማንነታቸውን እንዲገልጹ ይደረግ ጀመር። በዚያው ቀጥሎ እነሆ አሁን ከደረሰበት ደረጃ ደረሰ። አሁን ይፋ ወጣ ኤሊስ ቆጸሳት ተሾሙ። እሳቸው ግን ተወገዙ። የመጀመሪያው በፈቃድ ሁለተኛው ግን በግድ ሆነ።

ቀደም ያለሽረት በምሕረት የተያዘው ጉዳይ ከመሥመር ወጣ። አሁን የመጣው ይምጣ ሆነ። ይህን ችግር ተዉ ይብቃ የሚለው ማነው? ቅልም ተሠብረ አሞራም በረረ ሆናልና! ቤተ ክርስቲያናችን እንኳን በሕይወት ላሉት ይቅርና ለሙታን እንኳ የምትጸልይ ከፈጣሪ የምታስታርቅ ናትና ከባድ አይደለም አይሆንምም። እንደገና ሊስተካከል ይችላል። ይቅር መበባልም አይጸንም። አሁንም በጎ ፈቃዱ ካለ ነው። በጎ ፈቃዱ ከሌለ ደግሞ ከጲላጦስ ዓቢይ ነገር ተምረናል። እሱም ዕጅን ታጥቦ ከበደላችሁ ንጹሕ ነን ማለት ነው። እነሱ እሺ ባይሉ ተተኪዎቹ እሺ ይላሉ። ካሉን የመጽናኛ ተስፋዎች ውስጥ ይህ አንዱ ነው። ይሁንና የዘወትር ጸሎታችን እግዚኦ ዕቀቦ [ጌታ ሆይ ጠብቀው] ብለን መጸለያችን ይቀርና ሌላ ይሆናል። እሱን ለእግዚአብሔር ነው የምንነግረው። ሰሚውም አድራጊውም እሱው ነውና ነው። ይህ አንዱ በጸሎት ፈልገን የምናገኘው ከርስቲያናዊ መፍትሔ ነው። በሰው ሰውኛ ግን የሚቻል ቢሆን ኖሮ እስካሁንም ይሞከር ነበር። አሁንም ከእነሱ የምንወጣ የምንገባ ምዕመናን ታላቅ ድርሻ አለን። ተዉ ይብቃ ወደ ሰላም ምጡ ብንል ተሰሚነት አለን። ምክንያቱም ካልሰሙ የማርያም መገበሪያው ወይንም ማርያም ባርኪው ፍሬ ግብሩ ይቋረጣልና ነው። ከሆነ የተባበሩት መንግሥታት ዓይነቱ ማዕቀብ ያልሆነ መጣልና በሥራ መዋል አለበት።

ምዕመናን በዚህ ሁኔታ ላይ ቤተ ክርስቲያናችንን እያየንና እየተመለከትን ዝም ብለን ማለፍ የለብንም። ለዚህ ችግር መፍትሔ መሻት አለብን። መቼም የነበረውንና ተከብሮ የኖረውን ቅዱስ ሲኖዶስ ብዙዎቹ አባቶች የተሠዉበትና ደማቸውን ያፈሰሱበትን በጸሎት በምህላና በጸም በጸሎት ተጠምደው ያቆዩትን ሲኖዶስ

መንበር መነቅነቅ ያውም ለግል ክብርና ዝና ተብሎ ለፖለቲካ ማድመቂያና ማሽብረቂያ ሊገነጠል ቀርቶ ሊነነተል አይገባውም። ቂም በቀልን አጥፍቶ አብሮ መሥራት እንኳን ለአባቶች ይቅርና ለተራ ምዕመን እንኳ ይቻላል። ከዚህ ውጭ ግን እነሱ አንታረቅም ሰላም አንፈጥርም ካሉ እኛም ሰላማችንን መንሳት አለብን። ምርጫችን ቤተ ክርስቲያናችን ወይንስ ሽማግሌ አባቶችን? ይህ አይሆንም። አለቃ እንዳሉት በቤተ ክርስቲያናችን ምንም ነገር ይሁን ምን ጤናማዋን ዘለዓለማዊቷን ቤተ ክርስቲያናችንን ነገ ከነገ ወዲያ በሚያልፉና በሚጠፉ ሥጋ ለባሽ አባቶች ብለን በምንም ታምር አንለውጣትም። አንድነቷ ይጠበቅ። ቅርንጫፍም ሆነ ሥር ወይንም ሕጋዊም ሆነ ኃያለ ኃያላን ሲኖዶስ አሜሪካ በቀል አንቀበልም። እንዲያው ከአሜሪካ የሚሠራውን ሁሉ ተቀባይነታችን ቢታወቅም ቅሉ ብለን ብለን የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን የሚከፍልና የሚሸረሽርን ምንም ይሁን ምን አንቀበልም። ምዕመናን ጥማ እንያዝ።

ተዉ አይሆንም እንበላቸው። እምቢ ካሉ እንኳን ሙዳየ ምጽዋታችንን መንሳት ይቅርና ዕጅና እግራችንን እንኳ መንሳት ሃይማኖታዊ ግዴታ አለብን። አሜሪካ ለበቀለ ሲኖዶስ ሕጋዊም ይበሉት ባለ «ግሪን ካርድ» በምንም ዓይነት የማሳደጊያ ቀለብ አንሰፍርም። ከብር ወግ ማዕርግ ከፈለገ ወደ ቤቱ ሥልጣኑ ከህነቱን ወደ ሠጠ ወደ አጸደሰ ሲኖዶስ ይመልሱት። እነሱም ወደ ሕጋዊው የጋራ ጉባዔያቸው ወደ ቅዱስ ሲኖዶሱ ተመልሰው ይቅር ይበባሉ እንመማር ተበዳድለናል ይበባሉ። ያለው ዕድል ይህ ብቻ ነው። ያለበለዚያ በሕይወት እያለን ሳንሞት ቤተ ክርስቲያናችንን ለጥቂቶቻችሁ ሹመትና ክብር ስንል ከፍለን አንሞትም። ጥላችሁት የመጣችሁትን ክብር ትታችሁትም የምትሄዱትን ምሥጢር በሰው አገር አንደ ካባ ደርቦ እንደ ቀሚስ አጥልቆ መልበስ መልካም አይደለም አያደምቅም አያሳምርም። ይልቁንስ ያንገት መነቅነቂያ የጠላት መሳቂያና መሳለቂያ መሆን ነው።

አሜሪካ የሚሠራ ሁሉ ዕቃ ኢትዮጵያ ልትሸምት አቅምም ጉልበትም የላትም። እንዲያው ሌላው ያላነሰን ደግሞ ጵጵስና ከአሜሪካ መጥታችሁ ታመርቱልን? ምነው ካቶሊኮችን አትመለከቱም? ምነው ግሪኮችን አትመለከቱም? ምነው እናንተን የሥልጣን ካባ ለማሰፋት ለመደረብ አስፈለጋችሁ? ይህ በሰው አገር ያውም በእንግድነት ያውም በስደት ይህን ያህል ዓቢይ ሥልጣነ ከህነት የምታውሉበትና የምታሳድሩበት ለመሆኑ ቦታስ አላችሁን? የትም ልታውሉት ልታሳድሩት? እቡስ ከፍተኛ ታላቅ ቦታ አለው።

ሲኖዶስ አይሰደድም። በሥጋም በነፍስም ስደተኛ አይሆንም። እመክሮውም ተግባሩም ጸሎቱና ምኞቱም ከቶ አይሆንም አይደረግም። እንኳን ቅዱስ ሲኖዶስን ያህል ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ወሳኝ ኃይል ይቅርና ጸሎተ ቆብዕ ጸሎተ አስኬማና ጸሎተ ቅናት ዘዮሐንስ መጥምቅ የተደረገለት አባት ከተወሰነለት ባዕት ውልፍትም አይልም ነበር። እነሆ እናንተ ብፁዓን አባቶቻችን አደረጋችሁት። በሩን ከፍታችሁ ለቀቃችሁት። እንኳን እኛ እነ አባታችን ተሰደዋል እየተባለ ማፌዣያና መቀለጃ ሆናችሁብናል። ግን ይንገር? ምን አገባኝ። እኛ ለቤተ ክርስቲያን ለሃይማኖቱ ከእነሱ ልንቀርበው ነውን? የመገላቱቻ ምጸት ሆኗል። መስታውት ሆነን ምን እንደምትመስሉ ልናሳያችሁ አልቻልንም። መስታውቱም የሚያሳይ እንጂ የማይናገር ሆነ። ፍጥረቱ እንደዚያ ሆነና ነው። አብረዋችሁ የሚውሉት ካህናትና ዲያቆናት ወደ ላይ አንጋጠ ማያት ሆነባቸውና በትሕትና ፍርሃት ተዋጡ። ቢሆን የሚያደርጉት ወጣ ብሰው ከእናንተ ጀርባ ቆመው ማማትና ማሳማት ነው። እንዲያ ከሚያደርጉስ ዕጅ ነስተው መስቀል ስመው ከተዘጋ ከፍል ቆመው አባቶቻችን የሚባለው እንዲህ ነው የምታደርጉትም እንደዚህ ነው። እኛም የምንላችሁ እንደዚህ ነው ብትሏቸው አይገድሏችሁም። ከሥራም አያባርሯችሁም። ምንም አያደርጓችሁምና አትፍሩ። ታዲያ ማን ይንገራቸው? ሃሜቱን እንደሆነ ሁላችንም እናቀልጠዋለን። ከየቦታውም እየሰማነው ነው። እኔም አባቶች ናዛዥ እንጂ ተናዛዥ ስላልሆኑ የልባቸውን ምሥጢር ለማንም አያካፍሉትም። እንደያዙትና እንዳስጨነቃቸው አሉ ይኖራሉ። ሁኔታው ቢመቻችላቸው በእውነት ቢነገራቸው የሚያምኑት ሰው ቢያገኙ እናዳምጥም ይላሉን? አይሉም ይሰማሉ ይቀበላሉ። በብ ፁዓን አባቶችም ዘንድ እውነተኛ በቃሉ የጸና ሰው ጠፍቶባቸዋል። የላቸውም ፈልገው ወጥተው ወርደው ተስፋ ቆርጠው ያሉበት ሁኔታ ላይ እንደሆኑ እንገነዘባለን። የሚመጣውና የሚነግራቸውም ምን ያስባሉ ምንስ ያደርጋሉ ብሎ ቀርቦ እንደ ፖሲስ ሊመረምራቸው የመጣ ስለሚመስላቸው የልባቸውን ከመናገር ይቆጠባሉ። ያው ከእግዚአብሔር በቀር የሚነግሩት ሰው የሌላቸው መሆኑን የምንረዳው ከሚያደርጉትና ከሚፈጽሙት ተግባር ነው። ሰው ለሰው መድኃኒቱ ነበር። ግን እነሱ ዘንድ ሰው ጠፍቷል። አጠፋፉም እንደ መብራት እልም ድርግም ብሎ ነው።

ነገር ግን ማን ይንገር ማን ይድፈር? እናንተም ካህናቱም ምንም ቅስና ቢኖራችሁ ቀድሳችሁ ብታቆርቡም ቅሉ እርስ በራሳችሁ እንጂ ጳጳስን ማቁረብ አይቻልም። ከዚህ ላይ ትከከል ናችሁ። ነገር ግን ካባው ተዘቅዝቋል ቀሚሱ ተገልብጧል ብላችሁ የምትናገሩ ከሆነ እኮ ይህንኑም ጠጋ ብላችሁ በለኖሳስ መንገር

ትችላላችሁ። እናንተ እኮ የቅርብ ሰዎች ናችሁ። ከመቅደሱ ከመንበሩ ላይ ሁሉ ተቀራርባችሁ ትነጋገራላችሁ። ከዚያም ውጭ ቢሆን ምን የማትወያዩት ነገር ከቶ አለ? የእነሱ እኮ ዓይንና ጆሮ እናንተ ናችሁ። ግፋ ቢል ቢቆጧችሁ እንኳ ያ መከረኛ ሠይጣን ሰምከንያት ስለሚሆን እንዲህ በል በል ብሎኝ ነው ብላችሁ ንስሐ መቀበል ነው። ነገር ግን እይሏችሁም እንዲያውም ይወዷችኋል ያከብሯችኋል ይባርኳችኋል። እኛ እንኳ ጣልቃ ገብተን ዕድል አግኝተን ለማመልከት ብንደፍርም እሱ ማን ነው? ቢያንስ ቢያንስ ደፋር የሚለውን ቃል ይዘን እንወጣለን። ይሁንና ሌባ ተፈርቶ ላይተኛ አይታደርም እንዲሉ የነና ነና እንዲህ እንባላለን ብለን ነገሮች ሲበላሹ ከነበሩበት ወደማይሆኑበት ቦታ ሲሸሹ እያየን ዝም ማለት ከርስቲያናዊ ሕይወት አይደለም። ስለዚህ እውነቱን ለመመስከር የግድ ግድ ነው። እንግዲህ ቢፈቅዱ ቡራኪያቸውን ካልወደዱ ደግሞ ርግማናቸውን ዕጅ ነሥተን ለመቀበል ዝግጁ ነን። በተለይም እኔ ቆርጨ የተነሣሁበት ስለሆነ እንዳደርገው እንድመሰክር እግዚአብሔርን በጸሎቴ በመጠየቅ ነው። የልቤን ጽዳትና መቆሸሽ ራሱ ይመለከተዋልና ለቤተ ክርስቲያናችን ስል እናገር ዘንድ የግድ ሆነ።

ብፁዓን አባቶች ሆይ! ለእናንተማ ቅንዓተ አዲም ዘዮሐንስ መጥምቅን የታጠቃችሁ ቆብዕ ዘሠለሥቱ ደቂቅን የደፋችሁና አስኬማ ዘኤልያስን ያደረጋችሁ ለበጎ ነገር ሁሉ ቀዳሚ አይደላችሁ። ታዲያ ብፁዓን አባቶቻችን የበጎ ነገር ሁሉ ጀማሪዎችና ፈፃሚዎች አይደላችሁምን? ለእናንተና ለቤተ ክርስቲያናችሁ በጎውን ሁሉ ማለት አንድነቱን ሰላሙንና ፍቅሩን ሁሉ እንደ ሽማ እንድንለብሰው እንደ ቀሚስ እንድናጠልቀው እንደ ካባም እንድንደርበው የቃለ ዓዋዲነታችሁን ሥራ ሁሉም ይጠብቀዋል። የመልካም ዛፎች ሁሉ ፍሬ እንዲለቀም ማን ያሳስብ ማን ይንገር? ማንስ ያውጅ? ይህን ማድረግስ አባታዊነት አዋቂነት አይደለምን? ይህን ሳያደርጉ መቅረት ችላ ማለት ምን ያህል የዋህነት ምን ያህል ሞኝነት እንደሆነ እንዴትስ ራስ ዝቅ ማድረግ እንደሆነ እንዴት ማየት አቃታችሁ? የሚባለውን የሚነገረውን ሁሉ እንሰማለን ቻልነው አሁን ግን እኛንም ቤተ ክርስቲያናችንንም በክርናችሁ አደቀቃችሁን አጎባቆላችሁን። ከእናንተ ሊነገር የማይገባው ጽርፈት ሁሉ ጆሯችንን ጆረፌ በጆረፌ አስበላችሁብን። የምናከብራችሁ በአባትነታችሁ እንጂ እንደኛው ሰዎች ሥጋ ለባስያን መሆናችሁን ከደን አይደለም። ባለችሁ ሥልጣነ ከህነት መከራ ተቀባዮችና የሐዋርያትን ሥራ ታደርጋላችሁ ለመከራም ቢሆን ራሳችሁን አሳልፋችሁ ትሠጣላችሁ ብለን እንጂ እንደኛው ነፍሳችሁን የምትወዱና ከመከራው የምትሸሹ ከዚያም አልፎ ተርፎ ሹመታችንን እወቁ እያላችሁ የምታብጡ ከሆነ ልዩነታችን ከምኑ ላይ ነው? ለእናንተስ ምን ዓይነት አርዓያነት ነው?

በሚዘንመው የፖለቲካ ዝናም የሚበቅለው የተዘራው ብቻ አይደለም። ሙጃም ሳይዘሩት ይበቅላል። ታዲያ በሌለን ፈረሰ ሙጃው ምን ያደርግልናል? እኛንም አታሥቀስቱን በጸሎታችሁ ባትረዱን እንኳ ተባበሩን። ከቅድስት ቤተ ክርስቲያን አትለዩን አትነጥሉን። ምዕመናን የዋሃን ፍቾው ምላሊያቸውም እንደ በጎች አይደል? ታዲያ እኩ በግ ከበረረ የሰው ልጅ ካመረረ ነውና በሁሰቱም ይመለከተናልና ተዉን ብላሙን ስጡን። በምንም ታምር ከቤተ ክርስቲያናችን አስበልጠን እናንተን አንመርጥም። ይህ ይታወቅልን። ተዉ አይሆንም እናንተን አንከተልም ያሉትንና ያልደገፉትን ምደባቸው የኢሕአዴግ ደጋፊ ነው እየተባለ የሚሰበከውን ስብከት የሃይማኖታችንን ቅስም መስበር ነው።

በእናንተ ምክንያት ደግሞ እሰጥ አገባ እንግባ? ያችን ዕስተ ሞታችሁን ቆቡንና ቅናቱን ያጠለቃችሁባትን ቀን መለስ በሉና አስቧት። እንኳን ለሃይማኖታችሁ እንኳን ለቤተ ክርስቲያናችሁ መሞት መገረፍ መከራ መቀበል ይቅርና ለምትጠብቋቸው በጎች እንኳ ራሳችሁን አሳልፋችሁ መስጠት ይጠበቅባችኋል። ከታሪክም ካሰው ሁኔታም አመክሮ ውሰዱ። በዓለም ዙሪያ ምን እንደሚሠራና እንደሚከናወንም ተገንዘቡ። ያስበሰዚያ እኛም ከአሜሪካ ያሰን እናንተን ሰሾመና ለሽለመ ቅዱስ ሲኖዶስ ታማኞች እንዳልሆናችሁ እኛም ከናንተ ዘንድ ያለንን ልጅነት በውግዘት ሳይሆን በትዝብት እንተዋችኋለን። ማንም የሚያውቅና የሚረዳም የሰም ብላችሁ የተማረውን ሕዝብ የሃይማኖቱ መሀይምን አድርጋችሁ ከተቀደሰው ቦታ ላይ ሆናችሁ ያልተቀደሰ ሥራ አትፈጽሙብን። ይህ መቼም እጅግ የሚያሳዝንና የሚያሰቅቅ ተግባር ነው። ታገሡ ተመለሱ ቤተ ክርስቲያናችሁን በአንድነት በሰላምና በፍቅር አወድሱ። ልዩነቱ እንኳን ስለናንተ ለመንፈሳውያን አባቶች ይቅርና ሰሥጋውያኑም አላማረባቸው። ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ሕይወት ሰላምና ፍቅር ስትሉ አንድ ሁኑ። ይህ እውነቱን በሐሰት ተሰውጦ የሚመገበው ሕዝበ ክርስቲያን መመገብ ያቆመ እንደሆነ በቃን ጠገብን ያለ ጊዜ ወዮ ያን ቀን! ሌላዋ እውነተኛዋ የሰደት ቀን ትሆንብናለች።

በሌላው ገጽታ የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አባቶች ሆይ! ቅዱስ ሲኖዶስ አንድ ነው። ቤተ ክርስቲያናችንም አንዲት ናት። ይህን እናምናለን ይህንኑም እንቀበላለን እንናገራለን እንመሰክራለን። ስደት ለወሬ ያመቻል ሆነና ከመካከላችሁ ወንድሞቻችሁ ወደ እግር ባደረሰበት በተለያየ ምክንያት ሀገረ ስብከታቸውን ትተው ቤተ ክርስቲያን ባልፈቀደችውና ባልሠጠቻቸው ሀገረ ስብከት ፈጥረው ምንም እንኳ

በበጀት በቤት እንኳ ማረፊያ ባይኖራቸውም እኛ ነን ካሉ ውሎ አድሯል። ፈቅዶና ወዶ ለሄደ አባትም ሆነ ወንድም በሄደበት እግሩ ይመልሰው ብላችሁ ዝም አላላችሁምን? ሲያጠፉ ብቻ ስትቀጡና ስትቆጡ ከማየት በስተቀር ወደ ምክሩም ወደ ስትቆጡ አንድነቱም ስትጸልዩ አላየናችሁም ሰምን? አንድ መንፈሳዊ ወንድም ከመንፈሳዊው ማዕድ ሳይገኝ ሲቀር ምን ሆነ አይባልምን? ይህንስ ብላችሁ ይሆናል። ነገር ግን ደወል ሲመህ ነጋሪት ሲመታ አልሰማንም። እንዲሁ ሰምን ይሄዳል ለምንስ ባዕቱን ይለቃል ተብሎ እንደ ወንጀለኛም መቆጠር የለበትም። መቼም ምክንያቱ ሁሉ ወደሚወረወርበት ወደዚያ መከረኛ ሠይጣን እናመካኝና አሰስቷቸው ቢሆንሳ? እሰቲ ብለን እናስብ። ይህ ሁሉ ግንዛቤ ተወስዶበታል? ጉዳዩ ተወስቶ ተነጋግራችሁበታልን?

እንዲያው ከሄደ ሄደ ከቀረ ቀረ ከቱውንና በጎውን ያውቃል ቢባልስ በሰውነቱ በአዳም ልጅነቱ ሲባል መሰሳቱ ያባት የናቱ ተብሎ ታስቦ በይቅርታ አይፈለግምን? እናንተስ ከዚያ ብትሆኑ ሰመንበሩ ብትቀርቡም ሰራቂትም የማቅረቢያ ዘዴ ፈጥራችሁ መመለስ አትችሉምን? ለተራበ ሰው ለምን እሳት ይሙቅ ብቻ ትሉታላችሁ? ሆድ ስባሰው አባት ለምን ማጭድ ታውሱታላችሁ። ማደሪያና መጠለያ እንግዳ እንዴት መዋያና ማደሪያ ትከለክላላችሁ? የእግዚአብሔር እንግዳ ተብሎ ከማይታደርበት አገር ያውም የሰው ሰው ያውም የነጭ ቋንቋው ካልተጠና የሚያነጫንጭ ምግቡ የሚሰነፍጥ የሰው ፊት እንደ እሳት የሚስግጥ ቦታ ላይ ውሎ ማደር ቀና የሚያስመስክት ይመስላችኋል? ቤቱ ሠፈ ነው አይጠባችሁም በማኅበር ኑሩ። በጎቻችሁን በፍቅር ጠብቁ። ለእኛም ቡራኬያችሁ እንጂ ጭቅጭቁስ ይቅርብን። ከሰኞ እስከ ዓርብ የምንውልበትና የምናድርበት ሥራችን ነው። እሁድን እንኳ እፎይታ እንዳናገኝ ውህውን አደፈረሳችሁብን። በወንጌሉ ፋንታ ስለ ሕጋዊውና ኢሕጋዊው ሲኖዶስ ነው የማሰረጊያ ጸሎቱ ሐተታ መናፍስቱ። እንዲያው እናንተ ዘንድ እግዚአብሔር እንኳ አይፈራም እንዳልል አብራችሁ በመዋላችሁ የታዘባችሁበት ጉዳይ ይኖራል ብለን ስለምንሰጋ በእናንተና በእግዚአብሔር መካከል ልንነባ አልፈለግንም። በዚህ እንኳን ልትታመሙ ይቅርና ስትመሠገኑም አልሰማንም።

ብፁዓን አባቶቻችን ሆይ! ምነው እኩ! ወላጆቻችንን ያሰሳተ ያ መከሮ ከእናንተ ዘንድስ በሩ ቢዘጋበትም ቅሉ ሲከፈት እንኳ ጠብቆ መግባት ያቅተዋልን? እንዲያስ አይሁንብን። ፍቅር ከጦር መሣሪያ ለአሸናፊነት ለድል አድራጊነት የበለጠ ኃይል የለውምን? ታዲያ ለምን በሱ ጠላትን አታሸንፉበትም። ከዚህስ ወዲያ በደል

ምን ይምጣ? ስለ ምልጃ ስለ ይቅርታ ስለ ንስሐ ስለ ሰላም ስለ ቤተ ክርስቲያኗ ህልውና ማሰብ ከእናንተ ከብፁዓን አባቶች ወዲያ ለመሆኑ የሚቀርብ አለን? የለም አይገኝም። ነገር ግን ማሳሰብ መወትወት የግድ ነው። እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ አሥራ ሁለት ጊዜና ከማዕ በእንተ ማርያም አሥራ ሁለት ጊዜ የተሰመደው ጸሎት የጸሎት አቀራረብ ነው። ይህም ሲሆን ኪራይላይሶን ዓርባ ዘጠኝ ጊዜና አሥራ ሁለት ጊዜ አቡነ ዘበሰማያትን መጸለዩን እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው። ስለዚህ ወደ አባቶቻችን የመቅረቡን ፀጋ ያገኛችሁ ሁሉ አባካችሁ ሳትሰለቹ ጧትና ማታ ቀጥሉ አትሰልቹብን። ያሰብነውን ሰላም እንድናገኝ በተስፋና በእምነት በርቱ። ይሆናል ይሳካል። ከዚህ ከገጠመን ፈተናና መከራ ቤተ ክርስቲያናችንን እናድናት።

አሁን አባቶችም እኛም ያለነው በሰው አገር ነው። ምንም ሕጋዊ መታወቂያ ደብተር ሠጥተውን ብንኖርም የሠጠ ዕጃቸው መልሶ የማይወስድበት ጉልበት ያንሰዋል አይባልም። አንድ ቀን አነሱንም ጠብ ጠብ ቢላቸው አንዲያው የኢሚግሬሽን ጽ/ቤት ቢቆጣ ውጡ ቢል እንደ ውሀ ሙላት ጠራርጎ ቢያስወጣን ወዴት ነው እግራችንን የምንሠነዝረው? ያን ጊዜ ነው ታምር ተፈፀመ የሚሆነው። ለምን ተናገር ተናገር እንዳለኝ ባላውቅም ፍርሃት አለኝ። የአሜሪካና የኢትዮጵያ ዝምድና ከጓደኝነት ዘሰል ብሏል። አባቶች ተጠንቀቁ። የምትሠሩትን እወቁ። ወደ ሰላሟ በር አባካችሁ ዝለቁ።

ብፁዓን አባቶቻችን በዚህ በአሜሪካ ቆይታችሁ ከቦታ ቦታ በመሸጋገር ካንዱ ደብር ወደሌላው በዝውውር ከታየና ከተጠና በኋላ በተገኘው ልምድ በተደረገው ስብከትና አመክሮ አሥር ዓመት መቆየት። በዚህ ሁኔታ በአሜሪካ መንበር መመሥረት ሆነ። እንደዚሁ የሩሲያዊዋ ቤተ ክርስቲያን እንደ አርዓያም እንደ ምሳሌም ትታይ ነበር። አነሆ ከእናት ቤተ ክርስቲያኗ ጋር አሏም አንድነት ፈጠረች። ታዲያ እኛስ እንደ አነሱ ወደ አንድነቱ አይመጣም? መልካም ምሳሌም ሆኑልን። የቤተ ክርስቲያናችን አንድነት ከምድራዊው ሕይወት የበለጠ ዋጋ የምንሠጠውና የምናከብረው ጉዳይ ነው።

እንደ አመክሯችን የተበደለ ስበደለ ጸልዮ በዚያም ላይ ይቅርታ ጠይቆ ቢያደርገው ያስከብራል ትሑት ያሰኛል። በምዕመናንም ዘንድ እጅግ ያስወድዳል ፈጽሞም ያስከብራል። ያለ ሰላሙ ያለ ፍቅሩ ሌላ ምንም ነገር የሚረባም የሚጠቅምም የለም።

የእናንተ የአባቶቻችን አንድነት ማጣት ለኛም ልቅሷችን ቅጥ ያጣ ይሆናል። እንደተባለውና እንደተነገረውም ሁላችንም እንደምናውቀው የልቅሷችን ዝዙ የሚሆነውና የሚባለው «የሞተውም ባልሽ፥ ገዳዩ ወንድምሽ፥ ኃዘንሽ ቅጥ አጣ ከቤትሽ አልወጣ።» ይሆንብናልና ተማለዱን አንድ ሁኑልን። እናንተኮ በሰምና በአካል እንጂ ልዩነታችሁ በሥልጣን በጉባዔ በአምልኮ በመንበር አንድ ናችሁ። ያውም የተዋሕዶ የአንድ ባሕርይ አባቶች ናችሁና ይሽው ይጽናልን ይፈጸምልን። የምዕመናን ልመና ምልጃ ልቅሶና ሥዕለት ማቅረብ ያለመሰልቸት ማድረግ ይገባናል።

ቀደም ሲል ለልዩነቱ አርዓያ ሆና የቆየችው የሩሲያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አሁን ለአንድነቱ ለሰላሙና ለፍቅሩ አርዓያነቷ ከተራራ ላይ ያስቀመጧት መብራት ሆናለች። ይህች የሩሲያዊዋ ቤተ ክርስቲያን ከእናት ቤተ ክርስቲያኗ ተለይታ አሜሪካ መንበር መሥርታ ቆይታ ነበር። አሁን እነሱም ያን ልዩነታቸውን አፍርሰው ግንቦት አሥራ ሰባት ቀን ሁለት ሺህ ሰባት ዓመተ ምሕረት [5/17/2007] እንደ አውሮጳውያን አቆጣጠር አንድ ሆኑ። ይህን የአንድነት በዓል የሩሲያው ፕሬዚዳንት ፑንት በተገኙበት መስኮብ ከሚገኘው በመድኃኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በታላቅ ድምቀት ተከበረ። በበዓሉም ላይ በፓትርያርክ አሌክሰ ሁለተኛ የሩሲያ ፓትርያርክና በአሜሪካ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት የበላይ ኃላፊ የሆኑት ላቭር የአንድነቱ ቃል ኪዳን ፀና። እንኳን ደስ ያላችሁ። ይህን ዜና የሰማሁት ይኽን የአቤቱታ ደብዳቤ እየሞነጫጨርሁ ባስሁበት ጊዜ ስለሆነ እጅግ ደስ የሚል የምሥራች ድምፅ ተሰማኝ። ፈቴ በኃዘን ጠውልጎ የነበረው ዙፋ ጨንቧ አለ። የኛም አባቶች አሜሪካ ሲቀር መንበሩ የሚቀር ቢሆንም ቅሉ በሕይወታቸው እያሉ ታሪካቸውን ቢአድሱ እንዴት መታደል ነበር? ብዬ ተመኘሁ። አቤት ልልበት የነበረውን የእንጉርጉሮ ቅላጼ ሁሉ በል ተወው ሲሆን ወደ አንድነት ነገ ከነገ ወዲያ ይመለሱ ይሆናል። ካልሆነ ደግሞ ከእነሱ በኋላ በሁሉም ዘንድ ወደ አንድነቱ ይመጣል የሚል የተስፋ ድምፅ በጆሮዬ ሰማሁ። እኔም ያስ ባይሆን እነሱ ለዘለዓለም አይኖሩ ብዬም ተጽናናሁ። ነገ ከነገ ወዲያ ልዩነቱ ይመዘበራል ይቀራል ኃዘንህንና ልቅሶህን አቁም የሚል መንፈስ መጣልኝ አበረታታኝ አጽናናኝ። ይህን የሩሲያን ቤተ ክርስቲያን ተክፍሎ መኖር ሳስብ ለኛም ሰዎች አርዓያነቱን አልወደድሁትም ነበር። ስለሆነም አንዲያው ይኸው የሩሲያም ቤተ ክርስቲያን ተከፍላ ትኖራለች ምን ሆነች? ተከታይ አስካለ ድረስ ይባላል ብዬ ሠግቼ ነበር። ነገር ግን የአግዚአብሔር ታምር ቀደመና ቦታ ያዘ። እኛም እንደዚሁ የቀረው ይቅር ለቤተ ክርስቲያናችን ክብር ብቻ ሳይሆን

እንድትኖር የሰላሙ ነገር የሕይወት እስትንፋስ ነው። ከዚህስ በኋላ የሩሲያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ለአንድነት እንጂ ለመለያያ ምሳሌ አትሆንም በቃ አከተመ። ተመስገኑ አጋዕዝተ ዓለም ሥላሴ! አልሁ።

ታዲያ ይህን ምሥጋናም የኛዎቹ አባቶች ወደ ሰላም መጥተው አንድ ላይ ሆነው ስብሐቅ ወክብር ለሥሉስ ቅዱስ ይደሉ ብለው ማዕጠንተ እግዚአብሔር ያቀርቡ ይሆን? በእግዚአብሔር ማዕድስ አብረው ይሳተፉ ይሆንን? በሕይወት እያሉ እኛም እያሰን እናይና እንሰማ ይሆን? መቼም ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር ከቶ የለምና ይችን ቀዳሚት ወደኃሪት ፈተኛዋም ኃለኛዋም ቤተ ክርስቲያን አባቶች ወንድሞች በአንድ መቅደስ ስብሐተ እግዚአብሔር ሲያደርሱ እናይ ይሆናል። «ቅሩብ እግዚአብሔር ለየውሃነ ልብ» [እግዚአብሔር ቅን ልቡና ሳላቸው ሰዎች ቅርብ ነው ማለት ልመናቸውን ፈጥኖ ይሰማላቸዋል። መዝ. 33:18] እስቲ እናቶችና አባቶች እግዚአብሔርን ጠይቁ። ልመናችሁን ይሰማዋልና ቸል አትበሉ። የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ነውና!

ብፁዓን አባቶች ሆይ! መቼም አቤት ባይ ማመልከቻ ሲጽፍ የሚያገኘውን ብቻ እንዲሁ አይጠይቅም። እግዚአብሔር ያሳይዎት ክርስቶስ ያመልክትዎት ብሎ የምኞት ጸሎቱን ካቀረበ በኋላ ወደ ጉዳዩ ጨርሶ ከመዝለቁም በፊት አቤቱታ ተቀባይን ፍርድህ የቀና በሰዎች ዘንድ ሞገስን ያገኘህና ያለህ መሆንህን ስለማውቅ ትክክለኛውን ፍርድ እንደምትሠጠኝ በሙሉ እምነት ነው ብሎ አይደል የሚያቀርበው? አዎ! መወድስ የሚያበረክት ባለ ቅኔ ሲጀምርስ «ፍታሕ ሲተ እግዚኦ ወተበቀል በቀልየ» [ጌታዬ ሆይ ጠላቴን ተበቀል ፍርድህንም ስጠኝ።] ብሎ አይደል የሚጀምር? እንግዲህ አመክሯችን መቼም ዕፁብ ድንቅ ነው። እኔም በዚሁ መልክ ነው በማቅረብ ላይ ያለሁትና አዳምጡኝ። አቤቱታዬን እትናቁብኝ። ልመናዬንም አታቃሉብኝ እላለሁ።

በአሁኑ ሰዓት በዚህ ዘመን ያውም በዚህ በአሜሪካና በአውሮጳም ጭምር ስንት ምርምርና ጥናት የሚደረግበትን ጊዜ ስንት እጅግ ዕፁብ ድንቅ የሆኑ መምህራን የጥንቱንም ዘመናዊውንም እንደ ሐርና ወርቅ አስማምተው የሚያመርቱ ሊቃውንት በመጥፋትና በመመንመን ላይ በሚገኙበት ሰዓት ያላቸውን እውቀትና ጥበብ ወይ በቃል ያሊያም በጽሑፍ የሚያሠፍሩበትን ጊዜ በዕለት ዳቦ ፍለጋ እያባከኑት ነው። ታዲያ ይህ ሁኔታ በግልጽ እየታየ ባለበት ሰዓት ምዕመናኑን አሰባስባችሁ ድርጅት ፈጥራችሁ ሲቃውንቱ የሚረዱበት

ቤተ ክርስቲያናችን የምትጠነክርበትን ፈልጋችሁ ቅርስ ማስቀረት ሲገባችሁ በዚህ ፋንታ ሕጋዊ ሲኖዶስ አቋቁማችሁ ከወንድሞቻችሁ ጋር ጥልና ክርክር ፈጥራችሁ ለመልካም ነገር የተፈጠሩትን የሰው ልጅ ግኝቶች ራዲዮና ቴሌቪዥን ኢንተርኔት የጽርፈት የሙግትና የክርክር መወርወሪያ በቀላሉ አነጋገር መሰዳደቢያና መዘላለፊያ ማድረግ ያልደከማችሁበትን አንድ የምዕመናንን ገንዘብ ማበላሸት ሌላው የእናንተን ክብር ዝቅ ማድረግ መሆኑን እንዴት የሚያይ ዓይን የሚያስተውል አእምሮን ማን ቀማችሁ ማንስ ወሰደባችሁ? ሲኖዶስ ከማቋቋም ይልቅ የሊቃውንት ድርጅት ብታቆቁሞ ኖሮ እናንተም ተወድሳችሁ ክብራችሁም በዝቶ መልቶና ተርፎ ቤተ ክርስቲያኗም አገራችንም ተጠቅማበት በነበር። አንድ ቀን የአብነት ትምህርት ቤቶች ይ ጠናከሩ። የግዕዝ ቋንቋችን ይጠና። የዓይን መክፈቻ የሆነውና በዓለም ላይ በዓይነቱና በመልኩ ልዩ የሆነውን የቅኔን ትምህርት ምዕመናን አግዙ ብላችሁ ት/ቤቶች እንዲከፈቱ አድርጋችሁ አስባችሁ ሠብካችሁ አስተምራችሁ ታውቃላችሁን? ከዚህስ የበለጠ ምን እጅግ ዕፁብ ድንቅ ሥራ በምድር ላይ አለ?

ይህን የመሰለውን ታላቅ መንፈሳዊም ሥጋዊም ታላቅ ሥራ ትታችሁ እጅግ በጣም የሚዘገንን ነው ሕጋዊ ሲኖዶስ የእናንተን ክብር ዝና ማስጠበቂያ በፓትርያርኩ ላይ መፈንቅለ መንግሥት ተፈፀመባቸው እግዚኦ በሉ። የአዲስ አበባው የቅዱስ ሲኖዶስ አባላት «ጋንግስተሮች» ናቸው። የዋሽንግተን ዲሲ ካህናት «ፊናፊንታሞች» ናቸው። ከሕጋዊው ሲኖዶስ አባላት ያውም ከትልቁ አባት የሚተላለፈው መልእክት ይህ ነው። ስለ ራሳችሁ ሥልጣን ማጣት እንዲህ ሌት ከቀን እንደምትሮሁ ሰዓታት ኪዳኑ ቀርቷል ማለት ነው እኮ! እንኳን ኪዳኑ የዕለት ውዳሴ ማርያምስ መድገም የሚቻልበት ጊዜ አለ ይኖራል? እንዲያው የዲዮቅሲጥያኖስን ዘመን እንመኝላችሁን? እጅግ ተጎሣቆልን እጅግ አረርን ከሰልን ትቢያውን ነስነሳችሁብን። የቤተ ክርስቲያናችንን አንድነት ደሙን አፍሰችሁ አጥንቱን ከስክሳችሁ በየመንገዱ አልበተናችሁትምን?

እንዲያው ለኛ ሕጋዊው ሲኖዶስ ከዚህ አቆቋምነላችሁ ጳጳሳት ሾምንላችሁን ምን አመጣው? የኛ ችግር የኛ ረሀብ ጳጳሳትን ማጣት ነውን? አለቃ ገብረ ሃና አሉ የሚባል ምሳሌያዊ አነጋገር አለ። ከሰው ቤት ተገኝተው ባለቤቱ በዱላ ይዞ ሲቀጠቅጣቸው የሴት ያለሽ! የሌቶች ያላችሁ! እያሉ ሲሮሁ የሰማ ሰው የወንድ ያለህ ይበሉ ሲላቸው አይ! ወዳጄ አንዱ ሲያበቃኝ ደግሞ ሌላ ልጨምር? አሉ ይባላል። እናንተ መከራችንን እያሳያችሁን መች እነሰና ሌላ

እንጨምር። ችግራችንን አላወቃችሁትምሳ! እኛ ያጣነው እኛ የተራብነው የሰላም አባት የፍቅር አባት ስምምነት ወንድማማችነት አባትና ልጅነት እንዲሁም አንድነት ነው። ራበን ስንል እባቡን ዓሣ ነው እንኩ ብሉ ትሉናላችሁ። ማን በይ ማን ተበይ እንደሚሆን ባናውቅ ተመርዘን አልቀናል። ከናንተ ይህን የመሰለውን በጠታ ነውን የምንጠብቀው? «ዝንቱ ውእቱ ሥጋሁ ለአማኑኤል» [ይህ የክርስቶስ ሥጋ ነው] እያላችሁ በምታቀብሉበት ዕጅ እንዴት እባቡን ዓሣ ነው ብላችሁ ትሠጡናላችሁ? በዚህ ሁኔታ በእባብ ተነድፈንና ተመርዘን ብንሞት እናንተን በሁለተኛው ሞት ማስገደል አይሆንምን? ባይሆን ጽደቁብን እንጂ አትኮንኑብን።

አሁን የያዛችሁት በዘመኑ የአንጋገርና ቅላጼ የትግል ስልት ትክክል አይደለም። መቼም የሚጠይቅ የለም ቢኖርም ትቀሠፋለህ ሠይጣን አድሮብሃል ስለሚሆን መልሱ በመፍራት ዝምታ ተመርጧል። ነገር ግን አሁን የምታደርጉትን በእውነት ለማድረግ የምትሹ ቢሆን ኖሮ በመጀመሪያ ላይ ለምን ሹመቱን አንለቅም ብላችሁ አላንገራገራችሁም? አልተፈራገጣችሁም? አልጮኻችሁም? ለጋስ ደግ በአማን ብፁዕ ለመባል ነውን? በሰውኛም ብቻ ሳይሆን በእግዜሩም መንገድ ባትሄዱበት ታዩታላችሁና እንዲህ በዓይን ውስጥ እንደ ገባ በርበሬ ሲቆጠቁጣችሁ ለምን አሁንም በድጋሚ እንጠይቅ ያችን ሰዓት አሳለፋችኋት? ጴጥሮስም እኮ ዶሮው ከጮኸ በኋላ ነው ነገሩን የገለበጠው እንጂ ተመሳሳይ አቋም ወስዷል። በአርዓያነት ከተጠቀሰ እንደሱ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው እንደዚያ መሆን በተገባ በነበር። በምትቀመጡበት ሰዓት ያልጮኻችሁ ርዳታ ያልጠየቃችሁንን አሁን ጅብ ከሄደ ውሻ ይጮሃል አልሆነም ወይ? ሾማችሁ ተስማምታችሁ ቃል ኪዳን አስገብታችሁ ቦታችሁን አስረክባችሁ መጥታችሁ እንደኛው እንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በስደት ለመኖር ከወሰናችሁና ከዚህ ከደረሳችሁ በኋላ መንግሥት ምሰረታን የናንተ መንግሥት ሲኖዶስ መሆኑ ነውና ነው ለመሆኑ ምን አመጣው? ይህን ኃሳብ ምኑ አቀበላችሁ? መቼም በዚህስ መንፈስ ቅዱስ አይታማበትም ባይሆን ያ መከሮ የቆሮንቶሱ ሰው በሆነውም ባልሆነውም የሱ ስም ካልገባ ሌሊቱም አይነጋ ነውና! እሱ ይሆን ይሆናል እንጂ! ሌላማ በዚህ ጉዳይ ተጠርጣሪ ሊኖር አይችልም።

ለምን ከከቡር ሌተና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም ትምህርት አትወስዱም? ለምን እሳቸው ወደ ኩባና ሩሲያ አምባሳደሮች ሾመው አላኩም? ለምንስ ዝምባብዌ ውስጥ የስደት መንግሥት አልመሠረቱም? ሚኒስትሮችንስ አልሾሙም? ብልሃቱና እውቀቱ አልኖራቸው ብሎ ነውን? የሚሆንና የሚደረግ ቢሆን ኖሮ እጅግ በጣም ንቁና ብቁ አዋቂ ናቸው። በዚህ አልታመሙም በጣም

ፈጣን ነበሩ። ማንም አይቀድማቸውም ነበር። ነገር ግን ከወደቁ ወደቁ ካለቀ አለቀን ስለተረዱ ነው። ይህ ዓይነቱ አስተላለፍና ምርምር ግን ከአናንተ ዘንድ ታጥቦ ጠፍቷል። ምናልባትም ገና መወለድ ቀርቶ አልተፀነሰም ነበር። እንዲያው ለለ ትንሣዔ ሙታን ስለምታስተምሩ በዚያው ዓይን ተመክልታችሁት ይሆናል። መቼም እናንተን የተመለከተ በጣም ይገረማል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያላደገቻችሁ እናታችሁ ናት። አሁን በምታደርጉት ሥራ ውለታ መክፈላችሁ ይሆን? አሜሪካ መጥታችሁ ቤተ ሠራንልሽ ወይንስ ራስሽን ለሁለት ገመስንልሽ? መታወቅ ያለበት ግን ቤተ ክርስቲያኗ ትኖራለች እናንተ ግን ነገ ከነገ ወዲያ በሞት ጥላ ትጋረዳላችሁ። ይህ ደግሞ የተፈጥሮ ግዴታ ስለሆነም ነው የምናገረው። የእናንተ መኖርና ያለመኖር ጉዳቱም ሆነ ጥቅሙ ለቤተ ክርስቲያኗ ነበር።

አንድ የከተማ ወይዘሮ የገጠሩን ኑሮ ብዙም ያላወቁ ኖሮ ወደ ገጠር ሲሄዱ ገበሬው ያርሳል አለፍ ሲሉ ደግሞ አዝመራ ያጭዳል። ነገሩ ግራ ገብቷቸው ኧረ! ይህ ገበሬው እንዲያው መቼ ነው የሚያርፈው? ብለው ይጠያቃሉ። አመቤቴ እሱማ ሲሞት ብቻ ነው የሚያርፈው ሲሏቸው እባክህን ፈጣሪ ሞቱን አቅርብለት አሉ ይባላል። እኒህን ወይዘሮ አብነት አድርገን የእኛንም ቅላጼ እንዲያ እናድርገው? ሌሊት በጸሎት ቀን በቅዳሴ ከዚያ መልስ ማስታወቂያ በመጻፍ ስልክ በመደወል እንዲህ ብላችሁ ስበኩ ይህን ለምዕመናን ተናገሩ የሚለው የስልክ ስብከት እንቅልፍ ነስቷችኋል። መቼ ይሆን የምታርፉት? እንጸልይላችሁን? ወይንስ እንዲህ ቤተ ክርስቲያኗን በታውኩ ምዕመናንን በትወግሱ እያየን እንዳላየን ዝም እንበል? ምክሩን ምን እናድርግ?

እንዲያው ለመሆኑ ይህን የሕይወት ጎዳና ስትጀምሩ ምን ብላችሁ ነበር? «መኑ የኀድገነ ፍቅሮ ለክርስቶስ። ሕማምኑ ምንዳቤኑ ተሰዶኑ ረኃብኑ ዕርቃንኑ መጥባሕትኑ ጸዕርኑ።» [የክርስቶስን ፍቅሩን ማን ያስተወናል። መከራ ነውን። ጸዋትወ መከራ ነውን። ሀገር አስጥለው ቢሰዱን ነውን። ምግብ ቢነሱን ነውን። ልብሳችንን ቢገፉን ነውን። በሾተል ቢያስፈራሩን ነውን። ጭንቅ ጭንቅ መከራ ቢያመጡብን ነውን። ሮሜ. 8:35] ይህ አበባል የአባቶች መንፈሳዊ ፉከራቸውና የቃል ኪዳንቸው አባባል ነው። ታዲያ የት አለ በሥራ የተተረጎመው? ስደት ሲመጣ ምልጥ። ሾተሉ ላይሆን የሽጉጡ ማጎደር ከመጽሐፉ ማጎደር መልኩ ሲለይ እግዚኦ አድነን ረሀቡ ሲመጣ ትንሽ ዳቦ በለነፍስ መታረዝማ በየት አልፎ። ጭንቅ ሲመጣ አባት ሆይ ከዚች ጭንቅ አድነኝ አውጣኝ ሠውረኝ።

ለሰሚና ለተመልካችም ግራ የሚያጋባ ነው። መጽሐፉ ሌላ በተግባር የምናየው ሌላ መንገዱ እንኳ አንዱ ባንዱ ላይ አያቋርጥም። እንዱ በላይ አንዱ በታች ማዶ ለማዶ የሚተላለፍ እኛስ ምን እንበል? ይህ ቅዱስ ጳውሎስ ለራሱ ብቻ ነበርን የተናገረው? የኛምችን ብዙዓን አባቶችን አያጋራምን? ለካህናቱ አያካፍልምን? እሱስ ታሥሮ ቴንገላቷል። ከመካከለኛው ምሥራቅ ሮም ድረስ በእሥረኛነት ተጉዞ ሮም ላይ ለቤተ ክርስቲያኑ በገባው ቃል መሠረት አንገቱን በሠይፍ ሥቀልቶ እንደ በግ ታርዶ ሩጫውን ፈጽሟል። የገባውን ቃል ኪዳን በትክክል ፈጽሟል። ሞትን ለፈሩስ ቢኖሩሳ ምን ይላቸው ነበር? ሌላ ያለውን ለእንዲህ ላሉት ሠባክያነ ወንጌል ያለውን እንናገር? ምች ማስመታት ይሆናል እንዲያውም ምች አደሩ በዝቷል የሚያነብ ያንብበው።

ብዙዓን አባቶች ካህናት ምዕመናን ሁላችንም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ኃላፊዎች ተከታዮች ቤተ ክርስቲያን ተሳላሚዎች በሙሉ ስለዚህ ዋንኛዊት ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን እንጠንቀቅ አባቶቻችን እንዳስረከቡን ጠብቀንና ተንከባክበን ማስተላለፍ ሃይማኖታዊ ብሔራዊ ሰብአዊ ግዴታዎች አሉብን። በእግዚአብሔር ዘንድ አለቃና ዋፍራ የለም። ሁላችንም እኩል ነን። ይህም ሲባል መከባበር ይረሳ አይደለም። የበለጠ መሆን ያለበት መፈፀም ያለበት እንጂ! ይሁንና አሁን የት ነው ያለነው? በዚች ቤተ ክርስቲያን ላይ የምንሠራው የምንፈጽመው በእውነት ስለ እውነት የሚጠበቅብንን ነው? ወይንስ ይህን ዓለም ስንኖር ዋኝተን የምንወጣበትን አቋራጭ ብቻ ወንዝ ተሸግሯል ለመባል ነውን? እናስተውል እንመልከት እኛ ዘለዓለማዊ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደለም። በትንሽ ነገር መተንፈስ የምቷቋርጥ አጅግ በጣም በጥቂት ነገር እንዳልነበረች የምትሆን ሥጋ ላይ ነው ውለን የምናድረው። በጥሞና ካሰብንበት ለምን እጨነቃለሁ? ለምንስ እንገላታለሁ ሳይሆን ለምን ክፉ ሥራ በመሥራት እታወቃለሁ ብለን ራሳችንን መጠየቅ ይገባናል። አቤቱታው ለበጎ ነገር አርዓያ አንሁን ነው።

ስለዚህ ምን እናድርግ? እነሆ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይለናል። «ወአንስ እብለክሙ አፍቅሩ ጸላኢተክሙ ባርክዎሙ ለእለ ይሰዱድክሙ ሠናየ ግበሩ ለእለ ይጸልኡክሙ ወጸልዩ በእንተ እለ ይትዔገሉክሙ» [እኔ ግን እላችኋለሁ ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሙአችሁንም መርቁ ለሚጠሉአችሁም መልካም አድርጉ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ። ማቴ. 5:44] ከዚህ ወዲያ ምንም ዓይነት ቃል አያስፈልገንም ይህ እጅግ በጣም በቂ ነው። ስለሆነም

የጥላቻ ኮረጆ ይተርተር። ሰላምና ፍቅር ይዳብር። የቤተ ክርስቲያናችንን ህልውና እናስከብር። ጥላችንን በንስሐ እንጠብ። በእንድነት እንኑር። የአባትና የልጅነታን ትስስር ይጥበቅ። ልጅ ሲያጠፋ አባት ይምከር። አባትም ሲሰሳት ልጅም ይንገር።

ይህን ቃል መመሪያችን ካደረግን የምንጠላቸውን ከወደድን ምን ችግር አለብን? ይህ ደግሞ አሜሪካ አውሮጳ አውስትራልያ አፍሪቃ ኤሲያ ኢትዮጵያ መበባል ሳይኖር እንዲት ሃይማኖት እንዲት አገር ያንድ ሰው ዘር ነንና ፍቅራችንጓንድነት ይማገር። ለየግል ለየብቻ የምንሠራው መነጣጠሉ ለኛ ሳይሆን የሚያገለግለው ቤተ ክርስቲያናችንን ለሚያጠፉትና ለሚመዘብሯት ብቻ ነው። አሳዳጅም ተሰዳጅም አይኑር አንድ ቃል አንድ ጉባዔ አንድ ማኅበር በዚህ ጉዞ እንቅጥል። ይህን ብናደርግ የዘራነው ይበቅላል አድጎና አፍርቶም ይበላል። ሁሉን ለማድረግ የማይሳነው ሕያው እግዚአብሔር በሰላምና በፍቅሩ ይጎብኘን። ጥልንና ክርክርን ከመሃላችን ያጥፋልን። መንፈስ ቅዱስን ያቅርብልን ሠይጣናትን ያርቅልን። በመጨረሻም ብዙዓን አባቶቼ ከቡራን የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ካህናት ምዕመናን በጠቅላላው ኢትዮጵያውያን በሙሉ ለአገርና ለሃይማኖቱ መቆም መጠበቅ ውሳጣዊ ፍላጎት እንጂ አድርግ ሥራ ተብሎ የማያዝዙት ጉዳይ ነው። ማንም ከማንም አያንስም አይበልጥም ሁሉም ለአገሩና ለቤተ ክርስቲያኑ ያስባል ስትነቀፍ ይከፋል ስትወደስ ይደሰታል። ይህን መሠረት በማድረግ አባቶቼን እናቶቼን ወንድሞቼንና እኅቶቼን በአጸጸፌ ባንጋገራ ያስከፋሁት ቢኖር ቂም በቀል አትያዙብኝ። ይቅር በሉኝ። ዓላማዬ ለአገራችንና ለቤተ ክርስቲያናችን ቀናዒ በመሆን እንጂ! በጥላቻ ሰው ለመጉዳት ብዬ ያደረግሁት ያለመሆኑን በድጋሚ በእግዚአብሔር ስም አረጋግጥላችኋለሁ። ምን አገባህ ምን ዶለህ? የሚሉ ቢኖሩ የተሠጠችኝን መክሊት ወስጀ ብቀብራት መልካም አይሆንልኝም ብዬ ነው። ከዚህ ውጭ የሚጨመርም የሚቀነስም ምክንያት የለኝም። አረረም መረረም እነሆ! ማኅበሬን ተወጥቻለሁ።

የሰማይና የምድር ፈጣሪ አምላኬ ሆይ! ኃይሉን ድፍረቱን እውቀቱንና ጥበቡን ሠጥተህ ይህን እንድናገርና እንድመሰክር ስለ አደረግህ ምስጋና ለአንተ ይሁን። «አነ ኃጥእ ወአባሲ» እኔ ኃጢኣተኛውና በደለኛው አገልጋይህ ለይኩን ብርሃኑ።

ተፈፀመ።

ዋቢ መጻሕፍት

ሀዲስ አለማየሁ፡ *ሀዲስ አለማየሁ ትዝታ* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማ/ቤቅ 1985

ሀጎስ ዓለማየሁ፡ *ሀገረ እግዚአብሔር ወሕዝበ ኢትዮጵያ*፣ ዋሽንግተን ዲሲ 1994

ሰይኩን ብርሃኑ፡ *ዐፀት* ዋሽንግተን ዲሲ፣ ፈጣን ግራፊክ ማ/ቤት 1993

» ለምንት አንገለጉ አሕዛብ ጌይትስ በርግ ሜሪላንድ ሲግኔቸር ማተሚያ ቤት 1996

» የግዕዝ መማሪያ ጌትስበርግ ሜሪላንድ ሲግኔቸር ማተሚያ ቤት 1997

ሉሌ መልአኩ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት 1997

መሐሪ ትርፌ [ሊቀ ሊቃውንት] ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ፣ *የቅዱስ ጳውሎስ መጽሐፍ ንባቡ ከነትርጓሜው* ሁለተኛ እትም አዲስ አበባ፣ ቴት. ዘ. ማ/ቤት 1982

መልክአ ሕማማተ መስቀል አዲስ አበባ 1977

መዝሙራት ዘዳዊት፡ አሥመራ ኩከበ ጽባሕ ማ/ቤት 1968

መጽሐፈ ቅዳሴ፡ አሥመራ ኩከበ ጽባሕ ማ/ቤት 1968

መጽሐፍ ቅዱስ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት አዲስ አበባ፣ 1980

ማኅተመ ሥላሴ ወልደ መስቀል [ባላምበራስ] *ዝክረ ነገር*፣ አዲስ አበባ፡ ነፃነት ማ/ቤት 1942

ሰዋስው ግዕዝ፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማ/ቤት1992

ቃለ ዓዋዲ የሠበካ መንፈሳዊ ጉባዔ ደንብ አዲስ አበባ፣ ቴት. ዘ. ማ/ቤት 1991

ብሉይ ኪዳን ሰመንቱ ብሔረ አሪት፣ አዲስ አበባ ት. ዘ. ማ/ድርጅት 1994

ብርሃኑ ገብረ አማኑኤል [ሊቀ ካህናት] ተሾመ ዘሪሁን [መልአከ ታቦር]ና ሌሎችም አዘጋጆች፡ *የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትናንትና ዛሬ*፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማ/ቤት 1990

ተአምረ ኢየሱስ በልሣነ ግዕዝ፣ አዲስ አበባ፣ ተስፋ ማ/ቤት 1990

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፡ *ዓፄ ቴዎድሮስ እና የኢትዮጵያ እንድነት*፣ አዲስ አበባ፡ አርቲስቲክ ማ/ቤት 1981

ታደሰ ወ/ጊዮርጊስ [ዶ/ር] *የምዕራባውያን ሥል ጣኔና ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ ማኅበራዊና ሥነ ልቡናዊ ትንተና*፣ ሲግኔቸር ማተሚያ ቤት ሜሪላንድ ጌትስበርግ 1999

አስረስ የኔሰው፡ *የካም መታሰቢያ የኢትዮጵያ ፊደል መሠረትነት መታወቂያ*፣ አሥመራ፡ ኩከበ ጽባሕ ማ/ቤት 1951

አባ ገብርኤል [ሊቀ ጳጳስ]፡ *ክብረ ቅዱሳን*፣ አዲስ አበባ፡ ግራፊክ አታሚዎች 1990

አባ ሳርጎርዮስ [ሊቀ ጳጳስ]፡ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*፣ አዲስ አበባ፡ 1974

አቡነ መቃርዮስና አቡነ አብርሃም [ሊቃነ

ጳጳሳት]ና ሌሎችም አዘጋጆች፡ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮትና የውጭ ግንኙነት፣* አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት 1988

ኀ

አያሌው ታምሩ[አለቃ] ምልጃ እርቅና ሰላም፡
አዲስ አበባ፡ 1992

አስረስ የኔሰው *ትቤ አክሱም መኑ አንተ* አዲስ አበባ፡ ንግድ ማ/ቤት 1951
---------- *የክም ነገድ መታሰቢያ* አሥመራ ኮከበ ጽባሕ ማ/ቤት ዘማኅበረ ሐዋርያት ፍሬ ሃይማኖት አሥመራ 1951
---------- *ጠቃሚ ምክር* አዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት 1958

ዓሥራት ገብረ ማርያም፡ ትምህርተ መለከት፡
አዲስ አበባ፡ አርቲስቲክ ማ/ቤት 1983

አስቻለው ከበደ *ከርከሬዴል ላዶፍ፡ ኢትዮጵያና የሰማይ ኃይላት* አዲስ አበባ፡ ቅዱስ ጊዮርጊስ ማ/ቤት 1995

አባ ቀውስጦስ ሊቀ ጳጳስ *ይግባኝ ለክርስቶስ የአቡነ ጴጥሮስ የመጨረሻ እስትንፋስ* 1999

አባ ይስሐቅ በሀገረ ስብከቱ ስተፈጠረው ችግር የመፍትሔ ጥሪ፣ ኒው ዮርክ ሚያዚያ 1993

አድማሱ ጀንበሬ [መል አከ ብርሃን]፡ *መጽሐፈ ቅዳሴ [ዝክረ ሊቃውንት]፣* አዲስ አበባ፡ ትንሣዔ ዘጉባዔ ማ/ቤት 1963

ኤርምያስ ከበደ [ንቡረ ዕድ]፡ *ኢትዮጵያ የዓለሙ መፋረጃ፣* አዲስ አበባ፡ 1993

አሱባለው በለጠ *የገሃነም ደጆች ፕሮቴስታንታዊ ጅሀድ በኢትዮጵያዊነት – ተዋሕዶ ላይ ሲፋፋም አንደኛ መጽሐፍ* አዲስ አበባ፡ አርቲስቲክ ማ/ቤት 1997

ኪዳነ ማርያም ጌታሁን [መምህር]፡ *ጥንታዊው የቆሎ ተማሪ፣* ሦስተኛ እትም አዲስ አበባ፡ ትንሣዔ ዘጉባዔ ማ/ቤት 1980

_____ *የሐሰት ምሥክርነት፡ የቋሚ ምሥክርነት ለአባ መልከ ጼዴቅ የተሠጠ መልስ፣* አዲስ አበባ፡ ንግድ ማ/ቤት 1994

---------- *ገድል ለመናፍቃን ገደል* አዲስ አበባ፡ አፍሪካ ማ/ቤት 1997

ወንጌል ቅዱስ ዘእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡
አሥመራ፡ ኮከበ ጽባሕ ማ/ቤት 1953

ዘመድኩን በቀለ፡ ቅዱሳን መካናት በኢትዮጵያ፡
አዲስ አበባ፡ አርቲስቲክ ማ/ቤት 1990

ዘኢትዮጵያ ጋዜጣ ቅጽ 10 ፡ ፌይርፋክስ
ቪርጂኒያ መስከረም 1997

ዝክረ አበው መጽሔት አዲስ አበባ፡ 1997

የዛሬዋ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ አዲስ አበባ፡ 1990

ገብረ ሥላሴ [ፀሐፌ ትዕዛዝ]፡ *ታሪክ ዘ ዘመነ ጳጉሜዊ ምኒልክ ንጉሥ ዘኢትዮጵያ* አዲስ አበባ፡ ቤብርሃንና ሰላም ማ/ቤት 1959

ገድሰ ተክለ ሃይማኖት፡ አዲስ አበባ፡ ተስፋ ማ/ቤት 1984

ገድለ ጊዮርጊስ፡ አዲስ አበባ፡ ትንሣዔ ዘጉባዔ ማ/ቤት 1990

ጌታቸው [መምህር፡ ወስመ ጥምቀቱ ገብረ

ኢየሱስ] ፣ ገድል ወይስ ገደል? ፣ አዲስ አበባ፣ አፍሪካ ማ/ቤት 1995

ጌታቸው ኃይሌ ፣ ደቂቀ እስጢፋኖስ በሕግ አምላክ ፣ ኮሌጅቪል፣ ሚኒሶታ፣ 1996

ግርማ ዘውዴ ፣ ኢትዮጵስ ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማ/ቤት 1998

ፍትሐ ነገሥት ንባብና ትርጓሜው ፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት 1992

Ben-Jochannan, Y.A.A. *Africa: Mother of Western Civilization,* Baltimore: Black Classic Press, 1998

Breasted Henry James: *The Dawn of Conscience,* New York, 1933

Brooks F. Miguel, Ed. *The Glory of kings (KIBRE NEGEST).* Laurvencevill: The Red Sea Press, 2002

Felder, Cain Hope. *Troubling Biblical Waters.* Maryknoll, New York: Orbis Boodl, 1989

Hagos Alemayehu: *Live Free! Exposing the Satanic Life & Lies of Western History!,* Gaitsburg: 2005

Hancock Graham, *The Sign and the Seal,* New York: *Crown Publishers Inc.*, 1992

Ivan Van Sertima Ed. *Black in Science Ancient and Modern.* New Brunswick: Transaction Publishers, Inc., 1992

Leykun E. Berhanu: *Contemporary Challenges in the Ministry of the Ethiopian Orthodox Church*, Howard University, Washington, DC: 2005

Means M. Sterling. *Ethiopia and The Missing Link In African History*. Harrisburg: The Atlantis Publishing Co., 1945

Prochazka Roman Baron. *Abssinia: The Powder Barrel.* London: British International News Agency, 1006

Tadesse Tamirat *Church and State in Ethiopia.* London: Oxford University Press, 1972

Teshale Tibebu. *The Making of Modern Ethiopia. 1896-1974,* Lawrenceville: Red Sea Printing Press, 1995

Williams Chancellor. *The Destruction of Black Civilization: Great Issues of A Race From 4500 BC. To 2000 AD.* Chicago: Third World Press, 1987